ባለፉት ዓሰ ዓመታት በቪሠዎች ሥጫሕፉሩ መጫሕፍቶን አንብቢያለሁ። በእጀም ያዘሠት ያለሰ መጽሐፍ ማን በሕይወቱ ካስብዘዬችው ሁሉ ብቀቱ ሁኔታ የሚሠሳሰሞና ገልጭት ያለው ዝሩም መጽሐፍ ከመ።

ዶክተር ዌይን ዳባር፣ ደራሲና የአነቃቂ ንግግሮች አቅራቢ

የዘመን ሷጅ መንፈስ አጅግ ከፍቶና አሰፉት የሚያደጋግዋ መጽሐፍ፡
የክርስቶፈር ሽልማት ሰጪዎች

ይህ መጽሐፍ የቤሐሬ ጥላቻ የሚፈተፍ ፖሊሲያችን ለሚቃርርና በብሔረሰብ ስም ህገ-ወጥ ከተፍሰሰ ጥላቻ ለሚደሰሩ ሰዎች ሁሉ መማሯርት የሚሰጠንቀቂያ ደሰል ነው። መጽሐፉ ጥላቻ የሚደበቅባቸውን ብቀቃ ብግሷና ስሙግሯዬ ሁሉም ኢትዮጵያዊ እንዲያነበው በአጽኑት ስሜጠን በዓይኔ ዘብሯት ካርኮት ተራሮቼ ነው።

ዶ/ር ያቆቡ ኃይለ ማርያም
በተባበሩት መንግስታት የቀድሞ የሩዋንዳ ፍርድ ቤት ከፍተኛ የሕግ አማካሪ

ሁቱትሲ በሚል ርዕስ የቀረበው ይህ መጽሐፍ በዘ ዋነኛዊ ሷጅናሪዎ እውነተኛና የጨሰውት ታዞ ላይ ተመርኩዞ፣ አእምሮን በቅዘ ይዘ፣ ልብን አያንጠለጠለ የማለስ አስደናቂ ደርሰት ነው።
አሊሻ መሠሚ ኢብራሂሙ፣ ደራሲና ተርጓሚ

ብእጣቢያሌ ኢለባጣዝ የበብር፣ የጽናት፣ የድንንትና የይቅር በይነት ታሪክ ላይ በማያንጸባርቀው እጅግም ያልተለመደ መንፈሳዊነት ያማንጮት ታብር ዝቅ አደር ነሰው። እንደ ናዋንዛዊትነቱ እጅግ ብዙ ሷጅዎችንን፣ ወንዶቻቸንንና ሰቶታቸችንን በጩፉፉ ካስገደለቡብን በአማባቡ ካሷታገበብዳቸው፣ ልሃነቶቻቸን በላይ አሻግረን ለማዬት መቻላቸን ያመራኛል። የኢማኪዩሌ ከዘር ማጥፋቱ የመከሪያ ታሪክ በአውነት አስደማሚ ነው። ዮራሳቸውን እጅንዳ በማደራመጫትና ሰሰመሃዊነት ዓድ በማይሰጣቸው አነሳሳት ሆን ተብሎ የተፈጠረውን መከፋፈል በጽል የመወሰንትን ቀበፁ ይሰበናሷ። ከሚሮጨፈው የሞራቶትም ሆኑ አሳሳቢነቱ ሁሉ ይህን ታሪክ ማንበብ ይገባቸዋል። ሁሉንም የኢማኪዩሌን ዓይነት ጥልት መንፈሳዊ ለሠጥ ይናንጉና ልእንዲትና ሰላም ወገር ሰሞሥራት አነክሳባ ይዘድ ተበፉ አደርጋለሁ።»

ዣኔት ካጋሜ፣ የሩዋንዳ ቀዳማዊት እመቤት

ዋጋው 59. 75 ብር
HY International Printer

ሁቱትሲ

የወጣቷ ልብ አንጠልጣይ ትውስታዎች

ኢማኪዩሌ ኢሊቢጊዛ

እና

ስቲቭ ኤርዊን

ቀዳሚ ቃል በዶክተር ያዕቆብ ኃይለማርያም

ተርጓሚ - መሐመር ግሮማ

ሁቱትሲ
የወጣቷ ልብ አንጠልጣይ ትውስታዎች

ኢማኪዩሌ ኢሊባጊዛ
እና ስቲቭ ኤርዊን

ተርጓሚ
መዘምር ግርማ

© የተርጓሚው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።።

All Rights Reserved!

የመጀመሪያ እትም - ታህሳስ 2008 ዓ.ም.

ሁለተኛ በነሐሴ 2011 ዓ.ም. በተርጓሚው ፈቃድ ሕዝብ በነጻ እንዲያነበው በኢንተርኔት ተለቀቀ።።

<u>ለአስተያየትዎና ለተጨማሪ መረጃ</u>

E-mail mezemirgirma@gmail.com

Blog - mezemirethiopia.blogspot.com

Facebook – Mezemir Speed-reader

Telegram Channel – Hututsi

Youtube – Mezemir Girma

Twitter - @authenthiopia

የይዘት ማውጫ

ቀዳሜ ቃል 5

የተርጓሚው ማስታወሻ 7

አኩቴት 13

መቅድም 15

መግቢያ፡ ኢማኪዩሌ እባላለሁ 16

ክፍል ፩: ከፉ ቀን ዳር ዳር ሲል

ምዕራፍ 1: የዘላለማዊ ፀደይ ምድር 21

ምዕራፍ 2: ከመቀመጫችን ሲያስነሡን 30

ምዕራፍ 3: ቅድመ-ከፍተኛ ትምህርት 41

ምዕራፍ 4: ወደ ዩኒቨርሲቲ 49

ምዕራፍ 5: ወደ ሀገር ቤት 55

ምዕራፍ 6: *መመለስ አይታሰብም* 64

ምዕራፍ 7: የቁሱ ቤት 75

ምዕራፍ 8: ልጆቹን ስሰናበት 83

ክፍል ፪: የተደበቅሁበት ጊዜ

ምዕራፍ 9: ወደ መታጠቢያ ክፍሉ 91

ምዕራፍ 10፡ ቁጣዬን ስጋፈጥ 101

ምዕራፍ 11: ምኅረት ለማድረግ ስጣጣር 108

ምዕራፍ 12: የማዋየው ወዳጅ ሳጣ 112
ምዕራፍ 13: የእጓለማውታ ስብስብ 119
ምዕራፍ 14: በልሳን ሲያናግረኝ 129
ምዕራፍ 15: አድነው የማያድኑት 138
ምዕራፍ 16: በእምነቴ ስጸና 143

ክፍል ፫: አዲስ መንገድ

ምዕራፍ 17: የነጻነት ሕመም 153
ምዕራፍ 18: ከዳማሲን የተላከ ደብዳቤ 165
ምዕራፍ 19: የስደተኞች መጠለያው ምኞት 170
ምዕራፍ 20: ወደ አማጽያኑ የሚወስደው መንገድ 183
ምዕራፍ 21: ወደ ኪጋሊ 189
ምዕራፍ 22: የጌታዬ ሥራ 198
ምዕራፍ 23: ሙታኑን ስቀብር 208
ምዕራፍ 24: ቋሚውን ስምር 215

ድህረ-ታሪክ፡ አዲስ ፍቅር፣ አዲስ ሕይወት 219
ምሲጋና 225
የደራሲያኑ ማንነት *228*
ለመጽሐፉ የተቸሩ የአድናቆት አስተያየቶች 229
የኢማኪዩሌ አርዓያ ይናገራሉ 232
መውጫ 236

ቀዳሜ-ቃል

ኢማኪዩሌ ኢሊባጊዛ ከስቲቭ ኤርዊን ጋር በመተባበር የጻፈችው ሁቱትሲ የተሰኘው መጽሐፍ ምናልባት ስለ ሩዋንዳ ከተጻፉት መጻሕፍትም ሆነ ከታዩት ፊልሞች በላይ የፍጅቱን አሰቃቂነትና ዘግናኝነት ገላጭ ነው ማለት ይቻላል። ምክንያቱም መጽሐፉ ከሰሚ ሰሚ የወረደ ታሪክ ሳይሆን እጅግ ከሚዋደዱ ከስድስት ቤተሰብ አባላት ከግድያው የተረፈችው አንዲት ቱትሲ ወጣት ከአንድ ቁምሣጥን በማይበልጥ መጸዳጃ ቤት ከሰባት ቱትሲ ጓደኞቿ ጋር ከአሁን አሁን ተገደልኩ እያለች እየተጨነቀች የሃይማኖት ጽናቷ እንዴት ለሦስት ወር በሕያውነት እንዳኖራትና በኋላም እንዴት ነጻ ወጥታ ወልዳ ለመሳም የበቃች መሆኗን የሚተርክ ታሪክ ነው።

የሩዋንዳ የዘር ፍጅት ተዋንያንን ፍርድ ቤት እንዳቀርብ በተባበሩት መንግስታት በከፍተኛ የሕግ አማካሪነት ተቀጥሬ በሠራሁበት ጊዜ ከሰማኋቸው በላይ ልብን ሰቅዞ የሚይዝና አእምሮን የሚያናውጥ ታሪክ ይኖራል ብዬ አልገመትኩም ነበር። ሆኖም በዚህ መጽሐፍ ኢጋጥሞኛል።

ስሜታዊነት አይነካኝም፣ መንፈሴ በሚያየውና በሚሰማው የማይረበሽ ጠንካራ ሰው ነኝ ባይ ይህንን መጽሐፍ በሚያነብበት ጊዜ ከእንዴም ሁለቴ ዓይኖቹ በእንባ ችፍ ችፍ ማለታቸው አይቀርም።

የኢማኪዩሌ ታሪክ ምንጩ ወይንም የስቃይዋ ምክንያት የተወሳሰበ አይደለም። መንስኤው ርህራሄ የሚወልደውን የሰብአዊ ስሜትን ደምስሶ ከጥላቻ በላይ ጥላቻ ወልዶ ሰውን ከአውሬነት በታች የሚያውለው የዘር ጥላቻ ነው።

የዘር ጠላቻ አንድ ሰብዓዊ ፍጡር ለሌላው ሰብዓዊ ፍጡር ሊኖረው የሚገባውን ሐዘኔታና ርህራሄ ከሰው ልብ ፈልቅቆ አውጥቶ ከአውሬ በባሰ ጭካኔ ይተካዋል። በሩዋንዳው የዘር ፍጅት የተፈጸመውን አራዊት ከሚያደርጉት ጋር ማወዳደር የአራዊትን ስም ማጥፋት ይሆናል። የትኛው አውሬ ነው ሕጻናትን ከታትፎ እንደ ጌሾ በሙቀጫ የሚወቅጠው? የትኛው አውሬ ነው በኢማኪዩሌ ወንድም ላይ እንደተፈጸመው የሰውን አካላት ቆራርጦ ከምር ላይ የሚጥል? የትኛው አውሬ ነው የሰውን ጭንቅላት በገጀራ ለሁለት ሰንጥቆ ሰውዬውን በዝግታ እንዲሞት የሚያደርገው? የትኛው አውሬ ነው የአምስት ልጆችን እናት በልጆቿና በባሏ ፊት ደፍሮ ፊቷ አምስቱንም ልጆቿንና ባሏን አንድ በአንድ የሚከትፈው? ከአከራሪ ሁቱዎች በስተቀር የትኛውም አውሬ አያደርገውም።

የሩዋንዳ የዘር ፍጅት የሰው ልጅ ጭካኔ ልክ የታየበት ነው። ተመሳሳይ ፍጅትና ጭካኔ የተፈጸመባቸው የናዚዎችና የአርመኖች እልቂቶች እንደሩዋንዳው መንስኤአቸው የዘር ጥላቻ ነበር።

ኢማኪዩሌ በመጽሐፏ የጠቀሰችው የዘር ፍጅቱ ቀስቃሽና ዋና አስተባባሪ ኮሎኔል ቲዩኔስት ባጎስራ ፍርድ ቤት አቅርቢው ዳኞቹ ክሱን አንብበውለት ጥፋተኛ ነህ አይደለህም ብለው ሲጠይቁት ፈገግ እያለ «ጥፋተኛ አይደለሁም» ሲል ፈገግታው እንደ ጦር ይዋጋ ነበር፡፡

መጽሐፉ ከእንግሊዝኛ የተተረጎመ ሲሆን፤ ምናልባትም የአማርኛው ትርጉም ድርጊቶቹን ከእንግሊዝኛው በተሻለ ይገልጻቸዋል ማለት ይቻላል፡፡ ተርጓሚው የሥነ-ጽሑፍ ምሁር እንደመሆናቸው መጠን አገላለጹ ከኢማኪዩሌ በልጦ ቢገኝ አይገርምም፡፡ የቃላቱ ገላጭነት፣ የአረፍተ ነገሮቹ አሰካክ፣ የቋንቋው አወራረድና በጠቅላላው የአማርኛው ውበት ከታሪኩ መሳጭነት ጋር ሆኖ መጽሐፉን ማንበብ ከተጀመረ መልሶ ማስቀመጥ አስቸጋሪ ነው፡፡

ይህ መጽሐፍ የብሔር ጥላቻ የሚፈጥሩ ፖሊሲዎችን ለሚቀርጹና በብሔረሰብ ስም ህዝብን ከፋፍለው ጥላቻ ለሚያስፋፉ ሰዎችም ሆኑ መዋቅርት የማስጠንቀቂያ ደወል ነው፡፡ መጽሐፉ ጥላቻ የሚያስከትለውን ሰቆቃ በግልጽ ስለሚያሳይ ሁሉም ኢትዮጵያዊ እንዲያነበው በአጽንኦት ስማጠን በዓይኔ በብረቱ ካየሁት ተነሥቼ ነው፡፡

ዶ/ር ያዕቆብ ኃይለ ማርያም

በተባበሩት መንግስታት የቀድሞ የሩዋንዳ ፍርድ ቤት ከፍተኛ የሕግ አማካሪ

የተርጓሚው ማስታወሻ

በብዙ ሀገራት የሰው ልጅ በዘውግ[1] እየተባደነ ሲጋጭና ሲጫረስ ኖሯል። ከተፈጸሙት እልቂቶች በመጠነ-ሰፊነቱ ቀዳሚው 13 ሚሊዮን የአሜሪካ ቀደምት ሕዝቦች (ሬድ ኢንዲያንስ) በአውሮፓውያን መጤዎች የተገደሉበት ነው። በቤልጅዬሙ ንጉሥ ሊኦፖልድ ዳግማዊ ትዕዛዝ 10 ሚሊዮን ኮንጓውያን በየተወለዱበት ቀዬ የተጨፈጨፉበት ይከተላል። በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት ደግሞ ስድስት ሚሊዮን ይሁዲዎች በናዚ ጀርመኖች በመግደያ ጣቢያዎች በጅምላ እንዲያልቁ ተደርገዋል። ዘረኞች በመሰረተ-ቢስ ጥላቻና በራስ-ወዳድነት ይህን ሁሉ ሕዝብ በግፍ ፈጁ እንጂ የተጠቀሱት ሀገራት እነዚህን የተጨፈጨፉ ሰዎች ከነጨፍጫፊዎቻቸው ለማኖር የተፈጥሮ ገጸ-በረከቱ ነበራቸው። በየሀገሩ ስለተፈጸሙት ፍጅቶች ዶክተር ያዕቆብ ኃይለማርያም በፋክት መጽሔት ላይ እንደጻፉት ቦስኒያ ውስጥ ሰርብ ያልሆኑት ዜጎች መጨፍጨፍ፣ አርመኖች በኡቶማኖች የደረሰባቸው እልቂት፣ ኩርዶች በሳዳም ሁሴን የተካሄደባቸው የዘር ምንጠራና የካምቦዲያው ፖል ፖት ያካሄደው ገደብ-የለሽ ጭፍጨፋ በዘር ጥላቻ ላይ ተመስርተው ከተፈጸሙ ግድያዎችና ሰቆቃዎች ውስጥ ዋነኞቹ ናቸው።

በመቻቻል ላይ የተጻፈ አንድ ጽሑፍ እንደሚያትተው ዘውግን መነሻ ያደረገ ጭፍን ጥላቻ፣ ብሔራዊ ስሜት (የሌላን ሀገር ዜጎች እንዲጠሉ የሚያደርገው)፣ ወገናዊነትና ሃይማኖታዊ ጽንፈኝነት የሚያሳድጉት በዓለማችን የተወሰኑ ክፍሎች የነገሰው ተቻችሎ ያለመኖር አውሬ፣ ሰዎችን በሰውነታቸው እንዳንቀበል፣ ይቅር ባይ እንዳንሆንና ሰላማዊ ግንኙነትም እንዳይሰፍን ያደርጋል። እንግዲህ አንድ ዘውግ በጥላቻ ታውሮ ሌላውን በጠላትነት ፈርጆ ሲያሳቁልን፣ ሲያገል፣ ሲያሳድድ፣ ሲያስር፣ ሲገድል፣ ብሎም እጅግ የከፋውን የዘር ፍጅት ሲፈጽም ምን ዓይነት ውድመት እንደሚያስከትል ለመገንዘብ አያዳግትም።

የዘር ፍጅት እንዳይፈጸም በመከላከልና ሲፈጸምም በማስቆም ላይ የሚሰራው ተቋም *ፎጅናሳይድ ዎች* ሊቀመንበር የሆኑት ግሪጎሪ ስታንተን ባቀረቡት ምርምር የሰው ልጆች ልባቸው ሲደድር የሚጠናወታቸው የዘር ጭፍጨፋ አባዜ ስምንት ደረጃዎች እንዳሉት ይገልጻሉ። እነዚህም በተደራጀና ተቋማዊ በሆነ መንገድ የሚፈጸሙት ደረጃዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

[1] ዘውግ የሚለውን ቃል የተጠቀምኩት በነገድ፣ በዝርያ፣ በወገን መመሳሰልን ለማመልከት የተሻለና ርዕዮተ-ዓለማዊ ተጽዕኖ የማይንጸባረቅበት ቃል በመሆኑ ነው።

ሀ. መከፋፈል (Classification) - እኛና እነርሱ ብሎ በመከፋፈል ለየት ይላሉ ተብለው የሚታሰቡትን የኅብረተሰብ ክፍሎች በቀልድም ጭምር በማንቋሸሽ በሰዎች መካከል ያለውን ልዩነት አለማከበር

ለ. የሚታይ መገለጫ መስጠት (Symbolization) - ይህ የጥላቻ ግልጽ መገለጫ ሲሆን ይሁዲዎች በናዚ ጀርመን ቢጫ ኮከብ ያለበት ልብስ እንዲለብሱ እንደተደረገው ነው።

ሐ. ከሰው ክብር ዝቅ ማድረግ (Dehumanization) - ይህ ተግባር ከራስ የተለዩትን ሰብዓዊ ክብርም ሆነ ሙበት በመንፈግ ይፈጸማል። በሩዋንዳ አክራሪ ሁቱዎች የቱትሲ ዘውግ ተወላጆችን ‹በረሮ› ይሏቸው እንደነበረው መሆኑ ነው። ይህ ሂደት ገዳዮቹ ‹እየገደልን ያለነው ሰው አይደለም፤ ታዲያ ድርጊታችን ምኑ ላይ ነው ጥፋትነቱ?› እንዲሉ መንገዱን ይጠርግላቸዋል።

መ. ማደራጀት (Organization) - በጥላቻ ላይ የተመሠረቱ መንግሥታት አንድን ሕዝብ የሚያጠፋላቸውን ኃይል ያሰለጥናሉ።

ሠ. በተቃራኒ ጎራዎች ማሰለፍ (Polarization) - ሕዝቡ በዘውጉ ከጨፍጫፊውና ከተጨፍጫፊው ወገን ሚናውን እንዲለይ ይደረጋል። በብዛት ይህ የሚሆነው በጥላቻ ቡድኖች ውትወታ በመገናኛ ብዙሃን የጥላቻውን መርዝ በመርጨት ነው። አንዱን ዘውግ ከሌላው ለይቶ በማውጣት ጠላት ነው ብሎ ማወጁ ጀርመኖች ይሁዲዎችን ከመፍጀታቸው በፊት በምዕራብ አፍሪካ በሄሬሮዎች ላይ የ20ኛውን ክፍለዘመን አሰቃቂ ጭፍጨፋ ሲፈጽሙ፣ ይሁዲዎችን ሲፈጁና የሩዋንዳ አክራሪ ሁቱዎች ቱትሲዎችን ሲጨርሱ የገዳዩን ዘውግ አባላት በቀላሉ ለማሳመንና ለህሊናው እንዲቀለው ለማድረግ ተጠቅመውበታል።

ረ. ዝግጅት (Preparation) - ሰለባዎቹ በልዩነቶቻቸው ተለይተው ይፈረጃሉ። የጭፍጨፋው ንድፍ አውጭዎች ሰዎችን በመኖሪያ አድራሻቸውና በሌሎችም መለያዎች ይፈርጁና ለፍጅት ያዘጋጇቸዋል።

ሰ. ፍጅት (Extermination) - በታቀደና ሆነ ተብሎ በተመቻቸ ዘመቻ የጥላቻ ቡድኖቹ ሰለባዎቻቸውን ይጨፈጭፋሉ። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች በዘር ፍጅት ማንነታቸውን መለየት እስኪከብድ ድረስ ተጨፍጭፈዋል።

ሸ. ክህደት (Denial) - ግድያውን የፈጸሙትም ሆኑ ቀጣይ ትውልዶች ምንም ዓይነት ጥፋት ያልተፈጸመ በማስመሰል ክህደት ይፈጽማሉ።

ከዚህ የጭፍጨፋ ሂደት እንደምንረዳው የዘር ፍጅት በአንድ ሌሊት ያለምንም ዝግጅት ስለማይፈጸም ራሳችንን ከላይ ከተጠቀሱት በሌላው ላይ ጉዳት ከሚያደርሱ ክስተቶች ፈጽሞ ማራቅና የዕለት ከዕለት ድርጊቶቻችንን መገምገምም ያስፈልገናል።

እነዚህን የዘር ፍጅት አመላካች ሂደቶች በማናቸውም ደረጃ በእንጭጩ መቅጨት ከተቻለ እልቂትን ሙሉ በሙሉ ማስቀረት ይቻላል።

በመካለኛው አፍሪካ በምትገኘው በሩዋንዳ የተካሄደውና አንድ ሚሊዮን ገደማ የሚሆኑ ሰዎችን ሕይወት የቀጠፈው የዘር ማጥፋት በንጹሐን ዜጎች ላይ ከተፈጸሙ የተደራጁና መጠነ-ሰፊ ዘግናኝ ድርጊቶች አንዱ ነው። የዚህች ሀገር ሁቱ መሪ ከሀገሪቱ ያባረራቸውን ወደ አንድ ሚሊዮን የሚጠጉ ቱትሲ ስደተኞች ተመልሰው ወደ ሀገራቸው እንዳይገቡ በሕግ በመከልከልና ሀገር ውስጥ የነበሩትንም በማሰቃየት ከግፍ ጽዋ እንዲጎነጩ አስገድዷል። ከ1959[2] ጀምሮ ሁቱዎች ቱትሲዎችን በጠላትነት እንዲያዩ የሰበኩው አገዛዙ ነው። ይህም ጸረ-ቱትሲ የጥላቻ ውትወታ ሁቱዎች ቱትሲዎችን በየወቅቱ የጥቃቶቻቸው ሰለባ እንዲያደርጉ ገፋፍቷቸዋል። የሩዋንዳው ጭፍጨፋ ተራው ሕዝብ በሰፊው የተሳተፈበትና ‹ቱትሲዎች መጤዎች ናቸው› በሚለው የቆየ ቅስቀሳ ምክንያትነት በጨፍጫፊዎቹ ዓይን የነባርና የመጤ ግጭት ተደርጎ የሚታይ ነው። እዚህ ላይ አጽንኦት ሊሰጠው የሚገባው ነገር ቢኖር ሁቱዎች ሥልጣንና ትምህርት እንዲያገኙ ቱትሲዎችን ማጥፋት እንዳለባቸው ተሰበኩ እንጂ በተፈጥሯቸው ገዳዮች ሆነው አይደለም። መንግሥት የጥላቻውን ስብከት እንዲያቆም፣ በቱትሲዎች ላይ ይፈጽም የነበረውን ግፍ እንዲተውም ሆነ ጭፍጨፋውን እንዳያካሂድ ለማድረግ የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብም ሆነ የተመድ[3] ሳይቃጠል በቅጠል ብለው ጣልቃ አልገቡም። ለተጨፍጫፊዎቹ ጀርባ የመስጠቱ ይህ ድርጊታቸውም ይሄው እስካሁን እንዳስተቻቸው ነው።

የሩዋንዳውን ፍጅት ከፈፀሙት ወንጀለኞች መካከል 61 ዋነኛ ተዋናይ የነበሩ ሰዎች በተመድ ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ሲዳኙ ሁለት ሚሊዮን የሚሆኑት ደግሞ በሀገር በቀሎቹ የጋቻቻ[4] ፍርድ ቤቶች ፍርድ አግኝተዋል። ሰውን እንደ እንስሳ አድኖ በመግደል ሲደሰቱ የነበሩት ጨፍጫፊዎችና ከዘር ፍጅቱ ያመለጡት ሰዎች ግን እንዴት ነው ወደፊት አብረው መኖር የሚቀጥሉት? የሚል ጥያቄ በሁላችንም አእምሮ መምጣቱ አይቀርም።

በሩዋንዳ በቸልታ የታለፈው የዚህ የዘር ፍጅት መዘዝ የዛየርን መፈራረስ እንዳስከተለና እስካሁን መቋጫ ባላገኘው የኮንጎ ጦርነት ስድስት ሚሊዮን የሚደርስ ሕዝብ ሊያልቅ እንደቻለ ምርምሮች ያሳያሉ። የሩዋንዳው ሕመም ጦስ ወደ ኮንጎ ሊተላለፍ የቻለው ይህች ሀገር የዘር ፍጅቱን የፈጸሙትን ወንጀለኞች በማስጠጋቷ

[2] በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያሉት ዘመናት በሙሉ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ናቸው።

[3] የተባበሩት መንግስታት ድርጅት

[4] በሩዋንዳ ባሕላዊ የሽምግልና ሥርዓት ላይ የተመሰረተና በዘር ጭፍጨፋው የተሳተፉትን ወንጀለኞች የዳኝ የፍርድ ስርዓት

ከአዲሱ የሩዋንዳ መንግሥት በደረሰባት ተጽዕኖ ነው፡፡ ወደ ቻድ፣ ማእከላዊት አፍሪካ ሪፐብሊክና ዳርፉርም የዘር ፍጅቱ ግርሻ ተዛምቷል፡፡ ዓለማችን አንድ መንደር ሆናለች እየተባለም የዘር ጭፍጨፋ በዓለም የተለያዩ ክፍሎች በመፈጸም ላይ ነው፤ ስጋቱም እስከአሁን ድረስ እንዳንገበበ አለ፡፡

ዘውግ-ተኮር የሆኑ መቃቃሮችንና አለመግባባቶችን በኃይል ለመፍታት ሲሞከር የሚደርሰውን ጥፋት አስከፊነት ከሩዋንዳው ጭፍጨፋ በላይ ማሳያ የለም ብል ማጋነን አይሆንብኝም፡፡ የዚች ሀገር ሕዝብ ሀገሩን ያወደመውን የዘር ጭፍጨፋ ካመጡበት ተግባራቱ መማሩንና ችግሩ እንዳይደገም መቁረጡን የሚያሳዩ ምልክቶች አሉ፡፡ በአዲሱ የሩዋንዳ ሕገ-መንግሥት መግቢያ ላይ «እኛ ሩዋንዳውያን፣ የዘር ፍጅትንና ሁሉንም መገለጫዎቹን ለመዋጋትና ማናቸውንም ዓይነት የኃሣ፣ የክልልና ሌሎች ከፍፍሎችን ለማጥፋት ወስነናል» የሚል ብርቅዬ ዜጎቻቸውን ካጡ በኋላ የደረሱበት ውሳኔ ሰፍሯል፡፡ ከውድመቱ ቀድሞ ይህን ማድረግ ቢችሉ እንዴት ጥሩ ነበር! ከአንድነት ይልቅ ልዩነትን የማጉላትና የማራገብ ጠንቅ የገባቸው ከዚያ ሁሉ ውጣ ውረድ በኋላ ነው፡፡ የአዲሲቷ ሩዋንዳ ባለሥልጣናት እንደሚናገሩት ማንም ሰው ሁቱ ወይንም ቱትሲ ስለሆነ ብቻ የተለየ ጥቅም ወይም አገልግሎት ማግኘትም ሆነ ከሀገሪቱ መባረር የለበትም፡፡ ማናቸውም ሩዋንዳዊ ልጅም ሁቱ፣ ቱትሲ ወይንም ትዋ ነህ ተብሎ እንዲያድግ አይደረግም - ሩዋንዳዊ እንጂ፡፡ ለያይቶ ማየት እንደ ታላቅ ነውር ተቆጥሯል - በህግም፣ በተግባርም፡፡

በእጅዎት ይዘውት ያለው መጽሐፍ በ1994 በሩዋንዳ ከሁቱ ዘውግ የሚመደቡ ራሳቸውን ያደራጁ አካላት በተቀናጀ መልኩ በቱትሲዎችና አልፎ አልፎም ለዘብተኛ ሁቱዎች ላይ ባካሄዱት ፍጅት ወቅት ከግድያ የተረፈችው የቱትሲዋ የኢማኪዩሌ ኢሊባጊዛ ትዝብትና ትውስታ ተተርኮበታል፡፡ መጽሐፉ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት ናዚ ጀርመኖች ይሁዲዎችን ሲጨፈጭፉ በተደበቀችበት ማስታወሻ ስትጽፍ ቆይታ መጨረሻ ላይ የናዚ ወታደሮች አግኝተዋት የተገደለችውን የአና ፍራንክን ማስታወሻ የሚያስታውሰን ነው፡፡ ኢማኪዩሌን ‹ሩዋንዳዊቷ አና ፍራንክ› ብለው የሚጠሯትም አሉ፡፡ ከጭፍጨፋው ከገዳዮቿ ጋር በግንባር ጭምር ከተገናኘች በኋላ በተአምር የተረፈችው ይህች ሰው የእምነት ጽናትና ይቅር ባይነት ቋሚ ተምሳሌት ነች፡፡ በዳዮቿን በዝምታ ብዛት ሳትቀጣ ምህረት በማድረግ እፎይታን ለግሳቸዋች፡፡ መጽሐፉ ስለ ሩዋንዳው ጭፍጨፋና ስለ ኢማኪዩሌ ታሪክ በሚገባ ከማስረዳቱ በተጨማሪ የአንባቢውን ስሜት በእጅጉ በሚስብ አቀራረብ ተጽፏል፡፡ ኢማኪዩሌ ይህን መጽሐፍ ስትጽፍ ለቋንቋው ውበትና ለቅንጅቱ ስምረት ሲባል የረዳት ካናዳዊ ጋዜጠኛና የልብ ወለድ ደራሲ ስቲቭ ኤርዊን ታሪኩን ያቀናበረው ልብ አንጠልጣይ አድርጎ ነው፡፡ ምስል ከሳች የሆነ ገለጻና ለጽሑፉ እስትንፋስ የሆነውን ምልልስ መጠቀሙም ጽሑፉን ማንበብ ከጀመሩ ሳይጨርሱ እንዳያቆሙት ያስገድዳል፡፡ ይህ የኢማኪዩሌ የመጀመሪያ መጽሐፍ እስካሁን የአማርኛው ትርጉሙ ሳይቆጠር ወደ 17

ቋንቋዎች ተተርጉሟል፤ ሽያጩም ከሁለት ሚሊዮን ቅጂ በላይ ነው፡፡ ኒው ዮርክ ታይምስም ከፍተኛ ሽያጭ ያገኘ በማለት አወድሶታል፡፡ ከዚህም ባለፈ መጽሐፉ «የሰውን ልጅ መንፈስ እጅግ ከፍተኛ እሴቶች የሚያረጋግጥ» ተብሎ በመወደስ የክርስቶፈር ሽልማትን ለኢማኪዩሌ አስገኝቷታል፡፡ ታሪኩም በተንቀሳቃሽ ምስል ተቀርጾ በመገናኛ ብዙኃን ቀርቧል፡፡ ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች የክብር ዶክትሬት ዲግሪ የተበረከተላት ባለ ታሪኳም ስላለፈችበት ችግርና ዓለማችንም ወደፊት ስለሚያስፈልጋት ሰላማዊ ዓለም በየአህጉሩ እየተዘዋወረች ገለጻ ታደርጋለች፡፡

ሌፍት ቱ ቴል (Left to Tell) የሚል ርዕስ ያለውን ይህን የኢማኪዩሌን መጽሐፍ ያገኘሁት ደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ ነው፡፡ የተረጎምኩት ምን ልተርጉም ብዬ የሚተረጎም መጽሐፍ ሳፈላልግ አግኝቼው ሳይሆን ካነበብኩት በኋላ ሥሜቴን በእጅጉ ስለነካውና የሚሰጠው የይቅርታና ከውድመት የማገገም ትምህርት ለሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ አስፈላጊ መሆኑን በማመኔና ለአማርኛ አንባቢያን ተርጉሞ ማቅረብ የዜግነት ግዴታዬ መሆኑ ስለተሰማኝ ነው፡፡ ማን ይናገር የነበረ፣ ማን ያርዳ የቀበረ ነውና የዘር ማጥፋት ጉዳይ ሲነሣ ስሟ አብሮ በሚነሣው ሀገር የበቀለችውና ከሞት አፋፍ የተመለሰችው ወጣት የጻፈችውን ግሩም ማስታወሻ ማንበብ ስለ ክስተቱ ጥሩ እውቀት እንድንጨብጥ ያደርገናል፡፡ ታሪኩ በዚች የበርካታ ዘውጎች መገኛ በሆነችው ሀገራችን አብሮነታችንን ተንከባክበን የማቆየትን ጥቅም ያስተምረናል፡፡ ስተረጉም በታሪኩ ውስጥ የሚነሱት ማናቸውም ሃሳቦች እንዳይቀሩ በማሰብ ለይዘቱ ትኩረት ሰጥቻለሁ፡፡ ቋንቋውን ጉራማይሌ ላለማድረግም በተቻለኝ መጠን አማርኛ አማርኛ የሚሉ ቃላትን በመጠቀም የውሰት ቃላትን ለመቀነስ ሞክሬያለሁ፡፡

የ12ኛ ክፍል ተማሪ ሆኜ በአፍሪካ ህብረት አሳሳቢነት መላው አፍሪካውያን የሩዋንዳውን ፍጅት ሰለባዎች በኅሊና ጸሎት እንድናስባቸው መደረጉን አስታውሳለሁ፡፡ ይህ ፍጅቱ የተፈጸመበት አሥረኛ ዓመት መታሰቢያ የተደረገው የዚህ ዓይነቱ ከአብዛኞቻችን አእምሮ መፋቅ የማይችል አሰቃቂ ድርጊት በማንኛውም የአፍሪካ ክፍል በሚኖር መጪ ትውልድ ላይ እንዳይታሰብም ሆነ እንዳይፈጸም ለማሳሰብ ይመስለኛል፡፡ አሁን ደግሞ እንዲያው በደፈናው በሩዋንዳ የዘር ጭፍጨፋ ተካሂዶ እንደነበር ከማወቅ በዘለለ የቸግሩ ወላፈን የገረፋትን የኢማኪዩሌን ታሪክ ተረዳሁ፡፡ ታሪኳ ስለተዋሃደኝ ባለፈችበት በእያንዳንዱ ሥቃይ አብሬያት የነበርኩ ያህል ይሰማኛል፤ ሰቀቀኗም በአእምሮዬ ይመጣብኛል፡፡ ሁላችንም እርሷ የታደለችው ይቅር ባይነትና መረጋጋት እንዲኖረን እመኛለሁ፡፡ ማናቸውም የሰው ልጅ በምርጫው ሳይሆን በተፈጥሮ አስገዳጅነት በሚገባበት ዘውግ መነሻነት ብቻ አላስፈላጊ ሥጋት ውስጥ እንዳይገባ፣ በማናቸውም መንገድ ጉዳት እንዳይደርስበትና ከሌሎች ጋር በመፈቃቀርና በመተሳሰብ እንዲኖር መጣር ግድ ይለናል ብዬ አምናለሁ፡፡ በርካታ ኢትዮጵያውያን እስካሁን ስለ ሩዋንዳው የዘር ጭፍጨፋ በተለያዩ የመገናኛ አውታሮች፣ በመጻሕፍት፣ በተንቀሳቃሽ ምስል ትዕይንት (ለምሳሌ፣ *ሆቴል ሩዋንዳ*፣

ሹቲንግ ዶግስ፣ ሳምታይምስ ኢን ኤፕሪል) እና በሌሎችም መንገዶች ግንዛቤ አግኝተናል። የሀገራችን ሰላም አስከባሪ ሠራዊትም ሩዋንዳ ከጭፍጨፋው ታገግም ዘንድ ማገዙ የቅርብ ጊዜ ትውስታችን ነው። ተጨማሪ ግብዓት የሚሆነን ይህ ድርሰት በሩዋንዳው ችግር ላይ በአማርኛ የተጻፉ ጽሑፎችን እጥረት በመጠኑ በመፍታት ሌሎችም እንዲጻፉ ያነሳሳል የሚል እምነትም አለኝ። ችግሩ በአንዲት ከጭፍጨፋው በተረፈች ግለሰብ ዓይን እንዴት እንደሚታይም ያስገነዝበናል።

ከዚህ ታሪክ የዘር ጥላቻን አውዳሚነትና የይቅር ባይነትን የመፈወስ አቅም ልንረዳ እንጂ በስጋት ልንናጥ አያሻንም። በሀገራችን ‹ፍጅት ይፈጸማል›፣ ‹አይፈጸምም› በማለት ጎራ ለይተው የሚከራከሩ ልሂቃን መኖራቸው ባይካድም፣ የተዛቡ ታሪኮች እየተፈበረኩ በዜጎቻችን አስተሳሰብና ተግባራት ላይ ጥላቸውን ቢያጠሉም፣ ህዝቡን በየዘውጉ እያደራጁ የሚወተውቱ የፖለቲካ ድርጅቶች እንደ አሸን ቢፈሉም፣ ህዝባችን ከመቼውም በላይ ከአንድነቱ ይልቅ በልዩነቱ ላይ ያተኮረበት በሚመስል ወቅት ላይ ብንገኝም ይህን የሩዋንዳውን ዓይነት ፍጅት ኢትዮጵያውያን በወገኖቻቸው ላይ ያደርጋሉ የሚል እምነት የለኝም። ምክንያቴም በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን በጽኑ መተማመኔ ነው።

በመጨረሻም ደግመን ደጋግመን በማንበብ፣ የሚያነሳውን ሃሳብ በማብላላት፣ በጉዳዩ ላይ በመወያየት፣ ከተቻለም ይህች ልጅ ባለፈችበት የሕይወት መንገድ ያለፍኩት እኔ ብሆንስ ኖሮ ብለን በምናባችን የእርሷን ውጣ ውረድ በመሄድ ታላቅ ትምህርት ለመቅሰም እንድንጥር አሳስባለሁ። እርስዎ ይህን አስከፊ ታሪክ አንብበው ሲጨርሱ ከአሁኑ በላቀ ሁኔታ ለሰው አዛኝ፣ ርህሩህና በጎ አሳቢ እንደሚሆኑ አልጠራጠርም። በዘር ማጥፋትና ተዛማጅ ጠንቆች ላይ የራሳችንን ግንዛቤ ለማጎልበትና ሀገራዊ እንቅስቃሴ በማድረግ የማኅበረሰባችንን ጤናማ መስተጋብር ለማጠናከር እንጠቀምበት ዘንድ የሚረዳንን ይህን መጽሐፍ እንዲያነቡት በአክብሮት እጋብዝዎታለሁ።

መዘምር ግርማ

ደብረ ብርሃን

2008 ዓ.ም.

አኰቴት

ይህን የትርጉም ሥራ በማከናውንበትና በዚህ መልክ ለማሳተም በምጥርበት ወቅት በርካቶች አግዘውኛል፡፡ ረቂቁን በማንበብና በትርጉሙ ሂደት ሁሉ ገንቢ አስተያየታቸውን በመስጠት ከጎኔ የነበሩት ዳዊት ግርማ፣ አዲሱ ኃይሉና ጌጤ ፈለገ ባለውለታዎቼ ናቸው፡፡ ከበደ ይመር መጽሐፉን ካነበበልኝ በኋላ የውይይት ጥያቄዎችን አምጥቶ ከእኔ ጋር ተወያይተናል፡፡ «ጽንፈኛ ሁቱዎቹ አልገባቸውም እንጂ ዳማሲን እኮ ሐብታቸው ነበር!» ያለኝ በአእምሮዬ አሁንም ያቃጭላል፡፡ ዶክተር ያዕቆብ ኃይለማርያም የእንግሊዝኛውንና የአማርኛውን ቅጂ በአንድ ሳምንት ውስጥ አንብበው ለመጽሐፉ ቀዳሜ-ቃል ጽፈውልኛል፡፡ ማበረታቻና አክብሮታቸው እስካሁን ካጋጠሙኝ ከአብዛኞቹ ምሁራን በላይ ነው፡፡ ተማሪዎቻቸውንና ተወራጆቻቸውን አሸቆጥቁጠውና ተኩራርተው የሚገዙ ትልልቅ ሰዎች በየቦታው መጋረጣቸውን ስለታዘብኩ ምናለ ሁሉም እንደርሳቸው ቅን ቢሆኑ? አስብለውኛል፡፡ እንደ ዶክተር ያዕቆብ ሁሉ አሊሹ ሙሜ ኢብራሂምን መጀመሪያ የተዋወቅሁት በኢሜል ነው፡፡ ይሄው ከ1999 ዓ.ም. ጀምሮ የእኔን ጽሑፍ እንዳቃናና በዕውቀት ጎዳና እንደመራኝ አለ፡፡ የአሊሹ የትርጉም ሥራዎች ትኩረት ከፍ ባሉ የጥቁር ሕዝቦች የትግል ታሪኮች ላይ ነው፡፡ ለምሳሌም በማልከም ኤክስና በማርከስ ጋርቪ ላይ ስለሠራቸው ሥራዎች ማውሳት ይቻላል፡፡ እንደ መረሬ የተሰነጣጠቀች የምትመስለውን አገራችንን የባሰ ለማለያየት ስንጥቁን ለማስፋት ከሚጥሩ ልሂቃን በተቃራኒው ስለጥቁሮች አንድነትና ስለ ዓለማችን ሕዝቦች ወዳጅነት እንድናስብ እያደረገን ነው፡፡ እንደ እርሱ አይነቶቹን ያብዛልን! ገረመው ውቤ ደግሞ አፍቴ (ነዳኸው) እያለ የትርጉሜን ሂደት ስለሚከታተል፣ ሰርክዬ ጌታቸው በምቸገርበት ጊዜ ሁነኛ የአማርኛ አገላለጽ ስለምትፈልግልኝ፣ ይድነቃቸው ሰለሞን የትርጉምን ሳይንስ ስለሚያስታውሰኝ፣ አሊ ገበየሁ በእኔ ስለሚተማመንና ሥራው የት ደረሰ እያለ ስለሚንተጉተኝ የአክብሮት ምስጋናዬ ይድረስልኝ፡፡ አንድ ዓመት ለሚጠጋ ጊዜ ስለሩዋንዳ ጉዳይና ስለዘር ፍጅት አውዳሚነት ሳነሳላችሁ ብዙ ምክርና ግንዛቤን የሚያሻሽሉልኝን መዛግብት የለገሳችሁኝ ሁሉ ገለታ ይግባችሁ፡፡

ከራሳችሁ አስበልጣችሁ ለምትወዱኝና ወደር የለሽ ፍቅር ለምትሰጡኝ ለውድ ወላጆቼ፣ ሊኦናርድና ሮዝ፣ ለወንድሞቼ ዳማሲንና ቪያኒ፤ ገነትን አንጸባራቂ ስፍራ ታደርጓታላችሁ፣ ሁሌም እወዳችኋለሁ::

ለወንድሜ ለኤይማብል፣ ከማይነጥፍ ፍቅር ጋር፤ የማይነገር ህመምን ለማዳን ተስፋ ስለማድረግ

እናም ለአዲሱ ቤተሰቤ - ብርያንና የማይጠገቡት ልጆቼ፣ ኒኪና ብርያን ትንሹ - አዲስ ሕይወት፣ ፍቅርና መነሳሳት ስለሰጣችሁኝ:: ሕይወቴን ሙሉ ታደርጓታላችሁ::

በማናቸውም ስፍራ የዘር ማጥፋት ለተፈጸመባቸው መታሰቢያ ይሁንልኝ::

«አንድን ሁኔታ መለወጥ ሲያቅተን ራሳችንን ለመቀየር እንገደዳለን::»

ቪክተር ኢ. ፍራንክል፣ ፒ.ኤች.ዲ፣ ሜዲካል ዶክተር፣ የአእምሮ ሐኪም፣ ደራሲና ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጭፍጨፋ የተረፉ

መቅድም

ይህ መጽሐፍ የሩዋንዳ ወይንም የዘር ፍጅቱ ታሪክ እንዲሆን ታስቦ የተዘጋጀ አይደለም፣ የራሴ ታሪክ እንጂ። አንድ መቶ በሚሆኑ ቀናት ውስጥ በሩዋንዳ መንግሥት ግምት ከአንድ ሚሊዮን በላይ ሰዎች የተፈጁበትን የ1994ቱን የዘር ጭፍጨፋ ነገረ-ሥራ በጥልቀት የመረመሩ ብዙ በጣም ጥሩና መረጃ ሰጪ መጻሕፍት በቅርቡ ታትመዋል።

ይህ እንደሚታወሰኝ የተረኩት ታሪኬ ነው . . . የሚታወሰኝም ልክ ትናንት እንደተከሰተ ነው። ታሪኩም እውነተኛ ሲሆን፤ በውስጡ የራሴን ስምና የቤተሰቤን አባላት ስሞች እጠቀማለሁ። ሆኖም ግን አብዛኞቹን በመጽሐፉ ውስጥ የሚጠቀሱ ሌሎች ስሞችን በሕይወት የተረፉትን ማንነት ለመደበቅና የጥላቻንም ዑደት ላለማስቀጠል በማሰብ ቀይሬያለሁ።

የእያንዳንዳችን ሕይወት እንደተሳሰረና ከየልምዶቻችን እርስ በርስ መማማር እንዳለብን አምናለሁ። ይህን መጽሐፍ የጻፍኩት ሌሎች ከታሪኬ ሊጠቀሙ ይችላሉ ብዬ ተስፋ በማድረግ ነው።

- **ኢማኪዩሌ ኢሊባጊዛ**፣ ኒው ዮርክ

መግቢያ

ኢማኪዩሌ እባላለሁ

ገዳዮቹ ስሜን ሲጠሩ ሰማኋቸው፡፡

እኔ በግንቡ በአንደኛው በኩል ስሆን እነሱ ደግሞ በሌላኛው አቅጣጫ ናቸው፤ አንድ ጋት የማይሞላ ውፍረት ያለው ጭቃና ዕንጨት ብቻ ይለያየናል፡፡ ንግግራቸው ጭካኔ የሚንጸባረቅበትና ቆርጠው መነሳታቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

«እዚህ ነች… እዚህ የሆነ ስፍራ እንዳለች እናውቃለን፡፡ …. ፈልጓት - ፈልጓት ኢማኪዩሌን፡፡»

አካባቢው በሁካታ ተሞላ፡፡ ብዙ ገዳዮች መጥተዋል፡፡ በአእምሮዬ ይታዩኛል - ሁልጊዜ በፍቅርና በደግነት ሰላምታ ይሰጡኝ የነበሩ የቀድሞ ወዳጆቼና ጎረቤቶቼ በቤቱ ውስጥ ጦርና ገጀራ ይዘው ስሜን እየጠሩ ይዘዋወራሉ፡፡

«399 በረሮዎችን ገድያለሁ» ይላል አንደኛው ገዳይ፡፡ «ኢማኪዩሌ 400 ታደርግልኛለች፡፡ ይህን ያህል ከገደልኩ ምን እፈልጋለሁ!»

በትንሿ ምስጢራዊ መታጠቢያ ቤታችን ጥጋት አንድስ እንኳን የሰውነቴን ከፍል ሳላላውስ ተሸሽጌያለሁ፡፡ እንደኔው ሕይወታቸውን ለማትረፍ እንደተደበቁት ሌሎች ሰባት ሴቶች ሁሉ ገዳዮቹ ስተነፍስ እንዳይሰሙኝ ትንፋሼን ውጫለሁ፡፡

ድምጻቸው የሠራ አከላቴን ገማመሰው፡፡ በከሰል ፍም ላይ እንደተኛሁ፣ እሳትም ላይ እንደተጣልኩ ተሰማኝ፡፡ መላ ሰውነቴ የሕመም ውርጅብኝ ወረደበት፡፡ ሺህ የማይታዩ መርፌዎች ተቸከቸኩብኝ፡፡ ፍርሃት እንደዚህ የሚያርበደብድ ስጋዊ ሥቃይ ያስከትላል ብዬ አስቤ አላውቅም፡፡

ለመዋጥ ሞከርኩ፤ ጉሮሮዬ ግን ተዘግቷል፡፡ ምራቅ አልነበረኝም፤ አፌም እንደ ኩበት ደርቋል፡፡ ዓይኖቼን ጨፈንኳቸው፤ ራሴንም ለመደበቅ ሞከርኩ፤ ንግግራቸው ግን እየነላ መጣ፡፡ ምንም ዓይነት ምኅረት እንደማያደርጉልኝ አውቃለሁ፤ በአእምሮዬም አንድ ሐሳብ ያስተጋባ ጀመር - *ከያዙኝ ይገድሉኛል፡፡ ከያዙኝ ይገድሉኛል፡፡ ከያዙኝ ይገድሉኛል…*

ገዳዮቹ በራፉ ላይ አሉ፤ በማንኛዋም አፍታ እንደሚያገኙኝ አውቃለሁ፡፡ ገጀራው ቆዳዬን አልፎ ሲገባና አጥንቴ ድረስ ሲቆራርጠኝ የሚሰማኝ ስሜት ምን እንደሚመስል አሰብኩት፡፡ ወንድሞቼና ወላጆቼም ትዝ አሉኝ፤ ሞተው ወይንም በሕይወት እየኖሩ እንደሆነ፣ በገነት ከአፍታ በኋላ እንገናኝም እንደሆነ አለምኩ፡፡

እጆቼን እርስ በርሳቸው አጣመርኳቸው፤ የአባቴን መቁጠሪያም ጥብቅ አድርጌ ያዝኩ፤ በለሆሳስም መጸለይ ጀመርኩ - *እባክህ እግዚአብሔር ሆይ፣ እባክህ እርዳኝ፡፡ በዚህ ዓይነት ሁኔታ እንድሞት ሊታድርገኝ፣ እንደዚህ ሊይሁን፡፡ እነዚህ ጉዳዮች እንዲያገኙኝ ሊታድርግ፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስህ ከጠየቅን እንደሚሰጠን ትነግረናለህ… እንግዲህ ጌታዬ እየጠየኩህ ነው፡፡ ወይ በለኝ፡፡ እባክህን እነዚህን ጉዳዮች ወዲያ እንዲሄዱ ሊድርጋቸው፡፡ ኧረ በዚህ መታጠቢያ ቤት እንድሞት ሊታድርገኝ፡፡ እባክህ፣ እግዚአብሔር፣ እባክህ፣ እባክህ፣ <u>እባክህ</u> ሊድነኝ፡፡*

ጉዳዮቹ ከቤቱ ወጥተው ሄዱ፡፡ እኛም እንደገና መተንፈስ ጀመርን፡፡ ሄደዋል፤ ሆኖም ግን በቀጣዮቹ ሦስት ወራት ውስጥ ብዙ ጊዜ ይመላለሳሉ፡፡ ሕይወቴን እግዚአብሔር እንዳተረፋት አምናለሁ፤ ሆኖም ቁምሣጥን በምታክል መታጠቢያ ክፍል ውስጥ ከሰባት ሌሎች ሰዎች ጋር በፍርሃት እየተርበደበድኩ ባሳለፍኳቸው 9ነ ቀናት መትረፍ ከመዳን በጣም የተለየ አንደሆነ እማራለሁ… ይህ ትምህርትም ለዘለቄታው ለውጦኛል፡፡ ይህ ትምህርት በጅምላ ጭፍጨፋ ውስጥ የሚጠሉና የሚያሳድዱኝን እንዴት መውደድ እንዳለብኝ - ቤተሰቤን ያረዱትንም ሁሉ እንዴት እንደምምር ዕውቀት የቀሰምኩበት ነው፡፡

ስሜ ኢማኪዩሌ ኢሊባጊዛ ነው፡፡ ይህ በታሪክ ብዙ ሕዝብ ካለቀባቸው ጭፍጨፋዎች በአንዱ እግዚአብሔር እንዴት እንደተገለጠልኝ የሚያሳይ ታሪክ ነው፡፡

ክፍል ፩

ክፉ ቀን ዳር ዳር ሲል

ምዕራፍ 1

የዘላለማዊ ፀደይ ምድር

የተወለድኩት በገነት ነው።

ስለ ትውልድ ሀገሬ በልጅነት ዘመኔ የሚሰማኝ ይህ ነበር።

ሩዋንዳ በመካከለኛው አፍሪካ እንደጌጥ ጣል የተደረገች ትንሽ ሀገር ነች። በጣም ማራኪ ውበት ስላላት፣ በለምለም ሸንተረሮቿ፣ ጭጋግ በሸፈናቸው ተራሮቿ፣ በአረንጓዴ ሸለቆዎቿና በአንጸባራቂ ሐይቆቿ ተማርኮ ለምስጋና ወደ አምላክ አለማንጋጠጥ የማይታሰብ ነው። ከተራሮቿ ቁልቁል የተለያየ ዝርያ ወዳላቸው የጽድ ጫካዎቿ የሚወርደው ነፋሻ አየር በልዩ ልዩ አበቦች መዐዛ የተሞላ ነው። የአየሩም ሁኔታ ዓመቱን ሙሉ በጣም ተስማሚ በመሆኑ በነፃኛው ክፍለዘመን መጨረሻ አካባቢ ወደ ስፍራው የመጡት የጀርመን ሰፋሪዎች ሀገሪቱን «የዘላለማዊ ፀደይ ምድር» ብለው ሰየሟት።

ውድ ሀገሬን በደም ጎርፍ እንድትታጠብ ያደረጓት ለጅምላ ጭፍጨፋ መነሻ የሆኑት ርኩሳን ሃይሎች በልጅነቴ ተሰውረውብኝ ነበር። በልጅነቴ የማውቀው ነገር የከበበኝን አማላይ መልከዓምድር፣ የጎረቤቶቼን ደግነት፣ የወላጆቼንና የወንድሞቼን ጥልቅ ፍቅር ነበር። በቤታችን ዘረኝነትና ምክንያት የለሽ ጥላቻ በፍጹም አይታወቁም። ሰዎች የተለያየ ጎሳና ዘር እንዳላቸው እንኳ ግንዛቤው አልነበረኝም፤ *ቱትሲና ሁቱ* የሚሉትን ቃላትም ቢሆን ትምህርት ቤት እስከገባሁበት ጊዜ ድረስ አልሰማኋቸውም።

በሰፈሬ ትንንሽ ልጆች ከቤት ወደ ትምህርት ቤት ብቻቸውን ጭር ባለው አሥራ ሦስት ኪሎሜትር መንገድ ሲመላለሱ ወላጆቻቸው ልጄ ይጠለፍብኛል ወይንም በማናቸውም መንገድ ይጎዳብኛል ብለው አይጨነቁም። ልጅ ሆኜ በጣም የምፈራው ነገር በጨለማ ብቻዬን መሆንን ሲሆን፤ ከዚያ በስተቀር ግን ሰዎች የሚከባበሩበት፣ የሚተሳሰቡበትና ደስተኛ ይመስለኝ በነበረ መንደር ውስጥ ከደስተኛ ቤተሰብ ጋር የምኖር በጣም ፍልቅልቅ ልጅ ነበርኩ።

የተወለድኩት በምዕራብ ሩዋንዳዋ የኪቡዬ ክፍለ-ሀገር፣ በማታባ መንደር ነው። ቤታችን ከኪቩ ሐይቅ ትይዩ በሚገኝ ኮረብታ ላይ ያለ ሲሆን፤ ሐይቁም ከቤታችን እስከ ዓለም ጠርዝ የተዘረጋ ይመስላል። ጠዋት ሰማዩ ከጠራ በሐይቁ በሌላኛው ጠርዝ በጎረቤት ሀገር ዛየር፣ በአሁኑ አጠራሩ ኮንጎ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ፣ ያሉትን ተራሮች አያለሁ። ከቤታችን ወደ ሐይቁ የሚወስደውን አስቸጋሪ ቁልቁለት መውረድ

ከአስደሳች የልጅነት ትዝታዎቼ አንዱ ነው። የማለዳው ጤዛ በንጋቷ ጸሐይ ተኖ የሚያልቅበት ጊዜ ሲቃረብ ከአባቴና ከወንድሞቼ ጋር ወደ ዋና እወርዳለሁ። ውሃው ሞቃት፣ የአየሩ ቅዝቃዜ ውርር የሚያደርግና ከሐይቁ ዳርቻ ያለው የቤታችን እይታ ዘወትር አማላይ ነበር።

አቀበቱና በእግራችን የምንረግጠው አሳሳች ልል አፈር ወደ ቤት የምናደርገውን የመልስ ጉዞ አስፈሪም አስደሳችም ያደርጉታል። ብዙውን ጊዜ ስለሚያንሸራትተኝ ገደል ገብቼ ሐይቁ ውስጥ እንዳልወድቅ እፈራለሁ። አባቴም ሁልጊዜ ስፈራ ስለሚያውቅ እቤት እስክንደርስ ድረስ በእጁ ይደግፈኛል። ትልቅና ጠንካራም በመሆኑ በእነዚያ ትላልቅ እጆቹ በመያዜ ደህንነት ይሰማኛል፤ እንደተወደድኩም ይገባኛል። እንደዚያ በፍቅር ጢል መደረግ ደስ ያሰኘኛል። ለዚህም ምክንያት የሆነው በተለይ አባቴ ምንም እንኳን እንደሚወደን ብናውቅም በዘልማዳዊው መንገድ የሚያምን፣ ስሜቱን ብዙውን ጊዜ አውጥቶ የማያሳይና ወንድሞቼንም ሆነ እኔን እንደሚወደን የማይነግረን በመሆኑ ነው።

ከዋና ስንመለስ ቆንጆዋ እናቴ በየቀኑ ወደ ትምህርት ቤት ከመሄዳችን በፊት የምትመግበንን ትኩስ የሩዝና የፎሶሊያ ቁርስ እየሠራች በኩሽና ስትባትል እናገኛታለን። ብርታቷ እኔን ከማስደነቅ ቦዝኖ አያውቅም - እማማ ሁልጊዜ ከቤተሰባችን አባላት ሁሉ ከእንቅልፍ ለመነሳት የመጀመሪያዋና ወደ መኝታ ለመሄድ የመጨረሻዋ ነበረች፤ ቤቱን እንደሚጠበቀው ለማሠጋደድ፣ ልብሶቻችንን ለማስተካከል፣ መጻህፍታችንንና በትምህርት ቤት የሚጠበቁብንን ጉዳዮች ለማዘገጃጀትና የአባቴን የሥራ ወረቀቶች ለማደራጀት ከሁላችንም በፊት ቀድማ እየተነሣች ትለፋለች። ልብሶቻችንን ሁሉ እሷው በልካችን ትሰፋለች፣ ጸጉራችንን ትቆርጣለች፤ ቤቱንም በእጅ ሥራዎች ጌጦች ታሸበርቀዋለች።

ለቁርሳችን የምትሠራው ፎሶሊያ የሚለማው እኛ ጠዋት ከመኝታችን ሳንነሳ እማማ በምትንከባከበው በጓሮ አትክልት ማሳችን ነው። እህሉን ቃኝታ ለቀን ሠራተኞቹ የእርሻ መሣሪያዎች ታከፋፍልና ላሞቻችንና ሌሎቹ እንስሶቻችን እንዲቀለቡና እንዲታጠቡ ታደርጋለች። እነዚህን የማለዳ ሥራዎቿን ከጨራረሰች በኋላ እኛን ወደ ትምህርት ቤት ትሸኘና በእግሯ ቁልቁል መንገዱን ይዛ የሙሉ ጊዜ የማስተማር ሥራዋን ለመጀመር በአቅራቢያችን ወዳለው አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ትሄዳለች።

ወላጆቼ መምህራን ነበሩ። ድህነትንና ርሃብን ብቸኛው መመከቻም ትምህርት እንደሆነ በጽኑ ያምናሉ። በቆዳ ስፋቷ ከሞላ ጎደል ጂቡቲን የምታክለው ሩዋንዳ ከአፍሪካ ትናንሽ ሀገራት አንዷ ብትሆንም በአህጉሩ በከፍተኛ የሕዝብ ጥግግት ተጠቃሽና ከዓለምም ደሃ ሀገራት አንዷ ነች። እናቴና አባቴ ከየቤተሰቦቻቸው የመጀመሪያዎቹ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ያጠናቀቁ ሰዎች ሲሆኑ ልጆቻቸው እነርሱ

ከደረሱበትም በላይ እንድንደርስላቸው ቆርጠዋል። አባባ ጠንክሮ በመሥራትና በሕይወቱ ሙሉ በማጥናት አርዓያ ሆኖናል። በሥራ ሕይወቱ ብዙ ክብሮችንና ዕድገቶችን ያገኘ ሲሆን፤ በአጭር ጊዜም ከአንደኛ ደረጃ መምህርነት ወደ መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህርነት አድጓል። በኋላም በአውራጃችን ላሉት ለሁሉም የካቶሊክ ትምህርት ቤቶች ዋና አስተዳዳሪ ሆኖ ተሾሟል።

በሩዋንዳ እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ልዩ የሆነ መጠሪያ ስም አለው። ለእያንዳንዱ ልጅ ወላጆች ልጁ ሲወለድ እናቱ ወይንም አባቱ መጀመሪያ ባዩት ጊዜ የተሰማቸውን ስሜት የሚያንጸባርቅ ስም ይሰጡታል። ኪንያሩዋንዳ በሚባለው ያገራችን ቋንቋ የኔ ስም (ኢሊባጊዛ) ትርጉሙ «መንፈሰ-ብሩህና ግሩም ጸዳል ያላት» ማለት ነው። ይህን ስም ያወጣልኝ አባቴ ከተወለድኩባት ቅጽበት ጀምሮ ምን ያህል እንደሚወደኝ ስሜ ሁልጊዜ ሲያስታውሰኝ ይኖራል።

የአባቴ ስም ሊኦናርድ፣ የእናቴ ደግሞ ማሬ ሮዝ ሲሆን፤ እናቴን ባልንጀሮቿ ሮዝ እያሉ ይጠሯታል። በ1963 ከረምት በአንደኛዋ የአክስቴ ልጅ ቤት ወላጆቼ ወደጋራ ጓደኞቸው ሰርግ ሲሄዱ ይገናኛሉ። ሲተዋወቁ አባቴ ጸጉሩ አድጎ እንደነገሩ ስለነበር እናቴ አየት አድርጋው ከንፈሯን መጠጠችለት።

«ጸጉርህ እንደዚህ ሆኖ ሰርግ ልትሄድ ነው?» በማለት በቁጭት ጠየቀችው።

አባቴ ጸጉር አስተካካይ ማግኘት እንዳልቻለ ገልጾ ‹ምን ላድርገው ብለሽ ነው› በሚል ስሜት ትከሻውን ነቀነቀ። ወዲያውኑ እዚያው እናቴ መቀስ ፈልጋ አባቴን አመቺ ስፍራ አስቀመጠችና ጸጉሩን ማስተካከል ጀመረች። ጸጉር ቆረጣውን እንዳሳመረችው አይጠረጠርም - ከዚያ ጀምሮ አልተለያዩምና። በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ታጋብተው አባቴ ከዚያ በኋላ እናቴ እንጂ ሌላ ማንም ሰው ጸጉሩን እንደማያስተካክለው አረጋገጠ።

ወላጆቼ በማስተማር ሥራቸውና አያቴ የሰጣቸውን መሬት በማረስ (ባቄላ፣ ሙዝና ቡና እያመረቱ ይሸጡ ነበር) ከሚያገኙት ገቢ ትንሽ ገንዘብ መቆጠብ ቻሉ። በምዕራቡ ዓለም ደረጃ ልከኛ ሊባል የሚችለውና በመንደራችን በጣም የቅንጦት የሚባለው ቤታችን አባቴ ንድፉን አውጥቶ የገነባው ነው። ማእድ ቤት፣ መመገቢያ ክፍል፣ የየራሳችን መኝታ ቤቶች፣ የእንግዳ ቤትና የአባቴን የግል ሥራ ማከናወኛ ክፍልን ያጠቃልላል። የራሱ በር ያለው የቀን ሠራተኞቻችን የሚያሳልፉበት ተቀጥላ ግቢና ለእንስሶቹም ራሱን የቻለ ከግቢው የተለየ በረት ስለነበረን ላሞቹ ከኛ ጋር እቤታችን ውስጥ አይተኙም። አባቴ በቤታችን ጣራ ላይ የሚያርፈውን የዝናብ ውሃ ያጠራቅመው ስለነበር ከኪቩ ሐይቅ ድረስ ውሃ መጎተት ቀርቶልናል፤ የገጠማቸውም የጸሐይ ብርሃንን ቀን ቀን አምቀው ይዘው ማታ ለመብራት የሚጠቅሙ ዕቃዎች ምሽት የአንድ ሰዓት ብርሃን ይሰጡናል።

እኛ እንኖርበት በነበረው የሩዋንዳ ክፍል ተሰምቶ በማይታወቅ ሁኔታ ሁለት ተሽከርካሪዎች ነበሩን፡፡ አባቴ የሩቆቹን ገጠራማ ትምህርት ቤቶች ለመጎብኘት የሚንቀሳቀስበት ቢጫ ዶቅዶቄና በሰንበት ቤተክርስቲያን ለመሳምና ዘመዶቻችንን ለመጠየቅ የምንጠቀምባት ትንሽ ተሽከርካሪ ነበረችን፡፡ አንዳንድ የሰፈራችን ሰዎች ሃብታም ባንሆንም ናችሁ ይሉናል፤ አባቴንም *ሙሥንጉ* ማለትም «ፈረንጅ» ወይንም «ሃብታም» (ለአብዛኞቹ ሩዋንዳውያን ተመሳሳይ ናቸው) ይሉታል፡፡

በመንደራችን ማንም ሌላ ሰው ዶቅዶቄ አልነበረውም፡፡ ከዚህም የተነሣ እናቴ ሁልጊዜ አባቴ ጭር ባለ ተራራ ሲሄድ በሽፍቶች እንዳይጠቃ ትጨነቃለች፡፡ ስለቤተሰቧ መጨነቅ ልማዷ ሲሆን፤ ከአንድ ምሽት በላይ ከቤት ስንርቅ ሁልጊዜ ማታ ማታ በሬድዮ የሚነገረውን የሐዘን መግለጫ እስከመኪታተል ትደርሳለች፡፡

ከቶ ላይሳካልኝ «እማማ ስለ መጥፎ ኢጋጣሚ አብዝተሽ ከምትጨነቂ እስኪ ደግ ደጉን ተመኚ» እላታለሁ፡፡

«አይ ኢማኪዩሌ አንድ ሰው ከልጆቼ አንዱን ወይንም አባትሽን እንዲህ ያለ ክፉ ነገር ደረሰበት ብሎ በሩን ቢያንኳኳብኝ እኮ አልችለውም፡፡ ከማንኛችሁም በፊት እንድሞት ነው ጸሎቴ፡፡» ለጤናችንና ለደህንነታችን ያለማቋረጥ ትጸልያለች፡፡

ወላጆቼ ጽኑ የሮማ ካቶሊካውያን የነበሩ ሲሆን፤ እምነታቸውንም ለኛ አስተላልፈውልናል፡፡ እቤት የምሽት ጸሎት ማድረስ ልማዳችን እንደሆነው ሁሉ የእሁድን ቅዳሴም አናስታጉልም፡፡ እኔ በበኩሌ ጸሎት ማድረስ፣ ቤተክርስቲያን መሄድና ከአምላክ ጋር የሚያገናኝን ማናቸውንም ነገር ማድረግ እወዳለሁ፡፡ ድንግል ማርያምን ከገነት ሆና የምትጠብቀኝ ሁለተኛዋ እናቴ እንደሆነች በማመን በተለየ ሁኔታ ስወዳት እኖራለሁ፡፡ ለምን እንደሆነ ባላውቅም መጸለይን እወደውና ያስደስተኝ ነበር፡፡ በእርግጥ በጣም ያስደስተኝ ስለነበር በአሥር ዓመቴ አንድ ቀን ከጓደኛዬ ከጣኔት ጋር ከትምህርት ቤት የቤተሰባችን ጥሩ ወዳጅ የነበሩትንና እንደ አያቴ የማያቸውን ብልህ አረጋዊ ቄስ አባ ክሌሜንትን ለመጠየቅ ጠፍቼ ሄድኩ፡፡

ጣኔትና እኔ አባ ክሌሜንት ዘንድ ለመድረስ በእግራችን አሥራ አንድ ኪሎሜትር ሜዳና ጫካ ተጓዝን፤ ወንዝም አቋረጥን፡፡ ሞቅ አድርገው ሰላም ያሉን ቢሆንም መኖሪያቸው ጋ ስንደርስ በጣም ደክሞን፣ እያለከለክን፣ ረጥበንና ቆሸሸን ስለነበር ሐሳብ ገብቷቸዋል፡፡ ሲቀበሉን ገቮቅ ያለውን ነጭ ልብሰ-ተክህኗቸውን ለብሰው፣ እጆቻቸውን ዘርግተውና የሚያምር መቁጠሪያ ባንገታቸው አድርገው ልክ መልአክ መስለዋል፡፡«ምንድነው ልጆቼ? ምን ልርዳችሁ?» ሲሉ ጠየቁን፡፡

«አባ ሕይወታችንን ለእግዚአብሔር መስጠት እንፈልጋለን» አለች ጣኔት፡፡

«ልክ ነው አባ» ስል ተስማማሁ፡፡«አስበንበታል፣ መመንኮስ እንፈልጋለን፡፡»

ምንም እንኳን ሳቃቸውን እንደደበቁ እርግጠኛ ብሆንም «መመንኮስ? እህ» አሉ ራሳቸውን በመስማማትና በቁምነገር እየነቀነቁ፡፡ እጆቻቸውን ራሶቻችን ላይ አድርገው ልዩ ቡራኬ ሰጡን፡- «እግዚአብሔር ሆይ፣ እነዚህን ውድ ልጆች ባርካቸው፤ ከክፉ ጠብቃቸው፤ በዕድሜ ዘመናቸውም ሁሉ ካጠገባቸው አትለይ፡፡» ከዚያም አየት አደረጉንና «አሁን ወደየቤታችሁ ሂዱ፡፡ ከ8ኛ ዓመት ልደታችሁ በኋላ ተመልሳችሁ ኑ፤ የዚያን ጊዜም የመመንኮሱ ሐሳብ የሚኖራችሁ ከሆነ እንነጋገራለን፡፡»

ወላጆቼ ጽኑ ካቶሊኮች የነበሩ ሲሆን፤ ክርስቲያንነታቸው እውነተኛ ነው፡፡ «ሰዎች ለእናንተ ሊያደርጉላችሁ እንደምትፈልጉት አድርጉላቸው» በሚለው በወርቃማው ሕግ ስለሚያምኑ ጎረቤቶቻችንንም በደግነትና በአክብሮት እንድንቀርብ ያስተምሩናል፡፡ ከመንደራቸው ጋር ጥብቅ ቁርኝት እንዳላቸው ስለሚሰማቸው የበለጸገና ስሙር ማኅበረሰብ ለመፍጠር በሕይወት ዘመናቸው ሙሉ ግረዋል፡፡ አባቴ ብዙ ሰንበቶችን የበጎ አድራጎት ሥራ ላይ ያሳልፍ የነበረ ሲሆን፤ ለአብያተክርስቲያናት ቤቶችን መገንባትን የመሳሰሉ ሥራዎችን ወጭዎቹን ከኪሱ እየሸፈነ ያሠራል፡፡ ለደሃ ሕፃናት የትምህርት ዕድል የሚሰጥ ተቋም አቋቁሞ ከሩዋንዳ ጥቂት የቡና አምራቾች ሁለገብ የኅብረት ሥራ ማኅበራት አንዱን በመመስረት ደርዘን የሚደርሱ የቡና ገበሬዎችን ከትርፋቸው ትንሽ ገንዘብ ለተቋሙ እንዲሰጡ ከተስማሙ በራሱ መሬት ላይ ከኪራይ ነጻ ያሠራል፡፡ መርሃ-ግብሩ በጣም ስኬታማ ስለሆነለት በተወሰነው ገንዘብ የማኅበረሰብ ማእከል መመስረት፣ ለወጣቶች የእግር ኳስ ሜዳ መሥራትና ለትምህርት ቤቱ አዲስ ጣራ ማልበስ ችሎ ነበር፡፡

እናቴም ብትሆን በብዙ መልካም ሥራዎቿ ትታወቃለች፡፡ የተቸገረን ሰው አታልፍም፤ ቀን ጎድሎባቸው ወድቀው በእግራቸው መቆም እስኪችሉ ድረስ መቆያ ቤት የሚፈልጉ ሰዎችን ሁልጊዜ በቤታችን ታኖራለች፡፡

እናቴ የዕለት ሥራዋን ከጨረሰች በኋላ ተማሪዎችን በነጻ ታስጠናና ዕድሜ ልኳን ለሴት ተማሪዎች የደንብ ልብስ ለመስፋት ግብዓቶችን ትገዛ ነበር፡፡ አንዴ ጎረቤታችን ለልጇ የሙሽራ ልብስ መግዛት አለመቻሏ አሳስቧት ለእናቴ ስታዋያት ሰማሁ፡፡

«ሮዝ፣ የገዛ ልጄን በአሮጌ ልብስ ወደ አዲሱ ሕይወቷ የምልካት እንዲያው ምን ዓይነት እናት ብሆን ነው?» ስትል ሴትዮዋ አዋየቻት፡፡ «የሚሸጥ ፍየል ቢኖረኝ በሰርጓ ዕለት መልበስ የነበረባትን ልብስ ላለብሳት እችል ነበር፡፡»

እናቴ በፈጣሪ ዕምነት ካላት እንደሚሰጣት በመግለጽ እንዳትጨነቅ ነገረቻት፡፡ በቀጣዩ ቀን እናቴን ከወርሃዊ ደሞዟ ላይ የቆጠበችውን ገንዘብ ስትቆጥር አየኋት፡፡ ወደ መንደሩም በእግሯ ሄዳ እጆቿ በአብረቅራቂ ብትን ጨርቆች ተሞልተው ወደ ቤት

ተመልሳ መጣች፡፡ ሌሊቱን ሙሉ ተቀምጣ ለሴትዮዋ ልጅና ለሁሉም ሚዜዎች ቀሚሶቹን ስትሰፋ አደረች፡፡

እናቴና አባቴ መንደሩን በሙሉ እንደ ዘመዳችን ስለሚያዩ መንደርተኞቹም በበኩላቸው ብዙውን ጊዜ እንደ ወላጆቻቸው ነበር የሚያዩአቸው፡፡ ለምሳሌ አባቴ በክልሉ የተማረ፣ አስተዋይና ፍትሃዊ ሰው ተብሎ ይታሰብ ነበር፡፡ ስለሆነም ሰዎች በቤተሰብ ጉዳይ፣ በገንዘብ ችግርና በንግድ ሐሳቦች ላይ ምክሩን ፈልገው ብዙ ርቀት ተጉዘው ይመጣሉ፡፡ ግጭቶችን እንዲፈታላቸውና ባለጌ ልጆቻቸውን እንዲያርምላቸውም ይፈልጉታል፡፡

አብዛኛውን ጊዜ በሰፈራችን ያለ ችግር የእኛን በር በማንኳኳትና በሚከተለው ልመና ይታጀባል - «ሊአናርድ ልትረዳን ትችላለህ? ምክርህን እንፈልጋለን፡፡ ምን ብናደርግ ይሻላል ሊአናርድ?»

አባቴ ሰዎችን ወደ ቤት በማናቸውም ሰዓት ላይ ይጋብዝና ችግሮቻቸው መፍትሔ እስኪያገኙ ድረስ ያዋያቸዋል፡፡ ጥሩ ሽማግሌና ሰዎች የራሳቸውን ችግር በራሳቸው እንደፈቱ ያህል እንዲሰማቸው የሚያደርግ ሰው ነው፡፡

እናቴም ከባሎቻቸው ጋር ችግር ውስጥ በሚገቡ ሴቶች ለምክር ትፈለጋለች፡፡ ባሳለፈቻቸው ዓመታት በሙሉ ከጎረቤቶቻችን ብዙዎቹ በአንድ ወቅት ተማሪዎቿ ስለነበሩ አብዛኛዎቹ መንደርተኞች መምህርት ይሏት ነበር፡፡

ወላጆቼ ለመንደራቸው ኃላፊነት እንደሚሰማቸው ሁሉ በእርግጠኝነት ለልጆቻቸውም ያስባሉ - በተቻላቸውም መጠን ከኛ ጋር ብዙ ጊዜ ያሳልፋሉ፡፡

አባቴ አንድ ምሽት ሥራ ቦታ በማምሸት መጠጥ ለመጠጣት ከጓደኞቹ ጋር ሄዶ ወደ ቤት ሲመጣ ተኝተን ይደርሳል፡፡ ትንሽ ሞቅ ቢለውም በፍቅር ተሞልቶ «ልጆቼ የታሉ? የምወዳቸው ልጆቼ የታሉ?» ብሎ ይጠይቃል፡፡

እናቴ «ተኝተዋል፤ ሊአናርድ፣ መተኛት ስላለባቸው፤ ልታያቸው ከፈለግህ በጊዜ መምጣት ነበረብህ፡፡» ብላ ትቆጣዋለች፡፡ «በቃ ራት ብቻዬን አልበላም» ይልና ቀስ ብሎ ሁላችንንም ከመኝታችን ያስነሳናል፡፡ እሱ ራት ሲበላና ስላዋዋሉ ሲነግረን የሌሊት ልብስ ለብሰን በጠረጴዛው ዙሪያ እንቀመጣለን፡፡ አቤት እያንዳንዷን ደቂቃ እንዴት እንዳጣጣምናት!

አባታችን ራቱን በልቶ ከጨረሰ በኋላ ሁላችንንም ሳሎን ያንበረክከንና የምሽት ጸሎታችንን እንድናደርስ ያደርገናል፡፡

«ጸሎታቸውን እኮ አድርሰዋል ሊአናርድ፡፡ ነገ እኮ ትምህርት አለባቸው!»

«ምን እነርሱ ብቻ፣ እኔስ ብሆን? እንደምታውቂው ነገ ሥራ አለብኝ፣ ሮዝ፡፡ በይ ኢማኪዩሌ፣ ብዙ ጸሎት ማድረግ የለብሽም፡፡ ልክ ነኝ?»

«አዎን አባባ» እላለሁ አፍሬ፡፡ አባቴን አመልከው ስለነበር እንደዚህ ዓይነት ወሳኝ ጥያቄ ስለጠየቀኝ ደስታ ተሰማኝ፡፡

የአባቴ ኮስታራ መሳይ ገጽታ የማይኖርባቸውና የእርሱን ፍቅር ማየት ለኛ ቀላል የሚሆንባቸው እንደዚህ ያሉ አስደናቂ ጊዜያት ነበሩን፡፡

በቤተሰባችን ውስጥ አራት ልጆች ነበርን - እኔና ሦስት ወንድሞቼ፡፡ ትልቁ፣ ወላጆቼ ከተጋቡ ከአንድ ዓመት በኋላ በ1965 የተወለደው፣ ኤይማብል ነው፡፡ ልጅ ሆኖ እንኳን ኤይማብል ከቤተሰባችን በጣም ኮስታራው ነበር፡፡ ጸጥ ያለና የሚብሰለሰል ስለነበረ የቤተሰቡ ቁስ እያልን እንቀልድበታለን፡፡ እናታችን የበኩር ልጇ በመሆኑ ከሁላችንም አስበልጣ ብትወደውም ኤይማብል ግን እናታችን በምታደርግበት ተጨማሪ ትኩረት ራሱን ዝቅ ዝቅ ለማድረግ፣ ዓይናፋር ለመሆንና ለመሸማቀቅ በቃ፡፡ ለሰው የሚመች ስብዕና አለው፤ ረብሻንም አምርሮ ይጠላል፡፡ ሌሎቹ ልጆች ቤቱን ሲረብሹና እርስ በእርሳቸው ሲጣሉ በመካከላቸው ይገባና ይገላግላል፡፡

አባታችን በማይኖርበት ጊዜ ኤይማብል የእርሱን ቦታ በመተካት የቤት ሥራችንን መሥራታችንን፣ የማታ ጸሎታችንን ማድረሳችንንና በሰዓቱ መተኛታችንን ያረጋግጣል፡፡ ከዚያም በኋላ አምሽቶ በሮቹ መቆለፋቸውንና ቤቱ ሌሊቱን አስተማማኝ መሆኑን ይቆጣጠራል፡፡ ሰውነቱ ከዕድሜው በላይ ቢያስመስለውም እኔን ግን ስለ አዋዋሌ ለመጠየቅ የማይቦዝን፣ በትምህርቴ እንዴት እየገፋሁ እንደሆነና ጓደኞቼ በደኅና ይቀርቡኝ መሆኑን የሚጠይቀኝ አፍቃሪ ወንድሜ ነበር፡፡ በእኔና በኤይማብል መካከል የ5 ዓመታት የዕድሜ ልዩነት ሲኖር እንደ ልጆችነታችን እርስ በርስ ለመተዋወቅ ችግር ፈጥሮብናል፡፡

ወንድሜ ወደ አዳሪ ትምህርት ቤት ሲሄድ የሰባት ዓመት ልጅ ስሆን ከዚያም በኋላ እርስ በርስ የምንተያያው በበዓላት ቀንና በድግሶች ጊዜ ሆነ፡፡ ከቤት የሄደ ዕለት ግን የሚያስጨንቅ የሆድ ህመም ያዘኝ፡፡ ትምህርት ቤቱ የሚገኘው በአቅራቢያችን ባለች ከተማ ቢሆንም ለኔ ግን ወንድሜ ወደ ጨረቃ የሚሄድ መሰለኝ፡፡ የምወደውን ሰው በማጣቴ አካላዊ ህመም ሲሰማኝ ለመጀመሪያ ጊዜ ነበር፡፡ ከጥቂት ቀናት በኋላ እኛን ልጆቹን አባቴ ለኤይማብል ደብዳቤ እንድንጽፍለት ሲያደርገን ማለት የቻልኳቸው ሁለት ነገሮች ነበሩ፡፡ በትላልቅ ቅጥልጥል ፊደላት የሚከተለውን ጻፍኩ -

ውድ ኤይማብል፣

እወድሃለሁ፤ እናፍቅሃለሁ፤ እወድሃለሁ፤ እናፍቅሃለሁ፤ እወድሃለሁ፤ እናፍቅሃለሁ፤ እወድሃለሁ፤ እናፍቅሃለሁ፤ እወድሃለሁ፤ እናፍቅሃለሁ፤ እወድሃለሁ፤ እናፍቅሃለሁ፤ እወድሃለሁ፤ እናፍቅሃለሁ፤ እወድሃለሁ፤ እናፍቅሃለሁ፤ እወድሃለሁ፤ እናፍቅሃለሁ፤ እወድሃለሁ፤ እናፍቅሃለሁ፤ እወድሃለሁ… እናፍቅሃለሁ!!!!!

እወድሃለሁ፣

ኢማኪዩሌ

የቀረ ነገር አለ፤ ይሽውም - እናፍቅሃለሁ ነው!

አባቴ ሲያነበው ሳቀ፡፡ «የአያትሽን ቤት እንደጎበኘሽ ወይንም ወንድሞችሽ እንዴት እንደሆኑ ምንም የገለጽሽው ነገር የለም ኢማኪዩሌ፡፡ ትንሽ ወሬ ጨመር አድርገሽና እወድሃለሁና እናፍቅሃለሁ የሚለውን ቀንሰሽ እንደገና ለመጻፍ ሞክሪ እንጂ» ሲለኝ፤ «ግን የሚሰማኝ ያ ነው እኮ አባባ» በማለት መለስኩ፡፡

ወንድሜን ከዚያ አሳንሼ እንድወድ እንዴት እንደፈለገ ሊገባኝ አልቻለም - እና አባቴ ስለዚያ ደብዳቤ እያነሳ ሁልጊዜ ይቀልድብኛል፡፡

ኤይማብል ከተወለደ ከሁለት ዓመታት በኋላ ሌላኛው ታላቅ ወንድሜ ወደ ዓለም መጣ፡፡ ስሙ ዳማሲን ሲሆን፤ ጎበዝ፣ ተጫዋች፣ ቀልደኛ፣ ደግ፣ በማይታመን ሁኔታ ለሰው አሳቢና መቋቋም በማይችሉት መንገድ የሚወዱት ነው፡፡ በየቀኑ ያስቀኛል፤ ሳለቅስ እንዴት እንደሚያስቆመኝ ሁልጊዜ ያውቅባታል፡፡ ዳማሲንን እስከዛሬ ድረስ ፈገግ ሳልል ወይንም ሳላለቅስ ስሙን መጥራት አልችልም፡፡ በሦስት ዓመታት ቢበልጠኝም እንደመንትያዬ አየዋለሁ፡፡ የቅርብ ጓደኛዬና ነፍሴ ነበር፡፡

ሲከፋኝ ዳማሲን ደርሶ መንፈሴን መልሶ ያነቃቃዋል - ልክ እናቴ ወንዶቹ ልጆች እግር ኳስ እየተጫወቱ ግቢውን እንዳጸዳ ትዕዛዝ ሰጥታኝ እንደተናደድኩባት እለት፡፡ ዳማሲን ጨዋታውን ትቶ፣ ጓደኞቹን ረስቶ እኔን ሊያግዘኝ ወሰነ - ቀሚስ ለብሶ!

«የሴት ሥራ መቼም አያልቅ» እያለ ድምጹን ከፍ አድርጎ የቁም መጥረጊያውን ያዝ አድርጎ ሲዘፍን እስኪደክመኝ አሳቀኝ፡፡ ከሰዓት በኋላም ከኔ ጋር ሲለፋ ዋለ፡፡

አልፎ አልፎ አስቸጋሪ ጸባይ ቢታይበትም ሁኔታዎች በደግ ማለቃቸው የተለመደ ነበር፡፡ የ12 ዓመት ልጅ ሳለ በምስጢር የአባባን ተሽከርካሪ «ተውሶ» ራሱን በራሱ አነዳድ ለማስተማር ሞከረ፡፡ እንደ ወትሮው ቢሆን ኖሮ አባቴ ለጥፋቱ ከፉኛ ሊቀጣው ሲገባ ጉዳዩን ባወቀ ጊዜ ግን ይብሱኑ ልጁን አቀፈው፡፡ እናቴ አስሚ በድንገት በተነሣባት ወቅት አባቴ ለሥራ ጉዳይ ከአካባቢያችን ርቋል፡፡ በከፊል ራሷን

ስታና ለመተንፈስ ተቸግራ መሬቱ ላይ ትወድቃለች። ዳማሲን ትከሻው ላይ አውጥቶ ተሸክሟት፣ ተሸከርካሪው ጋ ወስዶ፣ በጥንቃቄ ከኋላ ወንበር አስቀምጧት፣ 15 ኪሎሜትር ነድቶ ወደ ቅርቡ ሐኪም ቤት ይወስዳታል። በመንገድ ላይ ከሁለት ላሞች፣ ሦስት ፍየሎችና ከብዙ ጎረቤቶቻችን ጋር ሊጋጭ ምንም አልቀረውም ነበር፤ ግን ልክ በሰዓቱ ደረሰ። ሐኪሙ እናቴ በደረሰችበት ሰዓት ሐኪም ቤት ባትደርስ ሟች ነበረች ብሎ ነበር።

ዳማሲንን ያገኘው ሁሉ ይወደዋል - ማራኪ ፈገግታውና ተግባቢ ስብዕናው ከያዙ አይለቁም። ተጫዋች ቢሆንም በትምህርት ቤቱ በቋሚነት ጥሩ ደረጃ ከሚይዙ ተማሪዎች ተርታ የሚሰለፍ ነበዝ ተማሪ ነበር። በዚሁም በመቀጠል በመላው ከፍለ ሀገራችን የማስተርስ ዲግሪ በማግኘት በዕድሜ ትንሹ ለመሆን ችሏል። ያለማቋረጥ የሚያጠና ቢሆንም በካራቴ ቡናማ ቀበቶ ለማግኘት፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቱና የዩኒቨርሲቲው የቅርጫት ኳስ ቡድኖች አምበል ለመሆን፣ ብሎም ቤተክርስቲያናችንን ለማገልገል ጊዜውን አብቃቅቷል። ቤታችንን ለቆ ወደ አዳሪ ትምህርት ቤት ሲሄድብኝ ለሳምንት ስላለቀስኩ ዳግመኛ የማልስቅ ያህል ተሰምቶኝ ነበር።

ዳማሲን የሕይወቴ ብርሃን ነበር።

የቤተሰቡ ሕጻን፣ ትንሹ ወንድሜ ቪያኒ ሲሆን የተወለደው ከኔ ሦስት ዓመት ዘግይቶ ነበር። እንደኔ አስተያየት ቪያኒ የባቄላ አበባ መሳይ ዓይን፣ እርጋታና የሰው መውደድ ያለው፤ ግን ሁሉም ታናሽ ወንድሞች እንደሆኑት ሁሉ አስቸጋሪ ነው። አድጎ ቆንጆ፣ ግዙፍና በቁመት ከኔም በላይ ቢሆንም በኔ ዓይን ቪያኒ ሁልጊዜ ሕፃን ወንድሜ ነው። እሱን መጠበቅ ኃላፊነቴ መሆኑን ማሰቤን አቁሜ አላውቅም። እንደ ቡችላ በየሄድኩበት የሚከተለኝ ውድ ልጅ ነው። ቋሚ ጓደኝነቱን በጣም ተላምጄው ካጠገቤ ሆኖ ካላስቸገረኝ ይናፍቀኛል።

እኔ ሦስተኛዋና ብቸኛዋ ሴት ልጅ ነኝ። ወንድ የበላይ በሆነበት ማኅበረሰባችን ውስጥ ብቸኛዋ ሴት ልጅ መሆኔ ተጨማሪ ግፊት አሳድሮብኛል። በሩዋንዳ ባህል «ጥሩ ስም» ይዞ መገኘት ወሳኝ ነገር ነው። በመሆኑም ወላጆቼ ብቸኛዋ ሴት ልጃቸው እንከን - የለሽ ስም ይዛ እንድታድግ ይጥሩ ነበር። ከወንድሞቼ ይልቅ በኔ ላይ ጥብቅ ቁጥጥር ነበረብኝ - ብዙ የቤት ሥራ በመስጠት፣ በጣም ጥብቅ የሰዓት እላፊ በመጣል፣ ልብሴን በመምረጥ፣ ጓደኞቼን በማጽደቅና አይሆኑሽም በማለት ወላጆቼ ተቆጣጥረውኛል። በትምህርት እንዲሳካልኝና አእምሮዬም እንዲነለብት ይገፋፉኝ የነበረ ቢሆንም ቅሉ በጣም ወግ አጥባቂ በነበረው ማኅበረሰባችን ውስጥ እንደምትኖር እንደማንኛዋም ወጣት ሴት እንድታይ እንጂ እንድሰማ አይጠበቅብኝም ነበር።

እኔ የቤተሰባችንን ታሪክ እነግር ዘንድ መትረፌ ታዲያ ምንኛ ይገርም!

ምዕራፍ 2

ከመቀመጫችን ሲያስነሡን

‹‹ቱትሲዎች ከመቀመጫችሁ ተነሡ!››

አንድ ቀን አራተኛ ክፍል ሆኜ እማርበት በነበረው መማሪያ ክፍል ውስጥ ስድስት ልጆች ከመቀመጫቸው ተስፈንጥረው ሲቆሙ ግማሽ ደርዘን ወንበሮች ወደ ኋላ ተንጓጉ። ከዚያ በፊት ሁልጊዜ እናቴ በምታስተምርበት አነስተኛ ትምህርት ቤት ውስጥ እማር ስለነበር ምን እየተከሰተ እንደነበር ልገምት አልቻልኩም። በዚያን ወቅት አሥር አመቴ ስለነበርና ትንሽ አደግ ላሉ ልጆች የሚሆን ትምህርት ቤት ውስጥ ስማር የመጀመሪያ ቀኔ በመሆኑ የልጆቹ መራበሽ ግራ አጋብቶኛል። ከዚያ በፊት አስተማሪ የዘውግ ጥሪ ሲያካሂድ በፍጹም አይቼ አላውቅም።

‹‹ቱትሲዎች *ብሙሉ* ከመቀመጫችሁ ተነሡ!›› መምህራችን፣ ቡሆሮ፣ አምባረቀ። በትልቅ እርሳስ ከዝርዝሩ ላይ ከተማሪዎች ስም አጠገብ ምልክት እያደረገ ነበር። ከዚያም አቆመና በቀጥታ እኔ ላይ አፈጠጠ።

‹‹ኢማኪዩሌ፣ ሁቱ ስል አልተነሣሽም፤ ትዋ ስል አልተነሣሽም፤ አሁንም ቱትሲ ብል ልትነሺ አልቻልሽም። ለምንድነው?›› ቡሆሮ ፈገግ እያለ ቢሆንም ድምጹ ግን ከፋቱን ያሳብቅበታል።

‹‹አላውቅም መምህር።››

‹‹ምን ዘውግ ነሽ?››

‹‹የት አውቃለሁ፣ መምህር?››

‹‹ሁቱ ነሽ ቱትሲ?››

‹‹እኔ - እኔ አላውቅም።››

‹‹ካላወቅሽ ውጪያ! ከዚህ ክፍል ውጪ፤ እና ምን እንደሆንሽ ሳታውቂ ተመልሰሽ አትምጪ!››

መጻሕፍቴን ሰበሰብኩና በሃፍረት አንገቴን ደፍቼ ክፍሉን ለቅቄ ወጣሁ። ገና ያልታወቀኝ ቢሆንም በሩዋንዳ የዘውግ ክፍፍል ላይ የመጀመሪያዋን ትምህርቴን ተማርኩ፤ ይህም ክው ነበር ያደረገኝ።

ወደ ትምህርት ቤቱ ጓሮ ሮጬ ወንድሜ ዳማሲን የዕለቱን ትምህርት እስኪጨርስ ድረስ ከቁጥቋጦ ጀርባ ተደብቄ መጠበቅ ጀመርኩ። እንባዬን ማቆም ተስኖኝ ሰማያዊ የትምህርት ቤት የደንብ ልብሴ እስኪረጥብ ድረስ ነፈረቅሁ። ምን እንደተከሰተ ስላልገባኝ ወደ ከፍል ሄጄ የቅርብ ጓደኛዬን ጣኔትን ጉዳዩን ታብራራልኝ ዘንድ ለመጠየቅ በጣም ፈለግሁ። መምህሩ ሁቱ የሚለውን ስም ሲጠራ ተነሥታለች - ምን አልባትም መምህሩ ለምን እንዳመናጨቀኝ ታውቅ ይሆናል። በቁጥቋጦው ውስጥ ተኮራምቼ ዳማሲን እዚያ እስኪያገኘኝ ድረስ እንባዬን ሳዘራ ቆየሁ።

«ማን መታሽ ኢማኪዩሌ?» ሲል ታላቅ ወንድሜ ባለችው የ13 ዓመት ሥልጣን ጠየቀኝ። አለኝታዬ ዳማሲን አንድ ሰው ጫፌን ከነካኝ ለመፋለም የተዘጋጀ ልጅ ነው። ቡሆሮ ያለኝን ነገርኩት።

«ቡሆሮ ጥሩ ሰው አይደለም» አለ ወንድሜ። «ቢሆንም አትጨነቂለት። ሌላ ቀን ስም ሲጠራ እኔ የማደርገውን አድርጊ፤ ከጓደኞችሽ ጋር ተነሺ። ጓደኛሽ ጣኔት ስትነሳ ተነሺ።»

«ጣኔት ሁቱ ብሎ ሲጠራ ነበር የተነሣችው።»

«በቃ እንደዚያ ከሆነ ሁቱ ሲሉ ተነሺ። ጓደኞቻችን የሆኑት ያንን ከሆነ መቼም እኛም የምንሆነው እንደዚያው መሆን አለበት። ሁላችንም አንድ ሕዝብ ነን፣ አይደል?»

በዚያን ወቅት የማውቅበት መንገድ አልነበረኝም፤ ዳማሲንም እንደኔው በሩዋንዳ ስለነበረው ዘውግኝነት ግንዛቤ አልነበረውም... ይህም በአካባቢው በጥሩ ሁኔታ ይማሩ ከነበሩት ልጆች ውስጥ ከመመደባቸን አንጻር እንግዳ ነገር ነው። በየዕለቱ ከትምህርት መልስ ወንድሞቼና እኔ ወደ ቤታችን በእናታችን ተቆጣጣሪነት የቤት ሥራችንን እንድንሠራ ከመጠራታችን በፊት የ90 ደቂቃ የእረፍት ጊዜ ነበረን። አባታችን ከራት በፊት የትምህርት ቤታችንን ሰሌዳዎች የምታከል ጥቁር ሰሌዳ በቤታችን መካከል አድርጎ ከአንድ ሰዓት ለሚበልጥ ጊዜ ያስጠናናል። የሒሳብ፣ ሰዋስውና መልክዓ-ምድር ጥናት ጠመኔ እየሰጠ ያለማምደናል።

ይሁን እንጂ ወላጆቻችን ስለራሳችን ታሪክ አላስተማሩንም። ሩዋንዳ የሦስት ዘውጎች፣ ማለትም የሚበዛው ሁቱ፣ አናሳ ቱትሲዎችና በጣም ትንሽ ቁጥር ያላቸው በጫካ ውስጥ የሚኖሩት ትዋዎች ስብስብ እንደሆነች አላስገነዘቡንም። የጀርመን ቅኝ ገዥዎችና ከእነርሱ በኋላ የመጡት ቤልጅየሞች የሩዋንዳን ነባር ማኅበራዊ አወቃቀር ማለትም ሩዋንዳን ለምዕተ-ዓመታት ሰላምና ስምምነት የሰጣት ቱትሲ ንጉሥ የሚመሩትን ዘውዳዊውን ሥርዓት በአግላይ ዘውግ-ተኮር የመደብ ሥርዓት ቀይረውት እንደነበር አልተማርንም። ቤልጅየማውያኑ የቱትሲውን ገዥ መደብ ደግፈውና በመሪነት ደረጃ ያለውን አስተዋፅኦም ተቀብለው፣ አገሪቱን በተሻለ መንገድ

ለማስተዳደርና ለቤልጅየማውያኑ ከፍተኛ ትርፍ ለማስገኘት ያግዝ ዘንድ ቱትሲዎች የተሻለ ትምህርት እንዲያገኙ አድርገዋል፡፡ ቤልጅየሞች በሁቱና ቱትሲ መካከል ፈጥረውት የነበረውን ክፍተት በማባባስ ሁለቱን ዘውጎች በቀላሉ ለመለየት የዘውግ መታወቂያ ደብተር አስተዋውቀዋል፡፡ እነዚያ የማይረቡ ስህተቶችም በሁቱዎች ዘንድ ዘላቂ ቁጭት በመፍጠር ለዘር ጭፍጨፋ መሠረት ለመጣል አገዙ፡፡

ቱትሲዎች የተሻለ ነጻነት በጠየቁ ጊዜ ቤልጅየማውያኑ በጠላትነት አዩአቸው፡፡ በ1959 ደም-አፋሳሽ የሁቱ አመፅን ደግፈው ዘውዳዊው ሥርዓት እንዲገረሰስ አደረጉ፡፡ ከ100 000 በላይ ቱትሲዎች በበቀል በቀጣዮቹ ጥቂት ዓመታት ውስጥ ተገደሉ፡፡ በ1962 ቤልጅዬም ከሩዋንዳ ለቃ ስትወጣ የሁቱ መንግሥት አንቀጥቅጦ በመግዛት ላይ ሲሆን ቱትሲዎችም በሁቱ አክራሪዎች ማሳደድ፣ ሽብርና ግድያ የሚፈጸምባቸው ሁለተኛ ዜጎች ለመሆን በቁ፡፡ በብዙ አሥር ሺህዎች የሚቆጠሩ ቱትሲዎች ግድያዎች የዕለት ከዕለት ከስተት በነበሩባቸው አሥርት ዓመታት ውስጥ ሞቱ፡፡ የሽብር ዑደቱ ተጧጡፎ መድሎ መፈጸሙ ቀጠለ፡፡ የሁቱው መንግሥት ከቤልጅየሞች የአገዛዝ ዘመናት የወሰደው የዘውግ መታወቂያ ደብተር አሠራር መድሎውን የበለጠ ይፋና ቀላል አደረገው፡፡

ወላጆቻችን እኔና ወንድሞቼ ቢያንስ በልጅነታችን እንዳንማራቸው ያልፈለጓቸው የታሪክ ትምህርቶች እነዚህ ነበሩ፡፡ ስለ መድሎም ሆነ ስለ ግድያ ዘመቻዎቹ፣ ስለ ዘር ማጽዳቱም ሆነ የዘር መታወቂያ ካርዶቹ አላወሩንም - እነዚህ ነገሮች ፈጽሞ የልጅነቴ አካል አልነበሩም፡፡

ዘርን፣ ሃይማኖትን ወይንም ዘውግን ከግምት ውስጥ ሳናስገባ በቤታችን ማንንም ሰው በደስታ እንቀበላለን፡፡ ወላጆቼ የእርስዎን ሁቱ ወይንም ቱትሲ መሆን ከስብዕናዎ ጋር አያገናኙትም፡፡ ጥሩ ጸባይ ካለዎትና ገራገር ከሆኑ እጆቻቸውን ዘርግተው ሰላምታ ያቀርቡልዎታል፡፡ ወላጆቼ ራሳቸው ግን በሁቱ ጽንፈኞች የደረሱባቸው የተወሰኑ አሰቃቂ ችግሮች ነበሩ ... እንዲያውም አንደኛውን ትንሽ ትንሽ አስታውሳለሁ፡፡

ያኔ የሦስት ዓመት ልጅ ነኝ፡፡ ነፍስ ባለማወቄ ምን እየተከሰተ እንደነበር አልገባኝም፡፡ የምሽቱን ሰማይ እሳት ሲንቦገቦግበት፣ እናቴም በእጆቿ ጥብቅ አድርጋ ታቅፋኝ ከቤታችን ስትሮጥ ይታወሰኛል፡፡ ይህ የሆነው ብዙ ቱትሲዎች በተሳደዱበት፣ ከቤቶቻቸው በተነዱበትና በየመንገዱ በተገደሉበት የ1973ቱ መፈንቅለ-መንግሥት ወቅት መሆኑ ነው፡፡ በኛ ክፍለሀገር ሁቱ ጽንፈኞች የቱትሲዎችን ቤቶች በየተራ ኢቃጥለዋል፡፡ እሳቱ ወደኛ ሽቅብ ሲገሰግስ መላው ቤተሰቤ አብሮ ቆሞ ወደ ኪቩ ሐይቅ ቁልቁል በማስተዋል ላይ ነበረ፡፡ ሩታካሚዜ ወደተባለው ጥሩ ሁቱ ወዳጅ ጎረቤታችን ቤት ሸሸን፡፡ እርሱም ግድያዎቹና ቃጠሎው እስኪያቆሙ ድረስ ሸሸገን፡፡ ወደ ቤታችን ስንመለስ የሚጫጫስ ፍርሥራሽ ብቻ አገኘን፡፡

እናትና አባቴ ቤታቸውን መልሰው ሰሩት። የተከሰተውንም ነገር ቢያንስ ከኛ ከልጆች ጋር ፈጽመው ተወያይተውበት አያውቁም። ምንም እንኳን ወላጆቼ በ1959 በተመሳሳይ ጸረ-ቱትሲ ረብሻዎች ሂላማ የነበሩ ቢሆንም ሁቱዎችን የሚያጥላላ አንዳች ቃል ሲናገሩ ሰምቻቸው አላውቅም። በፍጹም የመሠረተ-ቢስ ጥላቻ ተጠቂዎች አልነበሩም። ይልቁንም ከዘውግም ሆነ ዘር ይልቅ ርኩስ መንፈስ ሰዎችን ክፉ ነገር እንዲያደርጉ አነሳስቷቸዋል ብለው ያምናሉ። እናቴና አባቴ ይኖሩበት የነበረውን ማኅበራዊና አስተዳደራዊ እውነታ ቸል ብለው ይልቁንም ሁሉም እኩል ነው እያሉ ያስገነዝባሉ። ልጆቻቸውን ቱትሲ ሆነው ስለተወለዱ የሌለ የበታችነት ስሜት እየተሰማቸው እንዲያድጉ አልፈለጉም።

ስለዚህ መምህሬ ቡሆሮ ዘውጌን ባለማወቄ ሲያበሻቅጠኝ ለምን ግራ እንደገባኝ መገንዘብ አይከብድም።

ዳማሲን የዚያን ቀን እጁን በትከሻዬ ጣል አድርጎ አቅፎኝ ወደ ቤት ወሰደኝ። ሁለታችንም አንድ አጉል ነገር እንደገጠመን ገብቶናል፤ ምንነቱን ግን አላወቅነውም። በዚያን ምሽት ራት ላይ ለአባቴ የተከሰተውን ነገር ነገርኩት። ጸጥ ብሎ ቆየና ከመማሪያ ክፍል ውጪ ከተባልኩ በኋላ ለምን ያህል ጊዜ በጥሻ ውስጥ ተቀምጬ ሳለቅስ እንደቆየሁ ጠየቀኝ።

«ሙሉ ቀን ሊሆን ምንም አልቀረው አባባ።»

አባቴ ሹካውን አስቀምጦ መብላቱን አቆመ - ይህም እንደተናደደ የሚያሳይ እርግጠኛ ምልክት ነው። «ቡሆሮን ነገ አናግረዋለሁ» አለኝ።

«ግን አባባ፣ ምን ዘውግ ነኝ?»

«አይ! አሁን ስለዚያ አትጨነቂ። እሱን ነገ አስተማሪሽን ካነጋገርኩት በኋላ ልንወያይበት እንችላለን።»

ምን ዘውግ እንደሆንኩ በዚያኑ ሰዓት ለምን እንደማይነግረኝ ለመጠየቅ ፈለግሁ፤ ሆኖም ግን በቤታችን አዋቂዎችን እንጠይቅ ዘንድ አይፈለግም። አባቴ እውነታውንም ለመደበቅ ፈልጎ ከሆነ ጥሩ ምክንያት እንደነበረው ገመትኩ። ቢሆንም ግን ተጨነቅሁ - ሁሉም የቤተሰቤ አባላት ስለ ዘውግ ሲያወሩ ለምን በጣም እንደተበሳጩ ሊገባኝ አልቻለም!

አባቴ በሚቀጥለው ቀን መምህሬን ቢያናግረውም ስለምን እንደተወያዩና ዘውጌም ምን እንደነበር ባለፈው ቀን እነግርሻለሁ ባለው መሠረት አልነገረኝም። እስከቀጣዩ ሳምንት፣ ማለትም ቡሆሮ በድጋሚ ስም ጥሪ እስኪያካሂድ ድረስ፣ የዚያን

ጉዳይ መልስ አላገኘሁም። መቼም አባቴ ሳያሸማቅቀው አልቀረም፤ ከስም ጥሪ በፊት ወደሚቀመጥበት ወንበር ጠርቶ እጅግ በለሰለሰ ድምፅ አናገረኝ።

«ኢማኪዩሌ፣ ‹ቱትሲ› ስል ተነሺ።»

ወደ መቀመጫዬ ተመልሼ ስሄድ በልቤ *በቃ ቱትሲ ነኝ ማለት ነው* ብዬ ፈገግ አልኩ - *ኦሰይ!* ብዬ በማሰብ። ቱትሲ ምን እንደሆነ ምንም የማውቀው ነገር አልነበረኝም። ከፋም ለማም አንዱን ነራ በመቀላቀሌ ኮራሁ።

በክፍሉ የተወሰን ቱትሲዎች ብቻ ስላለን የተለየን እንደሆን አሰብኩ - በዚያም ላይ ‹ቱትሲ› ስሙ ያምርና ሲሉትም ደስ ያሰኝ ነበር። ከዚያም በኋላ ግን በቱትሲና ሁቱ ዘውጎች መካከል ይህ ነው የሚባል ልዩነት ማየት አልቻልኩም። ትዋዎች አካላቸው አነስተኛ በመሆኑ ለመለየት አያዳግቱም። አንድም ትዋ ግን ትምህርት ቤት ስለማይመጣ በሕይወቴ ያየኋቸው በጣም የተወሰኑ ናቸው።

በሁቱዎችና ቱትሲዎች መካከል ያሉት ልዩነቶች ለመለየት የሚከብዱ ናቸው። ቱትሲዎች ረዘም፣ መልካቸው ፈካ ያለና ሰልከክ፣ ጠበብ ያለ አፍንጫ ያላቸው ናቸው ተብሎ ይታመናል። ሁቱዎች ደግሞ አጠር፣ ጠቆር ያሉና አፍንጫቸው ሰፋ ያለ ተደርገው ይታሰባሉ። ሆኖም ግን ያ ፈጽሞ እውነት አልነበረም፤ ምክንያቱም ሁቱዎችና ቱትሲዎች እርስ በእርሳቸው ለምዕተ-ዓመታት ሲጋቡ ስለኖሩ የዘረመል መለያዎቻችን ተቀላቅለዋል። ሁቱዎችና ቱትሲዎች ኪንያሩዋንዳ የሚባል ቋንቋ ይናገራሉ። ተመሳሳይ ታሪክም ይጋራሉ። ከሞላ ጎደል አንድ ባህል ነበረን - አንድ ዓይነት መዝሙሮችን የምንዘምር፣ አንድ ዓይነት መሬት ላይ የምንኖር፣ አንድ ዓይነት የእምነት ሥፍራዎችን የምንሳለምና አንድ አምላክ የምናመልክ ነበርን። ኑሯችንም በተመሳሳይ መንደሮች፣ መንገዶችና አብዛኛውን ጊዜም በአንድ ዓይነት ቤቶች ጭምር ነበር።

በልጅ ዓይኔ (ወይም ቢያንስ *በዚ ዓይን*) ሳየው ሁላችንም አብረን መኖር የምንችል እንመስል ነበር። ሁቱዋ ጓደኛዬ ጣኔትና እኔ በእያንዳንዳችን ቤቶች ራት የበላንባቸውን ጊዜያት ቆጥሬ አልጨርሳቸውም። በልጅነቴ በሩዋንዳ የተለያዩ ዘውጎች መኖራቸውን ትዝ የሚያስብለኝ ነገር ቢኖር በመማሪያ ክፍል በሳምንት አንድ ጊዜ ለዘውግ ጥሪው መነሳቴ ብቻ ነው። የሚያበሳጭ ነገር! ሆኖም ግን ያኔ የመድሎውን ትርጉም ገና ስላላወቅሁ ብዙ አላስጨነቀኝም።

ያም የሆነው ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መግባት እስከፈለግሁበት ጊዜ ነው።

አሥራ አምስት ዓመት ዕድሜዬ በነበረ ጊዜ ስምንተኛ ክፍልን ስድሳ ተማሪዎች በነበሩበት ክፍሌ ሁለተኛ በመውጣት ጨረስኩ። 94 በመቶ አማካይ ውጤት

አግኝቼ፣ አንደኛ ከወጣው ቱትሲ ተማሪ በሁለት ነጥብ ብቻ ዝቅ ብዬና ከሌሎችም ተማሪዎች በጣም በልጬ ነበር። በክፍለ ሀገሩ ከነበሩት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአንዱ ቦታና ነጻ የትምህርት ዕድልም ለማግኘት ከበቂ በላይ የሆነ ነጥብ ነው። በትምህርት ዓመቱ መጨረሻም ስለ አዲሱ የትምህርት ቤት የደንብ ልብሴ በማለምና ከቤተሰብ ርቆ ሁሉም ትምህርቶች በፈረንሳይኛ በሚሰጥበት ጥሩ ትምህርት ቤት መማር ምን እንደሚመስል በማሰብ እየጓጓሁ ወደ ቤቴ ሄድኩ።

ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴም በኋላ ወደ ዩኒቨርሲቲ ለመግባት አቀድኩ፤ ከዚያ በኋላ ማን ያውቃል? አየር አብራሪ፣ የዩኒቨርሲቲ መምህርት፣ ወይንም የሥነ ልቦና ባለሙያ ልሆን እችላለሁ (በነገራችን ላይ በልጅነቴ መነኩሲት ለመሆን የነበረኝን ሐሳብ እርግፍ አድርጌ ትቼዋለሁ)። ወላጆቼ ጠንክሮ በመሥራትና በቁርጠኝነት ከማታባ ዓይነቷ ትንሽ መንደርም አንዲት ትንሽ ሴት ልጅ ትልቅ ሰው መሆን እንደምትችል አስተምረውኛል።

ይህን በመመኘቴ ግብዝ ልጅ እንደሚያስብለኝ እንዴት ላውቅ እችላለሁ? እነዚያ ሳምንታዊ ዘውጋዊ የስም ጥሪዎች መጥፎ ዓላማ እንዳላቸው መች ጠርጥሬ! ያም መጥፎ ዓላማቸው ቱትሲ ሕፃናትን «ዘውጋዊ ምጣኔ» የተባለ የግዙፍ መድሎ ዕቅድ አካል ማድረግ ኖሯል።

በ1973ቱ መፈንቅለ-መንግሥት ሥልጣን የጨበጡት ሁቱው ርዕሰ-ብሔር ዣቨናል ሃብያሪማና የሚያስተባብሩት ይህ ዕቅድ መንግሥቱ የሀገሪቱን የዘውግ ስብጥር ለማንጸባረቅ የትምህርት ዕድል አሰጣጡንና ጥሩ የመንግሥት ሥራ ምደባን «ማመጣጠን» አለበት ተብሎ የታወጀበት ነው። የሩዋንዳ ሕዝብ 85 በመቶ ገደማ ሁቱ፣ 14 በመቶ ቱትሲና አንድ በመቶ ትዋ ስለነበር አብዛኞቹ ሥራዎችና የትምህርት ዕድሎችም ለሁቱዎች ተሰጡ። በዕቅዱ ትግበራ በትክክል የተደረገው ቱትሲዎችን ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት፣ ከዩኒቨርሲቲና ጥሩ ደምወዝና ጥቅማጥቅም ከሚገኝባቸው ሥራዎች ማራቅ ሲሆን ይህም ሁለተኛ ዜጎች ሆነው መቅረታቸውን አረጋግጧል።

የዘውግ ምጣኔው እውነተኛ ትርጉም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን ከመጀመሬ ከጥቂት ሳምንታት በፊት ተገለጠልኝ። ቤተሰቤ ለራት በተሰበሰበበት ሰዓት አንድ ጎረቤታችን መጥቶ ስሜ በመንደራችን አዳራሽ ጋር በተለጠፈው የትምህርት ዕድል ያገኙ ልጆች ስም ዝርዝር ውስጥ አለመካተቱን አረዳን። ከፍተኛ ውጤት ባስመዘግብም ቱትሲ በመሆኔ ተዘልያለሁ - ሁሉም የነበሩት ቦታዎች ከኔ በጣም ያነሰ ውጤት ላገኙት ሁቱዎች ተሰጥተዋል። አንደኛ ወጥቶ የነበረው ቱትሲው ልጅም በዘውጉ ምክንያትነት ብቻ እድሉ ተጨናግፏል።

አባቴ ወንበሩን ከጠረጴዛው ራቅ አድርጎ ወሰደና ዓይኖቹን በታይል ጨፍኖ ለረጅም ጊዜ ተቀመጠ - በሐሳብ ባሕር ውስጥ የሰጠመ መሰለኝ - አድርጎ

የማያውቀውን ነገር:: ወላጆቼ ከመንግሥት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አሥር እጥፍ ክፍያው በሚወደደው የግል ትምህርት ቤት እኔን ለማስተማር አቅሙ እንደማይኖራቸው አውቃለሁ:: ሁለቱም ታላላቅ ወንድሞቼ ሌላ ቦታ በትምህርት ላይ ስለነበሩ ገንዘብ ይቸግረናል:: በዚያም ላይ በሩዋንዳ የነበሩ የግል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መንግሥት ወጪያቸውን ከሚሸፍንላቸው የመንግሥት ትምህርት ቤቶች አንጻር በአሳሳቢ ሁኔታ ላይ ነበሩ:: መምህራኑም ቢሆኑ ጥሩ የትምህርት ዝግጅት ያልነበራቸው፣ ሥርዓተ-ትምህርቱ እዚህ ግባ የማይባል፣ ብሎም ሕንጻዎቹ አስቀያሚና ለመማር የማይጋብዙ ነበሩ::

«አትጨነቂ ኢማኪዩሌ:: የምትማሪበትን ሌላ መንገድ እንፈልጋለን» በማለት አባቴ መጨረሻ ላይ ውሳኔውን አሳውቆኝ ስለ ገበታው ይቅርታ በመጠየቅ ምግቡን እንኳን ሳይጨርስ ወደ ማንበቢያ ክፍሉ ሄደ::

«ተስፋ አትቁረጪ» ብላ እናቴም አቀፈችኝ:: «ሁላችንም በዚህ ጉዳይ ላይ እንጸልይበታለን:: አሁን ራትሽን ብዪ::»

ከእራት በኋላ የአባቴን የግል ክፍል ዘግቼ ተቀምጬ እያለቀስኩ በትምህርት ቤት ልቤ እስኪጠፋ ያጠናሁትና የለፋሁት የከፍተኛ ትምህርት ሕልሜ እንዲህ ሊከስም ኖሯል? ስል አስብኩ:: የወደፊት ዕጣ-ፈንታዬ ምን እንደሚሆን ሳስበው አንቀጠቀጠኝ:: በማኅበረሰቤ ምንም ያልተማሩ ሴቶች እንዴት እንደሚያዙ አይቻለሁ:: ምንም ዓይነት ሙበት፣ ተስፋ ወይም ክብር አልነበራቸውም:: ቢያንስ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን ካልተማርኩ አንድ ወንድ ወደ ቤታቸን መጥቶ በሚስትነት እስኪወስደኝ ከመጠበቅ በስተቀር ምንም አማራጭ አይኖረኝም:: ገና በአሥራአምስት ዓመቴ የወደፊት ሕይወቴ ተስፋ የማይታይበት መሰለኝ::

በማግስቱ ጠዋት አባቴ በቁርስ ገበታችን ላይ አልተገኘም::

«ትንሽ ተአምር ለመሥራት እየሞከረ ነው» በማለት እናቴ አስረዳችኝ:: «አንዳንድ የግል ትምህርት ቤቶችን ያስገቡሽ እንደሆነ ለመጠየቅ ሄዷል::»

«እማማ፣ ግን እኮ በጣም ውድ ነው፤ አንችልም እኮ - »

«እሸሽ» አለችና አቋረጠችኝ:: «ተስፋ እንዳትቆርጭ ነግሬሻለሁ እኮ፣ አይደል?»

በኋላ ነገሩ ሲገባኝ አባቴ ማልዶ ከቤት የወጣው እኔን ወደ ግል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለማስገባት የሚያስፈልገውን ገንዘብ ለማግኘት ሁለቱን ላሞቻችንን ለመሸጥ ኖሯል:: በሩዋንዳ ባህል ላሞች የማኅበራዊ ደረጃ መገለጫዎችና በጣም ዋጋ የሚሰጣቸው ንብረቶች ስለነበሩ አንድ ላም እንኳን መሸጥ አባካኝነት ሲሆን ሁለት መሸጥ ደግሞ በገንዘብ ረገድ ውድቀትን ያስከትላል:: አባቴ ግን ከትምህርት ገበታዬ መለየት እንደሌለብኝ ቆርጧል:: ከላሞቹ ሽያጭ ያገኘውን ገንዘብ ይዞ፣ በስተደቡብ

ሦስት ሰዓት በተሸከርካሪው አዲስ ወደተከፈተው የግል ትምህርት ቤት ሄዶ የመጀመሪያ ዓመት የትምህርት ክፍያዬን በጥሬ ገንዘብ ከፈለልኝ፡፡ በሰው ፊት ስሜቱን በግልጽ ማሳየት ለአባቴ የሚያዳግተው ቢሆንም ለእኔ የነበረውን ፍቅር መደበቅ ግን አይሆንለትም፡፡

ከተወሰኑ ሳምንታት በኋላ ተጠናቅቄ ለመሄድ ተዘጋጀሁ፡፡ ጥሄት አቅፋ ተሰናበተችኝ፤ ተላቅሰን ብዙ ደብዳቤ ለመጻጻፍ ቃል ተገባባን፡፡ እናቴ እንባዋን እየተቆጣጠረች ደጋግማ ሳመችኝ፡፡ በቤታችን ካለነው ልጆች ትንሹ፣ ቪያኒ፣ ወደግል ክፍሉ ሄዶ መሰናበት አለመፈለጉን አሳየ፡፡ እኔና አባቴ በተሸከርካሪያችን ስንሄድ ብዙ ጎረቤቶቻችን ሊሰናበቱን ወጡ፡፡ ማታባን ለቅቄ ስሄድ የመለየት ሥቃይ ቢሰማኝም አዲሱን ሕይወቴን ለመጀመር ግን ጓጓሁ፡፡

አዲሱ ትምህርት ቤቴ ያን ያህል የሚወደድ አልነበረም፡፡ ጠባቡ መኝታ ክፍላችን ወለሉ ሊሾ ቢሆንም ከአሸዋ፣ ስሚንቶና ድንጋይ ከሰል ድቃቂ የተሠራው ጣውላ መሰል የግድግዳው ልባጥ ቀለም ቀቡኝ ቀቡኝ ይል ነበር፡፡ በጣም ተቀራርበው በተደረደሩና የክፍሉን ወለል ሙሉ በሙሉ በሸፈኑ ፍራሾች ላይ ከሌሎች አሥር ሴት ልጆች ጋር እተኛለሁ፡፡ የቧንቧ ውሃ ስለሌለ በየማለዳው ባልዲ እየያዝን ወደ አቅራቢያችን ምንጭ ሄደን ለማጠቢያና ምግብ ማሰናጃ የሚሆነን ውሃ እንቀዳለን፡፡ በቤቴ የነበረኝ አልጋ፣ የእናቴ ሩዝና ፎሶሊያ ናፈቁኝ፡፡

ይሁን እንጂ በማይስማማኝ ሁኔታ ለዚያች አጭር ጊዜ እንኳን መኖር ከባድ ቢሆንብኝም ትምህርቴን አቋርጬ ቤተሰቦቼ ወደ ቤቴ መልሰው እንዲወስዱኝ ለመጠየቅ ግን አልፈለኩም፡፡ በእርግጥም ለትምህርት ዓመቱ የሚሆኑንን የትምህርት ዓይነቶች የምንመርጥበት ጊዜ ሲደርስ በጣም አስቸጋሪዎቹን ትምህርቶች፣ ሒሳብንና ፊዚክስን፣ መረጥኩ፡፡ አባትና እናቴን ማስደሰት ብቻ ሳይሆን በወንድሞቼም ላይ ነጥብ ማስቆጠር ፈልጌያለሁ፡፡ እንደማናቸውም ሩዋንዳውያን ወንዶች ሁሉ፣ ሴቶች ኩሽና እንጂ መማሪያ ክፍል መገኘት እንደማይገባቸው በመናገር ይሳለቁብኝ ነበር፡፡ ይሁና! አሳያቸዋለሁ!

ከሁለት ዓመታት በኋላ በትምህርት ቤቱ ካሉት ከፍተኛ ነጥብ ያስመዘገቡ ተማሪዎች ውስጥ አንዷ ሆንኩ፡፡ መንግሥት ከፍተኛ ነጥብ ላላቸውና በመንግሥት ትምህርት ቤቶች መግባት ለሚፈልጉ ተማሪዎች ልዩ ፈተና እንደሚፈትን ሲያስታውቅም ለመፈተን ወሰንኩ፡፡ በሀገሪቱ ከፍተኛውን ውጤት ባመጣም እንኳን ዋጋ እንደሌለውና ቱትሲ በመሆኔ አሁንም እንደምዘለል ተሰማኝ፡፡ ቢሆንም ግን በትጋት አጠናሁ። ፈተናውንም እጅግ በሚያረካኝ መልኩ እንደሠራሁት እርግጠኛ

ሆንኩ፡፡ ይሁን እንጂ ምንም ወሬ ሳይሰማ ሳምንታት አለፉ፤ ስለሆነም ጉዳዩን ከአእምሮዬ አወጣሁት፡፡

ከወራት በኋላ ለክረምት ረፍት እቤቴ ሳለሁ ዳማሲን ቁና ቁና እየተነፈሰ እቤት ይመጣና «ኢማኪዩሌ! ኢማኪዩሌ ኢሊባጊዛ! የሥም ዝርዝሩን አየሁት፤ ፈተናውን አልፈሻል! በሊሴ ደ ኖትረ ደ አፍሪክ ተቀብለውሻል፡፡ በሩዋንዳ ካሉት ምርጥ ትምህርት ቤቶች አንዱ ሲሆን፤ ወደ ትምህርት ቤቱ የሚወስደው መንገድም የሚያልፈው በኔ ትምህርት ቤት አጠገብ ነው!»

በወቅቱ የቤተሰባችን አባላት በሙሉ በዋናው ቤት ስለነበሩ ሁሉም በደስታ አበዱ፡፡ ከመቀመጫዬ ዘልዬ «ተመስገን እግዚአብሔር፤ ተመስገን ጌታዬ!» በማለት ጮኬ እያማተብኩ ቤት ውስጥ በአሸናፊነት ጨፈርኩ፡፡ የእናቴ ዓይኖች እንባ አቀረሩ፤ አባቴ በበኩሉ «ይህ በሕይወቴ ሁሉ ወደር የማይገኝለት ደስታዬ ነው! ላለፉት ሁለት ዓመታት በየቀኑ እየተንበረከክሁ እዚያ ትምህርት ቤት ትገቢልኝ ዘንድ ጸልያለሁ፡፡ ይሽዋ! አምላክ ለልመናዬ መልስ ሰጠኮ!»

«ምንም እንኳን ሴት ብትሆኚ እኮ ጎበዝ ሳትሆኚ አትቀሪም» እያለ ኤይማብል ቢስቅም በደስታዬ እንደተደሰተልኝ ይታየኛል፡፡

ዳማሲን ቆንጆ ፈገግታውን እያሳየና በኩራት ተሞልቶ ስለነበር የሚፈነዳ መሰለኝ፡፡

ያን ምሽት የቤተሰብ ድግስ ደግሰን በደስታ አሳለፍን፡፡ ለረጅም ጊዜ ካሳለፍናቸው ደስታ የተሞላባቸው ጊዜያት መካከል አንዱ መሆኑ ነው፡፡ ሊሴ የብዙዎቹ የሀገሪቱ ከፍተኛ ባለስልጣናት ሴት ልጆች የሚማሩበት ግሩም የልጃገረዶች ትምህርት ቤት ነበር፡፡ ማንኛዋም ሩዋንዳዊት ብታገኘው የምትመኘውን እጅግ ምርጥ የሆነውን ትምህርት ማግኘት ከመቻሌም በላይ ወላጆቼ በግል ትምህርት ቤት ከፍያዎች አይጨናነቁብኝም፡፡ ብቸኛው ችግር ትምህርት ቤቱ ራቅ ብሎ በሚገኘው በጊሰኒ ክፍለ ሀገር መገኘቱ ነው፡፡ ትምህርት ቤቱ እጅግ በሚያስቸግረው መንገድ ከማታባ የአራት ሰዓት የተሸከርካሪ ጉዞ ስለሚጠይቅ ወላጆቼ ቶሎ ቶሎ ሊጠይቁኝ አይችሉም፡፡ በተጨማሪም ከነዋሪዎቹ የሚበዙት ሁቱዎች በሆኑበትና ለቱትሲዎች ግልጽ ጥላቻ ባለበት አካባቢ የሚገኝ ነው፡፡

«አይዞሽ የልጃገረዶች ትምህርት ቤት ነው» አለኝ ዳማሲን፡፡ «ያንቺን ደህንነት ለመጠበቅ ብዙ ዘበኞችና ትልቅ አጥር አለው፡፡ የእኔም ትምህርት ቤት በጣም ቅርብ ስለሆነ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ እጎበኝሻለሁ፡፡»

ሊሴን ወዲያውኑ ወደድኩት፡፡ ሕንጻዎቹ ሰፋፊ፣ ቆንጆና ንጽሕናቸው ደግሞ እንደ ጸሐይ የሚያበራ ናቸው፡፡ መማሪያ ክፍሎቹ ብሩህ ቀለም ከመቀባታቸውም በላይ በግቢው ዳር እስከዳር ውብ አበቦች ተተክለዋል፡፡ ግቢው ዙሪያውን ከፍ ያለ የደህንነት አጥር ስላለው ሰላም ተሰማኝ፡፡ በተለይ መነኩሲቶቹ ከምግብ በፊትና በኋላ እንደምንጸልይ ሲነግሩን እኔ ደስተኛ እንደነበርኩት ሁሉ አባቴም ደስተኛ እንደሚሆን እርግጠኝነት ተሰማኝ፡፡

ሳራ የምትባል ሁቱ ልጅ ካፈራኋቸው የመጀመሪያ ጓደኞቼ ውስጥ አንዷ ነበረች፡፡ እንደ እህት እጅግ የተቀራረብን ሲሆን በሩዋንዳ ዋና ከተማ፣ ኪጋሊ፣ ባለው የቤተሰቧ ቤትም ጋብዛኛለች፡፡ ልከኛ ሕይወት ለለመድኩት ለገጠር ልጇ ለእኔ ወደ ትልቁ ከተማ ያደረግሁት ጉዞ ዓይን መግለጫ ሆነኝ - በተለይ ጠያራዎቹን ለመጀመሪያ ጊዜ ቀርቤ ሳይ፡፡ ሳራና እኔ ወደ አየር ማረፊያው በምሽት ሄደን መንደርደሪያው በረጃጅም መብራቶች ሲደምቅ፣ የማረፊያው ሜዳ በቀይ፣ ነጭና አረንጓዴ የብርሃን ጎርፍ ሲጥለቀለቅ ሳይ፣ ትላልቆቹ ጠያራዎች ከሰማይ ሲወርዱና ጩኸታቸውንም ስሰማ አፌ በአግራሞት ተከፈተ፡፡

‹‹ውይ እስቲ እዪአቸው!›› ስላት ሳራ በሣቅ ሞተች፡፡ ‹‹አሁን እንግዲህ ቢቃ ሁሉንም ነገር አይቼዋለሁ›› ብዬ ተኩራራሁ፡፡

በመጀመሪያ ቀን ያገኘኋት ሌላኛዋ ጓደኛዬ ዓይናማዋ ክሌሜንታይን ነች፡፡ ከአዳዲስ ተማሪዎች መካከል እንዳየችኝ ወደኔ መጣች፡፡ እኔ ከአብዛኛው ተማሪ በቁመት የምበልጥ ብሆንም እርሷ ግን ይብሱኑ ቢያንስ ፣80 ያህል ትረዝማለች፡፡ ቱትሲዎች እርስ በርሳችን በቁመታችን እንተዋወቃለን፡፡

‹‹እንዳንቺ ዓይነት ቆንጆ ቱትሲ ልጃገረድ እዚህ ድረስ መጥተሽ ከነዚህ ሁሉ በጠላትነት ከሚያዩሽና ፊታቸውን ከሚያጠቁሩብሽ ሰዎች በአጥር ብቻ ተለያይተሽ እንዴት ነው የምትገፊው?›› በማለት ክሌሜንታይን ፈገግ አለች፡፡ ‹‹አብረን መሆንና እርስ በርሳችን መፈላለግ አለብን›› ብለን ወዲያውኑ ጓደኛሞች ሆንን፡፡

ክሌሜንታይን ፊታቸውን ያጠቁሩብሻል ያለችው ልክ ነው፡፡ ከትምህርት ቤቱ አጥር ግቢ ውጪ መሄድ ከባድ ነው - በሄድኩም ጊዜ አገሬው እኔን አትኩሮ ማየቱን እታዘብና በሚያስፈራ ሁኔታ ‹‹ቱትሲ›› እያለ ማንሾካሾኩን እሰማለሁ፡፡ ትምህርት ቤቱን የሚያስተዳድሩት ቄሶችና መነኩሲቶች፣ ተማሪዎችና ያገሬው ሰዎች በቤተ-ክርስቲያን ባንድ ላይ ቅዳሴ እንዳያስቀድሱ ተጠንቅቀው ይጠባበቃሉ፡፡ ያለ ትምህርት ቤታችን ሠራተኞች አጀብ የትምህርት ቤቱን ቅጥር-ግቢ ለቅቀን እንዳንሄድ የሚከለክል ጥበቅ ትዕዛዝም ተሰጥቶናል፡፡ ውጪው ቢያስፈራም በትምህርት ቤቱ ውስጥ ግን ምንም ዓይነት የዘውግ መድሎ አልተሰማኝም፡፡ መምህራን የዘውግ ስም ጥሪ በፍጹም የማይጠሩ ሲሆን አብዛኞቹ ልጆች ሁቱዎች ቢሆኑም ቅርርባቸን እንደ ቤተሰብ ነው፡፡

ጊዜዬን በትምህርት ቤት ብቻ እያሳለፍኩ፣ በጣም እያጠናሁና ራሴን ከናፍቆት ስሜት እያራቅሁ ከረምኩ። ወላጆቼና ሕፃኑ ወንድሜ ግን ይናፍቁኝ ጀመር። የቪያኒ ጭቅጭቅ ሳይቀር ውል ውል አለኝ። ሕፃኑን ወንድሜ ልብ የሚነካና የሚያስጨንቅ ደብዳቤ ከቤት ከሄድኩ ከጥቂት ወራት በኋላ ልኮልኛል። እጅጉን እንደናፈቀኝ፣ እኔ ከተለየሁት ወዲህ መተኛት እንዳልቻለና አንዳንድ ሌሊት ደግሞ መናፍስት ከከፍል ክፍል ሲዘዋወሩ እንደሚያይ ጽፎልኛል። ባያቸው ጊዜም በመሸበር በቤታችን ውስጥ በድንጋጤ ይሯሯጣል። ደብዳቤው ልቤን ነካው - አዎ ቪያኒና እኔ ብዙ ጊዜ በሆነ ባልሆነው እንነታረካለን፤ አሁን ግን እኔ ለእርሱ ምን ማለት እንደሆንኩ ገባኝ። ጥዬው በመጥፋቴ ጥፋተኝነት ሲሰማኝ ለእርሱ የተሻለች እህት ለመሆን ለራሴ ቃል ገባሁ።

ዳማሲን ለቃሉ ታምኖ በወር አንድ ጊዜ ይጠይቀኝ ጀመር። አብረን በሳሩ ላይ ተቀምጠን ለሰዓታት እናወራለን። በተለይ ጥናትን በተመለከተ ሁልጊዜ ጥሩ ምክር ይለግሰኛል።

«ጸልዩ ኢማኪዩሌ። የቤት ሥራሽን ከመሥራትሽ በፊትና ለፈተናዎች በምትዘጋጅበት ጊዜ ሁሉ ጸልዩ። ከዚያም በቻልሽው መጠን አጥኚ» ይለኛል። በምክሩ መሠረትም በተለይ ከሒሳብ ፈተናዎቼ በፊት በጣም በማጥናት በትምህርት ቤቱ ካሉ ተማሪዎች ሁሉ ከፍተኛ ውጤት እያገኘሁ ሄድኩ።

ዳማሲን ሊጠይቀኝ ሲመጣ ሴቶች ጓደኞቼ እንደዚያ አፍ ለአፍ ገጥሜ የማዋራውን ቆንጆ ልጅ ማንነት ሲጠይቁኝ «ታላቅ ወንድሜ ዳማሲን ነዋ!» በማለት በኩራት እመልሳለሁ።

«አይ፣ አይሆንም። ማንም ሰው ከወንድሙ ጋር እንደዚያ አይቀራረብም። ከእርሱ ጋር መሆንን በእርግጥ *የወደድሽው* ነው የምትመስይው።»

በሕይወቴ ውድ ዳማሲንን በማግኘቴ በጣም እድለኛ ነበርኩ።

ምዕራፍ 3
ቅድመ-ከፍተኛ ትምህርት

በሦስተኛውና በመጨረሻው ዓመት ጦርነት ከመፈንዳቱ በቀር ሕይወት በሊሴ ጥሩ ነበር።

የ1990 የጥቅምት ወር የመጀመሪያዋ ቀን ከሰዓት ቆንጆና ብሩህ ነበረች። የከፍል ጓደኞቼና እኔ የግብረገብ ትምህርት ክፍለጊዜያችን እስኪጀምር እየጠበቅን መምህሩ ለምን እንደዘገየ እናስባለን። አቶ ጋሂጊ ለመግባባት የማያስቸግር፣ የተረጋጋና ምናልባትም ካገኘኋቸው ሰዎች ሁሉ ልስልስ ጸባይ ያለው ነው። ስለሆነም በመጨረሻ እጆቹን ሊያይዘ ሲመጣና በክፍሉ ፊትለፊት ወደፊትና ወደኋላ ሄድ መለስ ሲል አንዳች ነገር እንደተከሰተ ገምተናል። አንደኛዋ ተማሪ ችግሩ ምን እንደሆነ ብትጠይቀውም ወደ እኛ ሳያይ መለስ ቀለስ ማለቱን ቀጠለ።

መምህራችን አንዳች መጥፎ ዜና እንደደበቀንና ምን አልባትም የተንቀሳቃሽ ምስል ትዕይንት ምሽትን መነኩሲቶቹ ሰርዘውት እንደሆነ ሊነግረን ይሆናል ብዬ አሰብኩ። ጉዳዩ ግን ከዚያ የባሰ ነበር። በትምህርት ቤት ውስጥ የዜና ዘገባዎችን ማዳመጥ ስለማይፈቀድልን በመኖሪያ ቤቴ እንደነበረው ሁሉ ከዓለም ወሬ ተነጥያለሁ።

«በሀገሪቱ ላይ ጥቃት እንደተፈጸመ ሰማሁ» ሲል አቶ ጋሂጊ በሃዘኔታ ነገረን። «በጣም አደገኛና በሁላችንም ላይ ለረጅም ጊዜ ተጽዕኖ የሚኖረው ይሆናል ብዬ እፈራለሁ።»

ከፍሉ በጸጥታ ተዋጠ - ከዚያ ሁሉም ባንዴ ማውራት ጀመረ፣ ጥያቄ መጠያየቅ፣ ሩዋንዳን ማን ለምን እንደሚያጠቃት ለማወቅ መጠባበቅ።

«በዩጋንዳ የሚኖር የአማጽያን ቡድን የአገሪቱን ድንበር አቋርጧል» ሲል መለሰልን። «በዋነኝነት ከሩዋንዳ የሄዱ ጥገኞች ልጆች ሲሆኑ ተሰባስበው ወደ ሀገሪቱ ለመግባት እየተዋጉ ነው። ከዚህ ስፍራ በስተሰሜን በኩል በአሁኑ ሰዓት በአማጽያንና በሩዋንዳ መንግሥት ወታደሮች መካከል ከባድ ውጊያ በመካሄድ ላይ ነው።»

አቶ ጋሂጊ ፍርሃትና ንዴትን የሚያንጸባርቅ የጥያቄዎች ዝናብ ወረደበት። «ቱትሲዎቹ ሽፍቶች ግን ምንድን ነው የሚፈልጉት? ለምን ጦርነት ይከፍቱብናል? ትምህርት ቤቱ ጋር ከደረሱስ ምን ያደርጉን ይሆን?»

የሃፍረት ሙቀት በማጅራቴ ተሰማኝ፤ በማስደገፊያዬም ስር ለመደበቅ ፈለግሁ። በክፍሉ ውስጥ ካለነው 50 ተማሪዎች 47ቱ ሁቱዎች ናቸው። በጣም ስለፈራሁና

ስለራሴ ስለተጨነቅሁ ሌሎቹን ሁለት ቱትሲ ልጃገረዶች ማየት እንኳን ተሳነኝ። በቱትሲነቴ ሳፍርና በሊሴም ተለይቼ ስታይ የመጀመሪያዬ ነው።

«አማጽያኑ ራሳቸውን የሩዋንዳ አርበኞች ግንባር (ሩአግ) ብለው አደራጅተዋል። ቡድኑ ሩዋንዳን ከዓመታት በፊት ለቀው የሄዱና እንዳይመለሱ የተከለከሉ የቱትሲዎች ድርጅት ነው። እነዚህ የውጪ ዜጎች ወደ ሩዋንዳ በመግባት መንግሥታዊውን መንበር ለመያዝ ጦርነት አውጀውብናል» አለ።

ስለ ሩአግ ምንነት ግንዛቤው ነበረኝ። አባላቱ መንግሥትን ለመጣል ሲሉ ብቻ እንደማይዋጉም አውቃለሁ። እኩልነት በሰፈነባትና በነጻ ሀገር መኖርን ይፈልጋሉ። አብዛኞቹ የሩአግ ወታደሮች ስደተኞች ቱትሲዎች ወይንም ልጆቻቸው ናቸው።

በ1959ና በ1973ቱ ችግሮች እንዲሁም ሁቱ ጽንፈኞች የግድያ ዘመቻዎችን ባካሄዱባቸው ሌሎች በርካታ ጊዜያት በመቶ ሺህዎች የሚቆጠሩ ቱትሲዎች የራሳቸውንና የቤተሰባቸውን ሕይወት ለማዳን ከሩዋንዳ ሸሽተዋል። አቶ ጋሂጊ አማጽያኑን «የውጪ ዜጎች» ያላቸው አብዛኞቹ እንደ ዩጋንዳና ዛየር ባሉ ጎረቤት ሀገራት ስላደጉ ነው - ያ የሆነው ግን ርዕሰ-ብሔር ሃብያሪማና ስደተኞች ፈጽሞ ወደ ሀገራቸው አንዳይመለሱ የሚከለክል ሕግ ስላወጡ ነው። በዚህም ምክንያት ግዙፍ የቱትሲ ስደተኞች ስብስብ እንዲፈጠር ያደረጉ ሲሆን አንድ ሙሉ የሩዋንዳ ቱትሲዎች ትውልድንም አንዴ እንኳን የእናት አገሩን አፈር ሳይረግጥ እንዲያድግ አስገድደዋል።

አቶ ጋሂጊ ያንን ፊጽሞ ባይገልጽም ቱትሲዎች ራሳቸውን ከጽንፈኛ ሁቱዎች ለመከላከል በሞከሩ ቁጥር ግን ምን እንደሚከሰት ያውቃል። ለእኛ መጨነቁን «ይህ ለቱትሲዎች በጣም አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል - ይህን ዓይነት ነገር ወደ ብዙ ግድያዎች ሊያመራ ስለሚችል መንግሥትና አማጽያኑ ችግራቸውን እንዲፈቱና ደም መፋሰስ እንዲቆም እንጸልይ።»

የዕለቱ ትምህርታችን በዚሁ አበቃ። ሴቶቹ ልጆች ግን የሚያወሩት ስለጥቃቱና ቱትሲ ወታደሮቹ ወደ ትምህርት ቤታችን ቢደርሱ ምን ማድረግ እንደሚኖርባቸው ብቻ ሆነ። ከሁለት ቱትሲ የክፍል ጓደኞቼ ጋር ጸጥ ብዬ ላለመታየት እየሞከርኩ ተቀመጥሁ። ቱትሲዎች እንዴት ኢ-ፍትሃዊ በሆነ መንገድ እንደተያዙ ሳስብ ሃፍረቴ ወደ ንዴት ተለወጠ። የመንግሥት ወታደሮችን አሸንፎ ለመድሎው ፍጻሜ ያበጅለት ዘንድ ተስፋ በማድረግ በልቤ ለሩአግ አጋርነቴን አሳየሁ። በመጨረሻ ግን ንዴቴ ወደ ፍራቻ የተቀየረው ስለመንደሬና ስለቤተሰቤ በተጨነቅሁ ጊዜ ነው። አምላኬ ቤተሰቤን ሰላም ያደርግልኝ ዘንድ ዓይኖቼን ጨፍኜ ተማጸንኩት - በወቅቱ ያለነሱ እንዴት በሕይወት እንደምቆይ ስለማላውቅ።

ብዙዎቹ ተማሪዎች ጦርነቱ አስከፊ በነበረበት በሰሜኑ ክፍል ዘመዶች ስለነበሯቸው የትምህርት ቤቱ ርዕሰ - መምህር የሬድዮ ዘገባ እንድናዳምጥና ስለ

ከስተቱ እንድንረዳ ፈቀደልን። ብሄራዊው ሬድዮ የሚያስተላልፈው ዘገባ ከሞላ ጎደል የጥላቻ ውትወታ ነው ማለት ይቻላል። ዘጋቢዎቹ አማጽያኑ እንደ አውሬ በጫካ እንደሚኖሩ፣ የሰው ስጋ እንደሚበሉና ከዝንጀሮዎች ጋር ወሲብ እንደሚፈጽሙ አተቱ። የለየላቸው ሰይጣኖች ስለሆኑ ቀንድ አብቅለዋል ተባለ። «አማጽያን በረሮዎቹ» በማናቸውም ስፍራና ጊዜ ሊተናኮሉ ስለሚችሉና መሰሪ ስለሆኑ ሩዋንዳውያን ራሳቸውን እንዲጠብቁ ማስጠንቀቂያ ተሰጣቸው። እነዚህ ዘገባዎች ቀድሞውንም የተዛባ አመለካከት የነበራቸውን ልጃገረዶች አቀጣጠሏቸው። አንዷ ማ በጣም ፈርታ ስለነበር ልታስገድለኝ ነበር።

ዳኒዳ ከመኝታ ቤት እህቶቼ አንዷ ስትሆን ስለአማጽያን ወታደሮቹ የተነገሩትን ሁሉንም አስፈሪ ገለጻዎች አምናቸዋለች። አንድ ምሽት ከመኝታ ቤቱ ውጪ ወደሚገኘው መታጠቢያ ክፍላችን ለመጠቀም ስሄድ ከእንቅልፏ ሳልቀሰቅሳት አልቀርም። ምሽቱ በጣም ይቀዘቅዝ ስለነበር እንዲሞቀኝ ትልቅ ፎጣዬን በራሴ አስሬ የሚረዝምብኝ የነበረ የሌሊት ልብስ ለብሻለሁ። ትንሽ ሳላስፈራ አልቀርም፣ ተመልሼ ለመግባት በሩን ለመክፈት ስሞክር ዳኒዳ ፊቴ ላይ በኃይል ዘጋችብኝ። ኡኡታዋን ስታቀልጠው ግቢው ተሸበረ።

«አድኑኝ! እርዱኝ! ወይኔ አምላኬ! ኧረ እርዱኝ። የሩአግ ወታደር ነው - ሊገድለን፣ ሊበላን መጣ። አቤት ቀንዶቹ!»

የዳኒዳን ጆሮ ሰንጥቆ የሚገባ ድምፅ ስላወቅሁት በእርጋታ «ዳኒዳ፣ እኔ እኮ ነኝ፣ ኢማኪዩሌ ነኝ። ወታደር አይደለሁም። ቀንድም የለኝ፤ ፎጣዬን ነው እኮ ራሴ ላይ ያሰርኩት!» አልኳት።

ሞቅ አድርገው የሚረግጡ እግሮች ከኮረኮንቹ ጎዳና በኩል ሰምቼ ዘወር ስል የትምህርት ቤታችን ትልቁ ዘበኛ በደረቴ ትይዩ ያነጣጠረ ጦር ይዞ በጨለማው ወደኔ ይገሰግሳል። ብርክ ይዞኝ ጉልበቴ ተሽመድምዶ መሬት ላይ ቁጭ አልኩ። ዘበኛው ከእኔ መጠነኛ ርቀት ላይ ይገኛል።

«ኢየሱስ ክርስቶስ! ኢማኪዩሌ፣ ገድዬሽ ነበር እኮ! ማናባቷ ነች እንደዚያ የምትፈጭሽው?» አለ።

በወቅቱ በመኝታ ቤታችን የነበሩት *ሁሉም* ልጆች እየፈጩኩ ስለነበር እኔም በሁካታው መካከል ዘበኛው እንዲሰማኝ መጮህ ነበረብኝ። ቢያንስ ለግማሽ ሰዓት በርካታ ጥበቃዎች ልጆቹን በሩን መክፈት ችግር እንደሌለው ለማሳመን ቢሞክሩም አሻፈረኝ አሏቸው። የትምህርት ቤቱ ርዕሰ-መምህር ማናቸውንም በር የሚከፍት ቁልፍ ይዘው እንዲመጡ ተጠርተው በሩን ከፍተውልን ወደ ውስጥ ከገባን በኋላ ፍርሃታችን እኛን እንዲቆጣጠረን መፍቀድ ስላለው አደጋ ሲያስተምሩን ብዙ ቆዩ።

የነበረው ሁኔታ አሳሳቢ ቢሆንም በትምህርት ቤቱ ውስጥ የነገሰው ውጥረት ሁሉ ግን አያስበረግገንም፡፡ አንድ ቀን ከሰዓት በኋላ ለእግር ጉዞ ወጥተን ሳለ በአገሬው ሁቱ ቡድን አቅራቢያ እናልፋለን፡፡ ከሰዎቹ አንደኛው ትልቅ ቢላዋ ይዞ ወደኔ ይሰብቃል፡፡ «ይችኛዋ እንዴት እንደተንቀፈረረች እዩ» በማለት እያጉረመረመ ያስፈራራኛል፡፡ «አስቀድመን እንገድልሻለን፡፡ አማጽያን ወንድሞችሽ እያደረጉ ላሉት እንድትከፍይ እናደርግሻለን!»

ሆዴ ከመሸበሩ የተነሣ ሊያስመልሰኝ ቃጣው፡፡ ሰው በአመፅ ሲያስፈራራኝ የመጀመሪያዬ ስለነበር ጉዳዩን እንዴት ማስተናገድ እንደነበረብኝ አላወቅሁም፡፡ ወደ መኝታ ቤቴ ሮጬ ተመልሼ በትምህርት ቤታችን ሽርሽር በፍጹም ድጋሚ አልሳተፍም ብዬ ማልኩ፡፡ ቁመናዬንም ረገምኩት፤ ረጅም መሆን በሀገሬ ለምን እንዲህ ወንጀል ሆነ ብዬም ተማረርኩ፡፡ ምን እንዳደርግ ነበር የሚፈለገው? ማደጌን ላቆመው አልችልም፡፡ ቱትሲነቴንም አልፍቀው!

በቀጣዩ ቀን በትምህርት መካከል ክሌሜንታይን ወደኔ ክፍል መጥታ በጆሮዬ «ነይ ተከተዪኝ ኢማኪዩሌ! እንደዚያ ቢላዋ እንደያዘው ሰውዬ ዓይነት ሰዎች ሲመጡብን ምን ማድረግ እንዳለብን ላሳይሽ፡፡»

ብዙም ሰው ወደማይገባበት ሕንጻ ወስዳኝ ውስጡ ባለ አንድ ክፍል ውስጥ ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ኃይል ያለው ሣጥን ከፈተች፡፡ «ከ1500 ቮልት በላይ ኤሌክትሪክ እዚህ አለ» ስትል ታስረዳኝ ያዘች፡፡ «ሁቱ ጽንፈኞች ትምህርት ቤቱን ከወረሩና የምናመልጥበት መንገድ ካጣን እዚህ መጥተን ይህን መክፈቻ ቁልቁል ሳብ አድርገን እጆቻችንን ወደ ውስጥ ማስገባት እንችላለን፡፡ ወዲያውኑም እንሞታለን - በሰው ከመገረፍ፣ ከመደፈርና ከመገደል በኤሌክትሪክ ተቃጥሎ መሞት በስንት ጣሙ፡፡ አረመኔዎች እኔን ከመግደላቸው በፊት በሰውነቴ ላይ እንዲጫወቱበት አልፈቅድላቸውም፡፡ እጅግም አይግረምሽ - በክፉ ቀናት ቱትሲ ሴቶች የማምለጫ ዕቅድ ስላልነበራቸው የተደፈሩባቸውንና የተሰቃዩባቸውን በርካታ ታሪኮች ሰምቻለሁ፡፡»

በመስማማት ራሴን ነቀነቅሁ፡፡ ሕይወታችንን ስለመቅጨት በ19 ዓመታችን ማውራት እንግዳ ነገር ቢሆንም ከሌላኛው አማራጭ የተሻለ ይመስላል፡፡ የትምህርት ቤቱ ባለስልጣናት ይህን ዕቅድ ሰምተው ሳጥኑን እንዳይዘጉት ክሌሜንታይንና እኔ ለማንም ላንናገር በመስማማት ተማማልን፡፡

አዲስ ዜና ለመስማት ስንል ሬድዮ ማዳመጣችንን ቀጠልን፡፡ የመንግሥቱ ጣቢያ ግን የተሳሳተ መረጃ በማሠራጨት አቻ የማይገኝለት ስለነበር ሩአማ ኪጋሊ ድረስ ተዋግቶ የርዕሰ-ብሔሩን ቤተ-መንግሥት እንዳጠቃ ወሸክቶልናል፡፡ ርዕሰ-ብሔሩ በብሔራዊው

ሬድዮ ወጥቶ ጦሩ ሁሉንም «በረሮ» ወራሪዎች ገድሎ እስኪጨርስ ሕዝቡ በየቤቱ እንዲቆይ አስጠነቀቀ። በኋላ ላይ ከብሪታንያው የዜና ምንጭ ከቢቢሲ እንደሰማነው ከዋና ከተማው በኪሎሜትሮች ርቀት ምንም የሩአግ ወታደር አልታየም - ርዕሰ-ብሔር ሃብያሪማና ጥቃቱን ራሳቸው ፈጥረው በሬድዮ የዋሹት ከሀገሪቱ ውጪ የሚኖሩ ዘመዶች ስለነበራቸው ብቻ በሺህዎች የሚቆጠሩ ቱትሲዎችን ለማሥራቸው የትክክለኝነት ማስረጃ መፍጠራቸው ነው። ርዕሰ-ብሔሩ ማንኛውንም በዩጋንዳ የአከስት ወይንም የአጎት ልጅ የነበረው ቱትሲ ከአማጽያኑ ጋር መተባበሩ አይቀሬ ነው ብለው አምነው ቅዠት ውስጥ የገቡ ይመስላል።

ቢቢሲ በዘገባው እጅግ ብዙ ንጹሃን ቱትሲዎች በመታሠራቸውና በሩዋንዳ በቱትሲ እስረኛ ያልታጨቀ እስር ቤት በመጥፋቱ ለወንጀለኞች ማሰሪያ የተረፈ ቦታ አልነበረም ብሏል። እንደሚባለው ከሆነ በወቅቱ ብዙዎቹ ቱትሲዎች በረሃብ እየተሰቃዩ፣ ድብደባ እየተፈጸመባቸውና የተወሰኑትም እየተገደሉ ነበር።

ለገና በዓል ወደ ቤቴ እንደሄድኩ አባቴ በወቅቱ ታስረው ከነበሩት አንዱ መሆኑን አወቅሁ። በማታባ ከሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ እንደወረድኩ ከረጅም ጊዜ ጎረቤቶቻችን አንዷና ቀንደኛ ወሬኛ ከነበሩት ከእመት ሲራኬ ጋር በድንገት ተገናኘን። «እስቲ ነይ ሳሚኝ ልጄ» ሲሉ አለቀሱ። እንኳንም አንቺን አሳየኝ! አንጀትሽ እንዴት ነው የተጣበቀው አንቺ! - እነዚያ መነኩሲቶች አያበሉሽም እንዴ?»

«ኧረ በደንብ ያበሉናል። ግን ከቤተሰቤ ጋር ራት ለመብላት ጓጉቻለሁ።»

«እንዲያው ያ አባትሽ በተለይ ያን ሁሉ ችግር አሳልፎ አሁን ዓይንሽን ሲያይ ደስ እንደሚለው ይታየኛል።»

«ምን ማለትዎ ነው?»

«አልሰማሽም ልጄ?»

ልቤ ተቻኮለ። ጦርነቱ ከጀመረ ወዲህ ወላጆቼን አላየኋቸውም፤ ለሳምንታት ያህልም ከቤት ምንም ዓይነት ወሬ አልመጣልኝም።

«በእውነቱ ታውቂያለሽ ብዬ ነበር ያሰብኩት» አሉ እመት ሲራኬ «አባትሽ እኮ ታስሮ ከረመ።»

በድንጋጤ አጠገቤ በተጋደመ ግንድ ላይ ቁጭ አልኩ። አባቴ ቱትሲ ከመሆኑ በቀር ሊያሳስረው የሚችል ምንም ነገር ሊያደርግ ይችላል ብዬ ማሰብ አልቻልኩም። ስለ እናቴም ጤና ተጨነቅሁ። የአባቴ መታሰር የሚያስከትልባት ጭንቀት አስሚን አስነስቶባት እንዳይሆን! የሰላሳ ደቂቃውን የእግር መንገድ መቼም ሄጀ በማላውቅበት ፍጥነት ፉት ብዬው እናቴን በሩ ጋ ስትጠብቀኝ አገኘኋት።

እቅፍ አደረጉችኝና «እንዴት ነሽ ሆዴ?» ስትል ጠየቀችኝ፡፡ ስለ አባቴ መታሰር ምንም አላነሳችም - ሁልጊዜ ከመጥፎ ስሜት ትጠብቀናለች፤ መቼም የማትቀየር መሆኗንም ታዘብኩ፡፡

«መቼም ርቦሻል፣ ኢማኪዩሌ፡፡ ምግብ እስካሰናዳልሽ ገላሽን ታጠቢያ፡፡ ዳማሲንና ቪያኒ የሆነ ቦታ አብረው ሄደዋል፤ ኤይማብልም ከዩኒቨርሲቲ ገና አልመጣም፡፡ አባትሽ ሥራ ቦታ ነው፤ ዓይንሽን ለማየት እንዴት እንደጓጓ አትጠዪቂኝ፡፡»

«ሁላችሁም ደኅና ናችሁ? አንዳችሁም ላይ ምንም ነገር አልተከሰተም?»

«አይዞሽ! ሁላችንም ሰላም ነን፡፡»

«በፈጠረሽ እማማ! አባባ ታስሮ መከረሙን አውቃለሁ፤ ስለዚህ ማለባበሱን ተዪና የተከሰተውን ሁሉ ንገሪኝ፡፡»

እናቴ መጥፎውን ዜና ለኔ መንገሩ ስለቀረላት ቅልል አላትና ወዲያውኑ ቁጭ ብላ ሁሉንም ነገር አጫወተችኝ፡፡

ጦርነቱ ከጀመረ ከጥቂት ጊዜ በኋላ አራት የመንግሥት ወታደሮች ወደ አባቴ የሥራ ቦታ ሄደው እጆቹን ወደኋላ አስረው ከግማሽ ደርዘን የሥራ ባደረቦቹ ጋር ኪቡዬ ከተማ እስር ቤት ወስደው ወረወሩት፡፡ ዘበኞቹንም ለብዙ ቀናት ምግብም ሆነ መጠጥ እንዳይሰጧቸው ከለከሏቸው፡፡ በኋላ ላይ አባቴ ሁቱውን ዘበኛ በጉቦ ደልሎ በቅርቡ ለምትኖረው አክስታችን ሲሲሌ መልዕክት እንዲወስድለት ያደርጋል፡፡ ሲሲሌም ወደ እስር ቤቱ ምግብ አምጥታ ዘበኛው ምግቡን ለአባቴና ጓደኞቹ አስገባላቸው፡፡

ከሁለት ሳምንታት በኋላ አባቴ እንዲታሰር የታዘዘው በዱሮ ጓደኛው በካባዬ እንደሆነ ይደርስበታል፡፡ ካባዬ የወረዳው አስተዳዳሪና አድራጊ ፈጣሪ ተደርጎ የተሾመ ሁቱ ነው፡፡ ካባዬና የኔ አባት አብረው የተማሩ ጥሩ የልጅነት ጓደኛሞች ነበሩ፡፡ ርዕሰ-ብሔር ሃብያሪማና ለዓለምአቀፍ ጫና ተንበርክከው በስህተት የታሰሩ በሺዎች የሚቆጠሩ ቱትሲዎችን ለመፍታት ከተስማሙ በኋላ ነበር ካባዬ ወደ እስር ቤት ሄዶ ዘበኞቹ አባቴንና ጓደኞቹን እንዲፈቷቸው ያዘዘው፡፡ ካባዬ ዘበኞቹ ለአባቴ ምንም ዓይነት ምግብ እንዳይሰጡት አዟቸው ስለነበር በሕይወት ሲያገኘው ክው አለ፡፡ የተበሳጨ መስሎና የሚገርም ስህተት መፈጸሙን ገልጾ አባቴን በእጅጉ ይቅርታ ጠየቀው፡፡

በዚያ ምሽትም ከእራት በኋላ ከበን ተቀምጠን ሳለ የተከሰተውን ነገር ከአባቴ ጋር ለመወያየት ስሞክር አባቴ «የተደበላለቀ ነገር ነው፡፡ ካባዬ የታዘዘውን ነበር

የሚፈጽመው፤ የግል ጉዳይ እንኳን አይደለም፡፡ እነዚህ ነገሮች ከፖለቲካ ጋር የሚያያዙ ስለሆኑ እናንተ ልጆች ባትነካኩ ይሻላል፡፡ ሁሉንም ነገር እንርሳው» አለ፡፡

ወንድሞቼ አባታችን ያን ያህል ይቅር ባይ መሆኑን ሊያምኑ አልቻሉም፡፡ ካባዬን በሕይወታቸው ሙሉ ያውቁት ስለነበር በአባታችን ላይ እንደዚያ በመነሳቱ ተናደዋል፡፡

«ካባዬ እኮ ጓደኛህ ነበር አባባ፡፡ ጠላትህ ሆኖማ ቢሆን ምን ሊከሰት እንደሚችል አስበው እስኪ፡፡ ለምንድነው ለሱ የምትሟገትለት? እነዚህ የምትቆምላቸው ሰዎች እኮ ሊያጠፉህ ይፈልጋሉ! ጦርነቱ እስኪያልቅ ድረስ አገሪቱን ለቀን መሄድ አለብን፡፡ ሌላው ቢቀር እማማንና ኢማኪዩሌን ከዚህ ማራቅ ይኖርብናል - የእነርሱ ነገር አሳስቦኛል» አለ ኤይሚየብል፡፡

«አይ እንግዲህ፣ ምነው አጋነንከው በል - ምንም ሥጋት የለብንም፡፡ ሁኔታው ከበፊቱ እየተሻሻለ ነው፤ ይህ ከፖለቲካ ጋር ብቻ የሚያያዝ ጉዳይ ነው፡፡ እናንተ ልጆቹ አትጨነቁለት፡፡ ምንም አንሆንም፤ ምን አለ በሉኝ» ሲል አባታችን አረጋገጠልን፡፡

እናቴ ወንድሞቼን ሌሎች በርካታ ቱትሲ ወንዶች ያደርጉት እንደነበረው ሾልከው የሩአግ ተዋጊዎችን እንዳይቀላቀሉ ለመነቻቸው - «አንዳችሁ እንኳን ከአማጽያኑ ጎን ለመዋጋት ብትሄዱ ውሳኔያችሁ እንደሚገድለኝ እንድታውቁት እፈልጋለሁ! *ኦንብግቦ ይገድለኛል!* እናታችሁን መግደል ግድ ካላላችሁ አሁኑኑ ሂዱ፡፡ ከወደዳችሁኝ ግን ጠፍታችሁ ለሥቃይ እንደማትተውኝ አሁን ቃል ትገቡልኛላችሁ፡፡ በሉ ማሉልኝ!»

እናቴ ራሷን በዚህ ሁኔታ ውስጥ በመክተቷ ወንድሞቼ አማጽያኑን እንደማይቀላቀሉ ደጋግመው ቃል ገቡላት፡፡

እኔም ወደ ሊሴ ሄጂ ቀሪ የተወሰነ ወራት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን ጨርሼ የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተናዬን ተፈተንኩ፡፡ በድጋሚም አመርቂ ውጤት አመጣሁ፤ ያለችኝ የመግባት ተስፋ ግን የመነመነች ነበረች፡፡ የዘውግ ተዋፅዖ የሚባው አሰራር ሩአግ መጨረሻ ይኖራቸው ዘንድ ከሚዋጋላቸው ነገሮች አንዱ ነው፣ በወቅቱ ግን ይህ ተዋፅዖ ተብዬው ለትምህርት ሕይወቴ መጨረሻ ያበጅለት መሰለኝ፡፡

በሊሴ ለነበሩኝ መልካም ጓደኞቼ ስንብት አድርጌ ዕጣ-ፈንታ ወዴት እንደምታመራኝ ወደምጠባበቅበት ወደ ቤቴ ለክረምት እረፍት አመራሁ፡፡ ጦርነቱ እየተፋፋመ መጣ፤ አማጽያኑም ብዙ ጦርነቶችን እያሸነፉና መንግሥትንም በስደት የሚኖሩ ሩዋንዳውያንን ወደ ሀገራቸው ይመለሱ ዘንድ እንዲፈቅድና ሥልጣንንም ለአማጽያኑ እንዲያጋራ ግፊት እያሳደሩበት መጡ፡፡

እናቴ እየተከሰተ በነበረው ነገር በጣም ተጨንቃ አዋቂዎችን ሳይቀር መጠየቅ ጀምራ ነበር፡፡ አንዷ ጠንቋይ ወደ ቤታችን እየመጡ ኩሽና ውስጥ ከእናቴ ጋር ሲቀመጡ አስታውሳለሁ፡፡ እናቴም ጦርነቱ ያበቃ እንደሆነና ሰላምንም መልሰን እናገኛት እንደሆነ ትጠይቃቸዋለች፡፡

‹‹በሁላችንም ዙሪያ መብረቅ ይታየኛል፣ ግን እነዚህ ሕፃናት ማዕበሎች ናቸው›› አሏት አዋቂዋ፡፡ ‹‹እናትየዋ ማዕበል እየመጣች ነው፡፡ ስትደርስ መሬቱን ታጋየዋች፣ ድርቅርቋ ያደነቁረናል፤ ከባዱ ዶፏም ሁላችንንም ያሰጥመናል፡፡ ለሦስት ወራት የሚቆየው ማዕበል ብዙዎቹን ይፈጃል፡፡ የሚያመልጡት ሰዎች የሚሸሽጋቸው አያገኙም - ሁሉም የሚያውቁት ፊት ይጠፋባቸዋል፡፡ ‹ይብላኝ ለእነርሱ››

ምዕራፍ 4
ወደ ዩኒቨርሲቲ

በ1991 ክረምት መጨረሻ የማይቻለው ተከሰተ - በቡታሬ በሚገኘው ብሄራዊው ዩኒቨርሲቲ መማር የሚያስችለኝ የትምህርት ዕድል ተሰጠኝ። በሕይወቴ ሙሉ ወደ ዩኒቨርሲቲ መግባትን በጽኑ ስመኝ ነበር። በመሆኑም በፊቴ እነዚያ ሁሉ መሰናክሎች ቢጋረጡብኝም በድንገት ሕልሜ እውን ሆነ።

ወላጆቼ ዜናውን ሲሰሙ በጣም ተደስተው ተቁነጠነጡ። በትክክለኛው የሩዋንዳ ደንብ - ያው በድግስ መሆኑ ነው - እናከብረው ዘንድም ምግብና መጠጥ ለማዘጋጀት ተፍ ተፍ ይሉ ጀመር።

«ዩኒቨርሲቲ በመግባት ከቤታችን የመጀመሪያዋ ሴት ልጅ ነሽ፣ ስለሆነም አሁኑኑ ይህን ለሁሉም ሰው ማሳወቅ አለብን!» ሲል አባቴ በኩራት ተናገረ። በማግስቱ ረጅም መንገድ ተጉዤ ለአያቴ፣ ለአክስቶቼ፣ ለአጎቶቼና ለሁሉም በአቅራቢያችን መንደሮች ለሚኖሩት ልጆቻቸው ወሬውን እንዳበስር አመቻቸልኝ።

ሌሊቱን ሙሉ ስንስቅ፣ ስንበላና ወደፊት ስለሚኖሩት በጎ ነገሮች ሁሉ ስናወጋ አሳለፍን። ወላጆቼ በዚያ ምሽት ሽክም ከትከሻዎቸው እንደወረደላቸው ሁሉ ወደ ወጣትነት የተመለሱ መሰሉኝ።

እናቴ በደስታ ፈክታ አመሸች። «ሁሉም ነገር ላንቺ ብሩህ የሆነልሽ ይመስላል፣ ኢማኪዩሌ» አለችኝ። «ከአሁን በኋላ ሙሉ በሙሉ የራስሽን መንገድ ማበጀት ትችያለሽ፤ ቀና በይ፤ ማንም ሌላ ሰው በገበታሽ ላይ በፍጹም ምግብ እንዲያስቀምጥልሽ አትጠባበቂ።»

አባቴም ከኔ ጋር መጠጫ ኢጋጭቶ ብዙ አባታዊ ምክር ለገሰኝ። «በዙውን ጊዜ በዩኒቨርሲቲ የሚማሩት ወንዶች ሲሆኑ እነርሱም አንቺን እንደነርሱ ጎበዝ ነች ብለው አያስቡም። ግን እንደነሱ መትጋት እንደምትችዪ አውቃለሁ፤ አንዲያውም ከማንኛውም ወንድ በተሻለ። አንቺ ቱትሲ ስለሆንሽ ዩኒቨርሲቲ መግባት ፈተና ሆኖብሽ ቆይቷል፤ ይኸው አስቸጋሪው ወቅት አለፈ። እንግዲህ የራስሽ ድርሻ ነው - በደንብ አጥኚ፣ ጸልዪ፤ ስታድጊ በስስት እናይሽ እንደነበርሽው ምስጉን፣ ደግና ቆንጆ ልጅ መሆንሽን ቀጥዪበት።»

በጣፋጭና ፍቅር የተሞላባቸው ቃላቱ ልቤ ሐሴት አደረገች። «አሳብ አይግባህ አባባ» አልኩት። «አንተንም ሆነ እማማን አላሳፍራችሁም። አኮራችኋለሁ።»

ስለ ሰው ልቦናና አእምሮ አሠራር ለመማር ሥነ ልቦናንና ፍልስፍናን ለማጥናት ብፈልግም የትምህርት ዕድሉ በተወሰኑ የትምህርት ዓይነቶች ባሉ ክፍት ቦታዎች የተወሰነ ስለነበር ራሴ የምፈልገውን የጥናት መስክ እንድመርጥ አልተፈቀደልኝም። በተግባራዊ ሳይንስ መርሃ-ግብር መመደቤ ተስማምቶኛል። በሊሴ ለወንድሞቼ ችሎታዬን ለማሳየት ስል ራሴን በሒሳብና ፊዚክስ አብቅቼ ስለነበር አሁን ያ ሥንቅ ይሆነኛል። ሻንጣዎቼን አዘገጃጅቼ ወዲያውኑ ከመንደሬ ደቡብ ምሥራቅ አራት ሰዓት ወደሚያስነዳውና ፍጹም አዲስ ሕይወት ወደሚጠብቀኝ ወደ ቡታሬ አቀናሁ።

ትምህርት ቤቱ ቅጥር-ግቢ ስደርስ ክሌሜንታይንን ጨምሮ ከሊሴ ስድስቱ የሴት ጓደኞቼ፣ የትምህርት ዕድሉን ማግኘታቸውን ተረዳሁ። ጓደኛዬ ሳራ እዚያው አንድ ዓመት ቀድማ ገብታ ስትማር የቆየች ሲሆን አንድ መኝታ ክፍል ውስጥ አብረን እንድንኖር ስትጠብቀኝ ኖሯል። በተጨናነቁ ክፍሎች ውስጥ ከተኛሁባቸው ከእነዚያ ዓመታት በኋላ ከአንዲት ሴት ልጅ ጋር ብቻ አንድ ክፍል መጋራት እጅግ ይመቻል። ክሌሜንታይን ብዙ ጊዜ የኛን ክፍል ትጎበኝ የነበረ ሲሆን በጦርነቱ መጀመሪያ ሰሞን ራሳችንን በኤሌክትሪክ የማቃጠሉን ዕቅዳችንን ባለመፈጸማችን እንዴት ዕድለኞች እንደነበርን በጨዋታ መካከል እናነሳለን። ያ ቢሆን ኖሮ የዩኒቨርሲቲን አስደሳች ነገሮች ሁሉ መች እናይ ነበር?

ትምህርቱን ወደድኩት፤ በጣም ጠንክሬም አጠና ጀመር። የዩኒቨርሲቲን አስደሳችነትና ነጻነት እንዴት እንደወደድኩት! የትምህርት ዕድሉ ለእኔ ትልቅ ነገር የነበረውን ወደ 30 የአሜሪካን ዶላር የሚሆን ወርሃዊ የኪስ ገንዘብንም ይጨምራል። በሕይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ እንደ ትልቅ ሰው ነጻነት ተሰማኝ። የትምህርት ቤት የደንብ ልብስ መልበስ ቀረልኝ፤ ከተማም ሄድ ብዬ ከጓደኞቼ ጋር ቆንጆ ቆንጆ ልብሶችን መግዛት ቻልኩ። አቤት ሲያስደስት!

ቡና ተፈልቶ በሚሸጥባቸው ስፍራዎች፣ በሰንበት ተንቀሳቃሽ ምስል በሚታይባቸው ቦታዎችና በየአሥራአምስት ቀኑ ቅዳሜ ምሽት በሚካሄዱት የትምህርት ቤት አቀፍ የዳንኪራ ጊዜያት እስከመገኘት ደርሼ በማኅበራዊ ሕይወት በጣም ንቁ ተሳታፊ ሆንኩ። የትዕይንት ማሳያ ቡድንንም ተቀላቅዬ ብዙውን ጊዜ የቡታሬ ከንቲባ በሚገኙባቸው በሁሉም ትዕይንቶች እዘፍንና እጨፍር ነበር። ሃይማኖታዊ ገጸባህርያትን ወክሎ መተወን ምርጫዬ በመሆኑ እንዲያውም አንድ ጊዜ የምወዳትን ቅድስት ድንግል ማርያምን ወክዬ ተጫውቻለሁ። ሁልጊዜ ለጸሎት የሚሆን ጊዜ እተዋለሁ። ያንን ጽናት ማግኘቴና ጸሎት ማድረጌ እጅጉን አረጋግቶኝና አትኩሮቴን እንድሰበስብ ረድቶኝ ነበር። ቤተ-ክርስቲያን በሳምንት ብዙ ጊዜ እሄዳለሁ፤ ከሴት ጓደኞቼም ጋር የጸሎት ቡድን አቋቁሜያለሁ።

ለናፍቆት ጊዜ ባይኖረኝም ከአባቴ የሚላኩልኝ ብቸኝነት የሚንጸባረቅባቸው ደብዳቤዎች ቤተሰቤን ቶሎ ቶሎ መጎብኘት እንዳለብኝ አስገነዘቡኝ። በወቅቱ ቪያኒ በአዳሪ ትምህርት ቤት ስለነበር ወላጆቼ ብቸኝነትን መላመድ አቅቷቸዋል። «ከልጆቼ አንዳቸውም እዚህ ሳይኖሩ ሕይወቴ እንደ ዱሮው ሊሆን አይችልም» ሲል አባቴ ጻፈልኝ። «ቤቱ በጣም ጭር ብሏል። አንዳንዴ እኔና እናትሽ እርስ በርሳችን እንተያይና እንገረማለን፣ ‹ያ ሁሉ ሣቅ የት ሄደ?› እንላለን። የራስሽ ልጆች ሲኖሩሽ፣ ኢማኪዩሌ፣ ሳትጠግቢያቸው ስለሚሄዱብሽ አብረውሽ እያሉ እያንዳንዷን ደቂቃ በደስታ ማሳለፍሽን እርግጠኛ ሁኚ፣ ...»

በማታባ ያሉትን የተወሰኑትን ጓደኞቼን የሚያውቅ ዮሃንስ የሚባል ተማሪ ጓደኛም አገኘሁ። ከእኔ ሦስት ዓመት ይበልጥ የነበረና «ድንገት» ከኔ ጋር በትምህርት ቤቱ የተለያዩ ስፍራዎች ግጥምጥም የማለት የተለየ ጸባይ የነበረው ልጅ ነው። መጽሐፍቴን ይይዝልኝ፣ የትምህርት ቤታችንን ግቢ ያሳየኝና ከጓደኞቹ ጋር ያስተዋውቀኝ ጀመር። አማላይ፣ ታጋሽና ለሰው አሳቢ ልጅ ነበር። በጫካው ውስጥ ለረጅም የእግር ጉዞ አብረን እየሄድን ለእኛ አስፈላጊ ስለሆነው ጉዳይ እናወራለን - ስለ እግዚአብሔር፣ ስለ ቤተሰብና ስለ ጥሩ ትምህርት። በኋላም ላይ ፍቅር ለመጀመር በቃን፤ በመጭዎቹም ዓመታት ውስጥ አንዳችን ለሌላችን በጣም እንተሳሰብ ጀመር። ዮሃንስ ሁቱ ቢሆንም ግን ይህ ጭራሽ ጉዳያችን አልነበረም። ለአባቴ ይልቁን ዮሃንስ ወንጌላዊ ክርስቲያንና የሰባኪ ልጅ መሆኑ ያሳስበዋል።

«ካቶሊክ መሆንሽን አትርሺ» እያለ አባቴ ያስታውሰኛል። «ዮሃንስ ጥሩ ልጅ ይመስላል፤ እንድታፈቅሪውም መርቄሻለሁ - ግን ወደ እርሱ ኃይማኖት ሊቀይርሽ እስካልሞከረ ድረስ ነው።» አባቴ በጣም ታጋሽ ሰው ሲሆን ሃይማኖተኛም ነው።

በዩኒቨርሲቲ የቆየሁባቸው ሁለቱ የመጀመሪያ ዓመታት በረሩ፤ ሁሉም ነገር መልካም ሆነልኝ - ውጤቴ ጥሩ፣ ቤተሰቤ ጤነኛ፣ ሕይወቴም አስደሳች። ሕይወት ስለሚመች አልፎ አልፎ ካልሆነ በስተቀር ጦርነት መኖሩን ለመርሳት አይከብደንም።

አልፎ አልፎ የሚካሄዱ የሰላም ድርድሮችና የተኩስ አቁም ስምምነቶች ቢኖሩም በቱትሲ አማጽያንና በመንግሥት ወታደሮች መካከል የሚደረገው ከባድ ውጊያ ቀጥሏል። አንዳቸው ሌሎቻቸውን አጥብቀው የሚቃወሙ ጽንፈኛ የፖለቲካ ድርጅቶች በብዙ ከተሞች አቆጠቆጡ። ሥራአጥ ወጣቶች ምንም ሌላ የተሻለ የሚሰሩት ነገር ስላልነበራቸው ወደ ተለያዩ የፖለቲካ ቡድኖች የወጣት ክንፎች ጎረፉ። ብዙዎቹም የፖለቲካ ተቋማቱን ለአልኮል መጠጥ ወይንም አደንዛዥ እጽ ሲሉ የሚቀላቀሉ የመንገድ ላይ የወሮበላ ቡድኖች አባላት ነበሩ።

የርዕሰ-ብሔር ሃብያሪማና የፖለቲካ ፓርቲ ራሱ *ኢንተርሃምዌ* ማለትም «አብረው የሚያጠቁት»፣ የተባለ የወጣት ክንፍ አቋቋመ። ኢንተርሃምዌም በሺዎች

የሚቆጠሩ ቤት-አልባ ልጆችን ሳበ፤ የአባላት ስርጭቱም በሀገሪቱ ዳር እስከ ዳር እንደ ወረርሽኝ ተስፋፋ፡፡ ስብስቡ የሁቱ ጽንፈኛ ታጣቂ ቡድን ለመሆን ቢቃ፡፡ ብዙዎቹ አባላቱም ሰው አገዳደልና ጥይት አተኳኮስ የሠለጠኑት በመንግሥት ወታደሮች ነው፡፡ በቡድን ይሄዱና የተለየ የደንብ ልብስ ይለብሱ ጀመር - ደማቅ ቀይ፣ ቢጫና አረንጓዴ የድርጅታቸውን ባንዲራ መሳይ ያለበት ሰፊ ጥብቆ ይለብሳሉ፡፡ የቱንም ያህል ቢደራጁ በግሌ ሁልጊዜ እንደ ህገወጥ የመንገድ ላይ ወሮበሎች እቆጥራቸዋለሁ፡፡

ኢንተርሃምዌዎችን *መጀመሪያ* ያየሁት በሚከተለው አኳኋን ነው፡- በ1993 የትንሣኤ እረፍቴ ኪጋሊ ላይ ከዮሃንስ ጋር ሳራንና ቤተሰቧን ለመጎብኘት ሄጄ ሳለ የተሳፈርንበት መጓጓዣ በመንገድ መጨናነቅ ምክንያት ይቆማል፡፡ ቆመን በመጠበቅ ላይ ሳለን በመካከለኛ ዕድሜ ላይ ያለች ቱትሲ ሴትዮ ከገበያ ወደ ቤቷ ስትመለስ የወጣቶች ቡድን ከቧት በመስኮት አየሁ፡፡ ልጆቹ እንደዋዛ ቦርሳዋን ነጥቀው፣ ጌጣጌጧን ቀምተውና የገዛችውን ሁሉ ወስደው ደበደቧት፡፡ ጫማዋን በኃይል አወለቁ፤ ቀሚሷንም ገፈፏት፡፡ ይህ እንግዲህ የተከሰተው በከተማው መካከል ሰው ይበዛበት በነበረ መንገድ ላይ ቀን በቀን ነው፡፡ ወጪ ወራጁ እንዳላየ ያልፋል እንጂ አንድ እንኳን ሃይ ለማለት ድፍረቱ ያለው አልነበረም፡፡

ዘልዬ ተነሥቼ በመስኮት እንዲያቆሙ መጮህ ስጀምር ዮሃንስ ሳብ አድርጎ አስቀመጠኝ፡፡ «ምንም አትበይ!» አለኝ፡፡ «በዚህ ከተማ ምን እየተከሰተ አንዳለ አታውቂም ኢማኪዩሌ፡፡ ከነዚህ ልጆች ጋር መነካካት የለብሽም - ይገድሉሻል፡፡»

«ለንድ ነገር እናድርግ እንጂ ዮሃንስ፡፡ ሌላው ቢቀር ጸጥታ አስከባሪ እንፈልግ፡፡»

«ጸጥታ አስከባሪ ምንም አያመጣም፡፡ እነዚህ ኢንተርሃምዌዎች የመንግሥት አካላት ናቸው፤ አታናግሪያቸው፤ በተለይ አንቺ ቱትሲ ስለሆንሽ እንዲያውም ባታዪአቸው ይሻልሻል፡፡»

ቀፈፈኝ፤ ረዳት-አልባነትም ተሰማኝ፡፡ ልጆቹ ጥለዋት ሲሄዱ ያቺ ምስኪን ከመሬት ለመነሳት ስትውተረተር ተከታተልኳት፡፡ የውስጥ ልብሷንና ሻሽ ብቻ ለብሳ ባዶ እግሯን እያነከሰች ሄደች፡፡

ሴትዮዋ በመንገዱ ስትዘልቅ እያየሁ *ለንደነዚህ ዓይነት ሰይጣናት መንገዶቻችንን ለንዲቆጣጠሩ ከፈቀድን በከፋ ችግር ውስጥ ነን ሰል አሰብኩ፡፡*

ከተወሰኑ ወራት በኋላ ከዚህ የባሰ የሚረብሽ ክስተት ገጠመኝ፡፡ ዳማሲንና እኔ ከማታባ ወደ ኪጋሊ ለሠርግ እንሄዳለን፡፡ ረጅም፣ ወበቃማና አቧራማውን ጉዞ እያገባደድን ሳለን የመንገደኞች ማጓጓዣ ተሽከርካሪያችን ድንገት ቆመ፡፡

ቢያንስ 300 የሚሆኑ ኢንተርሃምዌዎች መንገዳችንን ዘግተው ቆመዋል፤ የሁሉም አለባበስ ለዓይን ይቀፋል፤ አስተያየታቸውም እጅግ ያስፈራል፡፡ ብዙዎቹ አላፊ

አግዳሚው ላይ እየጮሁና እየተሳሰደቡ በቡድን ሲጨፍሩ የጠጡ ወይንም አደንዛዥ እጽ የወሰዱ ይመስላሉ። ነጂው ወደፊት ለመሄድ በጣም ስለፈራ ተሽከርካሪውን ወደኋላ ሊመልሰው እንደሆነ ነገረን። አብረነው የሁለት ሰዓቱን ለውጥ መንገድ እንድንሄድ፣ አሊያም ወጥተን በእግራችን እንድናዘግም አማራጭ ሰጠን።

«ተሽከርካሪው ውስጥ እንቆይ» አለ ዳማሲን። «እነዚህ ሰዎች አብደዋል።» እኔ ግን በተለይ በነዚህ ወረበሎች ተግባር ለመፍራት ባለመፍቀዴና በሌሎችም ምክንያቶች ተሽከርካሪው ላይ መቆየቱን አልመረጥኩትም።

«እንውረድ እንጂ ሠርጉ ያመልጠናል እኮ» አልኩት። «በእግራችን ብናዘግም ቤተ-ክርስቲያኑ ጋ አሁን እንደርሳለን።»

ከተጓጉቹ ግማሽ ከሚሆኑት ጋር ወረድን። እንደወጣንም አልፏቸው የሚሄደውን ሰው መታወቂያ ከሚያዩት ኢንተርሃምዌዎች ብዙዎቹ ገጀራ እንደያዙ አየን። ንዴት ተሰማኝና «ማነው መብቱን የሰጣቸው?» ስል ጠየቅሁ።

ዳማሲን ተጨንቆ «ብንመለስ ጥሩ ይመስለኛል፣ ኢማኪዩሌ። ስለነዚህ ሰዎች መጥፎ ነገሮች ሰምቻለሁ። ተይ በእግራችን ወደ ቤታችን እንመለስ» አለኝ።

«*በእግራችን?* በተሽከርካሪ አራት ሰዓት የፈጀብን በእግራችንማ በሦስት ቀንም አያልቅልን። ደግሞ እውነት እነዚህ ሰዎች ራሳቸውን እንደ ጸጥታ አስከባሪ አደራጅተው እኛ ቱትሲዎች ስለሆንን ብቻ ጉልበታቸውን ሊያሳዩን አይገባም።»

የዳማሲን ፊት ላይ ከሚነበበው ፍርሃት ይልቅ የኢንተርሃምዌዎቹ ነገር ቀላል ሆኖ አገኘሁት። ሁልጊዜ ሳቂታ ገጽታ የነበረውና ምናልባትም ከማውቃቸው ሰዎች ሁሉ ጠንካራው ነበር። በዚያን ጊዜ ግን በእርግጥ እንደፈራ አየሁ። ለወትሮው ምን እንደሚሻል አጠይቀው የነበረ ቢሆንም አንዳች ነገር ወደፊት እንድሄድ ገፋፋኝ።

«ና አልፈናቸው እንሂድ» አልኩት። «ምንም አንሆንም።»

«ያንን እንዴት አወቅሽ? እንደማይገድሉን ያሳሰበሽ ምንድነው? መንግሥት የፈለጉትን እንዲፈጽሙ ይፈቅድላቸዋል። ጸጥታ አስከባሪ አይነካቸውም።»

«ችግር በሚገጥመን ቁጥር የምትለውን እናድርግ ዳማሲን። እንጸልይ፤ እግዚአብሔር እንደሚጠብቀንም እንተማመን።»

ከቁጡ ጽንፈኞቹ ቡድን ኦሥር እርምጃ ርቀት ላይ በመንገዱ ዳር ቆመን ጸለይን። እግዚአብሔር ለአጭሯ መልዕክት ይቅር እንዲለኝ ጠይቄው በደኅና ወደ ቤተ-ክርስቲያኑ እንደርስ ዘንድ ግን የእርሱን ድጋፍ እንደምንፈልግ ነገርኩት። ወደኬላው ሄድኩ፤ የተወሰኑ ወጣት ወንዶች አይተውኝ በገጀራዎቻቸው ጭኖቻቸውን መታ መታ ያደርጋሉ።

«አይ በፍጹም፣ አይሆንም ኢማኪዩሌ... ስለዚህ ነገር እርግጠኛ ነሽ?»

«አዎን፣ አዎን በቃ ምንም እንዳልተከሰተ ሁን - እንዲያውም ምናልባት መቁጠሪያህን ከኪስህ ብታወጣ ሳይሻልህ አይቀርም፡፡»

ወደ ኢተርሃምዌዎቹ ስንሄድ መቁጠሪያዬን በእጇ አጥብቄ ይዣለሁ፡፡ ደርዘን የሚሆኑት ከበቡን፣ ላይ ታች አዩኝና መታወቂያ ደብተራችንን እንድናሳይ ጠየቁን፡፡ በመጀመሪያ ዓይናቸው ላይ ትከ ብዬ አየኋቸው፡፡ ከዚያም ፈገግ አልኩ፡፡ በመጨረሻም ሰነዶቹን ሰጠኋቸው፡፡ በጣም ደፋር በመሆን እንዳስቸገርኳቸው ታየኝ - አንዲት ቱትሲ ሴት እነርሱንም ሆነ ገጀራዎቻቸውን ለምን እንደማትፈራ ሊገባቸው አልቻለም፡፡ መታወቂያዎቻችንን መልሰው ሰጥተውን አሳለፉን፣ ሆኖም ግን በዳማሲን ዓይኖች ውስጥ ያየሁትን ፍራቻ በፍጹም አልረሳውም፡፡ ሲፈራ ሳየው የመጀመሪያ ጊዜዬ ሲሆን በሩዋንዳ ላይ አንዳች ከፉ ነገር እንደመጣባት የሚያሳየውን ስሜቴን ላናውጠው አልተቻለኝም፡፡

መንገድ ከተዘጋብን ከዚህ ገጠመኝ ከአንድ ወር በኋላ ርዕሰ-ብሔር ሃብያሪማና ወደ ታንዛኒያ ሄደው ከቱትሲ አማጽያን ጋር የሰላም ስምምነት ተፈራረሙ፡፡ ስምምነቱ የእርስ በርስ ጦርነቱን አቁሞ ቱትሲዎችን ሀገራቸውን በማስተዳደር ላይ ሚና እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ ግሩም ሐሳብ ይመስላል - ሩዋንዳ ሰላም ይሰፍንባትና ቱትሲዎችና ሁቱዎችም በመግባባት እኩል ዜጎች ሆነው ይኖሩባታል ስል አሰብኩ፡፡

ይህ የሰላም ተስፋ ግን ብዙ ተቃውሞዎችን አነሳሳ፤ መጠነ-ሰፊ ሁከትንም ቀሰቀሰ፡፡ ከነዚያ ያየለ ሁከት እንደሚመጣም ማስፈራሪያዎች ተሰነዘሩ፡፡ ስምምነቱ በተፈረመባት ደቂቃ ከሩዋንዳ እጅግ አደገኛ ወታደራዊ መኰንኖች አንዱና የኢንተርሃምዌ ዋና አዛዥ የነበረው አስፈሪው ኮሎኔል ቲዎኔስቴ ቦጎሶራ ከስምምነቱ አሻፈረኝ ብሎ ይወጣል፡፡ ቦጎሶራ «አባብ ቱትሲ» ብሎ ከሚጠራው ከሩአግ መሪ ከፖል ካጋሜ ጋር ርዕሰ-ብሔር ሃብያሪማና እጅ ለእጅ ሲጨባበጡ በማስተዋሉ ተጠይቋል፡፡ ከዚያም ከቱትሲዎች ጋር በምንም ዓይነት ስምምነት እንደማያደርግ ምሎ ወደ ሩዋንዳ በመመለስ «ለፍጅት ለመዘጋጀት» ቃል ገባ፡፡

በትክክል ያደረገውም ያንን ነው፡፡

ምዕራፍ 5
ወደ ሀገር ቤት

ሁልጊዜ ጠዋት ከእንቅልፌ ስነቃ የጥላቻ ድምፅ እሰማለሁ፡፡ የአር.ቲ. ኤል. ኤም. ሬድዮ የጥላቻ ድምጾች በመኝታ ቤቴ መስኮት ገብተው ህልሞቼ ውስጥ እስኪደነቀሩ ሌሊቱን በሰላም ተኝቼ አሳልፋለሁ፡፡ ልብ ይበሉ፣ በሦስተኛ ዓመት የዩኒቨርሲቲ ቆይታዬ አር. ቲ. ኤል. ኤም. በጽንፈኛ ሁቱዎች ዘንድ አዲሱና በጣም ታዋቂው ሬድዮ ጣቢያ ለመሆን ችሏል፡፡ ጸረ-ቱትሲ መርዝን የሚረጭ የተለየ የጥላቻ መሣሪያ ወጥቶታል፡፡

ሁሌ «ስለ ሁቱ የበላይነት» የሚጮህ አካል-አልባ ክፉ ድምፅ ሆነ፡፡ የሁቱ የበላይነትም ሁቱዎችን በቱትሲ ወዳጆቻቸውና ጎረቤቶቻቸው ላይ እንዲነሱ የሚያደርግ ተናዳፊ ተርብ ለመሆን ቻለ፡፡ «እነዚያ በረሮ ቱትሲዎች ሊገድሉን ወጥተዋል፡፡ አትመኗቸው… እኛ ሁቱዎች ቀድመናቸው ልንነሳ ይገባናል! መንግሥታችንን ገልብጠው ሊያሳድዱን እየዶለቱብን ነው፡፡ በርዕሰ-ብሔራችን ላይ አንዳች ነገር ቢከሰት ሁሉንም ቱትሲዎች ወዲያውኑ ማውደም ግድ ይለናል! እያንዳንዱ ሁቱ ሩዋንዳን ከነዚህ ቱትሲ በረሮዎች ለማጽዳት እጅ ለእጅ መያያዝ አለበት! የሁቱ የበላይነት! የሁቱ የበላይነት!»

ይህን በመሰለ አጉላኛ ሁኔታ ከእንቅልፌ እነቃለሁ፡፡ በእርግጥ ዘገባዎቹ እጅጉን በሚያስጠላ ሁኔታ እንጭጭ በመሆናቸው አልፎ አልፎ ያሥቃሉ፡፡ እነዚያን የልጅ ስድቦችና ልቅ ማስፈራሪያዎች ማንም ሰው ከምር ይቀበላቸዋል ብሎ ማመን አሰቸጋሪ ሲሆን መንግሥቱም የሕዝብ ንብረት የሆነውን የአየር ሰዓት ቱትሲዎችን ለማስፈራሪያ መፍቀዱን ማወቁ ይረብሻል፡፡ በወቅቱ ግን በሀገሪቱ በርካታ ስፍራዎች ቱትሲዎች በጽንፈኞች እየተገደሉ መሆኑን በሚገልጹ ወሬዎች ይበልጡን ተረበሸኩ፡፡

በዩኒቨርሲቲው ግቢ እንዳሉት ጓደኞቼ ሁሉ በመገናኛ ብዙሃን ስለሚተላለፉት ዘገባዎች ብዙ ላለማሰብና ላለማውራት ሞከርኩ፡፡ ቤተሰቤ ሁሌ አስደሳችና ልዩ ጊዜ የሚያሳልፍበት የትንሣኤ በዓል እየደረሰ ነው፡፡ ይህን የበዓል ወቅት ጎረቤቶቻችንን በመጋበዝና ወዳጅ-ዘመዶቻችንን በመጠየቅ እቤታችን እናሳልፋለን፡፡ የቤተሰቡ አባላት በሙሉ የምንገናኝበትን የትንሣኤን በዓል እቤቴ ማሳለፍ አምልጦኝ የማያውቅ ቢሆንም እየቀረቡ መጥተው ለነበሩት ፈተናዎቼ ለመዘጋጀት ያግዘኝ ዘንድ በትምህርት ቤቱ ለመቆየት ፈለግሁ፡፡ በፈተናው ጥሩ ውጤት ለማምጣት ቆርጫለሁ፡፡

ወላጆቼ ስልክ ስላልነበራቸው ለአባቴ ለምን እቤት እንደማልሄድ የሚያብራራ ደብዳቤ ጻፍኩለት፡፡ ወላጆቼ ሁልጊዜ ልጆቻቸው የተሻለ ውጤት ያመጡ ዘንድ

ከሚጠበቀው በላይ እንዲያጠኑ ስለሚፈልጉ ቅር እንደማይሰኙብኝ በጣም እርግጠኛ ነበርኩ።።

ይህ ለካ ትልቅ ስህተት ኖሯል!

አባቴ እቤት እንድሄድ የሚለምን ደብዳቤ ጻፈልኝ።። እንዲያውም የጠየቀኝ የትምህርት ቤት እረፍቴ እስኪደርስ ሳልጠብቅ *ወዲያውኑ* እንድሄድ ነው።። ከእርሱ ጋር እንድሆን እንደሚፈልግና እቤት ያላንዳች ረብሻ ማጥናት እንደሚቻለኝ ቃል ገባልኝ።። ልባዊ ተማጽኖው በዓይኖቼ እንባ ሞላባቸው።።

ውድ ልጄ፣

ትምህርት አንቺን ከኛ እንደነጠቀን ይሰማኛል።። እናትሽና እኔ እረፍትሽ እስኪጀምር በጉጉት እየጠበቅን ነው።። ምክንያቱም ከጀመረ አንቺ እቤት መጥተሽ እንደገና እንደ ቤተሰብ ስለምንኖር ነው።። መምጣትሽን እንፈልገዋለን፤ ወላጆችሽ ነን፤ እንወድሻለን፤ በእጅጉ እንናፍቅሽማለን - ይህን ሃቅ በፍጹም አትርሺው! ለሁለት ቀናት ቢሆንም እንኳን ልታዩን ልትመጪ ግድ ይልሻል፤ ጊዜውን ለሌላ ለምንም ጉዳይ መሰዋዕት እንዳታደርጊው።። ነዪልን፤ አብሮነትሽን እንፈልገዋለን ...

ደብዳቤውን አንብቤ ሳልጨርሰው ወደ ቤት ለመሄድ ወሰንኩ።። ከወላጆቼ ጋር ስድስት ቀናትን አሳልፌ ለፈተናዎቼ በሳምንቱ መጨረሻ ትምህርት ቤት ለመመለስ አቀድኩ።። የጉዞ ዝግጅቴን ሳደርግ የሳራ ታናሽ ወንድም የሆነው ኦገስቲን ከእኔ ጋር ለበዓሉ ወደ ወላጆቼ ቤት ሄዶ መዋል ይችል እንደሆን ጠየቀኝ።። ኦገስቲን የወንድሜ የቪያኒ የልብ ጓደኛ ሲሆን የመንፈቀ-ዓመቱን ትምህርቱን ኪጋሊ ላይ ካገባደደ በኋላ በትምህርት ቤት መኝታ ቤታችን ውስጥ ቆይቷል።። መለሎው፣ መልከ-ቀናውና አስደሳቹ የ18 ዓመቱ ኦገስቲን ከቪያኒ በቀር ማንም ሰው ፊት አያወራም።። እንግዳችን ቢሆንልን እንደምንደሰት ነገርኩት።።

ኦገስቲንና እኔ ማታብ ቅዳሜ ከሰዓት በኋላ ደረስን፤ የቤተሰቤም አባላት በመምጣቴ በእጅጉ ተደሰቱ።። በሳይንስ የድህረ-ምረቃ ትምህርቱን ለመከታተል ዓለም አቀፍ የትምህርት ዕድል ካገኘው ከኤይማብል በስተቀር ቤተሰቡ ተሟልቷል።። ኤይማብል አገሪቱን ለቆ ከ5 000 ኪሎሜትሮች በላይ ወደምትርቀው ሴኔጋል ሄዷል።። ዳማሲን በበኩሉ በታሪክ በሁለተኛ ዲግሪ ከተመረቀ ጀምሮ ከሚያስተምርበት ከኪጋሊ ተሳፍሮ መጥቷል።። ቪያኒም ከአዳሪ ትምህርት ቤት ተመልሷል።።

የመጀመሪያዋን ቀን ከዳማሲን የመንደር ወሬ ስሰማ፣ ጓደኞቼን ስጠይቅ፣ ከቪያኒ ጋር ስንጫወትና ስንከራከር አሳለፍኩ።። በመጭው ቀን፣ በትንሳኤ እለት፣ አብረን ጥሩ ምግብ በላን።። አምላክን ስለሰጠን ነገር ሁሉ አመስግነን በቤተሰባችንና በመንደራችን

ስላለው ስለ ሁሉም ሰው ደህንነት ጸለይን - በተጨማሪም ስለብቸኛው ቀሪ አባላችን ስለ ኤይማብል ልዩ ጸሎት አደረስን። በላያችን ያንጎበብ ከነበረው የፖለቲካ ውጥረት በስተቀር አዝናኝ ጊዜ በማሳለፍ ላይ ነን። ከወላጆቼ ጋር በመሆኔ ደህንነትና ችግር-አልባነት ተሰማኝ - ይህም የሆነው ምንም ነገር ቢከሰት ታጽናናን ዘንድ እናቴ ስለምትኖርና አባቴም እኛን የመከላከሉን ሥራ ስለሚሠራ ነው። ቢያንስ ያንን ነው ያሰብኩት ::

ይህ ምሽት የኛ ዓለም እስከዘላለሙ ልትቀየር ትንሽ የቀራት መሆኑን ለመገመት የሚያዳግትበት እንደወትሮው ያለ ምሽት መሆኑ ነው። ስለ ትምህርት፣ ሥራና በመንደሩ እየተከሰተ ስላለው ነገር እቤት ቁጭ ብለን እናወራለን። እናታችን ስለ ሠብሉ ስትነግረን አባታችን ደግሞ የቡና ጎብረት-ሥራው የትምህርት ወጪያቸውን ስለሚሸፍንላቸው ሕፃናት ያወራልናል። አገስቲንና ቪያኒ ይቃለዳሉ። እኔ በበኩሌ እየተዝናናሁና ሁሉንም ነገር እየታዘብኩ እቤት በመሆኔ ደስተኝነት ተሰምቶኛል።

ያልተደሰተው ዳማሲን ብቻ ነው። ሁልጊዜ በዓል ላይ ሕይወት የሚዘራው እሱ የነበረ ቢሆንም ምሽቱን ሙሉ ሲብሰለሰልና በሥጋት ሲናጥ ቆይቷል።

«ዳማሲን ምን ሆነሃል?» ስል ጠየኩት።

ወንድሜ ቀና ሲል ዓይኖቻችን ተገጣጠሙ። ከዚያም በኋላ ዝም ብሎ መቆየት አልተቻለውም። በተጣደፈ ቃላትና ስሜት ሸክሙን እኔ ላይ አቃለለ - «ኢማኪዩሌ አይቻቸዋለሁ፤ ገዳዮቹን አይቻቸዋለሁ። ወደ ቦን ቤት ስንሄድ በርቀት አይተናቸዋል። የኢንተርሃምዌን ባለ ደማቅ ቀለማት ልብሶች ለብሰዋል፤ የእጅ ቦምቦችንም ይዘዋል፤ *ቦምቦች ነበሯቸው ኢማኪዩሌ!*» ሲል ድምጹ አሰቀቀኝ።

ሁሉም ሰው ንግግሩን ስለሰማው ቤቱ እርጭ አለ። ወላጆቼ እርስ በርሳቸው ተያዩና ዳማሲንን አዩት።

አባቴ ልጁን ለማረጋጋት ሲል «ምናልባት ሐሳብህ አሸንፎህ እየወጣ እንዳይሆን» አለው። «ብዙ መጥፎ ወሬ ይሰማል። ሰዎችም አደጋን በሌለበት እያዩት ነው።»

«አይ፣ ዝም ብዬ እኮ እየቃዠሁ አይደለም» አለ ዳማሲን በድንገት ቆሞ የጉዳዩን አጣዳፊነት በሚያንጸባርቅ መልኩ በመናገር። «ያየሁት ያንን ብቻም አይደለም። በአካባቢው ያሉት የሁሉም የቱትሲ ቤተሰቦች ስም ዝርዝር አላቸው፤ የኛም ስም በዚያ ስም ዝርዝር ላይ ሰፍሯል! በዝርዝሩም ላይ ያሉትን ዛሬ ማታ መግደል ለመጀመር አቅደዋል!»

ዳማሲን በቤቱ ውስጥ እየተንቆራጠጠ አባቴን ይለምን ገባ። «አባባ፣ *ጸባከህ* እንሂድ፤ተለመነኝ። ነገሩን ማድረግ በሚቻልበት በዚህ ሰዓት ከዚህ ስፍራ መጥፋት አለብን። ቁልቁለቷን ወርደን፣ ጀልባ ፈልገን፣ የኪቩ ሐይቅን አቋርጠን እኩለ-ሌሊት

ላይ ዛየር በደኅና መግባት እንችላለን፡፡ ይሁን እንጂ ጊዜያችንን ሳናባክን አሁኑኑ መሄድ ግድ ይለናል፡፡»

ዳማሲን ያለወትሮው በድንገት እንደዚያ መጮሁ ሁላችንንም አስጨነቀን፡፡ ወንድሜን ስለማውቀው ምሽቱን በሙሉ ሲያወጣና ሲያወርድ ብሎም ሲጨነቅ አምሽቶ መሆን አለበት እላለሁ፡፡ የማምለጫው ዕቅድ እስኪመጣለት ድረስ ግን ምንም ሊለን አልፈለገም፡፡

«ቆይ ዳማሲን ለደቂቃ ረጋ በል» አለ አባቴ፡፡ «እናትህንና እህትህን እያበሳጨሃቸው እኮ ነው፡፡ ዛሬ በትክክል አየሁት፣ ሰማሁት ብለህ የምታስበውን ነገር ምንነት እንተንትነው፡፡ በደነገጥክና በፍርሃት በራድክ ጊዜ ውሳኔዎች ላይ ከደረስክ ስህተት ትፈጽማለህ፡፡ ሁሉንም ነገር በጥንቃቄ እንየው፡፡ እሺ፣ የተባለውን የሥም ዝርዝር በትክክል አይተኸዋል?»

ዳማሲን በአባቴ ጥርጣሬ ቢበሳጭም ዝርዝሩን በዓይኑ እንዳላየ ግን አመነ - ከጓደኞቹ ግን ስለዚህ ነገር ሰምቷል፡፡ ያያቸው ሰዎች ኢንተርሃምዌ ስለመሆቸውም እርግጠኛ ነው፡፡

«አየህ፣ እንዳልኩት ነው» አለ አባቴ፡፡ «ሁሉም ሰው ተደናግጧል፡፡ አንተም ብትሆን የራስህ ስሜት ሁኔታዎቹን ከሆኑት በላይ እያጋነናቸው ነው፡፡ ይህን ሁኔታ እኔ ካሁን በፊት አይቼዋለሁ፡፡ ስለ ገዳይ ቡድኖች የሚወሩ አሉባልታዎችንና ስለ ሟቾች ዝርዝር የሚነዛ ወሬ ትሰማለህ፣ ግን ከተወሰኑ ቀናት በኋላ ሁሉም ነገር በእጅጉ ተጋኖ እንደነበር ትረዳዋለህ፡፡ በበኩሌ በአሉባልታ ምክንያት ቤተሰቤን አንጋግቼ አልሸሽም፡፡ ፈሪዎች ለነሱ ግልጽ የሚመስላቸው ምናባዊ እይታ ስላላቸው ብቻ ቤታቸንንና የለፋንበትን ሁሉ ትተን አንሰደድም፡፡»

«ግን አባባ» ጣልቃ ገባሁ፤ «ዳማሲን ፈሪ የሚባል ዓይነት አይደለም፡፡ ጎበዝና እንዲህ በቀላሉ የማይታለል ነው፡፡ ምናልባት ብንሰማው ሳይሻለን ይቀራል?»

ተጨነቅሁ፡፡ በእርግጥ ኢንተርሃምዌዎች የሚገደሉ ሰዎችን ሥም ዝርዝር ይዘው በዚያ ምሽት ሰው መግደላቸው እውነት ከሆነ ወደ እኛም በማናቸውም ደቂቃ ይመጡብናል፡፡

«በእርግጥ ዳማሲን እንደሚለው ማድረግ ይኖርብናል» በማለት አባቴን ገፋፋሁት፡፡ «በሬድዮ ስንሰማ የቆየናቸውን ነገሮች ሁሉ እስኪ አስቧቸው፡፡ የምር አልመሰሉኝም ነበር፤ ግን ተሳስቻለሁ፡፡ ሁሉም ቱትሲዎች መገደል አለባቸው ይላሉ፡፡ ምናልባት ዳማሲን ልክ ሳይሆን አይቀርም - እኔም አሁን መሄድ አለብን ባይ ነኝ!»

«አይሆንም ኢማኪዩሌ፣ አንሄድም፡፡ መንግሥት ነገሮችን እያሻሻለ ነው፤ ሰላምም በቅርቡ ይሰፍናል፡፡ በሬድዮ እየቀሰቀሱ ያሉት ሰዎች አብደዋል፡፡ ሰዉም ከመጤፍ

አይቆጥራቸው! አትጨነቂ፡፡ ተረጋግተን በዓላችንን እናሳልፍ፡፡ የግድያ ዝርዝር ብሎ ነገር የለም፤ ሊገድለን የሚመጣም አለ ብለሽ አትስጊ፡፡ ዕድሜ ብዙ አሳይቶኛል» አለ አባቴ ደከም ባለ ፈገግታ፡፡ «እስኪ በፊጠራችሁ ተቀምጠን አብረን ራታችንን እንብላ፡፡»

የአባቴ ማረጋገጫ ሁሉ ነገር ጥሩ እንደሚሆን ለጊዜው አሳመነኝ፡፡ በኋላም ሁላችንም በመመገቢያ ክፍላችን ለእራት ተሰባሰብን፡፡ ምንም እንኳን ዳማሲን በአባታችን መከራከሪያዎች ፈጽሞ እንዳላመነ ለማየት የቻልኩ ቢሆንም በዚያ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ወንድሜ በራስ በመተማመን ስሜት ተቀምጦና እንደ ወትሮው ለመሆን እየጣረ ቀልድ የተሞላባቸውን ዘፈኖች መዝፈን፣ በሰፈራችን ባሉት ሰዎች ላይ መቀለድና ቪያኒን ስለ ሴት ጓደኞቹ በነገር ጠቅ ማድረጉን ተያያዘው፡፡ ግን ብዙ ባሳቀን ቁጥር እያስመሰለ እንደሆነ እርግጠኛ ነበርኩ፡፡ በአስደሳች ፈገግታው ሸፋፈነው እንጂ ወንድሜ በእጅጉ ተሸብሯል፡፡

የዚያን ምሽቱ እራት የቤተሰባችን የመጨረሻው መሆኑን ባውቅ ኖሮ ደስ ባለኝ፡፡ ከመቀመጫዬ ተነሥቼ አምላክን ስለ ሁሉም የቤተሰቤ አባላት አመሰግነው ነበር፡፡ በዚያ ገበታ ዙሪያ የተሰበሰቡትን ሁሉንም ስለወደዱኝ ምን ያህል እንደምወዳቸውና እንደማመሰግናቸው በነገርኳቸው፡፡ ግን የት አውቄ፡፡

ወደ መኝታ ከመሄዳችን በፊት ሁልጊዜ እናደርግ እንደነበረው አንድ ላይ የቤተሰብ ጸሎታችንን አደረስን፡፡ እናቴ ስማ ተሰናበተችን፤ አባቴም ምንም መጥፎ ነገር እንደማይከሰት ቃል ገብቶ ሰላማዊ እንቅልፍ ተመኘልን፡፡

የወላጆቻችን መኝታ ቤት በር መዘጋቱን አንደሰማን አራታችን - ዳማሲን፣ ቪያኒ፣ አገስቲንና እኔ - በዋናው ክፍል ተሰበሰብን፡፡ ዳማሲን በእለቱ ስለሰማቸው ወሬዎችና ስላያቸው ነገሮች ቢያንስ ለአንድ ሰዓት ያህል አወራልን፡፡ የዳማሲንን ስጋት ከምር ለመቀበል አባቴ ባሳየው ቸልተኝነት የተነሣም ተጨነቅን፡፡

«በነገራችን ላይ አባታችሁን አለማከበር እንዳይመስላችሁ እንጂ» አገስቲን አንሾካሾከ፡፡ «ደግሞ ከታላላቆቼ ጋር መሟገት እንደሌለብኝ አውቃለሁ፡፡ ቢሆንም ግን አባታችሁ የተሳሳቱ ይመስለኛል፡፡ በዳማሲን ሐሳብ እስማማለሁ - እዚህ መቆየት አደገኛ ይመስለኛል፡፡ የቤተሰባችሁ ስም በሚገደሉ ሰዎች ዝርዝሩ ላይ ካለ ይመጣሉ፣ ልናስቆማቸውም የምንችልበት ምንም መንገድ የለንም! አባታችሁም እንሂድ በሚለው ጉዳይ ላይ ሃሳባቸውን የሚቀይሩ ስለማይመስለኝ ለሁኑኑ ወላጆቻችሁን ትተን ብንሄድ ሳይሻል አይቀርም» ሲለን በጸጥታ ተዋጥን፡፡ ወደ ኪቩ ሐይቅ በአንድነት ሮጠን ወደ አንድ አነስተኛ በእጅ የምትንቀሳቀስ ጀልባ መዝለልን እንደፈለግን እርግጠኛ ነኝ፡፡ ግን ወንድሞቼና እኔ ወላጆቻችንን ደኅና ሁኑ ሳንል ልንሄድ

አንችልም፡፡ በተጨማሪም አባታችን በቤተሰቡ ውስጥ ውሳኔዎችን ማሳለፉን ስለለመድነው የእርሱን መርህ መከተል ልማዳችን ነው፡፡ ከዚህም በላይ አገስቲንና ቪያኒ በየተቀመጡባቸው ወንበሮች ላይ እንቅልፍ እያዳፋቸው ስለሆነ በጣም ዘግይተናል የሚል ምክንያት አመጣን፡፡ ስለዚህ ዳማሲንና እኔ አባታችንን እንደገና ለማናገር እስከ ጠዋት መጠበቅ እንዳለብን ወስነን ሁላችንም ወደየመኝታችን አመራን፡፡

መኝታ ቤቴን እንደ ጸሎት ቤቴ እቆጥራታለሁ፡፡ በስተቀኜ ባለው የምሽት ጠረጴዛዬ መጽሐፍ ቅዱሴንና የኢየሱስንና የድንግል ማርያምን ሐውልቶች አስቀምጬ ከአምላኬና ከራሴ መንፈሳዊ ኃይል ጋር እገናኛለሁ፡፡ አልጋዬ አጠገብ ተንበርክኬ ሐውልቶቹን እያየሁ እግዚአብሔር ቤተሰቤን ከአደጋ ይጠብቅልኝ ዘንድ ጸለይኩ፡፡

አጠገቤ የተቀመጠ ለዳማሲን የገዛሁት የልደት ካርድም አለ፡፡ ሃያ ሰባተኛው የልደት በዓሉ ተቃርቧል፡፡ ለቀናትም ምን ያህል እንደምወደውና እንደማደንቀው የሚገልጽ ግጥም ለመጻፍ ሞክሬያለሁ፡፡ ወላጆቻችን በግልጽ እንዴት እንደምንዋደድ እርስ በርስ እንድንገልጽ ባያስተምሩንም እኔ ያንን ልማድ ለመቀየር ፈልጌያለሁ፡፡ አዲሱ ተግባር በጣም ከምወደው፣ ከማከብረው እንዲሁም በዓለም ላይ ከማንም በላይ ከሚያበረታታኝ ከዳማሲን ሌላ ታዲያ በማን ይጀመራል?

ልጆች ሳለን ካጠፋሁና እንዳይሆን ካደረግሁ ዳማሲን ይቆጣኛል፡፡ ቃላቱ ይናደፉና ያበሳጩኝ የነበረ ቢሆንም በኋላ ላይ ግን የመከረኝን ሳስበው ትክክል እንደነበረ ይገባኛል፡፡ ልጅ ሆኖ እንኳን የማስተማር ተሰጥዖና ከዕድሜው በላይም ጥበብ ነበረው፡፡ በአሥራዎቹ ዕድሜዎች ሳለሁ የድምጹን ማራኪነትና ልግስናውን እያየሁ እግዚአብሔር እንደ እርሱ ያደርገኝ ዘንድ እጸልይ ነበር፡፡ አልባሳቱን ለደሆች በመቸር፣ በህመም፣ በድህነት ወይንም በአእምሮ ችግር የተገፉ ሰዎችንም በማረጋጋት ሰዓታትን ሲፈጅ እከታተለዋለሁ፡፡

ዳማሲን የመንደራችን ኮከብ ነው፡፡ በዚያን ምሽት እንደነገሩ ጋደም ብዬ ወንድሜ ለኔ ምን ማለት እንደሆነ አሰብኩ፡፡ ትንሽ ፈገግ አንደማለት ብዬ ቃላቱን ባነበበ ጊዜ ምን ያህል ሃፍረትና ደስታ እንደሚሰማው በማሰብ ብዕሬን አንስቼ በልደት ካርዱ ላይ በጻፍኩት ግጥም ላይ የተወሰኑ መስመሮችን አከልኩ፡፡ በፊቴ ላይ የነበረው ፈገግታ ሳይጠፋ መብራቴን አጥፍቼ ጋደም አልኩ፡፡

በሬ ብርግድ ብሎ ሲከፈት ዓይኖቼ ለደቂቃዎች ያህል የተከደኑ መሰለኝ እንጂ ተኝቼ ነቃሁ አልልም፡፡ ከእንቅልፌ ነቅቼ ተቀምጬ መንጋቱን ተገነዘብኩ፡፡ በግራጫው የመኝታ ቤቴ ብርሃን የዳማሲንን የተሸበረ ፊት እያየሁ በሆዴ «የባሰ አታምጣ» አልኩ፡፡ «ምንድነው ዳማሲን? ገዳዮቹ መጡ እንዴ? ገዳዮቹ እዚህ ናቸው

እንዴ?» ስል አንሾካሾክሁ፡፡ ፍርሃት የሚንጸባረቅበትን የራሴን ድምፅ እንኳን መስማት አልተቻለኝም፡፡

ወንድሜ አንዲት ቃል አልተነፈሰም፡፡ በሩ ላይ እንደቆመ ትንፋሹን ለመዋጥ ሲሞክር እሰማዋለሁ፡፡ መጨረሻ ላይ ሲናገር ድምጹ ከጥልቅ ጉድጓድ ጥግ የሚወጣ ይመስላል፡፡ «ተነሺ ኢማኪዩሌ - በፈጠረሽ ተነሺ፡፡ ርዕሰ-ብሔሩ ሞተዋል!»

«ምን? ርዕሰ-ብሔሩ ሞተዋል ስትል ምን ማለትህ ነው?» ስል ጮህኩበት፡፡ የሰማሁትን ማመን አልቻልኩም፡፡ ርዕሰ-ብሔሩ በሩዋንዳ ሰላምንና እኩልነትን ለማምጣት ቃል ገብተዋል፡፡ እንዴት ይሞታሉ?»

«ርዕሰ-ብሔር ሃብያሪማና ምሶዋል ማለቴ ነው! ትናንት ማታ ነው የተገደሉት፡፡ ጠያራቸው[5] በሰማይ ሲበር ተመቶ ነው፡፡»

ከተወሰኑ ቀናት በፊት በሬድዮ የሰማሁት ታሰበኝ - «ርዕሰ-ብሔራችን አንድ ነገር ቢሆኑ ሁሉም ቱትሲዎች ያልቃሉ!» የሚለው ዛቻ፡፡

በፍጥነት ከአልጋዬ ተነሥቼ በድንጋጤ የሚለበስ ነገር እፈልግ ጀመር፡፡ ጅንስ ሱሪዬን በለበስኩት ረጅም አረንጓዴ ሌሊት የምለብሰው ቀሚሴ ስር አጠለቅሁ፡፡ በወንድሜም ፊት ስለለበስኩ አፈርኩ፤ ይህ በሕይወቴ በፍጹም አድርጌው የማላውቀው ነገር ነው፡፡

«ርዕሰ-ብሔሩ ተገድለዋል፤ የሆነ አካል ርዕሰ-ብሔሩን ገድሏቸዋል» እያልኩ በተምታታበትና ባለማመን በተሞላ ሁኔታ ለራሴ ማጉተምተም ቀጠልኩ፡፡ ከመኝታ ቤቴ መስኮት ላይ ግርዶሾቹን ገላልጬ ወደ ውጪ አየሁ፡፡ የኔ ሐሳብ ይሁን አይሁን ባላውቅም መንደሩን ክብድ የሚል ቢጫ ጭጋግ ሸፍኖታል፡፡

«ሰማዩ ራሱ እየተቀየረ ነው» አልኩ አልጋው ላይ ተቀምጬ ራሴን በእጆቼ ይዤ፡፡ «ወይኔ ዳማሲን ሁላችንም ልንሞት ነው፡፡ በቃ አሁን ይመጡና በእርግጠኝነት ይገድሉናል፡፡»

ወንድሜ ተቀምጦ አቀፈኝ፡፡ «አዳምጭኝ ኢማኪዩሌ፣ አንምትምን» ሲል በልበ-ሙሉነት ተናገረ፡፡ «እኛን ከዚህ ነገር ጋር የሚያያዘን አንዳች ነገር የለም፡፡ ርዕሰ-ብሔሩ በታንዛኒያ ይካሄድ ከነበረ የሰላም ድርድር ከቡሩንዲው መሪ ጋር በመመለስ ላይ ነበሩ፡፡ ጠያራው ኪጋሊ ላይ ለማረፍ ሲሞክር ነው የተመታው... ኪጋሊ ላይ! አየሽ እዚህ ድረስ መጥቶ እኛን ማንም አይወነጅለንም፡፡»

[5] አውሮፕላን

በወቅቱ ዳማሲን ለእኔ ጀግና ለመሆን ቢሞክርም ቀሽም ተዋናይ ወጣው፡፡ እኔን ለማሳመን እየጣረ እንዳለው ሁሉ ራሱንም ለማሳመን ሙከራ እያደረገ መሆኑን አውቃለሁ፡፡

«ምናልባት አሁን እርሳቸው ስለሞቱ ሁኔታዎች ሊሻሻሉልን ይችላሉ» ሲል ቀጠለ፡፡ «ብዙዎች እነዚህን የሰላም ድርድሮችና የሃብያሪማናን የለዘብተኛ መንግሥት እቅድ አልደገፏቸውም፤ ስለዚህ ሞታቸው በእርግጥ ውጥረቶቹን ሊያረግብ ይችላል፡፡ እንደዚህ አትፍሪ፣ ኢማኪዩሌ፡፡ ነይ ውጪ እንውጣ፡፡ ሁሉም ሬድዮ እያዳመጠ እዚያ ነው ያለው፡፡»

እጇን ይዞ ወላጆቹ፣ ቪያኒና አገስቲን ሬድዮ ለማድመጥ ወደተቀመጡበት ወሰደኝ፡፡ ዜና አንባቢው የርዕሰ-ብሔሩ ጠያራ ከተመታ ከደቂቃዎች በኋላ በዋና ከተማዋ በሙሉ የመንገድ ኬላዎችና ወታደራዊ የፍተሻ ጣቢያዎች እንደተቋቋሙ አስታወቀ፡፡ በዚያን ምሽትም ኪጋሊ ላይ ሃያ የሚሆኑ ቱትሲ ቤተሰቦች መገደላቸውን አረዳን፡፡

ዘገባ የሚለውን ቃል ላለመጠቀም አንገራግራለሁ፡፡ ምክንያቱም የሬድዮው ሰውዬ የገዳዮቹ መሪ እንጂ ጋዜጠኛ ስለማይመስል ነው፡፡ የርዕሰ-ብሔሩ ልዩ ጥበቃ ጓድ አባላት ፍትህን በራሳቸው እጅ አስገብተው የመሪያቸውን ደም ለመበቀል ቱትሲዎችን መግደላቸውን ሲያስታውቅ የግድያዎቹን አግባብነት ሊያረጋግጥ በመሞከር ነው፡፡ የቤተሰብ አባላትን በሙሉ ወደ መንገድ እየጎተቱ አውጥቶ በግፍ መግደልን ሙሉ በሙሉ ምክንያታዊ አስመስሎ ተናግሯል፡፡

በማስከተልም ወታደሮቹ እስከዚያ ሰዓት ድረስ በኪጋሊ የገደሏቸውን ሰዎች ስም ዝርዝር አነበበ፡፡ አምስተኛውም ስም የአጎቴ የትዋዛ ሆኖ አረፈው፡፡

«ትዋዛን ገደሉት?» እናቴ ዓይኖቿን በእጆቿ ቶሎ ሸፍና ራሷን ባለማመን እየነቀነቀች ጮኸች፡፡ «ትዋዛን ለምን ይገድሉታል? እሰው ጥሞ አይደርስ፡፡»

በባለፈው ምሽት የማምለጥ እድላችን እንደተቃጠለብን ሲገባን የቤተሰቤ አባላት በሙሉ በአሰቃቂ ጸጥታ ተዋጥን፡፡ አባቴ እንደገና ፍራቻችንን ለማቅለል ጣረ፡፡ «በዋና ከተማዋ የሰዉ ስሜት በጣም እየተጋጋለ ነው፡፡ አብዛኞቹ ወታደሮች የሚኖሩት እዚያ ስለሆነ ግድያዎቹም የሚፈጸሙት እዚያ ነው» አለ የነበረውን እውነታ በማገናዘብ፡፡ «በአንድ ወይም ሁለት ቀን ውስጥ ሁሉም ነገር ይረጋጋል፤ ምናለ በሉኝ፡፡»

«ወደ ቤቴ ልሂድ መሰለኝ» አለ ቤተሰቡ ኪጋሊ የሚኖሩት አገስቲን፡፡ የትም ቦታ መሄድ የባሰ አደገኛ መሆኑን ስለምናውቅ ትኩር ብለን አየነው፡፡ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ በተከታታይ በራዲዮ በተነገሩ ማስታወቂያዎች ስጋታችን ተረጋገጠልን - «በየቤቶቻችሁ ቆዩ፡፡ መጓጓዝ ክልክል ነው፡፡ በመንገዶች ላይ መዘዋወር የሚችሉት

ወታደሮች ብቻ ናቸው፡፡ ከቤታችሁ ውጪ አትውጡ፡፡ የሕዝብ መጓጓጥ ስራ እንዲያቆም ተደርጓል፡፡ *ቤቶቻችሁን ትታችሁ እንዳትሄዱ!*»

«ሲመጡ እንዲያገኙን ተቀምጠን እንድንጠብቃቸው ይፈልጋሉ፡፡ እንደበግ ዝም ብለን እንታረድላቸዋለን!» አለ ዳማሲን ዓይኖቹ እየፈጠጡ፡፡ «ስሞቻችን በሚች ዝርዝራቸው ውስጥ ካሉ የት እንዳለን ያውቃሉ፤ እቤታችን መሆናችን ከእነርሱ የተሠወረ አይደለም፡፡»

የሚያዝያ 7፣ 1994 ማለዳ፣ ለእኛ ገና ባይታወቀንም የዘር ጭፍጨፋው ግን ተጀምሯል፡፡

ምዕራፍ 6

መመለስ አይታሰብም

እናቴ፣ አባቴ፣ ዳማሲን፣ ቪያኒ፣ ኦገስቲንና እኔ ቀኑን ሙሉ በግቢያችን ውስጥ በፍርሃት ተቆራምደን ሬድዮ ስናዳምጥ ዋልን። ከሀገራችን ውጪ የሚተላለፉት ዘገባዎች ተራ ሁቱ ዜጎች የመንግሥቱን ሰራዊትና የኢንተርሃምዌ ታጣቂዎችን ያልታጠቁ ንጹሃን ቱትሲዎችን በመግደሉ ተግባር ላይ እየተቀላቀሏቸው እንደሚገኙ ዘገቡ። የሀገር ውስጥ ጣቢያዎች በበኩላቸው ሁቱዎች ገጀራ እያነሱ ቱትሲ ጎረቤቶቻቸውን እንዲያጠቁ ያበረታቱ ገቡ።

እንደ ትንሽ ልጅ አደረገኝ - ወላጆቼ ምን እንደማደርግ እንዲመሩኝ ተመኘሁ። ከ1959 ጀምሮ ከፖለቲካ አለመረጋጋቶችና ከቱትሲ ጭፍጨፋዎች ስለተረፉ መቼም ምን ማድረግ እንዳለባቸው ማወቃቸው አይቀርም ስል አሰብኩ።

ብሔራዊው ሬድዮ ጣቢያ ሕዝቡ በየቤቱ እንዲቆይ አስጠነቀቀ፤ እኛም የወላጆቻቸውን ምክር እንደሚሰሙ ማለፊያ ልጆች ተቀበልነው። ከአጥራችን ውጪ ምን እየተከሰተ እንደነበር ለማወቅ በራችንን ለመክፈት እንኳን በጣም ፈራን። ከቅጥር-ግቢያችን ውጪ መንቀሳቀስ አደጋ ይኖረዋል ወይንም ሞት ያስከትላል ብለን እንደ እስረኛ እንቅስቃሴያችንን በቤት ውስጥ ገደብን።

ስልክ አልነበረንም፤ ቢኖርም ኖሮ እንኳን አብዛኞቹ የሀገሪቱ የስልክ መስመሮች ዝግ ናቸው። ሬድዮናችን ከሚያደርሰን ወሬ በቀር ከማንም ጋር ግንኙነት የምናደርግበት መንገድ አልነበረም። ራሴን ልስት መሆኑ አስኪሰማኝ ድረስ ስለ አሰቃቂዎቹ ግድያዎች ስንሰማ ለሰዓታት ተቀመጥን። ጥላ በረድ ሲል መጻሕፍቴን ሳብ አድርጌ ለፈተናዎቼ መዘጋጀት ጀመርኩ።

«እንዴት ይሆንልሻል ኢማኪዩሌ?» ሲል ዳማሲን ጠየቀኝ። «ለማጥናት የሚሆንሽን ጽናትስ ከየት አመጣሽው? ተመልሰሽ ትምህርት ቤት እንደምትገቢስ ለምን ታስቢያለሽ?»

ወንድሜ ከሰዓታት በፊት ተስፋ ስቆርጥ ሲያጽናናኝ እንዳልነበር አሁን ራሱም ተስፋ ቆረጠ። ለመበርታት ተራው የኔ ስለሆነ «መጨነቅህን ተው» አልኩት። «ይህን እናልፈዋለን፤ ሁኔታዎች ከተባባሱ በድንበሩ በኩል እንሸልካለን። እማማና አባባ ካሁን በፊት ይህን ዓይነቱን ችግር አልፈውታል። እምነት ይኑርህ።»

ስለ እውነት ለመናገር ግን እኔ ራሴ ያለኝ እምነት ተሟጧል - የማጠናው ከቤተሰቤ ጭንቀት ላይ ሐሳቤን ለማንሳት አስቤ እንጂ ለፈተና ለመዘጋጀት አልነበረም።

በእለቱ የሰማነው ብቸኛው አበረታች ዜና መነሻቸውን በዩጋንዳ ያደረጉት የቱትሲ አማጽያኑን መሪ የሩአጉን የፖል ካጋሜን መልዕክት ነው። በቱትሲዎች ላይ የሚፈጸሙት ግድያዎች ካላቆሙ በስተቀረ እየተፋለሙ ሩዋንዳን ለመውረርና ቱትሲዎችን ለመታደግ እስከመጨረሻው እንደሚጸኑ ቃል ገቡ። ካጋሜ ያንን ሲሉ መስማቱ ያበረታታል፤ ሆኖም ግን ብቸኛው «መልካም» ዜና የለየለት ጦርነት እንከፍታለን የሚል ማስፈራሪያ ብቻ በመሆኑ አዘንኩ።

በዚያ ምሽት ማናችንም ከጥቂት ደቂቃዎች በላይ አልተኛንም።

በሚቀጥለው ቀን በኪጋሊ ከሚኖሩት ከለዘብተኛ ሁቱዋ የሩዋንዳ ጠቅላይ ሚኒስትር ከአጋቴ ጋር የተደረገ የቢቢሲን የስልክ ቃለ-መጠይቅ ሰማን። ምንም እንኳን የተ.መ.ድ ሰላም አስከባሪዎች እየጠበቋቸው ቢሆንም በቤታቸው ዙሪያ ሁሉ የጥይት እሩምታ ይሰማል። በዚህ ንግግራቸው ወቅት እርሳቸው፣ ባለቤታቸውና አምስት ልጆቻቸው ወለል ላይ መተኛታቸውንና የማምለጫ መንገድም እንደሌላቸው ገለጹ። ወዲውኑም ቃለ-መጠይቁ ሳያልቅ የስልክ መስመሩ ተቋረጠ። በኋላ እንደሰማነው ወታደሮች ወደ ቤታቸው ድንገት ገብተው እርሳቸውንና ባለቤታቸውን ገድለዋቸዋል። ትረፉ ሲላቸው ልጆቻቸው አልተገደሉም።

የጠቅላይ ሚኒስትሯ ቃላት ስሜታችንን በእጅጉ ነኩት፤ በዚህ ወቅት ሁኔታዎች ይሻሻላሉ ብሎ ማሰብ ሞኝነት ነው። ገዳዮቹ ሁቱዋን ጠቅላይ ሚኒስትር ከገደሉ እኛስ ከመግደል ምን ያቆማቸዋል?

በነዚያ 24 ሰዓታት የነበረው ረፍት-አልባ ውጥረት ቤተሰቤን ጎዳው። እናቴ በደመ-ነፍስ ከከፍል ከፍል እየተዘዋወረች የነበረንን ማንኛውንም ሻንጣ እጇ በገቡላት እቃዎች ትሞላለች። «በስንት ልፋት ያሟላኋቸውን እቃዎች ሰዎች እንዲዘርፏቸው ትቼ አልሄድም» አለችን። «አርቄ እደብቃቸዋለሁ። እንድ ቀን ተመልሰን እናገኛቸዋለን።»

ወዴት ለመሄድ እንዳቀደች አላወቅሁም። ብቸኛው ሊያስኬደን የሚችለው የማምለጫው መንገዳችን (የኪቩ ሐይቅን አቋርጦ) በኢንተርሃምዌ ታጣቂዎች እንደተዘጋ ሰምተናል። ወደ ሐይቁ የሚጠጋን ማናቸውንም ቱትሲም ሆነ ለዘብተኛ ሁቱ በመግደል ላይ ናቸው።

አባቴ በግራ መጋባት ነባራዊውን ሁኔታ ሊያምን አልቻለም፡፡ «ግድያው ከቀጠለ ሩአግ ሊያቆመው ጣልቃ ይገባል፡፡ በጥቂት ቀናት ውስጥ እዚህ ይመጡና ያድኑናል» ሲል ግምቱን ይነግረን ጀመር፡፡

ለማመን ተቸግሬ «አባባ ምን እያሰብክ ነው» ስል ጠየኩት፡፡ «የሩአግ ወታደሮች ገና በስተሰሜን በዩጋንዳ ድንበር አቅራቢያ ናቸው፡፡ ተሽከርካሪ ስለሌላቸው በእግራቸው እየተጓዙ ጦሩንና ኢተርሃምዌን መዋጋት ግድ ይላቸዋል፡፡ እዚህ ለመድረስ ሳምንታት ይፈጅባቸዋል … ከነጭራሹ እዚህ መድረስ መቻላቸውንስ ማን ያውቃል!»

ከአባቴ ጋር የተከራከርኩባቸውን ውሱን ጊዜያት መጥቀስ እችላለሁ፤ ያለወትሮዬ መሟገቴ ሁሉም ነገር በመቀያየር ላይ በመሆኑ ነው፡፡ ወላጆቼ በትክክል እያሰቡ አይደለም፤ አገስቲንና ቪያኒም ልጆች ስለሆኑና ስለተደናገጡ ሊታመንባቸው አይችልም፡፡ በሕይወቴ ሙሉ የዳማሲንን መርህ እከተላለሁ፤ አሁን ግን ወደ ከፍሉ አፈፃፀን ግድግዳ ላይ አፍጥጧል፡፡

ፊልጌው ወደ ከፍሉ እንደገባሁ «እስኪ እንዲያው የምታስቢውን ሳትደብቂ ንገሪኝ፤ ይችን ቀን የምናልፋት ይመስልሻል?» ሲል ጠየቀኝ፡፡ «ይኸውልሽ በመጪው ዓመት የማደርገውን ነገር ተኝቼ ለማለም እየሞከርኩ ነው፤ ግን አልሆነልኝም፡፡ በሕይወት የምኖር አይመስለኝም፡፡ የወደፊት ሕይወት የለኝም፡፡»

«ዳማሲን ከዚህ ነገር ውስጥ እንደምንም መውጣት አለብህ!» ስል ጮህኩበት፡፡«ትግሉን ገና ሳትጀምር ተስፋ መቁረጥ የለብህም!» አንተ በመጭው ዓመት ምን እንደምትሠራ ማየት ካልቻልክ እኔ እችላለሁ! ከዩኒቨርሲቲ ስመረቅ ቡታሬ እኔ ጋ ትመጣለህ፡፡ ዲፕሎማዬን ስቀበል በፊት ወንበር ተቀምጠህ እያጨበጨብክ በደስታ ትጮሃለህ፡፡ ስለዚህ አሁን ተነሥና እነእማማን አግዛቸው!»

«ምናለ ያንቺ እምነትና ጽናት ቢኖረኝ» ብሎ ተነፈሰና መልሶ ግድግዳውን አተኩሮ ያይ ገባ፡፡

እኔ ብርታቱ ባይኖረኝም አንድ ሰው መልሶ ቤተሰቤን ማረጋጋት አለበት፡፡ ቤተሰቡ በለየለት ተስፋ መቁረጥ ውስጥ እንዳይገባ ለመበርታትና ቢያንስ *ጠንክሬ* ለመሥራት ሞከርኩ፡፡

ለጠቅላይ ሚኒስትሯ ጥበቃ ያደርጉ የነበሩ አሥር ቤልጅየማውያን የተመድ ሰላም አስካባሪዎች በመንግሥት ወታደሮች እንደተገደሉና በሩዋንዳ የሚኖሩ የቤልጅዬም ዜጎች ሁሉ ሕይወታቸው አደጋ ላይ እንደወደቀ ምሽት ላይ ሰማን፡፡ ቤልጅዬማውያኑና የሌሎች ሀገር ዜጎች አገሪቱን ለቀው ከወጡ ይህን የለየለትን ጭፍጨፋ ለማስቆም

ዐቅሙ ያለው ሌላ ማንም ሊኖር እንደማይችል እናውቃለን፡፡ በዚህ ምሽትም ስላልተኛን ለተከታታይ ሁለት ቀናት ሁላችንም እንቅልፍ አጣን ማለት ነው፡፡

ንጋት ላይ ጩኸት ይሰማን ጀመር፡፡ ሁለት ደርዘን የሚሆኑ የኢንተርሃምዌ ታጣቂዎች በየቤቱ ላይ የእጅ ቦንብ በመወርወር መንደራችንን አጠቁ፡፡ በየቤቱ ውስጥ ያሉት የቤተሰብ አባላት ለማምለጥ ሲሞክሩ በገጀራ ይጨፈጨፋሉ፡፡

ጩኸቱን እንደሰማን በራችንን ከፍተን ወደ መንገድ ወጣን፡፡ ተረተር ላይ ከነበረው ቤታችን የተወሰነ ርቀት ማየት ስለምንችል የረብሻውን ምንጭ አፈላለግነው፡፡ ከኛ ቤት አቅራቢያ በነበረው ወንዝ የታችኛው ክፍል ዳርቻ አንድ የኢንተርሃምዌዎች ቡድን ከጎረቤቶቻችን አንዱን ከቦት አየን፡፡ ገጀራዎቻቸውን ከራሳቸው በላይ ከፍ አድርገው ይዘው እንደ ተኩላ መንጋ ግር ብለው ሄደው ከበቡት፡፡ ከርቀት ለመግደል ሲሮጡና ያለ ምጎረት ረዳት-አልባውን ሰው ሲቆራርጡት አየን፡፡

በመሸበር ከግድያው ፈታችንን ስናዞር በደርዘኖች የሚቆጠሩ ቱትሲ መንደርተኞቻችን ከተረተሩ ከሌላኛው ወገን ወደኛ በፍጥነት ሲመጡ አየናቸው፡፡ ወንዶቹ ቤተሰቦቻቸውን ለመከላከል ዱላና ድንጋይ ይዘዋል፡፡ ሴቶቹ በበኩላቸው ትንንሾቹን ልጆቻቸውን በእጆቻቸው ይዘው ትልልቆቹን ወደኋላ እንዳይቀሩ በማሳሰብ ይጮሃሉ፡፡

አባቴን ሲያዩት «ሊአናርድ! ሊአናርድ!» ብለው ተጣሩ፡፡ «እባክህ እርዳን፡፡ ሊገድሉን ነው! ምን እናድርግ? የት እንሂድ?» ይላሉ፡፡

አባቴ እጅግ ከሚከበሩት የመንደራችን ሰዎች አንዱ ስለሆነ በተወሰኑ ሰዓታት ውስጥ ወደ 2000 ገደማ የሚሆኑ ወንዶች፣ ሴቶችና ልጆች ከቤታችን ፊት ለፊት የእርሱን ትዕዛዝና እገዛ ፍለጋ ጎረፉ፡፡ የሚፈልሰውንና መከራ የሚቀበለውን ሁሉ ብቻ ቤቱ ይቁጠረው! ያን ያህል ቁጥር የነበራቸው ሰዎች ከየቤቶቻቸው እንደተፈናቀሉ ማመን አልቻልኩም፡፡ በርካታ ሰዎች ምን ማድረግ እንዳለባቸው በመጨቃጨቅ በምድጆች ዙሪያ ተቀምጠዋል፡፡ ልጆቹ በበኩላቸው እየተጫወቱ በመስኩ ላይ አንዳቸው ሌላቸውን ያሯሩጣሉ፡፡ አልፎ አልፎ የሚሰማው የተኩስ ድምፅና በርቀት የሚፈነዳው ቦምብ ባይኖር የቤተ- ዘመድ ድግስ ነው ያስብላል፡፡

እገዛና ምክሩን ፈልገው የመጡት ሰዎች ቁጥር ማየሉ አባቴን ከመሸበር ወደ መረጋጋት አመጣው፡፡ የተገፈፈው ቀልቡ ተመልሶለት የተለያዩ ተግባራትን ማከናወን ጀመረ፡፡ «ሁላችሁም ተረጋጉ» አለ፡፡ «ይህን የምንወጣበትን መንገድ አብረን እናፈላልጋለን፡፡»

በዚያን ምሽት አባቴ ጤንነቴ እንዳሳሰበው ነገረኝ፡፡ «ጭራሽ አልተኛሽም እኮ ኢማኪዩሌ፡፡ ሌሎቻችን ከሰዎቹ ጋር ውጪ ላይ ስለምንቆይ አንቺ ወደ ክፍልሽ ሄደሽ ትንሽ ብትተኚልኝ፡፡»

«ግን አባባ፣ እኔ...» ስል አጉተመተምኩ፡፡ በቤት ውስጥ ብቻዬን መሆኑን አልወደድኩትም፡፡ በምሽት ለጥቃት እንዳረጋለን ብዬ ፈርቻለሁ፡፡

ማቅማማቴን አይቶ ፈገግ አለ፡፡ «አትጨነቂ ሆዴ፡፡ እኔ እዚሁ ስለሆንኩ እጠብቅሻለሁ፡፡ ውጪ ላይ ይበርድሻል፤ የተወሰነ ረፍት ማድረግ አለብሽ፡፡ እስኪ ግቢና ጋደም በይ፡፡»

ከኢንተርሃምዌ ሊያድነኝ እንደማይችል ባውቅም የእርሱን ክብር መጉዳት አልወነልኝም፡፡ ስለሆነም ያለኝን ፈጸምኩ፡፡ እናቴም ደህንነቴን ለማረጋገጥ ቤቱን እንደምትከላከል ቃል ገባችልኝ፡፡

ወላጆቼ ለኔ ያላቸውን ፍቅርና ሐሳብ ቢገልጹልኝም እንኳን በዚያን ምሽት መተኛት አቃተኝ፡፡ ትንሽ ሬድዮ በደረቴ ይዤ ጣቢያ መፈለጊያውን እየነካካሁ በአካባቢያችን ምን እየተከሰተ እንዳለ ሳዳምጥ ቆየሁ፡፡ ሌሊቱ እየገፋ ሲሄድ ዜናውም እየከፋ መጣ፡- በሁሉም የሀገሪቱ ማዕዘናት ብዙ ቱትሲዎች እየተገደሉ ሲሆን በመንግሥትና በቱትሲ አማጽያኑ መካከል የነበረውም የሰላም ድርድር ተቋርጧል፡፡ ሩአግም እየተዋጋ ወደ ዋና ከተማዋ ለመግባትና ግድያውን ለማስቆም ቃል ገባ፡፡

በውድቅት ሌሊት ወደ ውጪ ስወጣ እናቴን በግቢያችን ውስጥ ተኝታ አገኘኋት፡፡ ሳታስበው የውጪ በራችንን መጠበቋን ትታ እንቅልፍ ጥሏት ኖሯል፡፡

ልቀሰቅሳት ጠጋ ስል ሳግ ተናነቀኝ፡፡ በነጭ የአልጋ ልብስ ተጠቅልላ በዚያ በደብዛዛው የጨረቃ ብርሃን አስከሬን መስላኛለች፡፡ ባየሁት ነገር እጅግ ተደናግጬ ወደ ክፍሌ ሮጥኩ፡፡ አልጋዬ ላይ ወድቄ ውርጅብኙ ከመጣብን ጊዜ ጀምሮ ለመጀመሪያ ጊዜ አምርሬ አለቀስኩ፡፡

«ለምንድነው ይህ ሁሉ መኾት የሚወርድብን?» በማለት በትራሴ ላይ ተደፍቼ እንባዬን ዘረገፍኩት፡፡ «ይህን የሚያመጣብንስ ምን ጥፋት አጥፍተናል? ቱትሲ መሆን ለምንድነው እንደዚህ ወንጀል ተደርጎ የተወሰደው? ለምን ይህን ታመጣብናለህ፣ እግዚአብሔር?»

በማልቀሴ ራስ-ወዳድነት ተሰምቶኝ ዓይኖቼን አባበስኩ፡፡ *ምኝ ልጅ፣ ለቅሶውን ትደርሺበታለሽ* ብዬ አሰብኩ፡፡ *ይህ ሐዘን ገና መጀመሩ ነው፤ ለእንባ የተትረፈረፈ ጊዜ ይኖርሻል፡፡*

በኪቮ ሐይቅ ላይ ፀሐይ ስትወጣ ተመልሼ ውጪ ወጣሁና እያንቀላፋች ካለችው እናቴ ጎን ቆምኩ። እግሮቿን ቀሰ ብዬ እያሻሸሁ የታሰረውን ጸጉሯን በጥንቃቄ ፈታሁላት። እናቴ ሁልጊዜ ቆንጆና በተክለ-ሰውነቷ የምትኮራ ስለሆነች በዚያ ሁኔታ መታየቷ ያሸማቅቃታል። ጉንጯን ሳም አድርጌ ቀሰ ብዬ ቀሰቀስኳት። በቀስታ «እማማ ተነሺ» አልኳት። «እዚህ ይበርድሻል። ወደ መኝታሽ ሂጂ።»

ዓይኖቿን ስትገልጣቸው በፍርሃትና በድንጋጤ መሞላታቸውን አየሁ። «ዳማሲን የት ነው? ቪያኒስ? ኢማኪዩሌ... እቤት ጉበተሽ እረፍት አድርጊ እንጂ። በዚህ ጨለማ ውጪ ላይ ብቻሽን ምን ታደርጊያለሽ?» ስትል ለመነሳት እየተጣጣረች ጠየቀችኝ።

«እዚህ ምን እያደረግሽ ነው እማማ?» ስላት፣

«እቤት ብቻሽን ልተውሽ አልፈለግሁም፤ ከአባትሽና ከወንዶቹ ልጆቼም በጣም መራቅ አቃተኝ። ሁላችሁም ደኅና መሆናችሁን እርግጠኛ መሆን አለብኝ።»

«ሁሉም ደኅና ናቸው እኮ እማማ። ልጆቹም፣ አባባም ውጪ ከእንግዶቹ ጋር ሆነው ነው። ምናአልባት ዛሬ ሁኔታው ሊሻሻል ይችላል» አልኩ በፊቷ ላይ ከሚታየው ጭንቀት የተነሣ ልቤ እየታወከ። ሕይወቷን ሙሉ ለኛ ስትለፋ፣ መሥዋዕትነት ስትከፍልና ስለደህንነታችን በየዕለቱ ቁጥር ስፍር ለሌላቸው ሰዓታት ስትጨነቅ ኖራለች። አሁን እኛን ለማዳን አንዳች ነገር ልታደርግልን አለመቻሏን ማወቋ አንጉብግቧታል። ባለፉት ጥቂት ቀናት በደረሰባት መከራ ሰበብ በጣም ያረጀች መሰለችኝ።

አባቴንና ወንድሞቼን ፍሊጋ ወደ ውጪ ወጥተን ከስደተኞቹ ጋር ስናገኛቸው ገና በሯን ወጣ እንዳልን ያየነው ነገር ያልጠበቅነው ሆነብን። ቢያንስ 10 000 ቱትሲዎች ከቤታችን ፊት ለፊት ሰፍረዋል።

አባቴ በዚያ ሁሉ ሕዝብ መካከል እየሄደ ሰዎችን በማበረታቻ ቃላት ሰላምታ ይሰጣቸዋል። በዚያ ሌሊት አንዴ እንኳን ጋደም አላለም። ወደ ቤት ጉበተህ ተኛ፤ እረፍትም ውሰድ ቢባልም አሻፈረኝ እንዳለ ነው። ታጥቦ፣ አዳዲስ ልብሶችን ለብሶ ወዲያውኑ ወደ ተፈናቃዮቹ ተመለሰ። በደርዘን የሚቆጠሩ ሰዎች ወደርሱ ሲመጡ፣ ሲያናግሩትና ስሙን ሲጠሩት ብዙ ስለሆኑበት ማናገር አልተቻለውም።

በመጨረሻም በአንዲት ተገን ባለ ትልቅ ቋጥኝ ላይ ቆመና ወደተሸበረው ሕዝብ ዞሮ «ወዳጆቼ፣ ወዳጆቼ!» ሲል ጮኸ። ድምጹም በጀማው ላይ ተሰራጨ።

«እንደፈራችሁ አውቃለሁ፤ አትፍሩ። እነዚህ ሰዎች - ገዳዮቹ - ትንሽ ናቸው። እኛ ግን ብዙ ነን። በምንም ተአምር በኃይል አይበልጡንም፤ በልባችን የእግዚአብሔርን ፍቅር ከያዘን ከኛ አያይሉም። ርኩሰት ከሆነ እንደዚህ የሚያደርጋቸው፣ ለኛ ካላቸው ጥላቻ በስተቀረ ምክንያት ሳይኖራቸው ሊጎዱን ከመጡ

እናሸንፋቸዋለን፡፡ ፍቅር ምንግዜም ጥላቻን ያሸንፈዋል፡፡ በራሳችሁም ሆነ እርስ በርሳችሁ ተማመኑ፣ በእግዚአብሔርም እመኑ!»

ልቤ በኩራት አበጠች፡፡ ከሰዓታት በፊት እጅግ የተወዛገበ የመሰለው ያ ሰውዬ ነው ብሎ ለማመን ይቸግራል፡፡ ግን ይኸው ተመለሰለት - ጥንካሬውን ለብዙ መላው ለጠፋቸውና ለተሸበሩ ነፍሶች ያስተላልፍ ይዟል፡፡

«እንዋጋቸዋለን» ሲል ቀጠለ አባቴ፡፡ ሕዝቡም በቃላቱ ተማርኮ ስሙን እየጠራ ይዘምርና በደስታ ያወካ ጀመር፡፡ አባቴ ጸጥታ እንዲከበር እጁን ከፍ አደረገ፡፡

«እንዳልኩት እነዚህ ገዳዮች የሚነዱት በጥላቻ ብቻ ከሆነ እናባርራቸዋለን፡፡ ነገር ግን የላካቸው መንግሥት ከሆነና እነዚህ ጥቃቶችም ቱትሲዎችን ለማውደም የታለመ የተደራጀ እቅድ አካል ከሆኑ በፈታኝ ችግር ላይ ነን፡፡ መንግሥት ጦር መሣሪያ አለው፤ ወታደሮችና ታጣቂዎችም እንዲሁ - እኛ ግን ምንም ጠመንጃ የለንም፡፡ መንግሥት ሊገድለን ካቀደ ማድረግ የምንችለው ብቸኛው ነገር መጸለይ ነው፡፡ ያለንን ጊዜ ንስሐ ለመግባት እንጠቀምበት፡፡ እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ያስተሰርይልን ዘንድ እንጸልይ፡፡ የምንሞት ከሆነ ልቦናችንን ንጹሕ አድርገነው እንሙት፡፡»

የደስታ ሁካታውን አቁሞ ጀማው በጸጥታ ተዋጠ፡፡ በመጀመሪያ አባቴ ስሜታቸውን እንዳንኪታኮተባቸው ባስብም በኋላ እንደገባኝ ግን በሺህዎች የሚቆጠሩት ሰዎች ምክሩን ተቀብለው በጥሞና ተግተው ይጸልዩ ጀመር፡፡

«ኖርንም ሞትንም ምንም ማለት አይደለም - ዋናው ነገር ይህን ወደየቤታችን የመጣውን ክፉ ነገር መፋለማችን ነው!» ሲል አባቴ በጉልህ ድምጽ ተናገረ፡፡

በሺዎች የሚቆጠሩ ዓይኖች በላዩ እንደተተከሉ ቀኝ እጁን ከፍ አድርጎ አወጣ፡፡ ቀይና ነጭ መቁጠሪያውን እንደያዘ ይታየኛል፡፡

«አምላካችንን ከከፉ እንዲጠብቀን እንጠይቀዋለን» ሲል መቁጠሪያውን በአየር ላይ አያውለበለበ ጮኸ፡፡ ከዚያም ጎንበስ አለና በግራ እጁ ጫፉ ብረት የሆነ ጦር አነሳ፡፡ ጦሩንም በራሱ ትይዩ ይዞ እንዲህ ሲል ቀጠለ፡፡ «እግዚአብሔርን እንዲረዳን እንጠይቀዋለን፤ ቢሆንም ግን ራሳችንንም እንከላከላለን፡፡ ጦር ፈልጉ፤ ራሳችሁን አስታጥቁ፤ ታዲያ ማንንም እንዳትገድሉ! እኛ እንደነሱ አንሆንም - አንገድልም - እንደ በግም ግን ቁጭ ብለን አንታረድም፤ እንጠንክር፤ እንጸልይ፡፡»

ከአባቴ ንግግር ከተወሰኑ ሰዓታት በኋላ 50 ኢንተርሃምዌዎች ቢላዋና ገጀራ ይዘው ከቢታችን ውጪ ያሉትን ቱትሲዎች አጠቁ፡፡ አባቴ ከመቶ በላይ የሚሆኑ የቱትሲ ወንዶችን ሰብስቦ ወደ ገዳዮቹ ሄደ፡፡ በቅርብ በእጅ ቢወረውሩ በሚያደርሱበት ርቀት

ላይ ሲደርሱ ድንጋይ ወርውረው አባረሯቸው፡፡ ያች ግን ትንሽዬ ድል ነበረች - ሬድዮ ስለ መጠነ-ሰፊ ግድያዎች መዘገቡን ሲቀጥል፣ የቱትሲ ስደተኞች ጎርፍም ወደኛ በር መጉረፉን አላቆመም፡፡ እያንዳንዱ አዲስ የሚደርስ ሰው የየራሱን አሰቃቂ ታሪክ ይናገራል፡፡ ከነገሩን ነገር ስንረዳ ሙሉ በሙሉ በኢንተርሃምዌ ተከበን ኖሯል፡፡

ስካፑላር የሚባለውን ካቶሊኮች የምናጠልቀውን የጨርቅ ማተብ ላመጣ ከጥቃቱ በኋላ ወደ መኝታ ቤቴ ሄድኩ፡፡ ማተቡ በጣም ውድ ንብረቴና በድንግል ማርያም ቃል-ኪዳን የተባረከ ሲሆን «ማንም እሱን አጥልቆ የሚሞት ሰው በዘላለማዊ እሳት አይሰቃይም፡፡ የድኅነት፣ አደጋ የመከላከያና የሰላም ቃል-ኪዳን ምልክትም ነው፡፡» አንድ ችግር ቢገጥመኝ ይህ ማተቤ ወደ ገነት የማደረገውን ጉዞዬን ያፋጥንልኛል ብዬ በማመን ወደ ዩኒቨርሲቲ ስሄድ ነው የገዛሁት፡፡

አባቴ ኢንተርሃምዌዎቹን ካባረረ በኋላ ወዳመራበት ወደ ግል ከፍሉ ሄድኩ፡፡ የጠረጴዛውን ኪስ እየበረበረ የቤተሰባችንን ፎቶዎች ወደ ኪሶቹ ይሸጣል፡፡

«አባባ ላንተ የሚሆን አንድ ነገር አለኝ» አልኩት ስካፑላሩን አውጥቼ ይዤ፡፡

ምን እንደሆነና ለምን እንደሚጠቅም ያውቀዋል፡፡ «ለምን እዚህ ቤት ውስጥ አንተወውም? እንደዚያ ካደረግን ቤታችንን ማንም አያቃጥለውም» አለኝ፡፡

ዓይኖቼ በእንባ ተሞልተው «አይሆንም አባባ፣ ለንሥ ነህ ልታጠልቀው የሚገባህ፡፡» በዚህ ቤተሰብ ራሱን አደጋ ላይ የሚጥለው ማነው? በዚህ ሁሉ መካከል ሊገደል የሚችለው ማነው አባባ? ስለቤቱ መጨነቅህን ተወው - አሁን አሳሳቢው የቁሳቁሱ ጉዳይ ሳይሆን ያንተ መንፈስ ነው፡፡»

«በጄ፣ ኢማኪዩሌ ገባኝ» አለ ስካፑላሩን ተቀብሎኝ አንገቱ ላይ እያጠለቀ፡፡ «አሁን ላንቺ የሚሆን ግን ምን አለኝ? ለአንዲ ሴት ልጄ ምን ልስጥሽ?» ሲል ጠረጴዛውን እየበረበረ በመጨነቅ ጮክ ብሎ ተናገረ፡፡ «ምን እንደምሰጥሽ በሚገባ አውቀዋለሁ፡፡»

ለሕዝቡ ያሳየውን ቀይና ነጩን መቁጠሪያ ከሸሚዙ ኪስ አወጣው፡፡ ዶቃዎቹን መዳፌ ላይ ጫን አድርጎ ይዞ እጄን በእጁ ሸፈነና «ፈጽሞ አንዳይለይሽ፣ ኢማኪዩሌ» በማለት አሳሰበኝ፡፡

«ቃል እገባለሁ አባዬ፣ አይለየኝም፡፡»

ስጦታዎቻችንን እንደተለዋወጥን የፊት በራችን ብርግድ ብሎ ተከፈተ፡፡ ጎረቤታችን የሆነች ሴትዮ አባቴን በተስፋ መቁረጥ ትጣራ ጀመር፡፡ «ሊኦናርድ! ሊኦናርድ! እባክህ ቶሎ ና! ተመልሰው መጥተዋል! ገዳዮቹ ተመልሰዋል! ተበራክተዋል ደግሞ፤ አሁንስ እጅግ ብዙ ሆነው ነው የመጡት! አቤት! አቤት!»

አባቴ ወደ መኝታ ክፍሉ ሄዶ ከአልጋው ስር ደብቆት የነበረውን ጦር ይዞ ወደ ውጪ ወጣ፡፡ በተቻለኝ መጠን ብከተለውም እግሮቼ ተልፈሰፈሱብኝ፡፡ ልንሞት መሰለኝ ... በተለይ ገዳዮቹ ከቤታችን ግማሽ ኪሎሜትር ያህል ርቀው ሳያቸው፡፡

«እነዚህን ጨካኞች እንፋለማቸው! ይህን ምክንያት-አልባ ግድያ እናስቁም! ሊገድሉን ይችላሉ፤ የምንሞተው ግን በንጹሕ ልብ ነው!» አባቴ ሌሎቹ ቱትሲ ወንዶች ከጎኑ እንዲቆሙ በመጮህ ጠራቸው፡፡ ማናቸውም ሊከተለው አልቻለም፡፡

አባቴ አላበው፤ ዓይኖቹም ፈጠጡ፡፡ ጦሩን በአየር ላይ ከፍ አድርጎ ይዞ በራሱ ጊዜ ብቻውን ወደ ገዳዮቹ መሮጥ ጀመረ፡፡ እናቴም ረጅም ሰማያዊ ቀሚሷ ከኋላዋ እየተውለበለበ ተከትላው ሮጠች፡፡ የሸሚዙን ጫፍ ጥርቅም አድርጋ ይዛም ተረከዞቿን መሬት ላይ ተከለች፡፡ እናቴ ስሙን እየጠራች ስትጮህ አባቴ እየጎተታት መሮጡን ቀጠለ፡፡ «ሊአናርድ አትሂድ! ተመለስ! ብቻህን አትችላቸውም፡፡» እባክህ፣ እባክህ፣ *በፈጠረህ* ሌላ ሰው ይሂድ፡፡ እዚህ ብዙ ወጣቶች አሉ፡፡ *እነሱ* ይፋለሙ» ስትል ለመነችው፡፡

ሁሉም ሰው እርሷ ላይ ቢያፈጥም እርሷ ግን ምንም ግድ አላላት፡፡ የ28 ዓመታት ባሏን፣ ከሁሉ በላይ የምትወደውን ሰው፣ ወደ ሞቱ ሲሮጥ ስታየው ለማስቆም የሚያስችላትን ነገር ሁሉ አደረገች፡፡

አባባ ትንፋሽ አጥሮት እማማን ከዚያ በኋላ መጎተት አቃተው፡፡ ሚስቱ ሸሚዙን እንደያዘችው ቆሞ ትንፋሹን ያዝ ለማድረግ ሞከረ፡፡ እናቴም በጅሙ ውስጥ የነበሩትን ወጣት ቱትሲዎች «ምን ነካችሁ?» ስትል ጮኸችባቸው፡፡ «ታላላቆቻችሁ እንዴት የናንተን ጦርነት እንዲዋጉላችሁ ታደርጋላችሁ? ባሌ እንዴት ስለእናንተ እንዲገደል ታደርጋላችሁ? ወገባችሁን ጠበቅ አድርጉ እንጂ! - ሂዱ ተፋለሟቸው!»

ሰዎቹ ስለተሸበሩ ዝም ብለው ከማፍጠጥ በቀር አንዳች እገዛ ሊያደርጉ አልቻሉም፡፡ እናቴ ወደ አባቴ ዘወር ብላ በእጆቿ አቅፋው «አትሂድብኝ፣ ሊአናርድ፣ እባክህ!» ስትል ተማጸነችው፡፡

አባቴ ትከሻዎቿን ጥርቅም እድርጎ ይዞ «አዳምጭኝ ሮዝ፤ በአሁኑ ሰዓት ለነዚህ ሰዎች መቆም ግዴታዬ ነው፡፡ ያም ግዴታዬ መፋለም ከሆነ እፋለማለሁ፡፡ ትክክል ነው ብዬ ያመንኩበትን እፈጽማለሁ፡፡ ፍራቻሽን ተዪና ልጆች የያዙትን ወጣት እናቶች አግዢ፡፡ እመለሳለሁ፡፡»

ወላጆቼ እሰጥ-አገባቸውን ሲጨርሱ ገዳዮቹ ሄደዋል፡፡ ቀረብ ብለው ስለቃኙ ስንት ቱትሲዎች እደጃችን እንደነበሩ አጥንተው እንደሄዱ እገምታለሁ፡፡ ጠመንጃዎችና ቦምቦችን የያዙ መቶ ሰዎችና ምንም ያልታጠቀ አሥር ሺህ ሕዝብ አይመጣጠኑም፡፡ በምንም ተአምር የሚቀናን አይመስልም፡፡ አቤት ያመጣብን ጣጣ!

ከቤታችን ፊት ለፊት ወላጆቼ ካካሄዱት ትግል በኋላ ዳማሲን ፈልጎኝ መጣ። ዓይኖቹ ቀልተዋል፤ ድምጹም ጎርንኗል። «ገዳዮቹ አሁን ሮጡ፣ ኢማኪዩሌ፣ ተመልሰው ግን ይመጣሉ። ሲመለሱ ደግሞ በድንጋይና በዱላ ለማባረር የሚያዳግቱ ብዙ ሆነው ነው። አንቺን ከያዙሽ መጀመሪያ ይደፍሩሻል፤ ከዚያም ይገድሉሻል። ከዚህ ስፍራ መጥፋት አለብሽ። ሂጂና ቄስ ሙሪንዚ ጋ ሁኚ ... ይህ ችግር መፍትሔ እስኪያገኝ ድረስ እንደሚሸሸጉሽ እርግጠኛ ነኝ።»

«አይሆንም ዳማሲን። ቤተሰቤን ጥዬ መሄድ አይሆንልኝም። የምሄደው ሁላችንም ከሄድን ብቻ ነው። እኔ የሆነ ቦታ ተደብቄ እናንተ ልትገደሉ እንደምትችሉ እያወቅሁ መኖር አይሆንልኝም።»

ዳማሲን ዓይኖቹ እንባ አቅርረው አየኝ። አባታችንን ሄዶ ጠርቶት አብረው ሊያናግሩኝ መጡ። «ወንድምሽ ያለው ትክክል ነው፣ ኢማኪዩሌ» አለ አባቴ። «አንቺ ሴት ልጅ ስለሆንሽ ላንቺ እዚህ መሆን በጣም አደገኛ ነው። ወደ ቄስ ሙሪንዚ ቤት ሂጂ፤ ችግሩ በጥቂት ቀናት ስለሚያበቃ እኔ ራሴ መጥቼ እወስድሻለሁ።»

መጥቶ ሊያገኘኝ አለመቻሉን ስላወቅሁና በልቤም ይድናል ብዬ ስላላሰብኩ «ግን እዚህ ከናንተ ጋር ብቆይ ይሻለኝ ነበር» ስል መለስኩለት።

«አይሆንም፤ ትደበቂያለሽ አልኩ በቃ፤ ይህ የመጨረሻ ቃሌ ነው» በማለት ከዚያ በላይ እንዳልከራከረው በዚህ ንግግሩ አስቆመኝ።

«እማማስ? እሺ እሷ እንኳን ከኔ ጋር ትምጣ።»

«ብጠይቃት ወንድሞችሽን ትታ እንደማትሄድ ነው የነገረችኝ። አገስቲንንም ካንቺ ጋር ብትወስጂው ጥሩ ነው። አንድ ነገር ቢሆን ለወላጆቼ ምን እላቸዋለሁ?»

በአንድ ሰዓት ውስጥ አገስቲንና እኔ ወደ ቄስ ሙሪንዚ ቤት መንገድ ጀመርን። ልብሶቼን በጀርባዬ አዝዬ፣ አባቴ ያበረከተልኝን መቁጠሪያና መንግሥት የሰጠኝን ቱትሲ መሆኔን የሚገልጸውን መታወቂያ ደብተሬን ይዣለሁ።

አባቴ ለተወሰነ ርቀት ከኋላችን ተከተለን። ለመመለስ ፊቱን እንዳዞረ «አስታውሺ ኢማኪዩሌ፣ እኔ ራሴ ነኝ መጥቼ የምወስድሽ!»

ይህ አባቴ ለኔ ያለኝ የመጨረሻው ቃሉ ነው።

ወደ ቄሱ ቤት የሚወስደው ቁልቁለት መንገድ ስምንት ኪሎሜትር አቧራማ ጠባብ የእግር መንገድ ነው። በፍጥነት እንሄድ ጀመር። አገስቲን ሁቱ ነው። መልኩና ቁመናው ግን ቱትሲ ይመስላል። መንገድ ላይ ገዳዮቹን እንዳናገኛቸው ሲጋን። እቄሱ

ቤት ልንደርስ አንድ ኪሎሜትር ተኩል ገደማ ሲቀረን ገዳዮቹ ታዩን፡፡ አንድ መቶ የሚሆኑ ሁቱዎች ጦር፣ ቢላዋና ገጀራ ይዘው ወደኛ በመምጣት ላይ ናቸው፡፡

እየቀረቡን ሲመጡ «ወፍ ብሆንና ወደ ቤቴ ወደ ኪጋሊ አሁን ብበር» ሲል አገስቲን አንሾካሾከልኝ፡፡ ልቤ ደረቴን ሲደቃው ይሰማኛል፡፡

የተወሰኑት ወንዶች ገጀራዎቻቸውን እርስ በርሳቸው እያማቱ የሚያሸብር ድምፅ ያሰማሉ፡፡ ሌሎቹ ገጀራቸውን በስለቱ መንገድ ላይ ሲጎትቱት ብረቱን ድንጋይ ባገኘው ቁጥር ብርቱካናማ ቃንቄ ይፈናጠራል፡፡ ዓይኖቼን መንገዱ ላይ ተክዬም የመሣሪያዎቻቸው ጥላ ይታየኛል፡፡

አንድ ሰው በጀርባዬ ጦር እንዳይሰካብኝ ፈራሁ፡፡ ስለቱ ሲጋዬን እንዴት እንደሚያርሰው አሰብኩ፡፡ ዓይኖቼን ጨፍኜ ህመሙን ጠበቅሁት … እግዚአብሔር ግን ሁላችንንም ይጠብቀናል፡፡

«ኢማኪዩሌ እዚህ ምን እያደረግሽ ነው?»

ዓይኖቼን ከፍቼ የአባቴ ጥሩ ጓደኛ የሆኑትን ሁቱውን ካጌዮን አየኋቸው፡፡ በጣም ትልቅ ጦር የያዙ ቢሆንም ከዓይኖቻቸው ደግነት ይነበባል፡፡

የከበቡንን ሁቱዎች ካጌዮ «እነዚህን ልጆች ጫፋቸውን አንዳትነኳቸው! ወዳጆቼ ናቸው፤ ማናችሁም አትንኳቸው» ሲሉ ጮኹባቸው፡፡

ሁቱዎቹ በጣም መናደዳቸው ቢያስታውቅም እግረ-መንገዳቸውን ያገኙትን ግዳይ ሳይጥሉ ለማለፍ ተገደዱ፡፡

ካጌዮ «አይዟችሁ ልጆቼ፤ ሰላምን መልሰን እናሰፍናለን» አሉና ከሌሎቹ ጋር ሄዱ፡፡

አገስቲንና እኔ እግሮቻችን እስከተሸከሙን ድረስ ሮጥን፤ በቁሱ በር ፊት ደርሰን እስክንቆም ድረስም አላቆምንም፡፡

«ከዚህ በኋላ ምንም አንሆን» አልኩ፡፡

ምነው ያኔ ይህ አባባሌ ልክ በነበረ፡፡

ምዕራፍ 7
የቄሱ ቤት

አግስቲንና እኔ ቄስ ሙሪንዚ ቤት እያለከለክን ደረስን። ባሳለፍኳቸው ሥቃይ የተሞላባቸው ቀናት የተነሣ እጅግ በጣም ደክሞኝ በዚያው ላይ ከገዳዮቹ ለማምለጥ ባለ በሌለ ኃይሌ ስሮጥበት ጭንቅላቴ ይዋልል ጀመር። ቄሱ ከበራቸው ቆመው አተኩረው ሲያዩን ሳይ መናገር ተሳነኝ። «ጦር የያዙ ሰዎች አገኘን... እንትን ሊ.... » አለከለክሁ።

ቄስ ሙሪንዚ ከጡብ በተሠራው ቤታቸው ትልቅ የፊት በር ላይ ቆመዋል። የባህር ማዶ ዘዬ ያለው ቤታቸው ብዙ የሣር ጎጆዎችና ያረጁ ቆርቆሮ ቤቶች ባሉበት መንደር ያለስፍራው የተሠራ እንደሆነ ይገባኛል - ብዙ የመኝታ ክፍሎች፣ አንድ ትልቅ የእንግዳ መቀበያና መመገቢያ ክፍል እንዲሁም የቧንቧ ውኃ የተገጠመላቸው መታጠቢያዎች ያሏቸው መጸዳጃ ቤቶች አሉት። የግቢያቸው ፊተኛው ክፍል ከበጋው ሐሩር ጥላ ባለው ትልቅ ዛፍ በተከለለ የአበባ ጎርፍ ተጥለቅልቋል።

ቄሱ ጥሩ ወዳጃዊ ሰላምታ አቀረቡልን። ትንፋሼን ለመቆጣጠር እየታገልኩ እጃቸውን በሰላምታ ጨበጥኳቸው።

«እንኳንም እንደገና አየሁሽ፣ ኢማኪዩሌ» አሉኝ በፈገግታ። «ብዙ ጊዜ ሆነን እኮ።»

ከቄሱ የመጨረሻ ልጅ ጋር ከልጅነታችን ጀምሮ ጥሩ ጓደኛሞች ስለነበርን እቤታቸው ተመላልሻለሁ። በነዚያ ዓመታት ከአባቴ ጋር ብዙ የንግድ ግንኙነቶች ያደርጉ ስለነበር እኛም ቤት አያቸዋለሁ። በዚያም ላይ የወንድ ጓደኛዬ፣ የዮሃንስ፣ አጎት ስለነበሩ ለቤታቸው ባይተዋር አይደለሁም። እኝህ የወንጌላውያን ቄስ የአባቴን መልካም ሥራዎችና በማኅበረሰቡ የነበረውን ተወዳጅነት እንደሚመቀኙ በአንድ ወቅት አከስቴ የነገረችኝ በድንገት ትዝ አለኝ። ለኔ ግን ሁልጊዜ ትህትና ያሳዩኝና አከብራቸውም ስለነበር በደግ በደጉ ላይ ለማተኮር ወሰንኩ።

«አባቴ እዚህ እንድመጣ ልኮኝ ነው ቄስ ሙሪንዚ» አልኳቸው በመጨረሻ እጃቸውን አጥብቄ እንደያዝኩ። «ሁኔታዎች እንደተስተካከሉ እንደሚመጣልኝ ነግሮኛል። እርሱ ራሱ እንደሚመጣልኝ ቃል ገብቶልኛል።» ቄሱ ምንም አልተነፈሱም፤ ዓይኖቻቸው ግን ብዙ ይናገራሉ - *አባትሽ መቼም ሊይመጣልሽ፣ ፈጽሞ ድጋሚ ሊታይዉም* - እያሉ።

በቤተሰቤ አባላት ላይ ጉዳት እንደሚመጣባቸው ካሰብኩ ሙሉ በሙሉ ስለምንዳ የቁሱን አስተያየት ከአእምሮዬ አስወጣሁት፡፡ ከአገስቲን ጋር ካስተዋወቅኋቸው በኋላ ብዙ እንግዶች እርስ በርስ ወደሚያወሩበት እንግዳ ማስተናገጃ ክፍል እንድንገባ ጋበዙኝ፡፡ የራሴ ግምት ይሁን አይሁን እንጃ እንጂ እኛ ወደ ቤቱ እንደገባን ንግግሩ አቆመ፡፡

በመጀመሪያ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህሬን ቡሆሮን አየሁት፡፡ በዘውግ ስም-ጥሪው ወቅት ቢያሸማቅቀኝም ቂም አልያዝኩበትም፡፡ የማውቀው ሰው በማግኘቴ ተደስቼ በቀጥታ ወደ እርሱ ሄጄ ጥሩ ፈገግታ አሳይቼው እጄን ለሰላምታ ዘረጋሁለት፡፡

እጄን ቁልቁል አየ፤ ሸቅብ ወደ ዓይኖቼ ደግሞ አማተረ፤ ከዚያም በምላሱ የጥላቻ ድምፅ አሰምቶ ጆርባውን በመስጠት አሸማቀቀኝ፡፡ ከዚያ በፊት እንዲህ ባለ ሁኔታ ሰው ፊት ነስቶኝ አሊያም በጥላቻ ስሜት ንቀቱን አሳይቶኝ አያውቅም፡፡ እስኪ ይህ ከታች ክፍል ጀምሮ ከሚያውቀኝ መምህር ይጠበቅ ነበር? በክፍሉ ውስጥ የነበረው ማንኛውም ሰው የተከሰተውን ነገር አይቷል፡፡ አካኋኑ ስሜቱን ግልጥልጥ አድርጎ ያሳያል፤ አፍ አውጥቶ ይጮሃል፤ *«ዘወር በይ ኣንቺ ብጣሻም ቱትሲ!»* በሚል ዓይነት፡፡

ከጎልማሶቹ አንዱ ከጎኔ እንዲቆሙና ቡሆሮን ስለጥፋቱ እንዲቆጡት በማሰብ ዘወር ዘወር ብዬ አየሁ፡፡ ማንም ግን ነገሬ አላለኝም - ከፊት ለፊታችን ቆመው የነበሩት ቄሱም ቢሆኑ፡፡ አገስቲን ተሸሎ ቡሆሮ የተቀመጠበት ድረስ ሄዶ ሰላምታ ከነፈገው በኋላ ከጎኔ መጥቶ አብሮኝ በመቆም ኢጋርነቱን አሳየኝ፡፡

የቡሆሮን ሁቱ መሆን ለረጅም ጊዜ ባውቅም ቱትሲዎችን የሚጠላ ጽንፈኛ መሆኑን ግን ገና በዚህ አጋጣሚ ነው የተረዳሁት፡፡ *ጽንፈኛ…* ይሄን ቃል መስማቱ ምንኛ እንደሚያንገሸግሸኝ! እግዚአብሔር እኔን ሁኚ ብሎ በፈጠረኝ ነገር፣ በቱትሲነቴ፣ ቡሆሮ ዳግመኛ አሸማቀቀኝ፡፡ በጣም ስለተሸማቀቅሁም ከዚያ ክፍል ወደ ሌላው በሃፍረት ከመሄዴ በፊት ለሌሎቹ ሰዎች ሰላምታ አቀረብኩ፡፡

ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጀምሮ ጓደኛዬ የነበረችውን ጣኔትን በመመገቢያው ክፍል ውስጥ ተቀምጣ ከሌላ ሴት ልጅ ጋር ስታወራ ሳገኛት ቀለል አለኝ፡፡ ሮጬ ጮኬ ሄጄ «ጣኔት! ወይኔ እንኳንም አገኘሁሽ፡፡ በነዚህ ባለፉት ቀናት በጣም ተጨንቄ ከረምኩ፤ ዓለም አብዳለች፡፡ በመንደሩ በአጠቃላይ ሰዎች እየተገደሉ ነው፤ እኛም ይሄው እንደ ውሻ ታየን … ይመስገነው እንኳን አገኘሁሽ! በአሁኑ ጊዜ በደግ የሚያየይን ሰው ማግኘት እንዴት ጥሩ መሰለሽ፡፡»

በቻልኩት መጠን አቀፍኳት፤ ተጠመጠምኩባት፤ ሰውነቷ ግን ጠነከረብኝ፡፡ ለቅቄያት መልሼ ፊቷን አየት ሳደርጋት በፍጹም ጥሩ ገጽታ አይነበብባትም - ዓይኖቿም የኔን ዓይኖች ለማየት አልፈለጉ፡፡

በድንገትም ስለ ደህንነቷ ለሰብኩና ተደናግጣ ነው ብዬ ገመትኩ። ምን ነክቶኝ ነው? እንዴት ነሽ ብዬ እንኳን ሳልጠየኳትም እኮ!

«ደኅና አይደለሽም እንዴ ጣኄት? እኔም ይኸው እንቅልፍ እንኳን ከተኛሁ ስንት ቀኔ፤ አሁን ግን ተገናኘን። አባቴ ቄስ ሙሪንዚ ጋ ሂጂ ብሎኝ ነው፤ ግን እዚህ አልተስማማኝም። እንኳንም መጣሽልኝ! ካንቺ ጋር እቤታችሁ እሄዳለሁ፤ ነገሩ እስኪረጋጋ እናንተ ጋ እሆናለሁ።»

ጣኄት አቀረቀረች፤ የእጅ ቦርሳዋን ያዘችና ተነሣች። «ኢማኪዩሌ ምን እያሰብሽ እንደሆነ አይገባኝም» አለችኝ አሁንም ዓይኖቿን ከኔ አሸሸታ። «በተአምር አልደብቅሽም፤ አባቴም ቢሆን እንደዚያው። እቤታችን ቱትሲ አናስገባም።»

«ግን ... ጣኄት?»

ወደ ሌላኛዋ ልጅ ዞራ «መሄዴ ነው» ብላት ከቤቱ ስትወጣ መለስ ብላ እንኳን አላየችንም።

ተውተርትሬ ወደ አዳራሹ ሄድኩና ግንቡ ላይ ተደገፍኩ። እንዴት ውዷ ጓደኛዬ ፊቷን ታዞርብኛለች? በአንድ ወቅት ፍቅራችን እንደ እህትማማቾች እንዳልነበር አሁን እንዴት እንደዚህ ትጨክንብኛለች? እንዴት ነው አንጀቷ እንደዚህ ቶሎ ሊቆርጥላት የቻለው?

አገስቲን ከቄስ ሙሪንዚ የመጨረሻ ልጅ፣ ከምንጊዜም የቅርብ የወንድ ጓደኛዬ፣ ከለችም ጋር ወደኔ መጣ። ከአንደኛ ደረጃ ጀምሮ እንተዋወቃለን፤ ከዳማሲንም ጋር የቅርብ ጓደኛሞች ስለሆኑ እኛ ቤት ሁልጊዜ ይመጣል። በነዚያ ዓመታት ከሰፈራችን ለሸርሸር ወጣ ስንል ከሌሎች ጓደኞቻችን ጋር አብሮን የሚሄድ ሲሆን ከእኔ ጋር መዋደድም ጀምረን ነበር። ከ20ኛ የልደት በዓሌ ትንሽ ቀደም ብሎም በሕይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ የሳመኝ ወንድ እርሱ ነው። ያች የሳመኝ የፍቅራችን መጀመሪያም መጨረሻም ስትሆን ያን ዓይነት ግንኙነት ያቆምነው ግሩም ጓደኝነታችንን ላለማበላሸት ነው። አሁን በዚያ ጓደኝነታችን ሳቢያ በሜዳ ላይ ገጀራ በያዙ ገዳዮች መታደኔ ቀርቶልኝ በዚህ ፈረስ በሚያስፈትነው ቤት ውስጥ ቅዱስ እጅ አቅፎኛል።

ለችም በለስላሳ ድምፅ «ነይ ኢማኪዩሌ፣ አትበሳጪ። ዛሬ ሁሉም ሰው እንዴት ዓይነት እንግዳ ጸባይ መሰለሽ ያመጣው» አለኝ ጀርባዬን ቀስ ብሎ ትም ትም እያደረገ። «ነይ ወደ እህቴ ክፍል ልውሰድሽ፤ አገስቲን ደግሞ በወንዶቹ ልጆች ክፍል ይቆያል። ሴቶቹ ልጆች ይሻሉሻል።»

ለችም ስላገኘኝ በጣም ተደሰትኩ፤ እህቱን ዱዜንጂንም በደንብ አውቃታለሁ። እንደ እርሱው መልካምና ደግ ፍጥረት ነች። በደንብ የተግባባነው ከዚያን ጊዜ ጥቂት ዓመታት ቀደም ብለው የሞቱት እናታቸው ኤሌና ቱትሲ ስለነበሩ ነው። ለችምና

ዱዜንጂ አባታቸው ሁቱ በመሆናቸው የሚቆጠሩት እንደ ሁቱ ነው - በእናታቸው ማንነት ምክንያት ግን ሩዋንዳ ውስጥ ቱትሲ መሆን ምን ማለት እንደሆነ ይረዱታል።

ወደ ከፍሉ እየሄድን ሳለን ኦገስቲን ማለቃቀስ ጀመረ። «ልሂድ። እናቴን፣ አባቴንና እህቴን ማግኘት አለብኝ። ከዚህ ቦታ ለቅቄ ወደ ኪጋሊ መሄድ ይኖርብኛል።»

እጁን ይዤ «ተው» አልኩት። «እንደዚህ አትሁን። በርታ። አሁን ወዴትም መሄድ አትችልም - ውጪ ላይ የባሰ አደገኛ ነው። ደኅና በመሆናችን ተመስገን እንበል። በዚያም ላይ ቱትሲ ብትመስልም እንኳን ሁቱ ነህ፤ ያንንም ለማረጋገጥ የሚሆን መታወቂያ ደብተር አለህ። ማንም አይነካህ።»

«አዬ፣ ተሳስተሻል። እንግዳ ማረፊያው ቤት የነበሩት ሰዎች የቱትሲ አማጺ ቡድኑ ጆሮ ጠቢ ነው እያሉ ሲንሾካሾኩብኝ ሰምቻቸዋለሁ። ለሩአግ እየሰለልኳቸው መስሏቸዋል! መታወቂያ ደብተሬ ምንም ማለት አይደለም! የሐሰት ነው ይላሉ። እዚህ ማንም ማንነቴን አያውቅልኝም። ይገድሉኛል ... እንደሚገድሉኝ ታውቆኛል!» ወጣቱ ጓደኛዬ በጣም ስለፈራ እንባው ዱብ ዱብ ይልና እጁም ይንቀጠቀጥ ጀመር።

«አትፍራ ኦገስቲን። አብረን እስከሆንን ድረስ ስለምንጠባበቅ ምንም አንሆንም።»

ሲቃ ስለያዘንና ፈጽሞ ስለመዳናችን እርግጠኛ ስላልሆንኩ እንደዚህ ዓይነት ነገሮችን ለመናገር ብርታቱን ከየት እንዳመጣሁት እንጃ። እግዚአብሔር እንደሚያግዘን ግን እምነት ሊኖረኝ ግድ ነው፤ ካልሆነማ ይህን ሁሉ ሥቃይና መከራ ለምን እናሳልፋለን? ወዳጆቻችን ሲከዱንስ ለምን ቆመን እናያለን?

ዱዜንጂ ለጊዜው በከፍሏ ስለሌለች ዓይኖቼን ጨፍኜ ጸጥ ብዬ ጋደም አልኩ። ለቀናት ምንም ያልተኛሁ ቢሆንም እንቅልፍ የሚባል ዞር ሊልብኝ አልቻለም። ወደ ቁሱ ቤት ስሄድ ባጋጠሙኝ ነገሮች ላይ አእምሮዬ ያንጥብባል። የቤተሰቤ አባላት በሬድዮናችን ዙሪያ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ማወቅ ተስኗቸው ተኮልኩለው አየኋቸው። እናቴ ውጪ ላይ እኔን ለመጠበቅ እንደተኛች ያየሁት አመድ የመሰለው ፊቷ በምናቤ መጣብኝ። አባቴም በሺህዎች በሚቆጠሩ የፈሩ ሰዎች ፊት ቆሞ ሊያበረታታቸው ሲሞክር ታየኝ። ወደ ቁሱ ቤት ስንመጣ ገዳዮቹ ይዘው ያየኋቸው ገጀራዎች ሳይቀር መጡብኝ።

ሃሳቤ በተመሰቃቀለብኝ በዚህ ሰዓት የዳማሲንን በደስታ የተሞላ ድምፅ ሰማሁና ቁጭ አልኩ። በሕልም ዓለም ያለሁ መሰለኝ፤ ግን አልነበርኩም። ወንድሜ ከመኝታ

ቤቷ ውጪ ካለ ከአንድ ሰው ጋር ሲያወራ ነው የተሰማኝ። ከአፍታ በኋላ ወዳለሁበት ክፍል መጥቶ አገኘኝ።

«ዳማሲን እንዴት ሆናችሁ? እማማና አባባስ የት ናቸው?»

«እኔ እንጃ፣ ኢማኪዩሌ። ተለያይተናል፤ ማምለጥ ነበረባቸው።»

«ለምን? ምን ተፈጠረ?»

«ኢቃጠሉት።»

«ምን? እነማን ናቸው? ምኑን ነው ያቃጠሉት?»

«ገዳዮቹ ... ቤታችንን ኢቃጠሉት። በቃ ወድሟል።»

በአልጋው ላይ ተመልሼ ትኝት አልኩ። አባቴ ለእናቴ በራሱ እጅ የገነባላትን ቤት ገና መጨረሱ ነበር። የመጦሪያ እልፍኛቸው ሲወድም ማየቱ መቼም ልቡን ይሰብረዋል።»

«አባባስ ስለቤቱ ያውቃል?»

«በእርግጥ ያውቃል - ዓይኑ እያየ እኮ ነው ያቃጠሉት» አለኝ ዳማሲን። እኔ ከሄድኩ በኋላ በነበሩት ጥቂት ሰዓታት ውስጥ ስለተከሰተው ነገር ሁሉ ይነግረኝ ጀመር። እንደተገነዘብኩት አባታችን ከነዚህ ግድያዎች በስተጀርባ የመንግሥት እጅ እንዳለ ለማመን አልፈለገም፤ ስለዚህ አስተዳዳሪውን ካባዬን ከለላ ይሰጣቸው ዘንድ ለመጠየቅ በተሽከርካሪ ሄዶ ነበር።

«ካባዬ እኮ አባባን በእስር ቤት በቾጋር ሊገድለው ሞክሯል» ስል አቋረጥኩት። «ምን አስቦ ነው?»

«ምንም አማራጭ የለኝም አለን» ሲል ዳማሲን ቀጠለ። «ገዳዮቹ በቤታችን ዙሪያ ነበሩ፤ ብዙዎችም መጉረፍ ቀጠሉ። አባባ የእርሱን እገዛ ፈልገው ለመጡት ሰዎች ኃላፊነት ስለተሰማው ወደ ካባዬ ከለላ ፍለጋ ሄደ። ለአስተዳዳሪው በቤታችን በሺህዎች የሚቆጠሩ ቱትሲዎች እንዳሉ ነግሮ የተቻለውን ያህል ወታደሮች እንዲልክለት ጠየቀው።»

ዳማሲን እንደነገረኝ ካባዬ ለአባቴ ሐሳብ እንዳይገባው ነግሮ ወደ ቤት የሚያደርሱት ሁለት ወታደሮች ይሰጠዋል። እዚያ ሲደርሱ ግን ነገሩ ሁሉ አይሆኑ ሆኗል።

ወታደሮቹ በአባቴ ላይ ያሾፉበት ያዙ። መሳቂያ መሳለቂያቸው አደረጉት፤ እንዲህ ሲሉም ጠየቁት - «ምን ዓይነት ጅላንፎ ነህ? ምን ዓይነት ድድብና ቢኖርብህ ነው

አስተዳዳሪው አንተንና እነዚህን ሁሉ በረሮዎች ከጉዳት እንድንከላከል ይልኩናል ብለህ ያሰብከው? እነዚህ በረሮዎች ማለቅ አለባቸው!»

ቪያኒ ወዳለንበት ክፍል ድንገት መጣ። ሁለቱም ወንድሞቼ ተደናግጠዋል። ዳማሲን ፊቱ ቲማቲም መስሎ ቀልቷል፤ የቪያኒም ፊት የፍርሃትና የድንጋጤ ገጽታ ይነበብበታል። ዳማሲን በሲቃ ድምፅ ከዚህ ክስተት ቀጥሎ የተከሰተውን ነገረኝ።

«ወታደሮቹ ገዳዮቹን ለማሰባሰብ ወደ ሰማይ ጥይት ተኮሱ ... ገዳዮቹም እንደ አራዊት እየጮኹና ገጀራዎቻቸውን እየሰበቁ በሩጫ መጡ። እኛ ቤት አጠገብ የነበሩት ቱትሲዎች በጣም መጮህ ሲጀምሩ አንድ ግዙፍ የቁራ መንጋ የጮኸ ይመስል ነበር። በሺህዎች የሚቆጠሩት ስደተኞች በእጅጉ በመሸበር እግሮቻቸው ወዳመራቸው ሮጡ።

«አባባ፣ እማማና ቪያኒም ሸሹ። እኔም ገዳዮቹ ከኋላችን እንዳልተከተሉን አረጋግጬ የቤተሰባችን አባላት ተከተልኳቸው። ወታደሮቹ ወደ ገዳዮቹ ዞረው «ይህ ቤት በበረሮዎች ተሞልቷል - በጭስ አፍኑት! ምን እየጠበቃችሁ ነው? ስንት ሥራ ይጠብቃችኋል እኮ! እነዚህን በረሮዎች ረግጦ መግደያው ሰዓት አሁን ነው!» ሲሉ ጮሁባቸው።

«ያኔ ገዳዮቹ አሳበዳቸው። ቤቱን ሰብረው ገብተው ሁሉን ነገር ከሰባበሩ በኋላ ተሸከርካሪዋ ላይ እሳት ለቀቁባት። ያልሰባበሩትን ነገር ደግሞ ዘረፉት ... ከዚያም በኋላ ቤቱን አጋዩት። ከአምስት ደቂቃ ባነሰ ጊዜም መጠለያችን በነበልባል ተዋጠ። አባባም ራሱን ስቶ ወደቀ - ያየውን ነገር ሊያምን አልቻለም። ሁኔታው ይሻሻላል በማለት ሰዎችን ሲመክር ቆይቷል፤ አሁን ግን እንደተሳሳተና አንዳች ነገር ለማድረግም ሰዓቱ በጣም እንደዘገየ አየ። ሙሉ ሕይወቱ ከፊት ለፊቱ ጋየበት።

«ዶቅዶቄውን ደብቆ ወደነበረበት ስፍራ ቁልቁል አውርደነው አግኝቶ አስነሳትና እማማንም አፈናጠጣት። ገዳዮቹ እያበዱ ስለነበር የምናወራበት፣ የምናስብበትም ሆነ የምንሰነባበትበት ጊዜ እንኳን አልነበረንም። አባባ በጩኸት «ሩጡ! ወደ ቁስ ሙሪንዚ ቤት ሄዳችሁ እህታችሁን አግኟት። እናታችሁን ከዚህ ስፍራ ማራቅ አለብኝ። ተደበቁ - በኋላ እንፈላለጋለን!» ብሎ ሽምጥ ጋልቦ ጠፋ።

«እማማ የአባባን ትከሻ ተደግፋ እንባዋን ታወርደዋለች። አየት አድርጋን «ልጆቼ ... ልጆቼስ ምን ሊውጣቸው?› ስትል ብቻ ነው በዶቅዶቄው ድምፅ መካከል የሰማኋት። ከዚያም በቃ ሄዱ።»

«ግን የት ነው የሄዱት?» ስል ጠየኩት በተሰበረ ልብ።

«እኔ እንጃ - ምናልባት ወደ አክስታችን ወደ ሲሲሌ ቤት ወይም ወደ አንደኞቹ አብያተክርስቲያናት ሊጠለሉ ይሆናል። በጣም ያደናግራል.. በመጨጭኸ ስንሮጥ

ነበር፡፡ በሺህዎች የሚቆጠሩ ቱትሲዎች ሕይወታቸውን ለማዳን ይሮጣሉ - ወደየተራራው፣ ጫካው፣ ረግረጉና ወደ እግር ኳስ ሜዳው፡፡ ግን ኢማኪዩሌ የትም ይሂዱ የት ገዳዮች አሉ፡፡ እኛስ የሆንን እንደሆን የምንሸሸግበት ቤት እንኳን የት አለን?»

መናገር ቢሳነኝም ለወንድሞቼ የሆነ ተስፋ መስጠት እንዳለብኝ ተሰምቶኛል፡፡ «እዩ ቤታችንን አጣን፤ ግን ቤታችን አብረን በሄድንበት ሁሉ የትም ይሆናል» አልኳቸው በቻልኩት መጠን ተስፋ-ቢስነቴን አስወግጄ፡፡ «ሁላችንም ኪጋሊ ሄደን እንዳዲስ መኖር እንጀምራለን፡፡»

ሁለቱም ወንድሞቼ እንደ እብድ አዩኝ፡፡ «ኢማኪዩሌ ምንድነው የምትዪው?» ሲል ዳማሲን በጎ በጎውን በመመኘቴ ተሰላችቶ በንዴት ጠየቀኝ፡፡ «ግድያው በዙሪያችን እየተካሄደ ነው፡፡ አሁን የመጣነው አስከሬኖችን እያለፍን ነው፤ አብዛኞቹም የምናውቃቸው ሰዎች ናቸው! ወጥመድ ውስጥ ገብተናል፡፡ ከዚያ በፊት በእርሱ ፊት ላይ አይቼው በማላውቀው ገጽታ አየኝ፡፡ ይህ እይታው ምን እንደሚያንጸባርቅ ግን አላወቅሁትም - ውንጀላ፣ ብስጭት፣ ንዴት? ቀጣዮቹ ቃላቱ እንደ ጅራፍ ይጋረፉሉ - «ነገሮች ሁሉ እንደሚሻሻሉ ስትነግሪን የቆየሽው ለምንድነው?» አለኝ፡፡

ከልቤ ተጸጸትኩ፡፡ የኔ መልካም አሳቢነት ወንድሞቼንና ወላጆቼን ወደዚህ ወደገባንበት ቅዠት መርቷቸው ይሆን? አሁን ለሚገጥበት ዕጣ-ፈንታቸው ተጠያቂ እሆን ይሆን? አባባ ስፍራውን ለቅቄ አልሄድም ባለበትና ሁሉም ነገር በጣም በፍጥነት እየተካሄደ በነበረበት ሁኔታ ሌላ ምን ላደርግ ይቻለኛል? በደረሰብን ሥቃይ መነሻነት ተስፋ መቁረጥ፣ በትካዜ መስጠም ወይስ በፍራቻ መርበድበድ ነበረብኝ? ያም ቢሆን ሁኔታዎችን ያባብሳል፡፡ ሰዎች በሕይወት ለመቆየት ተስፋ ያስፈልጋቸዋል፡፡

እግዚአብሔር እኛን ቱትሲ አድርጎ የፈጠረን ሊያሣርደን ነው ብዬ ማመን አልፈለግሁም፡፡ በጣም እወደው የነበረው ዳማሲን ግን በንዴትና በተስፋ መቁረጥ አየኝ፡፡ «አዝናለሁ» አልኩት በእንባ ተሞልቼ፡፡ «የቀረን አንድ ብቸኛ ነገር ቢኖር ተስፋ ነው፤ ስለዚህ እሱን እንኳን አንጣው ብዬ ነው፡፡ ካሁኑ ተስፋ መቁረጥ የለብንም፡፡ ለምርቃቴ ለመጭው ዓመት እንደምትመጣ ቃል እንደገባህ እስኪ አስታውስ፡፡ በዚህ መንገድ ያንን አናሳካውም፡፡»

«እውን እንዲህ ታስቢያለሽ?» ሲል ጠየቀኝ ወንድሜ አንጸባራቂ ፈገግታውን ድጋሚ እያሳየኝ ግን አለማመኑ እያሳወቀበት፡፡

ያኛን ሌሊትም እንኳን እንቆይ እንደሆነ አላወቅሁም፣ ቢሆንም በቻልኩት መጠን ያለኝን ሁሉ በራስ መተማመን አሰባስቤ «ዳማሲን በእርግጠኝነት እንችላለን» አልኩት፡፡

«እሺ፣ አንቺ ተስፋ የማትቆርጪ ከሆነ እኔም አልቆርጥም» አለችና ወደ ቪያኒ ዞረ።።

«አገስቲን በጣም ስለፈራ አብረኸው ብትሆን ይሻላል።። ምንም ተከሰተ ምን ይህን ቤት ጥላችሁ አትሂዱ - ኢማኪዩሌንም እንድትሄድ አታድርጓት።። ገዳዮችና ደፋሪዎች በየስፍራው አሉ።። ያንን እንደምታደርግ ቃል ግባልኝ።።»

ትንሹ ወንድማችን «በጀ፣ ቃል እገባለሁ» አለ።።

ከዚያም ዳማሲን «እኔ እዚህ አልቆይም።። ቄሱ አባባን እንደማይወዱት አውቃለሁ፣ እኔንም እንደማይወዱኝ ይገባኛል።። በዚያም ላይ ብዙ ሰዎች ወደዚህ ስመጣ አይተውኛል፤ ያ ደግሞ ወዳንቺ ይመራቸዋል።።»

አብሮን እንዲቆይ ብንለምነውም ሃሳቡን ሊቀይር አልፈለገም።። ጥሩ ጓደኛው ቦን በቅርብ ስለሚኖር ዳማሲን ከሱ ጋር እቆያለሁ አለ።። ሁቱው ቦን ወንድሜን ለተወሰነ ጊዜ ሊደብቀው ይችላል።።

ዳማሲንን እስከ በረንዳው ድረስ ስሸኘው እርሱን ማናገር እንደሚያሳምም ተረዳሁ።። ለወትሮው «በኋላ እንገናኝ» ወይንም «በጥቂት ሳምንታት ውስጥ እንገናኛለን» ሳንባባል ተሰነባብተን አናውቅም።። ያ ጊዜ ቆንጆ ፊቱን የማይበት የመጨረሻ የመገናኛ ጊዜያችን እንደሆነ ባውቀውም በዚያን ወቅት ደኅና ሁን ማለት አቃተኝ።።

ወንድሜ፣ ነፍሴ፣ እጆቹን በኔ እጆች ላይ ሲያስቀምጣቸው እንደ ላባ ቀለሉኝ።። ምንም ያህል ብነካካቸው የእጆቹ ክብደት ሊሰማኝ አልቻለም - ልትጠፋ የነበረችን ነፍስ እጆች ነው የያዝኩት።። ልቤ ልትፈነዳ ደረሰች።።

ዳማሲን በመጨረሻ እጆቹን እስኪሰብ፣ በሐዘን ፈገግ እስኪልና በበሩ እስኪወጣ ድረስ እርስ በርሳችን በጸጥታ ተፋጠን ስንተያይ ቆየን።።

ምዕራፍ 8
ልጆቹን ስሰናበት

ዳማሲን ከመሄዱ የቁሱ ግቢ የፊት በር ተንኳኳ። ያንኳኳው የቪያኒ የሁለተኛ ደረጃ መምህር የሆነው ንዚማ ሲሆን አመጣጡም ቁስ ሙሪንዚን ፈልጎ ነው። የሹክሹክታ ንግግር ከተደረገ በኋላ በሩ ተዘጋ። ወጥቼ ንዚማን በቁሱ ዛፍ ጥላ ስር ተቀምጦ አገኘሁት። በዚያ ደብዘዝ ባለው ብርሃንም ቢሆን በፊቱ ላይ የሚነበበውን ህመም ማየት አይከብድም።

እንደፈራ ልጅ አድርጎታል - «ምን ያደርጉናል? የሚገድሉን ይመስልሻል?» ሲል ጠየቀኝ።

በሩ ጋ መምጣቱን እንደሰማሁ በራስ ወዳድነት ስሜት ተውጬ የማበረታቻ ቃላት ይሰነዝርልኝና ጥንካሬ ይለግሰኝ ዘንድ ተመኘቻለሁ፤ ግን እርሱ ነው ሁለቱንም ላያገኛቸው ይሻቸው የያዘው።

መምህር ንዚማ ሚስትና ልጆቹ ራቅ ባለ መንደር አማቱን ሊጠይቁ ሄደዋል። ደኅና ስለመሆናቸው ምንም የሚያውቅበት መንገድ ስላጣና ጥርጣሬ ስለገባው ተሰቃየ። «የማልተዋቸው ህልሞች አሉኝ» አለ። «ሚስቴና ልጆቼ ሲታረዱና እፊቴ ሲቆራረጡ ይታየኛል። ይህን ለማስቆም እንደምታዪኝ ምንም ማድረግ አልችልም። በአሁኑ ሰዓት እኮ ተገድለው መንገድ ላይ ተጥለው ነው የሚሆነው።»

በቻልኩት መጠን ላጽናናው ሞከርኩ፤ ግን ምን ልለው እችላለሁ? እኔ ራሴ እርግጠኛ ባልሆንኩበት ሁኔታ ነገሮች ጥሩ ሊሆኑ እንደሚችሉ ስንት ጊዜ ልናገር?

በጣም አቃሰተና «የት አባቴ ልግባ? ውጪ ያለው ሁሉም ሰው ገጀራ ይዟል፤ ጠመንጃ የያዙም አይቻለሁ።»

«ግድያው እስኪያቆም ድረስ እዚህ ቆያ፤ ከዚያም ከቤተሰብህ ትገናኛለህ» አልኩት መንፈሱን ለማረጋጋት።

ራሱን ነቅንቆ ቆመና «ልጄ፣ እዚህ አልቆይም፤ ሌላ የምሄድበት ቦታም የለኝ።»

«እጸልይልሃለሁ።»

«አመሰግናለሁ ኢማኪዩሌ።»

ተሰናብቶኝ ቁስ ሙሪንዚ ይጠብቁት ወደነበረበት ወደ ቤቱ ፊት ለፊት ሄደ። ቁሱ ንዚማን እንደማይሸሽጉት ነግረውት ሳይሆን አይቀርም በሩን በእጃቸው ሲያመላክቱት

ምንም ቃል ሳይተነፍስ ወጣ፡፡ በኋላ እንደሰማሁት ይህ ምስኪን ሰው ተቆራርጦ የተገደለው ከቁሱ ቤት ጥቂት መቶ ሜትሮች ርቆ ባለ መንገድ ላይ ነው፡፡

ከተወሰኑ ሰዓታት በኋላ ብቻዬን በተቀመጥኩባት በአንዲት ትንሽ መኝታ ክፍል ቁስ ሙሪንዚ ሌሎች አምስት ቱትሲ ሴቶችን በጸጥታ አስገቡ፡፡ ሁሉም የአካባቢያችን ሰዎች እንደሆኑ ባውቅም አንዳቸውንም በደንብ አላወቅኋቸውም፡፡

ሴቶቹን ወደ ክፍሏ ሲያመጧቸው ቁሱ ተደናግጠዋል፡፡ «ፍጠኑ፣ ፍጠኑ!» የሚንሾካሾኩት በጣም በፍጥነት ስለሆነ ልንሰማቸው አልቻልንም፡፡

«እዚህ ጠብቁኝ፤ ታዲያ ደሞ ዝም በሉ እሺ» አሉን በሩን ዘግተው ሲወጡ፡፡

አብረን የነበርነው ስድስት ቱትሲ ሴቶች ከሞላ ጎደል እርስ በርስ የማንተዋወቅ ቢሆንም ሁለት ነገሮች ግን ያመሳስሉናል - እየታደንን መሆናችንና የምንደበቅበት ምንም ስፍራ የሌለን መሆኑ፡፡ ለመናገርም ሆነ ለመተዋወቅ በጣም ፈርተን እርስ በርሳችን እየተያየን ቆመናል፡፡ ውጪ ምን እየተከሰተ እንዳለ አናውቅም፣ ከቁሱ ድንጋጤ እንደተረዳነው ግን ነገሮች ተበለሻሽተዋል፡፡

ከቤቱ ውጪ ድንገት ጩኸቶች ይሰሙ ጀመር - በእጆቻችን ላይ ያሉትን ጸጉሮች እንዲቆሙ ያደረጉ እጅግ የሚያስጨንቁ የሲቃ ጩኸቶች፡፡

ከዚያ በኋላ አሰቃቂዎቹ ንዴት የሚንጸባረቅባቸው ድምጾች መጡ፣ «ግደሏቸው! ግደሏቸው! ሁሉንም ግደሏቸው!»

ብዙ መጪጪህና የድረሱልኝ ጥሪ ይሰማል፤ «ግደለው! ግደሉት! ግደላት!» የሚልም ድምፅ ይከተላል፡፡

ፈራን፡፡ ከሴቶቹ አብዛኞቹ መሬት ላይ ተኙ፣ አልጋም ስር ተደበቁ፡፡ በጣም ከመንዘፈዘፌ የተነሣ መሬቱም ጭምር የሚንቀጠቀጥ መሰለኝ፡፡ ዓይኖቼ ቤቱን መደበቂያ ፍለጋ ሲያስሱ በኮርኒሱ ላይ ባለች አንዲት ቀዳዳ ላይ አተኮሩ፡፡

«እዚያ ላይ መደበቅ እንችላለን» አልኩ ወንበር ወደ ቀዳዳዋ ስር እየሳብኩና በእጆቼ ወደላይ እየተንጠራራሁ፡፡ አንዷን ሴትዮ ወደ ላይ ስቤ አወጣኋት፡፡ ሁለታችን ደግሞ አንድ ላይ ሌሎቹን በቀዳዳዋ ሽቅብ ሳብናቸው፡፡ ከዚያም ቁሱን እስኪመለሱ እንጠብቃቸው ያዝን፡፡ በዚያች በተጨናነቀችና በምታፍን ቦታ ልብሶቻችን በላብ እስኪጠመቁና አየር እስኪያጥረን ድረስ ጭብጥ ብለን ተቀመጥን፡፡ ቁስ ሙሪንዚ ከሁለት ሰዓታት በኋላ ተመልሰው በቤቱ መካከል ቆመው ራሳቸውን በግራ-ግባት ያኩ ገቡ፡፡

«የት ይሆኑ? አይ አምላኬ እዚህ ነበር የተውኳቸው!»

በጣም ባልፈራ ኖሮ ሳቄን እለቀው ነበር። በቀዳዳዋ ራሴን አውጥቼ «እዚህ ነን!» ስል አንሾካሾክሁ።

ቄሱ ራሳቸውን ነቅንቀው ሊያናግሩን መፈለጋቸውን ገልጸውልን ወዲያውኑ እንድንወርድ አዘዙን። ፊታቸው አሁንም በጣም እንደተቸገሩ ያስታውቃል። «ሁላችሁም እንደፈራችሁ አውቃለሁ፤ በእርግጥ ልትፈሩም ይገባችኋል» አሉን። «ውጪ ላይ ነገሩ ሁሉ ከቁጥጥር ውጪ ሆኗል። ገዳዮቹ *በሁሉም* ሰው ቤት እየዞሩ ነው። ዛሬ እኔ ቤት አልመጡም፤ በማናቸውም ሰዓት ግን ሊመጡ ይችላሉ። እውነቱን ንገረን ካላችሁኝ ምን እንደማደርጋችሁ አላውቅም... እስኪ ላስብበት።»

ፍራቻቸንን አይተው ወዲያውኑ መፍትሔ አመጡ። «አይዟችሁ አላስወጣችሁም» ሲሉ አረጋገጡልን። እስኪ በጥሞና አዳምጡኝ። ነገ ሲነጋጋና ማንም ከመኝታው ሳይነሳ ግድያው እስኪያቆም ድረስ ወደምትቆዩበት አንድ ሌላ ክፍል እወስዳችኋለሁ። በቤቱ ውስጥ ላሉት ሁሉ እንዳስወጣኋችሁ እነግራቸዋለሁ። የእናንተን እዚህ መኖር የማውቀው ብቸኛ ሰው እኔ ብቻ እሆናለሁ። ተራ ሐሜት እንኳን ሁላችንንም ሊያስገድለን ይችላል። እነዚህን የግድያ ዘመቻዎች ካሁን በፊት አይቻቸዋለሁ - አንዴ የደም ጥማቱ ከጀመረ ማንንም አታምኑም፣ የራሳችሁንም ልጆች ሳይቀር። አንድ ሰው ካገኛችሁ አለቀላችሁ! ስለዚህ በእግዚአብሔር ደማችሁ በቤቴም ሆነ በጂ እንዲፈስ አልፈልግም።»

ከዚያ ቄሱ ወደኔ ዞረው እንደ ቢላዋ የቆረጡኝን ቃላት ነገሩኝ - «ወንድምሽና ጓደኛው እዚህ መቆየት አይችሉም። አሁኑኑ ሄደው ሕይወታቸውን ያትርፉ። ወንዶችን ማስጠለል ለኔ በጣም አደገኛ ነው። እንደምታዪው እናንተ ሴቶቹም በዝታችሁብኛል።»

በሙሉ ዓይናቸው ሊያዩኝ አልቻሉም - ቪያኒንና ኦገስቲንን በዚያ ሰዓት ማባረሩ በእርግጠኝነት ማለት በሚያስደፍር ሁኔታ ወደ ሞታቸው መላክ ማለት እንደሆነ ሁለታችንም እናውቃለን።

«እንዴ! ቄስ ሙሪንዚ ኧረ እባክዎት! እንዴት -»

ጸጥ በይ በሚል ዓይነት ምልክት ጣታቸውን ከንፈራቸው ላይ አድርገው ንግግራችንን ቋጩት። «መሄድ አለባቸው፣ ኢማኪዩሌ። ልወስዳችሁ ከጥቂት ሰዓታት በኋላ ስመጣ ወደ በሩ ወስደሽ ታስወጫቸዋለሽ። ታዲያ ማንም እንዳያይሽ ተጠንቀቂ።»

ቄሱ ቤቱን ለቀው ሲሄዱ በሹክሹክታ ረገምኳቸው። ለኛ ከለላ በመስጠት እንደ ቅዱስ እየሰሩ እንዴት እንደገና ተገልብጠው ወንድሜንና ኦገስቲንን ወደ ገዳዮቹ እጆች ያስገቧቸዋል?

እያዳኑን የነበሩትን ሰው ልቆጣቸው አልፈለግሁም፣ ቢሆንም ራሴን መቆጣጠር አልቻልኩም - የባሰውንም ጠረጠርኩ። በሌሎች የግድያ ዘመቻዎች አንዳንድ የሁቱ ወንዶች ወንድ ቱትሲዎችን ትተው ሴት ቱትሲዎችን ይደብቃሉ። ቱትሲ ሴቶችን የሚይዟቸው በውበታቸው ምክንያት ወንዶቻቸው ካለቁ በኋላ በሚስትነት ሊይዟቸው ስለሚፈልጉ ነው። ቱትሲዎች፣ በተለይ ቱትሲ ሴቶች የሚጨቆኑበት ሌላ መንገድም ነው ይህ ተግባር። ቄሱ ስድስት ሴቶችን ሲያስገቡ ድብቅ ፍላጎት አላቸው ብዬም ማሰብ ጀምሬያለሁ።

በዚያ ምሽት ለመተኛት ሞከርን፤ ግን ወደፊት ምን እንደተደገሰልን ሳናውቅ ማረፍ አስቸገረን። ዓይኖቼን በጨፈንኩ ቁጥር እጅግ ወጣት የሆኑት የ20 አመቱ ቪያኒና የ18 አመቱ አገስቲንን ከቤቱ ሲወጡና የሚውለበለቡ ገጀራዎችንና የሚጮሁ እብዶችን ሽብር ሲጋፈጡ ታሰበኝ። ብቻቸውን እንዴት አስወጣቸዋለሁ? እንዲሄዱ ማድረግ አሳልፎ መስጠትና መክዳት ይሆንብኛል።

አብሬያቸው ለመሄድ ወሰንኩ፤ ግን ቆይቼ ሃሳቤን ቀየርኩት ... በተደጋጋሚም ቀያየርኩት። ብንጠቃ እንዴት ልከላከላቸው እችላለሁ? እንዲያውም ላዘገያቸው እችላለሁ። ከሴት ጋር ከሆኑ ደግሞ የባሰ አትኩሮት ሊስቡ ይችላሉ፤ ያ ደግሞ ሁላችንንም ያስገድለናል።

ከዚያ የዳማሲን የመለያያ ቃላት በጆሮዬ አቃጨሉ - «ምንም ቢመጣ ይህን ቦታ ትታችሁ አትሂዱ።»

በጸጥታ አቃሰትኩ። ሌሎቹም ሰምተውኝ ደነገጡ።

«አትጨነቂ፣ ወንድምሽ ትልቅ ሰው ነው፤ ትንሽ ልጅ አይደለም» አለች ከኔ ጋር ከተደበቁት ሴቶች አንዷና ለሰዓታት ስገላበጥ ያየችኝ ቴሬሴ። «ወጣቶች ስለሆኑ ለራሳቸው አያንሱም። ከነሱ ጋር ከሄድሽ ደፋሪዎቹን ትስቢያለሽ። ይሂዱ - የሚሻለው እሱ ነው። እመኚኝ፤ ወላድ ነኝ። ከኛ ጋር ብትሆኚ ነው የሚሻልሽ።»

ልክ እንደሆነች አሰብኩ፤ ግን ሃሳቤን ምንም አላቀለለልኝም። ቪያኒ ከሄደ ከቤተሰቤ *ማንንም* በድጋሚ ላገኝ አልችልም።

ለንጋት ሁለት ሰዓታት ሲቀሩ ቄሱ ወደ ከፍላችን መጥተው በጉልህ ሹክሹክታ «ተነሡ፣ እንሂድ! እንሂድ፣ ፍጠኑ!» ካሉ በኋላ እኔን አይተው «ቶሎ ወንድምሽን ተሰናብተሽ ነይ» አሉኝ።

ወደዚያ ክፍል ሄዶ ቪያኒንና አገስቲንን ከእንቅልፋቸው መቀስቀሱ እስከዚያን ጊዜ ድረስ በሕይወቴ ካደረኳቸው ነገሮች ሁሉ ከባዱ ነው። እንባ ከዓይኖቼ እንደ ዝናብ

ወረደ - አምላክ ገለታ ይግባውና ጨለማው በዓይኖቼ ላይ የነበረውን ሃፍረቴን፣ ሰቀቀኔንና ያለጥርጥር የሚያስታውቀውን ፍርሃቴን ደብቆልኛል።

እጇን በቪያኒ ጀርባ ላይ አድርጌ እንባዬን ለመቆጣጠር በዝግታ በመናገር ቀስ ብዬ ቀሰቀስኩት። «ተነሥ ... ነግቷል። ቁሱ እንዳሉት... ሁላችንም መቆየት አንችልም... ወንዶቹ ... መሄድ አለባችሁ... አትጨነቁ ... አባባን ታገኙታላችሁ... ምን እንደምታደርጉም ይነግራችኋል።»

ልቤ እየተጨመቀች እንደሆነ ሁሉ መጥፎ ስሜት ተሰማኝ።

ቪያኒና አገስቲን ከአልጋው ዘለው ወረዱ። «ምን? የት ነው የምንሄደው? ያለ ዳማሲን የትም ልንሄድ አንችልም። ያለሱ ብንሄድ እሱስ ምን ይላል?» አለ ትንሹ ወንድሜ እንቅልፍ የተጫጫነውን ዓይኑን እያባበሰ።

ቃላቱ ሸነታተሩኝ። እኔ ወደ አደጋ እየዶልኩት ሳለሁ ስለወንድማችን ደህንነት ያስባል። ሕፃን ልጇን ለተኩላ መንጋ እንደምትልክ እናት መሆኔ ተሰማኝ። «ዳማሲን ምንም አይሆን» አልኩ ድምጼ ላይ ምንም ለውጥ ሳላደርግ። «የሆነ ቦታ በደኅና ቁጭ ብሎ ነው የሚሆነው። ና! መሄድ አለብን።»

ልጆቹን በጨለማው መተላለፊያ ወደ ፊተኛው በር ወሰድኳቸው፤ ኧረ እንዲያውም አባረርኩ ማለት ይሻላል። ቪያኒን በተቻለኝ መጠን ጥብቅ አድርጌ አቀፍኩና ደጋግሜ ሳምኩት። «በርታ ቪያኒ፤ በቅርብ ቀን መልሰን እንገናኛለን።»

ልጆቹ ከግቢው ወጡ፤ በጨለማውም ተዋጡ።

ክፍል ፪

የተደበቅኩባቸው ጊዜያት

ምዕራፍ 9
ወደ መታጠቢያው ክፍል

በቪያኒና በአገስቲን ላይ በሩን ዘግቼ ሌሎቹን ቱትሲ ሴቶች ተቀላቀልኩ።

ቄስ ሙሪንዚም የእጅ መብራት እያበሩ በጨለማው ቤት አድርገው ቁልቁል ወደ መኝታ ክፍላቸው እየመሩ ወሰዱን። መብራቱም የጓሮ በር በመሰለኝ አንድ በር ላይ እስኪያርፍ ድረስ ዓይኖቻችን ተከተሉት።

«ይህ ነው የምታርፉበት» አሉን አዲሱን ቤታችንን እንድናየው በሩን እየከፈቱ። አራት ጫማ ርዝመትና ሦስት ጫማ ወርድ ያላት መታጠቢያ ክፍል ነበረች። መብራቱ ግንቡን ወገቡ ድረስ በሸፈነው በነጩ እምነበረድ ላይ እንዳረፈም አንጸባረቀ። ባንደኛው ጥግ መታጠቢያና በሌላኛው ደግሞ መጸዳጃ ሲኖር ፍሳሽ ማስወገጃ ያለው የቁም እጅ መታጠቢያ የሚያሠራ ትርፍ ስፍራ ግን አልነበረውም። ከኮርኒሱ አጠገብ ደግሞ ትንሽ የአየር ማስገቢያ ፉካ ስትኖር እርሷም በቀይ ጨርቅ ተሸፍናለች - ያም ክፍሏን የባሰ ጠባብ አስመስሏታል።

ስድስታችንም እዚያች ስፍራ ውስጥ ልንቀመጥ መቻላችንን ላምን አልችልም፤ ቄሱ ግን በበሯ አጣድፈው አስገቡንና አጣብቀው አጎሩን። «እዚህ ስትቆዩ ፍጹም ጸጥታ ሊኖራችሁ ግድ ይላል፣ በጣም *ጸጥ* ማለት ይኖርባችኋል» አሉ። «ምንም ዓይነት ድምፅ ብታሰሙ ትሞታላችሁ። ከሰሟችሁ ያገኟችኋል፤ ከዚያ ይገድሏችኋል። እዚህ መኖራችሁን ማንም ማወቅ የለበትም፤ የኔም ልጆች ቢሆኑ። ይገባችኋል?»

«አዎን *መምሬ*» አልን በአንድነት።

«የመጸዳጃ ቤቱን ውሃ አትልቀቁት፤ ገላችሁንም መታጠብም አትችሉም።» መብራታቸውን ከመጸዳጃው በላይ ባለው ግንብ ላይ አበሩ። «ይህኑ ዓይነት ልባጥ ያለው ሌላ መጸዳጃ ቤት ከዚህ ግንብ ጀርባ አለ። ስለዚህ ውሃ ማፍሰስ ግድ ካለባችሁ ሌላ ሰው ያንኛውን ሲጠቀም እስክትሰሙ ጠብቁና ከዚያኛው *ጋር በተመሳሳይ* ጊዜ አድርጉ። ገባችሁ?»

«አዎን *መምሬ*።»

የእጅ መብራታቸው ቀጭ ብሎ ጠፋ፣ የመጨረሻ ቃላቸውንም የተናገሩት በጨለማው ውስጥ ነው። «ለአንድ ሌላ ሳምንት ግድያቸውን የሚቀጥሉ ይመስለኛል፤ ምናልባት ላነሰ ጊዜ። ጠንቃቆች ከሆናችሁ ይህችን ወቅት ታልፏት ይሆናል። ምን እንደሚያደርጓችሁ ስለማውቅ ገዳዮቹ እንዳያገኟችሁ እፈራለሁ።»

በጨለማው ውስጥ እርስ በርሳችን ተጣብቀን እንደቆምን በሩን ዘግተውብን ሄዱ፡፡ የሚሰናፈጠው የትንፋሻችን፣ የላባችንና የሰውነታችን ሙቀት በአንድ ላይ ሲጨማመር አፍኖን ራሳችንን ልንስት ምንም አልቀረንም፡፡

ለመቀመጥ ብንሞክርም ሁላችንንም በአንድ ጊዜ የሚያንቀሳቅስ በቂ ስፍራ አልነበረም፡፡ ረዘም ያልነው አራታችን ጀርባዎቻችንን ወደ ግንቡ በጣም አስጠግተን ከወገባችን በታች ወደ እብነበረድ ንጣፉ ወለል ሸርተት አልን፡፡ ከዚያም ትንሾቹን ልጆች እላያችን ላይ ሳብንና ያዝናቸው፡፡ በዚህን ጊዜ ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት አልፏል፤ ሁላችንም በደንብ ነቅተናል፤ ለመነጋገር ግን አልደፈርንም፡፡ ከውጪ የሚሰማውን የፌንጣ ድምፅና የራሳችንን የጣር ትንፋሽ እያደመጥን በተቻለን መጠን ተመቻችተን ተቀመጥን፡፡

እግዚአብሔርን ቪያኒንና አገስቲንን እንዲጠብቅልኝ፣ ወላጆቼንና ዳማሲንንም በደኅና እንዲያቆይልኝ በጸጥታ በመጸለይ ጠየኩት፡፡ ወደ መታጠቢያ ቤቱ ስላስገባን አመሰገንኩት - በእውነት እግዚአብሔር ቁስ ሙሪንዚን እዚህ እንዲያመጡን መርቷቸዋል ብዬ አመንኩ፤ በቀናት ውስጥም ለመጀመሪያ ጊዜም ደህንነት ተሰማኝ፡፡ ይህን ግቢ ስንትና ስንት ጊዜ ያየሁት ፉኔ የተደበቅንበትን ክፍል ልብ ካላልኩት ሌላ ማንም መኖሩን ሊጠረጥር አይችልም፡፡

እግዚአብሔር እኛን ለመርዳት ሕይወታቸውን አደጋ ላይ ጥለው የነበሩትን ቁስ እንዲባርክልን ጠየኩት... ያኔ ግን በጸሎቴ መካከል ፊቴ ቅጭም አለ፡፡ ወንድሜንና ጓደኞቻንን እንዴት ወደ ጨለማው እንዳባረሯቸው ሳስብ የንዴት ጎርፍ ጉንጮቼን አቃጠላቸው፡፡ ሆኖም እግዚአብሔር ወደፊት ቁሱን እንድምራቸው እንዲረዳኝ ጸለይኩ፡፡

ጨረቃዋ ከደመና ጀርባ መሸጋ ብቅ ስትል ቀጭን ደብዛዛ ብርሃን በቀዩ መጋረጃ ላይ በነበረ ስንጥቅ አልፎ ስለገባ አብረውኝ የነበሩትን ሰዎች ፊቶች ገጽታ እንድስል የሚያግዘኝ በቂ ብርሃን አገኘሁ፡፡ ከኔ ጎን የተቀመጠችው አትናሲያ ቆንጆ ጠይም የ14 ዓመት ልጅ ስትሆን ትላልቅ የብር አሎሎ መሳይ ዓይኖቿ በጨረቃው ብርሃን ያበራሉ፡፡ እሷ ላይ የተቀመጠችው የ12 አመቷ በኣታ የትምህርት ቤት የደንብ ልብሷን እንደለበሰች ስትሆን በጊዜው መላው የጠፋትና በጣም የፈራች ትመስላለች፡፡ ሳብ አድርጌ ታቀፍኳት፤ ከትንሽ ቆይታ በኋላም ዓይኖቿን ከድን አደረገች፡፡

ከኔ ፊት ለፊት የነበረችው ቴሬሴ ዕድሜዋ 55 ዓመት በመሆኑ ከዚህ ቡድን ትልቋ ሰው ነች፡፡ ያገቡ ሴቶች የሚያዘወትሩትን ደማቅ የሚጠቀለል የሩዋንዳ ባህላዊ ቀሚስ ለብሳለች፡፡ በተለይም ከስድስቱ ልጆቿ አብረዋት ያሉት ሁለቱ ብቻ፣ ከሌርና ሳንዳ፣ በመሆናቸው ከሁላችንም በላይ ተጨንቃለች፡፡ ክሌር በጣም ፈገግ ያለ የቆዳ ቀለም ያላት ስትሆን ምንም እንኳን በኔ ዕድሜ ብትሆንም በፍርሃትና በራስ ማግለል

ተቆራምዳ የዓይን ግንኙነት አታደርግም፡፡ የሰባት አመቷ ታናሽ እህቷ ሳንዳ በቡድናችን ትንሿ ልጅ ነች፡፡ ቆንጆ፣ ተወዳጅና ደርባባ ነች፡፡ ሌሎቻችን ስንርበደበድ እንኳን አንዴም አልፈራችም፤ ለማልቀስም አልቃጣት፤ በመታጠቢያ ቤቱ በቆየንበት ጊዜ ሁሉ ድንጋጤ ላይ የሆነች ይመስለኛል፡፡

የቄሱ ተደጋጋሚ የዝም በሉ ማስጠንቀቂያዎች አዕምሯችን ውስጥ ተቀርጸዋል፡፡ በማይስማማ ሁኔታ፣ አቀማመጣችንን ለማስተካከልም ሆነ ወይንም በደንብ ለመተንፈስ በጣም ፈርተን፣ ተቀምጠናል፡፡ የምሽቱ ግራጫ ብርሃን ቤቱን እስኪሞላው ጠብቀን በጥንቃቄ ተለያይተን እንቆምና ሰውነታችንን እናፍታታለን፡፡ በአስቸጋሪው አቀማመጣችን ለመቀመጥ ወደ ወለሉ ከመመለሳችን በፊት የሁለት ወይንም የሦስት ደቂቃ ረፍት ለራሳችን እንፈቅዳለን፡፡

ጎህ ሲቀድ በቄሱ ትልቅ ዛፍ ላይ ያሉት ወፎች መዘመር ይጀምራሉ፡፡ ያስቀኑኝና *ወፎች ሆናችሁ በመፈጠራችሁና ነጻነት ሰላላችሁ ምን ዓይነት ኣደለኞች ናችሁ - ኣሰኪ ኣኛ ሰዎች የምናደርገውን ኣዩ ስል* አስባለሁ፡፡

በጣም ደክሞን፣ ርቦን፣ ታፍገንና ውብቆን ስለነበር በዚያች ክፍል ያሳለፍናት የመጀመሪያዋ ቀን በአስቸጋሪ ሁኔታ አለፈች፡፡ መተኛት አልተቻለንም - ሽለብ ሲያደርገኝም አንዱ እግር ሲላወስ አሊያም አንዱ ክርን ደረቴን ሲደቃኝ ወዲያውኑ እነቃለሁ፡፡

አመሻሹ ላይ ቄስ ሙሪንዚ ውጪ ላይ ካንዱ ጋር ሲያወሩ ሰማናቸው፡፡ «ሐሰት፣ ሐሰት፣ ሐሰት» አሉ፡፡ «ስለምን እያወራህ እንደሆነም አላውቅ - እኔ እኮ የተከበርኩ ሁቱ ነኝ፤ ቱትሲዎችን እንዴት እደብቃለሁ፡፡ እዚህ ቱትሲዎች ፈጹሞ የሉም ... ትናንት ማታ እኮ ሄደዋል፡፡»

ዓይኖቻችን ፈጠው እርስ በርሳችን ተያየን፡፡ ተሸበርን፡፡

«ከመንግሥት ጋር ችግር ውስጥ መግባት አልፈልግም» ቀጠሉ ቄሱ፡፡ «ያው እናንተ ታውቁኛላችሁ፤ ይህን ቤትም ልትከላከሉልኝ ይገባችኋል ... እነዚያ ቱትሲ አማጽያን እንደዚህ መልካም ሁቱ መሆኔን አይተው ጥቃት ሊፈጽሙብኝ ይችላሉ፡፡»

ከቄሱ ጋር ሲያወራ የነበረው ማን እንደሆነ ባናውቅም ሄዶልን ተገላገልን፡፡ ቄስ ሙሪንዚ እኛን ለማዳን ሲሉ ዋሹ - በዚህም ለገዳዮቹ አሳልፈው እንደማይሰጡን አረጋገጥኩ፡፡ አሁን ያላቸው አማራጭ በጣም ትንሽ ነው፡፡ ምክንያቱም አሳልፈው ከሰጡን ገዳዮቹ እርሳቸው ደብቀውን እንደቆዩ ያውቃሉ፡ ለዘብተኛ፣ ዘውጋቸውን የካዱ ብለው ይወነጅሏቸውና እኛን በእርግጠኝነት እንደሚገድሉ ሁሉ እርሳቸውንም ይገድሏቸዋል፡፡

በእፎይታ ተነፈስኩና ጭኔ ላይ ተኝታ የነበረችውን በኢታን እቅፍ አደረግኋት፡፡ በልጅነቱ አንድ ነገር ሲያስፈራኝ እናቴ እንዴት ጭኗ ላይ አስቀምጣ ታቅፈኝ እንደነበረም አስታወስኩ፡፡ የእናቴ ትውስታ አሳዘነኝ - ይህ በሕይወቴ ወላጆቼና ወንድሞቼ የት እንዳሉ ያላወቅሁበት የመጀመሪያው ጊዜዬ ነው፡፡ ቪያኒ፣ አገስቲንና ዳማሲን የቁሱን ቤት በር ሲያንኳኩ፣ ከኋላቸውም ቤታችን ሲቃጠል እያንጎላጀሁ ሕልም በሚመስል ሁኔታ ሆኜ ታየኝ፡፡ ወላጆቼ ዶቅዶቄዋን ጋልበው፣ እናቴ «ልጆቼስ ምን ሊውጣቸው?» እያለች ስትጠይቅ ያለው ትዕይንት ሁሉ ድቅን አለብኝ፡፡

በሕልሜ ላይ ሳለሁ ቄስ ሙሪንዚ በሩን ከፈቱት፡፡ ቃል ሳይተፍሱ አንድ ሳህን ያልሞቀ ቅቅል ድንችና ባቄላ አስገቡልን፡፡ መሸቷል - በግምት ከምሽቱ 5፡00 ሰዓት ይሆናል፤ ሁለት ቀናት ለሚጠጋ ጊዜ ማናችንም ምንም ዓይነት ምግብም ሆነ መጠጥ አላገኘንም፡፡

ምግቡን በቆሻሻ ጣቶቻችን በማጋበስና ወደ አፋችን በመጠቅጠቅ ሳህኗን ጠራረግናት፡፡

ቄሱ ከአምስት ደቂቃ በኋላ ሹካ ይዘው ሲመጡ ምግቡን እንዳለ ተሻምተነው አገኙን፡፡ ሳህኑ ላይ አፈጠጡ፤ እኛንም በሃዘኔታ አዩን፡፡ ከአፍታ በኋላ ወደ ክፍሉ በጣም ስስ ፍራሽ አስገቡልን፡፡ «መንገድ ጎድቷችኋል፡፡ እስኪ ትንሽ አረፍ በሉ» ብለው በሩን ዘጉት፡፡

በቀጣዩ ቀን ስንነሳ የሚያመንን የሰውነታችን ክፍሎች ለማፍታታት ተራ ገባን፡፡ እርስ በርሳችን ምንም መነጋገር ስለማንችል በሁለት የጣት አንጓዎች መካከል ያለ ርቀት ያህል እንኳን ሰውነታችንን ማንቀሳቀስ ትልቅ ነገር ነው፡፡ የራሳችን የጸጥታ መግባቢያ የሚሆነንን በመታጠቢያ ቤቱ በምንኖርበት ቀሪ ጊዜ የምንግባባበትን የምልክት ቋንቋ ወዲያውኑ ፈጠርን፡፡

እግሮቼ ደንዝዘው ሕመሙ አንጀቴ ሲገባ ፊቴን ቅጭም አደርጋለሁ፤ ከጦርነቱ በኋላ የምናገረው የችግር ወቅት ታሪክ ይኖረኝ ይሆናል ብዬም አስባለሁ፡፡ «ያሳለፍኩትን ልንገራችሁ አድምጡኝ» በማለት ለጓደኞቼ ጉራዬን እነፋ ይሆናል፡፡ «ቀንና ሌሊት ከአምስት ከማላውቃቸው ሰዎች ጋር በአንዲት ትንሽ መታጠቢያ ቤት ውስጥ ታፍኜ አሳልፌያለሁ፡፡ እንዴት ያለሁ ጀግና ነኝ!»

ትንሿን ቅዠቴን ገና ከመጀመሬ ቤተሰቦቼን የያዙ ትዕይንቶች ድቅን አሉብኝና ወደ ገሃዱ ዓለም መለሱኝ - ወላጆቼ በመቃጠል ላይ ከነበረው ቤታችን ሲሸሹ፣ ዳማሲን አዝኖ ከአጠገቤ ጥፍት ሲል፣ ቪያኒና አገስቲን የሚሸሸጉበት ሥፍራ አጥተው በባዶ ሜዳ ሲዋትቱ፡፡ አምላኬ ምስጋና ይግባህ፣ ኤይማብል በደህና ቀን ከሩዋንዳ

ወጥቶልኛል! እኛ ደጅ ሰፍረው የነበሩት በሺህዎች የሚቆጠሩት ተፈናቃይ ቱትሲዎችስ? እንዲያው ምን በጅቷቸው ይሆን? መጠለያ አግኝተው ይሆን? ወይስ የሆነ ቦታ ደማቸው እየፈሰሰ ሕይወታቸው እያለፈች ይሆን? በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ያለ ጥርጥር በባሰ ሁኔታ እየተሰቃዩ ሳለ ስለራሴ በማዘን ላይ በማተኮሬ ራሴን ሞኝና ራስ ወዳድ አድርጌ ቆጠርኩ።።

የሰውነት ማፍታቻ ተራዬ ሲደርስ ውጪ ላይ ሁካታ ጀመረ።። በደርዘኖች፣ ምናልባትም በመቶዎች፣ የሚቆጠሩ ሰዎች እየጮሁና እየዘመሩ ነው።። የገዳዮቹን መድረስ ወዲያውኑ አወቅን።።

«በየደኑ፣ በየሐይቁ፣ በተራራው እናድናቸው፤ በቤተክርስቲያኑም እንፈልጋቸው፤ ከምድረ-ገጽ እናጥፋቸው!»

በእግር ጣቶቼ ጫፍ ቆሜ በመጋረጃዋ ላይ በነበረችው ትንሽ ቀዳዳ ሳጨነቁር ሌሎቹ ሴቶች ይዘው ወደ ታች ሊስቡኝ ሞከሩ።። አትናሲያ ራሷን በአግራሞት እየነቀነቀች ድምፅ ሳታሰማ በከንፈሮቿ ብቻ «ውረጂ! እኛን አይደለም እንዴ የሚፈልጉት! ሳያዩሽ ውረጂ!» አለችኝ።።

ከቁበም አልቆጠርኳቸው፣ እጆቻቸውን ወዲያ አሽቀነጠርኩና በቀዳዳው ማየት ጀመርኩ።። ባየሁት ነገር ስለተደናገጥኩ ወዲያውኑ በድርጊቴ ተጸጸትኩ።።

በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ቤቱን ከበውታል።። አብዛኞቹ አለባበሳቸው ሰይጣን አስመስሏቸዋል - የዛፍ ልጥ አሸርጠዋል፣ የደረቀ የሙዝ ቅጠል ከወገባቸው በላይ ለብሰዋል፤ ይባስ ብሎ አንዳንዶቹ የፍየል ቀንድ ራሳቸው ላይ አስረዋል።። ሰይጣናዊ አልባሳት ቢለብሱም ፊቶቻቸውን በቀላሉ መለየት ይቻላል።። በዓይኖቻቸው ግድያ ይታያል።።

በደስታ ይጮሃሉ።። ጦር፣ ገጀራና ቢላዋ በአየር ላይ እያወናጨፉ ይዘላሉ።። የሚያሳምም የጅምላ ጭፍጨፋ መዝሙር ይዘምራሉ፤ ይጨፍራሉ - «ግደሏቸው! ግደሏቸው! ሁሉንም ግደሏቸው፤ ትልልቆቹንም ግደሏቸው! ትንንሾቹንም ግደሏቸው! ሽማግሌዎቹን ግደሏቸው! ወጣቶቹንም ግደሏቸው ... የእባብ ልጅ እባብ ነው፣ እርሱንም ግደሉት፤ ማንም አያምልጥ! ግደሏቸው! ግደሏቸው! ሁሉንም ግደሏቸው!» እያሉ።።

የሚዘምሩት ወታደሮቹ አይደሉም፤ ለቀናት ሲያሠቃዩን የነበሩት የሠለጠኑት ታጣቂዎችም አይደሉ - ጎረቤቶቼ እንጂ።። አብረውኝ ያደጉና የተማሩ ናቸው።። የተወሰኑት እንዲያውም በእጃቸን በልተዋል።።

ከልጅነቴ ጀምሮ የማውቀውን ካናንጋን ለየሁት።። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ያቋረጠ ሰው ነው።። አባቴ ግን ከዚያ በፊት ጸባዩን ሊያርመው ሞክሮ አልሆን ብሎት

ነው፡፡ ሰው ቀና ብሎ የማያየውንና በጣም ዓይነ አፋሩን ፊሊፕንም ከነዚህ ገዳዮች ጋር ተስማምቶ አየሁት፡፡ ከፊት ለፊት የዳማሲን ጓደኞች የነበሩ ሁለት የአካባቢያችን መምህራን ይታዩኛል፡፡ በስብስቡ ውስጥ በደርዘኖች የሚቆጠሩ የማታባን በጣም ታዋቂ ሰዎች ለየኋቸው - ሁሉም ግዳይ ለመጣል ተቻኩለው፣ ተቆጥተውና የቱትሲዎችን ደም ለማፍሰስ እየተጨጨሁ፡፡ የቡድኑ መሪዎች ገዳዮቹን ወደ ቄሱ ቤት ሲመሩ መጡ፤ ድንገትም ዝማሬያቸው ከየስፍራው ይሰማን ጀመር፡፡

«ፈልጓቸው፣ ፈልጓቸው፣ ሁሉንም ግደሏቸው!»

ራሴን አዙሮኝ ወደኋላዬ በሴቶቹ ላይ ወደቅሁ፡፡ ልተነፍስ አልቻልኩም፡፡ «አምላኬ ሆይ፣ አድነን ...» ስል አንሾካሾክሁ፤ ግን የማናቸውንም ጸሎቶቼን ይዘት አሁን አላስታውስም፡፡ የተስፋ መቁረጥ አበላ አጠበኝ፣ አይፈሩ ፍርሃት ፈራሁ፡፡

ለመጀመሪያ ጊዜ ሰይጣን በጆሮዬ ያንሾካሾከው ያኔ ነው፡፡ ለምንድነው አምላክሽን የምትጣሪው? ውጪ ያሉትን እስኪ እያቸው... በመቶዎች ሆነው ሲፈልጉሽ፡፡ እነርሱ አንድ ሻለቃ ጦር ይሆናሉ፤ አንቺ ግን አንድ ነሽ፡፡ አትድኚም - በምንም ዓይነት አትድኚም፡፡ እቤቱ ውሰጥ ናቸው፣ በየከፍሎቹም እየተዘዋወሩ ነው፡፡ ቀርበዋል፣ ያው እዚህ ናቸው ... ሊያገኙሽ ነው፣ ሊደፍሩሽ ነው፣ ሊቆርጡሽ ነው፣ ምን አለ በዩኝ ሊገድሉሽ ነው!

ልቤ ይመታል፡፡ ይህ ድምፅ ምንድን ነው? አሉታዊ ሐሳቦቼን ለመቋቋም ዓይኖቼን በተቻለኝ መጠን ጨፈንኩ፡፡ አባቴ የሰጠኝን ቀይና ነጩን መቁጠሪያ ይዤ ባለኝ ዐቅም ሁሉ በጸጥታ ጸለይኩ - አምላኬ ሆይ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ለማንም ማናቸውንም ነገር ልታደርግ እንደምትችል ተናግረሃል፡፡ እኔም ከነዚያ ማንምች አንዷ ስለሆንኩ የሆነ ነገር እንድታደርግልኝ እፈልጋሁ፡፡ እባክህ እግዚአብሔር ገዳዮቹን ወደ ቄሱ መኝታ ክፍል ሲደርሱ ሓሳውራቸው - የመታጠቢያ ቤቱን በር እንዳያገኙት አድርጋቸው፤ እንዲያገኙን አታድርግ! ዳንኤልን ከአንበሶች ጉድጓድ አድነሽዋል፤ አንበሶቹን እንዳይሻሙት አቁመሃቸዋል... እግዚአብሔር ሆይ እነዚህ ገዳዮች እኛን እንዳይሻሙን አቁማቸው! ዳንኤልን እንዳዳንከው እኛንም አድነን!

ጸልዬ ከማውቀው በላይ በጣም ጸለይኩ፣ ግን አሉታዊው ኃይል መንፈሴን ተፈታተነው፡፡ በእርግጠኝነት ሰይጣን ራሱ በራሴ ላይ ተቀምጦ እንደነበር ሁሉ የጥርጣሬ ድምፅ በጆሮዬ በድጋሚ ያስተጋባ ጀመር፡፡ በደም ስሮቼ ጥርጣሬ ሲረጭ ደሜም በእሳት ሲጋይ ተሰማኝ፡፡ መሞትሽ ነው ኢማኪዩሌ! ድምጹ አሾፈብኝ፡፡ ደግሞ ራስሽን ከዳንኤል ጋር ታወዳድሪያለሽ? እንዴት የታበይሽ ነሽ . . . ዳንኤል እኮ ልቡ ንጹሕና በእግዚአብሔርም የተወደደ ነቢይ ነበር፣ ቅዱስ! አንቺስ ምንድነሽ? ምንም ነሽ . . . ሥቃይና ህመም ይገባሻል . . . ልትሞቺ ግድ ይልሻል!

መቁጠሪያዬን ከእግዚአብሔር ጋር የሚያገናኝ መሥመር እንደሆነ ሁሉ አጥብቄ ያዝኩት፡፡ በአእምሮዬና በልቤ እንዲያግዘኝ ለእርሱ ጮህኩ - ለምን ምንም አይደለሁም፣ ግን አንተ መሐሪ ነህ፡፡ እኔ መቼም ሰው በመሆኔ ደካማ ነኝ፤ ቢሆንም ግን እባክህ ፈጣሪዬ ምኅረትህን አትንፈገኝ፡፡ መተላለፌን ይቅር በለኝ ... እባክህ እነዚህን ጉዳዮች እንዲያገኙን ወዲያ አባራቸው!

ጆሮ ግንዴ ትር ትር ይላል፡፡ ጨለማው ድምፅ ራሴን መነገር በማይችሉ አስፈሪ ምስሎች ሞላው፡፡ የምቱ ሰዎች አካላት በየቦታው አሉ፡፡ እናቶች ሕፃናት ልጆቻቸው ለሁለት ሲቆረጡና ሸሎቻቸው ከማህፀኖቻቸው ተቀደው ሲወጡ አይተዋል ... ታዲያ አንቺ መዳን ያለብሽ ይመስልሻል? እናቶች ለአምላክ ሕፃናታቸውን እንዲያድንላቸው ጸልየው ቸል ብሏቸዋል - ንጹሃን ሕፃናት እየተገደሉ ሳለ አንቺን ሰለምን ያድንሻል? የማታፍሪ ራስ ወዳድ ነሽ፡፡ አዳምጪ ኢማኪዩሌ... ትሰሚያቸዋለሽ? ጉዳዮቹ ከበሩ አጠገብ ናቸው - መጡልሽ፡፡

ራሴ ተቃጠለ፤ ጉዳዮቹን አዳራሹ ውስጥ ሲጮሁ እሰማቸዋለሁ፣ «ግደሏቸው! ሁሉንም ግደሏቸው!»

አይሆንም! እግዚአብሔር ፍቅር ነው አልኩት ለዚያ ድምፅ፡፡ ሰለሚወደኝ በፍርሃት አይሞላኝም፡፡ አይተወኝም፡፡ በተሸሸኩበት መታጠቢያ ቤት ወለል ላይ እንድሞት አያደርገኝም፡፡ በሃፍረት እንድሞት አይፈቅድም!

በአእምሮዬ የእግዚአብሔርን ምስል ለመሳል ተጣጣርኩ፣ ትላልቅ እግሮች የመሰሉ ሁለት የሚንቦገቦጉ ደማቅ ነጭ የብርሃን ዋልታዎች በፊቴ ሣልኩ፡፡ የፊራ ልጅ በእናቱ ላይ እንደሚጠመጠመው ሁሉ እጆቼን በነዚያ እግሮች ዙሪያ ጠመጠምኩ፡፡ አምላክን በብርሃኑና በጥንካሬው እንዲሞላኝ ለመንኩት - ጨለማውን ከልቤ እንዲያወጣልኝ - እግሮችህን ይዣለሁ እግዚአብሔር፤ እንደምታድነኝም አልጠራጠር፡፡ ጉዳዮቹንም እስከታባርራቸው ድረስ አልለቅህም፡፡

በጸሎቴና የዲያቢሎስ እንደሆነ እርግጠኛ በሆንኩበት ርኩሰ ሹክሹክታ መካከል የነበረው ትግል በአእምሮዬ ተጧጧፈ፡፡ መጸለዬን አልተውኩም... ሹክሹክታውም ጋብ አላደረገ፡፡

ምሽት ላይ ቁሱ በሩን ሲከፍቱት ሕልም በሚመስል ነገር ውስጥ ገብተን አገኙን፡፡ በላብ ታጥቤ፣ ደካክሜና መቁጠሪያዬን በሁለቱም እጆቼ ጨብጬ በአካባቢዬ እየተከሰተ ስላለው ሁኔታ ማገናዘብ ተስኖኛል፡፡ ጸሎት በጸሎት ላይ በማከታተል ሰዎቹ ላይ አፍጥጫለሁ - በትክክል እያየኋቸው ግን አልነበረም፡፡ ቴሬሴ በአንድ እጇ ዓይኖቿን ሸፍና በሌላው ደግሞ መጽሐፍ ቅዱሷን ከራሷ በላይ ከፍ አድርጋ አጥብቃ

ይዛለች፡፡ በአታ የተባለችው ወጣት በበኩሏ ተንበርክካ፣ እጆቿን ከፊት ለፊቷ አጣምራ በጸሎት ላይ ነች፡፡

ቄሱ ስማችንን ቢጣሩም ማንኛችንም አልሰማናቸውም፡፡ በመጨረሻም ከገባንበት የደመ-ነፍስ ሁኔታ ለማንቃት ሰውነታችንን ነቀነቁን፡፡ አየኋቸው፣ በግራ-ግባትም ዓይኖቼን እየጨፈንኩና እየገለጥኩ ተመለከትኳቸው፤ ሲሰቁበንም በፍጹም ተደናገርኩ፡፡

«እናንተ ሴቶች ምንድነው እያደረጋችሁ ያላችሁት? ስለ እግዚአብሔር ብላችሁ ተረጋጉ፡፡ ገዳዮቹ ከሰባት ሰዓታት በፊት እኮ ነው የሄዱት፡፡ እስካሁን እየጸለያችሁ መሆኑን አላምንም፡፡»

ለኔ እነዚያ ሰባት ሰዓታት ደቂቃዎች ነው የመሰሉኝ፤ ግን ሙሉ በሙሉ ደርቄያለሁ፡፡ ከዚያን ጊዜ በፊት ጸሎት ባደረግሁባቸው ዓመታት በፍጹም እንደዚህ በእግዚአብሔር ላይ አተኩሬ ወይንም ሙሉ በሙሉ የጨለማን መኖር በጽኑ ተገንዝቤ አላውቅም፡፡ በገዳዮቹ ዓይኖች ርኩሰትን አይቻለሁ፤ ቤቱም ሲፈተሽ ሰይጣን በዙሪያዬ እንዳለ ተሰምቶኛል፡፡ ልንታረድ እንደተቃረብን እንዲያሳምነኝ የፈቀድኩለትን ጨለማውን ድምፅ አደመጥኩት፡፡ ለፍርሃቴ እጅ በሰጠሁና የዚያን ከንቱ ሹክሹክታ ውሸት በሰማሁ ቁጥር ቆዳዬ እየተገፈፈ እንደሆነ ያህል ይሰማኛል፡፡ በእግዚአብሔር አምንታዊ ኃይል ላይ በማተኮሬ ብቻ ከመጀመሪያው የገዳዮቹ ፍለጋ በኋላ አገገምኩ፡፡ አባቴ ሁልጊዜ ብዙ አትጸልዩ ይለኝ የነበረው ትክክል እንደሆነ አሁን ገባኝ፡፡

ከዚህ ጦርነት ለመዳን የማደርገው ፍልሚያ በኔው ውስጥ የሚካሄድ እንደሆነ ገባኝ፡፡ በኔ ውስጥ ያለ ማንኛውም ጥሩና ጠንካራ ነገር - እምነቴ፣ ተስፋዬ፣ ብርታቴ ሁሉ - ለጨለምተኛ ሐሳብ ተጋላጭ እንደሆነ ገባኝ፡፡ እምነቴን ካጣሁ መዳን እንደማልችል ይታወቀኛል፡፡ እንድፋለም ያግዘኝ ዘንድ መተማመን የምችለው በአምላኬ ላይ ብቻ ነው፡፡

የገዳዮቹ ጉብኝት ሁላችንንም ጎዳን፡፡ ቄስ ሙሪንዚ አንድ ሳህን ምግብ አመጡልን፤ ብንራብም ኖሮ ለመብላት ግን በጣም ደክመናል፡፡ ወደ እኩለ ሌሊት ላይ ሲመለሱ ምግቡ ሳይበላ አገኙት፡፡

ቄሱ እንደገና ሌሊት ዶፍ በሚወርድበት ሰዓት መጡ፡፡ ዝናቡ ጣራው ላይ የሚያሰማው ድምፅ ከፍተኛ ስለሆነ ሰው ይሰማኛል ብለው ሳይሸማቀቁ በነጻነት ለማውራት ቻሉ፡፡ «አድለኞች ነን፡፡ ቤቱን በሙሉ አሠሡት፤ ሁሉንም ክፍል አዩት፡፡ ወደ ጓሮም ሄደው ከላሞቹ ቤት ጀርባ ያለውንም የፍግ ቁልል ሳይቀር ቆፈሩት፡፡ በኮርኒሱ ውስጥና በቤት እቃዎቹ ስር ሁሉ ድኽዋል - በቦርሳዎቼም ውስጥ ሕፃናት ቱትሲዎችን ደብቁ አንደሆነ ለማየት በገጀራዎቻቸው ፈትሸዋል፡፡ እንደ ቁጡ እንስሳም አብደዋል፡፡ ዓይኖቻቸው ቦዘዋል፣ ቀልተዋል... እጽ ያጨሱ መሰለኝ፡፡»

‹‹ግን መኝታ ቤቴ ጋ ሲደርሱ ንጹሕ መሆኑን ስላዩ ማበላሸት አልፈለጉም፡፡ መኝታ ቤቴን ለአሁኑ እንደሚተዉትና ሌላ ቀን በሚመለሱ ጊዜ እንደሚፈትሹት ነግረውኛል፡፡›››

‹‹ሌላ ቀን! እ...!›› አቃሰትን፡፡

ይህን ዓይነት ሥቃይን በድጋሚ ማሳለፍን ላስበው አልቸልም፡፡ በእርግጠኝነት አምላክ ያን ሥቃይ ሁለተኛ አያመጣብንም!

‹‹መቼ እንደሚመጡ አታውቁም›› አሉ ቄሱ፡፡ ‹‹በማናቸውም ጊዜ ሊመጡ ይችላሉ፤ ታዲያ ካገኟችሁ፣ ብቻ እግዚአብሔር ሁላችንንም ይሰውረን፡፡››

የስንብት ንግግራቸው በአእምሮዬ ያቃጭላል፡፡ ሌሊቱን ሙሉና ቀጣዩን ቀንም እንቅልፍ ነሳኝ፡፡

ቄስ ሙሪንዚ በቀጣዩ ምሽት በፍርሃት ተመለሱ፡፡ ‹‹አንድ ወዳጄ የገዳይ ቡድኑ መሪ ገዳዮቹ ቤቱን በደንብ አልፈተሹም ማለቱን ነገረኝ›› ሲሉ አንሾካሾኩ፡፡ ‹‹የተወሰናቸሁት በቤቱ ከጥቂት ቀናት በፊት ስለታያችሁ እዚህ ተደብቃችኋል የሚል ወሬ ይናፈሳል፡፡ ሌላ የገዳዮች ቡድን በደንብ እንዲፈትሽ ነገ ሊላክ ነው፡፡››

ሰውነቴ ዐቅም አጥቶብኝ አቃሰትኩ፡፡ ሌላ የገዳዮች የአደን ዘመቻን የምቋቋምበት ጥንካሬ አልነበረኝም፡፡ *እግዚአብሔር፣ ለምን አሁኑኑ ወደኛ መርተሃቸው ጉዳዩን አትጨርሰውም?* ስል ለመንኩት፡፡ *ለምን እንደዚህ ፍዳችንን እንድናይ ፈቀድክ? ለምን ታሰቃየናለህ?*

በድጋሚ እንዴት ልናመልጥ እንችላለን? ያ ባንድ ወቅት በጣም ትልቅ የነበረው ቤት እንደሆን የኔ እስር ቤት፣ የሞት ወጥመዴ ሆኗል፡፡ ላስብ የምችለው አንድ ብቻ ማምለጫ ነው - ወደ ገነት ለመሄድ አሰብኩ፡፡ *አቤቱ እግዚአብሔር ሆይ፣ ድምፅ ሳላሰማ ጸሎቴን ቀጠልኩ፣ ለመፋለም የቀረ ምንም ልብ የለኝም፡፡ ተሰፋ ልቆርጥ ነው... እባክህ ጥንካሬውን ለግሰኝና በዙሪያዬ ከከበቡኝ ሰይጣናት ሰውረኝ፡፡ ገዳዮቹን ድጋሚ እንዴት እንደማሳውራቸው አሳየኝ፡፡*

ራሴን ከፍ አድርጌ ዓይኖቼን ከፈትኩ፡፡ ቄሱን በራችን ላይ ቆመው ሳያቸው ግልጽ ምስል በአእምሮዬ መጣልኝ፡፡ ‹‹አንድ ሐሳብ አለኝ›› አልኳቸው በቀስታ ግን ጽኑ አቋሜን በሚያሳይ መልኩ፡፡ ‹‹ቁምሳጥኑን ወደ መታጠቢያው ቤት በር ሊያመጡት ይችላሉ? ሰፊ ስለሆነ ሙሉ በሙሉ ይሸፍነዋል፣ ስለዚህ ገዳዮቹ በሩን ማየት ካልቻሉ በፍጹም ሊያገኙን አይችሉም፡፡ እንደ እውር ነው የሚያደርጋቸው!››

ቄስ ሙሪንዚ ለአፍታ አስበው ራሳቸውን በአሉታ ነቀነቁ፡፡ «አይ፣ ምንም ለውጥ አያመጣም፤ እንዲያውም ሁኔታዎችን ሊያባብስ ይችላል፡፡ ከቁምሳጥኑ ጀርባ አይተው በሩን ካገኙት በጣም ሊጨክኑባቸው ይችላሉ፡፡»

«እንዴ አይሆንም! እባክዎት ያድርጉልን…» እግዚአብሔር መልዕክት ልኮልኝ ይሁን አይሁን እርግጠኛ አልነበርኩም፡፡ በውስጤ ታዲያ ቁምሳጥኑ ከበሩ ፊት ለፊት ቢሆን እንደምንድን አውቄዋለሁ፡፡ ቄሱ ግን ወይ ፍንክች አሉ፤ ስለሆነም በሕይወቴ አድርጌው የማላውቀውን ነገር አደረግሁ - ተንበርክኬና አጎንብሼ - «እባክዎን ይለመኑኝ» ስል ተማጸንኳቸው፡፡ «በልቤ በሩን በቁምሳጥኑ ካልከለሉት ቀጣይ በሚመጡ ጊዜ እንደሚያገኙን አውቃለሁ፡፡ እነርሱን ስለማበሳጨት አያስቡ - አንዴ ብቻ ነው ሊገድሉን የሚችሉት፡፡ እባክዎን ይህንን ያድርጉልን… ይህን ቢያደርጉ ከፈጣሪ ብድሩን ያገኙታል፡፡»

በጉልበቴ ተንበርክኬ ስማጸን ስላዩኝ አሳዝኖቸው ይሁን ከክፍሏ ውጪ ባሉ ሌሎች ሰዎች እንዳልሰማ ማሰባቸው አስፈርቷቸው መጨረሻ ላይ ተሸነፉልኝ፡፡ «ይሁን እሺ፡፡ እስኪ ለማንኛውም ድምፅሽን ዝግ አድርጊው ኢማኪዩሌ፡፡ አሁኑኑ አመጣዋለሁ፡፡ ሳይረዳን አይቀርም፣ ታዲያ እጠራጠራለሁ፡፡»

ወዲያውኑ ከዓይናቸን ሥውር አሉና ከአፍታ በኋላ ቁምሳጥኑን ከመታጠቢያ ቤቱ በር ፊት ለፊት ሲያን቏ቅቁት ሰማናቸው፡፡ ሴቶቹ አዩኝና አንሾካሾኩ፤ «በጣም ግሩም ሐሳብ ነው - ምን አስመለከተሽ ልጄ?» በማለት፡፡

የቄሱን ቁምሣጥን ከዚያን ጊዜ በፊት ማየቴን እንኳን አላስታውስም፡፡ ግን በእርግጠኝነት እሱን ከቦታው የማንቀሳቀሱ ሐሳብ የመጣልኝ ከጸለይኩ በኋላ ነው፡፡[6]

«ወይ አምላኬ» ብቻ ነው ያልኩት፡፡

[6] የተርጓሚው ትዝብት፡ - ኢማኪዩሌ በቅርቡ መድረክ ላይ ስትናገር በአንድ የገዳይ ቡድን አሰሳ ወቅት አንድ ገዳይ የተደበቀችበትን መታጠቢያ ቤት በር መክፈቻ እጀታ ለመክፈት ጨበጥ አድርጎት እንደነበር ተናግራለች፡፡ ክፈቱልኝ ማለቱንም ትቶ ወደ ቄሱ ዘወር ብሎ «አይ፣ ኧረ እናምንዎታለን መምሬ» ብሎ እንደተወውና ቤታቸውን ለቆ እንደወጣ ገልጻለች፡፡ ለቄሱና ለኢማኪዩሌ ሕይወት የሳሳ ርህሩህና የገዳይ ቡድኑን ተገዶ የተቀላቀለ ሰው ይሆን?

ምዕራፍ 10

ቁጣዬን ስጋፈጥ

በአንጻራዊ መረጋጋት በርካታ ቀናት አለፉ፡፡ አልፎ አልፎ ገዳዮቹ ውጪ ላይ የእብድ መዝሙራቸውን ሲዘምሩ እንሰማቸዋለን፡፡ ቀኑን ሙሉ በጽሞና እንጸልያለን፤ እርስ በርሳችንም በምልክት ቋንቋ እንግባባለን፡፡ ከሞላ ጎደል በየ12 ሰዓታቱ የተወሰኑ ተናፋቂ የሰውነት ማፍታቻዎችን እናደርጋለን፡፡ ከዚያ በስተቀረ ቀንና ሌሊት በአንድ ቦታ በመቀመጥ እንቅስቃሴዎቻችንን በተቻለን መጠን እንገድባለን፡፡

መጸዳጃ ቤቱን በቄስ ሙሪንዚ ትዕዛዝ መሠረት ውሃ እንለቅበታለን፡፡ ይህም ሌላ ሰው በዋናው ቤት ውስጥ ያለውን ሌላውን መጸዳጃ ቤት ውሃ ሲለቅበት መሆኑ ነው፡፡ መጸዳጃውን መጠቀሙ ፈተና ሆኑብን፡፡ ስፍራው በቂ ስላልሆነ የምትጠቀመው ሰው ከእብነበረድ በተሰራው መጸዳጃ ላይ ቁጢጥ ለማለት ትገደዳለች፤ ስለሆነም አንደኛችን ስንጸዳዳ ሁላችንም ቦታ መቀያየር አለብን፡፡ ያም ድምፅ የማሰማትና በገዳዮቹ የመገኘት አደጋን ጋርጦብናል፡፡

ባልተለመደ ሁኔታ በመታጠቢያ ቤቱ በቆየንበት ጊዜ ማንም መጸዳጃውን ሲጠቀም ማየቴን አላስታውስም፡፡ መጸዳጃው ከእብነበረድ የተሠራና እላዩ ላይ አስቀምጦ የሚያጸዳዳው ዓይነቱ ነው፡፡ ያለው በዚያች ትንሽ ቦታ መካከል ቢሆንም ሽታው ያስቸገረኝ ወቅት ትዝም አይለኝ፡፡ የወር አበባችንም ይደርሳል፤ ያንዳችን ሲሄድ የሌላችን ከተፍ ይላል፡፡ በመሆኑም ቄሱን ተጨማሪ የንጽሕና መጠበቂያ ወረቀት አምጡ እያልን እናስቸግራቸዋለን፡፡ ማንኛችንም ብንሆን ባለው ሁኔታ አንሸማቀቅም፤ እነዚህን ሁኔታዎች ረስተናቸዋል፤ የብቸኝነትም ጥሩ ጎኖች ትዝ አይሉን፤ በተለይ ይህ ችግር በሕይወት ከመኖራችን አንጻር ሲታይ ከግምት ውስጥ አይገባምና፡፡

ቄሱ ምግብ ይዘው በመጡ ቁጥር እንበላለን - የሚያመጡልን አልፎ አልፎ ቢሆንም፡፡ አንዳንድ ቀንማ ያለ ሌሊት 9 ወይንም 10 ሰዓት አይመጡም፡፡ (ሊያዩን ወይንም ምግብ ሊያመጡልን በፈለጉ ቁጥር ቁምሳጥኑን ገፍተው ይገባሉ፡፡ ሁልጊዜ ግን ሌላ ሰው እንዳይሰማቸው በጣም ይጠነቀቃሉ፡፡ ከቁምሳጥኑ ሲንቀሳቀስ ድምጹን ለማፈን የሚሆን ጨርቅ ከስሩ ተደርጎበታል፡፡ በዚህም እግዚአብሔር እንደገና ይጠብቀን ይዟል፡፡) ተጨማሪ ምግብ ቢያዘጋጁ ሌላ ሰው እንዳያውቅባቸው የልጆቻቸውን ትርፍራፊ ወይንም ሠራተኞቻቸው የሚበሉትን አሸር ባሸር ያመጡልናል፡፡ አንዳንዴ ምንም ብንራብም አንበላም እንላለን - የሚሰጡን የአሳማ ምግብ ይመስላላ፡፡ (እቤቴ ምን ዓይነት ምግብ አማራጭ እንደነበርኩ በማስታወስ በራሴ ላይ እሥቃለሁ፡፡) የምንጠጣውም ውሃ ይመጣልናል፡፡

የማይቻል ቢመስልም ከቀናት ጸጥታ በኋላ ትንሽ ዘና አልን፡፡ ያለንበትን ሁኔታ የሚያስታውሱን ቄሱ ብቻ ናቸው፡፡

አንድ ሌሊት ቄሱ መጥተው ገዳዮቹ ባቅራቢያችን ከቤት ወደ ቤት በመዘዋወር ቤቶችን እየፈተሹ ያገኙትን ቱትሲም እየገደሉ እንደሆነ ነገሩን፡፡ «በተወሰኑ ደቂቃዎች ውስጥ ሊመጡ ይችላሉ፤ ምናልባትም እስከ ነገ ወይንም ከነግወዲያ ድረስም ላይመጡ ይችላሉ፡፡ በእርግጠኝነት ግን ይመጣሉ፤ ስለዚህም ዝም በሉ» ሲሉ አስጠነቀቁን፡፡

በዚያች መታጠቢያ ቤት ውስጥ ትንሽ የአእምሮ ሰላም ለማግኘት የነበረን ተስፋ ተነነ፡፡ ስለገዳዮቹ መመለስ ያደረብን ሥጋት አዕምሯዊና አካላዊ ውጋት ሆነብን፡፡ ወለሉ ላይ ድምፅ በሰማሁና ዉሻ በጮኸ ቁጥር አንድ ሰው በስለት እንደወጋኝ ይሰማኛል፡፡ በአንዴ መተኛት የምንችለው ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ስለሆነ ቆዳዬ መድረቅና መላጥ አመጣ፡፡ ሁልጊዜም የማይተወኝ ራስ ምታትም ይዞኝ ተቸገርኩ፡፡

የአእምሮ ሥቃዬማ እንዲያውም በጣም ያይላል፡፡ በሃሳቤ ወጥመድ ውስጥ ብቻዬን እሰቃያለሁ፡፡ ከደረስኩ ጀምሮ የሚያስቸግሩኝ ጽኑ ፍርሃቶችና ቅዠቶች በልቤ ውስጥ እየተመላለሱ የእምነቴን መሠረት አናጉት፡፡ ገዳዮቹ ድምጻቸው ለኛ በሚሰማን ርቀት ሲጠጉ ሐሳቤ ከፈጣሪ ራቀና በአሉታዊው ሐሳብ ተጠመድኩ፡፡ በጸለይኩ ቁጥር ግን ወዲያውኑ ፍቅሩን አገኘዋለሁ፤ ስጋቴም ይቀልልኛል፡፡

ስለዚህ ሌሊት ከ10 ወይም 11 ሰዓት ጀምሬ በማንኛዋም እንቅልፍ ባልያዘኝ ሰዓት ለመጸለይ ወሰንኩ፡፡ ሁልጊዜ የመጀመሪያ ጸሎቴ የቄሱ ቤት ስለተሠራልንና በዘር ጭፍጨፋው ወቅት ስለተጠለልንበት አምላክን ማመስገን ነው፡፡ ከዚያም የቤቱ ንድፍ-አውጪ ከተጨማሪ መታጠቢያ ቤት ጋር እንዲነድፈው ስላደረገው፣ ብሎም ለቄሱ የኛን መደበቂያ ስፍራ መሸፈኛ የሚሆን ልከኛ ቁምሣጥን እንዲገዙ ስለገፋፋቸው አመሰግነዋለሁ፡፡

ከመጀመሪያው የምስጋና ጸሎቴ በኋላ በመቁጠሪያዬ መጸለይ እጀምራለሁ፡፡ ጸሎቶችን በቀዮቹና ነጮቹ ዶቃዎች አደርሳለሁ፡፡ አንዳንዴ በጣም ስለምጸልይ ያልበኛል፡፡ ሰዓታትም ያልፋሉ... ዶቃዎቹንና ጸሎቴን ስጨርስ የምወዳቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በማለት «እረፍት» አደርጋለሁ፡፡

እምነቴ በአደጋ ላይ እንደወደቀ ስለማስብ ከማርቆስ ወንጌል የማስታውሳቸውን ስለ እምነት ጉልበት የሚያወሱ ሁለት ጥቅሶች በመደጋገም ሰዓታትን አሳልፋለሁ፡፡ መጀመሪያ ይህ ነው - «ስለዚህም እላችኋለሁ፣ አምናችሁ ብትፀልዩ የምትለምኑትን ሁሉ ታገኛላችሁ፤ ይሆንላችሁማል» (ማርቆስ 11፡ 24)፡፡ ከዚያም ሌላውን እላለሁ - «እውነት እላችኋለሁ፣ ይህን ተራራ ተነሥተህ ወደ ባህር ተወርወር ብትሉት፣ በልባችሁም ባትጠራጠሩ፣ ብታምኑም እንደተናገራችሁት ይሆናል» (ማርቆስ 11፡23)፡፡

ሳልጸልይና ስለ እግዚአብሔር ሳላስብ የማሳልፋት ጥቂት ደቂቃ እንኳን ብትኖር ሰይጣን መንታ ጫፍ ባለው የጥርጣሬና በራስ የማዘን ቢላዋው ይወጋኝ ዘንድ መጋበዝ ይሆናል። ጸሎት መከላከያዬ በመሆኑ ልቤን አጥብቄ እጠቀልልበታለሁ።

ቄሱ ሁልጊዜ ያልሆነ ስህተት ሰርተን ድምፅ እንዳናሰማ ይፈራሉ። ስለሆነም ወደ መኝታ ክፍላቸው ሰው የሚያመጡት እጅግ አልፎ አልፎ ነው። አንዳንዴ ግን ከልጆቻቸው አንዷ ወይንም አስተናጋጃቸው ሊጠይቋቸው ሲመጡ እስኪሄዱ ድረስ እንደነዝዛለን። እዚህ ከመጣን ከአንድ ሳምንት ገደማ በኋላ ቄሱ ከልጃቸው ከሴምቤባ ጋር ሲያወሩ ሰማናቸው።

«አባባ፣ ስለዚህ ግድያ ምን ትላለህ? ጥሩ አይመስልህም - እኛ ሁቱዎች ማድረግ ያለብን ትክክለኛው ነገር አይመስልህም? ማለቴ በትምህርት ቤት ሲያስተምሩን ከመቶዎች ዓመታት በፊት ቱትሲዎች በእኛ ላይ ተመሳሳይ ነገር አድርሰዋል፤ ስለዚህ እያገኙት ያለው ነገር ይገባቸዋል አይደል?»

«ሴምቤባ ስለምን እያወራህ እንደሆነ አታውቅም። በል ተወኝ አሁን፤ ልተኛበት» ሲሉ መለሱ ቄሱ።

«ቱትሲዎች ሲባሉ ሁልጊዜ የበላይ ነን ብለው ያስባሉ... ሁሌ ሁቱዎችን ዝቅ አድርገው ያዩናል። ዛሬም ድረስ ሥልጣን ላይ ቢሆኑ ኖሮ አሁን እየገደሉን አይሆንም ነበር? ስለዚህ እነርሱን መግደል ራስን መከላከል ነው፣ አይደለም?»

ድምጹ በጣም በመጉላቱ ሴምቤባ ቁምሳጥኑ ጎን እንደቆመ መገመት እችላለሁ። የቁምሳጥኑንም መንቀሳቀስ ያውቅብናል ብዬ በጣም ተሸበርኩ። እንደፈራሁም ቢሆን ተነሥቼ ልጩህበት የሚለውን ሃሳቤን መቋቋም ነበረብኝ - ቃላቱ በጣም አናደዱኝ።

ይህን ለቱትሲዎች ያለውን ንቀት የተማረው በትምህርት ቤት እንደሆነ ስለማውቅና እኔም እዚያ ትምህርት ቤት ስለተማርኩ ለድንቁርናው ብቸኛው ተጠያቂ እንዳልሆነ ይገባኛል! ወጣት ሁቱዎች ከልጅነታቸው ጀምሮ ቱትሲዎች የበታችና የማይታመኑ እንደሆኑ ይባስ ብሎም ሩዋንዳውያን እንዳልሆኑ ተምረዋል። ሁቱዎች የቱትሲዎችን መገፋት መጀመሪያ በትምህርት ቤት ሜዳ ቀጥሎም በሥራ ቦታ በየቀኑ ያያሉ። ከዚያም እኛን «አባቦች» እና «በረሮዎች» እያሉ በመጥራት እንዲያሸማቅቁን ተምረዋል። እኛን መግደል ለነሱ በጣም ቀላል እንደሆነ አያጠራጥርም - አባቦች የሚገደሉና በረሮዎችም የሚጨረሱ እንደሆኑ ይታወቃሏ!

ዓለማችን ከዚያ በፊት ተመሳሳይ ነገር ሲከሰት ብዙ ጊዜ አይታለች። በናዚ ጀርመን ከተከሰተ በኋላ ሁሉም ታላላቅና ኃያል ሀገራት «በፍጹም አይደገምም!» ብለው ተማምለዋል። ስድስት ማንንም ልንነዳ የማችንል ሴቶች ይኸው

በመፈጠራችን ብቻ በጨለማ ውስጥ ታፍገን ለጭፍጨፋ እንፈለጋለን፡፡ ታሪክ እንዴት ራሱን ሊደግም ቻለ? ይህ ርኩሰት እንዴት ደግሞ ሊመጣ ተቻለው? ዲያቢሎስ እንዴት በመካከላችን የሚገዳደረው ሳይኖር፣ ልብንና አእምሮን እየመረዘ ያለገደብ እንዲህ መፍትሔ የመፈለጊያው ጊዜ እስኪያልፍ ይጎማለል ዘንድ ተፈቀደለት?

ቄሱ እኛ ይህን ንግግር እንደምንሰማ እርግጠኛ ሆነው ሳይሆን አይቀርም ልጃቸውን ተቆጡት፡፡ «ደደብ ነህ፤ የለየልህ ደደብ ሴምቤባ፡፡ ደምን ለማፍሰስ ጥሩ ሰበብ ያልተፈለገበት ወቅት አልነበረም፡፡ አሁን ከክፍሌ ውጣለኝ፡፡ ይህን ስትናገር ማዳመጥ ሰልችቶኛል፡፡»

«ቱትሲዎችን በመጥላቴ ደደብ ነኝ ብለህ ታስባለህ አባባ? እነርሱን መደበቅ የባሰ ድድብና አይመስልህም? ሰዎች ያንን እያደረግህ እንደሆነ እንደሚናገሩ የምታውቅ ይመስለኛል፡፡ እውነት ነው እንዴ? በቤታችን ውስጥ ቱትሲዎችን ደብቀሃል?»

ልቤ በአፌ ልትወጣ እስኪመስለኝ ዘለለች፡፡ ንዴቴ ጠፋ፤ እንደገና የተሰማኝ ነገር ቢኖር ፍራቻ ነው፡፡

«ቂልነትህን እስኪበቃኝ ተግቼዋለሁ ሴምቤባ፡፡ ቱትሲዎችን አልደበቅሁም፡፡ ያንተን ክፉ ቃላትም መስማት ያመኛል - የራስህ እናት ቱትሲ ነበረች እኮ! አክስቶችህ፣ አጎቶችህና ልጆቻቸው ሁሉ እየታደኑና እየተገደሉ ነው፡፡ አሁን ከክፍሌ ውጣልኝ፤ በድጋሚም አትምጣብኝ፡፡ *በል ውጣ!*»

ገና ከሲምቤባ መምጣት ሰቆቃ ሳናገግም በቅርቡ ቦንቦች ሲፈነዱ ሰማን - ሕንጻዎች ሲፈርሱ የሚሰሙ የሚመስሉ ተከታታይ አሰቃቂ ድምጾች ናቸው፡፡ ከያንዳንዱ ድምፅ በኋላም መዝሙር ተብዬውን እንሰማለን «ትልልቆቹን ግደሏቸው! ትንንሾቹንም ግደሏቸው! ግደሏቸው! ግደሏቸው! ሁሉንም ግደሏቸው!»

ከቤቱ አቅራቢያ ተኩስ ይሰማል፤ ከዚያም መዝሙሩ በጣም እየነላ ሲመጣ ገዳዮቹ በኛ አቅጣጫ እየመጡ እንደሆነ አወቅን፡፡ ድምጼን ሳላሰማ ጸሎት አደረስሁ፤ ከአፍታ በኋላ የነንድጓድ ድምፅ ሰማን፣ ከዚያም በኋላ ዶፍ ተከተለ፡፡ ገዳዮቹ ዝናብ እንዳይመታቸው ወደየቤታቸው ሄዱ መሰለኝ በተቀረው የሌሊቱ ክፍል የሰማነው ብቸኛ ነገር ዝናቡ በቆርቆሮው ጣራ ላይ የሚያሰማውን ድምፅ ብቻ ነው፡፡

የዚያን ምሽት ቄሱ ወደኛ መጡ፡፡ ፊታቸው ቀልቷል፤ ዓይኖቻቸውም ደም መስለው ቦዘዋል፡፡ ስለ ሴምቤባ ጥርጣሬ የተጨነቁ ይመስለኛል፡፡ ውጪ ላይ እየተዘዋወሩ በዙሪያችን የነበረውን አሰቃቂ ተግባር ታዝበዋል፡፡ የኢንተርሃምዌ ታጣቂዎች፣ ወታደሮችና ተራ ሁቱዎች ያገኙትን የቱትሲ ቤት በማፈራረስ ላይ እንደሆኑ አወሩልን፡፡

«ውጪ ላይ ችግሩ በጣም ከፍቷል» አሉን:: «በጣም በጣም ከፍቷል:: የ1959ኙንም ሆነ የ1973ቱን ግድያዎች አይቻለሁ፤ ከዚህ አንጻር ምንም የሚባሉ አልነበሩም:: ሁሉም ነገር እንዳቆመ ልትረዱት ይገባችኋል - ትምህርት ቤቶችና ገበያዎች ተዘግተዋል፤ ሰዎችም ወደ ሥራ መሄድ ትተዋል:: ሥራው እስኪያልቅ ድረስ አገሪቱ ተዘጋግታለች::»

«ሥራው እስኪያልቅ ድረስ ሲሉ ምን ማለትዎ ነው? *የትኛው ሥራ* ነው የሚያልቀው?» ስል ጠየቅሁ::

ቄሱም ቆም አደረጉና:: «ቱትሲዎችን መግደሉ ነዋ ልጄ:: ሁሉም ቱትሲዎች ሳይሞቱ ሥራው አለቀ አይባልም:: የመንግሥት ዋና ኢላማም ስለሆነ እንዲሳካ ሁሉንም ሰው እያተጉት ነው:: ምነው ባላየኋቸው ኖሮ የምላቸውን ነገሮች ዛሬ አይቻለሁ» አሉን::

በጣም ፈራሁ:: ስለ ቤተሰቤ አሰብኩ፤ የቄሱን ድምፅ ላለመስማት ጆሮዎቼን ለመንቀል ተመኘሁ::

«በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን ገድለዋል» ሲሉ ቀጠሉ፣ «ኢሥር ሺዎች... ምናልባትም መቶ ሺዎች፣ ቤቱ ይቁጠረው! እጅግ ብዙ ቱትሲዎች ወደ አብያተ ክርስቲያናት ከለላ ፍለጋ ሮጠው ስለሄዱ የአብያተ ክርስቲያናቱ በሮች አልተዘጉባቸውም:: አብያተ ክርስቲያናት ለወትሮው አይደፈሩም ነበር፤ አሁን ግን አልሆነም:: ገዳዮቹ አብያተ ክርስቲያናቱን ሰዉ በውስጣቸው ተጠልሎ ሳለ አቃጠሏቸው፤ ለማምለጥ የሞከረውንም ሁሉ በጥይት ፈጁት::»

«ወይኔ አምላኬ አይሆንም» አልኩ:: «በሬድዮ ሁሉም ሰው ወደ አብያተክርስቲያናትና የእግር ኳስ ሜዳዎች ለከለላ እንዲሄድ ይናገራሉ!»

«ያንን ብለው ሊሆን ይችላል፤ ግን ያ ማንንም አላዳነም:: ገዳዮቹ መትረየስና ቦምብ እየተሰጣቸው ወደዚያ ይላካሉ:: የአስከሬኖቹ ክምር የኔን ቤት ያክል ነበር.. ሽታውማ ወዲያ::»

«እባክዎን ይብቃዎት ቄሱ! ከዚህ በላይ አይንገሩን» ስል ለመንኳቸው::

ስለቤተሰቤ ልጠይቃቸው ፈለግሁ፤ ግን የሚሉኝን ነገር ለመስማት አልፈለግሁም:: ሌላ ቃል ለመስማት አቅሙ አልነበረኝም!

«እነዚህን ነገሮች ስለነገርኳችሁ አዝናለሁ፤ ቢሆንም ግን ምን እየተከሰተ እንደሆነ ማወቅ አለባችሁ» አሉን:: «እናንተ በመላው ሩዋንዳ ብቸኞቹ በሕይወት የተረፋችሁት ቱትሲዎች ልትሆኑም ትችላላችሁ:: ዛሬ ያየሁትን ብታዩ ኖሮ በሕይወት መኖርን የምትመኙ አይመስለኝም::»

ሌሎቹ ሴቶች ያለቅሱ ያዙ፤ እኔ ግን ምንም እንባ ፍጭጭ አላለኝ፡፡ በዚያን ሰዓት የሚወርድ እንባ አልነበረኝም፡፡ ሰቆቃም አልተሰማኝ፤ ንዴት እንጂ፡፡ ከመቼውም በላይ ተናደድኩ - ይቻላል ብዬ አምነውም ከነበረው በላይ፡፡ ቤተሰቦቻችን ያለምንም መደበቂያ ውጪ ላይ ባሉበት ወቅት ቁሱ እነዚያን አሰቃቂ ነገሮች ስለነገሩን ተናደድኩባቸው፡፡ መንግሥት ይህ የዘር ጭፍጨፋ እንዲካሄድ ስላደረገ ተናደድኩበት፡፡ ከምንም በላይ ግን በሁቱዎች ላይ ተናደድኩባቸው - በሁሉም ሁቱዎች፡፡ ቁሱም በቱትሲዎች ላይ እየተፈጸመ ስላለው ግፍ ያለማቆም ሲቀጥብሩ ንዴቴ ወደ ጥልቅ የጥላቻ ነበልባልነት አደገ፡፡

ከዚያ በፊት ማንም ላይ ንዴት የሚንጸባረቅበት ነገር አድርጌ የማላውቀው ሴትዮ በዚያን ሰዓት ጠመንጃ ኖሮኝ ሁሉንም የሚታየኝን ሁቱ ብገድለው ብዬ ተመኘሁ፡፡ አይ፣ ጠመንጃም አይደለ… መትረየስ፣ ቦንብና እሳት የሚተፋው ልዩ መሣሪያ አስፈለገኝ! ሁሉንም ለመግደል ፈለግሁ - ቱትሲዎችንም ሳይቀር… እንደ ራምቦ መሆንንና አገሪቷን በሙሉ በእሳት ለማጋየት ፈለግሁ፡፡ አቶሚክ ቦንብ ቢኖረኝ ኖሮ በደደቧና በጥላቻ በተሞላችው ሀገራችን በሩዋንዳ ላይ መጣል ነበር፡፡

ቁሱን አየኋቸውና እርሳቸውንም ለመግደል ተመኘኋቸው፡፡ እንደዚህ የመቆጣት ዐቅም ይኖረኛል ብዬ አስቢውም አላውቅ፤ እና ራሴን ከዚህ ነገር ለማጽዳት ብዙ ጸሎት እንደሚያስፈልገኝ አውቄያለሁ፡፡

ቄስ ሙሪንዚ ወሬያቸውን ጨረሱ፤ እኛም ተጨማሪ አሰቃቂ ዜና ጥበቃ እርሳቸውን ሸቅብ አንጋጠን እያየን ተቀምጠናል፡፡ አለንጋ አንስተው እስክንሞት ቢገርፉን ይሻለን ነበር፡፡ ቃላቸውን ያለ ማረጋገጫ ላምነው አልቻልኩም፡፡ እንደወጡ ሬድዮናቸው እንዲከፍቱትና የዜና ዘገባዎችን እንዲያስደምጡን ጠየቅኋቸው፡፡ ተስማምተውም በሩን ዘጉት፡፡

ከተወሰኑ ደቂቃዎች በኋላ አንድ የመንግሥት ባለሥልጣን በብሔራዊው ሬድዮ ጣቢያ ሲናገሩ ሰማናቸው፡፡ «በሩዋንዳ ያላችሁ ሁቱዎች ሁሉ… የጋራ ጠላታችንን ለመዋጋት አብረን የምንቆምበት ጊዜው አሁን ነው፡፡ የፖለቲካ ልዩነቶቻችንን ወደ ጎን ትተን ራሳችንን እንከላከል፡፡ እነዚህ እባብ ቱትሲዎች ሊገድሉን ነው… ቀድመን ልንገድላቸው ይገባል፡፡ ሳይቀድሙን እንቅደማቸው፡፡ ቱትሲዎቹን ባገኛችሁበት ግደሏቸው - አንድም አትተዉ፡፡ በእድሜ የገፉትንም ሆነ ሕጻናቱን ግደሏቸው - ሁሉም እባብ ናቸው፡፡ የሩአግ አማጽያን ወደ ሀገራችን ተመልሰው ከመጡ የቤተሰቦቻቸውን ሬሳ ብቻ ያግኙ፡፡ ሁላችሁንም ሁቱዎች ግዴታችሁን እንድትወጡና ሁሉንም ቱትሲ ጠላቶቻችንን እንድትገድሉ ጥሪ አቀርባለሁ፡፡»

አሁን ቁሱ እየዋሹ እንዳልሆነ በእርግጠኝነት አወቅሁ፡፡ አባቴም መንግሥትን በማመኑ እንደተሳሳተ ገባኝ፡፡ ያመነባቸው ሰዎች የዘር ጭፍጨፋውን የጠነሰሱና

አሁንም ተራ ሩዋንዳውያንን ለተግባራዊነቱ እየገፋፉ ያሉ ናቸው፡፡ በሩዋንዳ ትዕዛዝን የማክበር ልማድ አለ፡፡ በዚህም ምክንያት በሌላ ወቅት ሰው አክባሪ የነበሩ ሁቱዎች መሪዎቻቸው በሬድዮ ቱትሲዎችን እንዲገድሉ ሲነግሯቸው ሲሰሙ ትዕዛዙን ተቀብለው ገጀራዎቻቸውን አንደሚያነሱ አውቄዋለሁ፡፡

ከአንድ ሰዓት ገደማ በኋላ ቄሱ ወደ ቢቢሲ ዜና ሲቀይሩ ሩአጎች (የቱትሲው አማጺ ቡድን) ከሰሜን የሀገሪቱ ክፍል በድል አድራጊነት እየተዋጉ ወደ ኪጋሊ አንደደረሱ የሚገልጹ ዘገባዎችን ሰማን፡፡ እንደዘገባው ከሆነ ከዘር ፍጅቱ ጀርባ የነበረው ጽንፈኛው የሁቱ መንግሥት የመውደቅ አደጋ አንጣቦበታል፡፡ ዜናው ልቦቻችንን አዘለላቸው - ይህ ከሆነ ሩአጎች ኪጋሊ ከደረሱ በጥቂት ሳምንታት ውስጥ ወደኛ ክፍለ ሀገር ይገባሉ! ውሎ አድሮም ወደ ትንሿ መንደራችን ደርሰው ይታደጉናል፡፡

ይህ የሚሆንበት ጊዜ ከቆየ ለኛ በጣም ስለሚዘገይብን ወዲያውኑ ቢሆን ተመኘሁ፡፡

ምዕራፍ 11
ምጎረት ለማድረግ ስጣጣር

በጽሞና ጸሎት እያደረስኩ ሳለሁ ገዳዮቹ ድጋሚ ቤቱን ለማሰስ መጡ፡፡

የመጡት ከቀትር ትንሽ ዘግየት ብሎ በመቁጠሪያዬ ከጠዋት ጀምሮ እግዚአብሔር ፍቅሩንና ምህረቱን በዓለም ላይ ላሉ ሐጢአተኞች ሁሉ እንዲሰጥ እየጸለይኩ ባለበት ሰዓት ነው፡፡ በተቻለኝ መጠን ብጣጣርም ለገዳዮቹ ለመጸለይ ግን አልቻልኩም፡፡ ያ ነው ችግሬ፡፡ እግዚአብሔር ግን ከምንም ነገር በላይ ለሁሉም ሰው አንድንጸልይ ይፈልጋል፡፡ የፈጣሪዬ አብሮነት አሻኝ፡፡

በየቀኑ በተቻለኝ መጠን ለማካካሻ በመቁጠሪያዬ በጥልቀት ብዙ ጊዜ ጸለይኩ፡፡ ደጋግሞ ሰላም-ለኪና አቡነ ዘበሰማያት ማለቱ 12 ወይም 13 ሰዓታትን ይፈጅብኛል - በአባታችን ሆይ ጸሎት ላይ «የበደሉንን ይቅር እንደምንል» የሚለው ላይ በደረስኩ ቁጥር ገዳዮቹን ላለማሰብ እጥራለሁ - ምክንያቱም እነርሱን አንደማልምራቸው ስለሚታወቀኝ ነው፡፡

በሁለተኛው አሰሳ ወቅት የገዳዮቹ ጩኸት ከእንቅልፌ እንደሚቀሰቅሰኝ የተናደደ ሰው ድምፅ በጸሎቴ መካከል ጣልቃ ገባብኝ፡፡ ከዚያም ከጭንቅላቴ አጠገብ አራት ወይንም አምስት የሚንጓጓ ድምፅ ሰማሁ፣ ይህ ድምፅም ሙሉ ትኩረቴን ሳበው፡፡ በቁሱ መኝታ ቤት እንደገቡ አወቅሁ! የቁሱን ንብረት ይበረብራሉ፣ ከግድግዳው ላይ የተለያዩ ነገሮችን ይቀዳሉ፣ አልጋውን ያነሳሉ፤ ወንበሮችን ያገላብጣሉ፡፡

«እዚያ እዩ!» አንደኛው ይጮሃል፡፡ «እስኪ ደግሞ እዚህ ስር እዩ፡፡» ያንን ትልቅ ሣጥን አንሱት! *ሁሉንም ፈትሹ!*

ሰተነፍስ እንዲይሰሙኝ ብዬ አፌን በእጅቼ አፈንኩ፡፡ ገዳዮቹ የሚገኙት ከራሴ የጣቴን አንድ አንጓ በሚሆን ርቀት ብቻ ነው.... ከቁምሳጥኑ ፊት ለፊት ናቸው - አቤት የቁምሳጥኑ ውለታ! ስለሱ እግዚአብሔርን በድጋሚ አመሰገንኩት፤ ልቤ ግን አሁንም ደረቴን ይመታል፡፡

ሲሰቁ እሰማቸዋለሁ፡፡ እየተዘዋወሩ ሰዎችን በመግደል ደስታን በማግኘት ላይ ናቸው! ረገምኳቸው፣ በሲኦል እንዲቃጠሉም ተመኘሁ፡፡

ቁምሳጥኑ ከበሩ ጋር ተላተመ፡፡ ጀሮዎቼን ከድኜ ይዤ ጸለይኩ - እግዚአብሔር ሆይ፣ መቼም ቁምሳጥኑን እዚያ አስቀምጠሽዋል... አሁንም እዚያው ይሁን! እንዲያንቀሳቅሱት አትፍቀድላቸው፡፡ ጌታ ሆይ አድነን!

ራሴን አመመኝ፤ አስቀያሚው ሹክሹክታም መልሶ በራሴ ውስጥ መጣብኝ - ለምንድነው እግዚአብሔርን የምትጠሪው? የገዳዮቹን ያህል ጥላቻ በልብሽ ውስጥ የለም? አንቺስ እንደነሱ የጥላቻ ጥፋት አልፈጸምሽም? በሞቱ ብለሻል፤ እንዲያውም አንቺ ራስሽ ልትገድያቸው ተመኝተሻል! አምላክ ለሥቃይ እንዲዳርጋቸውና በሲኦልም እንዲያቃጥላቸው ሳይቀር ጸልየሻል::

ገዳዮቹን በበሩ በሌላው አቅጣጫ እሰማቸውና አምላክንም ወዲያ እንዲሄዱ አድርጋቸው እያልኩ አለማመን ያዝኩ.. ሰውረን ከ...

አምላክን አትለምኚ ኢማኪዩሌ፣ ድምጹ አቋረጠኝ:: ውሸታም እንደሆንሽ ያውቃል:: ሁሌ ስትጸልዩ እወድሃለሁ እያልሽ ትዋሸዋለሽ:: አምላክ ሁላችንንም በአምሳሉ አይደለም የፈጠረን? አምላክን እየወደድሽ እንዴት ብዙ ፍጡራኑን ትጠያለሽ?

ሐሳቦቼ ሁሉ ሸባ ሆኑ:: በአእምሮዬ የነበረው ሰይጣን ልክ ነው - ወደ አምላክ በጸለይኩ ቁጥር እዋሻለሁ:: በጅምላ ጭፍጨፋው ተጠያቂ በሆኑት ሰዎች ላይ ጥላቻ ሰላደረብኝ መተንፈስ አቃተኝ::

በዚያን ሰዓት ቢያንስ 40 ወይም 50 የሚሆኑ ወንዶች በቁሱ መኝታ ክፍል እየጮሁና እየዘላበዱ ነው:: የሰከሩና ስለሰው ግድ የማይሰጣቸው ይመስላሉ፤ ጩኸታቸውም ከወትሮው የባሰ ክፋት ይንጸባረቅበታል - «ትልቁንም ትንሹንም ቱትሲ ግደሉ.. በተናጠልም፣ በጅምላም ግደሏቸው:: ግደሏቸው!»

አምላክን ከቁምሳጥኑ እንዲያርቃቸውና ከቤቱም ጭራሹኑ እንዲያስወጣቸው ጸሎቴን ጀመርኩ::

ከአስቀያሚው መዝሙር ሰር ሰር እያለ ርኩሱ ድምፅ የባሰ አናደደኝ - ዋጋ የለውም... አምላክን አትጥሪ:: ገዳዮቹን እዚህ የላከልሽ ማን መሰለሽ? <u>እርሱ</u> እኮ ነው! ምንም ሊያድንሽ አይችልም:: አምላክ ዋሾዎችን አይረዳም::

ለገዳዮቹ መጸለይ ጀምሬ ወዲያውኑ አቆምኩ:: የእግዚአብሔር ከለላ በጣም አስፈለገኝ፤ በልቤ ግን እነሱ ሞት እንደሚገባቸው አምኛለሁ:: በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን እንዳላረዱና እንዳልደፈሩ አድርጌ ላስብ አልችልም - በብዙዎች ንጹሃን ነፍሶች ላይ ያደረሷቸውን አሰቃቂዎቹንና አስከፊዎቹን ነገሮች አልረሳቸውም::

የማይቻለውን ከኔ ሰለምን ትጠብቃለህ? እግዚአብሔርን ጠየቅሁት:: ሊገድሉኝ የሚቋምጡትን ሰዎች እንዴት ይቅር እላለሁ፣ ቤተሰቤንና ወዳጆቼን ማረዳቸውን የምጠረጥረውን? እነዚህን ገዳዮች መማር ለኔ ተቀባይነት የለውም:: እንዲያውም ለሰለባዎቻቸው ልጸልይ - ለተደፈሩት፣ ለተገደሉትና ለተቆራረጡት:: ለወላጅ አልባዎቹና የትዳር አጋሮቻቸውን ላጡት ልጸልይ ... ለፍትህ ልጸልይ:: እግዚአብሔር

ሆይ እነዚያን ርኩሳን ፍጡራን እንድትቀጣቸው አጠይቅሃለሁ፣ ልምራቸው ግን አልችልም- በቃ አልችልም።

በመጨረሻም ገዳዮቹ ሲሄዱ ሰማኋቸው። መኝታ ክፍሉን ለቀው ሄዱ፤ ቤቱንም ትተው ወጡ፤ ወዲያውም ቁልቁል ሲወርዱ መዝሙራቸው እየራቀ እየራቀ ሄደ።

ጸሎቴን እንደገና ጀመርኩ፤ አምላክ ስላተረፈንና ለኔም ቁምሳጥኑን ከመታጠቢያ ክፍሉ ፊት ለፊት እንዲቀመጥ ሃሳቡን ስላቀበለኝ አመሰገንኩት። በልቤ አምላኬ ያ ያንተን የአስተሳሰብ ምጥቀት ያሳያል አልኩና በድጋሚ አመሰገንኩት። ገዳዮቹ የት እንደሄዱ አሰብኩ፤ ከዚያም ስለ ወዳጆቼና ስለ ቤተሰቤ መጸለይ ጀመርኩ - ጌታዬ ሆይ እባክህ እናቴን ጠብቃት፤ ስለኛ አብዝታ ትጨነቃለች። በጣም ግትር በመሆኑ አባቴንም ጠብቅልኝ...

ምንም ፋይዳ አልነበረውም - ጸሎቴ ባዶ እንደሆነ ተሰማኝ። በነፍሴ ውስጥ ጦርነት ተጀመረ፤ ለፍቅር አምላክ በጥላቻ የተሞላ ልብ ይዤ ልጸልይ አይገባኝም።

ገዳዮቹን እንዲምራቸው እንደገና ለመጸለይ ሞከርኩ። በውስጤ ግን ፈጽሞ ይህ ምልጃ ይገባቸዋል ብዬ አላመንኩም። አሠቃየኝ... ለነሱ ለመጸለይ ሞከርኩ፣ ግን ለሰይጣን የምጸልይ ያህል ተሰማኝ። እባክህ አምላኬ ልቤን ክፈተው፤ እንዴትም ይቅር አንደምል አሳየኝ። ጥላቻዬን ለማፈራረስ ያን ያህል ጠንካራ አይደለሁም - ሁላችንንም በጣም በድለውናል... ጥላቻዬ በጣም ከባድ ስለሆነ ሊያጠፋኝ ይችላል። ልቤን ንካው አምላክ፤ እናም እንዴት ምኅረት እንደማደርግ አሳየኝ።

ከዚህ ማቅማማት ጋር ለሰዓታት ታገልኩ። ሌሊቱንና ቀጣዩንም ቀን ሙሉ ጸለይኩ፤ ከዚያ በኋላም ባለው ቀን፣ ከዚያም ቀጥሎ በሚመጣው። እዚህ ግባ የሚባል ምግብ ሳልበላና ውሃም ሳልጠጣ ሳምንቱን ሙሉ ጸለይኩ። መቼና ለምን ያህል ጊዜ እንደተኛሁም አላስታውስ፤ የጊዜውም ማለፍ አልታወቀኝ።

አንድ ምሽት ካለንበት ቤት ብዙም ሳይርቅ ዋይታ ሰማሁ፤ ከዚያም የሕፃን ለቅሶ ተከተለ። ገዳዮቹ እናትየዋን ገድለው ሕፃኑን መንገድ ላይ በራሱ ጊዜ እንዲሞት ትተውት ሳይሆን አይቀርም። ሕፃኑ ሌሊቱን ሙሉ ሲያለቅስ አደረ፤ ንጋት ላይ ለቅሶውና ሲቃው ድክምክም እያለ ሄዶ የሚሰማውም እየቆየ እየቆየ ሆነ፣ ይባስ ብሎ ሲመሽ ድምጹ ከነጭራሹ ጠፋ። ውሾች በአቅራቢያው ሲጮሁ ሰምቻቸው ስለነበር የሕጻኑ ሕይወት እንዴት እንዳለፈች ሳስብ ሰውነቴ ተንቀጠቀጠ። ለእግዚአብሔር የሕፃኑን ምስኪን ነፍስ እንዲቀበላት ጸለይኩ፤ ከዚያም እንዲህ ስል ጠየኩት *ሕፃን ላይ ይህን ለሚያደርጉ ሰዎች እንዴት ምኅረት ላድርግላቸው?*

ምላሹን ልክ ከእግዚአብሔር ጋር በዚያ ክፍል ኢያወራን እንደተቀመጥን ሁሉ ሰማሁት፡ ሁላችሁም ልጆቼ ናችሁ... ሕፃኑም አሁን ከኔ ጋር ነው፡፡ ይህን ያህል ቀላል ቃል ቢሆንም ግን ይህ ለቀናት ስጸልይበት ለነበረው ጸሎት የተሰጠኝ መልስ ነው፡፡

ገዳዮቹ እንደ ልጅ ያደርጋቸዋል፡፡ አዎን ስለ ድርጊቶቻቸው በጽኑ ሊቀጡ የሚገባቸው አረመኔ ፍጥረቶች ናቸው፤ ሆኖም ግን አሁንም ልጆች ናቸው፡፡ ልጆች አንዳንድ ጊዜ ሊሆኑ እንደሚችሉት ሁሉ ጨካኞች፣ ክፉዎችና አደገኞች ናቸው፤ ይሁን እነጂ ልጆች መሆናቸው ኣይካድም፡፡ እነሱ እያመጡት የነበረውን አሰቃቂውን ጉዳት ኣይተው አልተረዱትም፡፡ ምንም ሳያስቡ ሌላውን በጭፍን ጎድተዋል፤ ቱትሲ ወንድሞቻቸውንና እህቶቻቸውን ጎድተዋል፤ እግዚአብሔርን ጎድተዋል - ራሳቸውን እንዴት በኢጅጉ እየጎዱ እንደነበረም አልተረዱትም፡፡ አእምሮዎቻቸው በሀገሪቱ ተሰፋፍቶ በነበረው ርኩሰ ተግባር ተመርዘዋል፤ ነፍሶቻቸው ግን ርኩሳን አልነበሩም፡፡ የሚፈጽሟቸው ግድያዎች እንዳሉ ሆነውም የእግዚአብሔር ልጅነታቸው ኣይፋቅም፤ እኔም ታዲያ አንድን ልጅ ይቅር ልል እችላለሁ፡፡ እንደማውራት ቀላል ባይሆንም... በተለይ ያ ልጅ ሊገድለኝ እየምከረ ባለበት ሁኔታ፡፡

በጌታ ዓይኖች ገዳዮቹ ፍቅርና ይቅርታ የሚገባቸው የቤተሰቡ አካላት ናቸው፡፡ እግዚአብሔርን ልጆቹን ለመውደድ ሳልፈልግ እኔን እንዲወደኝ መጠየቅ እንደማልችል አውቃለሁ፡፡ በዚያን ጊዜ ገዳዮቹ ለሃጢአቶቻቸው ምኅረት እንዲያገኙ ጸለይኩላቸው፡፡ አምላክ እየሄዱበት የነበረውን መንገድ አሰቃቂ ስህተትነት በምድር ላይ ያለው ሕይወታቸው ሳያከትምለትና ስለሚችሉት ሐጢያቶቻቸው ሊጠየቁ ከመጠራታቸው በፊት ያውቁ ዘንድ እንዲመራቸው ጸለይኩ፡፡

የአባቴን መቁጠሪያ ጨብጬ ይገ አምላክ እንዲረዳኝ ስጠይቀው ድጋሚ ድምጹን ሰማሁት - ማሪያቸው፤ የሚያደርጉትን ኣያውቁትም፡፡

በዚያን እለት ገዳዮቹን ለመማር ወሳኝ እርምጃ ሄድኩ፡፡ ንዬቴ ከኔ ይወጣልኝ ጀመር - ለእግዚአብሔር ልቤን ከፍቼለት ማለቂያ በሌለው ፍቅሩ ሞላው፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ለገዳዮቹ አዘንኩላቸው፡፡ እግዚአብሔር ሐጢኣታቸውን ይቅር እንዲላቸውና ነፍሶቻቸውን ወደ አንጸባራቂው ቀጣናው እንዲመልስላቸው ጠየኩት፡፡

በዚያን ምሽት በንጹሕ ኅሊናና ልቦና ጸለይኩ፡፡ ወደ መታጠቢያ ቤቱ ከገባሁ በኋላም ለመጀመሪያ ጊዜ ሰላማዊ እንቅልፍ ተኛሁ፡፡

ምዕራፍ 12
የማዋየው ወዳጅ ሳጣ

በመታጠቢያ ቤቱ ውስጥ የራሴ የምለው ስፍራ እግኝቻለሁ - የልቤን ትንሽ ጥጋት፡፡ ስነቃ ወዲያውኑ ወደዚያ አፈገፍጋለሁ፤ እስክተኛ ድረስም በዚያው እቆያለሁ፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር የምነጋገርበት፣ ቃሉን የማሰላስልበትና መንፈሳዊ ማንነቴን የምንከባከብበት የተቀደሰ ስፍራዬ ነው፡፡

በምመሰጥበት ወቅት ከእምነቴ ምንጭ ደርሼ ነፍሴን አጠናክራለሁ፡፡ ሽብር ሲከበኝ በነበኘሁት ቁጥር በሚያስደተኝና ነይ ነይ በሚለኝ ዓለም ከለላ አገኛለሁ፡፡ ሰውነቴ ሲንኮታኮት እንኳን ነፍሴ ከእግዚአብሔር ጋር ባለኝ የጠለቀ ግንኙነት ትፋፋለች።

ወደ ልዩ ስፍራዬ በጸሎት እገባለሁ፤ አንዴም ከገባሁ በኋላም ያለ ማቋረጥ እጸልያለሁ፣ መቁጠሪያዬን ሃሳቤንና ሃይሌን ወደ እግዚአብሔር እንዳተኩር እንደመልህቅ እጠቀመዋለሁ፡፡ የመቁጠሪያው ዶቃዎች በወንጌል ላይ እንዳተኩርና የእግዚአብሔርን ቃል በአእምሮዬ ህያው አድርጌ እንዳቆይ ረድተውኛል፡፡ በጸጥታ እጸልያለሁ፤ ግን ራሴን በእውነት እያልኳቸው እንደሆነ ለማሳመን ሁልጊዜ ቃላቱን በአፌ ድምፅ ሳላሰማ እላቸዋለሁ... ያ ባይሆን ኖሮ ጥርጣሬ ይገባኝና አሉታዊው ኃይል እየተጣራ ይመጣብኛል፡፡

የአንድን ነጠላ ቃል ትርጉም ሳሰላስል ሰዓታትን እወስዳለሁ፣ እንደ ምሳሪት፣ እምነት ወይም ተስፋ ያሉትን፡፡ እጅ መስጠት የሚለውን ቃል ሳሰላስል ቀናትን አሳልፌያለሁ፡፡ በዚህም ምክንያት የራስን ስብዕና ለአንድ ከፍ ላለ ኃይል መስጠት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ተረዳሁ፡፡ ራሴን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር አሳልፌ ሰጠሁ፡፡ በማልጸልይበት ጊዜ በእርሱ ብርሃን ውስጥ እንዳልሆንኩ ይሰማኛል፤ የመታጠቢያ ክፍሉ ዓለምም በበኩሉ ለመቋቋም የሚከብድ ነው፡፡

በተደበቅንበት የመጀመሪያው ወር መጨረሻ አካባቢ ቁስ ሙሪንዚ አንድ ሌሊት ላይ በጣም አምሽተው ትርፍራፊ ምግብ ይዘውልን መጡ፡፡ ወደዚህ ሲያስገቡን በሃዘኔታ ስሜት ቢሆንም አሁን ግን ያ እየጠፋ የሄደ መሰለ፡፡ በዚህ ምሽት ፊታቸው ከወትሮው የአሳቢነትና የሃዘኔታ ገጽታ ወደ መኮሳተር መጣ፡፡ «አባትሽ በጣም መጥፎ ቱትሲ ነበር!» ሲሉ አያገጣብሩኝም!

«ምን? ምን ማለትዎ ነው?» ሙሉ በሙሉ የማደርገውን አሳጣኝ፤ ቢሆንም ግን በአባቴ ላይ የሰነዘሩት ጥቃት አባቴን ባለፈ ጊዜ የመግለጻቸውን ያህል አላናደደኝም፡፡

ከቤተሰቤ አባላት ማናቸውም ሊሞት የሚችልበትን እሳቤ አልቀበልም ብያለሁ፡፡ «አባቴ ጥሩ ሰው ነው ቄሱ - ምን አልባትም ካገኘኋቸው ሰዎች ሁሉ መልካሙ ሰው!»

«አይ ኢማኪዩሌ አባትሽማ መጥፎ ቱትሲ ነበር - መጥፎ ሰው ... የሩአግ አማጽያን የእርስ በርስ ጦርነት ያቅዱ ዘንድ ይረዳ ነበር፡፡» ሌሎቹን ሴቶች አይተው እኔ ላይ ጠቆሙና እንዲህ አሉ፤ «ይዘው ቢገድሏችሁ በኢማኪዩሌ ምክንያት ነው፡፡ ጎዳዮቹ እሷን የሚያድኗት እኮ በአባቷ ድርጊቶች ሰበብ ነው፡፡» ቄሱ አፍጠውብኛል፤ በዚያም ላይ የሌሎቹን ሴቶች ዓይኖችም በኔ ላይ እንደ ጦር መሰካታቸው ይታወቀኛል፡፡

«እናንተ ቤት ውስጥ 600 ጠመንጃዎችን አግኝተዋል» ሲሉ ቀጠሉ ወደኔ ተመልሰው፡፡ «ቦምቦችንና የሚገደሉ ሁቱዎችን ስም ዝርዝርም አግኝተዋል፡፡ ለዚያ ነው እናንተ ቱትሲዎች እየታደናችሁና እየተገደላችሁ ያላችሁት፡፡ ሁቱዎች ቀድመው ወደ ተግባር ባይገቡ ኖሮ ይሄኔ እኛ ነበርን በቱትሲዎች የምንገደለው!»

የሚናገሩትን ለማመን አልቻልኩም፡፡ ጽንፈኛ ሁቱዎቹ የሚያሠራጯቸው መርዘኛ ውሸቶች ቄስ ሙሪንዚን ምክንያታዊነት አሳጥተዋቸዋል፡፡ ከአባቴ ጋር ለዓመታት ወዳጅ ነበሩ፡፡ አባቴ የድሆችንና ኑሮ የማይሞላላቸውን ሰዎች ሕይወት ለማሻሻል ሕይወቱን የሰጠ ሰው ነው፡፡ አባቴ ትምህርት ቤቶችንና ለቱትሲዎች፣ ለሁቱዎችና ለትዋዎች ሁሉ አነስተኛ የጸሎት ቤቶችን ሰርቷል፡፡ ታዲያ ቄሱ መሣሪያ በመደበቅም ሆነ ግድያን በማቀነባበር እንዴት ሊወነጅሉት ቻሉ? አባቴ ከደጃችን ሆነው ተስፋ የቆረጡትን ቱትሲ ስደተኞች ሁቱዎቹን ሊገድሏቸው ቢመጡ እንኳን እንዳይገድሉ አላሳሰበም ነበር?

ቄስ ሙሪንዚ ይህን መረጃቸውን ከባለሥልጣናት እንደሰሙት ነገሩኝ፡፡ ጥሎባቸው እንደ ብዙው ሩዋንዳዊ ሁሉ በሥልጣን ላይ ያሉ ሰዎች የሚነግሯቸውን በጭፍን ያምናሉ፡፡

መንፈሴ ተንኮታኮተ፡፡ እንደዚህ ዓይን ያወጣ ውሸትን በአባቴ ላይ ማንም እንደዋዛ ሊያሠራጭ እንደማይችል እርግጠኛ ሆንኩ... አስቀድመው ገድለውት ካልሆነ በስተቀር፡፡ እርሱን አደገኛ ሰው አስመስሎ ማቅረብ በግልጽ የእርሱን መገደል ትክክለኛነት ለማሳየት የተጠቀሙበት እቅዳቸው መሆን አለበት፡፡ እኔ ግን ስለዚያ ላስብ አልችልም፡፡ ከቤተሰቤ ማንም ሰው ሞቷል የሚለውን ሐሳብ ለማስተናገድ አልፈለግሁም - ለዚህ ጊዜው አሁን አይደለም፡፡ ገና ያንን ለመቀበል አልጠነከርኩም፡፡

በቄሱ በጣም ስለተናደድኩባቸው ለመጮህ ፈለግሁ፤ አንዳች ነገር ማድረግ ግን እንዴት ይቻለኛል? እርሳቸው በኛና በሞት መካከል የቆሙ ብቸኛው ሰው ናቸው፡፡ ምንም እንኳን በወቅቱ ልግስናቸውን በጣም ባያሳዩንም በእርሳቸው በጎ አድራጎትና መልካም ፈቃድ ላይ ሙሉ በሙሉ ጥገኞች ነን፡፡ እኛን አደጋ ላይ እንዳለንና እገዛ

እንደሚያስፈልጋቸው ጎረቤቶቻቸው ማየታቸውን እንዳቆሙ አውቀነዋል፡፡ አሁን እያዩን ያለው ልክ ገዳዮቹ እንደሚያዩን ነው - ሰው እንዳልሆንን፣ ጦርነቱ ሳያልቅ መጥፋት ዕጣ ፈንታችን እንደሆነ በረሮዎች፡፡

ቄስ *ሙሪ*ዚ የአባቴን መልካም ስም ሲያጠፉ ንዴቴ በውስጤ ተንተገተገ፡፡ ንዴቴን መቆጣጠር አልቻልኩም - አባቴ የሚበቃውን ያህል ተዋርዷል! በመታጠቢያ ቤቱ ከቆለፉብን ወዲህ ድምጼን ለመጀመሪያ ጊዜ ከፍ አደረግሁ - «አባቴ ያን ያህል መሣሪያ ቢኖረው ለምን እኛ ጋ ከለላ ፈልገው ለመጡት በሺዎች የሚቆጠሩ ቱትሲዎች አልሰጣቸውም? ያን ያህል መሣሪያ ቢኖረው ገዳዮቹ ቤታችንን ሲያቃጥሉት ለምን አላስቆማቸውም? ሁቱዎችን ለመግደል ቢያስብ ቤተሰቡን ወደ መደበቅ ሳይገፋፉትና ኑሮውን ሳያበላሹት በገደላቸው ነበር! ይንገሩኝ ቄሱ፣ መሣሪያዎቹን ለምንድነው ሚስቱንና ሴት ልጁን ከገዳዮችና ከደፋሪዎች ለመከላከል ያልተጠቀመባቸው?»

ቄስ *ሙሪ*ዚ ድንገት መገንፈሌ ደነገጡ (ሴቶቹም እንደዚያው - ሕይወቶቻቸውን በእጁ ከያዘው ሰው ጋር ስገዳደር ሲያዩኝ ባለማመን ዓይኖቻቸው ፈጠጡ)፡፡ ዝም እንድል በእጃቸው ተዩ የሚል ምልክት አሳዩኝ - ከዚያም መሣሪያዎች በልጅነቴ መነኩሲት እንዲያደርጉኝ ጠይቄያቸው በነበሩት በደጉ ሽማግሌ አባ ክሌሜንት ቤተክርስቲያንም እንደተገኙ ነገሩኝ፡፡ እኝህ አባት እንስሶች ሲጎዱ ማየት ስለማይፈልጉ ዕድሜ-ልካቸውን አትክልት ብቻ የሚመገቡ፣ አመፅ የሚያንገፈግፋቸውና ጠመንጃ የሚጠሉ ነበሩ፡፡ የቄሱ ሐሳብ እንዲህ ያለ ነጭ ውሸት ስለሆነ ነው መገዳደር ያለብኝ፡፡

«እርስዎ ከነዚህ ከሚሏቸው መሣሪያዎች አንዱን እንኳን አይተዋል ቄሱ?»

«አይ... ግን ከትልልቅ ሰዎች ነው የሰማሁት - ከሚታመኑና ከማይዋሹ፡፡»

ከዚያን ጊዜ በፊት በተለይ በሀገሪቱ እየተከሰተ ከነበረው ነገር አንጻር የተማረ ሰው እንደዚህ እንጭጭ መሆን ይችላል ብዬ ላስብ አልችልም፡፡ «ስለዚህ አባቴን ለሚወነጅሉባቸው ነገሮች ምንም ማረጋገጫ የለዎትም፣ እስኪ ካለዎት ያምጡት፡፡»

ባዶ ነጭ ወረቀት ከኪሳቸው አውጥተው ያን ዓይነት ወረቀት የሩአግ አማጽያን መሣሪያና ገንዘብ ለሚለግሳቸው የሚሰጡት እንደሆነ ነገሩን፡፡ «እቤትሽ ተገኝቷል» አሉኝ እፊት ለፊቴ የጭስ ጋዝ የሚተፋ መሣሪያ እንደያዙ ሁሉ እያውለበለቡት፡፡

«ባዶ ወረቀት እኮ ነው፡፡ ባዶ ወረቀት፡፡»

«ያው አማጽያኑ እንደሚጠቀሙበት ዓይነት ወረቀት ነው፡፡»

ከዚያ በላይ ላዋራቸው አልቻልኩም፡፡ «እንግዲህ አንድን ሰው ለማውገዝ የምትጠቀሙት ማስረጃ ያን የመሳሰለው ከሆነ እዚህ ባሉ ሰዎች ላይ ግድያ ለምን እንደሚመጣባቸው መረዳት እችላለሁ፡፡»

ቄሱ ትንሿን ቁራጭ ወረቀት ወደ ኪሳቸው አስገብተው ሊሄዱ ተመለሱ፡፡

«ቆዩ» አልኳቸውና «የሚያውሱኝ መጽሐፍ ቅዱስ አለዎት? የእኔን እቤት ረስቼው ነው፡፡»

የተሸማቀቁ ይመስላሉ - ቤቴ ጋይቶ የፈራረሰ መሆኑን ያውቃሉ - እንደሚያመጡልኝ ተስማሙ፡፡ አመሰገንኳቸው .. በአምላክ ቆንጆ ቃላት አእምሮዬን ማጽዳት አለብኝ፡፡

ሌሎቹ ሴቶች ራሴን የሳትኩ ያህል ተሰምቷቸው አዩኝ፡፡ የቄሱን ትዕግሥትና ሥልጣን ያለአግባብና በማያስፈልግ ሁኔታ እንደተጋፋሁም አሰቡ፡፡ ምናልባት ይህን አድርጌ ሊሆን ይችላል፤ ግን ምንም ግድ አልሰጠኝም፡፡ አባቴን ለመከላከል ግዴታ እንዳለብኝ ስለተሰማኝ ነው ይህን ማድረጌ፤ በዚያም ሰዓት ቄሱ ከሸሻኒ ይልቅ አሳሪ መሰሉኝ፡፡

ቄሱ ስለ አባቴ ክፉ ክፉውን ማውራታቸው እኛ በሕይወት ለመቆየት የቀሩን ቀናት በጣት የሚቆጠሩ እንደሆኑ ማሰባቸውን የሚያሳይ በጣም ግልጽ ምልክት ነው፡፡ ሩዋንዳውያን ስሜታቸውን ለራሳቸው ብቻ የሚይዙ በእጅጉ ቁጥብና ምስጢረኞች ናቸው - እኔ ከጅምላ ጭፍጨፋው ድኜ አንድ ቀን ከእርሳቸው እኩል ሆኜ እንደገና እንደማነኛቸው ቢያስቡ ኖሮ በምንም ዓይነት ሁኔታ ቄሱ ለኔ ስሜታቸውን እንደዚያ አጋልጠው አያሳዩኝም፡፡

ከንዴቴ ለመገላገል በመጸለይ ላይ በሆንኩበት ጊዜ ቄስ ሙሪንዚ በመኝታ ክፍላቸው ያለውን ሬድዮ ከፈቱት፡፡

አዲሱ የሩዋንዳ ርዕሰ-ብሔር ይናገራል፡፡ የኛ ክፍለሀገር የኪቡዬ ስም ሲጠራ ጆሮዎቻችን ለመስማት አቆበቆቡ፡፡ ድምጻቸው ጉጉት ይንጸባረቅበታል - ጦርነቱ ማለቁ ይሆን ታዲያ? እኛስ በመጨረሻ መታጠቢያ ቤቱን ለቀን ወጥተን ቤተሰቦቻችንን ለመፈልግ መሄድ እንችል ይሆን? በመጨረሻ አንድ ጥሩ ዜና ልንሰማ ነው ብለን አሰበን ስድስታችን እርስ በርሳችን በጉጉት ታያየን፡፡ በመሸበር ስናደምጥ ሳለን ተስፋችን ተሟጠጠ፡፡

«በግሌ ታታሪዎቹን የኪቡዬን ሁቱዎች ለግሩም ሥራችሁ እንኳን ደስ አላችሁ ለማለት እፈልጋለሁ» አለ ርዕሰ-ብሔሩ ፡፡ «ቱትሲ ጠላቶቻችን በኪቡዬ ከማንኛውም ክፍለሀገር በላይ አልቀዋል፡፡»

አመመኝ፡፡ ዓለም አገሪቱን ሰቅዞ የያዛትን እብደት አላየውም? ማንም አካል መጥቶ ሊያግዘን አይችልም ማለት ነው?

ርዕሰ-ብሔሩ በኪቡዬ እየተሠራ ባለው «ጥሩ ሥራ» በጣም ስለረካ ገዳዮቹ ድሉን በአግባቡ እንዲያከብሩ ለምግብና መጠጥ መግዣ በሺዎች የሚቆጠር ዶላር ለመላክ ቃል ገባ፡፡ «ሥራውን ስትጨርሱና ሁሉም ጠላቶቻችን ሲሞቱ በገነት እንኖራለን፡፡ ከበረሮዎች ጋር ለሥራ መፎካከር ይቀርልናል፡፡ ትናንሽ በረሮዎች በማይኖሩበት በትምህርት ቤቶቻችን ለሁቱ ልጆች በቂ ቦታ ይኖራል፡፡» የቀጥታ ስርጭት ሳይሆን አይቀርም፤ ሰዎች ሲያጨበጭቡና ሲያውካኩ ይሰማናል፡፡

«በኪቡዬ በጣም ጥሩ ሥራ ስትሰሩ ቆይታችኋል - ከሞላ ጎደል ሁሉም ጠላቶቻችን ሞተዋል፡፡ ቢሆንም ታዲያ ሁሉንም መግደል አለብን፡፡ ሥራውን አናቋርጥ!»

በተስፋ መቁረጥ እርስ በርስ ተያየን፡፡ በእኛ አካባቢ የሚኖሩት ከሞላ ጎደል ሁሉም ቱትሲዎች ያለው ግን እውነት ይሆን? ከሩብ ሚሊዮን በላይ ቱትሲዎች በኪቡዬ ይኖራሉ... ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? የኛስ ቤተሰቦች? ወላጆቼ፣ ቪያኒና አገስቲንስ የት ይሆኑ? ወይኔ ዳማሲን የኔ ውድ የት ይሆን? አምላክን እየፈተንኝ እንደሆነ ጠየኩት - በድጋሚም እጆቼን ለጸሎት አንድ ላይ አደረኳቸው፡፡ ግን ሰይጣን በጆሮዎቼ እየጮኸ ባለበት በዚያ ሰዓት ከእግዚአብሔር ጋር የማወራባትን ያችን ጸጥ ያለች ስፍራዬን ማግኘት አዳገተኝ፡፡

የርዕሰ-ብሔሩ ንግግር ከተሠራጨ በኋላ በመስኮት ድምፅ ሰማን፤ አንደኛውም የረጅም ጊዜ ጓደኛዬ የጎኔት ድምፅ ነው፡፡ በግቢው ውስጥ በመታጠቢያ ቤቱ ግድግዳ በሌላኛው በኩል ቆማ ስለኔ ታወራለች፡፡ «ኢማኪዩሌ?» አለች፡፡ «ገና ማንም አላገኛት፡፡ ጓደኛዬ ስትመስለኝ ውሽታም ኖራለች፡፡ የሌለ ደህንነት ይሰማኝ ዘንድ ስታታልለኝ እንደምትወደኝ ለማስመሰል ሞክራለች፡፡ አባቷ ቤተሰቤን ሊገድል ማቀዱን ታውቃለች... አግኝተው ቢገድሏት ምንም አይመስለኝም፡፡»

ወይኔ አምላኬ ከዚህ ቀጥሎስ ምን ይመጣ ይሆን? ስል ተጨነቅሁ፣ ተጠበብኩ፡፡ እንዴት ጓኔት እንዲህ ትላለች*? ለመጨረሻ ጊዜ ያየኋት እለት እንደተበሳጨች አውቄያለሁ፤ ግን የአባቷ ተጽዕኖና የጦርነቱ ጫና ሊሆን እንደሚችል ገብቶኛል፡፡ ቢሆንም ግን የረጅም ጊዜ ውድ ጓደኛዬ ኖርኩም ምትኩ ግድ እንደማይሰጣት ስትነግር ገረመኝ፡፡*

ጓኔት ስታወግዘኝ መስማቱ በጣም ብቸኝነት እንዲሰማኝ ስላደረገኝ ከአንድ ጓደኛ ጋር ማውራት አስፈለገኝ፡፡ ወደ ትምህርት ቤቱ ተመልሼ በጋራ መኝታ ቤቱ ከክሌሜንታይንና ከሳራ ጋር እንድሰቅና እጆቼን ይዘው እያረጋጉኝ ሰቆቃዎቼን እነርሱ ላይ ማራገፍን ተመኘሁ፡፡

ዲያቢሎስ ሃሳቤን እየሰማ ነው የሚያስብለኝ ነገር ቢኖር ዣኔት ጓደኝነቴን ስትክድ ከመስማቴ በቁሱ ሬድዮ አንድ ዘገባ ተከተለ - ይህ ዘገባ በምማርበት ዩኒቨርሲቲ ግቢ በመቶዎች የሚቆጠሩ ተማሪዎችን ሞት ያስታወቀው ነው፡፡ የሞታቸውም መንስኤ ግድያ ነው፡፡

‹‹በቡታሬ መሬቷን ኢጋይተናታል… ከ500 የሚበልጡ እባቦችንና ከሃዲ ሁቱ ጓደኞቻቸውን በዩኒቨርሲቲው ገድለናል›› ሲል አንባቢው ጉራውን ነዛ፡፡

አብዛኛዎቹ ከሁለተኛ ደረጃ ጀምሮ የቅርብ ጓደኞቼ የነበሩትን የዩኒቨርሲቲ ጓደኞቼን ሁሉ ሳስብ አመመኝ፡፡ በእርግጠኝነት ብዙዎቹ ለትንሣኤ በዓል በዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢ እንደቆዩ አውቃለሁ፡፡ አብሬያቸው የሣቅሁ፣ ያለቀስሁና የጸለይኩትን እነዚያን ሁሉ ሴቶች ልጆች አሰብኳቸው… ስናድግ እንጋራቸው የነበሩት ህልሞቻቸንን፡- በፍቅር መውደቅንና ቤተሰብ መመስረትን አስታወስኩ፡፡ በዕድሜ ዘመናችን በሙሉ ጓደኛሞች እንደምንሆን እርግጠኞች ነበርን - አሁን ሕይወታቸው አክትሞለታል፤ ወድመዋል፡፡ የሞቱት ግርፋት ደርሶባቸው እንዳይሆን ጸለይኩ፡፡ ከዚያም ለበዓል እቤት እንድመጣ የሚጠይቀው የአባቴ ቆንጆ ደብዳቤ ባይደርሰኝ ኖሮ ከእነርሱ ጋር እሆን እንደነበር አስታወስኩ፡፡

ልቤ ታመመ፡፡ የምወደውን ሁሉ አጥቼ ይሆን እንዴ? ዓይኖቼን ጨፍኜ አምላክ ከኔ ጋር መሆኑን የሚገልጽ ምልክት አንዲሰጠኝ ጸለይኩ፡፡ የቀረኝ ላምነው የምችለው እርሱ ብቻ ነው፡፡ በምልክት ፈንታ የድረሱልኝ ጥሪ ጩኸት ሰማሁ፡፡

‹‹ቁስ ሙሪንዚ እንኳን ኖሩልኝ! እባክዎን ይርዱኝ፡፡ እየመጡብኝ ነው… ሊገድሉኝ መጡ!››

የሴትዮዋን ድምፅ አውቄዋለሁ - ባለቤታቸው በ1973ቱ የግድያ ዘመቻ የተገደለባቸው አዛውንቷ እመት ሶኒ ናቸው፡፡ ከትምህርት ቤት መጥቼ ከሕዝብ ማጓጓዣ ተሸከርካሪ ስወርድ ፍራፍሬና ለወንድሞቼ ደግሞ ትንሽ ስጦታ ይዘው ሁልጊዜ ሰላም የሚሉኝ ደግ አዛውንት ናቸው፡፡ እንደ አያቴ ናቸው፤ ስለሆነም ተነሥቼ ከኛ ጋር እንዲደበቁ ልጠራቸው ፈለግሁ፡፡

ቁሱ ግን ‹‹ከዚህ ሂጂ፡፡ እኔ ቱትሲዎችን አልደብቅም፡፡ አዝናለሁ፡፡ እዚህ መግባት አትችዪም›› ሲሏቸው ሰማሁ፡፡

‹‹ማሩኝ ቁሱ እባክዎትን፡፡ እርስዎ የእግዚአብሔር ሰው ነዎት - እባክዎ ሕይወቴን ያትርፏት… ለማንም አልናገርም፡፡ ዝም እላለሁ፡፡ መሞት አልፈልግም ቁሱ፡፡ አሮጊት ነኝ፡፡ ማንንም የሚጎዳ ነገር ፈጽሜ አላውቅም፡፡››

‹‹የሀገሪቱ ጠላት ነሽ፣ አልሸሸግሽም፡፡ ስመ-ጥሩ ሁቱ ነኝ፤ በይ ሂጂልኝ፡፡›› ከዚያም የፊቱን በር ዘጉባቸው፡፡

በርቀት ገዳዮቹ የአደን መዝሙሮቻቸውን እየዘመሩ ወደ ቤቱ እየቀረቡ ሲመጡ እሰማቸዋለሁ፡፡ ምስኪን ሶኒ እንደገና መጮህ ጀመሩ፡፡ በአእምሮዬ ይታዩኛል፣ ብርክ ይዟቸው ምርኩዛቸውን እየተመረኮዙ በአንካሳ እግራቸው ሲያዘግሙ ገዳዮቹ ወዲያውኑ ነው የሚደርሱባቸው፡፡

ማልቀስ ፈለግሁ፤ ግን ምንም እንባ አልወጣኝም፡፡ ልቤ በተደጋጋሚ በተከሰተብኝ የሰቆቃ ውርጅብኝ ምክንያት ደድሯል፡፡ ስለ ቄሱም ምንም ንዴት አልተሰማኝም፡፡ ምናልባት ገዳዮቹ እመት ሶኒ ሲደርሱ በጣም ቅርብ ሆነው ሊሆን ስለሚችል ሂጂ ብሎ ከመመለስ በስተቀር ምንም አማራጭ አይኖራቸው ይሆናል፡፡

ዓይኖቼን ጨፍኜ አምላክን የሶኒን ደግ ነፍስ እንዲቀበልና በገነትም ለእርሳቸው ስፍራ እንዲተው ለመንኩት፡፡ ከዚያም በድጋሚ እኛን እየጠበቀን እንደሆነ የሚያሳየን ምልክት ይልክልን ዘንድ ጠየቅሁት፡፡

ቄሱ በሩን ከፍተው ቃል ሳይናገሩ ቀደም ብዬ የጠየኩትን መጽሐፍ-ቅዱስ ሰጡኝ፡፡

ወዲያውኑ ከፈትኩትና መዝሙር ፺ነ (፩-፯ን) አየሁ፡፡

> በልዑል መጠጊያ የሚኖር ሁሉን በሚችል አምላክ ጥላ ውስጥ ያድራል፡፡ እግዚአብሔርን፡- አንተ መታመኛዬ ነህ እለዋለሁ፤ አምላኬና መሸሸጊያዬ ነው፤ በእርሱም እታመናለሁ፡፡ እርሱ ከአዳኝ ወጥመድ ከሚያስደነግጥም ነገር ያድንሃልና፡፡ በላባዎቹ ይጋርድሃል፣ በክንፎቹም በታች ትተማመናለህ፤ እውነት እንደጋሻ ይከብሃል፡፡ ከሌሊት ግርማ፣ በቀን ከሚበር ፍላጻ፣ በጨለማ ከሚሄድ ክፉ ነገር፣ ከአደጋና ከቀትር ጋኔን አትፈራም፡፡ በአጠገብህ ሺህ በቀኝህም አሥር ሺህ ይወድቃሉ፤ ወደ አንተ ግን አይቀርብም፡፡

ምዕራፍ 13
የእጓለማውታ ስብስብ

ከአንድ ወር ጊዜ በላይ አለፈ፤ እኛም ሰማይን በድጋሚ አናይም ብለን አሰብን፡፡ ወደ ቁሱም ቤት ገዳዮቹ ለማንም አስቀድመው ሳይናገሩ በቀንም ሆነ በማታ ባስፈለጋቸው ሰዓት እንደፈለጉ ይመላለሳሉ፡፡ ጥቂት ደርዘኖች ወይንም ጥቂት መቶዎች ሊሆኑ ይችላሉ - በታዘዙበት ወቅት፣ ጥቆማ በደረሳቸው ጊዜ ወይንም ስራ ሲፈቱና አዲስ የሚገረፉ ወይንም የሚገደሉ ቱትሲዎችን ለማደን ሲፈልጉ ይመጣሉ፡፡ ሁልጊዜ ይመጣሉ፤ እስኪያገኙን ወይንም በጦርነቱ እስኪሸነፉ ድረስ መምጣታቸውን እንደሚቀጥሉ እናውቃለን፡፡

በቁሱ ሬድዮ የሚሰሙት አዳዲሶቹ ዘገባዎች ያሰቅቃሉ፡- የመንግሥት አመራሮች እያንዳንዷን የሩዋንዳ የሬድዮ ጣቢያ ስለ ግድያ ወደመወትወቻ መሣሪያነት ለውጠዋታል፡፡ የሬድዮ ጣቢያው ሰዎች በማናቸውም ስፍራ የሚገኙ ሁቱዎች ቱትሲዎችን ምንም ጥያቄ መጠየቅ ሳያስፈልጋቸው ባገኙበት አጋጣሚ መግደል ግዴታቸው እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ ሀገሪቱ እስከዚያን ሰዓት ድረስ ሙሉ በሙሉ ዝግ የነበረች ሲሆን፤ ይህም የሆነበት ምክንያት ግድያው እንዳይደናቀፍ ነው፡፡ አንዳንድ ገበሬዎች ሰብላቸው እየተበላሸባቸው እንደሆነ ሲያማርሩበት፤ አንድ የመንግሥት ባለሥልጣን በሬድዮ አንድ ሰው ሰብሉን ለመንከባከብ ከግድያው አንድ ቀን እንኳን ቢቀር ሲሠራ ራሱን የሚከላከልበት መሣሪያ መያዝ አለበት ብሎ አሳሰበ፡፡

«መዘናጋት የለባችሁም!» እነዚህ እባብ ቱትሲዎች በየሣርና ቁጥቋጦው ውስጥ ተደብቀዋል» አለ፡፡ «ስለሆነም እባቦቹን ከሁለት ለመቁረጥ ገጀራችሁን ይዛችሁ መዘጋጀታችሁን እርግጠኛ ሁኑ፡፡ ከተቻለ መሣሪያችሁን አንስታችሁ ተኩሳችሁ ግደሏቸው! ጠመንጃ ከሌላችሁ መንግሥት ይሰጣችኋል፡፡ ማሳችሁ ላይ እየሠራችሁ ሴት ቱትሲ በየጥሻው ልጇን ስታጠባ ካያችሁ ወርቃማ እድሉን እንዳታባክኑት - ጠመንጃችሁን አንሱ፣ ግደሏት፣ እናም ግዴታችሁን እንደተወጣችሁ አውቃችሁ ወደ ሥራችሁ ተመለሱ፡፡ ሕፃኑን መግደላችሁን ግን አትርሱ - የእባብ ልጅ መቼም ቢሆን እባብ ነው፤ ስለዚህ እርሱንም ግደሉት!»

የአካባቢው ባለስልጣናት በመንደሩ ነዳጅ ማደያ ገጀራ ሲያድሉ ታጣቂዎቹ በበኩላቸው ከበር በር እየሄዱ ጠመንጃና ቦምብ ይሰጣሉ፡፡ በእርግጥም ቄስ ሙሪንዚ አንድ ምሽት ምግብ ሊሰጡን ሲመጡ ጠመንጃቸውን በኩራት ትከሻቸው ላይ አንግተውታል፡፡ «አይዟችሁ፤ ልገድላችሁ አይደለም» አሉን ጠመንጃውን ከፊት ለፊታችው እያንቀራበጡ፡፡ «የተወሰኑ የመንግሥት ወታደሮች ዛሬ መጡና ይሄን ሰጡኝ፡፡ አልወስድም ብዬ ነበር፤ በዚያው ብጸናበት ግን ለዘብተኛ ሆንክ ብለው

ሊገድሉኝ ይችሉ ነበር፡፡» ጠመንጃውን በትከሻቸው ከማንገታቸው በፊት በእጃቸው እያገላበጡ «በጣም አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር አልጠቀመውም» በማለት ቃል ገቡ፡፡

በሩዋንዳ ያለ ማናቸውም ሁቱ ጠመንጃ ወይንም ገጀራ ያለው መስሏል፤ ይህ እንግዲህ በቱትሲዎች ላይ እንዲጠቀሙት ከሚያዝ መመሪያ ጋር የመጣ ነው - ማንም በዓለም ላይ ያለ ሰው ሃይ አላላቸውም፡፡ ከሬድዮ ዘገባዎች በምንሰማው እርዳታ እየመጣ እንዳልሆነ አውቀነዋል፤ እናም ሌሎች አገሮች በተለይ ሠለጠኑ የተባሉት ምዕራባውያን እንዴት ፊታቸውን ሊያዞሩብን እንደቻሉ ሊገባኝ አልቻለም፡፡ እየተጨፈጨፍን እንደሆነ ያውቃሉ፡፡ ነገር ግን ምንም አላደረጉልንም፡፡

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (የተመድ) እንኳን ሳይቀር ግድያው ከጀመረ በኋላ የሰላም አስከባሪ ሠራዊቱን አስወጥቷል፡፡ ይሁን እንጂ የተመድ ሰላም አስከባሪዎችን የሚያዙት ካናዳዊ ጄኔራል ሮሜዎ ዳሊየር ለቀው ይውጡ የሚለውን ትዕዛዝ አልቀበልም ብለው ከተወሰኑ መቶ ወታደሮች ጋር ቀርተዋል፡፡ ብርታትና ግብረ-ገብነት የነበራቸው ሰው ቢሆኑም ቅሉ በገዳዮች ባህር ውስጥ ብቻቸውን ቀርተዋል፡፡ በሬድዮ ሁልጊዜ ሊሰማቸው የሚችልን ማናቸውንም አካል ግድያውን ለማስቆም ወደ ሩዋንዳ ወታደሮች እንዲልክ ሲለምኑ እንሰማቸዋለን፤ ግን ማንም ከመጤፍ አልቆጠራቸው፡፡ የሀገራችን የቀድሞ ቅኝ ገዥ፣ ቤልጅዬም፣ ወታደሮቿን ከሀገሪቱ በማስወጣት የመጀመሪየዋ ሀገር ሆነች፤ በሌላ በኩል ዩናይትድ ስቴትስ የጅምላ ጭፍጨፋ እየተካሄደ መሆኑን እንኳን እውቅና አልሰጥም ብላለች! እነዚህ አካላት ሁሉም ቱትሲ ወንድ፣ ሴትና ሕጻን ሳይሞት ፖለቲከኞቻችን ግድያውን እንደማያቆሙ አያውቁም ማለት አይቻልም፡፡ ማንም ሰው ማንኛውንም ሬድዮ ጣቢያ በመከፈት ምን እንዳቀዱና እያደረጉ እንደሆነ መስማት ይችላል፡፡

አንዳንዴ ቁሱ በሬድዮ ዘገባዎች ያልተካተቱትን የመንግሥትን የዘር ፍጅት እቅዶች ይነግሩናል፡፡ «ሁሉም ቱትሲዎች ሲሞቱ ጭራሽ ያልነበሩ ለማስመሰል ታቅዷል፡፡ ማንኛውንም አሻራቸውን ያጠፋሉ» ሲሉ ምንም ሳይመስላቸው ነገሩን፡፡ «በከተማው የማውቃቸው የመንግሥት ባለስልጣናት ሁሉንም ቱትሲ ነክ መዛግብት እንዲያጠፉ ታዘዋል፡፡ አብዛኞቹን የትምህርት ቤትና የሥራ መዛግብት አቃጥለው ወደ ልደት፣ ጋብቻና ሞት ምስክር ወረቀቶች ተሸጋግረዋል፡፡ ያው በማንኛውም ከተማና መንደር ተመሳሳይ ነው - ትዕዛዙ አንድም የቱትሲ አሻራ በሩዋንዳ አፈር ላይ እንዳይቀር የሚል ነው» አሉን፡፡

የሰማነው ብቸኛው ጥሩ ዜና ስለ ጦርነቱ ብቻ ነው፡፡ የሁቱው መንግሥት በሩአግ ያሉትን ቱትሲ አማጽያን ወታደሮች ሁሉ እየገደለ እንደሆነ ማስታወቁን ቀጥሏል፡፡ በኋላ ግን ከቢቢሲና ሌሎች የውጪ የመገናኛ አውታሮች በአገሪቱ አንዳንድ ክፍሎች ሩአግ ጦርነቱን እያሸነፈ እንደሆነ ሰማን፡፡ አንዳንዴ የሩአጉ መሪ ፖል ካጋሜ ቱትሲዎችን «እንታደጋችኋለን» እያለ ተስፋ እንዳይቆርጡ ሲያበረታታ እንሰማዋለን፡፡

ምንም እንኳን አማጽያኑ የሚዋጉት ከማታባ ርቀው ኪጋሊ አካባቢና በሰሜን ጫፍ እንደሆነ ብናውቅም ካጋሜ ለኛ ጀግናችን ነው። የካጋሜ ቃላት የኛን ሁኔታ አልቀየሩትም፤ አንድ ቀን ግን የሁቱው መንግሥት ተገረስሶ ቱትሲ ወታደሮቹ ሊያተርፉን እንደሚችሉ ትንሽ ተስፋ አጭረውብናል።

ጦርነቱ እየገፋ በሄደ ቁጥር ቄሱ ምን እንደሚያደርጉን በጣም እየተጨነቁ መጡ። «ጦርነቱ ከእንግዲህ ብዙ ወራትን ከፈጀ እናንተን የምመግበው ምግብ አይኖረኝም። እናንተን እዚህ ማቆየት አልችልም» በማለት ቄሱ ስጋታቸውን ገለጹልን።

በትከሻቸው አንግተውት የነበሩትን ጠመንጃ አስታወስኩና ምግብ ሲያልቅባቸው ምን ሊያደርጉን እንዳቀዱ አሰቤ ተጨነቅሁ። እኛን ለማዳን ሕይወታቸውን ከሰጡ በኋላ ወደ ገዳይነት ይቀየራሉ ብዬ ለማመን አልችልም። ግን በእርግጠኝነት ከቤታቸው በደረቅ ውድቅት በዳማሲንና በቪያኒ ላይ እንዳደረጉት እንደማያስወጡን አውቃለሁ። አካባቢያችን በገዳዮች የተሞላ እንደሆነና ከመታጠቢያ ቤቱም ከወጣን አንድ ሰዓትም መቆየት እንደማንችል ይታወቃል።

ቄሱ በመጨረሻም የእግዚአብሔር እርዳታ እንደሚያስፈልጋቸው መወሰናቸው ብዙ እንዳሰቡበት ያሳያል። አንድ ምሽት የመንግሥት ወታደሮችን እግዚአብሔር ያግዛቸው ዘንድ እንድንጸልይ ጠየቁን። አየናቸው .... ምን ያህል ስሜት-አልባ እንደሆኑ ለማመን አልተቻለኝም።

ይሁን እንጂ በተጨናነቀ ስፍራ ውስጥ ስለሆንን ሌላ ምን ማድረግ እንችላለን? እጆቻችንን አያይዘን የምንጸልይ አስመሰልን። በእርግጥ የጸለይኩላቸው በሺዎች ለሚቆጠሩ በግፍ ለተገደሉ ቱትሲዎች ነው። ከዚያም ገዳዮቹ ወደ አምላክ ቀርበው በፍቅሩ እንዲቀየሩ ጸለይኩ - *አማዚአብሔር ሆይ በመለኮታዊ ፍቅርህ ንካቸው። ያኔ ብቻ ገጀራቸውን ጥለው በጉልበታቸው ይወድቃሉ። አባክህ አማዚአብሔር ግድየቸውን እንዲያቆሙ አድርጋቸው። ማራቸው።*

ቄሱም በኛ ላይ በጣም እንዳይጨክኑብን ጸለይኩ፤ ልባቸው እኛን ሲያዩ እንዳይከፋብን፤ የሰው ልጆችም እንደሆንን እንዲያስታውሱ።

ከእርሳቸው ጋር መጸለያችንን እንደጨረስን ቄስ ሙሪንዚ ጦርነቱ ሲያልቅ እኛን ምን ሊያደርጉን እንዳሰቡ በመንገር አስደነገጡን። «ግድያው ሲያልቅ በሩዋንዳ ምንም የሚቀሩ ቱትሲዎች ስለማይኖሩ እናንተን ማንም ሳያየኝ እልካችኋለሁ። እናም የሆነ ማንም የማያውቃችሁ ስፍራ መሄድ ይኖርባችኋል - ማንም እኔ በጦርነቱ ጊዜ እንደሸሸግኋችሁ የማያውቅበት ስፍራ።

እንዳሉን ከሆነ ለአባሺ ጎሳ አባላት ሚስቶች እንድንሆን ኪቩ ሐይቅ መካከል ላይ አሁን ካለንበት ስፍራ 80 ኪሎሜትር ርቃ ወደምትገኝ ደሴት ሊልኩን አስበዋል፡፡

ባለማመን እርስ በርሳችን ተያየን፡፡ አባሺዎች ኋላቀር ሲሆኑ የሚኖሩትም በጫካው ውስጥ በጭራሽ ከውጪው ዓለም ጋር ምንም ግንኙነት ሳያደርጉ ነው፡፡ ምንም ትምህርት ቤቶች፣ አብያተ-ክርስቲያናት ወይንም ቋሚ ሥራ አልነበራቸውም፤ ከአንበሳ ቆዳ በስተቀር ምንም ዓይነት ልብስ የማይለብሱ ሲሆን የሚበሉትም በደኑ ውስጥ ያደኑትን ወይንም የለቃቀሙትን ነው፡፡ ሩዋንዳውያን ወላጆች ልጆቻቸው ሲያጠፉ የሚያስፈራሩት ከአባሺዎች ጋር እንድትኖሩ እናባርራችኋለን በማለት ነው - ከጭራቆች ጋር እንዲኖር ሰውን የማባረር ያህል ነው፡፡ ለአንዲት ሩዋንዳዊት ሴት ልትነግሯት የምትችሉት እጅግ መጥፎው ነገር አባሺ እንደምታገባ ነው፡፡

«ምን ይቀራችኋል? የምንወያየው ነገር የለንም» በማለት በጨርሻለሁ ስሜት ቁሱ ተናገሩና ስለ ዕጣ-ፈንታችን እኛው እንድንጨነቅ ተዉን፡፡

ቁሱ ስለኛ እያሰቡ ያሉበትን መንገድ ጠላሁት፡፡ ሆኖም ግን አስተሳሰባቸው ይገባኛል፡፡ ሁቱ ጽንፈኞቹ የጀመሩትን ከጨረሱ እኛ በሩዋንዳ ብቸኞቹ በሕይወት የምንቆይ ቱትሲዎች ልንሆን እንችላለን - በጠላት ሀገር እጓለማውታ እንሆናለን፡፡

ወላጅ አልባነት አልተሰማኝም፡፡ ለሳምንታት ያህል ያለማቋረጥ ስለጸለይኩ ከእግዚአብሔር ጋር የነበረኝ ግንኙነት ይቻላል ብዬ አስበው ከነበረው በላይ ጥልቅ ሆነ፡፡ ዓለም አይታ ከምታውቃቸው ሁሉ በላይ የደጉና ኃይለኛው ንጉሥ ልጅ እንደሆንኩ ተሰማኝ፡፡ በየቀኑ ወደዚያች በልቤ ወዳለች ልዩ ቦታ ከአምላኬ ጋር ለመነጋገር እየሄድኩ ስሸሽግ ሐሳቦቼን ሁሉ ለእግዚአብሔር እነግረዋለሁ፡፡ ያች ቦታ ልቤ ከቅዱስ መንፈሱ ጋር የሚነጋገርባትና የእርሱ መንፈስም ከእኔ ልብ ጋር የሚገናኝባት ትንሽ የጎነት ናሙና ነች ብዬ አሰብኩ፡፡ በእርሱ መንፈስ ስኖር ፈጽሞ እንደማይተወኝ፣ ብቻዬን እንደማልሆን እናም በፍጹም እንደማልጎዳ አረጋገጠልኝ፡፡

ድንጋይ ሆኜ በቆሻሻው ወለል ላይ ለሰዓታት ተቀመጥኩ፡፡ የእርሱን ሁለንተናዊ ንጽህና ሳሰላስል የፍቅሩ ኃይል ነፍሴን እያጸዳትና አእምሮዬን እያባበለው እንደ ቅዱስ ወንዝ በውስጤ ይሰራጫል፡፡ አንዳንዴ በፈጣሪ ኃይለኛ መዳፍ ተይዤ በአፍቃሪ እጆቹ ውስጥ በደህንነት ጉብቼ ከሰውነቴ በላይ እየተንሳፈፍኩ እንደሆነ ይሰማኛል፡፡ በአእምሮዬ ከዚያን ጊዜ በፊት ሰምቼ በማላውቀው እንግዳ ቋንቋ ስናገር ራሴን ሰማሁት - በደ-መነፍስ የእግዚአብሔርን ታላቅነትና ፍቅር እያወደስኩ እንደሆነ ገባኝ፡፡

በምነቃባቸውም ጊዜያት ሁሉ በየቀኑ ከ15 እስከ 20 ለሚሆኑ ሰዓታት ያክል በጸሎትና በተመስጦ ያለማቋረጥ ከፈጣሪ ጋር እገናኛለሁ፡፡ በምተኛባቸው ጥቂት ሰዓታት እንኳን ለተወሰኑ ሰዓታት ኢየሱስንና ድንግል ማርያምን አስባለሁ፡፡

በጭፍጨፋው መካከል ድኅነቴን አገኘሁ፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር የነበረኝ ትስስር መታጠቢያ ቤቱን፣ ጦርነቱን እናም ጭፍጨፋውን እንደሚሻገር ይታወቀኛል፡፡ ምድራዊ ሕይወትን ሳይቀር የሚሻገር ትስስር እንደተፈጠረ ገባኝ፡፡

ልቤን ለጌታ ከፈትኩት፤ እርሱም በፍቅሩና በምህረቱ ሞላው፡፡ በዚያ መታጠቢያ ቤት መሆኔ አስከመጨረሻው የማመሰግንበት በረከት ሆነ፡፡ ወላጆቼ ሳይቀሩ በጅምላ ጭፍጨፋው ውጪ ላይ ጠፍተው የሚገኙበት ሁኔታ ቢኖርም በምንም ዓይነት ወላጅ-አልባ አልሆንም፡፡ በመታጠቢያ ቤቱ እንደገና ተወልጄ የአባቴ የእግዚአብሔር ውድ ልጅ ሆኛለሁና፡፡

እኛ እዚህ ቤት ስንደርስ ከቄስ ሙሪንዚ ኢሥሩ ልጆች ለችም የተባለው ትንሹ ወንዱ ልጃቸውና ሴት ልጃቸው ዱዜንጄ ከእርሳቸው ጋር እየኖሩ ነበር፡፡ ጦርነቱ ሲፋፋም ግን ሌሎቹ ልጆቻቸው ወደ ቤት ተመለሱ፣ ስለሆነም ቤቱ ይሞላ ጀመር፡፡ ቄሱ እኛን ብቻቸውን መከታተል እየቸገራቸው ስለመጣም ለአምስት ሳምንታት ገደማ የእኛን መኖር በጥንቃቄ ከያዙት በኋላ በዚህች ዓለም በጣም ለሚያምኗቸው ሁለት ሰዎች ለልጆቻቸው ለለችምና ለዱዜንጄ በመናገር ተገላገሉ፡፡

ለችም የላቀ ልብ የነበረው ሰው ሲሆን ዱዜንጄ በበኩሏ የረጅም ጊዜ ጥሩ ጓደኛዬና ደግ ልጅ ነች፡፡ ብዙ ጊዜ ሲናገሩ እሰማቸው እንደነበረው በቱትሲዎች ላይ እየተከሰተ ባለው ነገር ተሳቀዋል፡፡

ቄሱ ልጆቻቸውን እኛን እንዲያዩን ሊያመጧቸው እንደሆነ ነገሩን፤ በሩን ሲከፍቱት በልጆቻቸው ላይ ያየሁት ነገር ሐዘኔታና መቆርቆርን ነው፡፡ ዱዜንጄ በደግነት ሰላም ስትለኝ ለችም ደግሞ እጆቼን በእጆቹ ጥብቅ አድርጎ ያዘ፡፡ «አይ ኢማኪዩሌ» ሲል አንሾካሽከና በጸጥታ ተዋጠ፡፡ መጨረሻ የተያየነው በተደበኩባት ቀን ሲሆን በመታጠቢያ ቤቷ አሁን ከመገናኘታችን በፊት የተከሰተውን ለመግለጽ ቃላት ልናገኝ አልቻልንም፡፡ እጄን ጨበጥ እያደረገ «አንቺ እዚህ በመደበቅሽ በጣም ደስ ይለኛል፡፡ የኔ ቤተሰብ ላንቺ አንድ ነገር ማድረግ በመቻሉ ጌታ ይመስገን፡፡ በደኅና እንይዝሻለን፡፡»

ያሳየኝ ደግነት ከዓመታት በፊት የነበረውን የንጹሕ ግንኙነታችንን በጎ ትውስታዎች አጫረብኝ፡፡ አምላክ ምክንያት-የለሽ ኣጋጣሚዎችን እንዳልፈጠረ አየሁ - ለችምንና እኔን ከዓመታት በፊት ስላገናኘን አሁን በእርሱ ቤት ለመደበቅ በቃሁ፡፡

ምንም እንኳን ስለቤተሰቤ ወሬ ባይነግሩኝም ሆነ የወንድ ጓደኛዬን የዮሃንስን መገኛ ባያውቁም የበፊት ጓደኞቼን ማግኘቱን ወደድኩት፡፡ (በሀገሪቱ የስልክ መስመሮቹ ከጦርነቱ መጀመሪያ ጀምሮ ስለጠፉ መገናኘት አስቸግሯል፡፡) ለችምና ዱዜንጄ ለመታጠቢያ ቤቱ ድምቀት ሰጡት፤ አንዳንዴም አንዳንድ ስኒ ሻይ ያቃምሱናል፡፡ በወቅቱ የማይታሰብ ድንቅ መጠጥ!

ቄስ ሙሪንዚ እኛን ወደ ወላጅ አልባነት ቢያወርዱንም ቅሉ ትንንሾቹ ልጆቻቸው እኛን ወላጅ አልባዎቹን በአሳዳጊነት ተቀበሉን፡፡

በግንቦት ወር አጋማሽ አንድ ምሽት ላይ የመታጠቢያ ቤቱ በር በድንገት ብርግድ ብሎ ተከፈተ፡፡ ወዲያውኑም ሁለት ወጣት የኢንተርሃምዌ ገዳዮች እላያችን ላይ ዘፍ አሉብን፡፡ ስቅጥጥ አድርጎን በማናቸውም አፍታ ገጀራ ሲሰነዘር እንጠብቅ ያዝን፤ ግን ከዚያ በኋላ አርፈን እንድንቀመጥ የሚያዘውንና እንዳንጨነቅ የሚጠይቀውን የቄሱን የሹክሹክታ ድምፅ ሰማን፡፡ ከአፍታ በኋላም እነዚያ ሰዎች በፍጹም ገዳዮች እንዳልሆኑ ገባን፤ ተስፋ የቆረጡና የድብቅ የእህቶች ማኅበራችንን ለመቀላቀል የመጡ ናቸው፡፡

ሁለት ሌሎች በሕይወት የተረፉና የሚተነፍሱ ቱትሲዎችን በማየታችን ደስ አለን፤ መቀመጫ ስፍራ ግን ልናገኝላቸው አልቻልንም፡፡ ቄሱ ልጆቹን ወደ ክፍሉ ሲጨምሯቸው እኛ ላይ ወደቁብን፡፡ «ምንም ድምፅ እንዳታሰሙ» በማለት አስታወሱንና በሩን ዘጉት፡፡ በመስኮት በሚገባው ደብዛዛ ብርሃን የሴቶቹን ፊቶች ያሳያል፡፡ በምልክት ቋንቋችን ለማውራት ብንሞክርም ልጆቹ በእርግጥ ምን እያልን እንደሆነ አልገባቸውም፡፡ ለጥቂት ደቂቃዎች ትንሽ ድምጻችን የሚሰማበት ቃለምልልስ አድርገን ከየት አንደመጡና በውጪው ዓለም ምን እየተከሰተ እንደሆነ ለማወቅ ቻልን፡፡

ስሞቻቸው ማላባና ሶላንዥ ይባላል - ማላባ የኔ እኩያ የምትሆን ስትሆን በልጅነቱ የተወሰኑ ጊዜያት አይቻት የነበረ ቢሆንም በደንብ አላውቃትም፡፡ ሶላንዥ ከዚያን ጊዜ በፊት አግኝቻት የማላውቅ በአሥራዎቹ ዕድሜ ውስጥ የምትገኝ ልጅ ነች፡፡ እኛ ሳናውቅ ከቄሱ ትልቅ ልጆች አንደኛዋ፣ ማሪያኔ፣ ሁለቱን ሴቶች ልጆች በሰሜን ሩዋንዳ በሚገኘው መኖሪያ ቤቷ ጭፍጨፋው ከጀመረበት ጊዜ ጀምራ ደብቃቸው ኖሯል፡፡ ከአማጽያኑ ጋር የሚካሄደው የእርስ በርስ ጦርነት በሰሜኑ ከፍል በጣም ስለሚያይል እዚያ የሁቱ ጽንፈኞቹ በማናቸውም ቦታ የቱትሲ ሰላዮችን ይፈልጋሉ፡፡ ማሪያኔ የደግነትና የአዛኝነት ስም ስላላት በጽንፈኞች ዘንድ ተጠረጠረች፡፡ ቤቷ ብዙ ጊዜ ተፈትሿል፤ ማላባና ሶላንዥም በማናቸውም ጊዜ ሊገኙ ይችሉ ነበር፡፡

ማሪያኔ ለማላባ የሐሰት መታወቂያ ካርድ ለማግኘትና ሁለቱንም ልጆች ገዳዮቹ የሚለብሷቸውን መሰል ልብሶች ለማልበስ ችላለች፡፡ ኢንተርሃምዌዎች ቱትሲዎችን

እንድትገድልባቸው የሰጧትን ገጀራዎች፣ ጠመንጃዎችና የእጅ ቦንቦች ተሸከርካሪዋ ውስጥ አድርጋ ሴቶቹን ልጆች ከመሣሪያዎቹ ጎን አስቀመጠቻቸው። ከዚያም ውጊያው በአካባቢያቸው ዳር እስከ ዳር ሲፋፋም ረጅሙንና አስቸጋሪውን ጉዞ ሁላቸውም ሰላም ያገኛሉ ብላ ወዳሰበችበት ያባቷ ቤት ወደሚገኝበት ወደ ደቡብ ይጀምራሉ።

በየጥቂት ኪሎሜትሮቹ የኢንተርሃምዌ ገዳዮች በየኬላው ላይ እንደሚያስቆሟቸውና መታወቂያ ደብተራቸውን እንዲያሳዩ እንደሚጠይቋቸው ማላባና ሶላንዥ ነግረውናል። ሶላንዥ መታወቂያ ስላልነበራት በየኬላው እንገደላለን ብለው ያስባሉ። መታወቂያ አለመያዝ የሞት ፍርድ እንደሚያስከትለው የቱትሲ መታወቂያ አንደመያዝ ይቆጠራል።

«አንድ ሰው የቱትሲ መታወቂያውን ሲሰጣቸው እፊታችን ራሱን ከታተፋት» ሶላንዥ ራሷን እያወዛወዘችና በዓይኗ በብረቱ ያየችውን ነገር ማመን እያቃታት በተዘጋ ድምጿ አንሾካሾከችልን።

«መታወቂያ ካርዶቻቸውን እቢታቸው የረሱ ሁቱዎችን ሳይቀር ገድለዋል» አለች ማላባ። «የገደሉትን አንደኛውን ሰውዬ ለይቼዋለሁ - ሁቱ መሆኑን አውቃለሁ፤ እነርሱ ግን አያውቁትም። ከእነርሱ ትንሽ በቁመት በለጥ ይላል... ያ በቂያቸው ነበር። የቱትሲ ሰላይ ነህ ብለው ገደሉት። ሌላውን ሁቱ ደግሞ ስለተከራከራቸው ብቻ ገደሉት... የተናገረው ብቸኛ ነገር ቢኖር ቱትሲዎችን መግደላቸው ስህተት መሆኑን ነው።»

መንገዳቸውን ከመጀመራቸው በፊት ማሪያኔ ለሴቶቹ ልጆች መዳን ከፈለጉ ገዳይ መስለው እንዲንቀሳቀሱ ትነግራቸዋለች። በኬላ ላይ እንዲቆሙ በሚደረግ ጊዜ ሁሉ ገጀራቸውን ወይንም ጠመንጃቸውን አንስተው በአየር ላይ ያወዛውዛሉ።

«የምንጮኸው እንደ እብድ ነበር» አለች ሶላንዥ። « ‹የሁቱ የበላይነት! የሁቱ የበላይነት! ሁሉንም በረሮዎች ግደሏቸው እነዚያን ውሻ ቱትሲዎች ግደሏቸው!› ገዳዮቹ እንደዚያ ስንሆን ማየቱን ወደውታል - ጥሩውን ሥራ እንድንቀጥልበት እየነገሩን እጃቸውን ያውለበልቡልናል። ቱትሲዎችን መግደል መፈለግ የይለፍ ወረቀት እንደመያዝ ይቆጠራል ... አገሪቱ አብዳለች። ከነዚያ ሰዎች ብዙዎቹ ሰክረዋል፤ ማሪዋናም ወስደዋል። በእርግጥ ወታደሮቹ በወታደራዊ ተሸከርካሪዎች ተሳፍረው መጥተው ሁለት ኬላዎች ላይ አደንዛዥ እጽና አልኮል መጠጥ ለገዳዮቹ ሲሰጡ አይተናል።»

እህትማማቾቹ ወደ ደቡብ እጅግ በርካታ አስከሬኖችን እያለፉ እንደመጡና እያዩ የነበረው አስከሬኖችን መሆኑን ለማወቅ ረጅም ጊዜ እንደፈጀባቸው ነግረውናል። «አስከሬኖቹ በጣም ብዙ ስለነበሩና ስለተከመሩ የአሮጌ ልብሶችና የቆሻሻ ክምር

እያለፍን ነበር የመሰለን፡፡ ጠጋ ብለን ስናይ ግን .... ቀረ...ብ ብለን የመስኮቱን መስተዋት ዝቅ አድርገን ስናስተውል ግን ምንነታቸውን አወቅነው፡፡ የተሸከርካሪው ድምፅም ኖሮ እንኳን እንኳን የዝንቡን ጩኸት ትሰሙታላችሁ፡፡ አስከሬኖቹን የሚበሉ በመቶዎች የሚቆጠሩ ዉሾችም በሰዉ በድን የአካል ክፍሎች ላይ ይራኮታሉ፡፡ የሚያሳምም ነበር፡፡ ሀገሪቷ በሙሉ የበሰበሰ ስጋ ይሸትባታል» አለች ሶላንዥ፡፡ ፊቷ ቀልቷል፤ ስትናገርም ያንቀጠቅጣታል፡፡ «እነዚያን ምስሎች ከራሴ ውስጥ ማውጣት አልችልም... ዓይኖቼን ስጨፍንም ቢሆን የማየው አስከሬኖች ብቻ ነው፡፡»

በራዲዮና ከቁሱ ተመሳሳይ አሰቃቂ ወሬዎችን ባንሰማ ኖሮ እነዚህ ሴቶች የሚሉትን ነገር ለማመን እንቸገር ነበር፡፡ የዓለም ፍጻሜ ደርሶ ከሩዋንዳ የተጀመረ ይመስላል፡፡

ስለኛ ቤተሰቦች የሚያውቁት ነገር ይኖር እንደሆነ ብንጠይቃቸውም የራሳቸውም እንኳን የት እንዳሉ አያውቁም፡፡ ግድያው ሲጀምር ልጆቹ የማላባን አያት እመት ማሪያኔን (ከደበቀቻቸው ልጅ ጋር የስም ሞክሼ መሆኑ ነው) ለመጠየቅ ሄደው ነበር፡፡ ማላባ በኛ ጭኖች ላይ አቀማመጧን እያስተካካለች ታለቅሳለች፡፡ «ማሪያኔ ባታስገባን ኖሮ እኮ ይሄኔ ከነዚያ የሬሳ ክምሮች ባንዳቸው ተጥለን በዉሻ እየተበላን ነበር፡፡»

የሚናገሩትን ማሰቡ አንቀጠቀጠኝ፡፡ እንደሰሞኑ ሁሉ ወላጆቼና ወንድሞቼ የት ሊሆኑ እንደሚችሉ ተጨንቄ እግዚአብሔርን እንዲጠብቃቸው ለመንኩት፡፡ የማዋይህ ብቸኛው ቤተሰቤ አንተው ነህ አምላኬ፡፡ ሌሎቹን እንድትጠብቅልኝ ባንተ ላይ ነው የምተማማነው፡፡

በዚያን ምሽት መታጠቢያ ቤቱ ከምንጊዜውም በላይ ተጨናነቀ፡፡ ቆንጆዋን የሰባት ዓመት ልጅ ሳንዳን እንቅልፍ ይዟት በጭኔ ላይ እንደታቀፍኳት በዚያች ትንሽ ክፍል ውስጥ ያለን እያንዳንዳችን ከቤተሰቦቻችን እንዴት እንደተለያየን ወይንም ቤተሰቦቻችን ከኛ እንዴት እንደተለዩ አሰብኩ፡፡ የሳንዳን ጸጉር እየነካካሁ የኔም እናት ትታቀፈኝ ዘንድ እዚያ ብትኖርልኝ ብዬ ተመኘሁ፡፡

ከንጋት ትንሽ ቀደም ብሎ ለአፍታ አሸለብኩና በሕይወቴ በጣም ጥልቁን ሕልም አለምኩ፡፡ ኢየሱስን እጆቹን ወደፊት ዘርግቶ ሊያቅፈኝ እንደሆነ ሁሉ ከፊት ለፊቴ ቆሞ አየሁት፡፡ ወገቡ ላይ የታሰረ እራፊ ጨርቅ ለብሷል፣ ረጅም ጸጉሩም በትከሻው ቁልቁል ዝቅ ብሎ ወርዷል፡፡ እንዴት እንደከሳ በማየቴ በጣም መደንገጤን አስታውሳለሁ፡፡ የጎድን አጥንቶቹ ወጥተዋል፤ ጉንጮቹም ጎድጉደዋል፡፡ እኔን ሲያየኝ ግን ዓይኖቹ እንደ ከዋክብት የሚያንጸባርቁ፤ ድምጹም ሸው እንደሚል ንፋስ ዝግ ያለ ነው፡፡

«ይህን ከፍል ለቀሽ ስትሄጂ ሁሉም የምታውቂውና የምትወጂው ሰው እንደሞተና እንደማይመለስ ታውቂዋለሽ» አለኝ፡፡ «እንዳትፈሪ ልነግርሽ ነው የመጣሁት፡፡ ብቻሽን አትሆኚም - አብሬሽ እሆናለሁ፡፡ እኔ ቤተሰብሽ እሆናለሁ፡፡ ተረጋጊ፤ ሁሌም ካንቺ ጋር ስለምሆን እመኚብኝ፡፡ ለቤተሰብሽ ብዙ አታልቅሺ፣ ኢማኪዩሌ፡፡ እነርሱ እኔ ጋ በፍሥሐ እየኖሩ ነው፡፡»

ቀለል ብሎኝና ተደስቼ ከእንቅልፌ ተነሣሁ፡፡ ስለ ኢየሱስ ማለም መታደል ነው፡፡ ሰለሆነም በጋለው ስሜቴ ተደሰትኩ፤ እግዚአብሔርንም እነዚህን ድንቅ ሐሳቦች ስለላከልኝ አመሰገንኩት፡፡ ቀኑ እየገፋ ሲሄድ ግን ልቤ ዋተተ፡፡ ኢየሱስ የቤተሰብሽ አባላት በሙሉ ሞተዋል ብሎኛል… እናም ላይሆንልኝ ይኖሩ ዘንድ ተመኘሁ፡፡ ወላጆቼን ማየትን፣ ለቪያኒም በዚያን ምሽት እንዲሄድ በማድረጌ እንዳዘንኩ መንገርን ፈለግሁ፡፡ ከዚያ የዳማሲንን ፈገግታ በፊቱ ሲንሠራፋ ማየትን ተመኘሁ፡፡ ያን ያህል ጻልዬ አምላክ ለምንድነው ሕይወታቸውን የማያተርፈው?

ዓይኖቼን ጨፍኜ ራሴን አረጋጋሁ፤ የታየኝ እንደወትሮው ያለ ሕልም ከሆነ ቤተሰቤ በሕይወትና በደኅና እየኖረ ሊሆን ይችላል… ሕልምም ካልነበረ አምላክ እኔን ሁልጊዜ ሊንከባከበኝ ቃል ገብቶልኛል፤ መቼም አምላክ ቃሉን ሲያጥፍ አላውቀውም፡፡

ከዚያ ሕልም ብዙም ሳይቆይ ሰዎች ከመታጠቢያ ቤቱ መስኮት ውጪ በቅርቡ ስላዩዋቸው ግድያዎች ሲያወሩ ሰማሁ፡፡ አንደኛው ጦርነቱ ከጀመረ ጀምሮ ተደብቆ ስለነበረ ወጣት መያዝ ማውራትን መርጧል - «ይህ ልጅ የማስተርስ ዲግሪ ነበረው፤ ጎዳዮቹም በዚያ አሾፉበት፡፡ ያን ያህል አዋቂ ከሆነ ለምን እጃቸው እንደገባ ጠየቁት፡፡ አንደኛው እንዲያውም ማስተርስ ዲግሪ ያለውን ሰው አንጎል ማየት እንደሚፈልግ ተናግሮ የልጁን ራስ በገጀራ ከሁለት ከፈለው፡፡ ከዚያም የራስ ቅሉን ውስጠኛ ክፍል አየ፡፡»

ልቤ ወከክ አለች፡፡ በስፍራው የማስተርስ ዲግሪ የነበራቸው ወጣቶች ያን ያህል አልነበሩም… የሚያወሩት ስለ ወንድሜ ስለ ዳማሲን መሆኑን እርግጠኛ ነኝ፡፡

ወይ አምላኬ እባክህ እርሱ አይሁን ስል ጸለይኩ፡፡ የሚያወሩት ስለ ወንድሜ መሆኑን እርግጠኛ መሆን አልችልም ብዬ ራሴን ለማረጋጋት ሞከርኩ፡፡ የኔ ወንድም እንዳይሆን ስል መጸለዬን ቀጠልኩ፤ እናም ቄስ ሙሪንዚ ምግባችንን ይዘው እስኪመጡ እጠብቅ ጀመር፡፡ ከሰዓታት በኋላ በሩን ሲከፍቱት የሰማሁትን ነገርኳቸው፤ እናም በቀጥታ ሰዎቹ ያወሩት ስለ ዳማሲን ግድያ እንደሆነ ጠየኳቸው፡፡

በጥያቄዬ ያልጠበቁትን ዱብዳ ሳወርድባቸው ዓይኖቻቸው ዓይናቼን ለማየት እንደማይችሉ አየሁ፡፡ «አይ፣ በፍጹም፣ በጭራሽ» አሉ፡፡ «ብዙ ወጣቶችን እየገደሉ ስለሆነ ያንችን ወንድም ማለታቸው ነው የሚያስብል ምንም ምክንያት አይኖርም፡፡ ስለማናቸውም ወንድሞችሽ ምንም የሰማሁት ነገር የለም የኔ ልጅ፡፡»

ኣይ መምሬ! የተሻሉ ዋሾ ቢሆኑ ምንኛ ደግ ነበር ስል አሰብኩ! በፊታቸው ላይ ይታይ የነበረው ገጽታ ዳማሲን እንደሞተ ነገረኝ… ግን እንዴት እርግጠኛ ልሆን እችላለሁ? ከንፈሬን ነክሼ መረጃ ስለሚያቀብሉንና እየተከላከሉን ስለሆነ አመሰገንኳቸው፡፡ ራሳቸውን ነቅንቀው በፍጥነት ከፍሉን ለቀው ሄዱ፡፡

ሌሎቹ ሴቶች ወንድሜ ደኅና እንደሆነና ሰዎቹ እያወሩለት የነበረው ሰው ማን እንደሆነ የሚታወቅበት ምንም ዓይነት መንገድ እንዳልነበረ በመግለጽ እንዳልጨነቅ ወተወቱኝ፡፡ ትንሽ ፈገግ አልኩና በሃሳባቸው የተስማማሁ መሰልኩ፡፡ ለማናቸውም መልከ መልካሙ ወንድሜ ዳማሲን በሕይወት ሊኖር የሚችልበት ጥሩ ዕድል አለ፡፡ ደስ የሚለውን ፊቱን ደግሜ ላየው እችላለሁ፤ በአስቂኝ ቀልዶቹም እሥቃለሁ ብዬ አሰብኩ፡፡

ልቤ ግን ራሴን ልታዳምጠው አልቻለችም፡፡ መጀመሪያ ቀስ ብዬ አለቅስ ጀመር፤ በኋላ ግን መጽናናት አቅቶኝ ማንባት ጀመርኩ፡፡ ሕመሙ ሃሳቤን ያቋርጥልኝና እንባዬን ያቆምልኛል ብዬ በማሰብ ፊቴን እመታና ሁለመናዬን በጣም እቆነጥጥ ጀመር ፡፡ ግን ምንም አልበጀኝ፡፡ ሌሎቹ ሴቶች ውጪ ያሉ ሰዎች እንዳያደምጡኝ ፈርተው እንደተሸበሩ ባውቅም ድርጊቴን ምንም ላቆም አልቻልኩም፡፡ ለቅሶዬን ለማፈን እጄን እየነከስኩ ቢሆንም እንባዬ ግን ፊቴን ማጠቡን አላቆመም፤ መንሰቅሰቁም እየጨመረ መጣ፡፡ ነገሩን ያባባሰው ደግሞ ትንንሾቹ ልጆችም ማልቀስ መጀመራቸው ነው፡፡ ማልቀሴን አንድተው ትልልቆቹ ሴቶች ድምፅ ሳያሰሙ እጆቻቸውን ያወናጭፉ ጀመር፡፡

ከአንድ ሰዓት በኋላ ማልቀሴን አቆምኩ፡፡ በመታጠቢያ ቤቱ ከዚያ በኋላ አልቅሼ አላውቅም፡፡

ምዕራፍ 14
በልሳን ሲያናግረኝ

በመታጠቢያ ቤቱ ሰባት ሳምንታት መቆየታችን ሁላችንንም በሚያስደነግጥ ሁኔታ አከስቶናል — አጥንቶቻችን ገጠው ወጥተዋል፤ ቆዳችንም አሸበሸበ። በሰውነታችን ውስጥ የነበረው ስብና ጡንቻዎቻችን ጠፍተው፣ መቀመጫችንም አጥንቱ ብቻ ስለቀረ በጠጣሩ ወለል ላይ መቀመጡ አልስማማ ይለን ጀመር። ሁለት ሴቶች ቢጨመሩብንም መታጠቢያ ቤቱ ግን ከቀን ወደ ቀን እየሰፋ ሄደ። መነመንን፤ ተቆጥቦ የሚሰጠን ምግብም ብዙውን ጊዜ ያደካክመንና ራሳችንንም ያዞረን ገባ። በልብሶቼ መስፋት ቢያንስ 17 ኪሎግራም እንደቀነስኩ መናገር እችላለሁ (መጀመሪያ ላይ ወደ 50 ኪሎግራም እመዝን ነበር)።

ቆዳችን ቀልቶ፣ ከንፈሮቻችን ተሰነጣጥቀው፣ ድዶቻችንም አባብጠውና ቆሳስለው እጅግ ተጎድተናል። በዚያ ላይ ከደረስንበት ጊዜ ጀምሮ ታጥበንም ሆነ ልብስ ቀይረን ስለማናውቅ በአሰቃቂ የተባይ ወረራ ተቸገርን። አንዳንዴ ትናንሾቹ ተባዮች ደማችንን መጠው ስለሚያብጡ በፊታችን ላይ ሲንፈላሰሱ እናያቸዋለን።

ሲያዩን የምናማልል ላንሆን እንችላለን። ግን ከዚያ በላይ ቆንጆነት ተሰምቶኝ አያውቅም። በየቀኑ እነሳና እግዚአብሔርን ሕይወትን ስለሰጠኝ አመሰግነዋለሁ። አምላኬም በየጠዋቱ እንደምወደድና የብርቅዮ እንደምያዝ እንዲሰማኝ አደረገኝ። ይህን ያህል ጊዜ በሕይወት ያቆየኝና በብዙ ሥቃይ ውስጥ ያሳለፈኝ በደም በሰከረ ገዳይ ገጀራ እንድገደል እንዳልሆነ አውቃለሁ! በአንድ የማይረባ የዕለት ህመም እንድሞት እንደማያደርገኝም ይታወቀኛል። በመታጠቢያ ቤቱ ለሁለት ጊዜ ያክል በተወሰኑ ክኒኖች በአንድ ቀን ልቆጣጠራቸው በምችላቸው ህመሞች ተይዤ ነበር ... ኪኒን ቢኖረን ኖሮ። የመጀመሪያው ህመሜ በመንዘፍዘፍና በራስ ምታት ባሰቃየኝ በ40.5 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ሙቀት ታጅቦ ነበር የመጣው። ሁለተኛው ደግሞ አሳልፌ ከማውቃቸው በጣም አሰቃቂ ከስተቶች አንዱ የሆነው አስከፊ የሽንት ቧንቧ መመረዝ ነበር። ቁሱ ሊያቀርቡልኝ የቻሉት ብቸኛው ነገር የሙቀት መለኪያ መሣሪያና መልካም ምኞታቸውን ነበር - የቀረ ምንም መድኃኒት አልነበራቸውም።

ማድረግ የምችለው ብቸኛው ነገር መጸለይ በመሆኑ ያንን ብቻ ነበር ያደረግሁት። ሕመሙና ትኩሳቱ ከምችለው በላይ ሲሆንብኝ አምላክ እንደተኛሁ ፈዋሽ እጆቹን እንዲያሣርፍብኝ ጠየቅሁት። በሁለቱም ጊዜያት ያለምንም ትኩሳትና ህመም ተነቃቅቼና ደኅና ሆኜ ተነሣሁ። በፍቅሩ ኃይል ተፈወስኩ።

ምንም ዓይነት ህመም ሕይወቴን እንደማይነጥቀኝ ተማምኖለሁ፡፡ አምላክ ለእኔ አንድ ታላቅ ዓላማ እንደነበረው እርግጠኛ ነበርኩ፡፡ እናም በየቀኑ ያንን ይገልጽልኝ ዘንድ እጠይቀዋለሁ፡፡ መጀመሪያ ላይማ ሁሉንም የወደፊት ሕይወቴን ባንዴ እንዲያሳየኝ እጠብቃለሁ፡፡ ምናልባት ለጥሩ ዓላማ እንደተሰነዘሩ ሁሉ፤ ልክ እንደ መብረቅ ብልጭታና እንደ ድርቅርቅ ምች፡፡ ግን አምላክ ምንም ቢሆን አንድን ልንረዳው ያልተዘጋጀንለት ነገር እንድናይ እንደማያደርገን እየተማርኩ መጣሁ፡፡ ይልቁኑ ለማየት የሚያስፈልገንን ልናይ በሚገባን ጊዜ እንድናይ ያደርገናል፡፡ ዓይናችንና ልባችን ክፍት እስኪሆኑለትም ይጠብቃል፡፡ ዝግጁም ሲሆኑ እግሮቻችንን ለኛ አመቺ በሆነው መንገድ ላይ ያስቀምጣቸዋል.... መራመዱ ግን የኛ ድርሻ ይሆናል፡፡

ቄስ ሙሪንዚ አንድ ቀን ስለ ጦርነቱ ሲያወሩ ጌታ ትክክለኛውን ነገር አስመለከተኝ፡፡ የተመድ የሰላም አስከባሪ ወታደሮቹን ወደ ሩዋንዳ ሊልክ ስላቀደ ለጦርነቱ ፍጻሜ ያበጅለታል ብለው በማሰብ ቄሱ በጣም ተደሰቱ፡፡ የተመድ ኦሥር ቤልጅዬማውያን ሰላም አስከባሪዎች በዘር ፍጅቱ የመጀመሪያ ቀን በሁቱ ወታደሮች ከተገደሉበት በኋላ አብዛኞቹን ወታደሮቹን አስወጥቷል፡፡ በእርግጥ ሁሉም ምዕራባዊ ሀገር ቱትሲዎችን ዕጣ ፈንታቸውን ብቻቸውን ይጋፈጧት ዘንድ በመተው ዜጎቹን ከሀገሪቱ አስወጥቷል፡፡ የዘር ፍጅቱ ከጀመረ ወዲህ ምንም የውጪ ዜጎች አልነበሩም ማለት ይቻላል - ያም ለኛ መንግሥት የዘር ፍጅትም ቢያካሂድ ዓለም ግድ እንደማይሰጠውና የቱትሲዎች ሕይወት ዋጋ እንደሌለው መልዕክት አስተላልፎለታል፡፡ ስለሆነም ግድያው ቀጠለ፡፡

የተመድ አዲስ ጦር መላኩ ትልቅ ነገር ነው... የዘር ፍጅቱን ሳይቀር ሊያስቆመው ይችላል! ቄሱ ግን ችግር እንዳለ ይናገራሉ፡፡ «በሩአግ ውስጥ ያሉት ቱትሲዎች የተመድ ወታደሮቹን እንዲልክ አይፈልጉም፡፡ ምክንያቱም ጦርነቱ እንዲቀጥል ስለሚፈልጉ ነው፡፡ ጦርነቱን እንደሚያሸንፉና ሥልጣን እንደሚይዙ ያስባሉ!» ሲሉ ጮሁበን፡፡ «ወግ ወጉ ተይዞልኛል፡፡ የተመድ ወታደሮችን ከላከ እንግሊዝኛ ተናጋሪ መሆን እንዳለባቸው እየጠየቁ ነው ... ይህን ያህል ድፍረት!»

ቄሱ አብዛኞቹ የሩአግ ወታደሮች በብሪታንያ ቅኝ በተገዛችው በዩጋንዳ ያደጉ ስለሆኑ እንግሊዝኛ እንደሚናገሩ ነገሩን፡፡ ይህም ፈረንሳይኛ በሚነገርባት በቤልጅዬም ከተገዛችው ከሩዋንዳ ጋር ይቃረናል፡፡ አብዛኞቻችን በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ፈረንሳይኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋችን ተምረናል፡፡

«የራሱ ወታደሮች ፈረንሳይኛ ቢችሉም እንኳን ሩአግ አንናገርም ብሎ ይቃወማል» ቄስ ሙሪንዚ ጨመሩልን፡፡ «የፈረንሳይ ጦር ሠራዊት የኢንተርሃምዌን

ገዳዮች አሰልጥኗል ብለው ይወነጅላሉ፡፡ ፈረንሳውያንን ይጠሏቸዋል... ሩአግ ጦርነቱን የሚያሸንፍ ከሆነ ሁላችንንም እንግሊዝኛ እንድንናገር ያደርጉናል!»

አምላክ በአእምሮዬ አንዳች ብርሃን አበራልኝ፡፡

ሁሉም ነገር የሆነው በቅጽበት ነው፡፡ በዚያን አፍታ ሩአግ ጦርነቱን እንደሚያሸንፍ እርግጠኛ ሆንኩ፡፡ ይህም ማለት እኔ እንግሊዝኛ ተናጋሪ የሆኑ ሰዎችን ከዘር ፍጅቱ በኋላ አገኝና የደረሰብንን ሁሉ የተከሰተውን እነግራቸዋለሁ ማለት ነው፡፡ ሀሉም ሰው እንግሊዝኛ ብቻ በሚናገርበት በተመድ ውስጥ እንደምሠራም ራእይ ታየኝ፡፡ ድንገት በመታጠቢያ ቤቱ ውስጥ ያለውን ቀሪውን ጊዜዬን እንግሊዝኛ ቋንቋን ስናገር አንደማሳልፍ በግልጽ ታወቀኝ፡፡ አምላክ የአንድን ትልቅ ሕጋዊ ቁማር አሸናፊ ቁጥሮች እንደሰጠኝ ተሰማኝ... ማድረግ የነበረብኝ ብቸኛው ነገር ቢኖር ዕጣው ሲወጣ ዝግጁ መሆኔን ማረጋገጥ ይሆናል፡፡ ዕጣ ፈንታዬን ለመጋፈጥ መዘጋጀት ነበረብኝ!

ፍጹም እንግዳ የሆነን ቋንቋ መማር የብዙ ሰዓታት ጥናት እንደሚጠይቅ አውቃለሁ፤ ይህም ጸሎቴን እንድቀንስ ያስገድደኛል፡፡ ይህም መሆኑ ለዲያብሎስ የሚጠብቀውን ዕድል ይሰጠዋል ብዬ ሠጋሁ፡፡ ወደ አእምሮዬ ተመልሶ ዘሎ ገብቶ በፍርሃትና በጥርጣሬ ሞልቶኝ ወደ ጨለማና ተስፋ መቁረጥ ውስጥ ይከተኛል፡፡

ማድረግ የምችለውን ብቸኛውን ነገር አደረግሁ፡፡ አምላክን ምን እንደማደርግ ጠየኩት፡፡ ውድ እግዚአብሔር - ይህን እንግሊዝኛ ተማሪ የሚለውን ሐሳብ አንተ ወደ ራሴ ከተኸዋል፤ ስለዚህ በማጠናበት ጊዜ ዲያብሎስን አርቅልኝ! እባክህ እዚህ መታጠቢያ ቤት ውስጥ ተቀርቅሬ አዲስ ቋንቋ እንዴት አንደምማር አሳየኝ፡፡

ለሌሎቹ ሴቶች ስለ ዕቅዴ ለመንገር ግድም አልሰጠኝ - በዚያ በምጸልይበት መንገድ ስጸልይ ሲያዩ ነገሩን ቀለል አድርጌ እንዳየሁት አስበዋል፡፡ ሕይወታችንን ለማትረፍ ስንጣጣር የውጪ ቋንቋ ለመቻል እንደፈለግሁ ብነግራቸው ቁሱን ለአንድ አባሺ ጎሳ አባል ወዲያውኑ አሳልፈው እንዲሰጡኝ ሊጠይቋቸው ይችላሉ፡፡ ስለሆነም ህልሞቼን ለራሴ ይገቼ ቆየሁ፡፡

በቀጣዩ ቀን ቁሱ ምግብ ሲያመጡልን የፈረንሳይኛ - እንግሊዝኛ መዝገበ-ቃላትና ሊኖራቸው የሚችልን ማናቸውንም በእንግሊዝኛ የተጻፈ መጽሐፍ ያውሱኝ እንደሆነ ጠየቅኳቸው፡፡ ሥጋ ጥብስ እራት ያዘዝኩ ያህል አተኩረው አዩኝ፡፡

«አእምሮዬን ትንሽ በሌላ ነገር ላስይዘው ፈልጌ ነው፡፡ ለሁለት ወር ያህል ግንብ ላይ አፍጥጠን ቆየን፤ እርስ በርሳችን እንኳን መነጋገር አንችልም» ስል ለቁሱ አንሾካሾክሁ፡፡

ራሳቸውን ነቀነቁና አንድን አብድ ‹ተው አንተ› የሚሉ መስለው ዘወር አሉ፡፡

«እንግሊዝኛ ከተማርኩ ለተመድ የሰላም አስከባሪዎች ከጦርነቱ በኋላ እርስዎ እንዴት በጀግንነት የኖን ሕይወት ለማዳን እንደጣሩ መናገር እችላለሁ» ስል በፍጥነት ጨመርኩላቸው።።

ቄስ ሙሪንዚ ወዲያውኑ በሃሳቡ ተስማሙና የመጽሐፍ ስብስባቸውን ለመቃኘት ቃል ገቡልኝ።። እድለኛ ነበርኩ - እንግሊዝኛ መጻሕፍት የነበሯቸው በጣም ጥቂት ሩዋንዳውያን ነበሩ።። ቄሱ ግን ሁለት አገኙልኝ - የፈረንሳይኛ - እንግሊዝኛ መዝገበ-ቃላቱንም ጭምር።።

«ለጀማሪ የሚሆን ምንም የእንግሊዝኛ መጽሐፍ የለኝም፣ ኢማኪዩሌ» አሉኝ።።

ፈገግ አልኩባቸው።። ጦርነቱ ምን ያህል ጊዜ ሊቆይ እንደሚችል የማውቅበት አንዳች መንገድ ባይኖረኝም ግን ትናንሽ ሂደቶችን መሄድ አልፈለግሁም - ወደ አዲሱ ሕይወቴ ታላላቅ እርምጃዎችን ነበር መራመድ የፈለግሁት።። «ይሁን ቄሱ» ስል መለስኩላቸው።። «ችኮላ ላይ ስለሆንኩ የጀማሪ መጽሐፍ አልፈልግም።። ያለዎትን ትልቁንና በጣም ከባዱን የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ያምጡልኝ።።»

ቄሱ በእቅዴ በጣም ተደሰቱ፤ የተመድን ሰላም አስከባሪዎች እንዴት ላውቃቸው እንደምችልም ጭምር ነገሩኝ።። «ሰማያዊ ኮፍያ የሚለብሱት እነርሱ ብቻ ናቸው» አሉኝ ሁለት ትላልቅ መጻሕፍትንና መዝገበ-ቃላቱን እየሰጡኝ።።

ወዲያውኑ ከፈትኳቸውና እንግዳ ቃላቱን በዓይኖቼ ገረፍ ገረፍ አደረኳቸው።። መጻሕፍቱን የወርቅ እንደሆኑ ሁሉ በፍቅር ያዝኳቸው - የአንድን ውድ የአሜሪካ ዩኒቨርሲቲ የትምህርት ዕድል ያሸነፍኩ ያህልም ተሰማኝ።።

በረጅሙ ተነፈስኩና አምላክን ለጸሎቴ ምላሽ ስለሰጠኝና እንግሊዝኛ ለመማር የሚስፈልጉኝን መሣሪያዎች ስላመጣልኝ አመሰገንኩት።። ምንም እንኳን የጸሎት ጊዜዬን የምሰዋ ቢሆንም አምላክ ሳጠና አብሮኝ እንደሚሆን አውቃለሁ።። ይህን ቋንቋ እንድማር ስላሰበ የአስተሳሰቡ ጉልበት በውስጤ ሲሄድ ይሰማኛል።። የጊዜዬን አንዲትም ደቂቃ በራሴ በማዘንና በጥርጣሬ እንዳላሳልፍ ስላገዘኝ ረጅም ትንፋሽ ወሰድኩና አመሰገንኩት።። አምላክ ስጦታ ሰጥቶኛል፤ እናም የኔ ድርሻ በምላሹ ደግነቱን በተቻለኝ መጠን መጠቀም ይሆናል።። ትልቁን መጽሐፍ ከፈትኩና ማንበብ ጀመርኩ።።

በመታጠቢያ ቤቱ የሚኖረኝን ቀሪውን ቆይታዬን ለጸሎት፣ ከአምላክ ለመገናኘትና በቻልኩት መጠን ጠንከሬ ለማጥናት መደብኩት።። እንግሊዝኛን በአንዴ አንድ ቃል፣ በአንዴ አንድ ቃል በማድረግ በማጥናት ተማርኩ - አዲስ ቃል በእንግሊዝኛው መጽሐፍ ላይ አይና መዝገበ-ቃላቱን በመጠቀም በፈረንሳይኛ ፈትቼ ትርጉሙን

ለማግኘት እሞክራለሁ። በመጀመሪያ አካሄዱ ቀሰስተኛ ቢሆንም ሂደቱ ግን አስደሳችና አዝናኝ ነው!

መጀመሪያ ያደረግሁት ነገር በእውኑ ዓለም ስገባ ያስፈልጋሉ ብዬ ያመንኩባቸውን ቃላት ማስታወስ ነው። በእንግሊዝኛ **አይ** ማለት የፈረንሳይኛው **ጊ** እንደሆነ አገኘሁት፤ ማስታወስ ያለብኝ በጣም ጠቃሚ ቃል እንደሆነም ገባኝ (በአማርኛ **እኔ** የሚለው መሆኑ ነው)። «እኔ ቱትሲ ነኝ፤ እኔ እገዛ እፈልጋለሁ» ብዬ ማለት መቻል ያስፈልገኛል። «እኔ ለሦስት ወራት ተደብቄ ከረምኩ» «እኔ ቤተሰቤን እየፈለግሁ ነው» ወይንም «እኔ ሥራ እፈልጋለሁ።»

እንግሊዝኛ ያጠናሁባት የመጀመሪያዋ ቀን ስትጠናቀቅ የመጀመሪያውን መጽሐፍ የመጀመሪያ ገጽ ደጋግሜ አንብቤዋለሁ። የዚያን መጽሐፍ ስም አሁን ባስታውሰው፤ ወይንም ቢያንስ ስለምን እንደሆነ እንኳን ባውቀው ጥሩ ነበር፤ ግን ብዥ ብሎብኛል። የማስታውሰው ነገር ቢኖር ለማንበብ በጣም ሲጨልምብኝ ደረቴ ላይ ጥብቅ አድርጌ ይገፍ የመጀመሪያውን የእንግሊዝኛ አረፍተነገሬን ቀስ ብዬ ሳነበንብ «ኢማኪዩሌ ነኝ። ተመስገን እግዚአብሔር!» ስል ነው።

በእያንዳንዱ ቀን መጨረሻ ብደካክምም እደሰታለሁ። አምላክ ያሰበልኝ አዲሱ ሕይወቴ ራሱን በዚህ ገና ልረዳው ባልቻልኩት ቋንቋ እንደሚገልጽ ታውቆኛል። ቀናቱ ሲያልፉ ብዙዎቹን የራሴን ታሪክ በእንግሊዝኛ ለመናገር የሚሆኑኝን ቃላት ማስታወስ ቻልኩ። «ማምለጥ»፣ «መደበቅ»፣ «ጦርነት»፣ «ጸሎት»፣ «ሥራ»፣ እና «እግዚአብሔር» እያደገ የሚሄደው የእንግሊዝኛ የቃላት ክምችቴ የማእዘን ድንጋዮች ሆኑ። እያንዳንዷ ቃል እንደ ውድ ጌጥ ነበረች። «በፊት» እና «በኋላ» የሚሉትን ቃላትም ለማስታወስ ጣርኩ፤ ምክንያቱም በወቅቱ ሕይወቴን ከጭፍጨፋው በፊትና በኋላ እያልኩ እንደምገልጽ ስላወቅሁ ነው።

አንድ ቀን ጠዋት መዝገበ ቃላቱን ሳስስ የእንግሊዝኛን ሰዋስው የሚመለከተውን ክፍል አገኘሁት። ህጎች! በጣም ተደሰትኩ - ከገነት የወረደ መና ማለት ነው! የእንግሊዝኛን ምስጢር የሚከፍቱትን ቁልፎች አገኘሁ - ግሶች፣ ስሞችና ቅጽሎች፤ የቃላት ማራቢያዎች፤ የበፊት፣ የአሁንና የወደፊት - ግሩም ነበር! ሌሎቹ ሴቶች በተኙበት አሊያም አጽናፍ ዓለምን ሽቅብ በሚያዩበት ጊዜ እኔ አዲስ አጽናፍ ዓለም አስሳለሁ። ቀኑን ሙሉ ጸሎቴን ሳደርስና መጻሕፍቴን ሳነብ እውላለሁ። በመስኮቱ በሚገባው ደብዛዛ ብርሃን ከእኩለ ሌሊትም በኋላ ጭምር አነብ ነበር፣ ዓይኖቼ አልከፈትም ብለው እስኪያስቸግሩኝ ድረስ አነባለሁ። አምላኬን ለማጥናት ስለሰጠኝ እያንዳንዷ ደቂቃ አመሰገንኩት።

ይህን ጥረት ከጀመርኩ ከሦስት ሳምንታት በኋላ ቄሱ የሰጡኝን ሁለት መጽሐፍት ከዳር እስከ ዳር አንብቤ ጨረስኩ። ወደ ቀጣዩ ደረጃ ለመሸጋገር ዝግጁ ሆንኩ -

ራሴን እንግሊዝኛ መጻፍ ለማስተማር። ከቄሱ ብዕርና ወረቀት ተውሼ ደብዳቤ ማርቀቅ ጀመርኩ።

ገና በሕይወት ለሌለ ግን በልቤ ሙሉ ለተማመንኩበት ሰው መጻፍ ጀመርኩ - ለአዳኛችን። ከጭፍጨፋው እንደምንተርፍ በጣም ስለተማመንኩና የወደፊቱን የመገናኘት ተስፋችንንም ይበልጥ እውን ለማድረግ ለምናባዊ ጀግናዬ ሁሉንም ገጽታዎችና መገለጫዎች ሰጠሁት። ትንሽ ሪዝ ያለችውና በጎልዳፋ የእንግሊዝኛ ቅላጼ የሚናገር ረጅም፣ ጥቁር የተመድ ወታደር አድርጌ ሣልኩት። ንጹሕና የተተኮሰ ሰማያዊ የደንብ ልብስና ወደ ቀኝ ጆሮው ወረድ ያለች ሰማያዊ ኮፍያ ለብሷል። ደግነት የሚንጸባረቅበት ግልጽ ፊት፣ እውነተኛ ፈገግታ፣ ብሎም የችግራችንን ታሪክ የሚገልጸውን ደብዳቤዬን ሲያነብ የሃዘኔታ እንባ የሚሞላባቸው ብሩህ ቡናማ ዓይኖች ነበሩት። ስለ እርሱ የነበረኝ ምስል ለገዳዮቹ ቀርጩው የነበረው ተቃራኒ ነው።

ያን ደብዳቤ መጻፌ ስለ ሕይወት የነበረኝን አዲስ አስተያየት ለማነልበት ወሳኝ ምዕራፍ ነው። በአእምሮዬ አዳኜን ደግና አሳቢ እንደሆነ አድርጌ ሣልኩት ምክንያቱም እኛን እንዲያድነን የፈለኩት ሰው ያን ዓይነት ስለነበረ ነው። አንድ ሰው አንድ ጊዜ ወደፊት እንዲከሰት የምፈልገውን ነገር በአእምሮዬ መሳል ወሳኝ እንደሆነ ነግሮኛል። እንግዲህ ይመስገነው፣ የዚያ ፍልስፍና ጽኑ አማኝ ሆኛለሁ።

እግዚአብሔር ዘሩን በአእምሮዬ ዘርቶታል። እንግሊዝኛ እንድማር ነግሮኛል። ያ ልምምድም በዘር ፍጅቱ ማግስት የተደላደለና የሚያስደስት ሕይወት እንደሚጠብቀኝ ያሳየኝ ይዟል። እምነቱ ካለኝ፣ ይህንንም እምነት በሙሉ ልቤና በቅን መሻት ከሣልኩት ያለምኩት ነገር አምላክ ለኔ ትክክል ነው ብሎ ያሰበልኝ ከሆነ እንደሚከሰትልኝ አውቃለሁ። ዕጣ ፈንታዬን ማለምና መሳል እንደምችል የተገለጸልኝ ያኔ ነው። የፈለግሁትን ለማግኘት ሁልጊዜ እንደማልም ለራሴ ቃል ገባሁ። እናም ፍቅር፣ ጤናና ሰላምን ስለመሳሰሉት በጎ ነገሮች ብቻ አልማለሁ ምክንያቱም አምላክ ለሁሉም ልጆቹ እንዲሆን የሚፈልገው ያ ስለሆነ ነው።

በሰኔ መጀመሪያ ካለፈው ሕይወቴ ጋር ፊት ለፊት ተገናኘሁ። የወንድ ጓደኛዬ ዮሃንስና እኔ ለሁለት ዓመታት በቁም ነገር የምንፈላለግ ኮበሌዎች ሆነናል። ትምህርቴን ስጨርስ እንደምንጋባ ሳይቀር አውርተናል። ምንም እንኳን ከትጉሣኤ በፊት ተጣልተን የነበረ ቢሆንም (ቤተሰቦቻችንን በወጉ ለማስተዋወቅ ያዘጋጀነውን የቀለበት ሥነ-ሥርዓት በመሠረዝ አሳፍሮኛል) አሁንም ቢሆን መታረቅ እንደምንችል አስባለሁ።

ግድያው ከጀመረ ወዲህ ተገናኝተን አናውቅም፣ ነገር ግን በመታጠቢያ ቤቱ በነበረኝ ጊዜ ስለ እርሱ አስባለሁ - ደኅና እንዲሆንና ክፉ ሳይነካው እንዲቆይ በመጸለይ። ሁቱ ስለሆነ ከችግር እንደሚድንና በገጠርም እንደፈለገ ለመንቀሳቀስ ነጻ

እንደሚሆን አውቃለሁ፡፡ ብዙ ጊዜ የት ገባች ብሎ እንደሚፈልገኝ አስቤያለሁ፡፡ እነዚያና ሌሎችም ጥቂት ጥያቄዎች ባልጠበቅሁት ሁኔታ ተመለሱልኝ፡፡

አንድ ቀን ረፋድ ላይ ውጪ ላይ ትልቅ ጩኸት ሰማን፡፡ እኔም ወዲያውኑ ሌሎች የአሰሳ ዘመቻ አድራጊዎች ሊያድኑን እንደደረሱ ገመትኩ ... ወዲያውኑ ግን በፍጥነት ይህ ጩኸት ሌላ ነገር እንደነበር አወቅሁ፡፡ ክፉ የግድያ መዝሙሮችን ወይንም የተለመደውን ማስፈራሪያና የንዴት ጩኸት አልሰማንም - እንዲያውም በድምጾቻቸው ላይ ደስታ ይነበባል፤ ጮቤ ይረግጡም ገቡ፡፡ ሰዎች ወደ ቤቱ በመጡ ቁጥር ልቤ ይፈራ የነበረ ቢሆንም በዚህን ሰዓት ግን መደሰትና መፍነክነክ መጣ፡፡ በነባር ጓደኛሞች የመልሶ መገናኘትና የእንኳን ደኅና መጣችሁ ድምጾች መካከል የዮሃንስን ሣቅ ሰማሁና ሳግ ተናነቀኝ፡፡

ከኪጋሊ ተነሥቶ ከቄስ ሙሪንዚ ብዙ ዘመዶች ጋር መጥቶ ኖሯል፡፡ እንደ ሌሎች በሺዎች የሚቆጠሩ ሁቱዎች ሁሉ የአማጽያኑ ወታደሮች ወደ ከተማዋ በተጠጉ ቁጥር ዋና ከተማዋን ለቀው እየወጡ ኖሯል፡፡ የበቀል ግድያዎችን በመፍራት ቤቶቻቸውን ጥለው ምንም ውኒያ ወዳልነበረበት ወደ ደቡብ አምርተዋል፡፡ ዮሃንስን ጨምሮ ቢያንስ 40 የሚሆኑ የቄሱ ዘመዶች ጦርነቱ እስኪያልፍ በሚል ተስፋ በኛ መንደር ለመስፈር አቅደው ነው የመጡት፡፡

የወንድ ጓደኛዬ በሕይወት፣ በጤናና በሰከነ መንፈስ መኖሩን በማወቄ ተደሰትኩ - በቅርቡ ዓይን ለዓይን እንደምንተያይ ማሰቡ ያስደስታል፡፡ ቀኑን ሙሉ የኔን በቤቱ ውስጥ መደበቅ ያውቅ እንደሆነ ሳስብ ቆየሁ፡፡

ማታ በጣም ከመሸ በኋላ በግቢው ያለው ሁሉም ሰው ሲተኛ ቄሱ ዮሃንስን ወደ መታጠቢያ ቤቱ አመጡት፡፡ ስላየሁት በጣም ደስ ስላለኝ ለተወሰኑ ደቂቃዎች በእርግጥ የት እንዳለሁ ረሳሁ- በጣም ጥብቅ አድርጌ ስላቀፍኩትም ራሴን ልስት ምንም አልቀረኝም፡፡ በመታጠቢያ ቤቱ ለሳምንታት በሹክሹክታና በምልክት ቋንቋ ከተግባባን በኋላ እንዴት እንደናፈቅኝና እንደጸለይኩለት ለመንገር ድምጼን ማውጣት ቸገረኝ፡፡

ዮሃንስ ወዲያውኑ ወደ ኋላ ተራምዶ ላይ ታች አየኝና «እንዴት ነው የመነመንሽው፣ ኢማኪዩሌ፡፡ ሳቀፍሽ እኮ ልክ አንድ እቅፍ አጥንት ያቀፍኩ ነው የመሰለኝ!»

እየሣቅሁና እያለቀስኩ አየሁት፡፡ በተናገረው ነገር ግን ተደናገጥኩ፤ ተገረምኩም - እንደሚወደኝ ይነግረኛል ወይንም ቢያንስ እኔን በሕይወት ስላገኘኝ እንዴት እንደተደሰተ ይናገራል ብዬ ተስፋ አድርጌ ነበር፡፡

«እንግዲህ ... ያ ግሩም ሰውነትሽ ከድቶሻል» ሲል ቀጠለ፣ «ግን አሁንም ታምሪያለሽ! እስካሁን በሕይወት እንድትቆዪና ማንም አስገድዶ እንዳይደፍሽ ስጸልይ ነበር፡፡ እናም ይኸው ሳይደፍሩሽ በሕይወት አለሽ!»

ቃላቱ አቆሰሉኝ፤ የወንድ ጓደኛዬ ሳይሆን አንድ ሌላ ሰው የሚያወራኝ ይመስላል፡፡ አብረን ከነበርንባቸው ጊዜያት ይበልጥ ተለውጧል፡፡ በእርግጠኝነት ተለውጧል - ጸጉሩ በጣም አድጎና የጎፈለለ ጺሙም ፊቱን ደብቆታል፡፡ የዘር ፍጅቱ ይካሄድ በነበረበት ወቅት በአገሪቱ ሁሉ ነገሯ ተዘጋግቶ ስለነበር ጸጉር አስተካካይ ለማግኘት አለመቻሉን ገለጸልኝ፡፡

ቄስ ሙሪንዚ ሰው እንዳይሰማን ብለው ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ውይይታችንን አቋረጡት፡፡ አብረን ረዘም ላለ ጊዜ መቆየት እንድንችልና የልባችንን እንድናወራ ብመኝም አልተቻለንም፡፡ ዮሃንስና እኔ ቄሱ የመታጠቢያ ቤቱን በር ከመዝጋታቸው በፊት አንድ ጊዜ ደግመን ተቃቀፍን፡፡

እግዚአብሔርን ዮሃንስን በሕይወትና በደኅና ስላቆየው አመሰገንኩት... ግን ወዲያውኑ በቤቱ መኖሩ የሚረብሽ መሆኑን ተረዳሁት፡፡ ነጻና እንደ ልዑል የሚኖር ነው - እርሱ እንዳሻው ወደ ውጪ እየወጣ፣ ጥሩ ምግብ እየበላ፣ አልጋ ላይ በንጹሕ አንሶላዎች ላይ እየተኛና ከእናቱ ጋር ሳይቀር እያወራ - እኔ በበኩሌ እንደ እንስሳ ወጥመድ ውስጥ ገብቼ፡፡ በየቀኑ ሲደሰት፣ ሲስቅ፣ ወሬ ሲያወራና ከሁቱ ጓደኞቹ ጋር ቅርጫት ኳስ ሲጫወትና ቀልድ ሲቀልድ በመታጠቢያ ቤቱ መስኮት በኩል እሰማዋለሁ፡፡ ልሰማው እንደምችልም ያውቃል፡፡ በእርግጥ ቁጭ ብሎ እንዲብሰለሰልም አልጠብቅም፤ ግን በመታጠቢያ-ቤቱ እስር ቤቴ ስር ያደርግ በነበረው መንገድ መቀጠል እጅግ ለሰው አለማሰብ ነው፡፡ የሚያደርገው ሁሉ ሽርሽር ላይ እንዳለ ነበር፤ ሰዎች - የኔ ወገኖች በእርሱ ዙሪያ ሲታረዱና የሴት ጓደኛው በወሮበሎችና ገዳዮች እየታደነች፡፡

አንዳንዴ ውጪ ላይ ሲዝናና ሳዳምጠው መጽሐፍ ቅዱሴን ከፍቼ የሚከተለውን አነባለሁ-

> ፍቅር ይታገሣል፣ ቸርነትንም ያደርጋል፤ ፍቅር አይቀናም፤ ፍቅር አይመካም፣ አይታበይም፤ የማይገባውን አያደርግም፣ የራሱንም አይፈልግም፥ አይበሳጭም፥ በደልን አይቆጥርም፤ ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለ ዓመፃ ደስ አይለውም፤ ሁሉን ይታገሣል፣ ሁሉን ያምናል፥ ሁሉን ተስፋ ያደርጋል፣ በሁሉ ይጸናል። ፍቅር ለዘወትር አይወድቅም። (1 ቆሮ. 13፣ 4-8)

የፈለግሁት ፍቅር ያ ነው፤ እግዚአብሔርም እኛ እያንዳንዳችን እንዲኖረን የሚፈልገው ያን እንደሆነ አውቃለሁ፡፡

ዮሃንስ ከመጀመሪያው ምሽት በኋላ አንድ ወይንም ሁለት ጊዜ አይቶኛል፤ ስለሆነም ባሳለፍናቸው ጥቂት ደቂቃዎች ተደስቻለሁ፡፡ ጉበኝቶቹ ሐሳቦቻችንንና ስሜቶቻችንን ለመጋራት እንዳንችል በጣም አጭርና የማይደጋገሙ ነበሩ - ላወራው የፈለግሁት ብዙ ነገር ነበር፡፡ እግዚአብሔር ምስክሬ ነው፡፡ እኔን ለማዋራትና ትንሽ እንኳን ወደ ልቤ ለመድረስ ምንም ጥረት አላደረገም፡፡ በተለይ የቁሱ ብዙ ሁቱ ዘመዶች በቤቱ ውስጥ ባሉበት ሁኔታ እኔን መጎብኘቱ ለእርሱ አስቸጋሪና አደገኛ እንደሆነ አውቃለሁ፤ ግን ቢሆንስ ታዲያ እንዲህ ይደረጋል!

በአንድ በተገናኘንበት አጋጣሚ እንደለመንኩት አስታውሳለሁ፡፡ «እባክህ ትንሽ ጊዜ ወስደህ ማስታወሻ ቢጤ ጻፍ አድርገህ ለቁሱ ወይንም ለዱዜንጂ ሌሊት ምግብ ሲያመጡ ላክልኝ፡፡ ያንን ብቻ ነው የምፈልገው ዮሃንስ ... በቃ ስለ እኔ እያሰብክ መሆኑን፣ እንዴት ሆነች ብለህ እንደምትጨነቅልኝ የሚያሳዩና ፍቅራችን ሕያው ሆኖ እንዲቀጥል እንደምትፈልግ የሚያስታውቁኝ ትንሽ ቃላት!»

ምንም እንኳን እንደሚጽፍ ቃል ቢገባልኝም ፈጽሞ አላደረገውም፡፡ በቀጣይ ጊዜ ሊያየኝ ሲመጣ የተወሰኑትን ያሳለፍናቸውን ውድ ጊዜዎቻችንን አንስቼ ልወቅሰው ሞከርኩ፡፡ «ቃል እንደገባኸው ለምንድነው ያልጻፍክልኝ? ምን ዓይነት ችግር እያሳለፍኩ እንደሆነ አይገባህም? ለምን ቸል ትለኛለህ?»

«እየውልሽ አንድ ነገር ይገባኛል - ሌሎች ወንዶች በጭራሽ አይፈልጉሽም፤ እናም የምትዪው ነገር አያስጨንቀኝም፤ ይገባሻል?»

በነዚያ ቃላት ዮሃንስ በመሀላችን የቀረን እንጥፍጣፊ ፍቅር አጠፋው፡፡ አምላክ ሁሉንም የፍቅር ስጦታ እንድንጋራና በየልባችን ተንከባክበን እንድናሳድገው ሰጥቶን ነበር፡፡ ዮሃንስ ግን ያን ውድ ስጦታ አባከነው!

ምዕራፍ 15
አድነው የማያድኑት

የመጀመሪያውን መልካም ዜና የሰማሁት ግድያዎቹ በከፉበትና የከፋት ሥራዎች የዕለት ተዕለት ተግባራት በሆኑበት ወቅት ነው።።

በሰኔ ኢጋማሽ ላይ፣ ከተደበቅን ከሁለት ወራት ገደማ በኋላ የቄሱ ልጅ ሴምቤባ በመታጠቢያ ቤቷ መስኮት ስር ሆኖ ለጓደኞቹ ሲያወራ ሰማሁት።። ያዩዋቸውን ወይም ያየ ሰው የነገራቸውን በአካባቢው በቅርቡ የተፈጸሙ ግድያዎች ይጠቃቅሳሉ።። እነዚህ የሚወራላቸው ግድያዎች ከሰማኋቸው ሁሉ አሰቃቂዎቹ ናቸው።።

ከልጆቹ አንዱ የማይታሰቡ አረመኔያዊ ተግባራትን ልክ ስለ እግር ኳስ ግጥሚያ እንደሚያወራ ሁሉ እንደዋዛ ሲገልጽ ሰምቼ ሊያስመልሰኝ ነበር - «አንዷን እናት ያዟት፣ ሁሉም ተፈራረቁባት።። ልጆቿን እንዲያርቁላት ብትጠይቃቸውም ባሏንና ሦስት ትንንሽ ልጆቿን አንገታቸው ላይ ገጀራ ደግነው በማስገደድ አሳዩአቸው።። ሁሉም የቤተሰቧ አባላት ስምንት ወይንም ዘጠኝ ገዳዮች ሲደፍሯት እንዲያዩ አስገደዷቸው።። የእርሷ ሲበቃቸው መላውን ቤተሰብ ገደሉ።።»

አሰቃቂ ወሬዎቻቸውን ሲያወሩ ራሴን ደገፍ አድርጌ ቆየሁ።። እጅና እግሮቻቸው ከተቆረጡ በኋላ ሆነ ተብሎ በሕይወት እንዲቆዩ ስለተተዉ ልጆች፣ ድንጋይ ላይ ስለተወረወሩ ሕፃናትና በበሽታው እንዲለከፉ ኤች. አይ. ቪ. በያዛቸው ወታደሮች እንዲደፈሩ ስለተደረጉ በአሥራዎቹ ዕድሜ ላይ ያሉ ልጃገረዶች ያወራሉ።።

ከዚህ በኋላ ብዙ ብዙ ወሬ ቢከተልም ኖሮ እኔ ግን ጆሮዎቼን ይዤ በጸጥታ አምላኬን ተለማመንኩ።። ወይ አምላኬ፣ እኔንም የሚጠብቀኝ ይህ ከሆነ አሁኑኑ በአፍቃሪ እጆችህ ውሰደኝ! በገነት ካንተ ጋር ልኑር፤ በዚህች ወደ ሲዖልነት በተቀየረች ሀገር እኖር ዘንድ አትፍረድብኝ።።

ቆይቶ ይህ ውጪ ላይ የነበረው ውይይት ከጦርነት ወንጀሎች ወደ ጦርነቱ ራሱ ዞረ።። የተወሰኑት ልጆች የመንግሥት ወታደሮች ክፉኛ እየተሸነፉ ስለሆነ ኪጋሊ በቅርቡ በአማጽያኑ እጅ እንደምትወድቅ ተናገሩ።። አማጽያኑ ካሸነፉ ሁቱዎች ምን እንደሚውጣቸው በማሰብ ሁሉም ተጨነቁ።።

ሴምቤባ ፈረንሳይ ወደ ሩዋንዳ ጦር ልትልክ እንደሆነ መስማቱን ተናገረ።። እርሱም ሆነ ጓደኞቹ ፈረንሳይ ከሁቱው መንግሥት ጋር ጥብቅ ቁርኝት ስላላት እፎይታ ያገኙ መሰሉ።። ልጆቹ ፈረንሳይ የመንግሥትን ወታደሮች የቱትሲ አማጽያኑን በመውጋትና ሩአግን ከሀገሪቱ በማስወጣት የምታግዝ አድርገው ያስቡ ይመስላል።። ያ

ከሆነ ጦርነቱ ያቆማል፤ ገዳዮቹም ርኩስ ዓላማቸውን በአጭር ጊዜ ማስፈጸም ይቻላቸዋል።

በመጀመሪያ ስለ ፈረንሳይ ወታደሮች መምጣት ምን ሊሰማኝ እንደሚገባኝ እርግጠኛ አልነበርኩም። ብዙ ሰዎች የፈረንሳይ የጦር ኃይል የኢንተርሃምዌን ገዳዮች በማስልጠን እንዳገዘ ይናገራሉ፤ ስለዚህ ምናልባት ወታደሮቹ የሚመጡት በእርግጥ መንግሥቱን የዘር ፍጅቱን እንዲያጠናቅቅ ለማገዝ ይሆናል።

ግን ያ ይሆናል ብዬ ለማመን አልቻልኩም። አይሆንም፣ ፈረንሳውያኑ ወደ ሩዋንዳ ከመጡ ቀሪው ዓለም ይከታተላቸዋል። ምስል አንሺዎችና ዘጋቢዎች ይኖራሉ፤ ይህም ማለት ዓለም ግድያዎቹን፣ ጭፍጨፋዎቹን ብሎም አስገድዶ ደፈራዎቹን ያያል ማለት ነው። በመሆኑም በሃብታም ሀገራት ያለው ሕዝብ እየተከሰተ ያለውን ነገር በዓይኑ ካየ - በእርግጥም ካየ - የሆነ ነገር ማድረግ ይኖርበታል። የዘር ፍጅቱን ማስቆም አለባቸው... አይደለም እንዴ?

ፈረንሳዮች ምንም እንኳን ገዳዮቹን ያሠለጠኑ ቢሆንም መምጣታቸው ጥሩ ነው፤ ማናቸውም የውጪ ዜጋ ሥቃያቸንን ለዓለም ትኩረት ያበቃልናል። ወታደሮቹ በሰላም እንዲደርሱ ጸለይኩ፣ አምላክንም ስለላካቸው አመሰገንኩት። በሀገራችን ያላቸው ታሪክ ሲታይ ፈረንሳውያን አድነው የማያድኑን መሆናቸው እርግጥ ነው። በመታጠቢያ ቤቱ ሳለሁ እየተቀበልኩት የመጣሁት ሐሳብ ግን አምላክ በእውነት በተዓምራዊ መንገዶች መሄዱን ነው።

ከጥቂት ቀናት በኋላ ስለ ዘመቻ ቱርኮይስ የሬድዮ ዘገባዎችን የሰማን ሲሆን ይህም የፈረንሳይ ወደ ሩዋንዳ ወታደሮችን የመላክ ዕቅድ ነው። ከፈረንሳይኛ ተናጋሪ ሀገራት የተውጣጡ ወታደሮች ያን ያህል ከኛ ሩቅ ካልሆነው ከኪቩ ሐይቅ አቅራቢያ የጦር ሰፈር ያቋቁማሉ።

ወታደሮቹ በጎረቤት ሀገር በዛየር ከሩዋንዳ ድንበር አቅራቢያ ባለችው ጎማ ከተማ ሲደርሱ ሁቱ ባለስልጣናቱ በአየር ማረፊያው ትልቅ የእንኳን ደኅና መጣችሁ ክብረ በዓል አዘጋጁላቸው። የሁቱዎች የኪነት ቡድን በተለይ ለክስተቱ በተዘጋጀ መዝሙር ሲቀበላቸው በሬድዮ ሰማን። ፈረንሳውያንን አሞግሰው የሁለቱን ሀገራት የረጅም ጊዜ ፍቅር የተሞላበትን ግንኙነት አወሱ።

ዝግጅቱ ፈረንሳውያን ወደ ሩዋንዳ የመጡት ቱትሲዎችን ለመግደል እንደሆነ የሚያረጋግጥ መሆኑን ቄሱ ቢነግሩንም በሀሳባቸው አልተስማማሁም። አምላክ በዚህ ሰዓት የሚያድነንን ሰው በመላክ በድጋሚ ለጸሎቴ ምላሽ እየሰጠኝ እንደሆነ እርግጠኛ ነኝ። የተመድ የፈረንሳውያኑን ዕቅድ ደግፏል፤ ይህም ጥሩ ተስፋ ነው። ወዲያውኑ እንደደረሱም ፈረንሳውያን ራሳቸው ዓላማቸውን በሬድዮ አስታወቁ - ሩዋንዳ

የመጡት ለተረፉት ቱትሲዎች «ከለላ» ለማቋቋም መሆኑን ተናገሩ፡፡ ቱትሲዎች ወደ ምሽንቻቸው መድረስ ከቻሉ ፈረንሳውያኑ ወታደሮች ያድኗቸዋል፡፡

«ተመስገን አምላኬ» ስል አንሾካሾክሁ፡፡

ከተወሰኑ ቀናት በኋላ የፈረንሳውያኑ የጦር ጠያራ አካባቢያቸንን መቃኘት ጀመረ፡፡ ልቦቻችንም አብረው ሲያንጥበጥብን ጊዜ የተረፉ ሰዎችን እየፈለጉ መሆናቸውን እርግጠኞች ሆንን! ከሬድዮ ዘገባዎች እንደተረዳሁት ፈረንሳውያኑን ሄደንም እንዳናገኛቸው አሁንም እኛ ካለንበት በጣም ሩቅ ናቸው፡፡ ጦርነቱም ገና ስላልተጠናቀቀ በሺህዎች የሚቆጠሩ የታጠቁ ገዳዮች ቱትሲዎችን ፍለጋ ገጠሩን በማሰስ ላይ ናቸው፡፡ ማድረግ ያለብን ነገር ግን ለኔ ግልጽ ነው፡፡

ቄስ ሙሪንዚ ትርፍራፊ ምግብ ይዘውልን ሲመጡ ያንን ሐሳቤን ሰነዘርኩ፡፡ «ሄደን ከፈረንሳውያኑ ወታደሮች ጋር ብንቆይ ይሻለን ይመስለኛል» ስል ነገርኳቸው፡፡

ያ መጥፎ ሐሳብ ነው ኢማኪዩሌ፡፡ ቱትሲዎችን ሊያግዙ መጡ ብለሽ ማመን የለብሽም - እንዳዩዋችሁ ይገድሏችኋል» አሉ እጃቸውን በማወናጨፍ ሐሳቤን አጣጥለው፡፡

«ችግር የለውም መምሬ፡፡ ለእነዚህ የኢንተርሃምዌ ገዳዮች እኔን የመግደልን እርካታ እንዲያገኙ ከማደርግ ይልቅ በውጪ ወታደር በፍጥነት በጥይት ብረሸን ይሻለኛል፡፡ በአሥቃዮቻችን ተዋርዶ ከመሞት በፈረንሳዮች እጅ በንጽሕና መሞት ይሻላል፡፡»

ቄሱ ባልኩት ነገር የተደናገጡ ይመስላሉ፡፡ እኔና ሌሎቹ ሴቶች በመታጠቢያ ቤቱ ሆነን ቀን እስኪወጣ መጠባበቅ እንደሚኖርብን ነገሩኝ፡፡ ከዚያ በኋላ ግን ሌሎቹ ሰባት ሴቶች ወደኔ እየጠቆሙና ራሳቸውን በጣም እየነቀነቁ በሃሳቤ መስማማታቸውን ቄሱ ተገነዘቡ፡፡

ሴቶቹ በመስማማት ራሳቸውን እየነቀነቁ ሳሉ «ከፈረንሳውያን ጋር በስደተኛ ምሽግ መኖሩ ወደ ጫካ ሄዶ አባሺ ከማግባት ይሻለኛል» ስል ተጨማሪ ሐሳብ ሰነዘርኩ ፡፡ «ፈረንሳውያኑ ያድኑናል ወይም ይገድሉናል... ቄሱ፣ የፈለገው ቢመጣ ግን እንደሚመስለኝ ከነሱ ጋር ዕድላችንን ብንሞክር ጥሩ ነው፡፡»

ረጅም የእፎይታ ትንፋሽ ተንፍሰው ትከሻቸውን ነቀነቁ - በጥያቄዎችን በእርግጥ እፎይታ ተሰምቷቸዋል፡፡ ሰውዬው ጦርነቱ ሲጀምር ከነበረው በላይ አሁን ብዙ ሰው ተጨምሮባቸዋል፤ በመሆኑም ለእኛ ከለላ መስጠታቸው ቋሚ የሆነ ፈታኝ ጭንቀት አስከትሎባቸዋል፡፡

«ሁላችሁም የምትፈልጉት ወደ ፈረንሳውያኑ መሄድ ከሆነ የት እንዳሉ አጣራና እናንተን ወደዚያ መውሰዱ የሚቻል መሆኑን አየዋለሁ» ሲሉ በመጨረሻ ተስማሙ፡፡ «ግን ብዙም ተስፋ አታድርጉ፡፡ አሁንም ቢሆን ውጪ ላይ እጅግ አስቸጋሪ ነው… በመንገድ ላይ የታየ ቱትሲ ወዲያውኑ ይገደላል፡፡»

ቄስ ሙሪንዚ ተጨነቁ፡፡ በትንሿ መታጠቢያ ቤት ለሦስት ወራት ያህል መጨናነቃቸን አዕምሯቸንን እንዳያበላሸው ፈርተው ሊያነቃቁን ፈልገው ኖሯል፡፡ አንድ ምሽትም ስለ ፈረንሳይ ወታደሮች ወሬ ስንጠባበቅ ድንገተኛ ግብግ ይዘውልን መጡ፡፡ ከቆለፉብን ጊዜ ጀምረው ለመጀመሪያ ጊዜ በዋናው ቤታቸው ጋበዙን፡፡ የተንቀሳቃሽ ምስል ትዕይንት እንጂ የተለየ ግብግ አይደለም፡፡

በደረቅ ውድቅት በቤቱ የነበረው ሰው ሁሉ እንደተኛ ቄሱ ምትሃተ-መስኩትና[7] የትዕይንቱን ማጫወቻ መሣሪያ ወዳስቀመጡበት ባዶ መኝታ ክፍል ወሰዱን፡፡ ለወራት ከተቀመጥን በኋላ እግሮቻቸን ስለተልፈሰፈሱ ግንቡ ላይ እንወድቅ ጀመር፡፡ ታዲያ ቢሆንም ቄሱ ካለንበት ስፍራ ትንሽ ለየት ያለ ቦታ ላይ ስላመጡን አመሰገንኳቸው፤ እየተንሾካሾክንም ፈገግ አልን፡፡

ቄሱ ሰው እንዳይሰማን ስለፈሩ ትዕይንቱን ያሳዩን ድምጹን አጥፍተው ነው፡፡ ዕድለኝነታችን ደግሞ በዚያን ወቅት ጥሩ ከንፈር አንባቢዎች ስለወጣን መላውን ምስል ለመረዳት ምንም ችግር አልገጠመንም፡፡ የምስሉን ስም ብረሳውም ታሪኩን ግን በግልጽ አስታውሰዋለሁ፡፡ በአንድ በትምህርት የገፉ ሃኪሞች በሌሉበት የበረሃ መንደር ስለምትኖርና የሰዎችን ሕይወት ለማዳን ያለፍቃድ የሕክምና አገልግሎት ስለምትሰጥ መለስተኛ ሐኪም ነው፡፡ በዚህ መልካም ሥራዋ ውንጀላ ቢደርስባትም በመጨረሻ ግን ትክክለኝነቷ ተረጋገጠላት - ባለድልና ታዋቂም ሆነች፡፡

ታሪኩ ያነሳሳል፡፡ በጣም የማስታውሰው ግን አንድ ወጣት ልጅ ቢሸከሊሊቱን በጫካ ውስጥ እየጋለበና እየዘፈነ የሚሄድበትን ትዕይንት ነው፡፡ ይህን ሳይ መጀመሪያ የተሰማኝ የያገባኛል ስሜት ነው፡፡ የተጨነቅሁት ልጁ በገዳዮቹ ታይቶ እንዳይገደል ነው፡፡ ስለሆነም እንዲደበቅ ጮኬ ልነግረው ፈለግሁ፡፡ ከዚያም እውነተኛ ድርጊት አለመሆኑንና በሩዋንዳም ያልተከሰተ መሆኑን አስታወስኩ፡፡ ቱትሲ መሆን በሞት የሚያስቀጣ ወንጀል ያልሆነባቸው ሀገራት በዓለማችን እንዳሉ ረስቼው ኖሯል፡፡ ልጁ ደኅና መሆኑን ካወቅሁ በኋላ በመስኮቱ ዘልዬ ገብቼ አብሬው መሆንን ፈለግሁ፡፡ ወደ ሳሩ ሮጬ ገብቼ ግሩም መዝሙር ዘምሬ አምላኬን ላስደስት ፈለግሁ! ሕጻናት በሚስቁበትና ማንም ሰው እንዲደበቅ በማይገደድበት ስፍራ መኖርን ተመኘሁ፡፡

[7] ቴሌቪዥን

አለመታደል ሆኖ የተንቀሳቃሽ ምስል ትዕይንቱ ምሽት ደስታችን በአጭር ተቀጨ፡፡ ከቄሱ የቤት ሠራተኞች አንዱ የምትሃተ-መስኮቱን ሰማያዊ ውጋጋን ጭራሽ ካልጠበቀው ከፍል ሲያንጸባርቅ አይቶት ኖሯል፡፡ ሽልማት ለማግኘት አስቦ ያየውን ሁሉ ለገዳዮቹ በማሳወቅ ለረጅም ጊዜ ቄስ ሙሪንዚ እቤታቸው የሆነ ቦታ ቱትሲዎችን እንደደበቁ ሲጠራጠር እንደቆየም ይነግራቸዋል፡፡

የቄሱ ወዳጅ የሆነ አንድ ሰው ቤታቸውን ለመፈተሽ እየተዘጋጀ ያለ እጅግ ትልቅ የገዳዮች ቡድን መኖሩን ያስጠነቅቃቸዋል፡፡ ለሳምንታት ያህል ጊዜ ቄሱ እንዳታለሏቸው ስላሰቡ በጣም መናደዳቸውን ይነግራቸዋል፡፡

ቄሱ የተከሰተውን ነገር ሊነግሩን ሲመጡ በጣም የፈሩ ይመስላሉ፡፡ እንደዚያ ፈርተው አይቻቸው አላውቅም፡፡ በጉልበታቸው ወድቀው ከደረስንበት ጊዜ ጀምሮ ለመጀመሪያ ጊዜ እጆቻቸውን አጣምረው ስለነፍሶቻችን ጸለዩ፡፡ «ጌታዬ ሆይ፣ እነዚህ ሴቶች ወዳንተ የሚመጡበት ወቅት ከሆነ ቶሎ ውሰዳቸው፡፡»

ጸሎታቸው በፍጹም የሚሙች ሆኖ አላገኘሁትም፡፡ ፈርተን ከምናውቀው በላይ አስፈሩን - አንድ ሰው ሊፈራ ይችላል ተብሎ ከሚታሰበውም በላይ፡፡ «ቄሱ፣ ሠራተኞዎት እኛን ከተንቀሳቃሽ ምስል ትዕይንቱ በኋላ ወደ መታጠቢያ ቤቱ ስንገባ ያየን ይመስልዎታል? በእውነት የት እንደሆንን ያውቃሉ ብለው ያስባሉ?» ስል አንሾካሾክሁ፡፡

«ምን ምን እንደሚያውቁ እርግጠኛ አይደለሁም፤ ግን ቶሎውኑ እናጣራዋለን፡፡ ገዳዮቹ መንገድ ላይ ናቸው፡፡ ስለ መታጠቢያ ቤቱ ካወቁና እዚህ ካገኟችሁ ሁላችንንም ይገድሉናል፡፡»

ምዕራፍ 16
እምነቴን ስጠብቅ

ገዳዮቹ ስሜን ሲጠሩ ሰምቻቸዋለሁ፡፡

የፍርሃት መአት በውስጤ ተሠራጨ፡፡ ዲያብሎስም ድጋሚ በጆሮዬ አንሾካሾከ - አሁን የት እንዳለሽ አውቀውታል... አሁን የት እንዳለሽ አውቀውታል...

አእምሮዬ ወደ ድሮው ተመለሰና ራሴን ሳትኩ፡፡ ለምን ስሜን ተጣሩ - እዚህ እንዳለሁ እንዴት ሊያውቁ ቻሉ? ወደ መታጠቢያ ቤቱ እየመጡ ይሆን እንዴ?

አምላክን ለመጥራት ብሞክርም የምሰማው ብቸኛ ነገር ግን በቤቱ ከሚያስተጋቡት ከገዳዮቹ ክፉና አረመኔያዊ መዝሙሮች ጋር አእምሮዬን የተቆጣጠሩትን አሉታዊ ድምጾች ነው፡፡ ልብሶቼ በላብ ተጠምቀው እምነቴን ፍለጋ እፍጨረጨር ገባሁ፡፡

የመጡት በመቶዎች ሆነው ነው፡፡ ቁሱን የዛቻና የውንጀላ መዓት ያወርዱባቸዋል፡፡ «የት ነች?» ሲሉ አንባረቁባቸው፡፡ «እዚህ እንዳለች እናውቃለን፡፡ ፊልጓት... ኢማኪዩሌን ፊልጓት፡፡»

ከግንቡ በስተጀርባ በቁሱ መኝታ ቤት ናቸው፡፡ ከግማሽ ጋት ያነሰ ውፍረት ያለው ጭቃና ዕንጨት ይለያየናል፡፡ እርምጃዎቻቸው ቤቱን አንቀጠቀጡት፣ ገጀራዎቻቸውና ጦሮቻቸውም ከግንቡ ጋር ሲጋጩ ይሰማኛል፡፡

በረብሻው መካከል አንድ የቤተሰቤ ወዳጅ የሆነን ሰው ድምፅ መለየት ቻልኩ፡፡ «399 በረሮዎችን ገድያለሁ» በማለት ጉራውን ይነፋል፡፡ «ኢማኪዩሌ 400 ታደርግልኛለች፡፡ ይህም ቀላል የሚባል ቁጥር አይደለም፡፡»

በጥጋቷ እንደተሸሸግሁ ዲያብሎስ በጆሮዬ ይስቅብኛል፡፡ ስምሽን ያውቃሉ... እዚህ እንዳለሽ ያውቃሉ፡፡ አሁንስ አምላክሽ የት አለ?

ገዳዮቹ ቁሱን ተጫኗቸው፡- «ቱትሲዎቹ የት ናቸው? ካገኘናቸው ምን እንደምናደርጋቸው ታውቃለህ፡፡ የት አለች፤ ቁሱ፣ ኢማኪዩሌ የት ነች? መጨረሻ የታየችበት ስፍራ እዚህ ነው፡፡ የት ነው የደበቅሃት?»

መንፈሴ በፍርሃትና ጥርጣሬ ክንዶች ላይ ተመልሶ ወደቀ፡፡ እናም ገዳዮቹ መጀመሪያ በመጡበት ጊዜ ከፈራሁትም በላይ በጣም ፈራሁ፡፡ ድምጾቻቸው ሥጋዬን ሸንታተሩት፤ በመቀጣጠል ላይ ባለ ከሰል ላይ የተኛሁ ያህል ተሰማኝ፤ ሁለመናዬን የህመም አበላ ዋጠው፤ ሺ የማይታዩ መርፌዎች በሰውነቴ ላይ ተሰገሰጉብኝ፡፡ ቢሆንም ግን ለመጸለይ ምከርኩ፡- ውድ አግዚአብሔር፣ ስለ እምነቴ መድከም ማረኝ...

አምንሃለሁ… እንደምትምረንም አውቃለሁ፡፡ በዚህ ቤት ውስጥ ካለው ርኩሰ መንፈስ ታይላለህ፡፡

ገዳዮቹ ተንቀሳቃሽ ምስሉን ባየንበት ክፍል የቤት እቃዎቹን ያገላብጣሉ፤ የእኔንም ስም ደጋግመው ይጠራሉ፡፡ «ኢማኪዩሌን እንፈልጋታለን… ኢማኪዩሌን መግደያቸን አሁን ነው፡፡»

ጆሮዎቼን በእጆቼ ይገፍ ከገዳዮቹ ገጀራዎች አንዱ የኔ እንዲሆን፣ ጆሮዎቼንም ቆራርጬ መስማት እንዳቆም ተመኘሁ፡፡ «ወይ አምላኬ …» ጮክ ብዬ መጸለይ ጀመርኩ፤ ምንም ቃላት ግን ማውጣት አልቻልኩም፡፡ ለመዋጥ ሞከርኩ፤ ጉሮሮዬ ግን ተዘጋ፡፡ ምንም ምራቅ አልነበረኝም፤ አፌም እንደኩበት ደርቋል፡፡

ዓይኖቼን ጨፈንኩ፡፡ ብጠፋም ተመኘሁ፤ ድምጹ ግን እየጨመረ መጣ፡፡ ምንም ዓይነት ምኅረት እንደማያደርጉልኝ አውቃለሁ፡፡ አእምሮዬም አንድ ሐሳብ ብቻ ያስተጋባ ጀመር - *ኪያዙኝ ይገድሉኛል፡፡ ኪያዙኝ ይገድሉኛል፡፡ ኪያዙኝ ይገድሉኛል፡፡*

መጽሐፍ ቅዱሴን በአፌ ያዝኩና በጥርሶቼ መካከል ጥብቅ አድርጌ ነከስኩት፡፡ የእግዚአብሔርን ቃላት ልውጣቸው ፈለግሁ፣ ወደ ነፍሴ ጥግ ጭልጥ አድርጌ ማስገባትንም ተመኘሁ፡፡ ጥንካሬውን በድጋሚ መፈለግ አሻኝ፣ ለረጅም ጊዜ ሲያስቸግረኝ የነበረው አሉታዊ ኃይል ግን በአእምሮዬ አስፈሪ ምስሎችን ያሳየኝ ይዟል፡፡ ገዳዮቹ ሲያገኙኝ ምን እንደሚያደርጉኝ ታየኝ - ግርፋቱን፣ ማሸማቀቁን ብሎም ግድያውን አየሁት….

ተው እግዚአብሔር፣ እባክህ! በጸጥታ ጮህኩ፡፡ በዚህ ውስጥ እንዳልፍ ምነው *ፈለግህ? ለምን? ፍቅሬን ላንተ ለማሳየት ምን ላድርግ?* አንተው እንደምታድነን ለማመን እፈልጋለሁ፡፡ ከዚህ የበለጠ እምነት እንዴት ሊኖረኝ ይችላል*? በጣም* እየጸለይኩ *ነው፣* እግዚአብሔር፣ በጣም… ግን በጣም ቀርበዋል፣ በቃ በጣም ደክሜያለሁ! እግዚአብሔር ሆይ… ደካክሜልሃለሁ፡፡

ራሴን የሳትኩ መሰለኝ - በቤቱ ዙሪያ የሚሰማው የገዳዮቹ ጆሮን እንደ መብረቅ የሚያደነቁር ድምጽ እስኪቀዛቀዝና በሩቅ የሚሰማ ሁካታ እስኪሆን ድረስ ራሰን መግዛት የሚባል ነገር ከኔ ሸርተት አለ፡፡ ከዚያም ተኛሁ፤ የኢየሱስንም ጣፋጭ ሕልም አልም ገባሁ፡፡

ከሌሎቹ ሴቶች በላይም እንደ ላባ ተንሳፈፍኩ፡፡ ከበታቼ በወለሉም ላይ መጽሐፍ ቅዱሶቻቸውን በራሶቻቸው ላይ አድርገው እግዚአብሔርን ለምኅረት በመለማመን ሲንቀጠቀጡ አየኋቸው፡፡ ቀና ስል ኢየሱስን በወርቃማ ብርሃን ታጅቦ ከበላዬ ሲያንጎበጉብ አየሁት፤ እጆቹም ወደ እኔ ተዘርግተዋል፡፡ ፈገግ ስል ለሳምንታት

ኩርምት ከማለቴ የተነሣ በሰውነቴ ላይ የነበሩት ቋሚ ሕመሞች ጠፉልኝ፡፡ ምንም ዓይነት ረሃብ፣ ጥምም ሆነ ፍርሃት የለ - በጣም ሰላም ተሰማኝ... ደስም አለኝ፡፡

ከዚያም ኢየሱስ ተናገረ፡ «ተራሮች በእምነት ይገፋሉ፣ ኢማኪዩሌ፣ እምነት ግን ቀላል ቢሆን ሁሉም ተራሮች ይሄዳሉ፡፡ በኔ ካመንሽብኝ መቼም ቢሆን እንደማልተውሽ እወቂ፡፡ በኔ እመኚ፣ ምንም ዓይነት ፍራቻም ዓይኑርሽ፡፡ በኔ እመኚ፤ አድንሽማለሁ፡፡ መስቀሌን በዚህ በር ላይ ስለማኖረው አይደርሱብሽም፡፡ እመኚብኝ፤ ትኖሪማለሽ፡፡»

ወደ ወለሉ በድንገት ተመልሼ ሌሎቹን ተቀላቀልኩ፡፡ ዓይኖቻቸውን አሁንም እንደጨፈኑ ነው፤ የኔ ዓይኖች ግን በመታጠቢያ ቤቱ በር ፊት ለፊት ከግንብ ግንብ በተንጣለለው አንጸባራቂ ነጭ የብርሃን መስቀል ላይ አፍጥጠው በሰፊው ተከፍተዋል፡፡ ሳየውም አንጸባራቂው ኃይል ፊቴን ነካው፤ እንደ ጸሐይ ሁሉ ቆዳዬንም አሞቀው፡፡ በደመ-ነፍስም ገዳዮቹን የሚመልስ አንዳች መለኮታዊ ኃይል ከመስቀሉ እየወጣ እንደሆነ አወቅሁ፡፡ እንደምንጠበቅና ደኅና እንደምንሆን ተገለጠልኝ፤ ስለሆነም የአንበሳ ጥንካሬ እንዳለኝ ሁሉ ተሰማኝ፤ ዘልዬም ቆምኩ፡፡ አምላኬን በፍቅሩ ድጋሚ ስለነካኝ አመሰገንኩት፤ ከዚያም ሌሎቹን ቁልቁል አየሁኋቸው፡፡

በመታጠቢያ ቤቱ ቆይታዬ ለመጀመሪያና ለመጨረሻ ጊዜ አብረውኝ ባሉት ሰዎች ላይ ጮህኩባቸው፤ «ምንም አንሆንም! እመኑኝ... ሁሉም ነገር ጥሩ ይሆናል!»

የድምጼ ጉልህነት በፊታቸው ላይ እንደተሰነዘረ ጥፊ ሁሉ መታቸው፡፡ እንደ እብድ አይተውኝ ተንጠራርተው ወደ ወለሉ ሳቡኝ፡፡ ፈገግ አልኩ - ምንም እንኳን ከዚያ ወዲያ መስቀሉን በበሩ ላይ ማየት ባልችልም እዚያ እንዳለ ግን አውቃለሁ፡፡ ገዳዮቹ ከቤቱ ሄደዋል.... እየዘመሩ ሲሄዱም ሰምቻቸዋለሁ፡፡

ሌሊት ቄሱ ሊያዩን መጡ፡፡ «በቀጥታ የሄዱት ተንቀሳቃሽ ምስሉን ወዳሳየኋችሁ ስፍራ ነው» ሲሉ አብራሩልን፡፡ «ከፍሉን ገነጣጠሉት፡፡ ምንም ማግኘት ሳይችሉ ሲቀሩ ሠራተኛዬን በድብደባ ሊቦጫጭቁት ምንም አልቀራቸው፡፡ ይቅርታ ጠይቀው ሄዱ፡፡ ቢሆንም ይህ ስፍራ ለእናንተ ደህንነት ከአሁን በኋላ ጥሩ አይደለም፡፡ ሠራተኛዬን አባርሬዋለሁ ... አሁን ተናዷል፤ ጥርጣሬም ገብቶታል፡፡ ከሌሎቹ ሠራተኞች ጋር ጓደኛ ስለሆነ ከአሁን በኋላ በእርግጠኝነት ሁሉም እያንዳንዷን እንቅስቃሴዬን ይከታተላሉ፡፡ ብቻ የፈረንሳይ ወታደሮች ወደ አካባቢያችን በቶሎ እንዲደርሱ ተስፋ እናድርግ፡፡»

ቀጣዩን ሳምንት በሙሉ ተደናግጠን ሰነበትን፡፡ ገዳዮቹ እንደገና ብርበራ አደረጉ፤ የቄስ ሙሪንዚን መኝታ ቤትም የተደበቀ ቱትሲ ፍለጋ አተራመሱት፡፡ እንደገና እንደሚመለሱም አስጠነቀቁ፡፡

ቄሱ ከትትል ውስጥ እንደገቡ በጣም ሠግተው ምግብ የሚያመጡልንን ጊዜ ቁጥር ቀነሱ፡፡ ተርቦ መሞትን ከገዳዮቹ እንደምናመልጥበት እርግጠኛ መንገድ ሆኖ አገኘነው እያልን ለመቀለድ ሞከርን፡፡ ችጋሩ ግን ክፉኛ ጋጠን፡፡

በሐምሌ ወር መጀመሪያ ላይ ከቀሪዎቹ ወንድ ሠራተኞች አንዱ የመኝታ ቤቱን በር ሲያንኳኳ ሰማነው፡፡ «ቄሱ እዚያ ያለው መታጠቢያ ቤት ውስጥ ከገባሁ ረጅም ጊዜ ሆነኝ እኮ፡፡ ለምን አሁን አላጸዳልዎትም?»

አከርካሪዎቻችን ድንጋይ ሆኑ ... ይህ ሥቃያችን አያልቅ ይሆን?

«የመታጠቢያ ቤቱ ነገር አያሳስብህ» ሲሉ ቄሱ መለሱ፡፡ «እኔ ራሴ አጽድቼዋለሁ፡፡»

«እንዴ እርስዎ ያንን ማድረግ የለብዎትም - ያ እኮ የኔ ሥራ ነው፡፡ ያስገቡኝና ጸሐይ ላስመስልልዎት፡፡»

«አይ ቁልፉ ጠፍቶብኛል፤ ስለዚህ እዚያ ያለውን መጸዳጃ እየተጠቀምኩት አይደለም... አሁን ወዲያ ሂድልኝ፡፡ መረበሽ አልፈልግም፡፡»

«ምን አልባት እኮ ያለ ቁልፍም ልከፍተው እችላለሁ፡፡»

«ሂድ! መረበሽ አልፈልግም አልኩህ አይደለም ወይ?»

በሦስት ወራት ውስጥ ሰው መታጠቢያ ቤቱን ላጽዳ ብሎ ሲጠይቅ የመጀመሪያው ነው፡፡ ስለዚህ ሠራተኛው እኛ የት እንዳለን የደረሰበት ይመስላል፡፡ ወደ ገዳዮቹ ሄዶ በትክክል የት እንደሚፈልጉ እንደሚነግራቸው አውቀንና በቤቱ ያላዩትን ብቸኛውን ክፍል እንደሚጠቁማቸው ጠርጥረን በጭንቀት የምናደርገው ነገር ጠፋን!

ሠራተኛው ከሄደ በኋላ ቄሱ እኛ ጋ መጥተው ወዲያውኑ ገዳዮቹ ጋ ይሄዳል ብለው እንደማያስቡ ነገሩን፡፡ «የባለፈውን ሠራተኛ ቱትሲዎችን እንዲያዩ በጠቆማቸው ስፍራ ቱትሲዎች ስላላገኙ ሊገድሉት ምንም ያህል አልቀራቸውም» ሲሉ አብራሩ፤ «ስለዚህ ይህኛው ማረጋገጫ እስኪያገኝ ድረስ ይጠብቃል፡፡ ወደነሱ ዛሬ ላይሄድ ይችላል፣ ግን በእርግጠኝነት በቶሎ ይሄዳል፡፡»

ጊዜያችን ሳንጠቀምበት እንዳይቃጠልብን በመፍራት እርስ በርሳችን ተያየን፡፡

«ዛሬ ጠዋት የፈረንሳይ ወታደሮች በዚህ አካባቢ የተረፉ ቱትሲዎችን እየፈለጉ እንደሆነ ሰምቻለሁ - ዛሬ አናግራቸዋለሁ፡፡ አደራ እኔ በምሄድበት ጊዜ በጣም ጸጥ በሉ» አሉ ቄሱ ከቤቱ ፈጥነው እየወጡ፡፡

እንደሄዱም የቤት ሠራተኛው ያሠቃየን ጀመር፡፡ ቀኑን ሙሉ ከመታጠቢያ ቤቱ መስኮት ውጪ ሲመላለስ ሰማነው፡፡ ድምፅ ወይንም ማናቸውንም እንቅስቃሴ

ለመስማት እንደሆነ አውቀንበታል። ወደ ገዳዮቹ ከመሄዱ በፊት ጥርጣሬዎቹን ሁሉ ለማረጋገጥ ይሞክራል። ለሰዓታት አንዲት የሰውነት ክፍል እንኳን አላንቀሳቀስንም።

አንዴማ በርጩማ ወይንም ጠረጴዛ ነገር ከመስኮቱ በታች አስጠግቶ ሲንጠላጠልና የእርሱም ጥላ ከመጋረጃው ትይዩ ሲታየን ራሳችንን ልንስት ምንም ያህል አልቀረንም። እግዚአብሔር ይመስገን መስኮቱ አልተደረሰለትም። ቀኑን ሙሉ ግን እዚያው ሲጠብቅና ሲያዳምጥ ቆሞ ዋለ። ምንም እንኳን ቀኑን ሙሉ በደም ስሬ በተረጨው የፍርሃት ፈሳሽ ምክንያት ቅፍፍ ብሎኝ ብውልም በኋላ ላይ ልጁን አንድ ሰው ጠራውና ትንሽ መላወስ ቻልን ።

ቄሱ በዚያን ምሽት ጥሩ ዜና ይዘውልን ተመለሱ። ምን አልባት ደርሰውኝ ከሚያውቁት ወሬዎች ሁሉ እጅግ ተወዳጁን መሆኑ ነው። «የፈረንሳይ ወታደሮችን አግኝቻቸው ስለ እናንተ ነገርኳቸው። ያሉበት ስፍራ ከዚህ አይርቅም፤ ዛሬ ሌሊት እነርሱ ጋ እንድወስዳችሁም ነግረውኛል፣ ሌሊት ስምንት ወይንም ዘጠኝ ሰዓት አካባቢ።»

ጆሮዎቻችንን ማመን አልቻልንም - በስተመጨረሻ ይሄው መታጠቢያ ቤቱን ለቀን ልንሄድ ነው! የተመካከርን ይመስል ባንድነት «ተመስገን አምላኬ» በማለት በአንድ ጊዜ አንሾካሾክን።

ቄሱ ግን ባንዴ ስሜታችንን አንኮታኮቱት። «አዎን፣ ተመስገን አምላኬ» አሉ። «እጅግ የሚዘገይባችሁ አይሆንም ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። ወታደሮቹን ትቼ ከሄድኩ በኋላ አንድ ወዳጄን አግኝቼው ገዳዮቹ መልሰው ወደኔ ቤት ለአሰሳ ሊመጡ እንደሆነ ነገረኝ። እዚህ የሚመጡት አንድም ዛሬ ማታ አለያም ነገ ጠዋት ነው - እስኪ ነገ በሆነልን ብላችሁ ጸልዩ።»

በጽኑ ጸለይን።

የምንሸከፈው ኮተት የለንም - ያሉን ብቸኛ ንብረቶች ለሦስት ወራት በተከታታይ የለበስናቸው ልብሶች ናቸው። አሁንም ቢሆን መታጠብ አይታሰብም። ቢሆንም ግን ጸጉራችንን እርስ በርሳችን በመጎናጎን ራሳችንን አረካን። የፈረንሳይ ወታደሮችን ስናገኝ በተቻለ መጠን ቆንጆና የሚቀበሉን ሆነን ለመቅረብ ፈልገናል። ባለንበት ሁኔታ ራሳችንን ማሰማመር አለመቻሉ ምንም አልገባንም።

ቄስ ሙሪንዚ ከሌሊቱ 8፡00 ላይ መጡና ልጆቻቸውን ቀስቅሰው ስለኛ እስኪነግሯቸው ድረስ በመኝታ ቤታቸው እንድንጠብቅ ነገሩን። እየጠበቅን ሳለ መልካችንን በመኝታ ቤቱ መስተዋት አየን። ከደረስንበት ጊዜ ጀምሮ የገጽታችንን ነጸብራቅ ስናይ የመጀመሪያችን ሲሆን እንዴት ክው እንዳልን መግለጽ እጅግ ይከብደኛል! የቆሙ ሙታን መስለናል። ጉንጮቻችን ሟሽውና ዓይኖቻችንም ወደ

ሰገባዎቻቸው ተደብቀው ራሶቻችን ቀፎ መስለዋል፡፡ የጎድን አጥንቶቻችን አግጠው ወጥተው ልብሶቻችንም መወልወያ ላይ እንደተንጠለጠለ ማግ ሁሉ በላያችን ተሰቅለዋል፡፡ ሁለመናችን ሟቧል! ወደ መታጠቢያ ቤቱ ስገባ 52 ኪሎግራም እመዝን ነበር፡፡ ስወጣ ግን 30 ኪሎግራም ሆኛለሁ፡፡ ልሞት ምን ቀረኝ ቆይ! ሁላችንም እንባ እንባ አለን፡፡

ቄሱ ከአሥር ልጆቻቸው ጋር ሲመለሱ፣ ሁሉም (ከለችምና ከዱዜንጂ በስተቀር) በፍጥነት ወደኋላቸው አፈገፈጉ፡፡ ስለእውነት ተደናግጠዋል፤ እጅጉን ግራ ተጋብተዋል፡፡ ሴቶቹ ልጆች ማልቀስ ጀመሩ፤ አንደኛዋ እንዲያውም ከቤቱ «ጭራቆች! የቱትሲ ጭራቆች! ከሞቱበት ተነሥተው ሊገድሉን መጡ!» ስትል ቄሱ ዝም እንድትልና እንድትረጋጋ ነገሯት፤ ከዚያ በኋላም ምኖች እንደሆንን ገለጹላቸው፡፡

አንዳቸውም እነርሱ ሳያውቁ ይህን ያህል ጊዜ እዚያ መኖራችንን ማመን ተሳናቸው፡፡ እውነትም ሰዎች ስለመሆናችን ራሳቸውን ለማሳመን ይረዳቸው ዘንድ ነካኩን - የፊትና የጎድን አጥንቶቻችንንና ከርኖቻችንን ደባበሱን፡፡ መቶ ጥያቄዎች አሏቸው - «የት ነበራችሁ? እዚያ እንዴት ለሁላችሁም ሊበቃችሁ ቻለ? ምን ትበሉ ነበር? እዚያ ለምን ያህል ጊዜ ቆያችሁ? እንዴት እንደዚያ ዝም ልትሉ ቻላችሁ? ገላችሁን ትታጠቡ ነበር ወይ? ኢታወሩም ወይ? ቁጭ ብላችሁ እንዴት እንቅልፍ ሊወስዳችሁ ቻለ?»

ልንመልስላቸው ብንሞክርም ከመቆማችን የተነሣ ደከመን፤ ጡንቻዎቻችንና መጋጠሚያዎቻችን ወለል ላይ ብዙ ወራት ካሳለፋችሁ በኋላ ለምን ቆማችሁ እያሉ አፍ አውጥተው ጮሁብን ማለት እችላለሁ፡፡

ቄሱ ለልጆቻቸው በደንብ እንዲያዩን ነገሯቸው፡፡ «በእግዚአብሔር ጸጋ ግን አንዳችሁ እንኳን እዚያ ከደረሳችሁ» በማለት አስታወሷቸው ልጆቻቸውን፡፡ «ዕድል የገፋቸውን እንደነዚህ ሴቶች ያሉትን በችግር ጊዜ ለመርዳት ዕድሉ ካጋጠማችሁ መተባበራችሁን እርግጠኛ ሁኑ - የራሳችሁን ሕይወት አደጋ ላይ እንድትጥሉ የሚያስገድዳችሁ ቢሆንም እንኳን፡፡ ፈጣሪ እንድንኖር የሚፈልገው እንዲህ ነው፡፡»

ልቤ ለቄሱ በመጠኑ ተለሳለሰች፡፡ ባለፉት ጥቂት ወራት በእርግጠኝነት በአመላቸው የተናደድኩባቸው በርካታ ጊዜያት ነበሩ፡፡ የተናገሯቸውም ድንቁርና የሚንጸባረቅባቸው የተወሰኑት ነገሮች ስሜትን ጎዳሁ አልጎዳሁ ብለው እንደማይጨነቁና ጭካኔ እንደሚታይባቸው የሚያስረዱ ነበሩ ... ቢሆንም ለእኛ ሲሉ ሁሉ ነገራቸውን አደጋ ላይ ጥለዋል፡፡ የሕይወቴን አዲስ ምዕራፍ ልጀምር እዚያ እንደቆምኩ በጣም አመሰገንኩ፡፡ አምላክንም እኛ ከሄድን በኋላ እኘህን ሰው እንዲጠብቅልን ለመንኩት፡፡

ልጆቹ አባታቸውን ኩራት፣ እኛን በሃዘኔታ አዩን - ከሴምቤባ በቀር ሁሉም መሆናቸው ነው። ሴምቤባ ከሳምንታት በፊት ለአባቱ ቱትሲዎች ሊገደሉ ይገባቸዋል ሲል የሰማነው ልጃቸው ነው። አሁን ይኸው ጥግ ላይ ቆሞ ወለሉ ላይ በንዴት አፍጥጧል። በወቅቱ አንድ ቀን እርሱ የእግዚአብሔርን እውነትና ምጎረት እንዲያገኝና ከስፍራው ሳንሄድም ለገዳዮቹ ስለኛ እንዳይናገር ጸልዬአለሁ።

መጀመሪያ ስታየን ከቤቱ ሮጣ ወጥታ የነበረችው ሽምቄ የተባለችው ልጃቸው አንድ ፎጣና ከሹራቦቿ አንዱን እንድለብሰው ሰጠችኝ። በተቻላት መጠን ጥብቅ አድርጋ ካቀፈችኝ በኋላ እንደምትጸልይልኝ ነገረችኝ። ከዚያ ሁሉ መለየትና መቸገር በኋላ ፍቅር የሚለግሰኝ ሰው ማግኘቴ በቃላት ከምገልጸው በላይ ውስጤን ነካኝ።

ስምንታችን የቀሩትን የቄሱን ልጆች ከተሰናበትን በኋላ ቄሱ ከመታጠቢያ ቤቱ ወደ ንጹሑ የምሽት አየር፣ ወደ ውጪ፣ አወጡን።

ክፍል ፫

አዲስ መንገድ

ምዕራፍ 17
የነጻነት ሕመም

የምሽቱ ድባብ የማልቆጣጠረው ስሜት አሳደረብኝ። የአየሩ ቅዝቃዜ ቆዳዬን ሲነካው፣ ለሳንባዎቼ አየሩ ሲቀላቸው፣ በዓይኔ ላይ የሚጨፍሩት እልፍ አዕላፍ ከዋክብት በውበታቸው ሲያፈዙኝ ነፍሴን «ተመስገን አምላኬ!» ብላ እንድትዘምር አደረጓት።

«ምን ላይ ነው ያፈጠጥሺው? እንሂድ እንጂ - በአስቸኳይ መሄድ አለብን!» ሲሉ የመጀመሪያዋን የነጻነት መጠጥ እንደተነነጨሁ ቄስ ሙሪንዚ ትዕግሥት አጥተው ሾር ብዬ እንድሄድ ተናገሩ። ቄሱ ከሌሎቹ ሴቶችና ወደ ፈረንሳዮች ምሽግ አብሮን ሊሄድ ከተነሣው ከዮሃንስ ጋር በሩ ጋ ይጠብቁናል። ዮሃንስ በጣም አረፈደ እንጂ መባነኑና እፊት እፊት ማለቱ ባልከፋ። በዚህ ጊዜ ከዘር ጭፍጨፋው መትረፌንም ሆነ ንጋትን እንደገና ለማየት መቻሌን አላወቅሁም - የግንኙነታችንም መሞት አልታወቀኝ።

ቄሱ በራቸውን ሲከፍቱት ከቤት ወንድ ልጆቻቸው (ከሴምቤባ በስተቀር) ጦሮች፣ ቢላዎችና ቀስቶች ይዘው ወጡ። ዙሪያችንን በሚገባ ከበው በሩን አስወጡን። ከጠርጣራ ወንድ የቤት ሠራተኞቻቸውና ክፉ ጎረቤቶቻቸው አደገኛ ዓይኖች ከለሉን።

ከዚያም ወደ ውጪ ወጣንና ወደ መታጠቢያ ቤቱ ከሦስት ወራት በፊት ባመጣኝ በአቧራማው የእግር መንገድ በፍጥነት ተራመድን። ዓይኖቼ ጨለማውን እየተላመዱት ሲሄዱም ቄስ ሙሪንዚም ሆኑ ዮሃንስ እንደታጠቁ አየሁ፤ ዮሃንስ ረጅም ጦር የያዘ ሲሆን ቄሱ በበኩላቸው ጠመንጃቸውን በትከሻቸው አንግተዋል። የገዳዮች ቡድን መንገዳችን ላይ ቢያጋጥመን ምን ሊያደርጉ እንደሚችሉ አሰብኩ።

ሰዎች በመንገዱ ሌላኛው አቅጣጫ ከጨለማው ውስጥ ብቅ ሲሉ በድንገት አየናቸው። ምን አልባትም 60 የሚሆኑ ኢንተርሃምዌዎች በሁለት መስመሮች በሰልፍ ይመጣሉ። አስፈሪ የደንብ ልብሶቻቸውን ያልለበሱ ቢሆንም ቅሉ ትዕይንቱ ያስበረግጋል፦ እስካፍንጫቸው ታጥቀው በፍጥነት ይጓዛሉ፤ ገጀራዎችን፣ ጠመንጃዎችን፣ ቦንቦችን፣ ጦሮችንና ረጃጅም ማረጃ ቢላዎቻቸውን ይዘው ወደ እኛ በመጠጋት ላይ ናቸው - አንደኛው እንዲያውም ቀስት ይዟል።

በአጠገባቸው በጣም ተጠግተን ስለሄድን እንዲያውም የሰውነታቸውን ጠረንና ከትንፋሻቸው የሚመጣውን የሚተናፈግ አልኮል ሳይቀር ማሽተት ችያለሁ። በሚገርም ሁኔታ በመታጠቢያ ቤቱ ከእነርሱ ተደብቄ ከነበርኩበት ጊዜ ይልቅ በአጠገባቸው ሳልፍ በአንጻራዊነት ፍርሃቴ ቀንሷል። በዚህም ጊዜ እግዚአብሔርን በደኅና እንዲያቆየንና ፍራቻዬን እንዲያረግብልኝ ለመንኩት።

ሌሎቹ ሴቶችና እኔ ኢንተርሃምዌዎቹ ሴቶች መሆናችንን እንዳይለዩ በማለት በቡድን አጀባችን መካከል ራሳችንን ዝቅ አደረግን፡፡ ያለ ምንም ችግርም አለፍን፡፡ እንዲያውም የተወሰኑት ገዳዮች ሰላምታ አቀረቡልን፤ ሲያልፉም ለዮሃንስና ለቄሱ መልካም ዕድል ተመኙላቸው፡፡ አንድም እኛን ሌሊት ድረስ ቆይተን እያደንን ያለን ገዳዮች አድርገው አስበውናል አለያም አምላክ ዓይናቸውን አሳውሯቸዋል … ሁለቱም ምክንያት እንደሆነ አሰብኩ፡፡ በተጨማሪም አሁን ባለው የዘር ፍጅቱ ደረጃ ይህን ያህል ቁጥር ያላቸው ቱትሲዎች በአንድ ቦታ በሕይወት ይኖራሉ ብለው አልጠበቁም፤ ወይንም አላመኑም፡፡ በየመንገዱ አስከሬኖች ስለወደቁ እንደዚያ ብለው ለማመን ጥሩ ምክንያት ነበራቸው፡፡

አምላክ ለጸሎቴ ምላሽ ሰጠኝ፡፡ ለገዳዮቹ ያለኝንም ፍራቻ አሸቀንጥሮ ጣለልኝ፡፡ ግን ከሁኔታው ሳየው ጌታ ለቄስ ሙሪንዚና ለዮሃንስ ተመሳሳይ በረከት ያጋራቸው አይመስልም፡፡ ኢንተርሃምዌዎችን በማግኘታችን ሁለቱም ተደናግጠዋል፡፡ ዮሃንስና ቄስ ሙሪንዚ ገዳዮቹ ከእይታችን እንደተሰወሩ የገቡበትን ጣጣ እንደገና አጤኑት፡፡

ቄሱ «እናንተ ሴቶች ከዚህ በኋላ ብቻችሁን ሂዱ» አሉን፡፡ «ፈረንሳውያኑ ከዚህ ቅርብ ናቸው… ሂዱ ቀጥሉ፤ ከእይታችን እስክትሰወሩ እናያችኋለን፡፡»

ቄሱና እኔ በፍጥነት ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ እርሳቸው፣ ወንዶች ልጆቻቸውና ዮሃንስ ከመንገዱ ወደ ጥሻ ውስጥ ለመደበቅ በችኮላ ሄዱ፡፡ ያኔ ሌሎቹ ሴቶችና እኔ ሙሉ በሙሉ ግልጽ ቦታ ላይ ስለሆንን የምናባክነው ምንም ዓይነት ጊዜ አልነበረንም፡፡ የፈረንሳውያኑ ምሽግ 500 እርምጃዎች ገደማ ይርቃል፤ ስለሆነም እግሮቻችን በቻሉት መጠን በፍጥነት ተጓዝን፡፡

የተተወ የወንጌላውያን ትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ በተቋቋመው ምሽግ ጋ ስንደርስ ልቤ ድው ድው ይል ጀመር፡፡ የተቀረው ቡድን ከዋናው በር ፊት ለፊት በጣም ፈርቶ ተመስጎ ሳለ እኔ በቻልኩት መጠን በሩን እደበድብና በጣም ጮኬ «እባካችሁ እርዱን! እባካችሁ እገዛችሁን እንፈልጋለን!» እል ጀመር፡፡

ከሹክሹክታ በላይ ከተናገርኩ በጣም ረጅም ጊዜ ስለሆነኝ ለመጮህ ካደረግሁት ጥረት የተነሣ ጉሮሮዬን አመመኝ፡፡ ድምጼ የታፈነና በጣም ዝግ ያለ ስለሆነ አይሰማም ለማለት ይቻላል፡፡ ሊያድነን የሚጠብቀን ማንም ሰው ሳናገኝ ስንቀር ሴቶቹ በፍርሃት ራዱ፤ ለቅሶና እዬዬም ጀመሩ፡፡ ከአፍታ በኋላ ስድስት ወይም ሰባት ወታደሮች መትረየሶቻቸውን ወደ እኛ ደግነው በአጥሩ በአንደኛው አቅጣጫ ብቅ አሉ፡፡ ፈረንሳይኛ የምናገረው እኔ ብቻ ስለሆንኩ ባልንጀሮቼን ዝም አስባልኩና ለወታደሮቹ ስለማንነታችንና ስለአመጣጣችን ነገርኳቸው፡፡

ወታደሮቹም በጥርጣሬ ተመለከቱን፣ ጠመንጃዎቻቸውንም እንዳቀባበሉ ናቸው፡፡

«እውነት ነው! የነገርኳችሁ ሁሉ እውነት ነው... ታድኑን ዘንድ እናንተን ስንጠብቅ ቆይተናል» አልኳቸው በተስፋ መቁረጥ::

በቡድኑ ውስጥ ካሉት ወታደሮች ትንሹ፣ ኮስታራው፣ መልኩ ፈገግ ያለውና ጸጉሩን የተላጨው ሰውዬ ወደ ዋናው በር መጥቶ በፊታችን ላይ ባትሪ አበራብን:: የአፍንጮቻችንን ቅርጽ እየተመለከተ እንደሆነ ግልጽ ነው:: ነባሩ አስተሳሰብ ሁቱዎች ደፍጣጣ ቱትሲዎች ደግሞ ሰልካካ አፍንጫ አላቸው የሚል ነው:: ስለሆነም ፈተናውን አልፈን ሳይሆን አይቀርም በሩን ከፍቶ አስገባን:: ይሁን እንጂ መታወቂያ ደብተሮቻችንን ለማየት ሲጠይቀንም መሣሪያውን እንደደገነ ነው::

ሴቶቹ በኃይል ሲተነፍሱ ይሰማኛል - ማናቸውም ቢሆኑ መታወቂያዎቻቸውን አልያዙም:: በዚህም ምክንያት ፈረንሳውያኑ እዚያው የሚረሽኗቸው መስሏቸዋል:: ደግነቱ በኔ በኩል መታወቂያዬን ከሦስት ወር በፊት ቤቴን ለቅቄ ስወጣ በኋላ ኪሴ ይዤዋለሁ:: ወታደሩ ሑቱሲ የሚል ቃል ከዳር እስከዳር የታተመበትን የኔን መታወቂያ አይቶ በአዎንታ ራሱን ነቀነቀ:: ወዲያውኑ ለሌሎቹ ሴቶች በእርግጠኝነት «ምንም የምንሆን አይመስለኝም» ስል አረጋገጥኩላቸው::

ለወራት የታመቀ ፍራቻ፣ ብስጭትና ሥጋት ከነፍሳችን ወንዝ ፈሰሰ፤ በውስጣችን ያለው የስሜት ግድብ ፈረሰ፤ የተወሰኑት ሴቶች ሊቆጣጠሩት በማይችሉት መልኩ አለቀሱ:: የወታደሮቹም አቀራረብ ከዚያ በኋላ ተቀየረ - ድምጻቸው በደግነትና በያገባኛል ስሜት ተሞልቶ ጠመንጃዎቻቸውን ዝቅ አድርገው በሐዘኔታ ያነጋገሩን ጀመር:: በወራት ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ያየነው የታሸገ ውሃና አይብ ተሰጠን:: ቁሱ እንደገመቱት ፈረንሳውያኑ እንደማይገድሉን አውቀን በጣም ሰፍ ብለን መጉረስ ጀመርን::

«አይዟችሁ ምንም ችግር የለም» አለ ትንሹ ወታደር:: «ከዚህ በኋላ ቅንጣት ታክል ልትጨነቁ አይገባችሁም ... ቅጥፓታችሁ አክትሟል:: ማንም ሰው እንዲጎዳችሁ አንፈቅድም:: ገባችሁ? ምንም ሥጋት አይግባችሁ፤ እንንከባከባችኋለን::»

ለሌሎቹ ተረጎምኩላቸው፤ ወዲያውኑም ሁላችንም እናለቅስ ገባን:: ሁሉ ነገር አብቅቶለታል የሚለው ነገር ግን እውነት አይመስልም:: ለማንኛውም ገዳዮቹ ከእንግዲህ ወደ እኛ እንዳይቀርቡ እንደሚያደርጉ ቃል እየገቡልን ባሉ ትልልቅ መሣሪያ በያዙ የሠለጠኑ ወታደሮች ተከበናል::

ስንረጋጋ አዳኞቻችን ያለነው በጊዜያዊ የመስክ ማቆያ ውስጥ እንደሆነና በመገናኛ ተደዋውለው የጭነት ተሽከርካሪ አስመጥተው በአሥራ ስድስት ኪሎሜትር ርቀት ላይ ወደሚገኘው ዋና ምሽጋቸው እንደምንወሰድ አብራሩልን:: ተሽከርካሪው እስኪመጣም ትንሽ ማንቀላፋት እንዳለብን ነገሩን::

ከሌሎቹ ተለይቼ ሄድ ብዬ ለረጅም ጊዜ አጥቼው የነበረውን ነገር ሳጣጥም ቆየሁ - አንድ አፍታ ብቻዬን መሆንን። መሬቱ ላይ ተኝቼ በዙሪያዬ ካለው ከሁሉም ነገር ጋር እነካካ ጀመር - አለቶቹ ጀርባዬን እየወጉት፣ ጣቶቼ እርጥቡን መሬት ነክተው፣ ደረቆቹ ቅጠሎች ጉንጩን እየወጋጉት፣ በጨለማ የሚዘዋወሩት እንስሳት ድምፅ እየተሰማኝ። አቤት! በሕይወት መትረፌ ይገርማል።

እንደገና በምሽቱ ሰማይ ላይ አፍጥጬ የጌታ ፍጥረት በሆኑት እልቆ መሳፍርት የሌላቸው ከዋክብት ወተት መሰል ድምቀትና አስደማሚ ውበት ተመሰጥኩ። ጉልሁ የከዋክብቱ ብርሃን የመጣንበትንና ወደ ቤቴ የሚወስደውን መንገድ ማየት አስቻለኝ - ጭራሽ ቤት ካለኝ። የቤተሰቤ አባላት በደኅና የሆነ ቦታ ተደብቀው ይሆን? ብዬ አሰብኩ። ወይስ ወደ ቀጣዩ ሕይወት ሄደው ከእኔ በላይ ባለው ዘለዓለማዊ አጽናፈ-ዓለም በሌላኛው አቅጣጫ የሆነ ቦታ ይሆኑ?

አትኩሮቴን እንደገና ወደ መንገዱ መለስኩ። ወንድሞቼና እኔ ይህን መንገድ ተከትለን እንዴት ወደ ፈለግነው ስፍራ እንሄድ እንደነበር አሰብኩ። በልጅነታችን ጠዋት ወደ ኪቩ ለመሞኘት፣ ወደ ትምህርት ቤት፣ እሁድ ወደ ቤተክርስቲያን፣ ጓደኞቼንና ዘመዶቼን ለመጠየቅ፣ በክረምት እረፍት አስደናቂ ተግባራትን ወደምንፈጽምበት ስፍራ ለማምራት ብቻ ይህ መንገድ ወደምወደው ቦታ ሁሉ ያስኬደኝ ነበር። በሕይወቴ ሁሉ መንገዱ ተመላልሷል፤ ሆኖም ያ ሕይወት አልፏል። መንገዱ አሁን የገዳዮችና የአስገድዶ ደፋሪዎች መፈንጫ ሆኗል። በመጭዎቹ ሰዓታትም ሆነ ቀናት ውስጥ ምንም ይከሰት ምን ነገሮች እንደነበሩት እንደማይቀጥሉ ቀስ በቀስ ሲገለጥልኝ በጥልቅ ብስጭት ውስጥ ገባሁ። ዓይኖቼን ጨፍኜ ለእግዚአብሔር አዲስ የምሄድበት መንገድ የመፈለጉ ሥራ የእርሱ እንደሆነ ነገርኩት።

ተንቀጠቀጥኩ። ቀዝቃዛው አየር ቆዳዬን እንዲያሸበሽብ ሲያደርገው ከዚያን ጊዜ በኋላ በተጨናነቀውና በትንፋግ በተሞላው መታጠቢያ ቤት ውስጥ እንዳልሆንኩ አስታወሰኝ። በጨለማው የተቀመጡ ሁለት ወንዶችን ድንገት እንኳን ሳገኝ በፍጹም አልፈራሁም።

አንደኛው በድንጋጤ ድንገት ቀጥ ብሎ ቆሞ ከአፍታ በኋላ «ኢማኪዩሌ ነሽ?» አለኝ።

«ገሪን ፖል?»

«እንዴት በሕይወት ልትተርፊ ቻልሽ?»

«አምላክ አተረፈኝ። አንተስ እንዴት ተረፍክ?»

«አምላክ አተረፈኝ፡፡»

«እንኳን አየሁህ!»

«እንኳን አየሁሽ!»

በንግግራችን አስቂኝ አካሄድና እንደገና ከጓደኛ ጋር ጮክ ብሎ ማውራት እንዴት አስቂኝና አስደናቂ ነገር እንደሆነ ሳስበው ልስቅ ቃጣኝ፡፡ ዣን ፖል የወንድሞቼ ጥሩ ጓደኛ ነው፡፡

«ጤና ይስጥልኝ ዣን ባፕቲስት፤ እንኳንም አገኘሁህ» አልኩት ለተቀመጠው የዣን ፖል ወንድም፡፡ ጅን ባፕቲስት አልመለሰልኝም፡፡ የዚህንም ምክንያት ያየሁት በርከክ ብዬ እጁን በሰላምታ ስጨብጠው ነው፡፡ በልብሱ ውስጥ ድብቅ የሚል አንድ የጣት አንጓ ያህል ርዝመት ያለው የጠገገ ቁስል በአንገቱ ላይ አለበት፡፡ ቁስሉም የተቆጣ፣ ነጣ ያለ ቀለም ያለውና ከጥቁር የቆዳ ቀለሙ ጋር ያለው ተቃርኖ ስቅጥጥ የሚያደርግ ነው፡፡ በራሱም ላይ ትልቅ ጠባሳ ይታያል፡፡ ገመምተኛ መሆኑ ያስታውቃል፡፡ እንደዚያ ተመትቶ እንዴት እንደተረፈም ገረመኝ፡፡

«አሁን ብዙም አይናገርም… በጣም አዝኗል» አለ ዣን ፖል በቀስታ፡፡

ዣን ፖል ራሱ ሰቀቀኑ በጣም የሚታይበት ቢሆንም ተቀምጠን አንዳንድ ወሬ አወራን፡፡ የት እንዳሳለፍኩና በቁሱ ቤት የነበረኝን ጊዜ ገለጽኩለት፡፡ እርሱም በሰሜን ዘር ማጥፋቱ በመጠኑ እንደቆመና ኪጋሊም በአማጽያኑ ቁጥጥር ስር እንደዋለች፣ እኛ የነበርንበት የኪቡዬ ግዛት ግን እስከዚያን ጊዜ ድረስ የአደጋ ቀጣና እንደሆነ አወጋኝ፡፡

«ኪጋሊ ተያዘች?» ስል ጠየቅሁት ተደናግጬና ተደስቼ፡፡

«አዎ፣ አሁንም ቢሆን ግን ብዙ ግድያ አለ» ሲል መለሰልኝ፡፡ «በእርግጥ እዚህ አካባቢ ከበፊቱ እንዲያውም መጥፎ ነው፡፡ ጦርነቱ በጣም እየከፋባቸው ሲመጣ እነርሱም እጅግ እየባሰባቸው መጣ፡፡ ተደናግጠዋል፡፡ በጣም ብዙ ቱትሲዎችን ስላረዱ አሁን ተጨማሪ የሚገደል ማግኘት አልተቻላቸውም፡፡

«ዣን ፖልንና ወንድሙን በምሽጉ ውስጥ በማየቴ ተገርሜያለሁ፤ ምክንያቱም ሁቱ ይመስለኝ ስለነበር፡፡ በጣም ጥቁሮች፣ አጠር ያሉና አፍንጫቸው ድፍጥጥ ያሉ ናቸው - በአውሮፓውያን አስተያየት ትክክለኛው የሁቱ ገጽታ፡፡ ለብዙ ትውልዶች የተካሄዱ የእርስ በርስ ጋብቻዎች ሃሳቡን ያረጀ ያፈጀና ባያሌው በጥላቻ ላይ የተመሠረተ ስላደረጉት ከአሁን በኋላ ምንም ትክክለኝነት የለውም፡፡ ግን ዣን ፖል ሲያብራራ ሁቱ መምሰላቸው በሕይወት የመኖራቸው አንዱ ምክንያት መሆኑን ይናገራል፡፡ «ያ … እና የአንድ ገዳይ ደግነት» አለ በቤተሰቡ ላይ የሆነውን ከመናገሩ በፊት፡፡

«ጎዳዮቹ የርዕሰ-ብሔሩ ጠያራ ከተመታ ከሳምንት በኋላ መጡ፡፡ ከኛ ጥቂት ቤቶችን አለፍ ብሎ የሚኖረውን ሁቱውን ጓደኛዬን ሎሬንትን ልጠይቅ ሄጀ በወላጆቼ ቤት መድረሳቸውን ሰማሁ፡፡ ሦስት መቶ የሚሆኑ ጎዳዮችን አየሁ - አብዛኞቹ ጎረቤቶቻችንና ወዳጆቻችን ናቸው፡፡ የፊተኛውን በር ሰብረው ገብተው ሁሉንም ሰው ከታተፉት - ወንድሞቼን፣ አራቱን እህቶቼን፣ እናቴንና አባቴን፡፡ ሁሉንም ገደሉ ... ቢያንስ የገደሉ መሰላቸው፡፡ የጊርን ባፕቲስት ሕይወት ግን አልጠፋችም ነበር - ቢሆንም ታዲያ በእጅጉ እየደማ ቆየ፡፡

«ብዙ ኪሎሜትር ርቀት ጎትቼ በጥሻው ውስጥ ሰው ወደማያውቀን ሐኪም ቤት ወሰድኩት፡፡ ከዚያ በኋላ ሎሬንት ፈረንሳዮቹ እስኪደርሱ ድረስ ቢደብቀንም ሁኔታው ያሰቅቃል፡፡ ደብቆ ቢያድነንም ግን በሕይወት መቆየቱ ሥቃይ ሆነብን፡፡ ሎሬንት በየቀኑ ጠዋት እንዴት አደራችሁ ለማለት ይቀሰቅሰናል፤ ከዚያም የቤተሰቤን አባላት ከገደሉት ሰዎች ጋር ቱትሲዎችን እያደነ ሲገድል ይውላል፡፡ አጥቦ ሊያስወግዳቸው የማይችላቸውን የደም ፍንጣቂዎች ማታ ሲመጣና እራት ሲሠራ በእጆቹና ልብሶቹ ላይ አያለሁ፡፡ ሕይወታችን በእጁ ላይ ስለነበር ምንም ማለት አንችልም፡፡ ሰዎች በአንዴ ጥሩም መጥፎም ነገር መፈጸም እንዴት እንደሚቻላቸው ሊገባኝ አይችልም» አለኝ፡፡

«የዘር ጭፍጨፋው እየተፈጸመ ያለው በሰዎች ልብ ውስጥ ነው፣ ጊርን ፖል» አልኩት፡፡ «ጎዳዮቹ ጥሩ ሰዎች ናቸው፡፡ ግን አሁን ርኩሰት ልባቸውን ተቆጣጥሮታል፡፡»

ለጊርን ፖል ለቤተሰቡ አባላት እንደምጸልይላቸው ነገርኩት፡፡ ከዚያም በዘር ጭፍጨፋው ጊዜ በአካባቢያችን ስላሳለፈ በወላጆቼ ላይ የተከሰተውን ነገር ማወቁ እንደማይቀር ተገለጸልኝ፡፡ ጥያቄው እኔ ራሴ በእነርሱ ላይ የተከሰተውን ነገር ማወቅ እፈልጋለሁ ወይ? የሚለው ነው፡፡ ለመቀበልስ ጥንካሬው አለኝ ወይ? በእርግጠኝነት መሞታቸውን ካወቅሁ ወደ በፊቱ ማንነቴና ሕይወቴ መመለስ የሚባል ነገር አይኖርም፡፡

እውነታውን መጋፈጡ እንደሚሻለኝ ወሰንኩ፡፡ የቤተሰቤን አባላት መሞት ያወቅሁ ማስመሰል እንዳለብኝ ገባኝ፡፡ ያለዚያማ ስሜቴን ላለመጉዳት ጊርን ፖል ምንም አይነግረኝም፡፡ ማወቅ የምፈልገውን ነገር እንዲነግረኝ ማታለል አለብኝ፡፡ የአባቴን ቀይና ነጭ መቁጠሪያ ፍለጋ ወደ ኪሴ ገባሁና አምላክን ጥንካሬ እንዲሰጠኝ ጠየቅሁት፡፡

«እና ጊርን ፖል ስለ አባቴ ... ያው እንደገደሉት አውቃለሁ፤ የት እንደሆነ ነው እንጂ የማላውቀው፡፡ የምታውቀው ነገር ይኖር ይሆን እያልኩ ሳስብ ነበር፡፡»

«እንዴ አዎና፣ ለዚያውም እያንዳንዷን ነገር ነዋ፡፡ ሎሬንት እዚያ ስለነበር ሁሉንም ነገር ሊይቷል፡፡ አባትሽን በኪቡዬ ከተማ ነው የገደሉት፡፡»

ቃላቱ ልቤን እንደጦር ወጉት፡፡ ዓይኖቼን በእጆቼ ሸፍኜና ፊቴን አዙሬ እንባዬን ለመደበቅ ሞከርኩ፡፡

«አባትሽ የኔ ወላጆች ከተገደሉ ከአንድ ወይንም ከሁለት ቀናት በኋላ ነው የተገደለው» ዢን ፖል ቀጠለ፡፡ «ሚያዝያ 14 መሰለኝ፡፡ ወደ አካባቢያችን አስተዳደር ጽ/ቤት ለቀናት ምንም ላልቀመሱት እግር ኳስ ሜዳ ላሉት በሺዎች የሚቆጠሩ ስደተኞች ምግብ እንዲላክ ለመጠየቅ ይሄዳል፡፡ ያም ትልቅ ስህተት ነው፡፡»

ወይኔ አባቴ! እንዴት እንዲህ ደግ መሆን አሰፈለገህ… ለምንስ ይህን ያህል ተሞኘህ? የኪቡዬ አስተዳዳሪ ሁሉም ነገር በእጁ የሆነና ለአባቴም የቅርብ ሰው ነው፡፡ አባቴ ጓደኞቹ የሆኑ ሌሎች ጽንፈኛ ሁቱዎች ከዚያን ጊዜም በፊት አሳልፈው ሰጥተውት ስለነበር ለምን እነርሱን ማመኑን እንዳላቆመ ሊገባኝ አልቻለም፡፡ የሚራቡ ሰዎችን ለመመገብ ሲል ግን ሕይወቱን እንዳጣ አውቃለሁ - ለእርሱ ሌላ አማራጭ አይኖርም፡፡ ዓይኖቼ ተቃጠሉ፤ ጨጓራዬ ተላጠ፡፡ ዢን ፖል ሲቀጥል፦

«ሎረንት እንደነገረኝ አስተዳዳሪው አባትሽን ምኝ ብሎ ሰድቦት ወታደሮቹ ወደ ውጪ ጎትተው እንዲያወጡት ይነግራቸዋል፡፡ በአስተዳዳሪው ጽ/ቤት መግቢያ ደረጃዎች ላይ በጥይት መትተው አስከሬኑን ሜዳ ላይ ጣሉት፡፡»[8]

«እንግዲህ… ዢን ፖል ይህን ሁሉ ስለነገርከኝ አመሰግናለሁ፡፡ ምንም ቢሆን ይጠቅመኛል ልጅ» አልኩ ድምጼን በትክክለኛው ለማድረግ ባለኝ ዐቅም እየተቆጣጣርኩ፡፡ ጨለማው ፊቴን ስለደበቀልኝ አምላኬን አመሰገንኩት፡፡ «እና እናቴስ በል፡፡ እሷም እንደተገደለች አውቃለሁ፣ ግን እንዴት እንደሆነ እንጃ -»

«አዬ ሮዝ፯» ሲል አቋረጠኝ፡፡ «በአካባቢያችን መጀመሪያ ከሞቱት ውስጥ አንዷ ነች፡፡ ከአባትሽ ከጥቂት ቀናት በፊት ነው የተገደለችው፡፡ ሎሬንት ከገዳዮቹ አንዱ ሳይሆን አይቀርም፤ ሁሉንም ዝርዝር ጉዳይ ያውቃል፡፡ ለማናቸውም እናትሽ የተደበቀችው በአያትሽ ጎረቤት ጓሮ ነበር፡፡ የሆነ ሰው በአቅራቢያው ባለ አካባቢ ይገደል ነበር፡፡ እናልሽ እናትሽ ጩኸቱን ስትሰማ ወንድምሽ ይመስላታል፡፡ ወደ መንገዱ ‹ልጄን አትግደሉት! ዳማሲንዬን አትግደሉብኝ!› እያለች እየሮጠች ወጣች፡፡ ‹ጎሽ ለልጄ ስትል ተወጋች!›

[8] <u>የተርጓሚው ትዝብት</u>፡- 60 ሚኒትስ ለተባለው ዝግጅት ኢማኪዩሌ እንደተናገረችው አባቷን ከገደሉት በኋላ መንገድ መዝጊያ ኬላ አድርገውት ነበር፡፡

«የሚገድሉት ዳማሲንን አልነበረም፤ ግን ገዳዮቹ እናትሽን እንዳዩዋት አሳደዷት፡፡ ገንዘብ ከሰጠቻቸው እንደሚተዋትም ነገሯት፡፡ ተስማማችምና ከወዳጇ ከሙሬንጇ ለመበደር ሄደች፡፡ ሙሬንጇም ሂጅልኝ ትላታለች፡፡ ‹ከቤቴ ሂጂ - በረሮዎችን አንረዳም!› ብላ ሙሬንጇ ለገዳዮቹ ግቢዋ እንዳይበላሸባት እናትሽን ወደ ጎዳናው ወስደው እንዲገድሏት ነገረቻቸው፡፡ ምስኪን እናትሽን ወደ መንገዱ ዳርቻ ወስደው ቀረጣጥፈው ገደሏት፡፡ የተወሰኑ ጎረቤቶቻችሁ ግን ቀበሯት፡፡ ከተቀበሩት የተወሰኑ ሰዎች ውስጥ አንዷ ነች … ከዘያ በኋላ አስከሬን በጣም ስለበዛ መቃብርም የሚቆፍር ጠፋ፡፡»

የሚነግረኝ እያንዳንዷ ቃል እንደ ግርፋት ሁሉ ታማለች፤ ቢሆንም ግን ለመረጃው እስረኛ ነበርኩ፡፡ ተጨማሪ እንዲነግረኝ ገፋፋሁት፡፡ «ስለ ትንሹ ወንድሜ ስለ ቪያኒ እንዲያው ሰምተህ ይሆን?» ስል ጠየቅሁት እንዴት ሕጻን ወንድሜን ከቄሱ ቤት በውድቅት ሌሊት እንዳባረርኩት ሳስታውስ የጸጸት ጦር እየወጋኝ፡፡

«ቪያኒ የተገደለው በኪቡዬ እግር ኳስ ሜዳ ከጓደኛው ከኦገስቲን ጋር ነው፡፡ እዚያ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ነበሩ - ሁሉም ተጨፍጭፈዋል፡፡ በመጀመሪያ ገዳዮቹ በመትረየስ ገደሏቸው፤ ከዚያም በኋላ ቦምቦችን ወረወሩባቸው፡፡ የዳነ ያለም አይመስለኝ፡፡»

እጆቼ ተንቀጠቀጡ፤ ወደ ሳንባዎቼም አየር ማስገባት አቃተኝ፡፡ በቻልኩት መጠን ራሴን አረጋግቼ ስለ ዳማሲን ለመጠየቅ ብሞክርም ስሙን መጥራት እንኳን አቃተኝ፡፡ በሕይወት ኖሮ የሆነ ቦታ ይጠብቀኛል በሚለው ተስፋዬ ላይ የሙጥኝ ብያለሁ፡፡ በመጨረሻ «ወንድሜ ኤይማብል ያለው ሴኔጋል ነው፤ ይህን ሁሉ ነገርም አያውቅ… ደብዳቤ የምልክበት አድራሻ እንኳን የለኝም…» አልኩት፡፡

«የዳማሲንን ጓደኛ ቦንን ጠይቂዋ፡፡ ሁሉንም የዳማሲንን ወረቀቶችና እቃዎች ይዟል … ወይንም ቢያንስ በፊት ነበረው፡፡» «ለምን?» ስል ጠየቅሁ ልቤ በጣም እየመታች፡፡

«እንዴ ምክንያቱም ወንድምሽን የደበቀው እርሱ ነበራ፤ እናም ዳማሲን ወደ ዛየር ለመሄድ ሲነሳ ዕቃውን ሁሉ እርሱ ጋ ነበር የተወው፡፡ አሁን ግን ዕቃዎቹን ሁሉ ይጥላቸው ይሆናል - ወንድምሽ ከተደገደለ በኋላ በጣም ተበሳጭቷል የሚል ወሬ ሰምቻለሁ፡፡»

ቃላቱ እንደ ጥይት መቱኝ፡፡ «አባከህ … አይሆንም … ዳማሲን አይሆንም … እሱንም!»

ከዚያ ወዲያ ለማወቅ አልጓጓሁም፡፡ ቆሜ የተወሰኑ ጫማዎች ያህል ተንገዳገድኩና ራሴን ሶቼ ወደቅሁ፡፡ ራሴም መሬት ላይ ተተከለ - በቀዝቃዛው መሬት ላይ

መጋደምንና ከሌላው ቤተሰቤ ጋር መተኛትን ፈለግሁ፡፡ ምንም ለመስማት፣ ለማየትም ሆነ ለመዳሰስ አልፈለግሁም፡፡ ብዙ ለቅሶ አለብኝ፡፡ በአቧራው ላይ አነባሁ፡፡ ገሪን ፖል አጠገቤ ሆኖ ሊያጽናናኝ ሞከረ፡፡ ከፊቴ ላይ አቧራውን ጠረገልኝ፤ አንገቴንም ቀስ ብሎ አባበሰኝ፤ እኔ ግን እጁን ወደዚያ መነጨቅሁት፡፡

‹‹ተወኝ፤ ይህን በራሴ ልወጣው፡፡ ገሪን ፖል አሁን ብቻዬን መሆን እፈልጋሁ፡፡ ማንም ምድራዊ ኃይል አያጽናናኝም ... ለአፍታ እንኳን ብቻዬን ተወኝ» ስለው ወደ ምሽጉ ሌላ ክፍል ዝምተኛ ወንድሙን ይዞ ዘወር አለ፡፡

በጀርባዬ ተንጋልዬ ወደ ሰማይ እያየሁ አለቀስኩ፡፡ አንዳች እንባ በዓይኖቼ እስኪጠፋ ድረስ አነባሁ፡፡ ኢየሱስ በሕልሜ የገባልኝን ቃል አስቤ ከእርሱ ጋር ማውራቴን ቀጠልኩ፡፡ መታጠቢያ ቤቱን ለቅቄ ስወጣ ሁሉም ሞተው እንደማገኛቸው ነግረኸኛል፤ ትክክልም ነበርክ» አልኩት፡፡

‹‹ሁሉም ሞተዋል፡፡ ሁሉንም በዚህች ዓለም የምወደውን ተነጥቄያለሁ፡፡ ሕይወቴን በእጆችህ አኑሬያለሁ ኢየሱስ ... ቃልህን ጠብቀህ ተንከባከበኝ፡፡ እኔ ቃሌን እጠብቃለሁ፡፡ ታማኝ ልጅህም እሆናለሁ፡፡» ዓይኖቼን ጨፍኜ የቤተሰቤን ምስል አሰብኩት፡፡ እግዚአብሔር አቅርቦ በጥሩ ሁኔታ እንዲይዛቸው ጸለይኩ፡፡

የተሸከርካሪው ድምፅ ድንገት ቀሰቀሰኝ፡፡ ሊነጋ የተወሰኑ ሰዓታት ሲቀሩ መንታ ባውዛዎች ወደ ምሽጉ ሰልተው ገብተው ሌሎቹን ሴቶች በክብ የብርሃን ባሕር ከገሪን ፖልና ከገሪን ባፕቲስት ጋር እንደቆሙ አጥለቅልቀዋቸዋል፡፡

ተሸከርካሪው አጥሩ ጋ ቆሟል፡፡ ትልቅ ወታደራዊ መጓጓጥ ሲሆን መመሳሰያ ቀለም በተቀባ ሸራ ተሸፍኗል፡፡ ፈረንሳውያኑ ወታደሮች ከኋላ እንድንሳፈርና ጸጥ እንድንል አሳሰቡን፡፡

‹‹የሁቱ ኬላዎች በየቦታው አሉ» ሲል አንደኛው አስጠነቀቀን፡፡

ከምሽጉ አንድ ኪሎሜትር ተኩል ገደማ እንደተጓዝን አንደኛው ኬላ ጋ ደረስን፡፡ የገዳዮቹን ድምጾች ከሸራው በስተጀርባ እሰማ ጀመር፡፡ በዚህ ሰዓት ልዩነቱ የታጠቁ አጃቢዎች ስላሉልን ነው እንጂ እንግዳ ነገር አልሆነብኝም፡፡ እንዲያም ሆኖ በእነርሱ ወገን በመቶዎች የሚቆጠሩ ገዳዮች ሲኖሩ በኛ ወገን ግን በጣት የሚቆጠሩ ወታደሮች ነበሩ፡፡

‹‹ምንድነው የጫናችሁት?» ሲል አንደኛው ገዳይ ጠየቀ፡፡

‹‹ከኪጋሊ እየመጡ ላሉት የሁቱ ስደተኞች ምግብና ንጹሕ ውሃ እየወሰድን ነው» ሲል ነጂው ዋሸ፡፡

«ምርጥ ሰው! እነዚህ ቱትሲ እባቦች ኪጋሊ ላይ እየገደሉን ነው... ማለፍ ትችላለህ፣ ቀጥል» ተባለ፡፡

ነጂው ተሸከርካሪውን እንደገና ኮርኩሮት ወደፊት አቀናን - እንደገናም መንገዳችንን ጀመርን፡፡ እኛን ከኬላው ለማሳለፍ ነጂው የሰጠውን ብልጠት የተሞላበት መልስ አደነቅሁ፡፡ ኪጋሊ በአማጽያኑ ቁጥጥር ስር ስለዋለች በአሥር ሺህዎች የሚቆጠሩ ሁቱዎች ከዚያ ወደ ደቡብ ይገሰግሳሉ፡፡ ኢጋጣሚው ደግሞ አብዛኞቹ ስደተኞች ወደ እኛ ክፍለ ሀገር ወደ ኪቡዬ የሚመጡት አንድም ለመስፈር አለያም ኪቩ ሐይቅ ወርደው ወደ ዛየር ለመሻገር ነው፡፡ ብዙ ከጦርነቱ ለማምለጥ እየሞከሩ ያሉ ሁቱ ቤተሰቦች አሉ፤ ግን ብዙ አዳዲስ ኢንተርሃምዌ ገዳዮችም በየስፍራው ተሠራጭተዋል፡፡

በቀጣዩ ኬላ ገዳዮቹ ወዲያውኑ አሳለፉን፡፡ «ፈረንሳዮች የኛው ናቸው... ሂዱ.. አሳልፋቸው!» አለ አንደኛው፡፡ በቀጣዮቹም አምስት ኬላዎች የሆነው እንደዚያው ነው፡፡ ሌሊቱን ስንሄድ አድረን ነጋብን - ነጂው መሄዱን ቀጥሎ ወደ አዲስ ሀገር ቢወስደን ተመኘሁ፡፡ ነፍሴ ከሩዋንዳ ወደ ሌላ ዓለም ለመብረር ፈለገች፡፡ መቼ ወይንም የት እንደሚጀምር ባላውቅም አምላክ አዲስ ሕይወት እያመቻቸልኝ እንደሆነ አምኛለሁ፡፡ ከሰላሳ ደቂቃ በኋላ ተሸከርካሪው ከዋነኛው ምሽግ ሲደርስ ወዲያውኑ ተበሳጨሁ - አዎን ነጻ ወጥተናል፤ ግን አሁንም በሩዋንዳ መካከል ነበርኩ - ገና በሽብሩ እምብርት፡፡

ከተሸከርካሪው ስወርድ ለመጀመሪያ ጊዜ ያየሁት ነገር የፊራረሱ የትምህርት ቤት ክፍሎችን ነው፡፡ በበሩ ላይ የተሰቀለው የዕንጨት ማስታወቂያ *ርዋምፒሊ* የሚል ቃል እንደነገሩ ተጽፎበታል፡፡ በዚህም ምክንያት እናቴ የማስተማር ሥራዋን ወደጀመረችበት ትምህርት ቤት እንደመጣሁ ገባኝ፡፡

በሰቆቃ ተሞላሁ፡፡ በመሆኑም ከክፍሎቹ ሄድ ብዬ ከእግዚአብሔር ጋር ፊጠን ያለ ወግ መጀመር አለብኝ፡፡ «አምላክ ግን ለምን እዚህ አመጣሽኝ? ለቤተሰቤ ላለቅስ እንደሚገባኝ አውቃለሁ፣ ግን አሁን አልችልም ... እባክህ ለመትረፍ የሚያስፈልገኝን ጥንካሬ ስጠኝና ባይሆን ሐዘኑን በኋላ ልዘን፡፡»

ከተወሰኑ ደቂቃዎች በኋላ በትምህርት ቤቱ ግቢ ገብቼ ፈገግ ለማለት ጥንካሬውን አገኘሁ፡፡ እናቴ ለረጅሙ ባለ አንድ ክፍሉና አቧራማ ወለሉ መማሪያ ክፍል የነበራትን ፍቅር አስታወስኩ፡፡ «ቁምነገሩ በዚህ ትምህርት ቤት የምንማረው ነው እንጂ ትምህርት ቤቱ ምን ይመስላል የሚለው አይደለም» ትል ነበር፡፡

በመንጋት ላይ ስለሆነና የማለዳዋም ጸሐይ በትምህርት ቤቱ ግቢ ስለወጣች አብረውኝ ያሉትን ሰዎች ለመጀመሪያ ጊዜ በደንብ ማየት ቻልኩ። ሌሎች 20 የሚሆኑ ቱትሲዎችም በመዘዋወር ላይ ስለሆኑ ድንገት ሴቶቹና እኔ ምን ያህል እንደተባረክን ገባኝ። እነዚህ ምስኪን ነፍሶች ላለፉት ሦስት ወራት በጫካ ውስጥ በየጉድጓዱ እየተኙ፣ ሣርና ቅጠል እየበሉ ነው የቆዩት።

ፀሐይዋ በጣም ስለከረረች ዓይኖቼን መከላከል አለብኝ። ከልዬም ሳለ የማውቃትን ሰው ፊት በጣቶቼ ጥላ አየሁት። «ኢስፔራንስ!» ስል ጮህሁ። የእናቴ እህት ነች። ግን የሰማችኝ አልመሰለኝም።

«ኢስፔራንስ! አላወቅሽኝም? ኢማኪዩሌ ነኝ እኮ! አምላክ ሆይ ምስጋና ይግባህ! አንድ ሰው ድኗል!» አልኩ ጥብቅ አድርጌ እያቀፍኳት።

ከመናገሯ በፊት ረዘም ላለ ጊዜ ጭምቅ አድርጋ አቅፋኝ አጸፋውን መለሰችልኝ። ምናልባት አእምሮዋን ስታ እንዳይሆን ተጨነቅሁ። «እስኪ ይሁን» አለች ደከም ብላ። «እንኳን በሕይወት ኖርሽልኝ። ሌላዋን አክስትሽንስ አየሻት?» አለችና ዝግ ብላ በትምህርት ቤቱ ግቢ እህቷ ጉኔትና ሦስቱ ያክስቶቼ ልጆች (ሁሉም ወጣቶችና በአሥራዎቹ ዕድሜ ላይ ያሉ ናቸው) ወደተቀመጡበት ወሰደችኝ።

ከእነርሱ አሥር እርምጃ ያህል ርቄ ቆሜ ከፊት ለፊቴ ያለውን ስሜትን የሚኮረኩር ትዕይንት ስመለከት ቆየሁ። ፊቶቻቸው በነፍሳት ንድፊያ አባብጠው፣ ከንፈሮቻቸው ተሰነጣጥቀውና ደምተው፣ ሰውነታቸው በእከከና በመግል ተሞልቷል። አካላቸው እዚህም እዚያም ተቆራርጧል። ለሳምንታት መመረዙ ወይንም ማመርቀዙ ያስታውቃል። ከቆምኩበት ሕመማቸው ሸተተኝ።

ጠንቃቃ ቁስል ተንከባካቢዋና መምህርቷ አክስቴ ጉኔት በንጽሕና ላይ እጅግ ትጉህ ስለነበረች እንግዶች እቤቷ ሲመጡ ልጆቿን ሰላም ከማለታቸው በፊት እጃቸውን እንዲታጠቡ ታዝ ነበር። አሁን ግን ከነልጆቿ እንደ ኋላቀር ህዝቦች ሁሉ ልብሳቸው አላልቆና መቀመጫቸው ወጥቶ እየታየ አቧራ ላይ ተቀምጠዋል።

በጉልበቴ አረፍ ብዬ ጉንን ለማቀፍ ሞከርኩ፤ እርሷ ግን ከኔ ርቃ እንባዋን ለመደበቅ ሞከረች። «ሉይ ኢማኪዩሌ ማሪኝ... ፈርቼ ነው። ዓይኖቼን ውሃ ሲያደርጋቸው ታወቀኝ።»

እናቴ በእንባዋ ተሸማቃ በተመሳሳይ ሁኔታ ላይ ልትል የምትችለው የነበረው በእርግጥ ይህንኑ መሆኑን አስቤ ፈገግ አልኩ። «ጉን ስላገኘሁሽ በጣም ደስተኛ ነኝ።» ቀስ ብዬ አቀፍኳትና ልጃገሮቹንም እያንዳንዳቸውን ሳምኳቸው። ዓይኖቻቸው እንደገና ያንጸባርቁ ጀመር፤ ፈገግታቸውም እየተመለሰ ሄደ።

አምላክን ሕመማቸውን እንዲያድንላቸው ጠይቄ ራሴም ሰውነታቸውን ለማዳን የምችለውን ሁሉ እንደማደርግ ቃል ገብቼ ስለሁላቸውም ጸጥ ብዬ ጸሎት አደረስኩ።።

አብሬያቸው ቁጭ ብዬ አሳዛኝ ወሬ ጀመርን።። እርስ በርሳችን በቤተሰባችን ማን እንደተገደለና እያንዳንዳችን ያለፍንበትን ውጣ ውረድ አወሳን።። ጥኔት ሦስት ልጆቿንና ባሏን አጥታለች፤ የኢስፔራንስ ቤተሰብ በሙሉ ተገድሏል።። ደጋጎቹ አያቶቼም ተገድለዋል፤ ቢያንስ ሰባቶቹ አጎቶቼም ዕጣቸው ያው ሆኗል።። ወዲያውኑ ሁላችንም እናለቅስ ገባን ... እንባችን ያቆም መሆኑንም ተጠራጠርኩ።።

ለአንድ ሰዓት ገደማ ካወራን በኋላ ኢስፔራንስ ደብዳቤ ሰጠችኝ።። ያን ሁሉ ጊዜ በጫካው ስትቆይ እንዴት እንዳቆየችው ሊገባኝ አልቻለም።። «ዳማሲን በተደበቅሁበት አግኝቶኝ ይህን ደብዳቤ አደራ ሰጥቶኝ ነው» አለች።። «ወደ ዛየር እየሄደ... ነገር ግን አልተሳካለትም።።»

ደብዳቤውን ከእጇ ወስጄ እንባ አርጥቦት የደረቀውን ማሸጊያውን አየሁት።። ከአክስቶቼና ከልጆቻቸውም ሸሸሁ።። ከማንም ሰው ጋር አብሮ መሆንን አልቋቋመውም።። የወንድሜን ስም መስማቱ በራሱ ለመሸበር በቂዬ ነው።። እና አሁን ከጻፈልኝ ቃላት ሁሉ የመጨረሻዎቹን ይዣለሁ።። እነርሱን ማንበቡም ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እኔን ሲያናግረኝ እንደመስማት ነው።።

ምዕራፍ 18
ከዳማሲን የተላከ ደብዳቤ

ከትምህርት ቤቱ በስተጀርባ ብቻዬን ሆኜ የዳማሲንን ደብዳቤ ከፈትኩት። ለማንበብ የሚያስቸግረውን የእጅ ጽሑፉን እንዳየሁ በትምህርት ቤት እንዳለን የጻፈልኝን ደብዳቤዎች ሁሉ አስታውሼ ልቤ ታመመ። ፈጽሞ ግልጽ ስሜት የማይንጸባረቅባቸው፣ ግን ሁሌ በፍቅርና በደግነት፣ በማበረታቻና አድናቆት፣ በግሩም ምክርና ረጋ ያለ ተግሳጽ፣ ስለ ወዳጆቻችን በሚያወሱ ወሬዎችና በብዙ ቀልዶች የተሞሉ ደብዳቤዎቹ ትውስ አሉኝ። ጀርባዬን በትምህርት ቤቱ ክፍል ግድግዳ ላይ አስደግፌ ተቀምጬ አነብ ጀመር።

ግንቦት 6፣ 1994

ውድ (አባባ፣ እማማ፣ ቪያኒ እና) ኢማኪዩሌ

ሁላችንም ከተለያየን አንድ ወር ገደማ ሆነን። ይሄው የቅዠት ኑሮ እየኖርን ነው። ሁናቴዎች ከሚያሳዩት ነገር ባሻገር አንድ ዘውግ ሌላውን ፈጽሞ የሚያጠፋው የእግዚአብሔር ፍቃድ ሲሆን ብቻ ይሆናል ብዬ አምናለሁ። ምናልባት የእኛ ሕይወት ለሩዋንዳ ድኅነት እንዲከፈል ግድ ብሎ ሊሆን ይችላል። ስለ አንድ ነገር እርግጠኛ ነኝ - እንደገና እንደምንገናኝ በአእምሮዬ ቅንጣት ታክል ጥርጣሬ የለም።

ከሀገሪቱ ለመውጣት ልሞክር ነው፣ ግን ይሳካልኝ አይሳካልኝ አላውቅም። በመንገድ ላይ ከገደሉኝ ስለ እኔ አትጨነቁ፤ በሚገባ ጸልያለሁ . . . ለሞትም ተዘጋጅቻለሁ። ከሩዋንዳ መውጣት ከቻልኩ ሰላም እንደተመለሰ ወዲያውኑ ሁላችሁንም አገኛችኋለሁ። የደረሰብኝን ሁሉ ቦን ይነግራችኋል።

የዳማሲን ጓደኛ ቦን በሌላ ጊዜ እንደነገረኝ ወንድሜ ደብዳቤውን እየጻፈ ሳለ እዚህ ሐሳብ ላይ ሲደርስ ዳማሲን ብዕሩን ቁጭ አድርጎ ቀና ብሎ እያየው «ቦን፣ ወዳጄ እንደሆንክ አውቃለሁ፤ ስሜቴም ሳይነዳ እንዲቆይ ሞክረሃል፣ አሁን ልትነግረኝ የሚገባህ ሰዓት ላይ ነን - ከቤተሰቤ አባላት የተገደለ አለ እንዴ?»

ቦን ሁቱ ስለሆነ በዘር ጭፍጨፋው ወቅት በነጻነት ይጓዝና በአካባቢው ከቱትሲዎች ማንኛቸው እንደተገደሉ ያውቃል። የወላጆቼንና የቪያኒን ሞት ለራሱ

በምስጢር የያዘው ለወንድሜ በጣም ስለሚጠነቀቅለትና ስሜቱን ሳይጎዳ ለመጠበቅ ስለፈለገ ነው።።

ዳማሲን በቀጥታ ሲጠይቀው ጊዜ ቦን ከባዱን መርዶ አረዳው።። ጓደኛው የሚወዳቸው የቤተሰቡ አባላት ገና በሕይወት ያሉ እየመሰለው ደብዳቤውን መጻፉን እስኪጨርስ መጠበቅን አልፈለገም።። ስለዚህ ቦን ለዳማሲን አባታችን፣ እናታችንና ታናሽ ወንድማችን እንደተገደሉና እኔ ምናልባት በሕይወት ተርፌ ሊሆን እንደሚችል ይነግረዋል።። ዳማሲን ቀኑን ሙሉ ማለት ይቻላል አልቅሶ እንደነበር የደብዳቤው ቋሚ ምልክት የሆኑት የእንባ ጠብታዎች ይህንን ይመሰክራሉ።።

ዳማሲን ኪቩ ሐይቅን ለማቋረጥ ጀልባ ፍለጋ ከመሄዱ በፊት ደብዳቤውን እንደገና አውጥቶ አባባ፣ እማማና ቪያኒ በሚሉት ቃላት ግራና ቀኝ ቅንፎችን አስቀምጦ የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች አከለ።።

> ኢማኪዩሌ እንድትጠነክሪ እለምንሻለሁ።። እማማ፣ አባባና ቪያኒ መገደላቸውን አሁን ሰማሁ።። በተቻለኝ ፍጥነት ላገኝሽ እሞክራለሁ።። ራስሽን ሳሚልኝ፤ እቀፊልኝም! በጣም የሚወድሽ ወንድምሽ!

ይህ ካነበብኳቸው ነገሮች ሁሉ የሚሠቀጥጠው ነው።። እንባ ባረጠባቸው ቃላት ላይ የጣቶቼን ጫፎች አላወስኳቸውና ይህንን ደብዳቤ ሳላለቅስ ማንበብ እንደማልችል ተረዳሁ።።

በኋላ ላይ እንደደረስኩበት ለዘላለም የኔ ጀግና ሆኖ የሚኖረው ቦን ወንድሜን በቤቱ ከቤተሰቡ ፍላጎት በተጻራሪ ሊሸሽገው ሞክሯል።። በዘር ፍጅቱ የመጀመሪያ ቀናት ዳማሲንን በምስጢር ከአልጋው ስር በደኅና በመደበቅ ሊያቆየው ችሎ ነበር።። የቦን ቤተሰብ ግን ያደረገውን ነገር ሲደርስበት ዳማሲንን ለገዳዮቹ እንዲሰጥ ግፊት ያሳድርበታል።።

ይባስ ብሎ ቱትሲ ልጆችን በዘውግ ስም ጥሪ ወቅት ማሸማቀቅ የሚወደው ቡሆሮ ከቦን አጎቶች አንዱ ነው።። ቡሆሮ በሀገሪቱ ወስጥ ካሉ ጽንፈኛ ሁቱዎች ውስጥ አንዱ፣ መጥፎና አደገኛ ገዳይ ሆኖ ነበርና ሲጠራጠርበት ጊዜ ቦን ዳማሲንን በጭራሽ ቤት ውስጥ ማቆየት እንደሌለበት ይረዳል።። አንድ ሌሊትም በጣም አምሽቶ በቤተሰቡ መሬት ራቅ ያለ ጥግ ላይ ጉድጓድ ቆፍሮ በዕንጨትና ቅጠላቅጠል ይሸፍነዋል።። ገዳዮቹ በቡሆሮ ተጠቁመው ከመምጣታቸው በፊት ዳማሲንንም በጥንቃቄ ከመኝታ ክፍሉ ያስወጣና በጉድጓዱ ውስጥ ይደብቀዋል ።።

ዳማሲን በጉድጓድ ውስጥ ከሦስት ሳምንታት ለበለጠ ጊዜ ያህል ተደብቆ ሳለ ገዳዮቹ በቡሆሮ ውትወታ በተደጋጋሚ የቦንን ቤት አሠሡ። እነዚህ አራጆች ግን የማይሰለቹ በመሆናቸው የቦንን እያንዳንዷን እንቅስቃሴ ተከታትለው መጨረሻ ላይ ምግብ ወደ ውጪ ይዞ ሲሄድ ያዩታል። ሸሻጊው ጓደኛውና ተሸሻጊው ዳማሲን ገዳዮቹ ግቢውን ሊያስሡበን ይችላሉ ብለው ሠግተው ዳማሲን የኪቩ ሐይቅን ተሻግሮ ወደ ዛየር እንዲያቀና ይወስናሉ። (ቦን የቱትሲዎችን ሕይወት ለማትረፍ ሐይቁን የሚያሻግራቸውን አንድ ደግ ሳምራዊ ዐሳ አጥማጅ ሁቱ ያውቃል።) ዳማሲንን ከጉድጓዱ አውጥቶ በየጥላው እየቆዩና ከጥሻ ጥሻ እየተሸጋገሩ ከእኩለ ሌሊት በኋላ ወደ ሐይቁ ሄዱ። መንገዱ ብዙ ጊዜ በመፍጀቱ ግን የዚያ ሌሊት ጀልባ ታመልጣቸዋለች።

ነጋባቸው። በመሆኑም ዳማሲን ወደ ቦን ቤት ረጅም መንገድ ተጉዞ ተመልሶ አደጋ ላይ መውደቅን ስላልፈለገ ንሴንጂ በሚባል በሐይቁ አካባቢ የሚኖር የእርሱና የቦን ወዳጅ ቤት ቆየ። ንሴንጂ ቤተሰባቸንን የሚወድ ለዘብተኛ ሁቱ ነው። አባቴ የብዙ ወንድሞቹን የትምህርት ክፍያ በመክፈል አግዟቸዋል። ስለሆነም ዳማሲንን ለዚያን ቀን መሸሸግ በመቻሉ ደስ ተሰኘ።

የንሴንጂ ወንድም ሳይመን ግን የወንድሙን ያክል ቸር አልነበረም። ዳማሲንን በቤታቸው ሲደርስ በፈገግታና በወዳጅነት ተቀብሎታል ... በማግስቱ ከሰዓት በኋላ ግን ወንድሜ በተኛበትና ንሴንጂም የጀልባ ጉዞውን ለማመቻቸት በወጣበት ሳይመን ከቤት ሾልኮ ወጥቶ የገዳዮቹን ቡድን ፈልጎ ዳማሲንን አሳልፎ ሰጠው።

ከእራት በፊት ሳይመን ወንድሜን ቀስቅሶ ወደ ዛየር ከመሄድህ በፊት ልብሶችህን ልጠብልህ ይለዋል። ዳማሲንም ልብሶቹን ሁሉ አወላልቆ በውስጥ ልብስ ብቻ ይቀራል። ሳይመንም ልብሶቹን ይወስድበታል። (በኋላ ላይ እንደተናገረው ይህን ያደረገው ወንድሜን ከመሞቱ በፊት ለማሳፈርና ለማሸማቀቅ ፈልጎ ነው።) ልብሶቹን ከወሰደበት በኋላም ሳይመን ወንድሜን በደርዘኖች የሚቆጠሩ ገዳዮች ይጠብቁት ወደነበረበት ወደ ዋናው ቤት ይጠራዋል። ወንድሜም ላይ ያለ ምኅረት ተረባረቡበት፤ እየደበደቡ ወደ መንገድ ጎተቱት። ከውስጥ ልብሱም ሌላ ምንም አልለበሰም።

እኛ ቤት ትሠራ የነበረች አንድ ሴት ነገሩን ሁሉ አይታ የዳማሲንን የመጨረሻ ሰዓት ዝርዝር ሁኔታ ነግራኛለች። «ቆንጆዋ እህትህ የት ነች?» ብለው ገዳዮቹ ወንድሜን ይጠይቁታል። «የት ነች ኢማኪዩሌ?» በቤተሰብህ ያሉትን በረሮዎች አስከሬኖች አይተናቸዋል፤ እሷ ግን ገና አልተደረሰባትም... የት ነች? ንገረንና በነጻ እንለቅሃለን፤ ካልነገርከን ግን ሌሊቱን ሙሉ ስንከትፍህ እናድራለን። በል ኢማኪዩሌ የት እንዳለች ንገረንና በነጻ ትሰናበታለህ።»

ፊቱ የተሰባበረውና ያባበጠው ዳማሲን የከበቡትን ገዳዮች አየት አድርጓቸው በሕይወቴ ሙሉ እንዳደረገልኝ ሁሉ በመጨረሻዋም ቅጽበት ለኔ ቆመልኝ - «ቆንጆዋ እህቴ የት እንዳለች ባውቅ እንኳን አልነግራችሁም፡፡ ኢማኪዩሌን መቼም አታገኟትም… እናንተ ሁላችሁም ተደማምራችሁ ብትቀርቡ እንኳን በብልሃት አታህሏትም፡፡»

በገጀሮቻቸው እየመቱና እየወጋጉትም «እንዳንተ ብልህ ነች? አንተ ማስተርስ ዲግሪ እያለህ ያዝንህ፤ አልያዝንህም ወይ? አሁን እህትህ የት እንደተደበቀች ትነግረናለህ አትነግረንም!»

ዳማሲንም ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ቀጥ ብሎ ቆመና ገዳዮቹ ላይ ሳቀባቸው፡፡ አለመፍራቱ ግራ አጋባቸው፤ ብዙ ቱትሲዎችን ገድለዋል፤ ሲገድሉም የተጠቂዎቻቸውን የአትግደሉኝ ተማጽኖ ማድመጥ ሲያረካቸው ቆይቷል፡፡ የዳማሲን መረጋጋት ደስታቸውን ነጠቃቸው፡፡

ከመደራደር ወይንም *ለወንድ ልጅ ለምላክ* እያለ ምህረታቸውን ከመለመን ይልቅ እንዲገድሉት ተገዳደራቸው፡፡ ‹‹ኑ›› አላቸው፡፡ «ምን ትጠብቃላችሁ? ዛሬ ወደ አምላኬ የምሄድባት ቀኔ ነች፡፡ በሁላችንም ዙሪያ አምላክ ይታየኛል፡፡ እያየ ነው፣ ወደ ቤቱ ሊወስደኝ እየጠበቀ፡፡ በሏ - *ሥራችሁን* ጨርሱና ወደ ገነት ላኩኝ፡፡ እንደ ሕፃናት የእቃ እቃ ጨዋታ አድርጋችሁት ሰውን ስትገድሉ ታሳዝኑኛላችሁ፡፡ ግድያ ጨዋታ አይደለም - አምላክን ካስቀየማችሁት አሁን ለተዝናናችሁበት ትከፍሉበታላችሁ፡፡ የምትቆራርጧቸው ንጹሃን ደም በፍርድ ቀን ይከተላችኋል፡፡ እኔ ግን ለእናንተ እየጸለይኩላችሁ ነው… የምትሰሩትን እርኩሰት እንድታዩና እጅግ ሳይዘገይባችሁ የአምላክን ይቅርታ እንድትጠይቁ እጸልይላችኋለሁ፡፡›››

እነዚህ የወንድሜ የመጨረሻ ቃላት ናቸው፡፡ የግፍ ግድያውን ሕመም ምንም ባይቀንሰው በገዳዮቹ ፊት በጽናት መቆሙና ይዞት ከኖረው ክብር *ጋር* መሞቱ ያኮራኛል፡፡

አንደኛው የሳይመን ወንድም፣ ካሬራ የተባለው የወንጌላውያን ቄስ፣ ዳማሲን ሲናገር አላገጠበት፡፡ «ይህ ልጅ ራሱን እንደ ሰባኪ ቆጠረ እኮ፡፡ እዚህ *ጋ* ያለሁት ሰባኪ እኔ ብቻ ነኝ እንግዲህ፡፡ ግድያውንም ባርኬያለሁ፡፡ ይህችን ሀገር ከአንድ ተጨማሪ በረሮ በማጽዳታችሁ ባርኬያችኋለሁ» ብሎ ገዳዮቹን አየት አድርጎ «ምን ትጠብቃላችሁ? ፈራችሁ እንዴ? አንድ በረሮ እንድትገድሉት ሲለማመጣችሁ ለምንድነው እሱ *ጋ* የምትገተሩት? *ግደሉታ!*»

ካሬራ ገዳዮቹን ወንጀል እንዲሰሩ አሸማቆ ገፋፋቸው፡፡

«ቱትሲዎች ስትባሉ ከእኛ ከሁቱዎች በላይ እንደሆናችሁ ልታሳዩ ትሞክራላችሁ» ብሎ አንዱ ገዳይ ጮኸና በዳማሲን ፊት ላይ ገጀራውን አነሳ፡፡ «ማስተርስ ዲግሪ ስላለህ በጣ...ም የምትበልጠን ይመስልሃል? እስኪ ማስተርስ ዲግሪ ያለው ሰው አንጎል ምን እንደሚመስል ልየው!»

ገጀራውን በወንድሜ ራስ ላይ ሲሰነዝርበት ወንድሜ በጉልበቶቹ ወደቀ፡፡ ሌላ ገዳይም ወደፊት ተራምዶ መጥቶ ገጀራውን ሁለቴ ሰንዝሮ ሁለቱንም እጆቹን ገነጣጠላቸው፡፡ የመጀመሪያው ገዳይ ገጀራውን ሌላ ዙር ሰነዘረ - በዚህን ጊዜም የዳማሲንን የራስ ቅል ከፍቶ ወደ ውስጥ ለማየት ሞከረ፡፡ ከዚያም በወንድሜ ደም ተጨማልቆ መንደር ለመንደር እየዞረ በሰው ጭንቅላት ውስጥ የማስተርስ ዲግሪን እንዳየ ጉራውን ሲነፋ ዋለ፡፡

የዳማሲን ግድያ ዝርዝር ላይ አተኩሬ መቆዘምን ለራሴ አልፈቅድም፡፡ ሞትን እንዴት እንደተጋፈጣት፣ ከመሞቱ በፊት እንዴት ፈገግ እንዳለ፣ ብሎም ለገደሉት ሰዎች እንዴት እንደጸለየ ብቻ አስባለሁ፡፡ ዳማሲን የኔ ውድ የልብ ወዳጄና ጠንካራ ወንድሜ ነበር፡፡

በኋላ ላይ ከገዳዮቹ አንዱና የዳማሲን የትምህርት ቤት ጓደኛ ስለነበረው ሰማሄ ስለሚባል ሰው ወሬ ሰማሁ፡፡ ስሜቱን መቆጣጠር አቅቶት ተጎድቶ ለብዙ ቀናት አለቀሰ አሉ፡፡ ያለማቋረጥ ዳማሲንና እርሱ ስላደረጓቸው ነገሮች ሁሉ ያወሳል፡፡ እግር ኳስ መጫወት፣ በቡድን መንፈሳዊ መዝሙር መዘመርና ቤተ-ክርስቲያንን ማገልገል አይነቶቹን ትውስታዎቹን ይጠቃቅሳል፡፡ ለእርሱና ለሌሎች ልጆች ወንድሜ ያሳያቸው የነበረው ደግነት እየታወሰው በደለኝነት ተሰምቶታል፡፡ ሰማሄ ለሚያዳምጠው ሁሉ ጸጸቱን ይገልጻል፡፡

«ከእንግዲህ አልገድልም» ይላል፡፡ «የዳማሲንን ፊት ከአእምሮዬ በፍጹም አላወጣውም፡፡ ቃላቱ ልቤን ለዘላለም ሲያቃጥሉት ይኖራሉ፡፡ ይህን ዓይነት ልጅ መግደል ኃጢአት እኮ ነው፡፡»

ምዕራፍ 19
የስደተኞች መጠለያው ምኞት

የፈረንሳዮቹ የስደተኞች መጠለያ የታጠቁ ወታደሮች የሚጠብቁት፣ ለቱትሲዎች ከለላ የሚሰጥና ሁቱዎችን የሚያገል ስፍራ ነው፡፡ ወታደሮቹ ስምንት ታንክ-መሰል ብረት-ለበስ ተሽከርካሪዎችን በግማሽ ክብ ቅርጽ ከትምህርት ቤቱ ሕንጻዎች ፊት ለፊት ያቆሙ ሲሆን የምሽጉን ውጨኛውን ክፍል ደግሞ ቀን ከሌት ቢያንስ መቶ የሚሆኑ ወታደሮች ይቃኙታል፡፡ እኛም ብረት-ለበስ ተሽከርካሪዎች ባሉበት ግማሽ ክብ ውስጥ ሙሉ ጊዜ ሰጥተው እንዲከላከሉንና መጸዳዳት ስንፈልግም ወደ ጫካ እንዲወስዱን ከተመደቡ ሰላሳ ወታደሮች ጋር እንኖራለን፡፡

የፈረንሳይ ወታደሮች በተደጋጋሚ ስለምንኖርበት ሁኔታ ይቅርታ ሲጠይቁን ያስቁኛል፡፡ ከመጣንበት ጋር ሲነጻጸር ፍጹም የምኞት ሕይወት በመኖር ላይ ነን፡፡ መጀመሪያ ላይ ከምንጭ ውሃ እናግዝና ገላችንንና ልብሳችንን በሳሙና እናጥብ ነበር!

ውጪ ላይ መተኛታችንን ፈረንሳውያኑ ወታደሮች እንደ ዋና መከራ ቢያዩትም እኛ ግን በደስታ ተቀብለነዋል፡፡ ብዙውን ጊዜ በቆሻሻና በዛፍ ቅጠላ ቅጠል ተሸፍኜ በአለትና ድንጋይ ላይ በመተኛቴ የተነሳ እያመመኝ ብነሳም ከዋክብት ላይ አንጋጥጬ መተኛቱን ወድጀዋለሁ፡፡ የእግዚአብሔርን ፊት በቀኑ መጀመሪያ ላይ የማየት ያህል ነው፡፡

ምግብ እንድናዘጋጅ አይፈቀድልንም፡፡ ይህ የሆነው ትኩስ ምግብ ስላልነበራቸው ሲሆን አለማዘጋጀታችንም ለእኛ ምንም ችግር አያመጣም፡፡ ወታደሮቹ የታሸገ አይብ፣ ጣፋጭ ኮቾሮ፣ እሸግ የዱቄት ወተትና ፍራፍሬ ይመግቡናል፡፡ የምመገበው የተወሰነ ምግብ ቢሆንም ቀስ በቀስ ሰውነቴ እየጨመረ ሄደ፤ ወገቤም ወደ ውስጥ መግባቱን አቆመ፡፡

ፈረንሳውያን ሥራቸው እኛን መከላከል መሆኑን ይናገራሉ፡፡ ይህንን ተግባራቸውንም በሚገባ ተወጥተውታል፡፡ በምሽጉ ውስጥ በቆየሁበት ወቅት አንድም ጊዜ እንኳን በገዳዮቹ ማስፈራሪያ ደርሶብኝ አያውቅም፡፡ ሆኖም ግን ሁቱዎች ብዙውን ጊዜ በውጪው የምሽጉ ክፍል በመሰብሰብ በተደረደሩት ተሽከርካሪዎች መካከል እኛን ለማየት ይሞክራሉ፡፡ በእንስሳት መጠበቂያ ያለን እንስሶች እንደሆንን ሁሉ ያፈጡብናል … ከመጥፋት ጠርዝ ድረስ የታደነ ዘውግ ብቸኛ ቅሪቶች፡፡

«እንስሳት እንደሆናችሁ ሁሉ ያዩዋችኋል፣ ግን እነርሱ ናቸው እንስሶቹ» አለኝ የወታደሮቹ አበጋዝ አንድ ቀን ጠዋት ከደረስኩ ከጥቂት ጊዜ በኋላ፡፡ ፈረንሳይኛ በጥሩ ሁኔታ እንደምችል ስለተረዳ ብዙ አዋራኝ፡፡ ታሪኬን ነገርኩት፤ በጣም እንዳዘነልኝም

ታየኝ፡፡ በሩዋንዳ ቱትሲዎች ያሳለፉትን፣ ታሪካቸንንና የዘውግ ግጭቶችን ጣጣ ሁሉ ያውቃል፡፡

«ባንቺና በኔ መካከል የሚቀር ነገር ልንገርሽ፤ የሀገሬ የርዕሰ-ብሔር ከራሱ ጋር አንዴት መታረቅ እንደሚችል አላውቅም - ጸጸቱ እንደማይገድለው» አለኝ፡፡ «ብዙ ሁቱዎችን እንዴት ሰው እንደሚገድሉ ስላሠለጠነች ፈረንሳይ በእጆቿ ላይ ደም አለባት፡፡»

በሩዋንዳ ለተከሰተው ነገር የውጪ ዜጋ ወቀሳውን ሲቀበል ስሰማ ይህ የመጀመሪያዬ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ለነፍሴ ጥሩ ነገር አደረገላት፡፡ ዓለም እየደረሰብን ያለውን ነገር አይቶ ለመርሳት መምረጡን በማወቄ የቄሱን ሬድዮ ስሰማ ብዙ ጊዜ ተስፋ እቆርጥ ነበር፡፡

«ይህን ያህል ስለተረዳሽኝ አመሰግናለሁ» ስል መለስኩለት፡፡ «ይህን እያደረጉ ያሉት ሰዎች በጣም መጥፎዎች ናቸው፡፡

«መጥፎ? መጥፎ! ኢማኪዩሌ ከንቱ ግፈኞች ናቸው፡፡ ጭራቆች ናቸው! በደኅና ሁናቴ ላይ እንዳለሽ እንድታውቂ እፈልጋለሁ፡፡ እኔ እዚህ በሥራ ላይ እያለሁ አንዳች ጉዳት አይመጣብሽም» አለኝ በወገቡ ላይ ያነሄደረውን ጠመንጃ መታ መታ እያደረገ፡፡ «ላንቺ ከመከላከልም በላይ አደርግልሻለሁ፡፡ የተወሰነ ፍትሕም እለግስሻለሁ፡፡ አሁንም ይህ በኔና ባንቺ መካከል ይቅር እንጂ በቀል ከፈለግሽ ያንቺው ድርሻ ነው፡፡ ይፈልጉሽ የነበሩትን ወይንም ወላጆችሽንና ወንድሞችሽን የገደሉትን ሁቱዎች ስሞች ብትሰጭኝ አስገድልልሻለሁ፡፡

ያቀረበው ሐሳብ አስደነገጠኝ፡፡ በመታጠቢያ ቤቱ በነበርኩባቸው የመጀመሪያ ቀናት ሰሞን የተመኘሁት ይህንኑ ነበር፡፡ በኛ ሰዎች ላይ እየተፈጸሙ የነበሩትን ግድያዎች ቄሱ በነገሩን ጊዜ በቀልን በጽኑ በመፈለጌ ሁቱዎችን የምገድልበት ጠመንጃና መድፍ ቢኖረኝ ተመኝቼ ነበር፡፡ ያ ግን ልቤን ለእግዚአብሔር ምኅረት ከመከፈቴና ከገዳዮቹ ጋር ሰላም ከመፍጠሬ በፊት ነው፡፡

መኰንኑ ያቀረበልኝ ትክክለኛውን በቀል ነው - በኔ ትዕዛዝ የሚገድሉ የሠለጠኑና የታጠቁ ወታደሮችን፡፡ ማድረግ የሚጠበቅብኝ ብቸኛው ነገር አንድ ስም ሹክ ማለትና የቤተሰቤንና በሺዎች የሚቆጠሩትን በየጎዳናው እየበሰበሱ የነበሩትን ሰዎች ደም መበቀል ነው፡፡ በቀሉ ከልቡ የመጣ ቢሆንም በመኰንኑ ድምጽ ውስጥ ዲያብሎስ ይሰማኛል፡፡ በወቅቱ የምፈልገው ብቸኛ ነገር ሰላም ሆኖ ሳለ ይህ መኰንን በግድያ ቃል ኪዳኖች ይፈታተነኛል፡፡ እጁን ወደ ኪሴ አስገብቼ በአባቴ መቁጠሪያ ጠቀለልኩት፡፡ «ይህን አደርግልሻለሁ በማለትህ አመሰግናለሁ -»

«የምትፈልጊውን ሁቱ እገድልለሻለሁ!» ለመግደል በጣም ከመጓጓቱ የተነሣ ንግግሬን እንኳን አላስጨርስ አለኝ፡፡ «በዚህ ምሽግ የምታውቂው ሁቱ ካለ ንገሪኝና እኔ ራሴ እገድለዋለሁ፡፡ ሁሉንም እጠላቸዋለሁ፡፡»

«አዎን፣ እነዚህ ገዳዮች እንጂ ሁቱዎች ሁሉ ከንቱ አይደሉም መኰንን ሆይ፡፡ በዲያብሎስ ተታለዋል... ከአምላክ ርቀው ሄደዋል እና -»

«ኢማኪዩሌ ሁቱዎች ከንቱ ናቸው» እንደገና አቋረጠኝ፡፡ «ያደረጉት ከንቱ ነው፡፡ ይህ የጌታ ፈቃድ አሊያም የዲያብሎስ ሥራ እንደሆነ አትንገሪኝ - የሁቱዎች ሥራ ነው፡፡ እናም ብድራቸውን ያገኟታል፡፡ ሐሳብሽን ከቀየርሽ አሳውቂኝ፡፡ ለሌላ ሰው እኮ ልግደል አልልም፤ ታውቂያለሽ፡፡»

አምላክ የመኰንኑን ልብ በምህረቱ እንዲነካ ጸልዬ ለገዳዮቹም እንደገና ገጀራዎቻቸውን እንዲጥሉና የእግዚአብሔርን ምሳሪት እንዲለምኑ ጸለይኩ፡፡ የመኰንኑ ንዴት በሩዋንዳ የጥላቻና ያለመተማመኑ ዕዳት በቀላሉ እንደማይሰበር እንዳስብ አደረገኝ፡፡ እንዲያውም ግድያው ካቆመም በኋላ በእርግጠኝነት የባሰ መራር ሁኔታ ሊኖር ይችላል፤ ወደ ባሰ ሽብር የሚፈነዳ መራርነት፡፡ የእግዚአብሔር መለኮታዊ ምሳሪት ብቻ ያንን አሁን ከመከሰት ያቆመው ይሆናል፡፡ በምንም ዓይነት መንገድ አምላክ ቢያስቀምጠኝ ያንን ማየት እችላለሁ - ሌሎች እንዲኖሩ ማድረግም የሕይወቴ ሥራ ዋነኛ ክፍል ይሆናል፡፡

በቀጣዩ ቀን መኰንኑ ቃሉን መጠበቁን አሳየ - ሁቱዎችን በእውነት ይጠላ ኖሯል፡፡ አንድ እየደማ ያለና «የዘር ጭፍጨፋ ተራፊ ነኝ፤ የቆሰልኩትም ከቱትሲ አማጽያን ጎን ስዋጋ ነው» የሚል ሰው ወደ ምሽጉ ገብቶ ይዘዋወራል፡፡ መኰንኑ ግን ስላላመነው ወታደሮቹ አንበርከከውና ጠመንጃዎቻቸውን ራሱ ላይ ደግነው እንዲጠይቁት አደረገ፡፡ መጀመሪያ ላይ ሲጠይቁት የኢንተርሃምዌ አባል መሆኑን ካደ፡፡ ከብዙ ምርመራ በኋላ ግን ተስፋ ቆረጠና ተናዘዘ፡፡ መኰንኑም ለወታደሮቹ ራሱን ሲነቀንቅላቸው ጎትተው ወሰዱት፤ ከዚያ በኋላም በጭራሽ አላየነውም፡፡ ከወታደሮቹ አንደኛው በሌላ ጊዜ ሰውዬው የኢንተርሃምዌ ሰላይ እንደሆነ ማመኑን ነገረኝ፡፡

«ስለሱ አትጨነቂ - ከአሁን በኋላ አያስቸግርሽም» አለኝ፡፡

ለአከሰቶቹና ለልጆቻቸው በቻልኩት መጠን በቂ ምግብ መቅረቡን በማረጋገጥ፣ መድኃኒት ከወታደሮቹ በማምጣትና ቁስላቸውን በማከም እንክብካቤ አደረኩላቸው፡፡ እንዲያውም ምሽት ላይ እንዳይፈሩ በማሰብ በአቅራቢያቸው እተኛለሁ፡፡ ሆኖም ግን የሚጠበቅብኝን ያህል ጊዜ ከእነርሱ ጋር አላሳለፍኩም፡፡ በሕይወት በመቆየታቸውና

ደኅና በመሆናቸው ደስተኛ ነኝ፡፡ ያም ሆኖ ግን ላጣሁት ቤተሰብ ምትክ አይሆኑኝም፡፡ አዲስ ሕይወት መጀመር እንዳለብኝ ተሰማኝ፡፡

በመታጠቢያ ቤቱ አብሬያቸው ከነበርኩት ሴቶች ጋር እንኳን መግባባቱ ከበደኝ፡፡ የምንኖረው በምሽጉ የተለየዩ ክፍሎች ተለያይተን ነው፡፡ እናም አንዳችን ላንዳችን ፈገግታ ብናሳይም ብዙም አንነጋገርም፡፡ በዚያች ጠባብ ስፍራ አብረን ለረጅም ጊዜ ብንቆይም እርስ በርሳችን በደንብ አልተዋወቅንም፡፡ የዘወትር ተግባቦታችን በእጅ ምልክቶችና በከንፈር ንባብ ስለነበር ፍራቻን፣ ሽብርንና ተስፋ መቁረጥን ያስተጋባል፡፡ ምናልባት በመታጠቢያ ቤቱ ልናወራ ችለን ቢሆን ኖሮ ጥሩ ወዳጆች ልንሆን እንችል ነበር፡፡ ሆኖም ግን ምሽጉ ውስጥ እርስ በርስ መተያየታችን ብዙ አሰቃቂ ትውስታዎቻችንን ይቀሰቅስብን ጀመር፡፡

ለማናቸውም አዳዲስ ሰው ለመተዋወቅ በርካታ ዕድሎች አሉን፡፡ ከጭፍጨፋው የተረፉ አዳዲስ የቱትሲ ስደተኞች በየቀኑ ይደርሱ ጀመር፡፡ ብዙዎቹ የተወዛገቡ፣ የተምታታባቸውና ኪንያሩዋንዳ ብቻ የሚናገሩ ናቸው፡፡ እኔ ሁለት ቋንቋ ስለምናገር መኩንኑ ሁሉንም አዲስ-ደራሽ ስደተኞች እንድመዘግብለት ጠየቀኝ፡፡ እኔም ለማገዝ ደስተኛ ነኝ፡፡ ዕድሜያቸውንና ስማቸውን እየመዘገብኩ ጉዳታቸውንና የሚያስፈልጋቸውን የሕክምና እርዳታ ለፈረንሳዮቹ ወታደሮች አሳውቃለሁ፡፡ የግል ታሪካቸውንና ያለፉበትን ችግር ሁሉ እጽፋለሁ፡፡ በዚህ ሂደትም ብዙ አሰቃቂ ታሪኮችን ሰምቻለሁ፡፡ ቢሆንም የተወሰኑ ዘላቂ ጓደኞችን አፍርቻለሁ፡፡

አንድ አዲስ ጓደኛ የሆነችኝ ፍሎረንስ ስትሆን በኔ ዕድሜ ያለች ማራኪና ሽቁጥቁጥ ስትል ፈገግታዋ የሚስብ ሴት ነበረች፡፡ በገጀራ ዓይኖቿ መካከል መትተዋት በፊቷ ላይ ቁልቁል ከሚታየው ጉልህ ጠባሳ በቀር የግምጃ እራፊ ትመስላለች፡፡ እንደ ሌሎቻችን ሁሉ አሰቃቂ የሆነውን ታሪኳን መዝግቤያለሁ፡፡

ፍሎረንስ የመጣችው ከኔ መንደር ብዙም ከማትርቅ ትንሽ ከተማ ነው፡፡ ጭፍጨፋው ሲጀምር ቤተሰቧና ሦስት መቶ ጎረቤቶቿ ገዳዮቹ የቤተክርስቲያንን ቅድስና ያከብራሉ ብለው በማሰብ በአቅራቢያቸው ባለች ቤተክርስቲያን ከለላ ይጠይቃሉ፡፡ ሆኖም ግን ቱትሲዎችን በአንድ ቤት ታጅበው ማግኘታቸው ለገዳዮቹ ነገሩን አቀለላቸው፡፡ በቤተክርስትያኒቱ ውስጥ ባሉ አግዳሚ ወንበሮች መካከል እየተራመዱ ገጀራዎቻቸውን በመደዳ ግራና ቀኝ እየሰነዘሩ ሰዉን ተራ በተራ መመድመድ አልከበዳቸውም፡፡

‹‹መሣሪያም ሆነ ራሳችንን የምንከላከልበት ምንም መንገድ አልነበረንም›› አለች ፍሎረንስ፡፡ «የተወሰነ ልመናና ጩኸት ቢሰማም ብዙዎቻችን እዚያ ተቀምጠን የምንታረድበትን ተራ እንጠባበቅ ጀመር፡፡ መገደል እንደሚገባን እንዳሰብን ነው የሆነው - በእርግጥ አግባብ እንደሆነ ሁሉ ... ወደኔ ሲመጡ የማስታውሰው ብቸኛ

ነገር ገጀራ ወደ ፊቴ ሲሰነዘር ነው፡፡ ከዚያም ወደ አስከሬን መጣያቸው ልጣል ተጭኜ በመወሰድ ላይ ሳለሁ ነቃሁ፡፡»

የፍሎሬንስ ጠባሳ ጥልቅ ቢሆንም ለሞት የሚያደርሳት ግን አልነበረም - ሆኖም ጉዳዮቹ በአንድ የጭነት ተሽከርካሪ ላይ ከሌሎች አስከሬኖች ጋር ይወረውሯታል፡፡ ስትነቃ በወላጆቿ አስከሬን ላይ እንደሆነች ይገባታል፤ እህቷም ከነሱ በላይ ታቃስታለች፡፡

«በእህቴ ደረት ላይ የተሰካ ጦር አየሁ ... ልትሞት ትንሽ ቢቀራትም ግን በማጓራት ላይ ነበረች፡፡ ወደ እርሷ ለመቅረብ ስሞክር ከኛ ጋር ተሳፍረው ከነበሩት ጉዳዮች አንዱ ስንቅሳቀስ አይቶ በቀስቱ ይጓጉጠኝ ጀመር፡፡ እዚህ፣ እዚህ፣ እዚህ ጋ ወጋኝ» አለች ወደ ደረቷ፣ ሆዷና ጭኖቿ እያመለከተች፡፡ «ሲወጋኝ ምንም አልተንቀሳቀስኩም፤ እንዲያውም እግዚአብሔር ሕመሜን አርቆ ሕይወቴን እንዲያተርፋት ነበር የጠየቅሁት፡፡ ብዙ ስለደማሁ ጉዳዩ የሞትኩ ሳይመስለው አይቀርም፡፡

የጭነት ተሽከርካሪው ከአካንያሩ ወንዝ በላይ ባለ ኢንተርሃምዌዎች ብዙውን ጊዜ አስከሬን የሚጥሉበት ገደል አፋፍ ላይ ቆመ፡፡

«ሁሉንም አስከሬኖች በገደሉ ቁልቁል ሲወረውሯቸው ወንዙ ውስጥ ያርፋሉ» ስትል ፍሎረንስ ቀጠለች፡፡ «እግሮቼን ይዘው አየር ላይ ሲወረውሩኝ አስታውሳለሁ፤ የወራጅ ውሃውም ድምፅ በርቀት ይሰማኛል፤ ግን መውደቄን አላስታውስም፡፡ በቀጣዩ ቀን ጠዋት ወንዙ ዳር ጭቃው ላይ ነቃሁ፡፡ ወላጆቼ፣ እህቴ፣ ሁሉ..... ም እዚያ ወድቀዋል፤ ነገር ግን ሁሉም ሞተዋል፡፡ ገደሉን ሸቅብ ሳየው እንዴት እንደዳንኩ ሊገባኝ አልቻለም - የተጣልንበት ጥልቀት ቢያንስ መቶ ሃያ ክንድ ይሆናል፡፡ ማመን የምችለው እግዚአብሔር ለአንድ ዓላማ እንዳተረፈኝ ብቻ ነው፡፡»

ፍሎረንስ በወንዙ ዳር ለአንድ ቀን ከተኛች በኋላ ተነሥታ መሄድ ቻለች፡፡ በአቅራቢያው ወዳለ የደግ ሁቱዎች ቤት የግዷን ሄደች፡፡ አስገብተውና ቁስሏን ጠራርገው ደበቋት፡፡ «ሕይወቴን ቢያድኑኝም ታዲያ» ስትል ቀጠለች፤ «ልጆቸው በጠዋት ይወጣና የሚገደል ቱትሲ እስኪያጡ ድረስ ከኢንተርሃምዌዎች ጋር ሆኖ በከተማዬ ያሉ ቱትሲዎችን መግደሉን ቀጥሏል፡፡ ከዚያ በኋላ ለኔ ምንም ስሜት የሚሰጠኝ ነገር ጠፋ፣ ኢማኪዩሌ፡፡ እህቴና ወላጆቼ ሲሞቱ ለምን የተረፍኩ ይመስልሻል?»

«እግዚአብሔር ለአንድ ዓላማ ነው ያተረፈሽ» ስል መለስኩላት፡፡ «ታሪክሽን እየጻፍኩት ነው፤ አንድ ቀንም አንድ ሰው ያነበውና የተከሰተውን ችግር ሁሉ ይረዳበታል፡፡ አንቺ እንደኔ ነሽ፡፡ የተረፍሽው የደረሰብንን ሁሉ እንድትናገሪ ነው፡፡»

በስደተኞቹና በፈረንሳውያኑ አስተናጋጆቻችን መካከል ብዙ የትርጉም ሥራ ስለሠራሁ የተወሰኑትን ወታደሮች ላውቅ ቻልኩ። ከመካከላቸው ፒየር የተባለው ወታደር በፍቅር ዓይን ያየኝ ጀመር። የውስጠኛውን የምሽጉን ክፍል ቀን ላይ እንዲጠብቅ ተመድቧል። ሌሊት ግን ኮከቦቹን እያየሁ ስቀመጥ ከኔ ጋር በማውራት ጊዜውን ያሳልፋል። ፒየር በዕድሜ ከኔ በተወሰኑ ዓመታት የሚያንስ ወጣት ነው። ትሁት፣ ለሰው አሳቢና ጥሩ አድማጭም ነው። በኔ ቤተሰብና በመንደሬ ላይ ተከስቶ የነበረውን ነገር ነገርኩት፤ እርሱም ስለ ቤተሰቡ፣ በፈረንሳይ ስላሳለፈው ሕይወትና ወደ ሩዋንዳ ከመምጣቱ በፊት ስለተለያቸው ሴት የፍቅር ጓደኞቹ ነገረኝ። የወንድ ጓደኛ እንዳለኝም ሲጠይቀኝ ስለ ዮሃንስና ስለተለያየንበት መላ ቅጡ የጠፋበት መንገድ ነገርኩት።

ከፒየር ጋር ስሆን በአብሮነቱ በጣም ደስተኝነት ይሰማኛል። ከእርሱ ጋር ማውራት አእምሮዬን ካለሁበት ገሃዳዊ እውነታ ቢያንስ በጊዜያዊነት ያወጣዋል። ጊዜው ሲሄድ ፒየር ከኔ ጋር የሚሆንባቸውን ሰበብ አስባቦች መፈላልግ አበዛ - የሚበላ ያመጣልኛል፣ ወደ ምንጭ ውሃ ልቀዳ ስሄድ ጥበቃ ያደርግልኛል፤ የማነባቸውን መጻሕፍትም እየያዘልኝ ይመጣል። ጓደኞቹ ስለዚህ ጉዳይ ቢቀልዱበትም በእኔ በኩል ምንም ግድ አልሰጠኝም። በዘር ጭፍጨፋው የማይሰቃይ ጓደኛ ማፍራቴ ለኔ እፎይታ ነው። ተስፋዎቼንና ህልሞቼን ለእርሱ መንገርም እንደገና ሰው እንደሆንኩ እንዲሰማኝ አደረገኝ።

አንድ ቀን ፖል የተባለው የፒየር ጓደኛ ይህ ወጣት ወታደር በኔ ፍቅር እንደተነካ ሲነግረኝ አሳቀኝ። ልብሶቼን አልቀየርኩ፤ ለሦስት ወራት ያህል ገላዬን እንኳን በአግባቡ አልታጠብኩ።

«አዬ፣ ፒየር እኮ ሁሌ ስላንቺ ነው የሚያወራው» ሲል አረጋገጠልኝ። «በዚህ ሁሉ ነገር ውስጥ ብታልፍም ልቧ ክፍት ነው፤ ሳቂታነትና ጨዋታ-አዋቂነትም አላት› ይላል።»

«አይ ምነው በል! እንዲህ ስትቀልዱብኝ ጨዋታ አዋቂ መባል ይነሰኝ?» አልኩት። ወዲያውኑ ግን ፖል ቀልዱን እንዳልሆነ ገባኝ - ፒየር በፍቅሬ ተቃጥሎ ኖሯል።

በዚህ የፍቅር ገጠመኝ ኩራት ቢሰማኝም ፍላጎት አልነበረኝም። ቤተሰቤን አጥቻለሁ፤ የጦርነቱን መጨረሻ ለማየት እበቃ እንደሆን እንኳን እርግጠኛ አይደለሁም። ዮሃንስ እንደዚያ ከጣለኝ በኋላ በፍቅር ተስፋ ቆርጫለሁ። ያም ሆኖ ፒየር የተሰበረ ልቤ ሌላ ሰው ድጋሚ መውደድ መቻሉን እንድገነዘብ ረዳኝ።

በዚያ ምሽት እየተጣራ መጥቶ ለእግር ጉዞ ሽርሽር እንዳካሂደው ሲጠይቀኝ ፍቅሩን በኔ ላይ እንዳያባክን ልነግረው ወሰንኩ፡፡ እርሱ ግን ከልቡና በፍቅር ሲናገር ያልተዘጋጀሁበት ነገር በመሆኑ አስደነገጠኝ፡፡

«ኢማኪዩሌ በእውነት ለመናገር ከጓደኛ በላይ ሆነሽብኛል» ሲል ከልቡ ነገረኝ፡፡ «በጣም ልዩ ሰው ነሽ፡፡ ጭፍጨፋው፣ ሕመሙ፣ በዙሪያችን ያለው አመፅ ሁሉ ባለበት ሁኔታ ልትሰሚ የምትፈልጊው የመጨረሻው ነገር ይህ ነው፡፡ ግን እንዲያው ካንቺ ፍቅር የያዘኝ ይመስለኛል፡፡ አብሮነትሽን እፈልጋለሁ፡፡» ያን ሁሉ ሰዓት ሽርሽር ስናደርግ ብዙ እንዲናገር ብጠብቀውም ይቺን ብቻ ተናግሮ ዝም በማለቱና ያን ያህል ግልጽ በመሆኑ አስገረመኝ፡፡

‹‹ፒየር» ስል በዝግታ መለስኩለት፤ «ልቤ በሰቆቃ ተሞልቷል፤ አሁን በልቤ ውስጥ የቀረችው ስፍራ ለፈጣሪዬ ብቻ የምትሆን ነች፡፡ በፍቅር መውደቅን ላስበው አልችልም… ወደፊት ለሚገጥሙኝ ፈተናዎች መስጠት ያለብኝን አትኩሮት ማጣት የለብኝም፡፡ ራሴን መንከባከብ እኮ ይኖርብኛል …»

እጇን ያዝ አደረገችና «የምናገረው እኮ ከልቤ ነው … እወድሻለሁ፤ አሁንም እንከባከብሻለሁ፡፡ ካንቺ ጋር መሆን እፈልጋለሁ፤ ላጣሽ አልፈልግም፡፡»

ያን ያህል አውጥቶ በመናገሩ ትንሽ ተገርሜያለሁ፡፡ በእግዚአብሔር ፍቃድ ሳይሆን በአጋጣሚ የተገናኘን ሆኖ ተሰምቶኛል፡፡ ጌታዬ ዮሃንስን ለኔ የፈቀደልኝ ሰው እንዳልሆነ እንዳሳወቀኝ ሁሉ አሁን ፒየርንም እንደማይሆነኝ እያሳወቀኝ ነው፡፡ ይህን ጥያቄ በአዎንታ መቀበል ያለብኝ አይመስለኝም - ዝግጁ ስሆን እግዚአብሔር ፍቅረኛ እንደሚያመጣልኝ ታውቄኛል፡፡ ሲያመጣልኝም ምንም ዓይነት ጥርጣሬም ሆነ ማመንታት አይኖርም፡፡

«አይ ፒየር … አይሆንም፡፡ አሁን ልቤ ከቆሙት ይልቅ ከሞቱት ዘንድ ነው - ማልቀስ እንኳን ገና አልጀመርኩም፡፡ ‹እዬዬም ሲዳላ ነው፡፡› ጓደኝነትህ ለኔ ትልቅ ነገሬ ስለሆነ ላቆየው እፈልጋለሁ፡፡ ስለዚህ እባክህ እንዲሁ ጓደኛሞች እንሁን፡፡»

«አውቃለሁ» አለ በብስጭት፡፡ «እንግዲህ ልብሽን ማግኘት ካልቻልኩ እየወደድኩሽም መለያየታችን ግድ ነው፡፡ እንዲሁ እንደዋዛ ደኅና ሁኚ ልበልሻ፣ በይ ደኅና እደሪ ሆዬ፡፡» ዘንበል ብሎ አፌ ላይ በመሳም አስደነገጠኝ፡፡ የእርሱ ከንፈሮች የኔን ባገኙባት አፍታ ልቤ እንደ ሰም ስትቀልጥ ዓይኖቼን ጨፍኜ የመሳሜ ሙቀት ሕመሜንና ብስጭቴን አስረሳኝ፡፡ ፒየርም ሌሎቹን ወታደሮች ለመቀላቀል ሾር ብሎ ሲሄድ ፈገግታዬ እየከሰመ ሄደ፡፡ የቀረኝ ብቸኛ ነገር እንዳረከ አርገኝ ብዬ ሁሉን ነገር ለእግዚአብሔር መተው ነው፡፡

ላይሆንልኝ ነገር ለወንድሜ ለኤይማብል በሕይወት እንዳለሁ ላሳውቀው ፈለግሁ፣ ግን ምንም ዓይነት የመልዕክት መላላኪያም ሆነ የስልክ አገልግሎት የለም፡፡ የስልክ ቁጥሩም ሆነ የምከፍለው ገንዘብ የለኝም፡፡ ኤይማብል 5000 ኪሎሜትር ርቆ ሴኔጋል እየተማረ ስለሆነ እዚያው እንዲቀር ተመኘሁ፡፡ ወደ ሩዋንዳ ከተመለሰ እንደተቀረው ቤተሰቤ ሁሉ ይሞታል፡፡ ስለዚህ መልሼ የማገኘው ጦርነቱ ሲያልቅ ይሆናል፡፡ ግን መቼ ይሆን ጦርነቱ የሚያልቀው? ፈረንሳውያኑ ምንም ወሬ አልነገሩንም፤ የምናዳምጠው ሬድዮም የለን፡፡ ያሉን ብቸኞቹ የወሬ ምንጮች በእጅጉ ወደ ተጨናነቀው ምሽጋችን የሚመጡ አዳዲስ ገቢዎች ናቸው፡፡

በሐምሌ መጨረሻ አካባቢ ቱትሲዎቹ የሩአግ አማጽያን በሰሜን ድል ማድረጋቸውን ሰማሁ፤ በምሥራቅና በደቡብ ግን ጦርነቱ ቀጥሏል፡፡ ፈረንሳውያኑ በበኩላቸው እኛ ያለንበትን ምዕራብ ሩዋንዳን፣ የኪቩ ሐይቅን ዳርቻና የዛየርን ድንበር ጨምሮ ተቆጣጥረዋል፡፡ ለእኛ ጥሩ ዜና ቢሆንም ሁኔታው አሁንም እጅግ አደገኛ ነው፡፡ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ሁቱ ስደተኞች የኪቩ ሐይቅን ለመጠጋትና ወደ ዛየር ለማምለጥ በመሞከር ላይ ናቸው፡፡

በየቀኑ አዳዲስ የተረፉ ቱትሲዎች በራችን ላይ ይመጣሉ፡፡ ወደ ምሽጉ ከደረስኩ ጀምሮ በሦስት ሳምንታት ቁጥራችን ከተወሰኑ ደርዘኖች ወደ 150 ገደማ አድጓል - እኔም የስደተኞቹን ታሪክና የጤና ሁኔታ እጽፋለሁ፡፡ ብዙዎቹ ስደተኞች አንድም እጅና እግሮቻቸውን አጥተዋል አለያም በሌሎች ዓይነት አሰቃቂ ግርፋቶች ሳቢያ ቋሚ አካላዊ ጉዳቶች ደርሰውባቸው በጽኑ ቆስለዋል፡፡ ብዙውን ጊዜ ቁስሎቻቸው ከፉኛ የተመረዙ ስለሚሆኑ እንደማይድኑ አውቃለሁ፡፡ እጅና እግሮቻቸውን ያላጡትም ቢሆኑ አብዛኛውን ጊዜ የሚመጡት የሚወዱትን በማጣት፣ በሐዘንና በአዕምሯቸው በተቀረጸው ሽብር ምክንያት አብደውና ራሳቸውን ስተው ነው ::

በምሽጉ ውስጥ ካስቸገሩኝ ነገሮች አንዱ የወላጅ አልባዎች ነገር ነው፡፡ ለአብነት ዕድሜያቸው ሦስትና አራት ዓመት የነበረውን ከኪጋሊ ወደኛ የመጡትን ወንድማማቾች ፈጽሞ አልረሳቸውም፡፡ ገዳዮቹ ሲደርሱ ወላጆቻቸው በቤታቸው ኮርኒስ ላይ ይደብቋቸዋል፡፡ ወላጆቻቸው ሲገደሉ ልጆቹ ግን ከተወሰኑ ቀናት በኋላ በደግ ሁቱ ጎረቤቶቻቸው ተገኙ፡፡ እነርሱም ወደ ደቡብ ጦርነቱን ለማምለጥ ሲመጡ ያመጧቸዋል፡፡ ሰዎቹ ልጆቹን ለመውሰድ አዳጋች ወደሆነው ወደ ዛየር ሊሄዱ መሆኑን በመግለጽ ለፈረንሳውያን ወታደሮች ይሰጧቸዋል፡፡

ወታደሮቹም በአንዳንድ ምክንያቶች ሰበብ የልጆቹንም ሆነ የጎረቤቶቻቸውን ስም አልጻፉም፡፡ በተጨማሪም ሁለቱም ልጆች በምሽጋችን ሲደርሱ ከባድ ትኩሳት ይዟቸዋል፡፡ በምሽጋችን ውስጥ በጣም በዕድሜ ትንሾቹ ልጆች ምንም ሃይ ባይ ወላጅም ይሁን ዘመድ ስለሌላቸው ለጊዜው እኔው በማደጎ ተቀብዬ እንከባከባቸው

ገባሁ፡፡ በፈረንሳዩ መኰንን እገዛ በመማሪያ ክፍሉ ውስጥ አልጋ ዘረጋሁላቸው፤ ትኩሳታቸውን የሚቀንስ መድኃኒትም አገኘሁላቸው፡፡

ሲናገሩ መስማቱ ልቤን ነካው፡፡ የወላጆቻቸውን አስከሬኖች ቢያዩም የሞትን አይምሬነት ለመረዳት ግን ዕድሜያቸው አይፈቅድም፡፡ ትልቀኛው ልጅ ታናሽ ወንድሙን ይንከባከባል፤ አዲስ ለሚያገኟቸው ሰዎችም ትሁት እንዲሆን ያሳስበዋል፡፡ ሦስት አመቱ የሆነው ልጅ ታላቅ ወንድሙን *ፍሬንች ፍራይስ* የሚባሉትን ጣፋጭ ምግቦችና ለስላሳ መጠጥ እንዲያመጣለት ይጨቀጭቀዋል፤ ታላቅየውም ሁልጊዜ በግሩም ትዕግሥት ይመልስለታል፡፡

«እቤታችን እንዳልሆንን አስታውስ እንጂ … እዚህ ፍሬንች ፍራይስና ለስላሳ ልናገኝ አንችልም፡፡ እማማና አባባ መጥተው እስኪያገኙን መጠበቅ አለብን - ከዚያ ይሰጡናል፡፡ ማስቸገር የለብንም፣ መባለግ አያስፈልግም፤ ያለዚያ የባሰ ችግር ይደርስብናል፡፡» ታናሽ ወንድሙ ሲያለቅስበት «አታልቅስ … እማማና አባባ ቶሎ ይመጣሉ፤ ከዚያ ፍሬንች ፍራይስ እንዳሻህ ትበላለህ፡፡ እንጠብቃቸው፤ እማማና አባባ ሁሉንም ነገር ያስተካክሉልናል፡፡»

እነዚህ ልጆች በምንም ተዓምር ወላጆቻቸውን በድጋሚ እንደማያዩ አውቃለሁ፤ ከሁኔታው መረዳት እንደሚቻለው ሁሉም ዘመዶቻቸው የሞቱ ሳይሆን አይቀርም፡፡ የወደፊት ሕይወታቸው በሐዘን፣ በመገፋትና የሚያስፈልጋቸውን በመነፈግ እንዳይሞላ ሠጋሁ - ምሬትና ጥላቻ በቀላሉ ስር የሚሰዱበት ዓይነት ሕይወት፡፡

በነዚያ ምስኪን ዓይኖች የጥላቻና ያለመተማመን ቀለበት ሲያደራ ይታየኛል፡፡ ስለሆነም እግዚአብሔር ለምን እንዳዳነኝ የሚያመለክት ሌላ ምክንያት እያሳየኝ እንደሆነ አውቄያለሁ፡፡ አንድ ቀን ስበረታና ዐቅም ሳገኝ በዘር ፍጅቱ ወላጆቻቸውን ያጡትን ልጆች ለማገዝ የምችለውን ሁሉ እንደማደርግ ቃል ገባሁ፡፡ በሕይወታቸው ላይ ተስፋና ደስታን ለማምጣትና ቤተሰቦቻቸውንና የቤተሰብ ፍቅርን የነጠቃቸውን ጥላቻን እንዲርቁ ለማድረግ እሞክራለሁ፡፡

በነሐሴ መጀመሪያ ላይ መኰንኑ ምሽጉ በጣም ስለሞላ አብዛኞቹን ስደተኞች ሊያጓጉዛቸው እንደሆነ ነገረኝ፡፡ አዲሱ ምሽግ በኪቡዬ ከተማ ባለ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ ይሆናል፡፡ ንጹሕ ውሃ፣ የተሻለ ምግብና አልጋዎችም ይኖሩታል፡፡ እንዲመቻቸው ብዬ «ወንዶቹ ልጆቼ» መጀመሪያ እንዲዛወሩ አደረግሁ፡፡ አክስቶቼና ልጆቻቸውም መሄዳቸውን አረጋገጥኩ - አዎን አሁን ተሸሏቸዋል፤ ግን የተሻለ ሰላም እንዲሰማቸው ከራሳቸው በላይ ጣራና በዙሪያቸው ግድግዳ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ሄጄ ሁሉንም ሰው ለመንከባከብ ባቅድም መኰንኑ ቀርቼ በምሽጉ

ባለው ሥራ እንዳግዝ ለመነኝ። አሁንም ቢሆን አስተርጓሚ ያስፈልጋቸዋል። በተጨማሪም አዳዲስ በሕይወት የተረፉ ሰዎችም መግባታቸውን ቀጥለዋል።

«ያው ከቆየሽ ሕይወት ታድኛለሽ» ሲል ነገረኝ። እንዴት አሻፈረኝ እለዋለሁ? እዚያው ቀረሁ፤ ትንንሾቹን ወንድማማቾችም ከዚያን ጊዜ በኋላ ፈጽሞ አላየኋቸውም። ሌሎች በረብሻ ወላጆቻቸውን ያጡ ልጆችን ለመንከባከብ የገባሁትን ቃል ግን አልረሳሁትም። በሩዋንዳ የእነዚህ ዓይነት ልጆች እጥረትም የለም።

በአሮጌው ምሽግ 30 የሚሆኑ ስደተኞች ሲቀሩ ከነርሱ ውስጥ ስምንቱ ፍሎሬንስና ዢን ፖልን ዓይነቶቹ አዲስ ያፈራኋቸው ጓደኞቼ ናቸው። በጣም ቅርብ የሆኑ አባላትን የያዘችው ትንሿ ቡድናችን እንደ አነስተኛ ቤተሰብ ሆነች። በእርግጥ ትሥሥራችን በጣም የጠበቀ ስለሆነ ዘጠኞቻችንም በአንድ ላይ ሆነን ካልሆነ በስተቀር ከምሽጉ አንዛወርም አልን።

ቱትሲ ተፈናቃዮችን መቀበላችንን ብንቀጥልም መጠለያው ግን እያገለገለ ያለው እንደ መሸጋገሪያ ጣቢያ ነው። በሕይወት የተረፉትን እመዘግብና በአንድ ወይንም በሁለት ቀናት ውስጥ በከተማው ወዳለ ትልቅ መጠለያ እንዲዛወሩ እናደርጋለን። ከዚያም በነሐሴ መጀመሪያ ለወራት ያልሰማሁትን ነገር ሰማሁ - ጥልቅ፣ የሚያሸካካና ከልብ የሆነ ሣቅ። ከአዲሶቹ መጭዎች ስደተኞች ጋር ከመጣች አንዲት ሴትዮ ነው ሳቁ የመጣው። በተሸከርካሪ ወንበር ላይ ተቀምጣ በሰው እየተገፋች የምትሄደውን ይህች ሴትዮ ወታደሮቹ ከመጣችበት የጭነት ተሸከርካሪ እያወረዷት ነው። ወፍራም ስለሆነችና እግሮቿም በሽተኛ ስለሆኑ መራመድ እንደማትችል አውቄያለሁ። ይህ ሁሉ መከፋት ባለበት ምን የሚያስቅ ነገር አገኘች ብዬ ተገረምኩ። በኋላ ሲገባኝ የምትስቀው በሕይወት በመትረፏ ደስታ ተሰምቷት ኖሯል።

ወታደሮቹ በጥንቃቄ ተሸከርካሪ ወንበሯን መሬት ላይ ሲያስቀምጡላትና ሁለት ትንንሽ ልጆቿን ሲሰጧት አየሁ። ልጆቿ የፊቷን የተለያዩ ክፍሎች ሳሟት፤ እንደገናም ትስቅ ገባች - ሳቋም በመጠለያውም ግቢ አስተጋባ።

«አሎይዜ ነች» አለ ዢን ፖል። «በመጠለያችን አንድ ታዋቂ ሰው ገባ ማለት ነው።»

በእርግጥ ስለ አሎይዜ ሰምቼ ነበር። በልጅነቴ አንድ ሰው ጠንከሮ በመሥራትና በቁርጠኝነት በሕይወቱ የት እንደሚደርስ እርሷን በአርዓያነት እያነሱ ወላጆቼ በጣም ሲያወሩላት ሰምቻለሁ። አሎይዜ በዘጠኝ ዓመቷ የልጅነት ልምሻ ይዟት መራመድ ቢሳናትም በትምህርቷ ጥሩ ውጤት በማምጣት በሩዋንዳ ካሉ እጅግ ጎበዝ ልጆች አንዷ ለመሆን እንደበቃች ነግረውኛል። ስለሷ ከሰማሁት የማስታውሰው ያንን ብቻ ነው፤ ግን እንደተባለው በሀገሪቱ ዝና በማግኘቷ በመጠለያው ያሉ ብዙ ሰዎች ስለ እርሷ ሰምተዋል።

ዣን ፖል እንደነገረኝ ባሏ ኪጋሊ ላይ በተመድ ውስጥ ይሠራ ስለነበር አሎይዜ ሁሉንም የሌሎች *መንግሥታት* መልዕክተኞች ማወቅ ችላለች፡፡ «ሁሉንም ሰው ስለምታውቅ ለማንም ቢሆን ጥሩ ሥራ ማግኘት ትችላለች» አለኝ በኢድናቆት፡፡ ሰዎች «አካል ጉዳተኛ ባትሆን ኖሮ ጠቅላይ ሚኒስትር መሆን ትችል ነበር ይላሉ፡፡ ቱትሲ እንደሆነች አውቃለሁ፤ ግን የመንግሥት ኮንትራቶችን ለማግኘት ስትል የሁቱ መታወቂያ ደብተር ከዓመታት በፊት ገዝታለች … ይገርምሻል በጣም ቆራጥ ሴት ነች፡፡»

«እንግዲህ ሄጄ ይህችን ዝነኛ እንግዳችንን እመዘግባታለሁ» ብዬ ደብተሬን ያዝኩና ወደ ተሸከርካሪው ሄድኩ፡፡

አሎይዜ ከተቀመጠችበት ወንበር ሽቅብ እያየችኝ ደስታዋ ወዲያውኑ ተኖ ታለቅስ ጀመር፡፡ «ወይኔ አምላኬ፣ እናትሽን ቁርጥ እኮ ነሽ … አባትሽንስ ቢሆን! ሁልጊዜ አንቺንም ሆነ ቤተሰብሽን እጠይቃችኋለሁ እያልኩ አስብ ነበር፤ ሆኖም አልቻልኩም፡፡ ምን ይሄን እግር ይገቴ እንዴት ይሁንልኝ!

ሴትዮዋ ራሷን የሳተች ወይንም ሌላ ሰው መስያት የተምታታባት መሰለኝ፡፡ እስካሁን አግኝቻት አላውቅ፤ ታዲያ ማንነቴን እንዴት ልታውቅ ትችላለች?

«አእምሮዬን እንደሳትኩ አድርገሽ አትዪኝ ኢማኪዩሌ ኢሊባጊዛ፡፡ ማን እንደሆንሽ በደንብ አውቃለሁ፡፡ አምላክ ነፍሳቸውን በገነት ያኑርልንና ወላጆችሽ - በጣም ጥሩ ወዳጆቼ ነበሩ፡፡» አሎይዜ ልጆቿን አስቀምጣ፣ እንባዋን አባብሳ እጆቿን ዘረጋችልኝ፡፡

እንደዋዛ ቀረብ ብዬ እጆቼን ለሰላምታ ስዘረጋላት ክርኔን አፈፍ አድርጋ ጎትታ በደንብ አቀፈችኝ፡፡ ልትለቀኝ አልቻለችም፡፡ «እናትሽ ሕይወቴን አትርፋኛለች - ያን እንደማታውቂ እወራረዳለሁ! የስምንት ዓመት ልጅ ሳለሁ እናትሽ ትምህርት ብወድም ወላጆቼ ግን ሊያስተምሩኝ አቅሙ እንዳልነበራቸው ትሰማለች፡፡ እናም የአንድ ዓመት የትምህርት ክፍያዬን ሸፈነችልኝ … ታምሜ መራመድ ባቃተኝ ጊዜ እንኳን መከፈሏን ቀጠለች፡፡ በጣም ውለታዋ ስለከበደኝም በሕይወቴ አንድ ደረጃ ላይ መድረስ አለብኝ ብዬ ከማውቀው ከማንም ሰው አጠናን በላይ ማጥናት ጀመርኩ፡፡ ኢማኪዩሌ አሁን ያለኝ ነገር ሁሉ በእናትሽ ውለታ የተገኘ ነው፡፡ *መ*ልአከ ነበረች!»

አሎይዜ በስተመጨረሻም ከረጅም ጊዜ እቅፏ ስትለቀኝ ወደኋላዬ ተንገዳገድኩ፡፡ ከዚህች ጎበዝ ሴት ጋር በገጠመኝ በእንግዳው ከስተትም ተደናግጬ ራሴን ለማረጋጋት ራቅ ብሎ መሄድ አስፈለገኝ፡፡ «እስኪ ላንቺና ለልጆችሽ ትንሽ ምግብና ውሃ ልፈልግላችሁ» አልኳት፡፡ «አሁኑኑ ተመልሼ እመጣና እመዘግባችኋለሁ፡፡»

እየሄድኩ ሳለሁ አሎይዜ ጠርታኝ «ኢማኪዩሌ እዚህ አንቺ ጋ ያመጣኝ የእናትሽ መንፈስ ነው መሰለኝ! ብድሯ ስላለብኝ አንቺን በማገዝ እከፍለዋለሁ፡፡ እስኪ ላስብበት፣ አንቺን የምረዳበትን መንገድ ልፈልግ» አለችኝ፡፡

አንዲት በተሸከርካሪ ወንበር የምትሄድና እገዛዋን የሚፈልጉ ሁለት ትንንሽ ልጆች ያሏት ሴትዮ ምን ልታግዘኝ እንደምትችል እያሰብኩ ለሰላምታ እጇን አውለበለብኩና መንገዴን ቀጠልኩ፡፡ ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እግዚአብሔር በተዓምራዊ መንገዶች እንደሚሄድ ሊያስተምረኝ ነው፡፡

በቀጣዩ ቀን አሎይዜን ስመዘግባት በሕግ ሁቱ ብትሆንም ባሏ ፋሪ፣ ቱትሲ እንደሆነ ነገረችኝ፡፡ ያም ማለት ልጆቿ ሳሚና ኬንዛ እንደ ቱትሲ ይቆጠራሉ ማለት ነው፡፡ ለልጆቿ ደህንነት በማሰብ በኪጋሊ ያለውን ቤታቸውን ትታ ወደ ወላጆቿ ቤት ለመደበቅ ሄደች፡፡ ባሏ እሷ ስትሄድ ኮርኒስ ውስጥ የተደበቀ ቢሆንም ይዳን ይሙት የምታውቀው ነገር የለም፡፡

«የእናትሽን ውለታ ለመክፈል ምን ማድረግ እንዳለብኝ ወስኛለሁ» አለች አሎይዜ፡፡ «ጦርነቱ ሙሉ በሙሉ እንዳበቃ ኪጋሊ ወዳለው ቤቴ እወስድሻለሁ፡፡ እንደራሳችን ልጅ ሆነሽ መኖር ትችያለሽ፡፡»

ስለ አሎይዜ ያላመንኩት አንድ ነገር አለ፡፡ ፈገግ ብዬ ስለ ቸርነቷ አመሰገንኳት፡፡ ቢሆንም በመጠለያው የተወሰኑ ጓደኛ ቤተሰቦች እንዳሉኝና አብረን ለመሆን ቃል እንደተገባባንም ነገርኳት፡፡ ትከሻዎቿን ነቅንቃ ከማምናቸው ሰዎች ጋር ለመቆየት መወሰኔ ግሩም ብልሃት መሆኑን ነገረችኝ፡፡ በዚያ ነገሩ ሁሉ የተቋጨ መስሎኛል፤ ሆኖም ግን በቀጣዩ ቀን ይህች ሴትዮ ከጓደኞቼ ጋር በተቀመጥኩበት መጣች፡፡

«ኢማኪዩሌ ጉዳዩን አስቤበታለሁ፤ ታግተኛለች ብለሽ ካሰብሽ ጓደኞችሽን ሁሉ ወደ ኪጋሊ ማምጣት ትችያለሽ፡፡ ዘጠኛችሁንም በቤቴ አስቀምጣችኋለሁ! ቢጣበብም ይመቻል፡፡»

እርስ በርሳችን ተያይተን ተሣሣቅን፡፡ እንደዚህ ያለ እንግዳና ቸርነት የሚታይበትን ስጦታ እንዴት እንደምንቀበለው አናውቅበት አልን፡፡

«አስቡበት» አለች አሎይዜ ወንበሯን እያሽከረከረች በመሄድ ላይ ሳለች፡፡ «ከጦርነቱ በኋላ ለማድረግ የምታስቡት ሌላ ምን እንዳለ አላውቅም፡፡ ሁላችሁም ተሸብራችኋል ... እናንተ ልጆች እዚያች ከተማ ባለ ምርጥ ቤት ኑሩ ብዬ ልለምናችሁ መገደዴን ላምን አልችልም፡፡ ጦርነቱ እያለቀ ነው - ስለ ወደፊቱ ሕይወታችሁ ማሰብ ጀምሩ እንጂ!»

አሎይዜ ትክክል ነች፡፡ ዋና ከተማዋ በአማጽያኑ ቁጥጥር ስር ውላለች፤ ጦርነቱም ፍጻሜ ሊያገኝ የጊዜ ጉዳይ ብቻ ነው፡፡ ሁላችንም ቤተሰቦቻችንን፣ ቤታችንንና

ልብሳችንን ሳይቀር ያጣን ሲሆን ከኛ መካከል አንዲት እንኳን ሳንቲም ያለው ሰው የለም፡፡ የአሎይዜን ችሮታ መቀበል ጥሩ ውሳኔ መሆኑን ለመወሰን ረጅም ጊዜ አልወሰደብንም፡፡ በማግስቱም ችሮታዋን ለመቀበልና ለማመስገን በአንድነት ሄድን፡፡

«እኔን አታመስግኙኝ፤ የኢማኪዩሌን እናት እንጂ» አለች፡፡ «ይህን የማደርገው ስለ ሮዝ እንጂ ስለ እናንተ አይደለም!»

ለራሷ መሣቅ ጀመረች፤ ከዚያም እንደገና ልባዊ የደስታ ሣቅ በምሽጉ ሙሉ እስኪያስተጋባ ድረስ ቀጠለች፡፡

ምዕራፍ 20

ወደ አማጽያኑ የሚወስደው መንገድ

በነሃሴ መጨረሻ በአንድ ሞቃት ከሰዓት በኋላ የፊረንሳዩ መኪናን ምሽጉን ለቀን ልንሄድ እንደሆነ ነገረኝ። ዘመቻ ቱርኮይዝ ተጠናቀቀ፣ ስለሆነም ፊረንሳውያኑ ከሩዋንዳ ለመውጣት ይዘገጃጃሉ። «ምሽጋችንን ዛሬ እንዘጋለን» አለኝ። «በሁለት ሰዓታት ውስጥ ሁሉም ሰው ይህን ምሽግ ለቆ እንዲወጣ ይዘገጃጅ።»

«የት ነው የምንሄደው?» ስል ጠየቅሁት። «እዚህ ሰላሳ ሰዎች አሉ… የት ሂዱ ልበላቸው? ቤት የለንም!» በድንገተኛው ዜና ተገረምኩ።

«ሁላችሁንም ከቱትሲ ወታደሮች ጋር እንድትቆዩ ልንወስዳችሁ ነው። ሩአግ ወደ አካባቢው የተጠጋ ሲሆን ካለንበት ስፍራ የተወሰኑ ኪሎሜትሮች ራቅ ብሎም ምሽግ አቋቁሟል። እዚያ ወስደን ለእነርሱ እንሰጣችኋለን። ከራሳችሁ ሰዎች ጋር መሆኑ ይሻላችኋል።»

የቱትሲ ወታደሮቹ በመጨረሻ ወደኛ እየተዋጉ መምጣታቸውንና ኢንተርሃምዌዎችን ከሀገር እያስወጡ መሆናቸውን በመስማቴ ተደሰትኩ። ጀግናችን፣ የሩአጉ መሪ ፖል ካጋሜ፣ በኪጋሊ አዲስ መንግሥት ማቋቋሙን ሳይቀር ሰማሁ። እግዚአብሔር ይመስገን በመጨረሻም ሰላም አገኘን - ያች ቀን ደረሰች፤ የዘር ጭፍጨፋው መቆሙ ነው!

መሄዳችን መሆኑን በምሽጉ እየተዘዋወርኩ ለእያንዳንዱ ሰው ተናገርኩ። በቅርቡ ከመጡት አንዳንዶቹ ተጠራጠሩ፤ ፊረንሳውያኑ የማይታመኑና የስደተኛ መጠለያውን ያዘጋጁትም የዘር ጭፍጨፋውን ያስተባበሩትን ሁቱዎች በኪቩ ሐይቅ የማሻገርና ከሩዋንዳ በደኅና የማስወጣት እውነተኛ ተልዕኳቸውን ለመሸፈን እንደ ሰብዓዊ መከላከያ አድርገው ለመጠቀም ነው ሲሉ ተናገሩ።

«ይህን እንኳን አላምንም» አልኳቸው። «ፊረንሳውያኑ ለሳምንታት በደኅና ይዘውን ከርመዋል፤ ነጻ ሊያወጡንም ትንሽ ነው የቀራቸው! እናደርጋለን ያሉትን ሁሉ እያደረጉልን ነው።»

በተጠንቀቅ ስለሆንን ለመዘገጃጀት ጊዜ አልወሰደብንም። ጓዝ ብሎ ነገር ያለው ስደተኛ የለም። በመሆኑም የምንሸከፈው ኮተት የለንም። ያሉኝን ጥቂት ንብረቶች ሰባሰብኩ - የቁስ ሙሪንዚ ልጅ የሰጠችኝን ሹራቤንና ፎጣዬን፣ ፒየር የሰጠኝን ሁለት መጻሕፍትና የተወሰኑ ወታደሮቹ የሰጡኝን ትርፍ ሳሙናዎችና ቲሸርቶችን በከረጢት አደረግሁ። ይህን ሳደርግ ግን እናቴ ገዳዮቹ በቤታችን አካባቢ እንደተሰበሰቡ

እቃዎቿን በሻንጣዎች ስትከት የነበረው ትዝ አለኝና ካለፈው ሕይወቴ እቃዎችን ወደ አዲሱ ሕይወቴ ማንኳተት እንደሌለብኝ ወሰንኩ፡፡ በሁለቱ ሕይወቶቼ መካከል ንጹሕ መለያያ ለማድረግ ወሰንኩ፡፡ ከረጢቱን አንድ ሌላ ምስኪን ቤት-አልባ ቱትሲ ያገኘው ዘንድ በመመኘት ወደ መማሪያ ክፍሉ ወስጄ ጥጋት ላይ ተውኩት፡፡

ልሄድ ዘወር ስል በሩ ላይ ከቆመው ከፒየር ጋር ድንገት ግጥምጥም አልን፡፡ በሐዘኔታ አየኝና አንዲት ወረቀት ሰጠኝ፡፡ «እንዲያው ምናልባት ሐሳብሽን ከቀየርሽ ይህ የፊረንሳዩ አድራሻዬ ነው፡፡ በጣም እናፍቅሻለሁ፤ በልቤም አኖርሻለሁ፡፡ አምላክ በደኅና እንዲያቆይሽ እጸልያለሁ፡፡»

«በል ደኅና ሁን ፒየር፡፡ እግዚአብሔር ይባርክህ» ብልም እርሱ ግን ምላሼን እንኳን ሳይሰማ ሄዶ ኖሯል፡፡

በተሸከርካሪው ኋላ ላይ ለመውጣት የመጨረሻዋ ነኝ፡፡ የኋላ መዝጊያው ገጭ ብሎ ሲዘጋ የሸራ ከለላው እኛን ለመደበቅ ቁልቁል ተጋረደ፤ ተሸከርካሪውም ወደፊት ተንቀሳቀሰ፡፡ መቼም አሳልፌ የማልሰጠው ንብረቴን፣ አባቴ የሰጠኝን መቁጠሪያዬን፣ አወጣሁና ጸሎቴን አደረስኩበት፡፡ እግዚአብሔርን በአዲሱ መንገዳችን እንዲባርከንና ወደ ቱትሲ ወታደሮቹ በደኅና እንዲያደርሰን ጠየቅሁት፡፡

ተሸከርካሪው በግማሽ ክብ ቅርጽ የተደረደሩትን ብረት-ለበስ ተሸከርካሪዎችና ቁልቁል ጥርጊያ መንገዱን አልፎ ወደ ገዳዮች ባሕር ሰጠመ! ሸራው ላይ ባለች ትንሽ ቀዳዳ አጮልቄ በሺዎች የሚቆጠሩ ሁቱዎች በዋናው መንገድ ወደ ኪቩ ሐይቅ ሲተሙ አየሁ - ከመካከላቸው በመቶዎች የሚቆጠሩት የኢንተርሃምዌን የደንብ ልብስ ለብሰው ገጀራ ይዘዋል፡፡

«ወይ አምላኬ» አልኩ ተሸከርካሪው ላይ እንደገና ወድቄ፡፡ «ድጋሚ አያምጣው!»

ሁቱዎቹ መንገድ እንዲለቁና እንዲያሳልፉን የተሸከርካሪውን ጡሩንባ እየነፋን በተጨናነቀው መንገድ እናዘግም ገባን፡፡ ኢንተርሃምዌዎቹ ካስቆሙን ወይም ተሸከርካሪዎችን ከተበላሸ በደቂቃዎች ውስጥ ይረባረቡብናል፡፡ መታጠቢያ ቤቱን ለቅቄ ከወጣሁ ወዲህ ይህን ያህል ፈርቼ አላውቅም፡፡

«እባክህ አምላኬ» ስል ጸለይኩ፡፡ «ይህን ያህል አምጥተኸናል - አሁን ቀሪውንም ጎዳና ውሰደን! እነዚህን ገዳዮችም አሳውርልን ... እዚህ ተሸከርካሪ ጀርባ ላይ እንዲያዩ አታድርጋቸው፡፡ መሐሪው ጌታ ሆይ! ከነዚህ ጥላቻ ከተሞላባቸው ዓይኖቻቸው ሰውረን!»

ወደ ሩአግ ምሽግ ከሚወስደን መንገዳችን ከግማሽ በላይ እንደሄድን ተሸከርካሪው ቆመ። ፈረንሳዊው መኰንን ወደ ኋላ መጥቶ ሽራውን ገለጠና «በአካባቢው ተኩስ አለ የሚል ወሬ ደርሶናል፤ ስለሆነም በማናቸውም ሁኔታ ቢሆን ተኩስን የማስቆም ግዴታ አለብን። ስለዚህ ልንመለስ ስለሆነ የግድ እዚህ መውረድ አለባችሁ።»

አሳስቼ የሰማሁት መሰለኝ። «መልሰህ ትወስደናለህ ማለት ነው፣ አይደል?»

«አይ፣ መጠለያውን ልንዘጋው ስለሆነ ብትመለሱም የምታርፉበት ስፍራ የለም። እዚህ መውረድ አለባችሁ... አሁኑኑ። ይቅርታ እንግዲህ ኢማኪዩሌ።»

ባለፉት ጥቂት ሳምንታት መኰንኑን በደንብ አውቄዋለሁ። ሁቱ ገዳዮችን ስለሚጠላ ቱትሲዎችን በተቻለው መጠን ለመርዳት እንደሚፈልግ ተናግሯል፤ ስለሆነም በታጠቁ ኢንተርሃምዌዎች እጅ ሊጥለን ነው ብዬ ላምን አልቻልኩም። እርሱን ለማሳመን ከተሸከርካሪው ወረድኩ። «እባክህ፣ መኰንን ሆይ፣ እዚህ ከተውከን ምን እንደሚከሰትብን ከማንም በላይ ታውቃለህ። በዙሪያችን ገዳዮቹ እያንጎበጡ ነው! እባክህ ተለመነኝ ... የሩአግ ምሽግ ከዚህ በኋላ ግፋ ቢል አንድ ኪሎሜትር ስለሚርቅ እባክህ እዚያ አድርሰን፤ አሊያም መልሰህ ውሰደን ... እዚህ ለእርድ አትተወን!»

«ይቅርታ ኢማኪዩሌ። ትዕዛዝ አለብኝ።»

«እባክህ መኰንን ብትወስደን ምናለ!»

«አይ! ሰዎቸሽን አውርጅልኝ። መሄድ አለብን።»

አንድ ደርዘን ገደማ ኢንተርሃምዌዎች አሥር ጫማ በሚሆን ርቀት እየተከታተሉን፣ የምንነጋገረውን እየሰሙና ፍላጎታቸው በጣም አይሎ ስለቆሙ እየተከሰተ ያለውን ነገር ልናምን አልቻልንም። ጨነቀኝ፤ መሬቷም ዞረችብኝ፣ ለአንድ አፍታ እንኳን የማየው ነገር የቁጡ ፊቶችን ብዥታ ሆነ። ራሴን በተሸከርካሪው አንድ ጎን ላይ አረጋግቼ ቆሜ ለመጀመሪያ ጊዜ በመሬት ላይ ያሉትን አስከሬኖች ምንነት አወቅሁ - መንገዱን ተከትሎ ዓይኔ እስከሚያየው ድረስ ሳማትር አስከሬኖች በየቦታው ወድቀዋል።

መኰንኑን ቀና ብዬ አይቼ በዓይኖቼ ለመጨረሻ ጊዜ ተለማመጥኩት። ረብ-አልባ ነው - ወይ ፍንክች አለ። ምናልባት ቄሱና ሌሎቹ ስለ ፈረንሳውያኑ የተናገሩት ልክ ነው ማለት ነው። እውነት እዚህ የመጡት ገዳዮቹን ለመርዳት ይሆን? ይኸው በእርግጠኝነት ለሞት ሊተዉን ነው።

ለጓደኞቼ «ኑ ውረዱ» አልኳቸው። «ሁላችሁም ውረዱ ... ፈረንጆቹ እዚህ ትተውን ሊሄዱ ነው።»

ከተሸከርካሪው ጀርባ የሚመጡት ያለማመንና የፍርሃት ጩኸቶች እየቀረቡን የመጡትን ገዳዮች ትኩረት የበለጠ ሳቡ፡፡ አንዱን ኢንተርሃምዌ ዓይኑን ትኩር ብዬ አይቼ አትኩሮቱን ያዝኩበት፡፡ እንደኔ ዓይነት ሰው እንደሆነና በእውነት መግደል እንዳልፈለገ ልቤ ነግሮኛል፡፡ መቁጠሪያዬን ይዤ ለእርሱ የፍቅር መልዕክት ለመላክ ቁርጠኝነቴን ሁሉ ሰበሰብኩት፡፡ አምላክ ገዳዩን በፍቅሩ ኃይል እንድዳስሰው እንዲጠቀምብኝ ጸለይኩ፡፡

ዓይኖቼን አልጨፈንኳቸውም ... እናም ያንድ ሰው ዕድሜ ለመሰለኝ ያህል ጊዜ ተፋጠጥን፡፡ በመጨረሻም ገዳዩ ሳፈጥበት እይታውን ወደ ሌላ አቅጣጫ አዞረ፡፡ ሰይጣን ሰውነቱን ትቶት እንደሄደ ሁሉ ጀርባውን አዙሮ ገጀራውን አሽቀንጥሮ ጣለው፡፡ በአንጻሩ ሌሎች ብዙ ዲያብሎሶች የእርሱን ስፍራ ለመተካት ተዘጋጅተዋል፡፡ ቢያንስ 15 ኢንተርሃምዌዎች ከተሸከርካሪው የተወሰኑ እርምጃዎች ርቀት ላይ ገጀራ ይዘው ፊታቸውን ተኮሳትረው ቆመዋል፤ እየተከሰተ ያለውን ነገር ምንነት በማጤን ከጓደኞቼ አንዳቸው እንኳን ለመውረድ አለመድፈራቸውን ያዩ ይዘዋል፡፡

ከመውጣት ውጪ ምንም አማራጭ የለንም፡፡ ሰላሳችንም እዚያ ገዳዮቹን ተጋፍጠን እስከንቆም ድረስ ጓደኞቼ አንድ በአንድ እየዘለሉ ወረዱ፡፡ ሁሉም ወርዶ እንዳለቀ ሁለት የፈረንሳይ ወታደሮች አሎይዜን አወረዷት፤ ልጆቿንም ኬንዛንና ሳሚን ከጎኗ አደረጉላት፡፡ ወታደሮቹ ተሳፈሩና ተሸከርካሪው በአቧራና እርግጠኝነት እጦት ደመና ውስጥ ትቶን በከፍተኛ ፍጥነት ነጎደ፡፡

አንደኛው ገዳይ «እነዚህን ሁሉ ቱትሲዎች እዩዋቸው» ሲል በመገረም ተናገረ፡፡ «እንዴት ነው እስካሁን በሕይወት ሊኖሩ የቻሉት?»

«የፈረንሳይ ወታደሮች ከለላ ሰጥተዋቸው የነበሩት በረሮዎች ናቸው» አለ ሌላኛው፡፡ «እስኪ አሁን ማነው የሚያድናችሁ? በረሮ ሁላ!»

ጓደኞቼ በጣም ስለፈሩ መንቀሳቀስ እንኳን ተሳናቸው፡፡ ለጨካኝ ገዳዮች መላ በመዘየድ ባለሙያ የሆንኩ ይመስል ጎሰም አድርገው ምን ማድረግ እንደሚገባን ጠየቁኝ፡፡ ፍሎሬንስና ቤተሰቧ ገዳዮቹ ቆራርጠው እስከሚገድሏቸው ተራቸውን እየጠበቁ በቤተክርስቲያን የተቀመጡችበትን ታሪክ እያስታወስኩ ፊቷ ላይ ያለውን የገጀራ ጠባሳ አየሁት፡፡ ያበጠው ይፈንዳ እንጂ እኔማ ቆሜ የምታረድበትን ተራ አልጠባበቅም፡፡

«እንሂድ» አልኩ፡፡ «ወደ ሩአግ ምሽግ በእግራችን እንሄዳለን - ወታደሮቻቸው ቅርብ ናቸው፡፡»

ገዳዮቹ ሩአግ ስል ሲሰሙኝ ጊዜ ተናደዱ፡፡

መንቀሳቀስ ብንጀምርም ብዙም መሄድ አልቻልንም። *መንገዱን* የድንጋይና የሰው አስከሬን በጣም ስለሞላው የአሎይዜን የ*መቀመጫ* ተሽከርካሪ *መግፋቱ* አስቸገረን - አንዱ ጎማው በተቀረቀረ ቁጥር ሁላችንም እንቆማን። የአሎይዜ ልጆችም እያለቀሱ የእናታቸውን ከርኖች ያዙ።

ጓደኞቼን ገርን ፖልንና ካሬጋን ከቡድኑ ነጥዬ ወሰድኳቸው። «እናንተ ሁለታችሁ ከኔ ጋር ኑ - ሌሎቻችሁ ከአሎይዜ ጋር ትቆያላችሁ... እና ደግሞ ጸልዩ። ቱትሲ ወታደሮቹን ፈልጌያቸው እመጣለሁ። ከዚህ ስፍራ አትሂዱ፤ ያለዚያ በዚህ የሁቱ ጎርፍ መካከል ላገኛችሁ አልችልም።»

አሎይዜ በጥርጣሬ እያየችኝ «እውነት መሄድሽ ነው? በእርግጠኝነት ይገድሉሻል! ይልቅ ወንዶቹ ቢሄዱ ይሻላል» ስትል ለመነችኝ።

«አይሆንም እኔ ነኝ የምሄደው ... እናንተ ብቻ በጸሎታችሁ ላይ አተኩሩ።»

ያን ካልኩ በኋላ ፈረንሳውያኑ ትተውን ከመሄዳቸው በፊት ይዘውን ይሄዱ የነበረበትን አቅጣጫ ተከተልኩ። ስንሄድ ከአምላክ ጋር በሙሉ ልቤና ነፍሴ እያወራሁ በመቁጠሪያው ጸሎት አደርስ ጀመር። «እግዚአብሔር ሆይ! እውነት በሞት ፈፋ ውስጥ እየሄድኩ ነው - እባክህ ድረስልኝ። በፍቅርህ ኃይል ከልለኝ። ይህን የምሄድበትን መንገድ ፈጥረኸዋል፤ ስለዚህ እባክህ እነዚህን ገዳዮች የልጅህን ደም እላዩ እንዲያፈሱት አታድርጋቸው።»

ከትልቁ ቡድን ተነጥለን ስንሄድ ሦስት ኢንተርሃምዌዎች ተከተሉን፤ አንዱ እንዲያውም እኔን ዐወቀኝ። «ይህችን በረሮ አውቃታለሁ» አለ። «የሊኦናርድ ልጅ እኮ ነች - ለወራት ስንፈልጋት ቆይተናል! አስካሁን አለች ብዬ አላምንም... ሌሎቹን ገድለናቸዋል፤ ግን ይቺ ደቃቃ በረሮ አምልጣናለች!»

በቻልኩት መጠን ፈጥኜ እየተራመድኩና የአባቴን መቁጠሪያ በእጄ አጥብቄ ይዤ «ጌታ ሆይ» ስል ጸለይኩ። «አንተ ታድነኛለህ። ፈጣሪዬ እንደምትንከባከበኝ ቃል ገብተህልኛል፣ እንግዲህ አለኝታነትህን አሁኑኑ እፈልጋለሁ። በጀርባዬ ሰይጣኖችና የሎሶች አሰፍስፈዋል። አምላክ ... እባክህ ጠብቀኝ። ከነዚህ ሰዎች ልብ ውስጥ ሰይጣኑን አስወጣው፤ ጥላቻቸውንም በቅዱስ ፍቅርህ አሳውረው።»

ድንጋይ ወይንም አስከሬን እንዳያደናቅፈኝ ሳልጠነቀቅ፣ እምነቴን በጌታዬ ላይ ጥዬና ደኅና ወደምሆንበት ስፍራ እንዲመራኝ እግሮቼን እንኳን ማየቴን ትቼ ተራመድኩ። የምንጓዘው በጣም በፍጥነት ነው፤ ቢሆንም ግን ገዳዮቹ ገጀራዎቻቸውን በአየር ላይ እያወናጨፉ ከበውናል። ማንም ከለላ የሚሆነን የለም። ታዲያ ለማጥቃት ምንድነው የሚጠብቁት?

«ከገደሉኝ፣ እግዚአብሔር፣ እንድትምራቸው እለምንሃለሁ፡፡ ልባቸው በጥላቻ ታውሯልና፤ ለምን ሊጎዱኝ እንደሚፈልጉም አያውቁትም፡፡»

ግማሽ ኪሎሜትር በዚያን ዓይነት ሁኔታ ከሄድን በኋላ ዣን ፖል «እዩ ሄደዋል...ሄደዋል!» አለኝ፡፡

ተመልሼ ሳይ እውነት ኖሯል - ገዳዮቹ ትተውን ተመልሰዋል፡፡ ዣን ፖል በኋላ ላይ ምናልባት የሩአግ ወታደሮች በቅርብ እንዳሉ ስላወቁ ይሆናል ቢልም ትክክለኛውን ምክንያት ግን አውቄዋለሁ፤ በዚያ መንገድ ላይ ሕይወታችን ስላተረፈልን እግዚአብሔርን ማመስገኔን አላቆምኩም!

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ በአንድ የሩአግ ኬላ ብዙ ደርዘኖች ረጃጅም፣ ቀጫችንና ኮስታራ የቱትሲ ወታደሮችን ዘበኝነት ቆመው አየን፡፡ በለየለት ሩጫ ሄጄ እፊት ለፊታቸው ተንበረከክሁ፡፡ ዓይኖቼን ጨፍኜ የምስጋና መዝሙር ዘመርኩላቸው፡፡

«ተመስገን አምላኬ፣ ተመስገን ጌታዬ፣ ድነናል! ተመስገን አምላኬ፣ ደረሳቸሁልና፡፡ ተባረኩ፤ ሁላችሁም ተባረኩ! አይ፣ ያለፍንበትን ብታዩልን፡፡ እናመሰግናለን ለ - »

አስደንጋጭ ቀጭ ቀጭ የሚል የጠመንጃ መሳቢያ ሲሸለቀቅ የሚያሰማው ድምፅ ስላቋረጠኝ የጀመርኩትን ንግግር ለመጨረስ አልቻልኩም፡፡ ዓይኖቼን ገልጬ ሳይ የጠመንጃው አፈሙዝ ፊቴ ላይ ተደግኗል፡፡

ምዕራፍ 21
ወደ ኪጋሊ

ወይ አምላኬ፣ ይህን የቅዠት ሕይወት ይበቃል የምትለው መቼ ይሆን?

ወደ ጠመንጃው አፈሙዝ ቀና ብዬ ካየሁ በኋላ ክፋት ወደሚነበብባቸውና ወደ ቁጡዎቹ የቱትሲው ወታደር ዓይኖች አማተርኩ። ሃያ ከማይሞሉ ደቂቃዎች በፊት ያፈጠጥኩባቸውን የገዳዩን ዓይኖች አስታወሱኝ።

የዘር ፍጅቱ ከጀመረ ጊዜ ጀምሮ ከመአት ይሰውሩናል ብለን ተስፋ ስናደርግባቸው የቆየነው የሩአግ ወታደሮች እነዚህ ከሆኑ አሁን ለኔ ትክክለኛው የመሞቻ ሰዓቴ ነው። ጎረቤቶቼ ከድተውኛል፣ ገዳዮቹ እንደዚያ ሲፈልጉኝ ከርመዋል፣ ፈረንሳውያኑ ትተውኛል፣ አሁን ደግሞ ቱትሲ ወገኖቼ ጭንቅላቴን ሊያፈርሱት ቃጥቷቸዋል።

ያንተው ድርሻ ነው፣ እማዚአብሔር፣ ሰል በውስጤ ጸለይኩ። ያንተን ፍቃድ እየፈጸምኩ እስከሆነ ድረስ ኖርኩም ሞትኩ ለኔ ምንም ችግር የለውም። እዚህ አምጥተሽኛል - መወሰኑ እንግዲህ ያንተው ድርሻ ነው።

ቀስ ብዬ እጆቼን በአየር ላይ እያነሳሁ ሁለቱ ጓደኞቼና እኔ ቱትሲዎች መሆናችንን እያብራራሁ ለመቆም ሞከርኩ «ፈረንሳውያኑ ወታደሮች መንገድ ላይ ጥለውን ሄዱ ... የጭፍጨፋው ሌሎች ተራፊዎች ከኋላችን በገዳዮች ተከበዋል። እባካችሁ እጅግ ከመዘግየቱ በፊት ልትረዷቸው ይገባል፤ ኧረ ድረሱላቸው።»

«አፍሽን ዝጊና መሬቱ ላይ ቁጭ በይ!» ወታደሩ በጠመንጃው እየጎሰመኝ ጮኸ።

«ቱትሲዎች ከሆናችሁ እንዴት ነው እስካሁን ልትኖሩ የቻላችሁት?!» ሌላው ጠመንጃውን በኔ ላይ ደግሞ ጮኸ። «ሁሉም ሞቷል፣ ሁሉም! እናንተ ራሳችሁ ገዳዮች ናችሁ... የሁቱ ሰላይ ሁላ! ጆሮ ጠቢዎችን ምን እንደምናደርግ ታውቃላችሁ? አርፋችሁ ተቀመጡ፤ እንዳትንቀሳቀሱ - አንዲትም ቃል እንዳትተነፍሱ፤ ዋ ቀስቀስ ትሉና! እያንዳንድሽ ቱትሲ ነኝ፣ ጂኒ ጃንካ ብትዪ የሚሰማሽ ያለ አይምሰልሽ!»

በቁጡ ወታደሮች ስለተከበብን ማውራት ፍሬ አልነበረውም። አፈን ዘግቼ ዕጣ ፈንታዬ ያስቀመጠልኝን እጠብቅ ገባሁ፤ ደቂቃዎች አለፉ። በቃሌ ጸንቼ ወታደሮቹን እንዲያድኗቸው እንድልክላቸው የሚጠብቁትን አሎይዜንና ሌሎቹን በገዳዮቹ የተከበቡትን አስብኳቸው። እንግዲህ እግዜር ይሁናቸዋ፤ ሌላ ምን እላለሁ?

በኋላ ላይ የአማጽያኑ ወታደሮች አዛዥ ሊመረምረን መጣ፡፡ ይጠብቁን የነበሩት ወታደሮች ሰላምታ ሰጡት፤ «ሻለቃ» እያሉም ይጠሩታል፡፡ ረጅም፣ እንደዱላ የቀጠነና በሕይወቴ ካየኋቸው ሰዎች ሁሉ የተረጋጋ የሚመስል ነው፡፡ ቤቱን ሰብረን ስንገባ የተያዝን ሌቦች እንደሆንን ሁሉ ገረመመን … የፈረንሳይ ወታደሮች የኢንተርሃምዌውን ሰላይ እንደያዙ በፊታቸው ላይ ይታይ የነበረው ዓይነት ገጽታ ይታይበታል፡፡ ያ ሰው ምን ዕጣ እንደገጠመው አስታውሼ አማተብኩ፡፡ ሻለቃው ከዘር ፍጅቱ የተረፍን መሆናችንን አለማመኑ ያስታውቃል፡፡ ይህንንም በማየቴ በመንገድ ዳር ስለተውናቸው ምስኪን ነፍሶች እጸልይ ጀመር፡፡

በዚች ቅጽበት እግዚአብሔር ለእኛ በድጋሚ ጣልቃ ገባልን፡፡

«ኢማኪዩሌ? ኢማኪዩሌ ኢሊባጊዛ?» *ከሻለቃው ጎን የተቀመጠ ወታደር ሰሜን እየጠራ ባለማመን አፈጠጠብኝ፡፡ «ኢማኪዩሌ! ኣይ፣ ኣንቺማ ኣትሆኚም፣ እንዲያው ትሆኚ ይሆን?* አንቺ ነሽ?»

«ባዚል?»

«አንቺ ነሽ!» ጠመንጃውን አስቀመጠና ተንበርክኮ አቀፈኝ፡፡

ባዚል ቱትሲ አማጽያኑን ደግፎ ለመዋጋት የዘመተ ሁቱ ጎረቤታችን ነው፡፡ ከትምህርት ቤት ጀምሮ እንተዋወቃለን፡፡ እናቴ ለረጅም ዓመታት ተሰጥኦ የነበረውና ጎበዝ ተማሪዋ ስለነበር ትወደዋለች፡፡ እማማ ለእርሱ የተለየ ፍቅር ስለነበራት እቤት ብዙ ጊዜ ስለምትጋብዘው «የመምህርት ብርቅዬ የቤት እንስሳ» እንለዋለን፡፡

«ይቺን ልጅ ታውቃታለህ?» ሻለቃው ባዚል አቅፎኝ ሲጨርስ ጠየቀው፡፡

«እንዴ አዎን አብረን ነው የተማርነው፡፡ ወላጆቿ በመንደራችን እጅግ የተከበሩ ቱትሲዎች ነበሩ - በጣም ጥሩ ሰዎች ናቸው፡፡ ምንም ችግር የለባትም ሻለቃ … ሰላይነቱ ኣይነካካትም፡፡ ኢማኪዩሌ የምትለው ሁሉ ፍጹም ሃቅ ነው፡፡»

ባዚልን በምፈልግበት አፍታ ስለላከልኝ አምላኬን በቶሎ አመሰገንኩት፡፡ ወታደሮቹ የደገኗቸውን ጠመንጃዎች ዝቅ አደረጉ፤ ሻለቃውም እጃቸውን ዘርግተው ሰላምታ አቀረቡልኝ፡፡ «ሻለቃ ንትዋሊ እባላለሁ» አሉኝ፡፡ «ስለ ግርታው ይቅርታ፤ በእርግጥ ሰላዮችም በየስፍራው አሉ፡፡ እዚህ አካባቢ አሁንም በጣም አስቸጋሪ ነው፤ ግን ከኛ ጋር ከሆናችሁ ዘንዳ ሐሳብ ኣይግባችሁ፡፡ ለእናንተ ጦርነቱ አልቆላችኋል … ከአሁኗ ደቂቃ ጀምሮ ከማናቸውም ጥቃት እንከላከላችኋለን፡፡»

«አመሰግናለሁ ሻለቃ፤ እጅጉን የእርስዎን ከለላ የሚፈልጉት ግን ጓደኞቼ ናቸው» ስል ወዲያውኑ ነገርኳቸው፡፡ «ፈረንሳውያኑ ወታደሮች የተዉን በኢንተርሃምዌዎቹ መሐል ነው፤ በመሆኑም በመንገዱ ወደ ግማሽ ኪሎሜትር ወርዶ 30 የቱትሲ

ርዝራዦች በገዳዮች ተከበው ይገኛሉ። እስካሁን ድረስ በሕይወት መኖራቸውንም አላውቅም። እባክዎን ...»

ተናግሬ እንኳን ሳልጨርስ ሻለቃው የተወሰኑት ወታደሮች አሎይዜንና ሌሎቹን እንዲያመጧቸው ለአንዱ ምልክት ሰጡት። «ስለጓደኞችሽ አትጨነቂ። እንደርስላቸዋለን።»

«አመሰግናለሁ... ፈጣሪ ይባርክዎ! አዪ፣ ሌላ ምን እላለሁ!»

ወታደሮቹ ሌሎቹን ለማገዝ ሲሄዱ ባዚል ከጎኔ ተቀምጦ በሥጋት የጥያቄ መአት አወረደብኝ - «ይኸው እቤት ከሄድኩ ስንት ወሬ ... የሰፈራችንን ወሬ ሰምተሻል? መምህርት እንዴት ናቸው - እናትሽን ማለቴ ነው? አልበረቱም? ስለ ወላጆቼ፣ ወንድሞቼና እህቶቼስ የሰማሽው ነገር አለ? ለመጨረሻ ጊዜ በጠየቅኳቸው ጊዜ አገሪቱን ለቀው ሊሄዱ እየተዘገጃጁ ነበር... ወጡ እንዴ?»

እጄን በባዚል ክርኖች ላይ ጣል አደረግሁ። ልቀሰቅስበት የምችለው ሕመም ይታወቀኛል፤ ስለሆነም በተቻለኝ መጠን ረገብ ለማለት ሞከርኩና «ስለዚህ ጉዳይ እንዴት እንደምነግርህ አላውቅም፣ ባዚል፣ እውነቱን ከመናገር በቀር። ሁሉም ሞተዋል - የኔም፣ ያንተም ቤተሰብ ... በመንደራችን ያለ ቱትሲና ለዘብተኛ ሁቱ ሁሉም ማለት በሚቻል ሁኔታ በሞት ጎዳና ተከታትለው ሄደዋል - አዪ! ደመ-ከልብ ሆነው ቀርተዋል ወንድሜ» ብዬ አረዳሁት።

መናገር እንደረሳ ሁሉ ብቻ ዝም ብሎ ያስተውለኛል፤ ከዚያም በእግሮቼ ስር ጥቅልል ብሎ ደረቱ ትር ትር እያለ በጠመንጃው ሰደፍ ላይ ያነባ ጀመር። ምስኪን ባዚል... ወላጆቹን፣ አራት ወንድሞቹንና ሦስት እህቶቹን አጣ። ውይ አንጀት ሲበላ!

እንደደረስን በዚያን ዓይነት ጥርጣሬ ለምን እንዳስተናገዱን አሁን ገባኝ። ከእነዚህ ወታደሮች አብዛኞቹ ከዩጋንዳ ድረስ እየተዋጉ ስለመጡ በመንገዳቸው ስለቤተሰቦቻቸው ምንም ወሬ አልሰሙም። አሁን ሲመለሱ ቤተሰቦቻቸውን በሕይወታቸው ሙሉ ባመኗቸው ሰዎች፣ በጎረቤቶቻቸው፣ ታርደው ያገኟቸዋል። በአማጽያኑ ምሽግ ቁዘማ ነግሷል።

እኔም ብዙም ደስታ አልተሰማኝም። ባዚልን በማርዳቴ ተጸጽቻለሁ፤ ደቂቃዎችም ባለፉ ቁጥር አሎይዜንና ቡድኗን የሚፈራው ነገር ገጥሟቸው እንዳይሆን በመስጋት ስለደህንነታቸው በጣም እየጸለይኩ ሳለ የደስተኛዋን ጓደኛዬን የተለመደ ሣቅ እየመጣ ካለው የሩአግ ተሽከርካሪ ሰማሁት።

«ኢማኪዩሌ፣ ይህ የምትጸልዩው ጸሎት ምንም ዓይነት ይሁን ምን መጸለይሽን እንዳትተዪ።» ስትል አሎይዜ እየሳቀች ነገረችኝ። «እነዚያ ገዳዮች እኮ ሊቆራርጡን ቢፈልጉም መንቀሳቀስ እንደተሳናቸው ነው እይታቸው የሚያሳየው ... እዚያው ባሉበት

እንደ በረዶ እኮ ነው የሆኑት! በአንበሶች ጉድጓድ እንደተጣለው እንደ ዳንኤል ነበር እኮ የሆንነው ... በአንበሶች ጋጣ እንደተጣለው ዳንኤል ልጇ!»

አሎይዜ ልጆቿን ሳብ አደረገችና ጠበቅ አድርጋ አቀፈቻቸው፤ ከዚያም እንባ በጉንጮቿ እስኪወርድ ድረስ በሣቅ ትንከተከት ገባች፡፡ ልቤ ተነሣሳችና «አምላክ ከእንግዲህ ከገዳዮቹ ጋር ድጋሚ አያገጣጥመንም፡፡ ይህችን ደፍሮ ለማለት ያደርሰኝ እንደሆነ ካሁን በፊት አላውቅም ነበር፤ ለማንኛውም አሁን ጭፍጨፋው አብቅቷል - እግዚአብሔር አትርፎ አዲስ ሕይወት ሰጥቶናል፡፡ አምላክ ይመስገን! እናመሰግንሃለን ፈጣሪ!» አልኩ፡፡

አሎይዜ ሣቅ ብላ «ይሁን ይደረግልን፣ ኢማኪዩሌ... ይሁና!» አለችኝ፡፡

የአሎይዜ ሳቂታነትና ነጻነት ያለበት መንፈሷ ያዘኑትን ወታደሮች አስደሰታቸው፡፡ በምሽቱ ባሳለፍናቸው የመጀመሪያዎቹ ጥቂት ሰዓታት እስካሁን ስላገኘቻቸው ዝነኛ ሰዎች የተለያዩ ነገሮችን በማውጋት ስታዝናናቸው ቆየች፡፡ ከሁሉም በላይ የተማረኩት ግን በማይናወጠው አዎንታዊ ምኞቷ ነው - በሕይወቷ ስለገጠማት ዕጣ በፍጹም አታማርርም - እያንዳንዷንም ቅጽበት በተቻላት መጠን ትጠቀምባታለች፡፡

አሎይዜና እኔ በጣም ስለተግባባን ሻለቃ ንዋትሊ እናቴ እንደሆነች ጠየቁኝ፡፡ «አይደለችም» ስል መለስኩለት፤ ግን እንደ ልጇ ነው የምታየኝ፡፡ ወላጆቼና ሁለቱ ወንድሞቼ በእርግጥ የጭፍጨፋው ሰለባዎች ናቸው - ሌሎቹም ዘመድ አዝማዶቼ እንዲሁ፡፡

«ይቅርታ» አሉ ሻለቃው፡፡ «ትወቅሱናላችሁ?»

«ምን ማለትዎ ነው?» ስል ጠየቅኋቸው በጥያቄያቸው ተደናግሬ፡፡

«በተከሰተው ነገር ብዙዎቹ ወታደሮቼ ራሳቸውን ይወቅሳሉ፡፡ የራሳቸውን ቤተሰብ ጨምሮ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ቱትሲዎች ሲገደሉ ኪጋሊን ለመቆጣጠር ስንዋጋ ብዙ ጊዜ እንደፈጀን ያስባሉ፡፡ እዚህ ለመድረስ ረጅም ጊዜ እንደወሰድን ይሰማቸዋል፡፡»

«እንደዚያ ማሰብ የለባቸውም ሻለቃ - የእናንተ ችግር አይደለም፡፡ እኛን ለማዳን ነው እኮ የተዋጋችሁት ... ዲያብሎስን ነው የተፋለማችሁት፡፡ አሁን ተመሳሳይ ጦርነት እንዳይመጣብን መጣር አለብን፡፡ መግደልን አቁመን እንዴት ምሳረት ማድረግ እንዳለብን እንማር፡፡»

ባለመስማማት ራሳቸውን ነቀነቁብኝ፡፡ «ስለ እግዚአብሔር ወይንም ስለ ዲያብሎስ አታውሪልኝ - ይህን ማን እንዳደረገው አውቃለሁ፡፡ ለምትፈልጊያቸው

ሁሉ ምኅረት ማድረግ ትችያለሽ፣ ኢማኪዩሌ። አንቺ ግን ምናልባትም እኔ ያየሁትን ያህል የጅምላ መቃብሮች አላየሽም። እነዚያን መቃብሮች የሞሉት ሰዎች አሁንም እዚያው ናቸው፤ እና እመኝኝ ገዳዮቹ ምኅረትሽ የሚገባቸው አይደሉም። መገደል አለባቸው፤ ስለሆነም እኔ የእጃቸውን መስጠትን እመርጣለሁ። ባይሆን ገድዬ ይቅር እላቸዋለሁ።

ሻለቃው በቅርብ ያለ የባፕቲስት ቤተክርስቲያንን አመለከቱን። «ሌሎች ከግድያው የተረፉ ሰዎችን እዚያ ታገኟቸዋላችሁ። ስለናንተ ምን እንደምናደርግ እስክንወስን ድረስ እዚያው ሁኑ፤ ደግሞ እንዳትዟዟሩ። አስታውሱ፣ አሁንም ቢሆን በጦርነት ቀጣና ውስጥ ናችሁ። ጥቂት ኢንተርሃምዌዎች ቢያገኟችሁ እናንተ እንደምትምሯቸው አይምሯችሁም።»

የኔ ቡድን ከሌሎች አንድ መቶ ከሚሆኑ ሌሎች የተረፉ ቱትሲዎች ጋር በቤተክርስቲያኑ ቆየ። በዚያ ስፍራ አልጋም ሆነ ብርድልብስ የለም። ከራሳችን በላይ ጣራ በመኖሩ ግን ደስተኞች ነን። በዚያም ላይ በእግዚአብሔር ቤት መሆናችን አስደስቶናል። ባዚል ምግብ ስለሰጠን እኔ አዘገጋጅ ጀመር። ውጪ ላይ እሳት ለማያያዝ ስሞክር አንዳች መጥፎ ሽታ አጥወለወለኝ።

«በፈጣሪ ስም ይህ ሽታ ምንድነው?» ስል አንደኛውን እኛን እንዲጠብቅ የተመደበውን ወታደር ጠየቅሁት። እጄን ይዞ ምንም ሳይናገር ወደ ቤተክርስቲያኑ ጓሮ ወሰደኝ። ከሲዖል የመጣ ምስል ነው ማለት ይቻላል - በሙቶዎች የሚቆጠር ሬሳ በሬሳ ላይ እንደ ግንድ ተከምሯል። ላዩን ደግሞ ጥቁር የዝንብ ምንጣፍ ሸፍኖታል፤ አሞራም ላይ ላዩን ይራኮትበታል። አንድ ሽማግሌ ሰውዬ በክምሩ ዳርቻ ቆመው ውሾችን በዱላ ያባርራሉ።

አፈን ሸፈንኩ፤ ዓይኖቼም በመሸበር ፈጠጡ። ከዚያም ወታደሩ ከክምሩ አለፍ ብሎ 30 ሜትር ርዝመትና 20 ሜትር ጥልቀት ያለውን ጉድጓድ አመለከተኝ። በአሥር ሺዎች በሚቆጠር አስከሬን የተሞላ ነው። ራሴን አዞርኩ፣ አስመለሰኝና ወደ ቤተክርስቲያኑ ግቢ ፊተኛ ክፍል እየተንገደገድኩ ሄድኩ። ወታደሩም ምንም ሳይተነፍስ ተከተለኝ።

«የዚህ አካባቢ ሰው ነህ?» ስል ጠየቅሁት። ራሱን በአዎንታ ስለነቀነቀልኝ በዚያ እየበሰበሰ ባለ የሰው ክምር ውስጥ አንድ ቦታ ቤተሰቡ እንዳለበት ገባኝ። ሰቀቀኑ ቃላት ከሚገልጹት በላይ ነው።

ከስንት ዓመት፣ ከስንትስ ትውልድ በኋላ ይሆን ሩዋንዳ ከዚህ አሰቃቂ ድርጊት የምታገግመው? የቆሰሉ አንጀቶቻችንስ በምን ያህል ጊዜ ይሽሩ ይሆን? የደደሩት ልቦቻችን በምን ያክል ጊዜ ይመለሳሉ? ለኔ ረጅም ጊዜ ሆኖ ታየኝ። የወታደሩን ዓይኖች ሳይ ሩዋንዳን ለቅቄ መሄድ እንዳለብኝ ገባኝ።

ቢያንስ ለተወሰነ ጊዜ የዚህችን ሀገር ሰቆቃና ሥቃይ ትቼ መሄድ አለብኝ፡፡ እግዚአብሔር ሌሎች ጉዳተኞች እንዲድኑ አግዝ ዘንድ ይህን አንዳደርግ እንደፈቀደ ስለማውቅ ጊዜና ቦታ ብቻ የሚፈቅዱልኝን በማመዛዘን የምወስንበት ሁኔታ ያስፈልገኛል፡፡ መጀመሪያ ራሴን ማዳን አለብኝ ሌሎቹን ለማገዝ - በፈረንሳውያን ምሽግ ያሉትን ወላጅ አልባዎች፣ ልባቸው በቀል የተሞላውን ሻለቃ፣ አሁንም መግደል በዓይናቸው ላይ የሚነበብባቸውን አራጆችና ሐዘኑ ነፍሱን ያፈነችበት ከፊት ለፊቴ የቆመው ወታደር - ሁሉንም፡፡

እሄዳለሁ፣ ግን ገና ጊዜ መጠበቅ አለብኝ፡፡ መጀመሪያ ብዙ ማድረግ ይኖርብኛል፤ በተጨማሪም ምንም ሥራ፣ ገንዘብም ሆነ ራእይ የለኝም፡፡ ያለኝ ብቸኛው ነገር የለበስኳቸው ልብሶችና በኪሴ ያለው የአባቴ መቁጠሪያ ነው፡፡

ጓደኞቼና እኔ አብዛኛውን ጊዜያችንን ያለ ምንም ገንዘብ ወደ ኪጋሊ እንዴት መሄድ እንደምንችል በማሰብ ከአማጽያኑ ታጋዮች ጋር ለተወሰኑ ቀናት ቆየን፡፡ አንዴ እዚያ ከደረስን አሥራ ሁለታችንም አሎይዚ ቤት ልንቆይ እንችላለን፣ አሁንም ቢሆን ግን አስቸጋሪውን የአምስት ሰዓት ጉዞ ማድረግ የምንችልበት ምንም መንገድ አልነበረንም፡፡ በግሌ ለቀናት ጸልዬበት ሁሉም አንደኔ እንዲጸልዩ ጠየቅሁ፡፡ በመጨረሻም እግዚአብሔር በምላሹ ሻለቃ ንትዋሊን ከነመፍትሔው ላከልን፡፡

ሻለቃው አሎይዚ በር ላይ የሚያደርሰን የጭነት ተሽከርካሪ ከነዘዋሪው ሰጠን፡፡ ያ ብቻ አይደለም፤ ተሽከርካሪው ላይ ወጥተን ስናበቃ ብዙ ኬሻ ሩዝ፣ ዱቄት፣ ስኳር፣ ባቄላ፣ ቡና፤ የቆርቆሮ ወተትና ዘይት አስጫኑልን፡፡ ለረጅም ጊዜ ካየሁት ምግብ ሁሉ በላይ ሲሆን ለወራት ሊያቆየን ከሚችለውም የበለጠ ነው፡፡ ደኅና ሁኑ በማለት እጆቻችንን ስናውለበልብና ወደ ኪጋሊ ስናመራ ሻለቃውን ለችሮታቸው ደጋግመን አመስግነናቸዋል፡፡

ከተወሰኑ ወራት በፊት ቢሆን ወከባ የበዛበት የሥራ ቀን ይሆን በነበረ ዕለት ቀትር ላይ ከዋና ከተማዋ ደረስን፡፡ ወደ አስፈሪው ከተማ ገባን፡፡ መንገዶቹ አልፎ አልፎ ከሚመጣው የተመድ የጭነት ተሽከርካሪ ወይም መንገድ ውር ውር ከሚሉት ከሩአማ አነስተኛ ወታደራዊ ተሽከርካሪዎች በስተቀር የሚንቀሳቀስ አልነበረባቸውም፡፡ ያሉትም እነዚህ ተሽከርካሪዎች በመንገዶቹ ያሉትን የሰው አስከሬኖች ወይንም ወታደሮቹ እነዚህን አስከሬኖች እንዳይበሉ በጥይት መትተው የገደሏቸውን ዉሾች ላለመዳጥ ተጠንቅቀው ይሄዳሉ፡፡ አየሩ ሞት ሞት ይሸታል፤ ንፋሱም ሰው በሌለባቸው ቤቶች ውስጥ ከሰው ላይ እንደተነሡ መናፍስት ሲሄድ ይሰማኛል፡፡ እጅግ ብዙ ሕንጻዎች በጥይትና በአዳፍኔ ተኩስ ተቃጥለውና ተበሳስተው ፈራርሰው ወድቀዋል፡፡ የሱቆች በሮች ከማጠፊያዎቻቸው ተገነጣጥለዋል፣ የዕቃ መጋዘኖችም ተዘርፈዋል፡፡ አልፎ አልፎም በርቀት ፍንዳታዎች ይሰሙናል፡፡ በአሥራዎቹ ዕድሜዬ ላይ ሆኜ ደማቅ

ሰማያዊ መብራቶቿና በሰው የሚጨናነቁት መንገዶቿ ያስደመሙኝን ውቧን ከተማ በዚህ ወቅት ላውቃት አልቻልኩም።።

ዘዋሪው «ተጠንቅቃችሁ ተጓዙ» ሲል አስጠነቀቀን።። «በየሄዳችሁበት ፈንጂዎች ተቀብረዋል ... የት የት እንደቀበርናቸው አናስታውስም።። እዚህ አካባቢ ልትላወሱ ወጥታችሁ እግራችሁን በአንድ አፍታ ልታጡ ትችላላችሁ።።»

የአሎይዜን ባለቤት፣ ፋሪን፣ እናገኘው እንደሆነ ብለን በቀጥታ ወደ ተመድ ዋና ጽሕፈት ቤት ነዳን።። «ከኛ ቤት እስከ ተመድ በእግር የሚያስኬደው አሥራ አምስት ደቂቃ ነው።። ኮርኒሳችን ውስጥ ተደብቆ ከዳነ ሊመጣ የሚችለው እዚህ ነው።። ይህ ኪጋሊ ውስጥ በጣም ሰላም ያለበት ስፍራ ነው» አለች አሎይዜ።።

በትልቁ የብረት በር ፊት ለፊት ቆመን አሎይዜን አወረድናት።። ተንቀጠቀጠች - ካገኘኋት ጀምሮ ለመጀመሪያ ጊዜ መንፈሷ ተናወጠ።። «ፋሪን ገድለውት ከሆነ እንዴት እንደምኖር አላውቅም» ስትል እውነቱን ተናገረች።። «ነፍሴ፣ ሁሉ ነገሬ ነው፣ ጥንካሬዬንም የማገኘው ከእርሱው ነው።። በሕይወት እንዲኖርልኝ በጣም ስጸልይ ቆይቻለሁ... አምላክ ያንቺን ጸሎት እንደሚሰማ ሁሉ የኔንም በሰማኝ፣ ኢማኪዩሌ።።»

አምላክ እውነትም አሎይዜን ሰምቷት ኖሯል።። ተናግራ ሳትጨርስ ያን ዓይኗ ማየት የለመደውን ሰው በግቢው ሲንቀሳቀስ አየችው።። «ወይ አምላኬ ... እሱው ነው! እርግጠኛ ነኝ እሱው ነው - አካሄዱን የትም ቢሆን እለየዋለሁ።። ጥሩት፤ አንድ ሰው ይጥራልኝ!»

አንደኛውን የተመድ ዘበኛ ሮጦ አሎይዜ የጠቆመችበትን ሰውዬ እንዲያመጣልን ለመንነው።። ሰውዬው አሎይዜን እስኪያያት ድረስ ወደኛ በቀስታ መጣ ... በቻለውም መጠን ሮጠ።። ዋናውን በር አልፎም በጉልበቶቹ ወደቀና ይስማት ገባ።። «የኔ ውድ» አላት።። ትንንሾቹ ልጆች ኬንዛና ሳሚም ክርኖቹ ላይ ወደቁና በማቀፍና መሳም ብዛት አፈኑት።። ይህ በሕይወቴ ካየኋቸው የቤተሰብ አባላት መልሰው የተገናኙባቸው ክስተቶች አንዱና እጅግ አስደሳቹ ነው።። ይህ የሆነው ግን ፋሪ፣ «ሕጻኗስ?» ብሎ እስኪጠይቅ ድረስ ብቻ ነው።።

የአሎይዜ ዓይኖች በእንባ ተሞሉ።። «ፈጣሪ ወሰዳት» ስትል ኢቃሰተች።። «ትኩሳት ነበረባት፤ አልችል አለችው።።»

ፋሪ ራሱን በአሎይዜ ጭኖች ላይ አድርጎ ከ15 እስከ 20 ደቂቃ ያህል አለቀሰ፤ ሌሎቻችን በበኩላችን ተሳቀን እርስ በርሳችን እየተያየን ቆምን።። አንዳችንም አሎይዜ በፈረንሳውያኑ ምሽግ ከመድረሷ በፊት ልጅ እንደሞተባት አላወቅንም።። በጥንካሬዋ ተገረምን።።

በኋላም ፋሪ ቀና ብሎ ስለኛ ማንነት ጠየቃት፡፡ «በስደተኞች መጠለያው ልጆቹ አድርጌ የተቀበልኳቸው እጓለማውታ» ስትል አሎይዜ ነገረችው፡፡ «ከኛ ጋር ይቆያሉ፡፡»

«እንኳን ደኅና መጣችሁልኝ» አለ ፋሪ፡፡

«ያች ረጅሟ የሮዝና የሊኦናርድ ልጅ ነች ... ሁለቱም ወዳጆቻችን አርፈዋል፡፡»

«ወይኔ» አለ ፋሪ ተነሥቶ እጇን ይዞ፡፡ «ቁርጥ ወላጆቿን የኔ ቆንጆ፡፡ ጠንክሪ - እናትና አባትሽ ቆንጆዎችና ደጋጎች ነበሩ፡፡ አንቺን አምላክ ለዓላማ ነው ያተረፈሽ... ያ ዓላማ ምን እንደሆነ እስክታውቂው ድረስ እኛ ጋ መቆየት ትችያለሽ፡፡»

«አመሰግናለሁ» ከማለት በስተቀር ምን እንደምልም አላውቅም፡፡

ወደ ተሸከርካሪው እንደገና ወጥተን ወደ አሎይዜ ቤት ሄድን፡፡ በመንገድም ላይ ሳለን ፋሪ ላለፉት አራት ወራት ቤቱን ትቶ በተመድ እንደኖረ ነገረን፡፡ «አሎይዜ ከልጆቹ ጋር ባትመለስልኝ ኖሮ» አለ «በጭራሽ አልመለስም ነበር፡፡ ቤት እኮ ያለ ፍቅር እስር ቤት ነው፡፡»

ስፍራው ተተረማምሷል፤ መስኮቶቹ ብትንትናቸው ወጥቷል፤ ግንቡ በጥይት ተበሳስቶ፣ የጣራውም ግማሽ ክፍል ተገልጧል፡፡ ግን ሁላችንም ተረባርበን መጪውን ሳምንት ቤቱን ስንጠግንና ስናጸዳ አሳለፍን፡፡ በጥረት፣ የግንባታ እቃዎች ከተለያዩ የፊራረሱ ቤቶች ተፈልገው ስፍራው እንደገና ቤት መሰለ፡፡ ዢን ፖልና ሌሎቹ ወንዶች የራሳቸው ክፍሎች ሲደርሷቸው ፍሎረንስና እኔ በአንዷ ክፍል ተዳብለን ተቀመጥን፡፡ የወላጆቼን ቤት ከለቀቅሁ ጀምሮ ለመጀመሪያ ጊዜ አልጋ ላይ ተኛሁ፡፡ ሁላችንም ገነት ገባን!

ሻለቃ ንዋትሊ የሰጡን ምግብ ቢኖረንም ምንም ገንዘብ የለንም - ልብሶቻችን ለወራት በመለበሳቸው ነታትበዋል፡፡ ወደ ባዶ ቤቶች እየሄድን ጫማና አዳዲስ የሚለበሱ ነገሮች እንፈልግ ያዝን፡፡ በአንድ ቤት ጥንድ የወርቅ የጆሮ ጌጥ አገኘሁ፡፡ ይህን ሁሉ ካሳለፍኩ በኋላ ጥሩ እንዲሰማኝ የሚያደርግ አንድ ቆንጆ ነገር እንደሚገባኝ ራሴን አሳመንኩና ኪሴ ውስጥ አደረግኋቸው፡፡ በአሎይዜ ቤት በመስታወቱ ፊት ስሞክራቸው ግን የማየውን ምስል ልቋቋመው አልቻልኩም፡፡ የሚታየኝ የዚህ ጌጥ ባለንብረት የነበረችው ሴትዮ ፊት ብቻ ሆኖ አረፈው፡፡ የጆሮ ጌጦቹ የኔ አይደሉም፤ ምንም ትውስታዎቼም የሉባቸው፤ ሌላ ሰው እነዚህን ለማግኘት በርትታ ሰርታለች ወይንም እንደ ፍቅር ስጦታነት ተቀብላቸዋለች፡፡ በሌላ ሰው ሕይወት ውስጥ ሳይፈቀድልኝ እንደገባሁ ተሰማኝ፡፡ ለፍቼ ያላገኘኋቸውንና የማይገቡኝን ንብረቶች አልፈለኩም፤ ስለዚህ በመጭው ቀን ጌጦቹን ወዳገኘሁበት ወስጄ መለስኳቸው፡፡

በኋላም በጆሮዬ አንድ ድምፅ ያንሾካሹክ ገባ፤ በሰማሁትም በመስማማት ራሴን ነቀነቅሁ፡ ለመንቀሳቀስ ሰዓቱ አሁን ነው፡፡ ሥራ ማግኛ ጊዜዬ አሁን ነች፡፡

ምዕራፍ 22
የጌታዬ ሥራ

ሰዎች በመንገድ ላይ ለመዘዋወር እንኳን በሚፈሩበት ከተማ ሥራ የት እንደማገኝ የሚያውቀው አምላክ ነው፡፡ ውድቅዳቂ ፈንጂዎች የኪጋሊን መንገዶች ሞልተዋቸዋል፤ ለመሥራት ከፈለግሁ ግን በነዚህ ጎዳናዎች ሥራን እያነፈነፍኩ መኳተን ይኖርብኛል፡፡ የሕዝብ ማጓጓዣ ተሸከርካሪዎች መንቀሳቀሳቸውን ትተዋል፤ ለአነስተኞቹም ማጓጓዣዎች የምከፍለው ምንም ገንዘብ አልነበረኝም፡፡

ፋሪን በቤቱ አቅራቢያ ያሉ ከፍት የሥራ ቦታ ያላቸውን ድርጅቶችን ያውቅ እንደሆነ ጠየቅሁት፡፡ «አሁን ማንም እየቀጠረ ስላልሆነ አማራጮቹሽ በጣም ውሱን ናቸው» ሲል መለሰልኝ፡፡ «ያለው ብቸኛ አማራጭ የተመድ ነው ... እዚያ ለመግባት ግን እንግሊዝኛ መናገር ያስፈልጋል፡፡»

በአእምሮዬ የሆነ ነገር ብልጭ አለልኝ፡፡ በእርግጥ! እግዚአብሔር በመታጠቢያ ክፍሉ እንግሊዝኛ እንዳጠና ያደረገኝ ዋነኛው ምክንያት እኮ የተመድ ነው፡፡ በተመድ የመሥራት ሕልምም ነበረኝ፡፡

በዚያን ምሽት ልብሶቼን በሚገባ አጥቤ አምላክ በተመድ ሥራ እንዳገኝ ያግዘኝ ዘንድ ጸለይኩ፡፡ በመጨረሻ እንግሊዝኛዬን በሥራ ላይ የማውልበት መሆኑን አስቤ በጣም ተደሰቼ አብዛኛውን የሌሊቱን ጊዜ መስታወት ሳይና ራሴን በራሴ ያስተማርኳቸውን ሐረጋት ስለማመድ ቆየሁ፡፡

«እንደምን አደራችሁ»

«እንዴት ነዎት?»

«ሥራ ፈልጌ ነው፡፡» ስሜ ኢማኪዩሌ ኢሊባጊዛ ነው፡፡»

«ሩዋንዳዊት ነኝ፡፡»

«ቡታሬ ባለው ዩኒቨርሲቲ ሳይንስ አጥንቻለሁ፡፡»

«ሥራ ፈልጌ ነው፡፡»

አቤት! እንዴት ደስ ይላል! ትክክለኛ የእንግሊዝኛ አረፍተ ነገሮችን መናገር ጀምሬያለሁ፤ ነገ በአዲስ ቋንቋ እነጋገራለሁ ... ከዚያም አዲሱን ሥራዬን እሠራለሁ! ተመስገን አምላኬ!

ልክ ከጠዋቱ ሁለት ሰዓት ላይ በተመድ ሕንጻ በር ፊት ለፊት ሄጂ ቆሜያለሁ። ጋናዊ ዘበኛ እንግሊዝኛ በሚመስል ቋንቋ ሞቅ አድርጎ ሰላምታ ሰጠኝ። «እንደምን አደርሽ፣ ምን ልርዳሽ?» ያለኝ ይመስለኛል። እኔ የሰማሁት ግን «ታታታ ታታታ ታታታታ?» ዓይነት ነገር ነው። ምንም እንዳለ አንዳች ፍንጭ ባላገኝም የገባኝ አስመሰልኩ። ራሴን ከፍ፣ አገጩን ወጣ አድርጌ «እንዴት ነዎት? ስሜ ኢማኪዩሌ ኢሊባጊዛ ነው። ሥራ ፈልጌ ነው» አልኩ በእንግሊዝኛ።

ውይ። የዓይኖቹ አካኋን አነጋገሬ እንዴት አስቂኝ እንደሆነበት ነገረኝ። ቢሆንም ግን እንደገና ሞከርኩ። ይህን ሁሉ ርቀት የመጣሁት ተመለሽ ለመባል አልነበረም። «እንዴት ነዎት? ስሜ ኢማኪዩሌ ኢሊባጊዛ ነው። ሥራ ፈልጌ ነው»

«አሃ! ሩዋንዳዊት ነሽ... የምትችይው ፈረንሳይኛ መሆን አለበት» አለኝ። ፈገግ ብዬ በአዎንታ ራሴን ነቀነቅሁ። ዋናውን በር ከፍቶልኝ ሌላ ዘበኛ ወደ አንዲት ትንሽ የእንግዳ መቀበያ ክፍል ወሰደኝ፤ ብዙ ቅጻቅጾችን ሞልቼ እንድጠብቅ ተነገረኝ። ጠበቅሁም ... ጠበቅሁ... ጠበቅሁ ... ጠበቅሁ። የተመድ ሠራተኞች ማታ ከሥራ ሲወጡ እንግዳ ተቀባይዋን ሥራውን እስካገኝ ምን ያክል መጠበቅ እንዳለብኝ ጠየኳት።

«ረጅም ጊዜ ትጠብቂያለሽ ውዴ ... ሥራ የለም።»

ወደ ቤቴ ተበሳጭቼ ግን ተስፋ ሳልቆርጥ ሄድኩ። በተመድ መሥራት ዕጣ ፈንታዬ - የማልመውና ቆርጬ የተነሣሁበት ጉዳይ ነው። ፈጣሪ እዚያ እንድሠራ ከፈቀደ ከግቢ ከመድረስ ምንም አያስቆመኝም።

በቀጣዩም ቀን ተመለስኩ፣ እነዚያኑ ቅጾች ሞላሁና ከሰዓቱን ጠበቅሁ። በቀጣዩም ቀን ይህንኑ አደረግሁ፤ በቀጣዩም፤ በቀጣዩም። ቅጾችን ስሞላና ስጠብቅ ከሁለት ሳምንታት በላይ ፈጀሁ። በየቀኑ ወደ ቤቴ ስሄድ እንግዳ ተቀባይዋ «እኔ አንቺን ብሆን ተመልሼ አልመጣም ነበር ውዴ። ምንም ሥራ እኮ የለም» ትለኛለች።

በሁለተኛው ሳምንት መጨረሻ ተስፋዬ እየተሟጠጠ መጣ። ሥራ ሳላገኝ ወደ አሎይዚ ቤት መሄድ አስፈራኝ። ስለሆነም ለራሴ አዝኜ በቤታችን ሰፈር በፈራረሱ መንገዶች እዞር ገባሁ። በራሴ ዐቅም ላይ ለማተኮር ከአምላክ ጋር ጸጥታ የተሞላበት ተግባቦት እያደረግሁ ለመቀመጥ ፈለግሁ፤ ለዚያ ተመስጦ ግን የአሎይዚ ቤት በጣም ረብሻ የሚበዛበት ነው። እርስዎ አመኑኝም አላመኑኝ ከአምላኬ ጋር ለሰዓታት ያለማቋረጥ የማወራበትን በቁሱ መታጠቢያ ክፍል ያሳለፍኩትን ወቅት ናፈቅሁ። በነዚያ ረጃጅም ጸጥ ያሉ ጸሎቶቼ ወቅት ልቤን የሞላበትን ደስታና ሰላም አስታወስኩ - ከዚያ በኋላ አገኝ የነበረውን የአእምሮ ንጽሕናም ጭምር።

ከአሎይዜ ቤት ሁለት ግቢ አልፎ ወደተቃጠለ ቤት ፍርሥራሽ ሄድኩ። በጉልበቶቼ በተቃጠለው ፍርሥራሽና በተሰባበረው መስታወት ላይ ተንበርክኬ ጸሎቶቼን ጀመርኩ። «እግዚአብሔር ሆይ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ጴጥሮስ ሌሊቱን ሙሉ ዐሳ ለማጥመድ ቢሞክርም ምንም ሳይዝ ቀርቶ ተስፋው ቢሟጠጥ፤ አንተ ግን በዚያው ቦታ ላይ ሄዶ እንዲያጠምድ ነገርከው - እናም ብዙ ዐሳ አጠመደ! በጣም ደስተኛም ሆነ! እኔንም ታዲያ ወደ ተመድ ስለመራኸኝ እስካሁን ይህን ሁሉ ቀን ሥራ ‹እንዳጠመድኩ› አለሁ። ግን ምንም ዓሶች እዚህ የሉም። እግዚአብሔር፣ ምን እንደማደርግ አላውቅም። ገንዘብ የለኝም፤ ልብሶቼ እየተበጣጠሱ ነው፤ ሥራም አያስገኙኝም። ስለዚህ እገዛህን እፈልጋለሁ። እነዚህን የተመድ ሰዎች እንዲያዩኝና ጥሩ የጽሕፈት ቤት ሥራ እንዲሰጡኝ አድርግ፤ አንተ እንደምፈልገው ታውቃለህ። አግዘኝ፤ እኔም በበኩሌ ራሴን አግዛለሁ! ይሁን ይደረግልኝ።»

ራሴን አጸዳድቼና የፈራረሰውን ቤት ትቼ በታደሰ የራስ መተማመን ሄድኩ። እግዚአብሔርን እገዛውን ጠየቅሁት፤ የምፈልገው አሁን እንዲከሰት ማድረጉ የራሴ ድርሻ እንደሆነ ታውቆኛል። በተመድ መሥራት የምፈልገውን በአእምሮዬ መቅረጽ ጀመርኩ - ማስታወሻ መያዝ፣ ስልክ መመለስና ጠቃሚ ውሳኔዎች ሲደረጉ ማገዝ።

ወደ ቤት ስሄድ የተመዱን ሥራዬን አንዴ ካገኘሁ በኋላ ስለሚያስፈልጉኝ ነገሮች ሳስብ ቆየሁ። የተወሰኑ ለሰው ፊት የሚቀርቡ ልብሶች ሊኖሩኝ ይገባል፤ እናም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ያጠናቀኩበት ምስክር ወረቀትና ዩኒቨርሲቲ ለሦስት ዓመታት መከታተሌን የሚያረጋግጥ መረጃ ያስፈልጉኛል። ያለመታደል ሆኖ ሁሉም ንብረቶቼ አራት ሰዓት በተሸከርካሪ በሚያስነዳው ቡታሬ በሚገኘው በትምህርት ቤት የመኝታ ክፍሌ ናቸው፤ እንደሚታወቀው ወደዚያ ለመሄድ ደግሞ የምከፍለው ገንዘብ የለኝም።

በሐሳብ በጣም ተውጬ አንድ ተሸከርካሪ በአጠገቤ አልፎ ነጂው ስሜን ሲጣራ ልብ አላልኩትም ማለት እችላለሁ - በዩኒቨርሲቲዬ መምህር የሆነው ዶክተር አቤል። «መች አወቅሁሽ ኢማኪዩሌ» አለኝ። በጣም ከስተሻል! በመትረፍሽ በጣም ተደስቻለሁ ... እንዲያው ምግብስ እየበላሽ ነው? የምትኖሪበትስ ቦታ አለሽ?»

ዶክተር አቤል የህክምና ዶክተር በመሆኑ ስላለፍኩበት ሁኔታና ስለጤናዬ ጉዳይ ጠየቀኝ። ለማገገም እንዲያግዘኝ ከእርሱ፣ ከሚስቱና ከቤተሰቡ ጋር ቡታሬ እንድኖር ቢጋብዘኝም አመስግኜው የምቆይባቸው ቤተሰብ እንዳሉኝ ነገርኩት። በቅርቡ ግን ቡታሬ የሚሄድ ከሆነ እንዲወስደኝ ነገርኩት።

«ምን ችግር አለ? በእርግጥ ነገ ሂያጅ ነኝ።»

እንደገና የዕድል ገጠመኝ ነው ብዬ ባሰብኩት በዚህ ጉዳይ የአምላክን እጅ አየሁት፡፡ በቀጣዩ ቀን ዶክተር አቤል በዱሮ ዩኒቨርሲቲዬ የፊት በር ጋ ጣለኝ፡፡ ትምህርት ቤቱ ተዘርፎ፣ ወታደሮች በበሩ ስር ተቀምጠው አገኘሁት፡፡ ጠባቂዎቹ ወደ መኝታ ክፍሌ አናስኬድም አሉኝ፡፡ «ትምህርት ቤቱ ከነጭራሹ ተዘግቷል» በማለት፡፡ ይባስ ብለው ወደ ኪጋሊ እንድመለስ ነገሩኝ፡፡

እግዚአብሔር እንዴት ወደ ግቢው እንደሚያስገባኝ እስኪያሳየኝ እየጠበቅሁ በመንገዱ ዳር ተቀምጬ በአባቴ መቁጠሪያ ጸለይኩ፡፡ በአሥር ደቂቃ ውስጥ የወታደሮቹን አለቃ ኮሎኔል የጫነች ተሽከርካሪ ዋናው በር ጋ ቆመች፡፡ ለኮሎኔሉ ወታደሮቹ ሰላምታ ለማቅረብ ሲራኮቱ እኔም ሄጄ ተዋወቅሁ፡፡

«እዚህ ምን እያደረግሽ ነው ሚጡ?» ሲሉ መለሱልኝ፡፡ «ወላጆችሽ የት ናቸው? እዚህ ብቻሽን መሆንሽ አደገኛ እኮ ነው፡፡»

ሃያ አራት ዓመቴ ቢሆንም በጣም ከመከሳቴ የተነሣ የ12 ዓመት ልጅ መስያለሁ፡፡

«ጌታዬ ወላጆቼማ ሞተዋል፡፡ ከተቀረው ቤተሰቤ ጋር በዘር ጭፍጨፋው ነው የተገደሉት፡፡ በዓለም የቀረኝ ነገር መኝታ ክፍሌ ብቻ ነው፤ ወታደሮችዎ ወደ ትምህርት ቤቱ አናስገባም አሉኝ እንጂ፡፡ ሊያግዙኝ ይችላሉ?» ስል በተቻለኝ መጠን ተሸቆጥቁጬ ጠየቅኋቸው፡፡

ኮሎኔሉ በሩን ከፍተውልኝ ከአንደኛው ወታደር ጋር ገባሁ፡፡ በበሩም ገብተን ወደ መኝታ ቤቴ አሳዛኙንና አጭሩን ጉዞ አደረግን፡፡

ብዙ አስደናቂ ትዝታዎቹ ያሉብኝና ግሩም ጓደኞችን ያፈራሁበት ውቡ ትምህርት ቤቴ እንዳልነበር ሆኗል፡፡ በየቦታው የቆሻሻ ክምር ይታያል፤ ብዙዎቹ ሕንጻዎችም ጋይተዋል፤ ፊራርሰውማል፡፡ የተማሪዎችን የትምህርት ማስረጃ በግቢው ሙሉ ደርቆ እንደረገፈ ቅጠል ነፋስ ያንገላታቸዋል፤ ከእነዚህ ሁሉ ሳምንታት በኋላም እንኳን አሁንም መሬት ላይ እጅግ ብዙ አስከሬኖች ይታያሉ፡፡ የሳራንና የሌሎቹን የሴት ባልንጀሮቼን አስከሬን እንዳላይ ፈርቼ ደፍሬ ማየት አልቻልኩም፡፡ ከተዝናናሁባቸው የትምህርት ቤት ጭፈራዎች አንዱን፣ የተሳተፍኩባቸውን ተውኔቶችና ከዮሐንስ ጋር ያደረኳቸውን የፍቅር ሽርሽሮች ለማስታወስ ሞከርኩ፡፡ ግን ሁሉም አስቀድሜ ባየሁት የወዳጆቼና የንብረቶቻቸው በየቦታው መውደቅ ሰበብ ጠፉ፡፡

ኮሎኔሉ መኝታ ቤቴ ጋ አውርደውኝ ተሟጦ ወደተዘረፈው መኝታ ክፍሌ ስሄድ ወታደራቸው ተከተለኝ፡፡ በሩ በመጥረቢያ ተገንጥሎ እያንዳንዷ የነበረችኝ ነገር ተወስዳለች - ቦርሳዎቼን፣ ልብሶቼን፣ ጫማዎቼንና ፍራሼን ሳይቀር ዘርፈዋቸዋል፡፡ ይመስገነው፤ የተወሰኑ የወላጆቼ ምስሎች - የአብሮነት ሕይወታችን ብቸኞቹ ማስታወሻዎቼ - በግቡ ላይ እንደተሰቀሉ አሉ፡፡ ከወለሉ ላይ የተወሰኑ የተበታተኑ

የደብዳቤ ኪስ ወረቀቶችን ብለቃቅምም ወታደሩ ከእጇ እየመነጨቀ ያነባቸው ያዘ። ከትከሻው ጠመንጃውን አውርዶ በማስፈራራት፣ «ኤይማብል ማነው?» በማለት ጠየቀኝ።

መሣቅ ስጀምር አስገረምኩት። ከዘር ጭፍጨፋው መትረፌ አስቆኖል፣ ግን ባዶ የመኝታ ክፍሌን በመዝረፍ ሰበብ በቱትሲ ወታደር በጥይት ተመትቼ ሊያበቃልኝም ይችላል።

«ኤይማብል ወንድሜ ነው። ያ ደብዳቤ እርሱ ከሚኖርበት ከሴኔጋል የተላከ ነው» አልኩት። አያጉረመረመ ደብዳቤዎቼን ሊያነብ ወደ አዳራሹ ገባ።

መሬት ላይ ያሉትን ሌሎች የተወሰኑ ወረቀቶች ሳስተካክል ያየሁትን አላመንኩም። እዚያ በአንድ ትልቅ ኪስ ወረቀት የሁለተኛ ደረጃ ምስክር ወረቀቴ፣ የዩኒቨርሲቲ ውጤቴና ትምህርት ቤቱ በትምህርት እድሉ ሰበብ ሰጥቶኝ የደበቅሁት ወደ 30 የሚጠጋ ዶላር አለ። በድንገት ሃብታም ሆንኩ ... ከዚያም በኋላ ይህን የተገኘውን ማስረጃ ተጠቅሜ የተማርኩ መሆኔን ማስረዳት እችላለሁ ማለት ነው!

ከትምህርት ቤቱ ግቢ ወዲያውኑ ወጥቼ ከአሜሪካ ዶላሮቼ አንዱን ወደ ኪጋሊ ለመመለስ ተጠቀምኩበት፤ አንድ ሌላ ጸሎቴን ስለመለሰልኝ እቤት እስክደርስ እግዚአብሔርንም አመሰገንኩት። በእውነት ቃሉን ጠብቆ እንደ ልጁ ተከታትሎኛል።

በከተማው የተወሰኑ ሱቆች ስለተከፈቱ የተወሰኑ ልባሽ ጨርቆችን፣ አዳዲስ ጫማዎችንና ሽቶ ገዛሁ። ከዚያም በአምስት ወራት ለመጀመሪያ ጊዜ ጸጉሬን ተሠራሁ። መልሶ ሴትነት እየተሰማኝ ወደ ቤት ሄድኩ። አሎይዚ ለባብሼና አምሮብኝ ከክፍሌ ብቅ ስል ስታየኝ የልብ ድካም የተነሣባት ያህል አደረጋት።

«ምንም ነገር እንድታገኚ ስትጸልዩ እኔም ትንሽ እንዳገኝ እስኪ ጸልዩልኝ» አለች ካንጀቷ እየሳቀች። በተረፈኝ ገንዘብ የገዛሁትን ለአንድ ሌላ ወር የሚበቃንን መጠጥ ሳሳያትማ ይበልጥ ሳቀች!

በቀጣዩ ቀን ጠዋት ሥራ ፍለጋዬን እንደገና ለመቀጠል ወደ ተመድ አመራሁ - አምሮብኝ፣ አልባብ አልባብ እየሸተትኩ፣ የትምህርት ማስረጃዬን ይዤ ሙሉነት ተሰምቶኝና በራሴ ተማምኜ። በአዲሱ ዓለሟ ስፍራዋን ለመያዝ የተዘጋጀች ሥራዋን የምታስቀድም ሴት ወጥቶኛል።

ጋናዊው የጥበቃ ጓድ በዚህ ወቅት በሩ ጋ አላስቆመኝም፤ በእርግጥ ያለ ምንም ጥያቄ ሳልፍ ፈገግ ብሎ ስላስገባኝ ያወቀኝም አልመሰለኝ። ሕንጻው ጋ እንደደረስኩ ወደ ሰው ኃይል ኃላፊው ክፍል አቅንቼ በሩን አንኳኳሁና ኃላፊውን በወሬያቸው መካከል አቋረጥኳቸው።

«ምን ልርዳሽ እህቴ?» ሲሉ በፈረንሳይኛ ጠየቁኝ::

«ሥራ ፈልጌ ነው ጌታዬ» አልኩ በእንግሊዝኛ ... ወይንም ያልኩ መሰለኝ:: ተምታታባቸው:: «ሥራ እፈልጋለሁ ነው የምትዪው?»

«አዎን ጌታዬ፣ ልክ ነው - ሥራ ፈልጌ ነው» ስል በፈረንሳይኛ መለስኩ:: እንግሊዝኛዬ የሆነ ማሻሻያ እንደሚያስፈልገው አያጠራጥርም::

«አሃ ... እስኪ አንዴ እዚሁ ጠብቂኝ» አሉኝና ወደ ክፍሉ ገቡ:: ከተወሰኑ ደቂቃዎች በኋላ ጸሐፊያቸው ልታነጋግረኝ መጣችና ከላይ እስከ ታች ምንጥር አድርጋ አየችኝ:: ሩዋንዳዊት ነች:: ብቻ በሆነ ምክንያት ገና ስታየኝ ዓይነ-ውኃዬን አልወደደችውም:: «ወደዚህ ሕንጻ እንዴት ልትመጪ ቻልሽ? ምንድነው የምትፈልጊው?» ስትል በኪንያሩዋንዳ ቋንቋ ጠየቀችኝ::

«ሥራ ነው የምፈልገው::»

«ምን ልምድ አለሽ?»

«ኤሌክትሮኒክ ምህንድስናና ሒሳብ ሳጠና በዩኒቨርሲቲ ነው የቆየሁት::»

«እዚህ ያሉት ሥራዎች የጽሑፍ ሥራዎች ናቸው - ያም የሚሆነው ደሞ ሥራው ሲኖረን ነው:: መቀምር[9] መጠቀም ወይንም እንግሊዝኛ መናገር ትችያለሽ?»

«የጽሕፈት ሥራ ሰርቼ አላውቅም፣ ግን ትንሽ ትንሽ እንግሊዝኛ እሞካክራለሁ::»

«አሃ» አለች እንደዋዛ:: «እንግዲህ ምንም ሥራ የለንም - ምናልባት በሦስትና አራት ወር ውስጥ ካለ ነው:: ግን ባለሽ ክህሎት ምንም ሥራ የምናገኝልሽ አይመስለኝም:: እባክሽ ስትወጪ በሩን ዝጊው::»

ከፍሉን ለቅቄ ስወጣ በጣም ስለተበሳጨሁ ወደ ጓሮ በሚያስወጡት ደረጃዎች ማንም ሳለቅስ እንዳያየኝ ብዬ እየሮጥኩ ወረድኩ:: የተወሰኑትን ደረጃዎች እንደወረድኩ አንድ በመካከለኛ ዕድሜ ላይ ያሉ ሰውዬ በፈረንሳይኛ ጠሩኝ: «ጠብቂኝ! አንዴ ቆይ እህቴ! ላናግርሽ?»

ሩጫዬን ለመቀጠል ብፈልግም ለታላላቆቼ አክብሮት ስላለኝ ምላሽ መስጠት አለብኝ ብዬ ቆምኩ:: እንባዬን ወዲያውኑ ጠራረግሁና «አቤት?» አልኩ::

ሰውዬው ሲያዩኝ አካኋናቸው ከሆነ እንግዳ መንፈስ ጋር ግጥምጥም እንዳሉ ሁሉ አስመሰላቸው:: «እም... እ... እዚህ ምን እንዳመጣሽ አልገባኝም?»

[9] ኮምፒውተር

ዘበኛ ሊጣሩ ነው ብዬ ባስብም «ሥራ ጌታዬ ... ሥራ ፈልጌ ነው» ስል መለስኩላቸው::

«የሰው ኃይል ኃላፊውን አናገርሽው?»

የደረጃ ላይ ጥያቄያቸው ቢያበሳጨኝም እንደገና በአክብሮት መለስኩላቸው:: «አዎን ጌታዬ፣ አናግሬያቸዋለሁ:: ግን ምንም ሥራ እንደሌለ ተነግሮኛል::»

«እ ... እንግዲህ እንደዚያ ካለ» ብለው በአድራሻ ወረቀታቸው ላይ የሆነ ነገር ጻጽፈው ሰጡኝ:: «ነገ ጠዋት ዋናው በር ላይ ይህንን አሳይተሽ ግቢ» አሉ:: «አራት ሰዓት ላይ እኔ ሥራ ቦታ እንድትመጪ:: ሥራ እንድታገኚ ማድረግ የምንችለውን ነገር እስቲ እናያለን::»

ምን እንደምል አላወኩም፤ ብቻ እርሳቸው ደረጃውን ሲወጡ በሰጡኝ ወረቀት ላይ አፍጥጬ ቆየሁ:: ጽሑፉ ሳነበው አንዲህ ይላል፡-

ፒየር ሜሁ

ቃል አቀባይ፣ ዩናሚር

የተመድ የሩዋንዳ ኢጋዥ ተልዕኮ

ቃል አቀባይ ምን እንደሆነ ምንም የማውቀው ነገር የለም፤ ሲያዩት ግን ትልቅ ነገር ይመስላል:: ዩናሚር ከጦርነቱ በፊት የተቋቋመው በሩዋንዳ የተሻለ የመንግሥት አሠራር ለማምጣት ነበር:: ምን አልባት ባልደረባው ልሆን እችል ይሆናል!

በቀጣዩ ቀን ጠዋት ከአቶ ሜሁ ጋር ስገናኝ በዋዜማው በደረጃው ላይ እንዳዩኝ በጣም የሚወዷት ከጦርነቱ በፊት ሠራተኞቸው የነበረችውን ወጣት ሩዋንዳዊት መስያቸው እንደነበር ነገሩኝ:: በዘር ጭፍጨፋው ወቅት ከነቤተሰቧ ነው አሉ የተገደለችው:: ከዚያ በኋላ ታሪኬን አንድነግራቸው ጠይቀውኝ ነገርኳቸው::

«እንዲያው ወርሃዊ ገቢሽ ስንት ነው?» ሲሉ ጠየቁኝ::

«ምንሽ?»

«ምን ያህል ገንዘብ ታገኛለሽ በወር?»

«ምንም:: ለዚያ ነው እኮ እዚህ የመጣሁት::»

«እስኪ እንግዲህ ... ግን የለንም:: ያው መቼም ሥራ እንድታገኚ አግዝሻለሁ:: ወላጆችሽ በደንብ እንዳሳደጉሽ ያስታውቃል:: ወላጅ-አልባ የምትሆኚው መሆን ከፈልግሽ ብቻ እንደሆነ እወቂ:: ከአሁን ጀምሮ የተመድ ቤትሽ ነው፤ እኔንም እንደ አባትሽ ቁጠሪኝ::»

እስኪያመኝ ድረስ ፈገግ አልኩ - እግዚአብሔር በእውነት የሚንከባከቡኝ መላዕክት በመላክ ቃሉን ጠብቋል።

«በእርግጥ ሁሉንም ፈተናዎች መፈተን ይኖርብሻል» አቶ ሜሁ ቀጠሉ፤ «ይህን ትምህርትሽን ይዘሽ ግን ያ አያዳግትሽም። የመቀምር ጽሑፍና የእንግሊዝኛ ክህሎትሽ እንዴት ነው?»

«መተየብ ባልችልም በመታጠቢያ ቤቱ እንደተደበቅሁ ግን ራሴን እንግሊዝኛ አስተምሬያለሁ።»

«እንደዚያ ከሆነ እንግዲህ .... አስቸኳይ የአጭር ጊዜ ትምህርት ያስፈልግሻል።»

አቶ ሜሁ ከጸሐፊያቸው ከጣኒ ጋር አስተዋወቁኝ፤ እርሷም መቀምር አጠቃቀም፣ ቃለ - ጉባኤ አያያዝና የአቀማመጥ ዝርዝሩን ሁሉ አሳየችኝ። በመቀምሩ ላይ ያሉትን ሁሉንም ቁልፎች ማስታወስ ቻልኩ። በተጨማሪም የመጻፊያ ሰሌዳውን ትከክለኛ አምሳል በቁራጭ ክላሴር ላይ ሣልኩት። በመቀምሩ ላይ ሦስት ቀናት በመፍጀት ሦስት ሌሊቶችን ሙሉ ሳልተኛ አድሬ በእጅ በተሳለው ሰሌዳዬ ላይ ስጽፍና ስለማመድ ቆየሁ።

እግዚአብሔር ጣቶቼን መርቷቸው ሳይሆን አይቀርም፤ በአራተኛው ቀን የተመድን የትየባ ፈተና በአጥጋቢ ውጤት አለፍኩ። ከተወሰኑ ቀናት በኋላም የእንግሊዝኛውን ፈተና አለፍኩና በተመድ ለመሥራት ብቁ ነሽ ተባልኩ። በአእምሮዬ ስዬው፣ አልሜው፣ ጸልዬበት ነበረና አገኘሁት!

ለጊዜው ባይነገረኝም የመዝገብ ቤትን ሥራ ቀጥ አድርጌ ይገፍው ኖሯል። ወዲያውኑም ሁሉንም ከውጪ ወደ ሩዋንዳ የሚገቡ የተመድ አቅርቦቶች የመከታተል ኃላፊነት የኔ ሆነ - ከአዳዲስ አነስተኛ ተሽከርካሪዎች እስከ ግዙፍ የምግብ አቅርቦቶች። ወሳኝ ሥራ ስለሆነ ከተወሰኑ ወራት በፊት እሞት እድን ሳላውቀው በአንድ ሌላ ሰው ትንሽ መታጠቢያ ቤት ውስጥ ቁጢጥ ብዬ እንደነበር ላምን አልቻልኩም።

ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ የሆኑት የጸሎትና የአዎንታዊ አስተሳሰብን ዐቅም ቋሚ ማሳያ ነኝ። አምላክ የሁሉም አዎንታዊ አስተሳሰብ ምንጭ ነው፤ ጸሎትም የእርሱን ዐቅም ለማጉረፍ ሁነኛው መንገድ ነው።

አምላክ ከመታጠቢያ ቤቱ ስንትና ስንት መንገድ አምጥቶኛል፤ ይህን መንገድ ስጓዝም እያንዳንዷን እርምጃ አብሮኝ ተጉዟል። ከገዳዮች አድኖኛል፤ ልቤን በይቅር ባይነት ሞልቶታል፣ እንግሊዝኛ እንድማርም ረድቶኛል፣ ወደ ደህንነትም መርቶኛል፤ ጓደኞች፣ መጠለያና ምግብ ሰጥቶ፤ በመጨረሻም አቶ ሜሁንና የማልመውን ሥራዬን

አስተዋውቆኛል፡፡ ባለፉት ብዙ ወራት ያለፍኩበት ምንም ይሁን ምን እግዚአብሔር ከአጠገቤ አልተለየም፤ ብቻዬንም አልሆንኩም፡፡

አዲሱን ሥራዬን ወድጀዋለሁ፤ እያንዳንዷ ቀን ካለፈው የበለጠ አስደሳች ነች፡፡ በተመድ ብዙ የተለያየ ዜግነት ያላቸው ሰዎች ስላሉ በገዛ አገሬ ጎብኝ የሆንኩ ያክል ተሰማኝ፡፡ አዳዲስ ክህሎቶችን በተከታታይ ስማር፣ ሰዎችን ስተዋወቅና እንግሊዝኛዬን ሳሻሽል ቆየሁ፡፡

ያለኝ የእግዚአብሔር ቡራኬ ብቻ ሳይሆን ደሞዜም ጭምር ነው! ወዲውያኑም ለአከስቶቹ ገንዘብ መላክና አሎይዜና ልጆቿን ላደረጉልኝ ነገር ሁሉ ለማመስገን ምግብና አዳዲስ ልብሶች መግዛት ቻልኩ፡፡ ቤትና ቤተሰብ በጣም በፈለግሁበት ወቅት ሰጥተውኛል … ግን የመሄጃ ጊዜዬም እንደተቃረበ አውቄያለሁ፡፡

በጥቅምት መጀመሪያ ሁሉም ከፈረንሳይ ምሽግ የመጡት ጓደኞቹ የአሎይዜን ቤት ለቀው ስለሄዱ በአቅራቢያዬ ያለው ሁሉም ነገር መቀያየር ጀምሯል፡፡ በ1959ኙና 1973ቱ የዘር ጭፍጨፋዎች ያመለጡ የነበሩ ከሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ቱትሲ ስደተኞች ከዓለም ዙሪያ ልጆቻቸውን፣ የልጅ ልጆቻቸውንና ያላቸውን አዲስ የባህል ቅርስና እንግዳ ቋንቋዎች ይዘው መመለስ ጀማምረዋል፡፡ የሀገሪቱንም ገጽታ እየቀየሩት ነው፡፡ አንድ ሚሊዮን ስደተኛ ተመለሰ፡፡ በዘር ፍጅቱ የተፈጀውን ያህል ቱትሲ መሆኑ ነው - ልረዳው የማልችለው ቁጥር፡፡

ቱትሲዎቹ ሲመለሱ ከሁለት ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ሁቱዎች የበቀል ግድያዎችን ፈርተው ሩዋንዳን ለቀው ተሰደዋል፡፡ አብዛኞቹ በሌሎች አገሮች ባሉ ቆሻሻ የስደተኞች መጠለያዎች መሰቃየት ዕጣቸው ሲሆን ብዙዎች በበሽታና በምግብ እጥረት ሞተዋል፡፡ በየስፍራው ሥቃይ ነሳሏል፡፡ አንድ ቀን ብዙ እንዳወቅሁና በቂ ገንዘብ እንዳጠራቀምኩ በሀገሬ ሆኜ የተሸከምኩትን ብስጭት ትቼው ርቄ እሄዳለሁ፡፡ ለአሁኑ ግን የማደርጋቸው ትናንሽ ለውጦች አሉኝ፡፡ ሕይወት በሩዋንዳ እየተለዋወጠ ስለሆነ እኔም አብሬው እለዋወጥ ይገ’ለሁ፡፡

አምላኬን በፍቅርና በበጎ ስሜቶች የምከበብበትን አዲስ ቤት እንዲሰጠኝ ለመንኩት፡፡ በዚህ ወቅት የአሎይዜን ቤት የፊት በር ስከፍት የራሴን ጸሎት ራሴው እንድመልስ አደረገኝ፡፡ ውድ ጓደኛዬና አንድ ክፍል በኮሌጅ አብራኝ ትማር የነበረችው ሳራ በሩ ላይ ቆማ እኔን በማግኘቷ በደስታ ታነባለች፡፡ ስትፈልገኝ ቆይታ ነው ያገኘችኝ፤ ሁለታችንም ተጫጨቸን ተቃቀፍን፡፡ ለሰዓታት ስለነበረው ነገር ሁሉ እንዲሁ ስንጠያየቅና እንባችንን ስናዘራ ቆየን፡፡ ቁሱ ወንድሞቻችንን አገስቲንንና ቪያኒን እንዴት አድርገው በሌሊት እንዳባረሯቸውና ልጆቹ እንዴት አብረው እንደሞቱ ስነግራት ልቤ እንደገና ተሸበረች - በጣም እንወዳቸው ስለነበሩት

ስለወንድሞቻችንና ስለተቀረው ቤተሰቤ በጣም ተላቀስን - ሳራ ሁሉንም ታውቃቸዋለች፤ ትወዳቸውማለች::

«ሁሌም ቢሆን እኛ ቤተሰብሽ እንሆናለን» አለች ሳራ:: «ነይ እኔ ቤት ኑሪ... መልሰን እህቶች እንሆናለን!» ሳራ ለኔ እጅግ ልዩ ስለሆነችና ችሮታዋንም ስለምፈልገው ወዲያውኑ ተቀበልኩት:: በዚያኑ ቀን እቃዎቼን አስሬ ወደ ወላጆቿ ቤት ሄድኩ:: አሎይዜ የሳራ ቤት ከቤቷ አምስት ደቂቃ ራቅ ብሎ ስለሚገኝ መሄዴ ምንም አልመሰላት፤ ቶሎ ቶሎ እንደምጠይቃትም ቃል ገባሁላት::

በወቅቱ ከሳራ ቤት የበለጠ ሰላማዊና ፍቅር የሞላበት ቤት አልተመኘሁም:: በዕድሜ የገፉት ወላጆቿ ለ55 ዓመታት ያህል በጋብቻ ኖረዋል፤ እርስ በርሳቸው ግን አሁንም በአሥራዎቹ ዕድሜ ያለን ነን እያሉ ይቀላለዳሉ፤ ይኩራሩማል:: አጥባቂ ክርስቲያኖች ሲሆኑ በየቀኑ ጠዋት አብረው ወደ ቤተክርስቲያን በመሄድ ይጸልያሉ:: ቤታቸው ከእግዚአብሔር ጋር የነበረኝን የግል ግንኙነት መልሶ ለመገንባት ትክክለኛው ስፍራ፣ ስለ ቤተሰቤም ለማልቀስና ራሴን መልሼ ለማዳን ሁነኛው ቦታ ነው::

ቀስ በቀስ የቆሰለው ልቤ እነ ሳራ ቤት አሁንም እንኳን ወረቀት ላይ ላሰፍራቸው የማልችላቸውን ቃላት እንድናገር ብርታቱን አገኘ:: በዚያን ወቅት ሴኔጋል ሆኖ ልኑር ልሙት ለማያውቀው ለወንድሜ ለኤይማብልም የምጽፍበት ሰዓቱ ደረሰ:: በከፊል ምንም የመላላኪያ አገልግሎት ባለመኖሩና በዋነኛነት ቃላቱን ካላየኋቸው እነዚያ አሰቃቂ ተግባራት በእውነት እንዳልተከሰቱ አስባለሁ በማለት ይህን አስቸጋሪ ተግባር በይደር አቆይቼዋለሁ:: ችግሮቹ ግን ያው ተከስተዋል - እውንም ናቸው:: ስለሆነም መጨረሻ ላይ መቀበል ጀማመርኩ::

የአባቴን መቁጠሪያ በአጠገቤ ጠረጴዛው ላይ አስቀምጬ መጻፉን ተያያዝኩት:- የኔ ውድ ኤይማብል፣ ይህ በሕይወቴ የጻፍኩት እጅግ አሳዛኙ ደብዳቤዬ ነው፣ አንተም የምትቀበለው እጅግ ዘግናኙ ...

ምዕራፍ 23
ሙታኑን ስቀብር

«ወላጆቸሽ የት ነው የሚኖሩት?» ይህ ጥያቄ በተመድ ሥራዬን ከጀመርኩ ከጥቂት ወራት በኋላ የቀረበልኝ።።

«ልቤ ውስጥ ካልሆነ በስተቀር በሕይወት የሉም» በማለት በትዕግሥት መለስኩ።። «በዘር ፍጅቱ ተገድለዋል።።»

የተመድ ሰቆቃዬን ለመርሳት የምችልበት ስፍራ አይደለም።። እዚያ የሚሰሩት አብዛኞቹ ከሀገሪቱ ውጪ የመጡ ስለሆኑ የቤተሰቤን ዕጣ ፈንታ ሲያውቁ የዘውጌ አባላት አብዛኞቹ በተገደሉበት ሁኔታ እኔ እንዴት ልተርፍ እንደቻልኩ ለማወቅ በጣም ይጓጓሉ።።

«ይቅርታ» አሉኝ እያዋሩኝ ያሉት ሰውዬ።። «አላወቅሁም።። እንዳላበሳጨሁሽ ተስፋ አደርጋለሁ።።» ስማቸው ኮሎኔል ጉዬ ሲሆን ወደ ሩዋንዳ አገሪቱን በማረጋጋቱ ተግባር ለማገዝ የመጣው የተመድ ሰላም አስከባሪ ጦር አዛዥ ሴኔጋላዊ ናቸው።።

እኔን ስለማበሳጨት እንዳይጨነቁ ለኮሎኔሉ ነገርኳቸው።። ጥያቄ መጠየቅ ያለፍኩትን ሁሉ ከግምት ውስጥ ሳስገባው ከሚያሳስቡኝ ነገሮች በጣም ዝቅተኛውን ደረጃ ነው የሚይዘው።። አሁንም ቢሆን ከጦርነቱ ወዲህ ባላያቸውም አክስቶችና በመጣሁበት ኪቡዬ ክፍለሀገር የሚኖር አጎት እንዳለኝ አሳወቅኋቸው።።

«አሃ፣ ኪቡዬ ... እዚያ የሰፈሩ የተወሰኑ ወታደሮች አሉኝ» በማለት መለሱልኝ።። «ዘመዶቸሽን መጠየቅ ካስፈለገሽ ላጓጉዝሽና ራሴ ላጅብሽ እችላለሁ።። ጓደኛም ከፈልግሽ ማምጣት ትችያለሽ።።»

በሀገሪቱ መዘዋወር ያን ጊዜም ቢሆን አስቸጋሪና አደጋ ላይ የሚጥል ስለሆነ የእርሳቸው ግብግ ትልቅ ችሮታ ነው።።

«በእውነት? መቼ እንደሆነ ይንገሩኝና እንሄዳለን ኮሎኔል።።»

ከሁለት ሳምንታት በኋላ ሳራና እኔ ወታደራዊ ጠያራ ላይ በቀበቶ ታስረን አንዳችን የሌላችንን እጆች እየያዝንና በደስታ እየሣቅን በሩዋንዳ አረንጓዴ ተራሮች ላይ እንበር ጀመር።። ሁለታችንም በአየር በርረን ስለማናውቅ ኮሎኔሉ የመብረር እድሉን ሲሰጡን እውነት አልመሰለንም ነበር!

ውቧን አገሬን ቁልቁል ሳያት የዘር ጭፍጨፋውን አስቀያሚ እውነታ ማመን አስቸገረኝ።። በነዚያ ጨለማ ቀናት ምን ያህል ጊዜ ነው ወፍ ሆኜ በተወለድኩ ብዬ

የተመኘሁት? ምን ያህልስ ጊዜ ነው ከመታጠቢያ ቤት እስር ቤቴ ወጥቼ ከአሰቃቂው ሰቆቃ በላይ ርቄ መብረርን ያለምኩት? እና አሁን እዚህ ወንጀሉ የተፈጸመበትን ስፍራ ተመልሼ ለመጎብኘት ይኸው እበር ይጥለሁ፡፡ ከማታባ አምልጬ ኪጋሊ ለመድረስ ስንት ጊዜ ፈጅቶብኝ እንደነበር አውርቼልዎታለሁ - ለመመለስ ይኸው 30 ደቂቃ ብቻ ፈጅብኝና አረፈው፡፡

ኤይማብል ከኔ ጋር ቢሆን ብዬ ተመኘሁ፤ ግን አልተቻለም፡፡ የመልዕክት መላላኪያ አገልግሎቱ ገና ቀርፋፋ ሲሆን፤ በዚያም ላይ ከእርሱ የመልስ ደብዳቤ እንኳን ለማግኘት ሳምንታት ፈጅቶብኛል፡፡ ከኔ ይህ ደብዳቤ ስለደረሰውና በሕይወት መኖሬን በማወቁ በጣም ደስተኛ ስለሆነ ስሜቱን ለመግለጽ ቃላት ሊያገኝልኝ እንዳልቻለ ገልጾ ጻፈልኝ፡፡ በዘር ፍጅቱ ወቅት የዜና ዘገባዎችን ይከታተል ስለነበር ሁሉም የቤተሰባችን አባል ከሌላው ሩዋንዳ ውስጥ ካለ ሁሉም ቱትሲ ጋር ወድሟል ብሎ አምኖ ተስፋ ቆርጦ ነበር፡፡ ለመገደል ካልሆነ በቀር በዘር ፍጅቱ ወቅት ወደ ሀገሪቱ የሚመለስበት ምንም መንገድ አልነበረውም፡፡

ለመምጣት ችግር የሆነበት ደግሞ በወቅቱ ለመመለስ ወጪውን መሸፈን አለመቻሉ ነው፡፡ ተማሪ ስለሆነ ገቢ የለውም፣ የሚኖረው 5 000 ኪሎሜትር ርቆ በሴኔጋል ነው፡፡ የአየር መሳፈሪያ ወጭው ብቻ 2 000 የአሜሪካን ዶላር ይፈጃል፤ ይህም የማይታሰብ ነው! ሙሉ ወጭውን ሸፍኖ የሚያስተምረው የአውሮፓ ድርጅትም ሩዋንዳ በጣም አደገኛ የጦርነት ቀጠና ስለሆነ ወደዚያ የምትሄድበትን ክፍያ አልከፍልልህም ይለዋል፡፡ ወንድሜ ትምህርቱን አቋርጦ መጥቶ ከኔ ጋር ለመኖር ቢፈልግም እማማንና አባባን የሚያኮራበት ሁነኛ መንገድ ትምህርቱን በከፍተኛ ውጤት መጨረስ እንደሆነ ነገርኩት፡፡ በየሳምንቱ ለመጻጻፍ፣ ለወደፊቱ ለመጠያየቅና ገንዘብም ለማጠራቀም ተስማማን፡፡ እናም አሁን ወደ ማታባ ላገኘሁት የነጻ የአየር ጉዞ ምስጋና ይግባውና ቤታችንን ያለ ብቸኛው ቀሪ ወንድሜ እጎበኛለሁ፡፡

ትንሿ ወታደራዊ ጠያራ መሬት ላይ ካረፈች በኋላ ኮሎኔል ጉዬ ትራኡሬ ለሚባል ብርቱ ወጣት መኪናን አደራ ብለው በወታደሮቹ ምሽግ አስቀምጠውን ይሄዳሉ፡፡ እርሱም ለእያንዳንዱ ወታደር የኮሎኔል ጉዬ ልጆች ናቸው ብሎ አስተዋወቀን፡፡ ከዚህን ጊዜ በፊት በነበሩኝ የወታደር ምሽግ ቆይታዎቼ አግኝቼው የማላውቀውን አገኘሁ - ሳራና እኔ የየራሳችን ክፍል፣ የምንተኛባቸው አልጋዎች፣ ምርጥ ምግብ ብሎም የእያንዳንዱ ወታደር አክብሮትና እገዛ ተቸረን፡፡ እንዲያውም እስከ ንጋት ድረስ ባህላዊ የሴኔጋል ዘፈኖችን ሲዘፍኑና እርስ በርሳቸው ሲቀላለዱ አብረን አነጋን፡፡ ሳራ በአቀባበሉ ደስ ከመሰኘቷም በላይ ደኅንነት ሲሰማት እኔም አገሬ በመግባቴ ደስ ተሰኘሁ፡፡

በማግስቱ ወደ መንደሬ ለመሄድ ስምንት ኪሎሜትር የሚርቀውን የእግር መንገድ ለመጓዝ ስዘገጃጅ መኪንን ትራኦሬ ስለደህንነታችን ያለውን ሥጋት ይናገር ጀመር። የዘር ፍጅቱ ቢያበቃም በሀገሪቱ ግልጽ የሆነ ጥላቻ ስለነገሰ በዚያን ወቅትም ግድያ ይፈጸማል። መኪኖኑ በትጥቅ አጀብ ሊልከን ወሰነ - አጀቡም ከሁለት ደርዘን ያላነሱ ወታደሮችንና አምስት ብረት-ለበስ ተሽከርካሪዎችን ያጠቃልላል። ማታባ በጀግና ኩራት እንገባለን እንጂ እንደ ተመላሽ ስደተኛ አንሹለከለክም። በዚያች መንደር ያን ያህል ጊዜ በፍራቻና ሥጋት ተሸሽጌባታለሁ፤ አሁን ግን ራሴን ቀና አድርጌ መሄዴ መልካም ነው።

በልጅነቴ በጣም በማውቀው ሰማይ ስር ተሸከርካሪዎቻችንን ስንነዳ ስሜቴ በፍጥነት ወደ ኃይለኛ ብስጭት ተለወጠ። ወንድሞቼና እኔ ብዙውን ጊዜ እንሄድበት ወደነበረው መንገድ ስንገባ ማልቀስ ጀመርኩ፤ ከዚያም በወቅቱ ጭር ባለው እናቴ ታስተምርበት በነበረው ትምህርት ቤት አልፈን አባታችንን ተከትለን በጠዋት ኪቩ ሐይቅ ወርደን ልንዋኝ በምናልፍበት መንገድ ቁልቁል ወረድን።

ሳራ እጇን በትከሻዬ አድርጋ ልታጽናናኝ ብትሞክርም አልሆነም - መጽናናት የምችል አልነበርኩም። በፈራረሱ መስኮቶችና በተዘጉ የውጪ በሮች አጮልቀው የሚያዩን ፊቶች ጥላ ይታየኛል ... ብዙ ወገኖቼን አሳደው የገደሉ ጽንፈኛ ሁቱዎች ፊቶች። ብዙዎቹን የቱትሲዎችን ቤቶች ራሳቸው ካቃጠሉ በኋላ አሁን ብቻቸውን ቆመው ያሉትን ብቸኛ ቤቶች በንብረትነት ይዘዋቸዋል።

ከዚያም የራሴ ቤት ጋ ደረስን።

ጣራ የለ፣ መስኮት የለ፣ በር የለ፤ ሙሉ በሙሉ ወድሟል። ገዳዮቹ ለጭፍጨፋቸው ሲዘገጃጁ እኛ ለቀናት ሬድዮ ስናዳምጥበት የነበረውን የተቃጠለውን መሬት የተወሰኑ ከፊል ግንቦች እየጠበቁት ዙብ ቆመዋል። አንድ ወቅት የወላጆቼ ሕልም የነበሩትን ባዶ ክፍሎች እየቃኘሁ በድንጋይ መዋቅሩ ውስጥ ተዟዟርኩ። የተጎዱ የቤት እቃዎችም ሆኑ የተቃጠሉ ልብሶች አሻራ የለም - ማንም ሊገምት እንደሚችለው ቤቱ ከመጋየቱ በፊት ንብረታችን ተዘርፏል።

ብዙ በሕይወት የተረፉ ቱትሲ ጎረቤቶቻችን ወታደራዊ አጀባችንን አይተው ሰላም ሊሉኝ መጡ። በተደበቅኩባቸው ጊዜያት ስለተከሰቱት መጥፎ ነገሮች ነገሩኝ፤ እናቴ በተቀበረችበት ቦታ ላይ ሆነንም እምዬ እናቴ አንዴት እንደተገደለች ያስረዱኝ ገቡ።

የተወሰኑ የዳማሲን ጓደኞች ሊያገኙ የቻሏቸውን የሰውነቱን ክፍሎች በችኮላ ወደቀበሩባት አነስተኛ ጉድጓድ ወሰዱኝ። ዘበኛችን የነበረው ካሩቡ ወንድሜ ሲገደል ስላየ ንግግሩን ቃል በቃልና እያንዳንዷ ጥቃት ስትሰነዘርበት የነበረውን ክስተት ነገረኝ።

ዘግናኞቹ ትውስታዎች፣ ጭካኔ የተሞላባቸው አረመኔያዊ ዝርዝሮቹ በዝተው ከምችለው በላይ ሆኑብኝ፡፡ ከሃዘኑ ገና ማገገሜ ስለሆነ ቁስሎቼ እንደገና በዚህ አሰቃቂ እውነታ ምክንያት በግድ ሲቀረፉ ተሰማኝ፡፡ ጎረቤቶቼንና ወታደሮቹን ለእናቴና ለወንድሜ የሚገባቸውን ቀብር እንዳደርግላቸው እንዲያግዙኝ ለመጠየቅ ፈለግሁ፤ መናገር ግን አቃተኝ፡፡ በጉሮሮዬ የተፈጠረው እብጠት ድምጼን ስላቆመው ለወታደሮቹ መልሰው ወደ ምሽጉ እንዲወስዱኝ በእጄ ምልክት ሰጠኋቸው፡፡

እማማንና ዳማሲንን ከሸፈነው ምልክት-አልባ የአቧራ ክምር አልፈን ከቤቴ ርቀን እየነዳን ሳለን በአፌ መራራ፣ ቆሻሻ የጥላቻ ጣዕም በአፌ መጣብኝ፡፡ በመልስ ጉዟችን ወቅት ስናልፍ አጨንቁረው የሚያዩንን ፊቶች አየሁና እነዚያ ሰዎች በእጃቸው ደም እንዳለባቸው በሙሉ ልቤ ታወቀኝ - የጎረቤቶቻቸው ደም ... የቤተሰቤ ደም፡፡ ወታደሮቹ ማታባ ላይ ነዳጅ አርከፍክፈውልኝ ወደ አመድነት የሚቀይራትን ክብሪት ጭሬ እንድለኩስባት እንዲያደርጉኝ ፈለግሁ፡፡

ምሽጉ ጋ ስንደርስ ከማንም ጋር ሳላወራ በቀጥታ ወደ መኝታዬ ሄድኩ፡፡ ነፍሴ ከራሷ ጋር ተጣላች፡፡ ምኅረት ለማድረግ በጣም ብሚሚትም ይህን በማድረጌ እንደተታለልኩ ተሰማኝ፤ ጭላጭ ምኅረት እንኳን አልቀረኝም፡፡ የቤቴን መፈራረስ ማየቴና የምወዳቸውን ሰዎች የተተዉና ብቻቸውን የቀሩ መቃብሮች መኅብኘቴ መሃሪዋን መንፈሴን አስጨነቃት። ጎረቤቶቼ የቤተሰቤን አሰቃቂ የግድያ ወሬ በጆሮቼ ሲያሠራጩት ከነፍሴ አስወግጄዋለሁ ብዬ ያሰብኩት የጥላቻ ስሜት ከማንነቴ ጥግ በታደሰ ጉልበት በግድ ተስፈንጥሮ ወጣ፡፡ ልቤ በቀልን ተርባ በውስጤ በገንኩ፡፡ *እነዚያ ክፉ እንሰሳት! አራዊት ናቸው፣ አራዊት፣ አራዊት፣ አራዊት!*

ለሰዓታት መኝታዬ ላይ ተገላበጥኩ፡፡ ዲያብሎስ እየፈተነኝ እንደሆነ ታውቆኛል - ከእግዚአብሔር ብርሃን፣ ከምህረቱም ነጻነት አርቆ እየወሰደኝ እንደሆነ፡፡ የአሉታዊ ሐሳቦቼ ክብደት በጨለማው እየመራ ካመጣኝ ብርሃን ሲነጥለኝና ሲጎትተኝ ይታወቀኛል፡፡ በዚያ ሌሊት እንደተሰማኝ ዓይነት ብቸኝነት ፈጽሞ ተሰምቶኝ አያውቅም፡፡ እግዚአብሔር እውነተኛው ባልንጀራዬ ነው፤ እነዚህ ስሜቶች በመሀላችን እንደ ግንብ ቆመዋል፡፡ ሐሳቦቼ እንዳሳመሙት አወቅሁ፤ ይህም አሰቀቀኝ፡፡

ከአልጋዬ ወርጄ ተንበረከክሁ፡፡ «ስለ ርኩሳን ሐሳቦቼ እግዚአብሔር ሆይ ማረኝ» ስልም ጸለይኩ፡፡ «አባከህ ... ሁልጊዜ እንዳደረከው ይህን ህመም ከኔ አርቀህ ልቤን አንጻልኝ፡፡ በፍቅርህና በምኅረትህ ኃይል ሙላኝ፡፡ እነዚያን አሰቃቂ ነገሮች ያደረጉት አሁንም ቢሆን ልጆችህ ናቸው፡፡ ስለዚህም ልርዳቸው፤ አንተም እንድምራቸው አግዘኝ፡፡ ኧረ አምላኬ፣ እንድወዳቸው እርዳኝ፡፡»

ሳንባዎቼን ድንገተኛ የአየር መአት ሞላቸው፡፡ በከባድ የእፎይታ ትንፋሽ አቃሰትኩ፤ ራሴንም ትራሱ ላይ እንደገና አሳረፍኩት፡፡ ሰላሜን እንደገና አገኘኋት፡፡

አዎን፣ ተበሳጭቼ፣ በእጅጉ በግኜም ነበር፤ ብስጭቴ ግን ለበጎ ሆነ፡፡ እንዲቆጣጠረኝ የፈቀድኩለት ይህ ብስጭት ንጹሕ መሆኑን አወቅሁ፡፡ ምሬት ወይንም ጥላቻ የሚባል ነገር የሌለበት፡፡ ቤተሰቤን በእጅጉ ብናፍቅም እንደ ግርሻ ወጥሮ ይዞኝ የነበረው ኀዴቴ ግን ለቆኛል፡፡

ቤተሰቤን የጎዱት ሰዎች እንዲያውም ራሳቸውን በበለጠ ጎድተዋል፤ በመሆኑም ላዝንላቸው ይገባኛል፡፡ በሰብዓዊነትና በእግዚአብሔር ላይ ለፈጸሟቸው ግፎች መቀጣት እንዳለባቸው ማንም ጥርጥር አልነበረውም፡፡ ተጠያቂ የሚሆኑትን ለመያዝ ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ለማቋቋም በተመድ ውይይት ተጀምሯል፤ ይህም እንዲከሰት፣ ርህራሄም እንዲኖር ጸልዬአለሁ፡፡ እግዚአብሔርን የጥላቻን ዑደትና ጽንፍ የረገጠን ጥላቻ የሚያቆመውን ምኅረት እንዲለግሰን ጠይቄዋለሁ፡፡

ልቤና አእምሮዬ ሁሌ ኀዴት ሊሰማቸው እንደሚዳዳቸው አውቄዋለሁ - ውንጀላንና ጥላቻንም እንደሚፈልጉ፡፡ አሉታዊ ስሜቴ ሲመጣብኝ ይህን ችግር ፈታሁት፤ እንዲያድግ ወይንም እንዲባባስ አልፈለግሁም፡፡ የሁሉም እውነተኛ ኃይል ምንጭ ወደሆነው ወዲያውኑ ፊቴን እመልሳለሁ፡፡ ወደ እግዚአብሔር እዞራለሁ፤ ፍቅሩና ምህረቱም ከለላና ድኅነት ይሆኑኛል፡፡

ራሴን ቀና ሳደርግ ጨረቃ እንደወጣች አየሁ፡፡ ወታደሮቹ ሲስቁና ሲዘፍኑ ስለሰማኋቸው ወደ ውጪ ወጣሁ፡፡ ሳራና እኔ እርስ በርሳችን ተሣሣቅንና እንደገና እዚያ ባሉት በሁሉም ላይ ፈገግ አልኩ፡፡ ወታደሮቹ እየተዝናኑ ስለሆነ እኔ በጣም ደስ ያለኝ መስዬ ስቀላቀላቸው ተገረሙ፡፡ ሌሊቱን ሙሉ ሲጨፍሩ ሳራና እኔ ታዳሚ በመሆን ስናደማምቅላቸው ቆየን፡፡

በቀጣዩ ቀን እናቴንና ወንድሜን እንደ ደንቡ ለመቅበር መኰንኑ መልሶ ወደ መንደሩ ይወስደኝ እንደሆን ጠየቅሁት፡፡ በዋዜማው የገባሁበትን ሐዘን አስቦ በእውነት አስፈላጊው ጥንካሬ እንዳለኝ ጠየቀኝ፡፡ ጥንካሬው እንዳለኝም አረጋገጥኩለትና ወደ መንደሩ ያለፈውን ቀን የሚያህል የወታደር አጅብ ፈቀደልኝ፡፡

መንገዶችን ላይ በድሮው ቤታችን አቅራቢያ የሚኖሩትን አከስቶቼን ጎኒንና ኢስፔራንስን ለመጠየቅ ቆምን፡፡ ከፈረንሳውያኑ ምሽግ ከወጣን ወዲህ አልተገናኘንም፡፡ ሁለቱም ከሰቆቃቸው ሙሉ በሙሉ ባያገግሙም (እንዳያያዛቸውማ መቼም የሚያገግሙ አይመስሉም) በወቅቱ ግን ቢያንስ በጣም በተሻለ ሁኔታ ላይ ነበሩ፡፡ ስሜት በተቀላቀለበት ሁኔታ በመንገድ ዳር መልሰን ተገናኘን፣ እኔ ግን ልቤን ወደፊት ለሚጠብቀኝ ጽኑ ግዳጅ በደኅና አቆየሁት፡፡ የእማማና የዳማሲን ቀብር ላይ የሚገኙ ሰዎችን እንዲፈልጉና አሮጌው ቤቴ ጋ እንዲያገኙኝ ነገርኳቸው፡፡

አብዛኞቹ በመንደሬ ያሉት ቱትሲ የዘር ፍጅት ተራፊዎችና የተወሰኑ ሁቱ ወዳጆቻችን ተገኙ። አንድ ካይታሬ የተባሉ ሽማግሌ የቤተሰቤ ወዳጅ ሁለት የሬሳ ሣጥን፣ አንድ ሌላ ሰው ደግሞ አካፋና መጽሐፍ ቅዱስ አምጥተው ሁላችንም አስከሬናቸውን ፍለጋ ሄድን። በመጀመሪያ ዳማሲንን ፍለጋ ተቆፈረ፤ የተወሰኑ ጎረቤቶቻችን እንዳላይ ለመከለል ከበቡኝ - ቀስ ብለው የተገኘውን የአካሉን ክፍል እንዳላይ ከለከሉኝ።

ተጋፍቼ አለፍኳቸው። «ወንድሜ አይደል እንዴ - ማየት አለብኝ» ብዬ አስቸገርኩ። አስከሬኑን በዓይኔ ባላይ ኖሮ ዳማሲን ሞቷል ብዬ መቼም የማምን አይመስለኝም። ከዚያ አካፋው ከአጥንት ጋር ሲጋጭ ሰማሁት፤ ከዚያም አየሁት ... የጎድን አጥንቶቹን አየሁ። መጀመሪያ ያየሁት ምንም ልብስ እንዳልለበሰ ነው፤ ከመግደላቸው በፊት ምን ያህል ክብሩን ሊገፉት እንደሞከሩም አስታወስኩ።

«አትዪ» አለችኝ ኢስፔራንስ። ግን ግድ ይለኛል - የጎድን አጥንቶቹን እንጂ ምንም አላየሁም። ከታትፈውታል - ክርኖቹን፣ ራሱን ... ወይኔ፣ እግዚአብሔር፣ የኔ ውድ ዳማሲን፣ ምንድነው ያደረጉህ? ስል እንደ እንስሳ ግሳት ዓይነት ድምፅ አወጣሁ።

አንድ ሰው ወደ መቃብሩ ጎንበስ ብሎ የወንድሜን የራስ ቅል በእጁ ይዞ ቀና አለና ወደኔ ዞረ። መንጋጭላው ወጣ ብሎ ጥርሱን አየሁት ... በጥርሱ አወቅሁት። ጥርሱ ከአማላይ ፈገግታው የቀረው ብቸኛው ነው። እኔ ላይ በአሰቃቂና አስፈሪ ፈገግታ አተኩሮብኛል። አይ ዳማሲንዬ! እንዲህ መጨረሻህ ሳያምር ይቅር!

«እንዴ አይሆንም! ... እንዴ ዳማሲን! ... ወይኔ! ቅድስት ማርያም! የአምላክ እናት!» መሬቷ ወደኔ ሮጠችና ራሴንም ድንጋይ መታው፣ ከዚያማ በቃ ጽልመት ብቻ።

ራሴን እስታለሁ ብዬ ባልጠበቅም አእምሮዬ በመጨረሻ የወንድሜን ሞት ሲያምን ከዓለም የምንተነፍሰው አየር ተመጣ እንዳለቀ ተሰማው። ዘመዶቼና ጎረቤቶቼ እንድነቃ አድርገው ደጋግፈው በእግሮቼ አቁመውኝ የዳማሲንን አስከሬን ወደ ሣጥን አስገብተን ደግሞ የእማማን ፍለጋ ይዘነው እንዞር ገባን። አንዴ ለጉድ ጎልቶኝ! ሰዎቹ በዚህን ሰዓት የሰውነቷ ክፍሎች አይለዩም፤ ደግሞ በጣም አፈር ስለበላው እጅጉን ያበሳጭሻል ብለው አስቸገሩኝ። የሕመሜ ወሰን ላይ ስለደረስኩም ተስማማሁ። ምንም ያህል ልቤን ባጠነክረውም እናቴን በእንደዚያ አይነቱ ሁኔታ ማየቱ ለአፍታሪ ዓይኖቼ መቻል ከሚችሉት በላይ ይሆንባቸዋል። አስከሬኗን ሳላይ ለመቅበር ተስማማሁ። ይልቅ በሕይወት እንደነበረችው ባስታውሳት ይሻለኛል ... ዘላለም በልቤና በህልሞቼ እንደምትኖረው ሁሉ።

አንድ ሰው እናቴ ባለችበት ሣጥን ክዳን ላይ ሚስማር ሲመታ የጓደኞቼንና የዘመዶቼን ፊቶች አየሁ - የተሸበሩ ሕይወቶችን የሚያንጸባርቁ የተሸበሩ ፊቶች።

ሶስቱ ልጆቿ እፊቷ ሲታረዱ እንድታይ የተገደደችው የአከስቴ ልጅ፤ በሚወዳት ሚስቱና በሰባት ልጆቹ ሞት ከበፊቱ ማንነቱ ጥላው ብቻ የቀረው በአንድ ወቅት የሚንቀለቀል ቁርጠኝነት የነበረው አጎቴ ፖልና ባሎቻቸው ሞተውባቸው ልጆቻቸው መዳን በማይችሉበት ሁኔታ ታመው ያሉት አከስቶቹ ሁሉ ቆመዋል። ከተራራ የከበደ ሐዘን የተሸከሙ ፍጡራን!

በመንደሩ ላይ የወረደውን ትካዜ ሁላችንም እንጋራዋለን፣ ግን በዙሪያዬ የተሰበሰቡት ሰዎች ከኔ በላይ ብዙ ሰው እንደተነጠቁ አውቄያለሁ። እምነታቸውን አጥተዋል - በዚያም ተስፋ አጥተዋል። በእናቴና ወንድሜ አስከሬኖች ላይ አፍጥጬ አስከሬኖቻቸውን ላገኘው የማልችላቸውን አባቴና ቪያኒን አሰብኩ ... አምላክንም አመሰገንኩት። ሁሉንም ባጣም እምነቴን ግን ጠብቄያለሁ፤ እሱም ያጠነክረኛል። አበርትቶኛል፤ አሁንም ሕይወት ዓላማ እንዳላት አሳውቆኛል።

«የት እናድርጋቸው በይ? የት እንቅበራቸው?» እጆቹን በጽድ ሳጥኖቹ ላይ ወዲያና ወዲህ እያላወሰና እያነባ አጎቴ ፖል ጠየቀኝ።

«እቤት» አልኩት። «እቤት ወስደን እናሣርፋቸው።»

የእናቴንና የወንድሜን አስከሬኖች ይዘን ወደ ቤታችን ፍርሥራሽ ወሰድንና በአንድ ወቅት ሣቅና ፍቅር የሚያስተጋባበት የነበረው አንደኛው ቤት በነበረበት ስፍራ ወለል ላይ ትልቅ የመቃብር ጉድጓድ ቆፈርን። በመንደሩ ያሉ የቀሩ ምንም ቄሶች ስለሌሉ ራሳችን የደንቡን አደረግን። እማማ ትወዳቸው የነበሩ የተወሰኑ መዝሙሮች ዘመርን፤ ብዙ ጸሎትም አደረስን። እግዚአብሔርን ቤተሰቤን ወደራሱ አቅርቦ እንዲይዝልኝና ንጹሕ ነፍሶቻቸውን በገነት ባለህ እንዲልልኝ ጠየቅሁት ... ከዚያም ደኅና ሁኑ አልኩ።

«በቃ መሄጃችን ሰዓቱ አሁን ነው ሳራ - ኪጋሊ መሄጃችን ደርሷል» ስል ለውዷ ባልንጀራዬ፣ በማደጎ ተቀብላ ለምታኖረኝ እህቴ ብሎም አዲስ ቤተሰብ ለሰጠችኝ ለሳራ አንሾካሾክሁ።

ወዲያውኑም ተመልሰን በደመና ውስጥ ገብተን ከመንደሬ በላይ ከፍ ብዬ እበር ጀመር፤ ሕይወታችንን ካጨቀዩት ሰቆቃዎች በላይ ... በጣም ከፍ በማለቴም የእግዚአብሔርን ፊት መንካት የምችል መሰለኝ።

ምዕራፍ 24
ቋሚውን ሰምር

ቤተሰቤ በገነት እንዳለ ማወቄ እነሱን የማጣቴን ሕመም አላቀለለልኝም። አሟሟታቸው በታሰበኝ ቁጥር ልቦናዬን የሚቆጣጠረውን ሰንካዩን ሰቀቀን ላራግፈው አልተቻለኝም። እንቅልፍ ከሚነሳኝና ቀን ከሚያስቸግረኝ ሥቃይ ለመገላገል በየምሽቱ ጸልያለሁ። የተወሰነ ጊዜ ወሰደብኝ፣ ግን እንደሁሌው እግዚአብሔር ጸሎቴን ሰማኝ። በዚህ ወቅት ይህን ያደረገው እስከዚያን ጊዜ አይቻቸው ከነበሩት የተለየ ሕልም በማሳየት ነው።

በቤተሰቤ ቤት ላይ በወታደራዊ ጠያራ እየበረርኩ ሳለሁ ጥቁር ደመና ከበበኝ። እማማን፣ አባባን፣ ዳማሲንንና ቪያኒን ከኔ በላይ ከፍ ብለው በሰማይ ቆመውና ጸጥታን በሚያንጸባርቅ ልዩ፣ ነጭ ብርሃን ተጥለቅልቀው ታዩኝ። ብርሃኑ የሸፈነኝን ጥቁር ጨለማ እስኪገፈው ድረስ በሰማይ ላይ ተንሠራፋ። በድንገትም እንደገና ከቤተሰቤ ጋር ተገናኘሁ። ሕልሙ በጣም እውን ስለሆነ በእጇ ተንጠራርቼ የሰውነታቸውን ሙቀትና የንክኪያቸውን ሃያልነት ተረዳሁ። በጣም ደስ ስለተሰኘሁ በአየሩ ላይ ዳንኪራ ረገጥኩ።

ዳማሲን አዲስ፣ ንጹሕ፣ ምርጥ ነጭ ቲሸርትና ሰማያዊ ሱሪ ለብሷል። በደስታ በፈካ ፊት ካየኝ በኋላ ፈገግ አለ። ከኋላው እማማ፣ አባባና ቪያኒ እጅ ለእጅ ተያይዘው እኔን ሲያዩ በደስታ ፈክተው ቆመዋል። «ታዲያስ ኢማኪዩሌ፣ አሁንም አንቺን ለማስደሰት መቻላችንን ማየታችን መልካም» አለ መልከ ቀናው ወንድሜ። «ይህን ሁሉ ጊዜ ደብቶሻል፤ ለቅሶሽን መተው አለብሽ። ያለሽበትን ድንቅ ስፍራ እስኪ እዩ ... እንዴት ደስ እንዳለን አታዪም? በሥቃይ ላይ እንዳለን በማመንሽ ከቀጠልሽበት ትተነው ወደሄድነው ህመም እንድንመለስ ታስገድጅናለሽ። ምን ያህል እንደምትናፍቂን አውቃለሁ፣ ቢሆንም ግን ... ተመልሰን መጥተን እንድንሰቃይ ትፈልጊያለሽ?»

«አይሆንም፣ አይሆንም፣ ዳማሲን!» ስል ጮህኩ የደስታ እንባ ከዓይኖቼ እየወረደ። «እዚህ አትምጡ! እዚያው ጠብቁኝ፤ ስመጣ ሁላችሁንም አገኛችኋለሁ። አምላክ በዚህ ሕይወቴ በቃሽ ሲለኝ ወደናንተ እመጣለሁ።»

«እዚሁ እንጠብቅሻለን እህት ዓለም። አሁን ልብሽን ፈውሺ። ማፍቀር አለብሽ፤ በኛ ላይ የተላለፉትንም መማር አለብሽ።»

የቤተሰቤ አባላት ቀስ በቀስ ወደ ሰማይ እያፈገፈጉ መንግሥተ-ሰማያት ውስጥ ተደበቁ። ከዚህ ክስተት በኋላም በቤቴ ላይ እያንጎበጎኩ ቢሆንም ከጨለማው

ደመናና ከምበርበትም ጠያራ ወጥቻለሁ፡፡ በመንደሬ ላይ እንደ ወፍ በረርኩባት፤ በቄሱ ቤትና በፈረንሳዮቹ ምሽግ ላይ፣ በውድ ሀገሬ ሁሉም ወንዞችና ፏፏቴዎች በላይ - በሩዋንዳ ላይ አንጎበብኩባት፡፡

ከሐዘንና ከመሬት ስበት በጣም ነጻ ስለወጣሁ በደስታ መዘመር ጀመርኩ፡፡ ከልቤ ዘመርኩ፤ ቃላቱ በደስታ ከአፌ ጎረፉ፡፡ መዝሙሩ «ምዋሚ ሺሚርዋ» የሚል ሲሆን በኪንያሩዋንዳ «እግዚአብሔር ሆይ ከአእምሮ በላይ ለሆነው ፍቅርህ አመሰግናለሁ» ማለት ነው፡፡

እኩለ ሌሊት ስለሆነ ዝማሬዬ ቤተሰቡን በሙሉ ከእንቅልፉ ቀሰቀሰው፡፡ የሳራ እናት ወይ አመማት ወይ ትኩሳት ያዛት ብለው በመሥጋት ወደ ክፍሌ ሲሮጡ መጡ፡፡

ከዚያን ምሽት በኋላ እንባዬ መድረቅና ሕመሜም መቀነስ ጀመረ፡፡ ስለቤተሰቤ ዕጣፈንታ አስቤ ድጋሚ በፍጹም አልተሰቃየሁም፡፡ ሁሌም አለቅስና እናፍቃቸዋለሁ ብዬ ባምንም አንዲትም ቀን ስላዩት ሥቃይ ስጨነቅ አላሳልፍም፡፡ አምላክ የቤተሰቤ አባላት ሥቃይ ካለበት ስፍራ ርቀው ወዲያ ማዶ እንዳሉ በሕልም አሳየኝ፡፡

ወደ መንደሬ ሌላ ጉዞ ማድረግ እንዳለብኝም አሳይቶኛል፡፡

ከተወሰኑ ሳምንታት በኋላ ኮሎኔል ጉዬ እንደገና ወደ ሀገር ቤት የመሄድ ዕድል ሰጡኝ፣ በዚህ ጊዜ ግን የነዳነው በሀገር አቋራጭ ነው፡፡ የአገሬ መልከዓ-ምድር በዚያን ወቅት አላበሳጨኝም፤ እንዲያውም በዙሪያዬ ባሉት ትዕይንቶችና ድምጾች ሰበብ በሚነሳሱት ትኩስ ትዝታዎቼ ተነቃቅቻለሁ፡፡ በእናቴ የሙዝ ልማትና በተራራ ጥግ በሚገኘው የአባቴ የቡና ማሳ ውስጥ ከጓደኞቼ ጋር ተዘዋውሬያለሁ፡፡ ለአክስቶቼ ዱር መሄድ ካልፈሩ የአትክልቶቹን አላባ እንዲጠቀሙበትና ኑሯቸውን እንዲደጉሙበት ነግሬያቸዋለሁ፡፡

አክስቴ ጉኒ ስለመፍራቱ እንዳላስብ ነገረችኝ፡ ጠመንጃ በቅርቡ ስለምታገኝ አተኳኮስም ትማራለች፡፡ «ለወደፊቱማ ዝግጁ እሆናለሁ» አለች፡፡

ለወደፊቱ በማለት፣ በጣም ተንፍሼ አሰብኩ፡፡

እማማንና ዳማሲንን ለመጠየቅ ወደፈራረሰው ቤታችን አቀናሁ፡፡ በመቃብሮቻቸው አጠገብ ተንበርክኬ ለመጨረሻ ጊዜ ካየኋቸው በኋላ የተከሰተውን ሁሉ ነገርኳቸው፡፡ በተመድ ስላገኘሁት ሥራና ወደፊት ምን ለማድረግ እንዳሰብኩ ነገርኳቸው፡፡ ፊቶቻቸውን ማየትና ድምጾቻቸውን መስማት ስለናፈቅኝ አለቀስኩ፡፡ የዚያን ሰዓቱ እንባዬ ግን የነጻነት እንጂ የሰቆቃ አይደለም፡፡

ከዚያ በኋላ ላደርግ የመጣሁትን ነገር ማድረጊያው ጊዜ ደረሰ።

ከሰዓት በኋላ ዘግየት ብዬ ማረሚያ ቤት ስደርስ አዲሱ የኪቡዬ አስተዳዳሪ ሴማና ተቀበለኝ። ሴማና ከዘር ፍጅቱ በፊት መምህር፣ የአባቴ የሥራ ባልደረባና ጥሩ ጓደኛ ሲሆን፤ እኔ ደግሞ እንደ አጎቴ አየው ነበር። ከስድስት ልጆቹ አራቱ በእርዱ አልቀዋል። ስለሆነም እኔ ልጆቹ ከእግዚአብሔር ጋር እንደሆኑ እምነቱ እንዲኖረው ነገርኩት።

«ዓለም ምን ያህል እንደተቀየረች ማየት ቻልኳ፤ ልጆች ወላጆቻቸውን ያጽናናሉ» በማለት በሆድ ብሶት መለሰልኝ።

እንደ አስተዳዳሪነቱ ሴማና አካባቢያችንን ያሸበሩትን ገዳዮች የማሰሩንና በቁጥጥር ስር የማቆየቱን ሥራ የሚሠራ ትልቅ ዐቅም ያካበተ ፖለቲከኛ ሆኗል። በመቶዎች የሚቆጠሩ ኢንተርሃምዌዎችን ስለመረመረ ከማንም በተሻለ የትኛው ገዳይ ማንን እንደገደለ ያውቃል።

በመሆኑም ለምን ጉዳይ እንደመጣሁ አውቋል። «እናትሽንና ዳማሲንን የገደለውን ቡድን የመራውን ማግኘት ትፈልጊያለሽ?»

«አዎን ጋሼ፣ እፈልጋሁ።»

በጽሕፈት ቤቱ መስኮት ስኪታተል ሴማና ግቢውን አቋርጦ ወደ ወንጀለኞች ማቆያው ክፍል ደርሶ ሲመለስ አየሁት። ሁሉ ነገሩ የቆሻሻና የሚያነክስ ሽማግሌ እየነዳ ተመለሰ። እየቀረቡኝ ሲመጡም ወዲያውኑ ሰውዬውን ስላወቅሁት በድንጋት ወደ ሰማይ ዘለልኩ። ይህ የተሳካለት ሁቱ ነጋዴ አያ ፌሊሲን ነው። በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ስማር ከልጆቹ ጋር እጫወት ነበር። ረጅም፣ መልከ መልካም፣ ሁሌ ውድ ሱፍ ልብሶች የሚለብስና ለንጽሕናው ጥንቁቅ ነበር። ገዳዮቹ ወደ ቄሱ ቤት መጥተው ሲፈልጉኝ ስሜን እየተጣራ ሲፈልገኝ ድምጹን ስለሰማሁት ተንቀጠቀጥኩ። ፌሊሲን ሊገድለኝ ሲያድነኝ ሰንብቷል።

ሴማና ፌሊሲንን ወዳለሁበት ክፍል ሲገፈተረው በጉልበቱ ወደቀ። ከወለሉ ቀና ብሎ የምጠብቀው እኔ መሆኔን ሲያስተውል አመዱ ቡን አለ። ድንገትም እይታውን ወደ ሌላ አቅጣጫ መልሶ መሬቱ ላይ አፈጠጠ።

«ተነሥ፣ አንተ ነፍሰ-በላ!» ሲል ሴማና ጮኸበት። «ቆመህ ለዚህች ልጅ ቤተሰቧ ለምን እንደሞተ ንገራት። እናቷን ለምን እንደገደልክና ወንድሟን ለምን እንዳረድክ አብራራላት። ተነሥ ብያለሁ! ተነሥና ንገራት!» ሴማና የበለጠ ጮክ ብሎ ተናገረ፤

የተጎዳው ሰውዬ ግን ተነሥቶ ዓይኔን ማየቱ በጣም አሸማቆት እንደተንበረከከና እንዳቀረቀረ ቀረ፡፡ ቅስሙ ተሰብሯል፡፡

አዳፋ ልብሱ በመነመነው ሰውነቱ ላይ ተቀዳዷል፡፡ ቆዳው ከመገርጣቱ፣ ከመቆሳሰሉና ከመሸብሸቡም በላይ ዓይኖቹን አንዳች ነገር አድርቶባቸዋል፡፡ ፊቱ በአዳፋና ጎፍላላ ፂም ተሸፍኗል፡፡ ጫማ የናፈቃቸው እግሮቹም ቆሳስለዋል፡፡

ሁኔታውን ሳይ አነባሁ፡፡ ፌሊሲን ዲያብሎስ ልቡ ውስጥ እንዲገባ ፈቅዷል፤ ርኩሰትም ሕይወቱን እንደ ነቀርሳ ሆኖ አበላሽቶበታል፡፡ አሁን በሥቃይና በጸጸት እንዲኖር የተፈረደበት የተጠቂዎቹ ተጠቂ ሆኗል፡፡ ስለዚህ ሰውዬ የተሰማኝ የመራራት ስሜት ጎዳኝ፡፡

«የወላጆችሽን ቤት ዘርፏል፤ የማሳቸውን አላባ ጠቅሎ ወስዷል፣ ኢማኪዩሌ፡፡ የአባትሽን የእርሻ ማሽኖች እቤቱ አግኝተናቸዋል፣ አላገኘንም እንዴ?» ሴማና ፌሊሲን ላይ ጮኸበት፡፡ «ሮዝንና ዳማሲንን ከገደለ በኋላ አንቺን መፈለጉን ቀጥሎ ነበር … ንብረትሽን ለመውሰድ ሲል አንቺ እንድትሞቺለት ፈልጎ ነበር፡፡ አልፈለግህም አንት አሳማ?» ሴማና በድጋሚ አምባረቀበት፡፡

ድንገት ሳላስበው ሴማና ሲያየኝ ጊዜ ወደ ውስጥ በረጅሙ ተንፍሼ ወደ ኋላዬ ሸሸት አልኩ፡፡ ሴማና ባሳየሁት ምላሽ ተደናግጦና በፊቴ ላይ በሚወርደው እንባ ግራ ተጋብቶ አየኝ፡፡ ፌሊሲንን የሸሚዙን ኮሌታ ይዞ በጡጫ መታው፡፡ «ምን የምትላት አለህ? ምን የምትነግራት አለህ ለኢማኪዩሌ?»

ፌሊሲን አለቀሰ፡፡ ሐፍረቱ ተሰማኝ፡፡ ለአፍታ ቀና ብሎ ቢያየኝ ዓይኖቻችን ተገጣጠሙ፡፡ ተንጠራርቼ እጁን ነካሁና ልናገር የመጣሁበትን በፍጥነት ተናገርኩ፡፡

«ምሬሃለሁ» ስለው ልቤን ወዲያውኑ ቀለል አለኝ፡፡ ሴማና ወንጀለኛውን በሩን አሳልፎ ወደ ግቢው ከማስወጣቱ በፊት በፌሊሲን ትከሻ የነበረው ጭንቀት ሲቀል አየሁት፡፡ ከዚያም ሁለት ወታደሮች ፌሊሲንን አንጠልጥለው ወደ ማረፊያ ክፍሉ እየነተቱ ወሰዱት፡፡ ሴማና ሲመለስ እንደተናደደብኝ አየሁ፡፡

«ምን ማለትሽ ነው፣ ኢማኪዩሌ? ይህ እኮ ቤተሰብሽን የጨረሰው ሰውዬ ነው፡፡ ያመጣሁት እኮ በጥያቄ እንድታፋጥጪው … ከፈለግሽ እንድትተፊበት ነበር፡፡ ግን አንቺ ማርሽው! እንዴት እንደዚያ ታደርጊያለሽ? ለምን ማርሽው?»

እውነቱን ነገርኩት፡ «የምሰጠው ነገር ምጎረት ብቻ ነው መሆን ያለበት፡፡ »

ድህረ-ታሪክ

አዲስ ፍቅር፣ አዲስ ሕይወት

አንድ የተሰበረ ልብ ለማገገም ምን ያህል ጊዜ ይወስድበታል ብሎ ለመተንበይ ያዳግታል፤ እኔ ግን ተባርኬያለሁ፡- በእግዚአብሔር እርዳታ ልቤ ከሁለት ዓመት በኋላ ሌላ ለማፍቀር ችሏል፡፡ ስድን ግን የኖርኩት ዝምተኛና አመዛዛኝ ሕይወት ነው ::

በተመድ እየሠራሁና ከሳራ ቤተሰብ ጋር እየኖርኩ በትርፍ ጊዜዬ ኪጋሊ በሚገኝ አንድ የእጓለማውታ ማሳደጊያ በደርዘኖች ለሚቆጠሩ የተሸበሩ ብቸኛ ልጆች በታላቅ እህትነት በማገልገል በበጎ ፈቃደኝነት ሥራ አሳለፍኩ፡፡ በፈረንሳይ ምሽግ እንከባከባቸው የነበሩትን ሁለት ወንድማማቾች ሥራዬ ብዬ ብፈልጋቸውም ላገኛቸው አልቻልኩም፡፡ ይሁን እንጂ ሌሎች ብዙ ፍቅር ፈላጊ ወጣቶችን አግኝቻለሁ፡፡

በ1995 መጨረሻ ከኤይማብል ጋር ተገናኘሁ፡፡ ነጻ የትምህርት ዕድል የሰጠው አካል በሩዋንዳ ሰላም ተመልሷል ብሎ ስላመነ ወደ አገሩ የሚመጣበትን የአየር መጓጓዣ ወጪ ሸፈነለት፡፡ ከመምጣቱ በፊት ብዙ ጊዜ ተጻጽፈናል፡፡ ለተወሰኑ ጊዜያትም በስልክ አውርተናል፡፡ በአካል ለመገናኘት ግን በመንፈስ አልተዘጋጀንም፡፡ በአየር ማረፊያው የተገናኘንበትን ሁኔታ መቼም አልረሳውም፡፡ ልቦቻችንን ከከፉ እየጠበቅን ይመስል ስሜታችን ፈንቅሎ በመውጣት ወይም እንባ በመራጨት ፈንታ አቀባበሉ በስሱ ተከናወነ፡፡ ተቃቀፍን፣ ተሳሳምን፤ እኔ የእርሱን፣ እርሱም የኔን ህመም ላለመንካት ግን ተፈራርተን ጥንቃቄ አደረግን፡፡ ዓይን ለዓይን ለመተያየት ተፈራራን፡፡ እውነተኛ ስሜታችን ከወጣ መቆጣጠር እንደሚያቅተን አውቀን ከበደን፡፡ ማልቀስ ከጀመርን ማቆሚያ እንደሌለን ገብቶናል፡፡

ወንድሜና እኔ ከተወሰኑ ጓደኞቼ ጋር ወደ ምግብ ቤት ሄደን ራት እየበላን ስለ እርሱ ትምህርትና ስለኔ ሥራ እያወራንና በጓደኞቼም ቀልዶች እየሣቅን እናስመስል ያዝን፡፡ በዚያ ሌሊት ግን ብቻዬን መኝታዬ ላይ ሆኜ እንባዬን ዘረገፍኩት፡፡ ወንድሜም እንዲሁ እንዳደረገ እርግጠኛ ነኝ፡፡

በቀጣዩ ቀን አብሮ መሆኑ ይበልጥ ቀለለን፡፡ ምንም እንኳን እርስ በርስ መተያየቱ የቤተሰባችንን አሳዛኝ ፍጻሜ አሰቃቂ ትውስታ የሚቀሰቅስብን ቢሆንም በጣም ስለምንዋደድ አንዳችን በሌላችን መኖር ምቾት ተሰምቶናል፡፡ ህመሙን ለመቋቋም የሚያግዘኝን ጥንካሬ እንዳገኘሁ ልነግረውና ላጽናናውም ፈልጌያለሁ፡፡ ይሁን እንጂ የማያጽናኑት ዓይነት እንዳልሆነ ወዲያውኑ ታወቀኝ፡፡ ከአፍታ በኋላም በቤተሰባችን ስለተከሰተው ሰቆቃ ላለማንሳት ሳንነጋገር እንደተስማማን ገባን፡፡ የቤተሰባችንን አባላት ሁሉ በስም ጠቃቀስን፡፡ ያኔም ቢሆን አሁንም በሕይወት እንዳሉ አድርገን

ነበር ያወራነው - የምንቋቋምበት ብቸኛው መንገዳችን ይህ ነው፡፡ ለቀጣዮቹም ሁለት ዓመታት በደብዳቤና በስልክ እንደዚያው ስናደርግ ቆየን፡፡ ኤይማብል የእንስሳት ሕክምና የድህረ ምረቃ መርሃ-ግብሩን ጨርሶ ወደ ኪጋሊ ሲመለስም ሁኔታው አልተቀየረም፡፡ በየቀኑ በአካል ብንገናኝም ስለ ዘር ጭፍጨፋው የምናወራው አንድ የሆነ ሰው ላይ የተከሰተ ይመስል እንዲያው በደምሳሳው ነው፡፡ የእማማንና የዳማሲንን መቃብርም ሲያይ እንኳን እንዳካሂደው አልጠየቀኝም፤ ብቻውን ሄደ፡፡

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ያው እንዲሁ አለን፡፡ ኤይማብል አሁንም የሚኖረው ኪጋሊ ነው፤ ስኬታማ ሐኪም ሲሆን ቆንጅዬ ሚስትና ልጆች አሉት፡፡ እርስ በርሳችን በጣም እንዋደዳለን፤ ከመቼውም በላይ ቅርርብ አለን፡፡ በየጊዜው እንደዋወላለን፤ ቢያንስ በሳምንት አንድ ጊዜም እንጻጻፋለን፡፡ አሁንም ቢሆን ከእነዚህ ሁሉ ዓመታት በኋላም ስለቤተሰባችን ስንነጋገር ‹ነበር› አንልም፡፡ ትዝታቸውን ህያው አድርጎ ማቆያ መንገዳችን ይህ ነው ብዬ እገምታለሁ፡፡

ብዙ ምሽቶቼን በአቅራቢያዬ ባለና ሁለተኛ ቤቴ ሆኖ በነበረው በጀስዊቶች ማእከል በጸሎትና ተመስጦ ተጠምጀ አሳልፋሁ፡፡ በተደበቅሁባቸው ረጅም ወራት ወቅት ያዳነኝን ከእግዚአብሔር ጋር የነበረኝን የጠበቀ ቁርኝቴን በድጋሚ የጀመርኩት በነዚያ ርጭ ባሉ ስፍራዎች ነው፡፡

ልቤ ቀስ በቀስ ሲያገግምልኝ የወደፊቱን ሕይወቴን አብሬ የሚጋራ አንድ ልዩ የራሴ የምለው ሰውና የምንከባከበው ቤተሰብ ማለም ጀመርኩ፡፡ ግን ሐሳብ ገባኝ … ከዮሃንስ ጋር የነበረኝን ሁኔታ አስታወስኩና በቀላሉ ሊሰበር የሚችለውን ልቤን የትም ለማይደርስና በሚያሳምም መልኩ ለሚቋጭ ግንኙነት ላለመስጠት ወሰንኩ፡፡ ስለዚህ ችግር ወይም ፈተና በሚያጋጥመኝ ጊዜ ሁሉ እንደማደርገው የአምላክን እገዛ ጠየቅሁ፡፡ በገነት የሚሆን ጋብቻ ከፈለግሁ ከአምላኬ በተሻለ የሚኩለኝና የሚድረኝ ከቶ ማን ይኖራል?

መጽሐፍ ቅዱስ ከጠየቅን እንደምናገኝ ይነግረናል፤ በእርግጥም ያንን አደረግሁ፡፡ እግዚአብሔርን የማልመውን ሰው እንዲያመጣልኝ ጠየቅሁት፡፡ ራሴን ማጭበርበር አልፈልግሁም - እግዚአብሔር እንዲልክልኝ የምፈልገው ሰው ምን ዓይነት እንደሆነ በጣም ግልጽ ማድረግ ነበረብኝ፡፡ ስለሆነም ወረቀት ይዤ ተቀመጥኩና ላገባው የምፈልገውን ሰው ፊት ነደፍኩ፡፡ ከዚያም ቁመቱንና ሌሎቹን ገጽታዎቹን ዘረዘርኩ፡፡ ጠንካራ ማንነትና ምቹ ስብዕና ያለው፣ ደግ፣ አፍቃሪና ርህሩህ፣ ተጨዋች፣ ምግባረ-መልካም፣ ማንነቴን የሚወድልኝ፣ እንደኔ ልጆችን የሚያፈቅርና ከሁሉም በላይ እግዚአብሔርን የሚወድ ሰው ይሰጠኝ ዘንድ ጠየቅሁ፡፡

ለእግዚአብሔር ቀን አልቆረጥኩለትም፡፡ በዘር፣ በዜግነት ወይንም የቆዳ ቀለም ላይም ምንም ገደብ አልጣልኩ፡፡ በዓለም ላይ ከአምስት ቢሊየን በላይ ሰዎች እንደመኖራቸው - ጌታዬ የሕይወቴን ኣጋር የሚልከበትና እኔም የምጠብቅበት አግባብ ያለው የቆይታ ጊዜ ስድስት ወራት እንዲሆን አቀድኩ፡፡ አንድ ማስጠንቀቂያንም ጨመርኩ፡- ድንግል ማርያምን እጅግ ስለምወዳት እግዚአብሔር ከእምነቴ ተመሳሳይ የሆነ ባል ቢልክልኝ እንደሚሻል ነገርኩት፡፡ በሃይማኖት ሳቢያ በትዳሬ ምንም ዓይነት ውጥረት እንደማይኖር ማረጋገጥ እንዲሁም ባሌ እግዚአብሔርን እኔ በማመልከው መልኩ እንዲያመልክ ፈለግሁ፡፡

ምን እንደምፈልግ በትክክል ካወቅሁ በኋላ ፍላጎቴን አልመው ጀመር፡፡ ጌታ የተመኘሁትን ባርኮ እንደሚሰጠኝ፣ የልቤ መሻት እንደሚሆንልኝና የጊዜ ጉዳይ ብቻ እንደሆነ አምኜ ሁሉንም ለእርሱ ተውኩት፡፡ ሂደቱን ለማፋጠን የአባቴን ቀይና ነጭ መቁጠሪያ አወጣሁና ባሌ እንዲመጣልኝ መጸለይ ጀመርኩ፡፡ ከሦስት ወራት በኋላም መጣልኝ፡- ከእግዚአብሔር የተላከውና የተመድ የሸለመኝ አቶ ብርያን ብላክ ከአሜሪካ ድረስ ከተፍ አለ! የነገሩ መገጣጠም ደሞ ብርያን ወደ ሀገሪቱ የመጣው የዘር ማጥፋቱን በማቀድ የተሳተፉትን ለፍርድ ለማቅረብ የሚጥረውን የተመዱን ዓለም አቀፍ የሩዋንዳ ፍርድ ቤት በማቋቋሙ ሂደት ለማገዝ ሆኖ እርፍ፡፡ ብርያን ለተመድ ለብዙ ዓመታት ስለሠራ ገዳዮቹን ፍትሃዊ ቅጣት እንዲያገኙ የሚያደርገው የተልዕኮው አካል በመሆኑ ይደሰታል፡፡ በግሌ እርሱ ከእግዚአብሔር የተሰጠውን ተልዕኮ በማስፈጸም ላይ ነው፡፡

ብርያንን ለመጀመሪያ ጊዜ በተመድ ግቢ ሳየው በትክክል እግዚአብሔር እንዲልክልኝ የጠየቅሁትን ሰውዬ መሰለኝ፡፡ በኋላ በአዳራሹ ሳልፈውና በዓይኖቹ የነበረውን ጥልቅ እርጋታ ሳይ እርሱ እንደሆነ እርግጠኛ ሆንኩ፡፡ ግን በእግዚአብሔር እምነቴን ስላደረግሁ ብርያንን ወደኔ እንዲያመጣው ጠበቅሁት ... አመጣልኛ፡፡

ብርያን አብረን እንድንዝናና ጋብዞኝ ግሩም ጊዜ አሳለፍን፡፡ በምሽቱ መጨረሻም ሁኔኛ ጥንዶች እንደሆንንና የተቀረውን ሕይወቴን አብሬው የማሳልፍ እንደሆነ እርግጠኛ ሆንኩ... ክርስቲያን ቢሆንልኝ! ራሴን አረጋግቼ ትልቁን ጥያቄ ጠየቅሁት፡ «ሃይማኖትህ ምንድነው?»

«ክርስቲያን ነኝ፡፡»

ዘልዬ እቅፉ ውስጥ ገብቼ «አምላኬ ምስጋና ይግባህ! ወደ ሕይወቴ እንኳን በደኅና መጣህ - አብረን ኖርናታ!» ማለት አሰኘኝ፡፡ ግን ያንን ምስኪን ሰው እንዳላስደነብረው ፈራሁ፡፡ ስለዚህ እንዲያውም እጁን ይዤ፣ ፈገግ አልኩና «እኔም ነኝ» አልኩት፡፡

ብርያንን በዘር ጭፍጨፋው ወቅት ያለፍኩበትን ነገር ሁሉ በመንገር በፍጹም ባላጨናንቀውም ልቤ በተከፋ ቁጥር ያዳምጠኛል። ሲያስፈልገኝም ትከሻው ላይ ደገፍ ብዬ እንዳለቅስ ይፈቅድልኛል።

ከሁለት ዓመታት በኋላ ብርያንና እኔ በባሕላዊ የሩዋንዳ የሰርግ ሥነ ሥርዓት ተጋብተን ከተወሰነ ጊዜም በኋላ፣ በ1998፣ ወደ አሜሪካ መጣን። በፍቅር የተሞላና መተጋገዝ ያለበት ትዳር አለን፤ እግዚአብሔር ሁለት ቆንጆ ልጆችንም ሰጥቶናል - ሴቷ ልጃችንን ኒኬይሻንና ወንዱን ብርያን ትንሹን። በየቀኑ ከእንቅልፌ ነቅቼ ሁለቱን ትናንሽ መላዕከቴን ሳይ የአምላክን ውበትና ዐቅም በፊታቸው አነባለሁ። ስለ ውድ ስጦታዎቹ ሁሉ እርሱን ማመስገኔን መቼም አላቆምም።

በማናቸውም ቀንና መንገድ እግዚአብሔር የሕይወቴ አጋር ሆኖ ይቀጥላል፤ የሚያኖረኝ፣ የሚጠብቀኝ፣ የሚያረካኝ እርሱ ነው። የተሻለች ሚስት፣ እናት ብሎም ሰው ያደርገኛል። ሥራ እንዳገኝ አድርጎኛል። ልጆቼን ከወለድኩ በኋላ የሥራ ሕይወቴን መቀጠል ብፈልግም ኒው ዮርክ ከተማ ላይ ሥራ ማግኘት ኪጋሊ ላይ ከዘር ፍጅቱ በኋላ ከነበረው በላይ ፈታኝ ነው - ብዙ ሰዎች፣ ግን በጣም ጥቂት ሥራ።

እግዚአብሔር እንዲመራን ጸለይኩ፤ በማንሃታን፣ በተመድ ውስጥ የምሻውን ሥራም ፈለግሁ። አንዴ የት መሥራት እንደምፈልግ ካወቅሁ በኋላ እዚያ ሥራ እንዳለኝ አድርጌ አለምኩ - ሁሌ የምጠቀመውን በጎ አሳቢነት መሳሪያ በማድረግ፡- እመኑ ታገኛላችሁ! ወደ ተመድ ድረ-ገጽ ገብቼ የሠራተኞቹን ስምና ማዕረግ የሚዘረዝረውን ክፍል አትሜ አወጣሁና ስሜን በዝርዝሩ ውስጥ ጨመርኩት። ለራሴ የውስጥ ስልክ መሥመር ሳይቀር ሰጠሁ! የስልክ መዘርዝሩን ግድግዳዬ ላይ ለጥፌ በየቀኑ አየዋለሁ። ማመልከቻ በእርግጥ ሞልቻለሁ፣ የትምህርትና የሥራ ልምድ ማስረጃ ሰነዶችን አስገብቻለሁ፣ በስልክም እየደወልኩ ከምን ደረሰልኝ እላለሁ - በሺዎች የሚቆጠሩ ሌሎችም ሰዎች ግን ይህንኑ ያደርጋሉ። መዘርዝሬን ማየቴንና ሥራው የኔ መሆኑን ማመኔን በመቀጠል በየቀኑ ስልኬ እስኪጮህ እጸልያለሁ። እንደጠበኩትም ከመቶዎች ሌሎች አመልካቾች ተመርጬ ቃለ መጠይቅ ከተደረገልኝ በኋላ ሥራውን በጀ አስገባሁ። የእግዚአብሔርን ኃይል በተግባር በማየቴ መገረሜን በፍጹም አላቆምኩም!

ይህ ወደ ሕይወቴ ቀጣይ ምዕራፍ ለመሸጋገር ወደፊት የሚገፋፋኝ ተመሳሳይ ኃይል ነው። አምላክ ሕይወቴን ያዳናትና ነፍሴን ያተረፋት ለምክንያት ነው። ከሞት ያስቀረኝ ታሪኬን ለሌሎች አንድነግርና በተቻለኝ መጠን ለብዙ ሰዎች የፍቅሩንና የምህረቱን የማዳን ኃይል እንዳሳይ ነው።

ትቻቸው የመጣኋቸውና ልረዳቸው የሚገባኝ ሰዎች አሉኝ፡፡ በዘር ፍጅቱ ተራፊዎች በተለይ በአጓለማውታ ልብ ውስጥ ተስፋን መልሶ በማምጣቱ ሂደት ለማገዝ በቻልኩት መጠን ቶሎ ቶሎ ወደ ሩዋንዳ እየተመላለስኩ ለመሥራት ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ በአሁኑ ወቅት በማናቸውም ስፍራ ያሉ የዘር ፍጅትና የጦርነት ሰለባዎችን በአካል፣ በአእምሮና በመንፈስ እንዲድኑ የሚያግዝ ድርጅት በማቋቋም ላይ እገኛለሁ፡፡

የእግዚአብሔር መልዕክት ድንበር ሳይገድበው የትም ቦታና ከማንም ልብ ውስጥ ይደርሳል፡፡ ማንም በዓለም ላይ ያለ ግለሰብ የነዳውን ማንንም ሰው እንዴት እንደሚምር መማር ይችላል - ጉዳቱ አነሰም በዛ፡፡ የዚህን እውነትነት በየቀኑ አየዋለሁ፡፡ ምሳሌ ለመጥቀስም ያህል ታሪኬን ያጋራኋት አንዲት አዲስ ጓደኛዬ ከተወሰኑ ቀናት በኋላ የኔ ታሪክ አንድ ወቅት በጣም ትቀርበው ከነበረና ለዓመታት ካኮረፈችው አጎቷ እንድትታረቅ እንዳነሳሳት ደውላ ነገረችኝ፡፡

«በጣም በመጨቃጨቃችን ስለበገንኩ ከእርሱ ጋር ሁለተኛ አልነጋገርም ብዬ ምዬ ነበር» ስትል ምስጢሯን አጋራችኝ፡፡ «ቤተሰብሽን የገደሉትን ሰዎች እንዴት መማር እንደተቻለሽ ከሰማሁ በኋላ ግን ስልኩን አንስቼ ልደውልለት ግድ አለኝ፡፡ ይቅርታ አልጠየቅሁትም - በቀጥታ ልቤን ከፍቼ ማርኩት እንጂ፡፡ ወዲያውኑ በፊት እናወራበት በነበረው መንገድ እናወራ ጀመር - በልዩ በፍቅር፡፡ በኩርፊያ ብዙ ዓመታት እንዳመለጡን ማመን አቃተን» አለችኝ፡፡

በተመሳሳይ አንድ ከዘር ፍጅቱ የተረፈችና በቅርቡ ወላጆቿ ሩዋንዳ ላይ የተገደሉባት ሰው በስልክ አራጆቹን ለመማር ያደረግኋቸውን ነገሮች ቅደም ተከተል እያለቀሰች ጠየቀችኝ፡፡

«እነርሱን ስትምሪ በልቤ አብዳለች አልኩሽ፣ ኢማኪዩሌ - የእጃቸውን ከማግኘት ስታድኛቸው፡፡ ለ11 ዓመት በልቤ የያዝኩት ሕመምና ምሬት ሊገድለኝ ነው፡፡ ለረጅም ጊዜ ሕይወቴ አሰቃቂ ስለነበር ከአሁን በኋላ የምኖርበት ምንም ዐቅም የለኝም፡፡ ሰዎች ግን አንቺ የቤተሰብሽን ገዳዮች ምረሽ ሕይወትሽን እንደቀጠልሽ ሲያወሩ ስሰማ ቆይቻለሁ ... ደስተኛ እንደሆንሽና ባል፣ ልጆችና ሥራም እንዳለሽ! እኔም ጥላቻዬን ለመተው እንዴት እንደምችል መማር ያስፈልገኛል፡፡ እንደገና መኖር መጀመር አለብኝ፡፡ »

በአምላክ እንዴት እንደምታመን ነገርኳት፤ ምኅረት ለማድረግና ወደ ፊት ለመራመድም ያደረግሁትን ሁሉ ተረኩላት ... በዚህ መጽሐፍ ያሰፈርኩትን ነገር ሁሉ፡፡ አመስግናኝ እርሷም ገዳዮቹን እንድትምር እግዚአብሔርን እንዲያግዛት መጠየቋን ነገረችኝ፡፡

ከዚያም በአትላንታ ካቀረብኩት ንግግር በኋላ እያለቀሰች የቀረበችኝን ሴትዮ አስታውሳለሁ፡፡ በሕጻንነቷ ወላጆቿ በናዚ ጭፍጨፋ እንደተገደሉባት ነገረችኝ፡ «ዕድሜዬን ሙሉ ልቤ በንዴት ተሞልቶ ኖሯል… ሥቃይ ሲሸነቁጠኝ ኖሬያለሁ፤ ስለ ወላጆቼ ለብዙ ዓመታት አልቅሻለሁ፡፡ ያሳለፍሽውን የስቃይ ታሪክና ምኅረት ማድረግ መቻልሽን መስማቴ አነሳሳኝ፡፡ ዕድሜዬን ሙሉ ወላጆቼን የገደሉትን ሰዎች ለመማር ስጥር ኖሬያለሁ፤ አሁን ግን የማደርገው ይመስለኛል፡፡ ንዴቴን ትቼ ደስተኛ ሳልሆን አልቀርም፡፡»

በትምህርታዊ ጉባዔው ላይ የ92 ዓመት ሴት አዛውንት እጃቸውን ጠመጠሙብኝና አጥብቀው አቀፉኝ፡፡ በጣም ስሜታዊ ስለሆኑም መናገር አዳግቷቸዋል፤ ቢሆንም እንደ ምንም ድምፅ ለማውጣት ተችሏቸዋል፡፡ ቃላቸውን አልረሳውም፡- «ምኅረት ለማድረግ እጅግ ዘገየሁ ብዬ ነበር፡፡ እንዲያው አንድ ሰው አንቺ ያልሽውን ሲል ለመስማት ስጠብቅ - የማይማረውን መማር እንደሚቻል ማወቅ አስፈልጎኝ ነበር፣ ልጄ» አሉኝ፡፡

የትውልድ ሐገሬን ሩዋንዳን በተመለከተ እያንዳንዱ ሰው የምኅረትን ትምህርት ለመቅሰም ከቻለ ሀገሬ ራሷን ማዳን እንደሚቻላት አውቃለሁ፡፡ በዘር ማጽዳቱ ወቅት የግድያ ወንጀል በመፈጸማቸው የታሰሩት በአሥር ሺህዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ከእስር እየተፈቱ ወደ ቀድሞ ከተሞቻቸውና መንደሮቻቸው እየገቡ ነው፡፡ ስለሆነም ከመቼውም ጊዜ በላይ ምኅረት የማድረጊያው ጊዜ አሁን ነው፡፡ ሩዋንዳ መልሳ ገነት መሆን ትችላለች፤ ሆኖም እናት ሀገሬ እንድትድን መላው ዓለም ፍቅሩን ሊሰጣት ይገባል፡፡ መቼም ያለፈው አልፏል፤ በሩዋንዳ የተከሰተው ግን በሁላችንም በሰው ልጆች ላይ የተፈጸመ በመሆኑ መላው የሰው ዘር በዘር ማጥፋቱ ቆስሏል፡፡

ከአንዲት ልብ የሚመነጭ ፍቅር የልዩነት ዓለምን መፍጠር ይቻለዋል፡፡ በአንድ ጊዜ አንዲትን ነፍስ በማዳን ሩዋንዳን ብሎም ዓለማችንን ማዳን እንደምንችል አምናለሁ፡፡

ምስጋና

በመጀመሪያ ከሁሉ በላይ እግዚአብሔርን ድንቅ አባት፣ ሁነኛ ጓደኛ፣ እውነተኛው ምስጢረኛ ... ብሎም አዳኜ ስለሆነልኝ ማመስገን ግድ ይለኛል። ጌታ ሆይ፣ በደስቹም ሆነ በእጅግ መጥፎዎቹ ጊዜያት ቋሚ ባንጀራዬ እንደሆንክ አለህ። ልቦናዬን ስለከፈትክልኝና እንደገና እንዳፈቅር ስላስቻልከኝ ክበር ተመስገን። ያላንተ ምንም አይደለሁም፤ ካንተ ጋር ግን ሁሉንም ነገር ነኝ። ጌታዬ፣ ላንተ እጄን እሰጣለሁ - በሕይወቴ ሙሉ ፈቃድህ ይፈጸምልኝ። ባንተ ዱካ መራመዴን እቀጥልበታለሁ።

ለተባረከሽው ቅድስት ድንግል ማርያም፣ ሁሌ አለሁ ለምትዪኝ - ዘወትር ካጠገቤ እንዳለሽ ይታወቀኛል። ስለ ፍቅርና እንከብካቤሽ ያለኝን ምስጋና ግዝፈት ቃላት አይገልጹትም። ልቤን ለልብሽ አቅርቢልኝ፣ እናቴ - ሙሉ ታደርጊኛለሽ፤ እስከ ዘላለሙ እወድሻለሁ። በኪቦሆ ተገልጠሽ ከፊታችን እየመጣ ስለነበረው አደጋ ስላስጠነቀቅሽን አመሰግንሻለሁ ... ምነው ሰምተንሽ ቢሆን ኖሮ!

ዶክተር ዌይን ዳየር - ከገነት የተላኩ መልአክ ነዎት። እግዚአብሔር እርስዎን ወደኔ ሕይወት ስላመጣዎት አመሰግነዋለሁ፣ መንፈሶቻችንም እርስ በርሳቸው ለዘላለሙ እንደተዋወቁ ይሰማኛል! ወደር-የለሹ ደግነትዎ፣ በዕውቀት የተገነባው ምክርዎና አባታዊ ፍቅርዎ ለእኔ እንደ አጽናፍ ዓለም ሰፊ ነው። እጅግ በርካታ ሰዎች ለምን በእርስዎ ቃል እንደተነሣሱ መገንዘብ ቀላል ነው - እርስዎ የኔ ጀግና ነዎ፣ እወድዎማለሁ። ስለተማመኑብኝና ወደ ሕልሜ ስለመሩኝ፣ እውነተኛውን የነፍሴን ጥሪም እንዳውቅ ስላደረጉኝ ከልቤ አመሰግናለሁ። በተጨማሪም ይህንን መጽሐፍ እውን ስላደረጉልኝና ታሪኬን እንድናገር ስላደረጉኝ ገለታ ይግባዎት።

ስካይ ዳየር፡- ከአባትሽ ጋር ስላስተዋወቅሽኝ እንዴት እንደማመሰግንሽ! እወድሻለሁ!

ለሄይ ሃውስ ድንቅ ቡድን፡- ጂል ክራመር፣ ሻነን ሊትረል፣ ናንሲ ሌቪን፣ ክሪስቲ ሳሊናስ፣ ጃክዊ ክላርክ፣ ስቴሲ ስሚዝና ጃኒ ሊበራቲ - አብረዋችሁ ሲሰሩ ማስደሰታችሁ! ስለ መንገድ ጠቋሚነታችሁ፣ ትዕግሥትና ማበረታቻችሁ ገለታ ይግባችሁ።

ተባባሪዬ፣ ስቲቭ ኤርዊን፣ በዚህ መጽሐፍ ዝግጅት አብረሽኝ ከሠራህ በኋላ ማንም ሰው አንተ የምታውቀኝን ያህል ያውቀኛል ብዬ አላስብም። አንተ አስገራሚ ሰው ነህ፤ አሁን ለኔ እንደ ወንድም ማለት ነህ። እንደዚህ ያለህ ጥሩ ሐኪም ስለሆንክልኝ አመሰግንሃለሁ - ስለቤተሰቤ በርካታ ግላዊ ነገሮችን ስትጠይቀኝ ያሳየኸው ሆደ-ቡቡነት ለኔ ብዙ ቁምነገር አለው። ስለ ተዓምራዊ ኢጆችህ አምላክን አመሰግናለሁ - ጽሑፍህ ቃላቴንና ስሜቴን ነፍስ ዘርቶባቸዋል። በተጨማሪ

ሁለታችንም እናቶቻችንን ገና ሳንጠግባቸው የማጣትን ሕመም ስለምንጋራ በዚህ መጽሐፍ የገለጽኳቸውን ሁሉንም ስሜቶች ለምትረዳው ለባለቤትህ ለናታሻም ምስጋናዬ ይድረስ፡፡ ናታሻ፣ አንቺ እኮ ለኔ እንደ እህቴ ነሽ!

ቪንሴንት ካዬዡካና ኤስፔራንስ ፉንዲራ፡- ከመጀመሪያው እንዴት እንዳበረታታችሁኝና እንደተማመናችሁብኝ በጭራሽ አልረሳውም፡፡ እወዳችኋለሁ! ለዋሪያራ ምቡጋ፣ ሮበርት ማክማሆን፣ ሊላ ራሞስ፣ አና ኬሌት፣ ቢል በርክሌይና ርብቃ ማርቴንሰን ለእገዛቸው፣ ለለገሳችሁኝ ሐሳብ፣ ለምክራችሁና አስፈላጊ ማበረታቻችሁ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

በተመድ የልማት መርሃ-ግብርና በግምገማ ጽሕፈት ቤት ላላችሁ የሥራ ባልደረቦቼ ምስጋናዬ ይድረስልኝ - በተለየ ሁኔታ የማመሰግነው ዴቪድ ራይደር ስሚዝን፣ ሩት አብርሃምን፣ አኒሽ ፕራድሃንን በመረዳታችሁና በእገዛችሁ ሰበብ ነው፡፡ እሱ ፈጣሪ ይባርካችኋ - እወዳችኋለሁ፡፡

ስማችሁን ያላነሳኋችሁ ግን በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ ያገዛችሁኝ በርካታ ውድ ጓደኞቼ፡- አመሰግናችኋለሁ - ሁላችሁም በልቤ አላችሁ፡፡

ተጨማሪ በጣም ልዩ ምስጋና ለሁለት እጅግ ልዩ ቄሶች፣ ለአባ ጋንዛ ዢን ባፕቲስትና ለንስሐ አባቴ ለአባ ዢን ባፕቲስት ቡጊንጎ፡፡

እጅግ ብዙ የፍቅርና የሰቆቃ ትውስታዎችንና ብዙ የማይነገር ሰቆቃ ለምጋራህ ለወንድሜ ለኤይማብል ንቱካንያግዌ፡- *ሁቱትሲ ውሰጥ ልትጠይቃቸው ላልቻልካቸውና እኔም መልሰ ልሰጥህ ላልቻልኳቸው ብዙ ጥያቄዎች ምላሽ ታገናኘለህ ብዬ እመኛለሁ፡፡ አንተ በሕይወት ስላለህልኝ አምላክን አመሰግነዋለሁ - አንተ ለኔ ሁሉ ነገር ነህ፡፡ ሰለ ሰዎቻችን አትጨነቅ ... ደስተኞችና በገነት የኛ ልዩ ጠበቆች ናቸው!* ወንድም ጋሼ፣ ግሩም ወንድም ስለሆንክልኝ ምስጋና ይግባህ - ከማስታውሰው ጊዜ ጀምሮ ላሳየኸኝ የማያሰልስ ፍቅር፣ በኔ ላይ ስላለህ እምነትና ሁልጊዜ የቤተሰባችንን ታሪክ እንድጽፈው ስላበረታታኸኝ አመሰግንሃለሁ፡፡ ባያሌው የማመሰግናት ደግሞ ሳውዳ ነች፡፡ ምራቴና ጓደኛዬ ብዬ ስጠራሽ ተባርኬያለሁ - ዘራችንን ስላበዛሽው ምስጋና ይግባሽ፡፡ እንደ ዘር ጭፍጨፋ ተራፊ የታሪክ ተጋሪነትሽ ይህ መጽሐፍ ላንቺ ልዩ ትርጉም ይኖረዋል፡፡ በእጅጉ እፈቅርሻለሁ፡፡

ሾንታል ንዬራሩኩንዶ፣ ኮንሶሊ ንሺምዌና ስቴላ ኡሙቶኒ፡ ትናንሽ እህቶቼ ናችሁ! በዚህ መጽሐፍ ስለተነሣሳችሁ አመሰግናችኋለሁ - ትልቅ መነሳሳትን አምጥታችሁልኛል፡፡ ለእናንተም መሆኑን እወቁልኝ፤ ስለመዳናችሁ፡፡

ቆንጆዎቹ ልጆቼ ንኪይሻና ብርያን ትንሹ፣ ትንሹ የወንድሜ ልጅ ርያን፡- ውዶቼ፣ እንደ አበቦች ሁሉ ከፈጣሪ ዘንድ የመጣችሁ ትናንሽ መላዕክቴ ናችሁ፡፡ ለፍቅራችሁ

ንጽሕናና እንደገና እንድኖር ምክንያት ስለሆናችሁኝ አመሰግናችኋለሁ፡፡ ንጹሃን ነፍሶቻችሁ በጥላቻ በማይጎዱባት ዓለም ብንኖርና የዘር ፍጅትና ጭፍጨፋ የሚሉትን ቃላትም ባትሰሚቸው ምኞቴ ነበር፡፡ ስታድጉ አያቶቻችሁንና አጎቶቻችሁን ሁቱትሲ ገጾች ውስጥ ታገኟቸዋላችሁ - ትውስታዋቻቸው በመጽሐፌ ይኖራሉ፡፡ ለአሁኑ ግን ውድ እጆቻችሁን እኔን ለማቀፍ በኔ ዙሪያ በዘረጋችሁ ቁጥር ፍቅራቸውን አስተላልፍላችኋለሁ፡፡ ሕይወቴ ናችሁ፤ እወዳችኋለሁ፡፡

በመጨረሻም፣ በእርግጠኛነት ግን መጨረሻ ላይ ያደረኩህ ከሌሎቹ አሳንሼህ አይደለም፣ ድንቁ ባሌ፣ ብርያን፣ አመሰግንሃለሁ፡፡ ከብቸኝነት አድነኸኛል፤ በእውነት ግማሽ አካሌ ነህ - ከአምላክ እኔን እንድታሟላ የተላክህ ግማሽ ገላዬ፡፡ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳትል ስለጣርክና ታሪኬን እንድነግር ስለረዳኸኝ፤ በአያሌው ስላበረታታኸኝ፣ አምሽተህ ስለምታነብልኝና ስለምታርምልኝ አመሰግኛለሁ፡፡ ለማይነጥፍ ፍቅርህና ከለላነትህ ገለታ ይግባህ፤ እግዚአብሔርን እንደ ወዳጃችን በመቀበልህም ጭምር፡፡ የኔ ፍቅር፣ በሙሉ ልቤና ነፍሴ እወድሃለሁ፡፡

- **ኢማኪዩሌ**

ኢማኪዩሌ፣ ይህን ድንቅ ታሪክሽን ለዓለም እንድትናገሪ አግዝሽ ዘንድ ስለፈቀድሽልኝ አመሰግንሻለሁ፡፡ ብርታትሽ፣ እምነትሽ፣ ከአዲጋ የማገገም ዐቅምሽና እይታሽ ያነሳሱኛል፤ ያበረታቱኝማል፡፡ ካንቺ ጋር መሥራት ለእኔ መታደል ሲሆን አንቺንም ወዳጇ ልልሽ በመቻሌ ተባርኬያለሁ፡፡

የሄይ ሃውሷ ለጂል ክራመር ለተሰጠኝ ለዚህ ዕድል - ለሙያ አክባሪነትሽ፣ ለጸባይሽና በብርሃን ፍጥነት ለምትልኪያቸው መልዕክቶችሽ አመሰግንሻለሁ፡፡

የሄይ ሃውሷ ሻኖን ሊትረል ለግሩም ምክሮችሽና አስተያየትሽ አመሰግንሻለሁ፡፡

የፋይናል አይዝ ኮሚዩኒኬሽንሱ ፌይዝ ፋርዚንግ ለጥልቅ ምክርህና ለዝርዝር ጉዳዮች ስላለህ ሁሌ ልክ ይሁን የሚል ትኩረት ልዩ ምስጋናዬ ይድረስህ፡፡

ከሁሉም በላይ ደግሞ ባለቤቴ፣ ሕይወቴና ሁሉ ነገሬ ናታሻ ስታይኖፍ አመሰግንሻለሁ፡፡ ያላንቺ ምን ይውጠኝ እንደነበር የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡

- **ስቲቭ ኤርዊን**

የደራስያኑ ማንነት

ኢማኪዩሌ ኢሊባጊዛ

ኢማኪዩሌ ኢሊባጊዛ በሩዋንዳ ተወልዳ በብሔራዊ ዩኒቨርሲቲ ኤሌክትሮኒክና ሜካኒካል ምህንድስና አጥንታለች፡፡ በ1994 በተፈጸመው ጭፍጨፋ አብዛኛዎቹን የቤተሰቧን አባላት አጥታለች፡፡ ከአራት ዓመታት በኋላም ከሩዋንዳ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ተሰዳ በኒው ዮርክ ለተባበሩት መንግሥታት መሥራት ጀመረች፡፡ ሌሎች ከዘር ማጥፋትና ከጦርነት የረጅም ጊዜ ተጽዕኖዎች ይድኑ ዘንድ ለመርዳት የኢሊባጊዛ ፋውንዴሽንን በማቋቋም ላይ ትገኛለች፡፡ ኢማኪዩሌ በሎንግ ደሴት ከባለቤቷ ከብርያን ብላክና ከልጆቿ ከኒኬይሻና ብርያን ትንሹ ጋር ትኖራለች፡፡

ስቲቭ ኤርዊን

ስቲቭ ኤርዊን ጸሐፊና በሕትመትና በብሮድካስት መገናኛ-ብዙሃን የሚሠራ ተሸላሚ ጋዜጠኛ ነው፡፡ በቅርቡ የካናዳ ብሮድካስቲግ ኮርፖርሽን የውጪ ሀገር ዘጋቢ ነበር፡፡ በማንሃታን ከባለቤቱ ከጋዜጠኛ ናታሻ ስቶይኖፍ ጋር እየኖረ ሁለተኛውን ረጅም ልብወለዱን በመጻፍ ላይ ነው፡፡

ለመጽሐፉ የተቸሩ የአድናቆት አስተያየቶች

«በኢ ማኪዩሌ ኢሊባጊዛ የሽብር፣ የጽናት፣ የድኅነትና የይቅር ባይነት ታሪክ ላይ በሚያንጸባርቀው እጅግም ያልተለመደ መንፈሳዊነት ምክንያት ራሴን ዝቅ አደርጋለሁ:: እንደ ሩዋንዳዊትነቴ እጅግ ብዙ ልጆቻችንን፣ ወንዶቻችንንና ሴቶቻችንን በ1994 ካስጨረሱብን በአግባቡ ካልተገነዘብናቸው ልዩነቶቻችን በላይ አሻግረን ለማየት መቻላችን ያኮራኛል:: የኢ ማኪዩሌ ከዘር ጭፍጨፋ የመትረፍ ታሪክ በእውነት አስደማሚ ነው:: የራሳቸውን እጅንዳ በሚያራምዱትና ለሰብዓዊነት ግድ በማይሰጣቸው አካላት ሆን ተብሎ የተፈጠረውን መከፋፈል በድል የመወጣትን ተስፋ ይሰጠናል:: ከጭፍጨፋው የተረፉትም ሆኑ አሳዳጆቹ ሁሉ ይህን ታሪክ ማንበብ ይገባቸዋል:: ሁላችንም የኢ ማኪዩሌን ዓይነት ጥልቅ መንፈሳዊ ለውጥ ይናፍቀንና ለእንዲትና ዘላቂ ሀገር ለመሥራት እንነሳሳ ዘንድ ተስፋ አደርጋለሁ::»

- **ግኔት ካጋሜ**፣ የሩዋንዳ ቀዳማዊት እመቤት

«የኢ ማኪዩሌ ኢሊባጊዛ መጽሐፍ የግብረገብ አቅጣጫ ጠቋሚዋን አጥታ ወደተወዛገበችው ዓለም ብርሃናማ መንገድ እያሳየንና ቀጥታ ወደ ዕርቅ ጎዳና እየመራን መጣ:: የሩዋንዳው የዘር ጭፍጨፋ አሰቃቂ ተግባራት ሲፋፋሙ የኢ ማኪዩሌ እምነት እየጠበቀ ይሄዳል:: እንባዬና ማቅለሽለሹ ካቆመልኝ ከረጅም ጊዜ በኋላ በአእምሮዬ ይመላለስ የነበው ይህ በሽብርና በእምነት መካከል ያለ የማይረጋ ውጥረት ነው:: የኢ ማኪዩሌ ታሪክ ዝርዝሩ የተለየ ቢሆንም ሁሉም ሰው በአንድነት የሚጋራው በመልካምነት ያላት ዕምነት በተደጋጋሚ መፈተኑን ነው:: በቃላት መገለጽ የማይችል ርኩሰት ይጠናወታታል፤ በዚህም ምክንያትነት ለሰው ማዘንን፣ ተስፋንና መጨረሻ ላይ ድኅነትን የሚያቀዳጀውን እውነተኛ ምኅረት ማድረግን ለማግኘት ብዙ መልፋት ነበረባት:: ሁቱትሲ የሚለው ይህ መጽሐፍ እርስዎን አስደምሞና አንበርክኮ በታደሰ እምነት ላይ ይጥልዎታል::»

- **ጋይል ስትራውብ**፣ የኢምፓወርመንት ተቋም ዳይሬክተርና የዘ ሪትም አፍ ኮምፓሽን ደራሲ

«ሁላችንም ኢ ማኪዩሌ ኢሊባጊዛ በሀገሯ በነበረው የዘር ጭፍጨፋ ወቅት ያጋጠማት ዓይነት ሽብርና የቅርብ ሰዎችን መነጠቅ ቢያጋጥመን ምን ልናደርግ እንደምንችል ራሳችንን እንጠይቃለን:: ፍርሃትና ተስፋ መቁረጥ በጥላቻና ተስፋ ማጣት እንዲሞሉን

እንፈቅዳለን? በሕይወትስ እንተርፋለን? መንፈሳችንስ ይመረዛል? የሕይወታችንን ዓላማ ለማሳካት ከአመድ ላይ ለመነሳት ብርታቱ ይኖረን ይሆን? ከዚያስ፣ ፍቅርን ለመስጠትና ለመቀበል ይቻለናል? እንደ ቪክተር ፍራንክልና እና ፍራንክ ሁሉ ኢ.ማኪዩሌ ሰዎች ከፋትን መቋቋም ብቻ ሳይሆን፣ በውድቀትም ብርታትን፣ እጅግ ተስፋ አስቆራጭ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥም እምነትን ማግኘት እንደሚችሉ ቋሚ ማሳያ ነች። በተቸገርን ጊዜ ጥበብንና ጸጋን ለማግኘት የሚረዳንን ብርታት በተቸገርን ጊዜ ትቸረናለች።»

- **ኤሊዛቤዝ ሌሰር**፣ የአሜጋ ተቋም ተባባሪ አባልና የብሮክን ኧውጥን፣ ሃው ዲፊከልት ታይምስ ካን ሽልፐ ኣስ ግሮው ደራሲ

«ሁቱትሲ ‹ዓይን ያጠፋ ዓይኑ ይጥፋ፤ ጥርስ ያረገፈ ጥርሱ ይረገፍ› የሚለው አብዛኛውን ዓለም የሚያሠቃየው በአሰቸጋሪ ጊዜ ሰዎች የሚጠብቁት ብሂል ለማይዋጥለት ለማንኛውም ሰው ይሆናል። ኢ.ማኪዩሌ ኢሊባጊዛ ያንን ልማድ የጣሰችው በጀግንነት በውስጧ ያለውን ማዕበል በማቆምና ውጪም ያለውን ማዕበል ለማጽናት፣ ከዚያም ባለፈ ምህረት ለማድረግ ለሚያስቸግረው ምህረት እንድታደርግ የፈቀደላትን ታላቅ ኃይል በማግኘት ነው። የርሷ ታሪክ ለማንም ሰው መነሳሳትን ይሰጣል - ከወንድሙ፣ ከሀገሩ ወይንም ከራሱ ጋር ለተቃቃረ ለማንም።»

- **ጁዲዝ ጋርተን**፣ መምህርትና የ50/50 ዎርክ አማካሪና ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጭፍጨፋ ልጅ ሆና የተረፈች

«ይህ መጽሐፍ ለዘላለም በቀየረኝ እውነተኛና በጥልቅ መንገድ በእግዚአብሔርና በአጽናፍ ዓለም ያለኝን እምነት አድሷልኛል።»

- **ክርስቲያን ኖርዝረፕ፣ ሜዲካል ዶክተር**፣ የዊሚንስ ቡዲስ ዊሚንስ ዊዝደም ደራሲ

«የሚያነሳሳና ሕይወትን የሚቀይር መጽሐፍ! አንደኛዋን ገጽ እንደገለጧት እስከዘላለሙ ይቀየራሉ። ኢ.ማኪዩሌንና ሕይወትን በጭለማው ጊዜ ይዞ የመቆየትን ምንነት እስከ መጨረሻው ኣይረሱም።»

- **ሲዲ ፐርልማን**፣ ኒውዮርክ ታይምስ ሲንዲከት

-

«ኢማኪዩሌ ኢሊባጊዛ በዚህ መጽሐፍ የተገለጹትን የማይታሰቡ ተግባራት ለፈጸሙት ሰዎች የቸረችው የምኒረት ስጦታ የማያወላውለው ጥንካሬዋ አንድ የሚገርም ምሳሌ ነው። ይህ መጽሐፍ በማይታሰቡ መንገዶች ሰሜቴን ነክቶኛል። በተጨማሪም ከእምነትና ምኒረት የሚወለደውን ታላቅ ጸጋ እንደገና አስታውሰኛል።»

- **ዴኒስ ሊን**፣ የ ኢፍ ኣይካን ፎርጊቭ፣ ሶ ዩ ካን ደራሲ

«ይህን መጽሐፍ ማንበብ የእኔን ሕይወት በእውነት ቀያይሮታል - ወደፊት ወይንም በአንድ የሆነ ወቅት ሳይሆን አሁኑኑ! ስሜቴን እንኳን መግለጽ አልችልም፤ ሆኖም ግን ቃላቱን ማግኘት በማልችልበት ሁኔታ በውስጤ ያሉትን ነገሮች ቀያይሮታል። ይህ በቂ ገለጻ ላድርግልህ ሲሉት አሻፈረኝ የሚል መጽሐፍ ነው።»

- **ቪማላ ሮጀርስ**፣ ደራሲና አነቃቂ ተናጋሪ

«የኢማኪዩሌ ታሪክ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ገጽ ሙሉ በሙሉ ሰቅዞ ይይዛል። በጣም ግሩም ታሪክ በመሆኑ እጅግ አጓጊ እንኳን ብዬ ለመግለጽ አልፈልግም... ሆኖም ግን ነው። ይህ መጽሐፍ ከኔ ጋር ለዘላለሙ ይቆያል።»

- **አል በርተን**፣ ጸሐፊ፣ ዳይሬክተር፣ እና የብዙ ስኬታማ የቴሌቪዝን ትዕይንቶች ፈጣሪ

«ሁቴትሲ እኛ ሁላችንም የእግዚአብሔር ልጆች እንደሆንን፣ በእምነት ተዓምራት ሁልጊዜም እንደሚፈጸሙና ምኒረትም የዐርነት ቁልፉ እንደሆነ ያስታውሰናል። ችግር በበረከተበት በዚህ ጊዜ ልናነበው ግድ የሚለን መጽሐፍ ነው።»

-**ኮሌቲ ባረን ራይድ**፣ የ ሪሜምበሪንግ ዘ ፊዩቸር ደራሲ

«ሁቴትሲ በማይተመን ሁኔታ ድንቅ ታሪክ ነው። የሰብዓዊነታችንን ጥሩውንም ሆነ መጥፎውን ገጽታ ይነካካል። ኢማኪዩሌ የማይሸነፈው የሰው መንፈስ ቋሚ ምሳሌ ነች። ታሪኳም ዘመን-አይሽሬ ነው።»

- **ሱዚቭ ካላፈር**፣ ሦስት ጊዜ የአካዳሚ ሽልማትን ያሸነፈ

የኢማኪዩሌ አርዓያ ይናገራሉ!

ባለፉት 50 ግድም ዓመታት በሺህዎች የሚቆጠሩ መጻሕፍትን አንብቤያለሁ፡፡ በእጅዎ ይዘውት ያለው መጽሐፍ ግን በሕይወቴ ካነበብኳቸው ሁሉ በላቀ ሁኔታ የሚመስጥና ጥልቀት ያለው ግሩም መጽሐፍ ነው፡፡

እርስዎ የእምነትን ዐቅም የሚያዩበትን መንገድ ለዘላለም ያለ ጥርጥር የሚቀይረውን ጉዞ ሊጀምሩ ነው፡፡ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተመዘዘች አንዲት ሐረግ እንደምታስታውሰን «በእግዚአብሔር ሁሉም ይቻላል፡፡» በምሰጣቸው ትምህርቶች ይህችን ሐረግ በተደጋጋሚ የሚከተለውን የማሳመኛ ጥያቄ እያከልኩ እጠቅሳለሁ «ይህ ታዲያ አሁን ምን የማያካትተው ነገር አለ?» መልሱ ለሁሉም ግልጽ ነው «ሁሉም ነገር ሲባል ሁሉም ነገር ማለት ነው»

እርስዎ ምንም ጥርጣሬ ያልገባበት ንጹሕ ዕምነት ተራሮችን እንደሚያንቀሳቅስና ግመልንም በመርፌ ቀዳዳ እንደሚያሾልክ አንብበዋል፡፡ በእርስዎ የማይናወጥ ዕምነት ግን እንኳን ሙሉው ፍጥረት በረቂቋ ቀዳዳ ያልፍ ቀርቶ ምናልባት ተራራው ሁሌም በነበረበት እንደቆመ፣ የመርፌ ዓይንም የግመልን የቅንድቡን ጸጉር እንኳን ማስተናገድ አቅቶት ይሆናል፡፡ በእርግጥ *ሁለትሺ* መጀመሪያ አንብበው ሲጨርሱ *የሁሉም* ከስተቶች ዳራ ምን እንደሚመስል አዲስ እይታ እንደሚኖርዎት ሳስገነዝብዎት በደስታ ነው፡፡ እርስዎ ኢማኪዩሌ ኢሊባጊዛ ለማሰብ እንኳን በሚሠቀጥጥ ዘር ጭፍጨፋ ውስጥ ያለፈችበትን ያልተለመደ አጋጣሚ ሲታዘቡ የንጹሕና የማይናወጥ እምነት ገደብ - የለሽ ዐቅም ተዓምራትን ሊሠራ እንደሚችል ይገባዎታል፡፡

ከአሥር ዓመታት ግድም በፊት በሩዋንዳ ሰዎች በሰዎች ላይ የፈጸሙትን አሰቃቂ ኢ-ሰብዓዊነት ብናይም ይህ ታሪክ በእውነት የፍቅር ታሪክ ነው ለማለት እደፍራለሁ - የሰው ልጅ መንፈስ የተቀዳጀው የድል ታሪክ፡፡ ይህ ታሪክ አንዲት ሴት የማይቻሉ መሰናክሎችን አልፋ ታሪኳን ለማጋራትና አዲስ መንፈሳዊ ግንዛቤ ለመጀመር የለውጥ አርዓያ ለመሆን ስትል ለመዳን የምታደርገው ጥልቅ እምነትና ቁርጠኝነት የሚታይበት ነው፡፡ ጥላቻና በቀልን የሚያፈራርሰው ለፈጣሪ ያላትን ጠንካራ ፍቅርም ያንጸባርቃል፡፡

ያለፈው ዓመት ኢማኪዩሌን በሚገባ ላውቃት የቻልኩበት ዓመት ነው - በእርግጥ በየቀኑ እንገናኛለን፡፡ ከእኔ ጋር በመጓዝ በምናገርባቸው መድረኮች በሺህዎች ለሚቆጠሩ ታዳሚዎች አብራኝ ታሪኳን ተናግራለች፡፡ በግላችን ለሰዓታት በዘር ፍጅቱ ጊዜ ስለነበረችበት ሁኔታና ስለ ዛሬ ፍላጎቷ አውርተናል፡፡ ከዚህ አልፎም ከእርሷና ከቤተሰቧ ጋር አሳልፌያለሁ፡፡ ከሥራ ባልደረቦቿና በተለይም አብረዋት ከዘር ጭፍጨፋው ከተረፉት ጋር የተነጋገርኩ ሲሆን፤ እርሷም በበኩሏ ከልጆቼ ጋር በርካታ ጊዜያትን አሳልፋለች፡፡ ከእርሷ ጋር በተለያዩ ስፍራዎች በምንሰጣቸው ትምህርቶች

መካከል በምናደርጋቸው የአየርና የባቡር ጉዞዎች ወቅት ውይይቶች ያደረግሁ ሲሆን፤ ከብዙም ሆነ ትንሽ ታዳሚ ፊት ቆማም አይቻታለሁ፡፡ ይህችን ጠንካራና ብርቱ ሴት በደንብ በማወቄ ከቅርብ ጓደኞቼ እንደ አንዷ ነው የምቆጥራት፡፡ በእርግጥ በጣም ስለምወዳትና ስለማደንቃት በቅርቡ የጻፍኩትን ፈንሰገሬሸን የተሰኘውን መጽሐፌን ለእርሷ መታሰቢያ አድርጌዋለሁ፡፡

እዚህ ድንቅ ሥራ መከፈቻ ገጾች ላይ ከኢማኪዩሌ ጋር ያለኝን የግል ግንኙነት የምገልጸው እርስዎ ሕይወትዎን ለዘላለሙ ወደሚቀይር አጋጣሚ ሊገቡ ስለሆነ (እንዲያውም ዓለምን ሳይቀር በጥሩ መንገድ ለመቀየር ይችላል ብዬ አምናለሁ) ኢማኪዩሌ በእኔ እይታ ምን ዓይነት የተለየች ታላቅ ሰው እንደሆነች እንዲያዩ ስለፈለግሁ ነው፡፡ በበርካታ ግላዊና ሕዝባዊ መቼቶች ቁጥር ስፍር በሌላቸው ከእርሷ ጋር ባሳለፍኳቸው ሰዓታት፣ በሃቅ ለመናገር ይህች ከመጠን ያለፈች መንፈሳዊት ሴት ሁልጊዜ ማንንም ሰው ስቦ በድንበሩ ውስጥ የሚከት ብርሃን ትፈነጥቃለች፡፡

በራት ሰዓት ስታወራ የተገኘ ሰው ሁሉ ማዳመጥ ብቻ ሳይሆን ማግኔት ብረትን እንደሚስብ ሁሉ በእጅጉ ወደ እርሷ ይሳባል፤ ሕዝብ በተሰበሰበባቸው መድረኮች ከልቧ ስትናገርም መርፌ እንኳ ቢወድቅ ይሰማዎታል፡፡ በእነዚህ ዐውዶች ከግርማ ሞገስም በላይ የሆነ ነገር እንደሚንጸባረቅባት ልብ ይሏል - ኢማኪዩሌ ስለ ቅድመ-ሁኔታ አልባ ፍቅር በመጻፍና መናገር ብቻ ሳይሆን በየሄደችበት ታንጸባርቀዋለች፡፡ ከፍ ባለ የመንፈሳዊ ደረጃ የምትኖረው ይህች እንስት ይህን በማድረጓ የእኔን ጨምሮ የምታገኛቸውን ሰዎች ሁሉ ዐቅም ታጎለብታለች፡፡

ለመጀመሪያ ጊዜ በተገናኘንበት ቅጽበት በተለየ ሁኔታ ከቅድስት ጋር እንደሆንኩ አወቅሁ፡፡ (ይህ እንግዲህ ይህን መጽሐፍ አንብበው ሲጨርሱ የሚገለጽልዎት ነገር ነው)፡፡ በኒው ዮርክ ለአሜጋ ተቋም አጭር ትምህርት ካቀረብኩ በኋላ ለአንድ አፍታ ተነጋገርን፤ ከአፍታ በኋላም ከእይታዬ ተሠወረች - በዚያች ቅጽበት ግን ተያዝኩ፡፡ ከብዙ ዓመታት በፊት ቅድስቲቱን እናት ሆነው ተከሰቱ ተብለው የሚታመንባቸውን ህንዳዊቷን እናት ሜራን ካገኘሁ በኋላ የተሰማኝን ዓይነት እጅግ ልዩውን የኢማኪዩሌን ጉልበት ተረዳሁ፡፡

ይህን መጽሐፍ ለማሳተም ኢማኪዩሌ ለእገዛ አልፈለገችኝም - ፈለግኋት እንጂ፡፡ አብሬያት በነበርኩበት ጊዜ የተሰማኝ ውስጣዊ የደስታና የፍቅር ብርሃን ሊለቀኝ ባለመቻሉ ከኢማኪዩሌ ጋር መልዕክት የምትላላከውን ልጄን ስካይን እርሷን ታገኝልኝ ዘንድ ጠየኳት፡፡ ቀናት በሳምታት ቢተኩም መገናኘት አልተቻለንም፡፡ ስካይን በየቀኑ «ሩዋንዳዊቷን ሴት አገኘሻት?» እያልኩ መጠየቄን አላቋረጥኩም፡፡

በመጨረሻም ኢማኪዩሌ ለልጄ ጥያቄዎች ምላሽ ትሰጥና በድንገት ስልክ እደውልላታሁ፡፡ አንድ ጥያቄም ጠየኳት፣ «የመትረፍ ታሪክሽን ልትጽፊው ትወጃለሽ?

መልዕክቱ ለዓለም ይደርስ ዘንድ አንቺን የማገዝ ግዴታ እንዳለብኝ ይሰማኛል። ያኔ ነበር ኢማኪዩሌ እርሷ ራሷ በ1994ቱ የሩዋንዳው የዘር ጭፍጨፋ በቱትሲነቷ ለግድያ የታደነችበትን ሰቆቃዋን እያንዳንዷን ዝርዝር እንደጻፈች የነገረችኝ። ከሞት የተረፈችበት ምክንያት ይህ እንደሆነ ገለጸችልኝ። ለማሳተም ያደረገቻቸው ጥረቶች ግን በተለይ እንግሊዝኛ ሶስተኛ ቋንቋዋ ስለሆነና የታሪኳን ጭብጥ ይበልጥ ተነባቢ ወደሆነ ገጽታ ለመቀየር እገዛ ስላስፈለጋት እንዳልተሳኩ ነገረችኝ።

የጻፈችውን ሁሉ እንድትልክልኝ የጠየቅኳት በዚህን ጊዜ ነበር፤ እርሷም ሩዋንዳን ለቃ ከወጣች ከአምስት ዓመታት በኋላ በሚገርም ጥራት እያንዳንዷን ዝርዝር ጉዳይ የጻፈችበትን 150 000 ቃላት ገደማ የሚሆነውን ጥራዝ ሰጠችኝ። የሄይ ሃውስ አሳታሚ ድርጅት ሊቀመንበርን ወዳጄ ራይድ ትሬሲን ስልክ ደውዬ አናግሬው ደራሲ ስቲቭ ኤርዊን የኢማኪዩሌን ታሪክ በነዚያ ገጾች ላይ እንደተጻፈው አድርጎ እንዲጽፈው እና ኢማኪዩሌን እንዲያግዛት ሁኔታዎችን አመቻቸን። ለራይድም በሚቻለኝ መንገድ ሁሉ በዚህ ሥራ እንደምደግፋቸው ነገርኩት - ይህን አጭር መግቢያ መጻፍ ብቻ ሳይሆን ኢማኪዩሌንና ታሪኳን በምገኝባቸው ህዝባዊ መድረኮች ሁሉ እንዲቀረቡ እንደማግዝ ገለጽኩ። በተጨማሪም ግድያው ባቆመበት ወቅት ወላጅ-አልባ ሆነው የቀሩትን ልጆች የማገዝ ተልዕኮዋን ለማሳካት ገንዘብ በማሰባሰብ ከእርሷና ከቤተሰቧ ጋር ወደ ሩዋንዳ በመጓዝ እንደማግዛት ቃል ገባሁ።

ከዚህም በዘለለ ለራይድ ኢማኪዩሌን በቴሌቪዥን ትዕይንቴ፣ *ኢንሰፓሬሽን - ዩር ኦልቲመት ኮሊንግ* በሚለው መርሃ- ግብር፣ ለማቅረብ እንደምፈልግና የዚህችን መንፈሳዊት ሴት ታሪክ ለሕዝብ እይታ ለማቅረብ የተቻለኝን ሁሉ እንደማደርግ ገለጽኩለት። ይህ ሁሉ የሆነው ለመጀመሪያ ጊዜ በሰው በተሞላ ከፍል ጥግ ለአፍታ ባገኘኋት ወቅት በተሰማኝ ስሜት አነሳሽነት ነው።

የዚህ የቁሳዊ ዓለም ሀጎች እግዚአብሔር ባለበት ዓለም ኢይሰሩም ይባላል። እነዚህን ቃላት ይህን መጽሐፍ አጉበበው በጨረሱ ጊዜ ይረዷቸዋል። ከጊዜ ወደ ጊዜ ኢማኪዩሌ ንጹሕ፣ እግዚአብሔርን የተረዳ ውስጣዊ ማንነቷ ገጀራ የያዙ ከእርሷ አንድ ጋት ብቻ ርቀው የነበሩ ገዳዮች አካላዊ መቼቷን ታውረው እንዳያዩ የማይታዩ መሰናክሎችን እንድታቆም አስችሏታል። እምነቷም እየጠለቀ በሄደ ቁጥር ተዓምራቱ ይበልጥ አስደማሚ እየሆኑ መጥተዋል። ራዕዮቿ በጣም እውን እየሆኑ ሲሄዱ ከአእምሮዋም ጥርጣሬዎች ሁሉ ተወግደውላታል፤ ከፈጣሪም ጋር በእጅጉ ተስማምታለች። የብርሃን መስቀል እርሷንና ባልንጀሮቿን ከሞት አፋፍ በከለላቸው ጊዜ አምላክ አብሯት እንዳለ ታውቋታል። ኢማኪዩሌ ከፈጣሪያችን ጋር የነበራትን የስሜት መስተጋብር በምታጣጡፍበት ወቅት የፍቅርና የመተዛዘን መላዕክት በድንገት ከየት መጡ ሳይባል እንደመጡላት ይሰማናል። ቆርጦ የመጣን ገዳይ ለረጅም ጊዜ

ዓይኖቹን አተኩራ በማየት ለማሸማቀቅ፣ በእርግጠኝነትም መሣሪያውን ሲጥል፣ መንቀሳቀስ ሲያቅተውና ንቀቱም ወደ ደግነት ሲቀየር ለማየት ችላለች።።

በመጨረሻም ለገዳዮቹ የነበራትን የጥላቻና የበቀል ስሜት ሁሉ አስወግዳ በአንድ ወቅት የማይቻል የሚመስለውን ለአሠቃዮቿ ሃዘኔታን ብቻ ሳይሆን ሙሉ ምኅረትንና ቅድመ-ሁኔታ አልባ ፍቅርን በመስጠት ከእግዚአብሔር ጋር ቅዱስ አንድነት ወደመፍጠር ተሸጋግራለች።። አዎን ከመንፈስ ጋር በአንድነት ትኖራለች - ዛሬ ካለችበት ስፍራ ማለት ነው።።

የእርሷ ታሪክ በጽኑ ይነካዎታል።። ፍርሃቷ ይሰማዎታል፤ ያለቅሳሉ፤ እንደ ሰዎች ስንጠይቅ የኖርናቸውን ጥያቄዎችም ራስዎን ይጠይቃሉ - *ይህ እንዴት ሊከሰት ቻለ? ይህ ጠላትነት ከየት መጣ? ለምን የሁላችንም ምንጭ እንደሆነው እንደ ፈጣሪ አንሆንም?* ግን አንድም ሌላ ነገር በእጅጉ ይሰማዎታል - ሰዎች ጋት በጋት ወደ አዲስ ጎዳና እየሄድን እንደሆነ የሚያሳይ ተስፋ - ቅዱስ ሕይወት ለመኖር መንገድ እንደጀመርን።።

ለእኔ ኢማኪዩሌ ከሞት የተረፈችው ይህን አእምሮን የሚያናውጥ ታሪክ ለመናገር ብቻ አይደለም፤ ከዚያም ባሻገር ሁላችንም ወደየራሳችን ተመልሰን ከተፈጠርንበት መንፈስ ጋር በመጣጣምና በእውነት ለመኖር ስንመርጥ መቀዳጀት የምንችለው ነገር ሕያው ምሳሌ ነች።።

ይህንን አሰቃቂ ታሪክ ለዓለም እንዲታወቅ ለማብቃት ባበረከትኳት ትንሽ አስተዋፅኦ ታላቅ ክብር ይሰማኛል።። ከኢማኪዩሌ ጋር ተባብሬ የፍቅርና ለሰው የመራራት ራእይዋን ለማሳካት በማገዜ ክብር ይሰማኛል።። ይህም ራእይ በሩዋንዳ ብቻ የተገደበ ሳይሆን በሁሉም ለረጅም ጊዜ ጥላቻ በሰፈነባቸው ስፍራዎች ይፈጸም ዘንድ የታለመ ነው።። ሁለመናዎን ሊያሰጥሙበት በተዘጋጁበት በዚህ መጽሐፍ ላይ እነዚህን ጥቂት ቃላት በማስፈሬም ጥልቅ ክብር ይሰማኛል።። ይህን ሲያደርጉም ሁላችንም ከተፈጠርንበት መለኮት ጋር በአንድነት ወደመኖር አንድ ጋት ርቀት ድረስ መቅረብ እንደሚቻልዎ ላረጋግጥልዎ እወዳለሁ።።

ይህን መጽሐፍ እወደዋለሁ፤ ኢማኪዩሌ ኢሊባጊዛንም እንዲሁ።። ኢማኪዩሌ ወደ ሕይወቴ ስለመጣሽልኝ ገለታ ይግባሽ።።

– **ዌይን ዳየር**፣ ማዊ፣ ሃዋዪ

መውጫ

ሁቱትሲ በሚል ርዕስ የቀረበው ይህ መጽሐፍ በሩዋንዳዊቷ ልጃገረድ እውነተኛ የሕይወት ጉዞ ላይ ተመርኩዞ፣ አእምሮን ሰቅዞ ይዞ፣ ልብን እያንጠለጠለ የሚፈስ አስደናቂ ድርሰት ነው።።

ትረካው አንባቢው በገመተው መንገድ ሳይሆን ባልተጠበቀ ውጤት የሚጠናቀቀውን ይህን በወጣቱ የደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ መምህር የተተረጎውን መጽሐፍ በማንበቤ ደስተኛ ነኝ።።

ዘውገኝነትን በከረረ ሁኔታ መያዝ ለአዶልፍ ሂትለርም ሆነ ለመሰሎቹ እንዳልበጀ ሁሉ በሩዋንዳም የእርስ በርስ መገዳደልን ያስከተለ አጉል አካሄድ ነው።። እንዲህ ዓይነቱን መቅሰፍታዊ አካሄድ አስቀድመን እንድንጸየፍ የሚመክረን ሩቅ አገናዛቢ ድርሰት መርጦ ስለተረጎመልን ተርጓሚውን አመሰግነዋለሁ።።

የእኔና የመዘምር ትውውቅ ከስምንት ዓመት በላይ ዘልቋል።። ወጣቱ የዩኒቨርሲቲ የሥነጽሑፍ መምህር የምጡቅና ጠሊቅ አስተሳሰብ ባለቤት መሆኑን ቀደም ሲል ባነበብኩለት ድርሰቶች ተገንዝቤያለሁ።። የሚያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ እንደሚባለው እነሆ መዘምር እሳት የላሰ ፀሐፊ እንደሚወጣው ተጉበዬ ስለነበረ እነሆ ግምቴ ዕውን እየሆነ መምጣቱን ተመለከትኩ።። ወጣቱ ይህን የትርጉም ሥራውን ሲያስነብበኝ ደግሞ ትንቢቴ እንደሰመረ ተረዳሁ።።

ለወደፊቱም ይህ ወጣት ከሀገራችን ቁንጮ ደራሲያን ተርታ እንደሚመደብና ለዚያም የሚሆኑ ሌሎች ድርሰቶቹን ይዞ ብቅ እንደሚል አልጠራጠርም።። እደግ ተመንደግ በርታ ብዬዋለሁ በምርቃቴ።።

መዘምር ይህን ድርሰት እንዲተረጉም የገፋፋው ሀገር ወዳድነቱና ለወገን ተቆርቋሪነቱ ብሎም አርቆ የማየት ስጋቱ ስለሚመስለኝ - በበኩሌ እድሜ ጠገብና የአኩሪ ታሪክ ባለቤት የሆነችው ኢትዮጵያችን የእንደዚህ ዓይነቱ መቅሰፍት ሰለባ ትሆናለች ብዬ አልገምትም።። በሳል፣ ፈጣሪን በማዕከልነት የያዘ ሕይወትን የሚገፋው፣ ባለራዕዩ፣ ባለ ዘጠና ዘውግ፣ የዘጠና ሚሊዮን ሕዝብ ባለቤት ከመጠፋፋት ይልቅ አብሮ መኗኗርን መርጧልና፤ ይመርጣልምና።።

አሊሹ ሙሜ ኢብራሂም

ደራሲና ተርጓሚ